# ይህች አለም ምን ትሆናለች?

## የእግዚአብሔር የማዳን እቅድ

ኤቫንጌልዩም ሚሲዮን
ባድ ዛልስ ኡፍን

የኢቫንጌልየም ሚሽን
ፖ.ሣ.ቁ. 19747
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ትርጉም፡- ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ በወ/ዊ ሽመልስ ረጋ

የማተምና የማባዛት መብት
ኢቫንጌልየም ሚሽን ዮአኪም ላንግሐመር
1998 እ.አ.አ.

መጽሐፉ የተተረጎመባቸው ቋንቋዎች፡-

| ቋንቋዎች | ብዛት |
|---|---|
| ራሽያ | 700000 |
| ሮማንያ | 110000 |
| ኮርአንቲያ | 70000 |
| ግሪክ | 25000 |
| ሃንጋሪ | 40000 |
| ስሎቫኪያ | 20000 |
| ቡልጋሪያ | 15000 |
| እንግሊዝኛ | 10000 |
| አልባንሽ | |
| ጀርመን | 15000 |
| አማርኛ(ኢትዮጵያ) | 5000 |

## ማውጫ

መቅድም ....................5
መግቢያ ....................6
ይህች አለም ምን ትሆናለች ....................7
የእግዚአብሔር የማዳኒ ምክር....................9
የእግዚአብሔር የማዳን እቅድ በመጽሐፍ ቅድስ ....................11
አልፋና ኦሜጋ /የመጀመሪያና መጨረሻ የሌለው/....................20
የጐልጐታው መስቀል ....................23
የአምላክ ሶስትነት /ስላሴ/....................25
1. እግዚአብሔር አብ....................27
2. እግዚአብሔር ወልድ....................27
3. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ....................30
የአለም ሕዝብ የእስራኤል ሕዝብ እና
የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ....................35
1. የአለም ሕዝቦች....................36
2. የእግዚአብሔር የመዳን ታሪክ ከእስራኤል ጋር....................44
3. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን....................63
እስራኤል - በእግዚአብሔር በአለም ሰአት ላይ ....................77
1. የእስራኤል ሕዝብ መበተን ....................78
2. የእስራኤል ተበትና በነበረችበት ዘመን....................87
3. የእስራኤል ሕዝብ መመለስ....................99
4. የእስራኤል በመጨረሻዎቹ ቀናት ....................113
የአሕዛብ ዘመን....................114
1. የዓለም አራቱ ኃያላን መንግስታት መነሳት ....................125
2. ፀረ ክርስቶስና መንግሥቱ ....................121
የጐግ ማጉግ....................170
የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ....................181
1. የጌታ ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያኑ መመለሱ....................183
2. የኢየሱስ ክርስቶስ ለአህዛብ መመለስ ....................186
3. የኢየሱስ ክርስቶስ ለእስራኤል ህዝብ መመለስ ....................194

የመሲሁ የሰላም መንግስት (የሺህ ዓመት መንግሥት) ........................................ 198
የመጨረሻው ፍርድ ........................................ 212
አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ........................................ 219
መግለጫ ክፍል 1 ሁለቱ የኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረጎች........................................ 222
መግለጫ ክፍል 2 ከመጽሐፍ ቅዱስ የጊዜ አቆጣጠር ጋር ያለ ችግር ........................................ 235
መግለጫ ክፍል 3 በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ውስጥ የቤተ መቅደስ መስፋፋት...... 240
መግለጫ ክፍል 4 በእግዚአብሔር የማዳን እቅድ ውስጥ ሰባቱ ዘመናት........................................ 250
ምሥጋና........................................ 258



# መቅድም

የሚቀጥሉት መግለጫዎች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን የድነትን ታሪክ ካርታ የሚያብራሩ ናቸው:: የበለጠ እይታ ለማግኘት ይቻል ዘንድ የሚያብራሩ ይሆናሉ:: ካርታው የእግዚአብሔርን የማዳን ታሪክ በጂኦግራፊ አቀማመጥ በተቻለ አቅም ለማብራራት የሚያስችል ነው::

ያለፉትና በአሁን ጊዜ ያሉት ሁኔታዎች መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ እንደተነበየው የድነት ታሪክ በቅርብ ጊዜ የሚፈጸም መሆኑን ያረጋግጡልናል:: የድነትን ታሪክ በማገናዘብ የእግዚአብሔርን ቃልና ዋናዎቹን የድነትን ትይይዝ በቀላሉ ልንረዳ እንችላለን:: በማዳን ዕቅድ ስብከት ብዙ ሰዎች በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወዳለው የማዳን ዕውቀት በመምጣታቸው እግዚአብሔርን እናመሰግናለን:: ይህ ካርታ የትንቢትን ቃል፣ የእግዚአብሔርን የማዳን ታሪክ ከእስራኤል ጋር ያለውን፣ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ዘመንና የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምጽአት ላጠኑ አማኞች ከፍተኛ ድጋፍ ሆኗል፣

የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ የታቀደው ለእኛ ለሰው ልጆች ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ መላዕክት እንኳን የእግዚአብሔር ልጅ ስለ እኛ የፈጸመውን ታላቅ ደህንነት ይመለከቱ ዘንድ እንደሚናፍቁ ይናገራል (1ጴጥ.1:12):: በእርሱ ምህረትን ያገኙት ኃጢአተኞች ብቻ ከመዝሙር ደራሲው ጋር ኢየሱስ ኃጢአተኞችን ይጠራል ይህን የማጽናናት ቃል ለሁሉም «አውጁ» በማለት ከእርሱ ጋር ሊደሰቱ ይችላሉ:: *«ኢየሱስ ሐጢአተኛን ይቀበላል ስለዚህ ይህን አጽናኝ ቃል ለሁሉም ተናገር»*

የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ አንድን ነገር በጣም ግልጽ ያደርጋል:: ይኸውም እግዚአብሔር በአድልዎ አንዱን ከፍ ሌላውን ዝቅ እድርጎ ሳይመለከት ሁሉንም እኩል መውደዱን ነው:: ኃጢአተኞች ሆነን ሳለ ወደ እርሱ እንዳለን እንመጣለን:: ጌታ ኢየሱስም ሕይወታችንን ይቀይራል (ይለውጣል):: በእርሱ ለናምን በክበረ ደሙ ከኃጢአት ያነጻንና የሕያው እግዚአብሔር ልጆች ያደርገናል:: ምክንያቱም «ለተቀበሉት ሁሉ ግን፣ በስሙ ለሚያምኑት ሁሉ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው» (ዮሐ.1:12) ተብሏልና:: ጥልቅ የሆነው ትልቁ የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ፍቺ ይህ ነው ለማንኛውም የደህንነትን ታሪክ ካርታ ይህን መጽሐፍ ድጋፍ አድርገው ለሚያጠኑት የእግዚአብሔርን የዘላለም ደህንነት እንዲይዙና ጌታ በግላቸው :-

«ይህን ለአንተ አደረግሁ፣ አንተ ደግሞ ለእኔ ምን ታደርጋለህ?»ብሎ የሚገልፅላቸውን እንዲገነዘቡ መልካም ምኞቴ ነው::

ዮአኪም ላንግ ሐመር በ1998 እ.ኤ.አ

# መግቢያ

የደህንነትን ስዕላዊ መግለጫ ከማጥናትዎ በፊት ሀሳብዎን ወደሚከተሉት ነጥቦች ለመሳብ እንፈልጋለን፡፡

1. ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ ፍቼን የሚሰጥ አይደለም፡፡ ነገር ግን በዚህ አስደናቂ በሆነው የመዋጀት ዕቅድ ውስጥ ያሉትን ዋናዎቹን የደህንነትን ክፍሎች እይታ የሚሰጥ ነው፡፡
2. ማገናዘቢያው በመጽሐፉ መጨረሻ የሚገኘው የደህንነት ካርታ መግለጫ ነው፡፡ በተቻለ አቅም የታሪኮቹን ቅደም ተከተል ዘመናቸውን ሳናዛባ ለማቅረብ ጥረት አድርገናል፡፡ አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ካርታውን ቀንጨብ በማድረግ አቅርበናል፡፡
3. በተቻለ አቅም መጽሐፉ በውስጡ ድግግሞሽ እንዳይኖር ታቅዶ የተዘጋጀ ነው፡፡ ስለሆነም የደህንነትን ካርታ መግለጫዎችን በየደረጃቸው (ቅደም ተከተላቸው) እንዲያጠኗቸው እናሳስባለን፡፡
4. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት መግለጫዎች ፍጹምና እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ነው ብለን በምናምነው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ዓላማ በማድረግ የተለያዩ ሀሳቦችንና ትርጉሞችን ከማቅረብና ከመነጋገር ተቆጥበናል፡፡
5. የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከአማርኛው መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ እና ክጥንቱ የግሪክ መፅሐፍ ቅዱስ ነው፡፡
6. በካርታ መግለጫ ላይ ያለው አስተያየታችን የተጠናቀቀ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በዚህ ትምህርት ልንረዳቸው ያልቻልናቸው ነገሮች እንዳናጠናቅቀው አድርገዋል፡፡ መጽሐፉ እግዚአብሔር ስለ ደህንነት ያለውን ሃሳብ ግንዛቤ ለሌላቸውና ወይም ጥቂት እውቀት ላላቸው ስለዚህ ትምህርት የሚያሳውቅ ነው፡፡ እንደዚሁም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ለሚያነቡና ለሚያጠኑ ተጨማሪ በረከት ይሆናል ተብሎ ታቅዶ የተዘጋጀ ነው፡፡





## በማዳን ዕቅድ መግለጫ ካርታ ላይ ዋናው ጥያቄ

## ይህች ዓለም ምን ትሆናለች?

የሰው ልጅ በመጽሐፍ ቅዱስ ብርሃን አማካኝነት በዓለም ላይ ስለሚካሄዱት ድርጊቶችና በመጨረሻው የፀጋ ዘመን ውስጥ ስለመኖሩ በቀላሉ መረዳት ይችላል፡፡ ይህች ዓለም ምን ትሆናለች? ብለው የሚጠይቁት ብዙዎች ናቸው፡፡ ይህን ጥያቄ አማኞች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ሰዎች በተለያየ መንገድ የሚያስቡትና የሚያሰላስሉት ነው፡፡

ዓለም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨለመች ስለመሔዷ የዓለም የፖለቲካ ሁኔታ በደንብ ያረጋግጥልናል፡፡ በዚህ በያዝነው በሃያኛው ክፍለ ዘመን ብቻ የሰው ልጅ 65,000,000 ሚሊዮን ያህል ህይወት ያስፈበትን ሁለት አስቃቂ የዓለም ጦርነቶችን አሳልፏል፡፡ የሚገርመውና የሚያሳዝነው ጦርነቱ በዚህ ብቻ አለማብቃቱ /አለመቆሙ/ ነው፡፡ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ 140 የሚሆኑ ወታደራዊ ግጭቶች፣ ጦርነቶች፣ ጭቅጭቆች ሲደረጉ 30 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡ ይህን ለሚያይ ሰው በዚህ መቶኛ ክፍለ ዘመን በብዛት የሚካሄደው የነፍስ ግድያ ማብቂያ የሚኖረው አይመስልም፡፡

በዚህ ላይ ተጨማሪ የምናደርገው በኃጢአት የተሞላ ሰው ሌላውን ሰው ለመጉዳትና ለማጥፋት የቻለው በቴክኖሎጂ ግኝቶች አማካኝነት ነው፡፡ በፍጥነት እያደገ ያለው የኒውክለር የጦር መሳሪያ ቴክኖሎጂ ስንመለከት ዓለም ከግምት በላይ በሆነ አደገኛ ሁኔታ ላይ መድረሷን እንገነዘባለን፡፡ በዚህ ላይ በተጨማሪ የዜና አገልግሎቶች፡- ቴሌቪዥን፣ ሲኒማ፣ቪድዮ፣ጋዜጦች የመሳሰሉት በሚሰጡት ልዩ ልዩ አገልግሎቶች በየጊዜው ሀፍረተ ቢስ ጨቋኞች፣ አደገኞችና የገበያ አቀራረባቸው የሰውን ጠባይና ሞራል በማበላሸት ከፍተኛ ውድቀት ላይ አድርሰውታል፡፡ እንዲሁ ደግሞ የአካባቢው መበከል የተፈጥሮን ሁኔታ በፍጥነት እያቃወሰውና እያጠፋው ነው፡፡ ቴክኖሎጂ በየጊዜው በተፈጥሮ ላይ እያደረሰ ያለው ተፅዕኖ፣ የሚያስፋፋው ወረርሽኝና የበሽታ ዓይነት እጅግ አሳሳቢ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ትዕይንቶች ሁሉ የዓለምን የወደፊት እድል ፈንታ የት ያደርሱት ይሆን? የሚለውን ጥያቄ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ መልኩ የሚነሳ አንገብጋቢ ጥያቄ አድርገው ከፊታችን ደንቅረውታል፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ የዚህ ዘመን ችግሮች የሚያስደነግጡና የሚያስፈሩ ናቸው:: ይህም ሆኖ በፖለቲካ፣ በአገር አንድነትና በሳይንስ መስኮች ለዚህ ጥያቄ ምንም ዓይነት መልስና መፍትሔ አለመገኘቱና ለጉዳዩ ተጠሪ የሆኑት አዋቂዎችም አደገኝነቱን ያለመገንዘባቸው ነገር ተስፋ አስቆራጭ ሆኖአል::

### *ይህ ለምን ይሆን?*

ይህ በዓለም ላይ ያለው የመዘበራረቅ ሁኔታ በየጊዜው እየጨመረ የሄደው የሰው ልጅ ወደ እውነተኛ የህይወት ምንጭ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ባለመመለሱ ነው:: ስዚህ «ይህች ዓለም ምን ትሆናለች?» ለሚለው ጥያቄ አስተማማኝ መልስ ከፈለግን በሙሉ መንፈስ ወደ ፈጠራት ፈጣሪ መቅረብ ብቻ ነው:: ይህም ሲሆን በዚህ ጥያቄ ላይ ያለንን ጉጉት ለማርካት ብቻ ሳይሆን የበለጠ ለመፍትሔው መጽሐፍ ቅዱስን መመርመር ይኖርብናል::

ይህች ዓለም ከየት እንደመጣችና ወዴት እንደምትሄድ በትክክል ሊነግረን የሚደፍረው አንዱ ምንጭ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው:: ከመጽሐፍ ቅዱስ የምንማረውና የምንረዳው:-

1. እግዚአብሔር የዓለም ፈጣሪ ነው::
2. እግዚአብሔር የዓለም አዳኝ ነው::
3. እግዚአብሔር የዓለምን ፍጻሜ የሚያመጣ መሆኑን ነው::

ዓለምን የፈጠረውና በክርስቶስ ኢየሱስ ያዳነን እግዚአብሔር ዓለምን ወደ ፍጻሜ ያመጣታል::





በደህንነት ታሪክ ማዕከላዊና ዋና ህሳብ የሆነው የደህንነት ካርታ መግለጫ

## የእግዚአብሔር የማዳን ምክር

## ሐ.ሥ.20:27

*«የእግዚአብሔርንም ምክር ሁሉ ነግሬአችኋለሁና ምንም አላስቀረሁባችሁም» (ሐ.ሥ. 20:27)*

ከላይ የተጠቀሰውን ቃል ሐዋርያው ጳውሎስ የተናገረው የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በተሰናበተበት ጊዜ ነበር:: ጳውሎስ በኤፌሶን የሦስት ዓመታት ቆይታው የእግዚአብሔርን ምክር አስታውቋቸው ነበር:: የግሪኩ መሠረታዊ ትርጉም የእግዚአብሔርን ሙሉ ምክር ብሎ ይተረጉመዋል:: ይህ «ምክር» የሚለው ቃል ከ10 ጊዜ በላይ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጽፎ እናገኘዋለን:: ይህ «ምክር» የሚለው ቃል አስፈላጊ ወደ ሆነው የህይወት ለውጥ በሚደረግ ውሳኔ የምንጠቀምበት ቃል ነው:: ይህ ቃል በየቀኑ ለሚያጋጥሙን ምድራዊ ነገሮች ላይ ውሳኔ ለመስጠት የምንጠቀምበት ነው:: የእግዚአብሔር ምክር የሚያተኩረው ወደ ግል ደህንነታችን ነው:: የተጠሩት ደህንነትን ኃጢአተኞች የኃጢአት ይቅርታንና የዘለዓለም ህይወትን እንዲያገኙ ነው::

*«ለአንዳንዶች ጌታ የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፣ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሃ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንደይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሳል»* (2ኛጴጥ.3:9)::

*«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና»* (ዮሐ.3:16)::

የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ አስደናቂና ዘለዓለማዊ ዕቅድ ነው:: ይህም ምድር ከመመስረቷ በፊት ከነበረው ጊዜ ጀምሮ አሁን ያለችውን ምድርና የመዳኛ ጊዜ በተጨማሪም ወደፊት እግዚአብሔር የሚፈጥራቸውን አዲስ ሰማይንና አዲሲቷን ምድር ያጠቃልላል:: የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ *«በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው ሃሳቡንም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው» (ኤፌ.1:10)* የሚለውን ሃሳብ የሚያመለክት ነው:: ይህም «በሰማይና በምድር ያሉ ነገሮች ሁሉ ተጠቃልለው በአንድ በክርስቶስ ስልጣን ስር የሚሆኑበት ጊዜ ነው» እርሱ ሁሉንም በመስቀሉ ላይ ከእግዚአብሔር የነበረው

መነጣጠልንና ሰውንና እግዚአብሔርን የነጣጠለ የኃጢአትን ጥልቀት ለዘለዓለም ያሸነፈ ነው::

ስለዚህ ደህንነት ከእርሱ በቀር በሌላ በማንም የለም:: ምክንያቱም እኛ ልንድንበት የሚገባን እግዚአብሔር ለሰዎች የለጠው ስም ከእርሱ በቀር በመላው ዓለም ማንም ሌላ የለም:: ማቴ1:21፤ ሐሥ.4:12 ይመልከቱ::

ዋነኛው ጉዳይ እግዚአብሔር ለእኛ የዘላለም ደህንነት የመስጠቱ ነገር ነው:: ይህ ደህንነት የተመሠረተው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንደሚለው ሙሉ በሙሉ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ብቻ ነው:: በ1ኛ ጢሞቲዎስ 2:4 እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ያለውን ፈቃዱን ለዓለም ምስክርነቱን ይሰጣል:: ቃሉም «ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድሃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው» ይላል:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነትን እንዲያውቁ ነው:: ይህ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው ሥጋዊ ሰው ራሱን የማዳን ኃይል የሌለው በመሆኑ ነው:: በኃጢአቱ ምክንያት ሰው ደህንነት የሚያስፈልገው ሆኗል::

የሰው ልጅ ደህነትን መፈለጉ በኃጢአት ከመውደቁ ውጤት የተነሳ ነው:: የመጀመሪያው ሰው አዳም ኃጢአት በመስራቱ የሰውን ልጅ ሁሉ በኃጢአት ውስጥ ጣለው (ሮሜ 5:12):: ኃጢዓትም በሰው ልጅ ላይ ሞትን አመጣበት (ሮሜ.6:23):: መሞታችን ከአዳም መምጣታችንን ያረጋግጥልናል (ይመሰክርልናል) (ዘፍ.2:16-17):: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰው ለዘላለም ስለ ጠፋ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው ደህንነት የሚያስፈልገው ሆኗል:: ስለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ የሚለው:-

1. ማንኛውም ሰው ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለበት!
2. ማንኛውም ሰው ንስሃ መግባት ይኖርበታል!
3. ማንኛውም ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት ተቀብሎ ደህንነትን ማግኘት ይኖርበታል!

ይህንንም ዕቅድ እግዚአብሔር ከዓለም መፈጠር በፊት ለእኛ ወስኖ ነበር:: *«ቅዱሳንና ነቀፋ የሌለን ሆነን በፊቱ እንድንገኝ ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ መረጠን:: በፍቅሩም እግዚአብሔር በጎ ፈቃዱ ሆኖ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት በነፃ የሰጠን የክብር ፀጋ እንዲመሰገን ነው» (ኤፌ 1:4-5)::*
ይህ ደህንነት በተፈጸመው የክርስቶስ ኢየሱስ ሥራ ላይ የተመሰረተና እኛም በእምነት የተቀበልነው ነው::





# የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

*«በእውነትህ ቀድሳቸው ቃልህ እውነት ነው» (ዮሐ.17:17)*

መጽሐፍ ቅዱስ የእውነት ቃል ነው:: የእግዚአብሔር ልጅ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ቃላት በደንብ ያረጋግጥልናል:: ከዚያም በላይ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መገለጥ ምንጭ ናቸው:: እግዚአብሔር ሰውን በራሱ እምሳያ በፈጠረ ጊዜ ለሰው ልጆች ራሱን ገልጧል (ዘፍ.1:27)::

«ይህች ዓለም ምን ትሆናለች?» ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት የሚችለው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው:: በአምላካዊ ሥልጣን ይህች ዓለም ከየት እንደመጣችና ወዴት እንደምትሄድ ይነግረናል:: በዚህም ከዓለም ፍጥረት በፊት ምን እንደነበር፣ የአሁኑ ዓለም ምን እንደሆነና በሚመጣው ዘለዓለማዊ ዓለም ምን እንደሚሆን ይነግረናል::

መጽሐፍ ቅዱስ 40 በሚደርሱ እስራኤላውያን ሰዎች በ1600 ዓመታት ውስጥ የተጻፈ ነው:: እነዚህ ሰዎች በተለያዩ የጊዜ ክፍሎችና ዘመናት ከተለያዩ የኑሮ ሁኔታዎች የመጡ ነበሩ:: ይህም ሆኖ የ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት አንድነት በጣም የሚያስደንቅ ነው:: በመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ምሪት (መረዳት) ብቻ ላይ የተመሰረተ ነወ (2ጴጥ.1:20-21፤ 2ጢሞ.3:16-17)::

መጽሐፍ ቅዱስ የደህንነት ታሪክ መጽሐፍ ነው:: በዚህ መጽሐፍ እግዚአብሔር የደህንነት ንድፉንና ዕቅዱን ለሰው ልጅ ሁሉ ይገልጽበታል:: ጠቅለል ባለ መልኩ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት የመዋጀትን ዕቅድ በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች ያሳያሉ:: ቀጥታ እነዚህ ክፍሎች በመዋጀት ዕቅድ ካርታ ላይ ከመለኮታዊ ሰላሴ፣ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ መስመር በታች ይገኛሉ:: በስተጨመረሻ ከመፅሐፉ ጋር ተያይዞ ያለውን የደህንነት ካርታ ይመልከቱ::

## 1. ብሉይ ኪዳን - የደህንነት ዝግጅት

የመጀመሪያዎቹ 39 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እግዚአብሔር እንዴት በረጅም ጊዜ ውስጥ ይህንን የደህንነት ሥራ እንዳዘጋጀ ያረጋግጣሉ:: የደህንነት ዝግጅት ሥራ ከዘፍ.3:15 ጀምሮ ከአዳም፣ ከኖህና ከሴም እስከ አብርሃም መስመሩን ይዞ ከዘር ዘር ተላልፏል:: በዘፍ. ምዕ. 5፣10 እና 11 የምናነባቸው የዝርያ ዝርዝሮች የተጻፉበት ዋናው ምክንያት የማዳኑን ሥራ ወደ አብርሃም የሚመራውን መስመር ለመጠቆም ነው::

ትክክለኛው የማዳን ሥራ ዝግጅት ከአብርሃም ይጀመራል:: ከዚህ ከትልቁ የእምነት አባት አንድ ልዩ የሆነ ዘር እንዲመጣ አደረገ:: የደህንነት ህዝብ (ዘር) እስራኤል በሲና ተራራ ላይ በተደረገው ህግና ኪዳን የእግዚአብሔር ህዝብ ሆነ ዘፀ. ከምዕራፍ 12 እስከ 24 ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለእግዚአብሔር ክብር በቅድስና እንዲኖሩ ነበር:: ይህም ማለት በእስራኤል ውስጥ ማንኛውም ዓይነት የጣዖት አምልኮ እንዳይኖር ነበር:: ምክንያቱም ምንም ቢሆን የእግዚአብሔር ልጅ የጣዖት አምልኮ በሞላበት አገርና ህዝብ መካከል ከቶ ሊመጣ ስለማይችል ነው:: የጣዖት አምልኮ ሁልጊዜ ለሰይጣን የሚደረግ መስዋዕት ነው:: አረማውያን መስዋዕት የሚያቀርቡት ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለአጋንንት ነው (1ቆሮ.10:20):: ለዚህ ነው ለደህንነት ሥራ ዝግጅት የእስራኤል ህዝብ ከሌላው አህዛብ ተለይቶ በቅድስና እንዲኖር የተደረገው:: መሲሁን ለመቀበል እግዚአብሔር እስራኤልን ለኢየሱስ ስራ መረጠ:: ይኸውም «ደህንነት ከአይሁድ ስለሆነ» ነው (ዮሐ.4:22):: በዚህ ላይ አስመግባባት መፈጠር የለበትም:: የእስራኤል ነገድ (ህዝብ) ራሳቸው አዳኙን አይደሉም:: ሆኖም ግን ደህንነት ከእነርሱ መካከል የሚወጣ ነበር (ኤር. 30:21):: ይህም ጌታና አዳኝ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ደህንነት እንደሚመጣ ያመለክታል ማለት ነው::

ስለሆነም ብሉይ ኪዳን ደህንነት (መዋጀት) ይመጣል ብሎ የሚያውጅ መጽሐፍ መሆኑን እንረዳለን::

## 2. አራቱ ወንጌሎች - የደህንነት መሠራት

በአራቱም ወንጌሎች በማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ውስጥ የእግዚአብሐር ልጅ ወደ ምድር ወርዶ የደህንነትን ሥራ ለእኛ ለሰው ልጆች እንደፈጸመ ተመዝግቧል:: ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስ በጎልጎታ መስቀል ላይ

«ተፈጸመ» ብሎ ጮኸ» (ዮሐ.19:30)

በ1ኛው ቆሮንጦስ መጽሐፍ እንደተፃፈው ይህ ትልቁ የመዋጃ እውነትና የመዳናችን መሠረት ነው::

*«ከተመሠረተው በቀር ሌላ ማንም መሰረት ሊመሰርት አይችልምና፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው»* (1ቆር.3:11)::

ስለሆነም ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በስብዕናውና አስደናቂ በሆነው የማዳን ሥራው የማይነቃነቀው የደህንነታችን መሠረት ነው:: ይህም ማለት ኃጢዓተኞች ለመዳን ይችሉ ዘንድ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ያሟላ እርሱ ነው ማለት ነው:: በዚህ መሠረት (ዓለት) ላይ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን ይገነባል (ማቴ.16:18):: ስለሆነም





የዚህ የማዳን መሠረት በአራት ምሰሶዎች ማለትም:-

1. ከኃጢዓት ነፃ በሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ሰው በመሆን፣
2. በተተኪነት በተከፈለው በኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕታዊ ስቃይ፣
3. በክብር የተመላው የኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት በመነሳትና፣
4. በአሸናፊነት በቷሞላው የኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ማረግ፣ ላይ ያረፈ ነው::

እነኚህ አራቱ የደህንነት ምሰሶዎች የማይነጣጠሉ ናቸው:: የሚመሰረቱትም ሙሉ በሙሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስብዕናና ሥራ ላይ ብቻ ነው:: አራቱ ወንጌሎችም መሠረቱንና በክርስቶስ የሆነውን የመዳን እውነት ይገልጻሉ:: ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሠረት (ዓለት) ነው::እርሱ ብቻ ዘላለማዊ መሠረት ነው::

## 3. የሐዋሪያት ሥራ - የደህንነት መስራጨት

የሐዋሪያት ሥራ ወንጌል እንዴት ወደ ዓለም እንደተሰራጨ ይነግረናል:: *28ቱም ምዕራፎች ይህ በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመው ደህንነት እንዴት በወንጌል ስብከት እስከ ዓለም መጨረሻ እንደደረሰ በሰፊው ይገልጻሉ (ያስታውቃሉ):: ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለደቀመዛሙርቱ እንደዚህ አላቸው:-

*«ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በዚያን ጊዜ በኢየሩሣሌም፣ በይሁዳ አገር ሁሉ በሰማሪያ እስከ ምድርም ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ»* (ሐሥ.1:8)::

ደቀመዛሙርቱና ሐዋርያቱ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የኢየሱስንና በእርሱ የተደረገውን የጎልጎታ የማዳን ሥራ መስክረዋል::

*«እኛ ግን ክርስቶስ ስለ እኛ መሰቀሉን እንመሰክራለን»* (1ቆሮ.1:23)::

ይህ የተሰቀለውና የተነሳው ክርስቶስ ኢየሱስ የመሠረተው የድል ወንጌል ሞልዕክት በኢየሩሣሌም፣ በይሁዳና በሰማሪያ ባሉት ህዝብ ልብ ውስጥ ዘልቆ ገባ:: 100 ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ይህ ወንጌል የሮምን መንግስት ዘልቆ ገባ:: ሰሜን አፍሪክ፣ ትንሹ እስያ፣ ፐርሺያ፣ ሶሪያ፣ ሱዳንና ግብጽ ለመቶ ዓመታት የክርስቲያን አገሮች ሆኑ:: በዚያን ጊዜ መላው ዓለም በወንጌል ተሞልቶ ነበር ይህም ሊታመን የማይቻል ነበር:: እ'.ህ ላይ ነው የጎልጎታ ድል ትርጉም ግልጽ የሆነውና የተገለጸው:: ጠላት ሰይጣን ለአንዴና ለዘላለም የተሸነፈ ሆነ:: ለዘለዓለምም የተሸነፈ ጠላት ሆኖ ይቀራል::

ከ2000 ዓመታት ጀምሮ በክርስቶስ የተገኘው ደህንነት በመላው ዓለም እየተሰበከ ነው:: ይህን እንዲሠሩ እግዚአብሔር መላዕክትን ከሰማይ ወደ ምድር አልላከም:: የተፈጸመውን የደህንነት ሥራ ለሰዎች ለማዳረስ እግዚአብሔር ይህን ደህንነት በህይወታቸው በእምነት ለተለማመዱት ሰዎች አደራ ሰጠ:: ለእነርሱም እንዲፈጽሙት ግልጽ የሆነውን

*«ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ»* የሚለውን ተልዕኮ ሰጣቸው *(ማር.16:15):: «እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን» (2ቆሮ.5:20)*

*«ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ» (1ቆሮ.11:26)::*

ጌታ ኢየሱስ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ ወንጌልን የማሰራጨት ተልዕኮ የእያንዳንዱ አማኝ ኃላፊነት ይሆናል:: ስለሆነም የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ወንጌልን እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ የማሰራጨት መለኮታዊ ተልዕኮን በጥልቀት የሚያሳይ ነው::

## 4. የአዲስ ኪዳን መልዕክቶች - የደህንነት ትርጉምና መግለጫ

21ዱ የአዲስ ኪዳን መልዕክቶች የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነትና በእርሱ የተፈጸመውን የመዋጀት ሥራና ጥልቅ የሆነውንና በክርስቶስ ያለውን የደህንነት ይዘት ይገልጻሉ:: አራቱ ወንጌላት ስለ ክርስቶስ መስቀል ሲናገሩ መልዕክቶቹ ደግሞ ይህ ለምን እንደሆነ ያስረዳሉ::

*«እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለምን ከራሱ ጋር ሲያስታርቅ የለዎችን በደል አይቆጥርባቸውም ነበር» (2ቆሮ.5:19)::*

የአዲስ ኪዳን መልዕክቶች የኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና በእርሱ የተደረገውን ለዘለዓለም ጥልቅ የሆነውን የመዋጀት ሥራን ያሳዩናል:: ከዚህም በላይ እኛ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ያለንን ህብረት ያመለክቱናል:: እያንዳንዳችን የአካሉ ብልትቶችና በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ደግሞ አካሉ መሆናችንን ያሳዩናል (ኤፌ. 1:23 እና ኤፌ.5:30):: ምስጢሩ፣ ጥሪውና የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የእርሱ አካል መሆኗን ሐዋሪያው ጳውሉስ በጻፋቸው መልዕክቶች ልዩ በሆነ መንገድ ተገልጧል::

በተጨማሪም እነዚህ መልእክቶች በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን ደህንነታችንን በእምነት «በፍርሀትና በአክብሮት ተግታችሁ ሥሩ» (ፊል.2:12) እንደዚሁም በውስጣችን ያለውን ኃጢአት ድል እንድናደርግ «እንዲሁም እናንተ ደግሞ





ለኃጢዓት እንደ ሞታችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ» (ሮሜ.6:11) «ክርስቶስ በእናንተ እስኪሳል ድረስ...» (ገላ.4:19፤ ኤፌ.4:15-16) በማለት ደህንነታችንን በጥንቃቄ እንድንፈጽም ያስተምሩናል::

ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን ደህንነት በእምነት ካልተቀበለ በስተቀር በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን የደህንነት ትርጉም (ምንነት) መረዳት አይችልም:: አማኝ ብቻ ነው ወደዚህ የደህንነት ሙላት የሚገባው ስለዚህ ምክንያት ነው ሀያ አንዱ መልዕክቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉት አማኞች በቅድምያ የተጻፉት:: አዳኙ ጌታ «መጽሐፍትን መርምሩ» (ዮሐ.5:39) በማለት አማኞችን አዝዟል::

የቤሪያ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ይህን ትዕዛዝ «መጽሐፍትን በመመርመር» በትክክል መንገድ ታዘዙት (ሐሥ.17:11):: ዛሬም ቢሆን እኛ ፍጹም የሆነውን መለኮታዊ የማዳን ሥራ ለመረዳትና ለመገንዘብ ያላቋረጠ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ልናደርግ ይገባናል::

## 5. ራዕይ የደህንነት /የመዋጀት/ መፈጸም

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስ ራዕይ ነው (ራዕ.1:1):: ይህ መጽሐፍ ደግሞ የዮሐንስ ራዕይ በመባል ይጠራል ራዕዩ የተሰጠው አንድ ጊዜ በኢየሱስ ደረት ላይ ጠጋ ብሎ ወደነበረው ወደ ሐዋሪያው ዮሐንስ ነው (ዮሐ.13:23፣ 21:20) በአዲስ ኪዳን ብቸኛ የትንቢት መጽሐፍ ነው:: የመጽሐፉ ዋና መልዕክት እንዴት እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደህንነትን እንደፈጸመና እንደሚፈጽም ማሳየት ነው:: በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የእግዚአብሔር ልጅ የሚመጣው መሲህ፣ የዓለም ፈራጅና የሁሉ ፈጻሚው (ሙላት) መሆኑ ራሱ ገልጿል::

*«አብ በማንም ላይ አይፈርድም ነገር ግን የፍርድን ሥልጣን ሁሉ ለወልድ ሰጥቶታል» (ዮሐ.5:22)::* ይህም ማለት አሁን ንስሐ ለሚገቡት ኃጢአተኞች አዳኝ መድሃኒት የሆነው ያው ጌታ አምላክ-የለሽ በሆኑት ላይ ለመፍረድ ይገለጣል ማለት ነው:: በህይወታቸው ሳሉ በኢየሱስ የሚገኘውን ደህንነት ያጣጣሉ ሁሉ ለዘለዓለም ይጠፋሉ:: የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ኢየሱስን «በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ የሚንበረከኩለት» ብቸኛ ገዢ አድርጎ ያቀርበዋል (ፊል.2:10)::

ከብዙዎች አስቃቂ ከሆኑት እግዚአብሔር-የለሽ ህዝቦች ላይ ከሚወርደው ፍርድ ሌላ ራዕይ ደህንነት እንዴት አድርጎ ከአዲስ ሰማይና

ከአዲስ ምድር ጋር እንደሚጋጠም ያሳያል (ራዕ.21:1):: ከዚያ በኋላ ነው የእግዚአብሔር የደህንነት እቅድ ተሟልቶ ለፍጻሜ የሚደርሰው::

<u>**ማ ጠ ቃ ለ ያ**</u>

እስካሁን በተሰጠው መግለጫ እንዳየነው ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ በሆነና ሊታይ በሚችል መልኩ የደህንነትን ይዘት የዘረዘረ መጽሐፍ ነው:: ይኸውም:

***ከዘፍ. 1 - እስከ 11***

የዓለም ታሪክ መግለጫ፣ ፍጥረት፣ የሰው ውድቀት፣ የጥፋት ውሃ፣ የባቢሎን ግንብ ግንባታ

***ከዘፍ.12 እስከ - ሐዋ.12***

የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ታሪክ ከእሥራኤል ጋር ከአብርሃም ጀምሮ በክርስቶስ መጨረሱ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ደህንነትን በጎልጎታ መስቀል ላይ መፈጸሙ

***ከሐዋ. 13 እስከ - ዮሐ.ራዕይ 3***

እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ (መጨረሻ ድረስ) የማዳን ሥራ መሰራጨት፣ የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ከአይሁዶችና ከአረማውያን በተውጣጡ መሰብሰብ

***ከራዕ. 4 እስከ 22***

በምድር ላይ የሚወርደው የፍርድ ጊዜ የማዳን ሥራ መፈጸም፣ የኢየሱስ እንደገና መምጣት፣ የመጨረሻ ቀን ፍርድ፣ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር





## መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ የሆነውን የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ይገልጻል

ከላይ እንደተመለከትነው ሁሉ የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ በአምስት ንዑሳን ክፍሎች ይከፈላሉ ይኸውም:-

1. የደህንነት ዝግጅት፣
2. የደህንነት ሥራ እርግጠኝነት፣
3. የደህንነት መስፋፋት፣
4. የደህንነት ትርጉም፣
5. የደህንነት መፈጸም::

እጅግ ጥልቅ የሆነውን የመስኮታዊ ደህንነት ሥራ በዚህች ምድር ላይ ማንም ሙሉ በሙሉ ሊለካውና ሊረዳው አይችልም:: ጥልቅ በሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የእግዚአብሔርን የደህንነት ሥራ የሰው ልጆች በሁለት ጉዳዮች ሊገነዘቡ ይችላሉ::

1. የእግዚአብሐር ማዳን «ለእኛ»
2. የእግዚአብሐር ማዳን «በእኛ ውስጥ»

«የእግዚአብሐር ማዳን ለእኛ» በ12 ቲዮሎጂያዊ (ሥነ-መስኮታዊ) አከፋፈሎች ሊጻፍ (ሊገለጽ) ይችላል::

በዚህ ላይ የምናየው የደህንነት መፈፀም በሰዎች ማመንና አለማመን ላይ የተመረኮዘ ያለመሆኑን ነው::

አብዛኛውን የሰው ዘር እግዚአብሔርን ባለማመንና በእግዚአብሔር ላይ ጠላትነታቸውን በመግለጽ ይሄዳሉ:: ይህም ሲሆን ለሰው ልጆች የሆነው ደህንነት የማይለወጥ ሆኖ ይኖራል:: ነገር ግን ልክ አንድ ሰው በእምነት ወደ ኢየሱስ ከመጣ በኋላ ይህ እውን የሆነው ደህንነት በእውነት ይገልጻል:: ይህም ማለት ኃጢአተኝነቱን አምኖ ንስሐ የገባው ሰው በእግዚአብሔርና በኢየሱስ በማመኑ የእግዚአብሔርን ሙሉ ደህንነት ይቀበላል ማለት ነው:: ይህ ልዩ የሆነ አስደናቂ ልምምድ «የእግዚአብሐር ደህንነት በእኛ ውስጥ» የሚለው በ12 (ስነመለኮታዊ) ሀሳቦች ሊከፋፈል ይችላል:: ህያ አራቱ ዋና ሀሳቦች በሚቀጥለው ቻርት ላይ ባጭሩ ተጠቃልለው ይገኛሉ::

ለማንኛውም ሰው እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ለማዳን የወጣውን የሥዕላዊ መግለጫ የማዳን ዕቅድ ለመመርመር የሚፈልግ ሁሉ እነዚህ ባጭር የተገለጹት ሃሳቦች እርዳታ ይሰጣሉ::

## የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ

## በልጁ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ

### የእግዚአብሔር ማዳን «ለእኛ»

1. የእግዚአብሔር የማዳን ምክርና ዕቅድ
   (ሐሥ.20:27)
2. የእግዚአብሔር የማዳን ፍላጎት በልጁ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ
   (ዕብ.10:5-7፤ ኤፌ.1:5)
3. ከዓለም ፍጥረት በፊት ለደህንነት መመረጥ
   (ኤፌ.1:4-5)
4. በኃጢአትና በሰው ውድቀት ምክንያት የደህንነት አስፈላጊነት
   (ሮሜ.3:23፣ 5:12)
5. የማዳን ተስፋ በኢየሱስና በእርሱ ሥራ
   (ዘፍ.3:15)
6. የደህንነት ታሪክ ከእሥራኤል ህዝብ ጋር
   (በዘፍ.12:1) ጀምሮ
7. በእስራኤል ታሪክ ለደህንነት ዝግጅት
   (ዮሐ.4:22)
8. የደህንነት አገር የእሥራኤል ምድር
   (ዘፍ.12:1)
9. የደህንነት ህዝብ የተመረጠው የእሥራኤል ነገድ
   (ዘፍ.12:2)
10 የደህንነት ጊዜ – የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ
   (ገላ.4:4)
11. በአራቱ ወንጌሎች የተፈጸመው የደህነት ሥራና እውነት
   (ዮሐ.19:30)
12. የደህንነት መሠረት የኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ
   (1ቆሮ.3:11)





## የተፈጸመው የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ በልጁ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ

### የእግዚአብሔር ማዳን «በእኛ ውስጥ»

1. የደህንነት ለዓለም ህዝብ ሁሉ መሠራጨት
   (የሐሥ. 1: 1 -28)
2. መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ በማንበብ የሚገኘው የደህንነት ፍቺ መገለጥ (ዮሐ.5:39)
3. የደህንነት ይዘት፣ ኢየሱስና የእርሱ ሥራ
   (ዮሐ.14:6፤ ሐሥ. 4:12)
4. ደህንነትን በእምነት ስለመቀበል
   (ሮሜ.3:21-31)
5. በክርስቶስ ላመነው አማኝ የመዳን እርግጠኝነት
   (ሮሜ.4:1-25)
6. በመንፈስ ቅዱስ ምሥክርነት ደህንነት እርግጠኛ ሆኗል።
   (ሮሜ. 8:16፣ 38፣ 39)
7. የደህንነት ደስታ በተዋጁትና በዳኑት ዘንድ
   (ሮሜ.14:17፤ ፊል. 4:4)
8. አማኝ የሚያድግበት የደህንነት እውቀት
   (2ኛ ጴጥ.3:18)
9. የቅድስና ህይወት ለመኖር የደህንነት ተጋድሎ
   (ሮሜ.6:1-7፣25)
10. ደህንነትን በተቀበሉና በዳኑ የደህንነት አዋጅ መደረግ
   (2ቆሮ.5:20)
11. በእውነት ለዳኑት የመዳናቸው ያለመናወጥ ደህንነት (ሮሜ.3:1-39)
12. በእውነት ለዳኑት የደህንነት መፈጸም
   (ፊል.1:6)




ዘፍ. 1 እና 2
ያለ ኃጢአት

በመጀመሪያ

እግዚአብሔር

ሰማይንና

ምድርን

ፈጠረ::

ዘፍ. 1:2

## ሁለቱ የእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ አዕማዶች

# አልፋና ኦሜጋ

### Ā እና Ω


በእግዚአብሔር የማዳን ሥዕላዊ መግለጫ ላይ «Ā» እና «Ω» ፊደሎች ከቀኝና ከግራ ተጽፈው ይገኛሉ:: አልፋና ኦሜጋ ሁለቱ የግሪክ የመጀመሪያና የመጨረሻ ፊደላት ናቸው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልፋና ኦሜጋ ከሚለው ገለጻ በስተኋላ ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ትርጉም አለው:: በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሙሴ በሚነድ ቁጥቋጦ ውስጥ:-
*«ያለና የምኖር እኔ ነኝ »* (ዘፀ.3:14)

በአዲስ ኪዳን ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት በነበረበት ጊዜ ጌታ:-
*«ያለውና የነበረው የሚመጣው ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋና ኦሜጋ የመጀመሪያውና የመጨረሻው እኔ ነኝ»* (*ራዕ*.1:8)

እነዚህን ሁለት ጥቅሶች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው:: ዘለዓለማዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን መገለጽ ይናገራሉ:: ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም የሚኖር ነው (*መዝ.* 90:2) ያም ማለት እርሱ ብቻ ዘለዓለማዊ ነው ማለት ነው:: እርሱ ከዓለም ፍጥረት በፊት ዘለዓለማዊ ነው:: እንዲሁም:-



የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ማብራሪያ




ራዕ.21 እና 22
ያለ ኃጢአት

አዲስ

ሰማይና

አዲስ

ምድር

አየሁ

ራዕ.21

እና

22

## መጀመሪያና መጨረሻ

እግዚአብሔር የደህንነት ሥራውን በአስደናቂ ቃል ይጀምራል::
*«በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ»* (ዘፍ.1:1)::
የመጀመሪያው ሁለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች ስለ ዓለም መፈጠር ይናገራሉ:: በዕብራውያን መልዕክት እግዚአብሔር ዓለምን ከማይታየው እንደፈጠረ ተጽፏል:: «ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠሩ የምንረዳው በእምነት ነው ስለዚህ የሚታየው ነገር ሁሉ ከማይታየው እንደተሰራ እናውቃለን» (ዕብ.11:3)::
ይህም ማለት ከዓለም ፍጥረት በፊት እግዚአብሔር ብቻ (አብ፣ ወልድ፣መንፈስ ቅዱስ) ነበሩ:: ፍጥረት ሁሉ በሚቻለው ቃሉ ከማይታየው ወደ መሆን መጣ ከዘለዓለም ወደ ጅማሬ መጣ እርሱ ቢተናገረው ተፈጠረ በትዕዛዙም ሁሉ ነገር ተመሥርቶ ታየ:: *መዝ.*33:9
የእግዚአብሔር የደህንነት ዕቅድ በአዲሱ ሰማይና በአዲስ ምድር የሚፈጸመው ስለዚህ ነው::
«አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ» *ራዕ*.21:1

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች የአዲስ ሰማይና የአዲስ ምድርን መፈጠር ይገልጻሉ::

### ኃጢዓት የሌለባት አለም

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያዎቹና የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች ከሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች በአንድ ነገር የተለዩ ናቸው:: በዘፍ.1 እና 2፤ በራዕ. 21 እና 22 ከኃጢአት ነፃ ስለሆኑት ዓለም ይገልጻሉ:: እግዚአብሔር ዓለምን

ውብና ድንቅ አድርጎ ነበር የፈጠረው:: የፈጠረው ሁሉ መልካም ነበረ (ዘፍ.1:31):: የመጀመሪያዎቹ ሰዎች አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም በሆነ ሕብረት የኖሩና ኃጢዓት የሌለባቸው ነበሩ ኃጢዓት በሌለበት ዓለም የኖሩና በእግዚአብሔርና በእነርሱ መካከል ምንም ኃጢዓት ያልታየ ነበር:: ይህ ኃጢዓት የሌለበት ዓለም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ሁለት የራዕይ ዮሐንስ ምዕራፎች ተገልጿል::

እግዚአብሔር የደህንነትን ሥራ ሲጨርስ አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን ይፈጥራል:: በዚያም በአዲሱ ዓለም ኃጢዓትም ሆነ ሞት አይታይም:: ይህ ሞትና ኃጢዓት የሌለበትን ዓለም የመጨረሻዎቹ ሁለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች ያሳዩናል::

**የጅማሬውና የፍጻሜው አንድ መሆን**

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያዎቹና የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች እርስ በርስ ሲነፃፀሩ ዘለዓለማዊና ጸንተው እንደሚኖሩ ምሰሶዎች ይመስላሉ:: የዘመናትና የሰው ልጆች ታሪክ በእነዚህ ሁለት ግዙፍ ምሰሶዎች መካከል ይገኛሉ:: ማንኛውም ሰው ኃጢዓት፣ ጥፋት፣ ስቃይና ሞት ወዳለበት ዓለም ይወለዳል::

ክፋትንና ኃጢዓትን ወደ ዓለም ያመጣው ሰይጣን ነው (ዘፍ.3) «በኃጢዓት ምክንያት ደግሞ ሞት መጣ»:: ይኸውም ሰው ሁሉ ኃጢአትን ስለ ሠራ ነው (ሮሜ. 5:12)::

የእግዚአብሔር የደህንነት ዕቅድ እግዚአብሔር የጠፋውን የሰውን ዘር ለመዋጀትና ለማዳን ሁሉን ነገር እንዳደረገ ያሳየናል:: እግዚአብሔር የደህንነትን ዕቅድ ያዘጋጀው በብሉይ ኪዳን ጊዜ ነበር:: በደህንነት ታሪክ እግዚአብሔር ልጁን በመስጠቱና በመላኩ የዕቅዱን ግብ የመታ ሆነ:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የደህንነት ሥራውን በቀራንዮ መስቀል ላይ ፈፅሞ እኛን ከኃጢዓት፣ ከሞትና ከዘለዓለም ጥፋት አዳነን:: ሰው ደህንነት የሚያገኘው በጌታ ኢየሱስ ሲያምንና እምነቱን ሲገልጽ ወይም ሲያውጅ ነው::





## የእግዚአብሔር የደህንነት ዕቅድ መካከለኛ /እምብርት/
## የጎልጎታው መስቀል


*«ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው»* (1ቆሮ.3:11)::

በትልቁ የእግዚአብሔር የደህንነት ዕቅድ ዕምብርት ሆኖ የቆመው የጎልጎታው መስቀል ነው:: ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት የእግዚአብሔር ልጅ ለጠፋው የሰው ዘር ኃጢዓት የሞተው እዚያ ነው:: የጎልጎታው መስቀል የእግዚአብሔር የደህንነት ታሪክ ያተኮረበት ነጥብ ነው:: የመዋጀት ብርሃን ከዘላለም እስከ ዘላለም ከዚህ ያንጸባርቃል::

ጌታ ኢየሱስ በስብዕናው በዚህች ምድር ላይ በኖረበት ጊዜ ነው የጎልጎታው መስቀል በምድር ላይ የተተከለው:: እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስን ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የዓለምን ኃጢዓት እንዲሸከም የእግዚአብሔር በግ አድርጎ ያዘጋጀው::

*«ዓለም ሳይፈጠር እንኳን አስቀድሞ የታወቀ ነገር ግን እምነታችሁና ተስፋችሁ ከእግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ከሙታን ባስነሳው ክብርንም በሰጠው በእግዚአብሔር በእርሱ ስለምታምኑ ስለ እናንተ በዘመኑ መጨረሻ ተገለጠ»* (1ጴጥ.1:20)::

ስለሆነም ክርስቶስ የእግዚአብሔር በግ ነበር:: በመጨረሻ የመፅሐፍ ቅዱስ መፅሐፍ በዮሐንስ ራዕይ ጌታ ኢየሱስ የተገለፀው «በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም» የተገባው የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ነው:: (ራዕ.5:13)



የእግዚአብሔር ልጅ የእግዚአብሔር በግ በመሆን ለዘላለም ይኖራል (ራዕ.5:13)። ይህ እውነት በመጀመሪያ ግልጽ የሆነው አዳኙ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሞተበት ጊዜ ነው። ስለዚህ የተሰቀለው የክርስቶስ መልዕክት ሁልጊዜ ትኩረት የሚደረግበት አብይ ነገር ነው።

በመጀመሪያው የሐዋሪያው የጳውሎስ መልዕክት ወደ ቆሮንጦስ ሰዎች *«እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን»* ብሎ ይፅፈዋል (1ቆሮ.1:23)።

## የተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስ

ብሉይ ኪዳን በአጠቃላይ በሚሰቀለው ክርስቶስ ላይ ሲያተኩር። አዲስ ኪዳን ደግሞ በመስቀል ላይ በሞተው የዓለም አዳኝ በሆነው ላይ ወደኋላ በማየት ያተኩራል። ስለሆነም የተሰቀለውን ክርስቶስን የማይሰብክ እርሱ ሐሰተኛ ሰባኪ፣ ሐሰተኛና ውሸታም ነብይ ነው።

በዓለም ውስጥ ብዙ ሰዎች ስለ «እግዚአብሔርና» ስለ «ኢየሱስ» ያወራሉ። በቤተ ክርስቲያንም መድረኮች ብዙ ይሰበካል ቢሆንም የሚሰበከው ፍጹም የተሟላ አይደለም። ምክንያቱም ብዙ ጊዜ አስፈላጊው ነገር ስለሚተው ነው። እውነተኛ ደህንነት የሚገኘው በእርሱ ብቻ ነው (ሐሥ.4:12)። ስለዚህ ነው ጠቅላላ ዘለዓለማዊ ሃሳብ በተሰቀለው በክርስቶስ ላይ የሚያተኩረው። በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ እምብርት የተሰቀለው ክርስቶስ ብቻ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ከዘላለም እስከ ዘላለም ጸንቶ ይቆማል /ይኖራል/።

### «ተፈጸመ!»

በዮሐ.19:30 የሚገኘው ይህ ቃል በክርስቶስ ኢየሱስ የማዳን ሥራ ውስጥ መካከለኛ (እምብርት) ነው በጎልጎታ የደህንነት ሥራ ተፈጽሟል። ይህም ማለት ማንም ሰው አንዳች የማይጨምርበት የመስኮት ሥራ ነው። የእኛም የአማኞች የራሳችን ሥራ የተጣለ ነው። እንደ እግዚአብሔር ልጆች ክርስቶስን ልንከተለውና በእምነት ልናድግ ይገባናል። ዓለምን ልንክድና በቅድስና ልንኖር ይገባናል። ይህንንም ልናደርግ የምንችለው በጎልጎታ የማዳን ሥራ መሠረት ብቻ ነው። ይህ ሥራ በእኛ ሳይሆን በጌታችንና በአዳኛችን የተፈ[illegible]መ ነው።

ከክርስቶስ ጋር ተሰቅለናል ተሰቅለንም እንኖራለን (ሮሜ6:6)። ማንም ሰው ራሱን መዋጀት አይችልም። በክርስቶስ ኢየሱስ ጎን የተሰቀለው የነፍሰ ገዳይ ሰው ታሪክ እንኳን ይህንን ግልጽ በሆነ መንገድ ያስተምረናል። ይህ ሰው ንስሐ ገባ የጌታችንን ስም ጠራ ጌታም «ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» ብሎ ተናገረው (ሉቃ. 23:43)።





ይህ ሰው እጆቹና እግሮቹ በመስቀል ላይ በሚስማር ስለተቸነከሩ ምንም ማድረግ አይችልም ነበር። እጆቹን ማጠፍም ሆነ መጠመቅ አይችልም ነበር አዳኙ በገነት እንደሚሆን ተስፋ ሰጠው። እኛም በዚህ ጊዜ ደህንነትን ልንቀበልና ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ልንሞት እንችላለን። ደህንነትን ስናገኝና አዳኙን በልባችንና በህይወታችን በእምነት ስንቀበል አዲስ ህይወት በእኛ ይጀምራል። ስለዚህ በኋላ ራሳችንን ለጥምቀት እንሰጥና እማኞች በመሆን እንካፈላለን። ሕብስቱና ወይኑ የጎልጎታን ሥራ የሚያስታውሱን ማዕድ ናቸው (1ቆሮ.11:24-25)።

## ከክርስቶስ በፊት – ከክርስቶስ በኋላ

ጎልጎታ በዓለምና በማዳን ታሪክ እምብርት ላይ ይገኛል። ከዚህም የተነሳ ነው ታሪካዊ ድርጊቶችን ለማመልከት ከክርስቶስ ልደት በፊትና ከክርስቶስ ልደት በኋላ በማለት የምንጠቀመው። የእግዚአብሔር ጠላቶች እንኳን ይህን የጊዜን አቆጣጠር ለመጠቀም የተገደዱ ሆነዋል። ይህም ታላቅ የሆነውን የማዳን ሥራ ከዓለም ላይ ለማጥፋት እንደማይቻል ግልጽ ያደርገዋል። በአምስቱ የዓለም አህጉሮች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በተሰቀለው በክርስቶስ ኢየሱስ እያመኑ ይከተሉታል። ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት በጎልጎታ መስቀል ላይ የተፈጸመው የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ የማያጠራጥር የታሪክ መሠረትና ነጥብ ነው።

### ሦስቱ መለኮታዊ መስመሮች የሚመስሉት

# የአምላክ ሦስትነት /ሥላሴ/

እግዚአብሔር መካከለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ ነው። ነገር ግን እኛ ሰዎች በዙሪያችን የሚዞረውን ተፈጥሮ በመመልከት ራሳችንን መዓከላዊ በማድረግ የፍጥረተ-አለም መካከለኛ የሆነውን እግዚአብሔርን እንዘነጋለን። በእውነትም እግዚአብሔር ለፍጥረተ-ዓለም መዓከላዊ ነው።

*«ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና» (ሮሜ.11:36)።*

እግዚአብሔር የማይታይ ነው ስለዚህም በአይንና በህሊና እርሱን መሳል (መቅረጽ) አይቻልም። ምክንያቱም በእግዚአብሔር ቃል ተከልክሉአልና። ስለዚህ ጉዳይ ሙሴ በጌታ መንፈስ ተመርቶ «በላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው፣ በታችም በውሃ ካለው ነገር ማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ጣኦት አድርገህ አትስራ» (ዘፀ.20:4)። በማለት ስለዓፈ እግዚአብሔርን በምንም ነገር መስለን ልንገልጠው አልተፈቀደልንም።

**መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር አብ (አባትነት)**

*«እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፣ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ።»* (ዮሐ.20:17) በማለት ይናገራል።

**መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ወልድም**

*«እነሆ ድምጽ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው»* በማለት ይገልፃል (ማቴ.3:17)።

**መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይናገራል**

*«አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ፣ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፣ እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል»* (ዮሐ.14:26)።

በዚህም አንዱ እምላክ ራሱን በሦስትነት መግለጹን እንገነዘባለን። ሥነ-መለኮታውያን /የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎች/ የእምላክን ሦስትነት ለመግለጽ በሥነ-መለኮታዊ ቋንቋ ስላሴ የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ። ይህንን በመዋጀት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ለመግለጽ ሞክረናል። በሁለቱ ታላላቅ ርዕሶች ሥር እነዚህን ሦስት መስመሮች እናገኛለን። ከእነዚህ ሦስት መስመሮች ብርቱካንማ የሆነው የመጀመሪያው መስመር እግዚአብሔር አብን ያመለክታል፣ ቡናማ የሆነው የመካከለኛው መስመር ደግሞ እግዚአብሔር ወልድን ሲያመለክት ከስር ያለው አረንጓዴው ደግሞ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ያመለክታል።

እነዚህ ሦስቱ የመለኮት መግለጫ መስመሮች በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ እግዚአብሔር አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስ በመላው ዓለምና በሰዎች ታሪክ የበላዩን ሥፍራ እንደያዙ ግልጽና ጉልህ ያደርጉታል።

**አብ** ዮሐንስ 10.29 ኤፌ 3,14.15; 4,6

**ወልድ** 1ኛ ጴጥ 1,18-21 ዕብራ 1,2.3 ዮሐ 1,1-18

**መንፈስ ቅዱስ** ዮሐ 16,7-15 ሮሜ 8,2.9,14-16





**1. ብርቱካንማው መሥመር፣ /እግዚአብሔር አብ/**

*«ስለዚህ ምክንያት በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ፊት እንበረከካለሁ»* (*ኤፌ.3:14፣15*)።

በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ካርታዊ መግለጫ ላይ እግዚአብሔር አብን የሚያመለክተው በብርቱካንማ ቀለም ተለይሞ ያለማቋረጥ በቀጥታ ከግራ ወደ ቀኝ ይሄዳል። በዚህ መሥመር እግዚአብሔር አብ ሁልጊዜ በስማይ ያለና የሚኖር መሆኑን ለመግለጽ እንፈልጋለን። «ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም» እርሱ አምላክ ነው (*መዝ.(90):2*) ። በዮሐንስ ወንጌል የእግዚአብሔር ልጅ ስለዚህ እውነት እንዲህ በማለት ምስክርነቱን ሰጥቷል።

*«መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም። በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው»* (*ዮሐ.1:18*)።

ስለሆነም በልጁ ብቻ ነው አብን የምናውቀው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱን (አብን) ለእኛ ገልጾልናል «እኔን ያየ አብን አይቷል» ያለው እርሱ ብቻ ነው (*ዮሐ.14:9*)። እግዚአብሔር አብ እስከ አዲሱ ሰማይና ምድር መፈጠር ሳይታይ ይኖራል (*1ጢሞ.6:15-16*)።

**2. ቡናማው መሥመር - /እግዚአብሔር ወልድ/**

**ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ ለመኖሩ**

*«ዓለም ሳይፈጠር እንኳ አስቀድሞ ታወቀ ስለ እናንተ በዘመኑ መጨረሻ ተገለጠ»* *(1ጴጥ.1:20) ከሚለው ጥቅስ እንረዳለን።*

በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ቡናማው መስመር የእግዚአብሔርን ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ያመለክታል። ከዘላለም ዘመናት በፊት ክርስቶስ እምላክ ነበር። እግዚአብሔር አብ ከቶ ክርስቶስን አልፈጠረውም። ክርስቶስ እንደ እግዚአብሔር አብና እንደ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው። *«እኔና አብ አንድ ነን»* (*ዮሐ.10:30*) ብሏልና። ስለሆነም ጌታ ኢየሱስ ዘለዓለማዊው ልጅ ነው ልክ እንደ አብ ከዓለም ፍጥረት በፊት ለዘለዓለም ነበር። በሥነ-መለኮት ጥናት ይህ እውነት «የኢየሱስ እስቀድሞ መኖር» በሚል ይገለጻል። *«አሁንም አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ»* (*ዮሐ.17:5*)

## የኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ መገለጥ /ሰው መሆን/

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ራሱን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መግለጡን ያስተምረናል:: *«ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ» (ገላ.4:4)*:: እኛን ለማዳን ከድንግል ማሪያም በመወለድ ወደዚህች ወደ ተረገመች ዓለም ገባ::

*«ቃልም ሥጋ ሆነ፣ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ:: አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን» (ዮሐ.1:14)*::

በካርታው ላይ የኢየሱስ መሆንን በሚያመለክተው መስመር ላይ በሚሄደው ቡናማ ቀለም መስመር የተገለጠው ነው:: በዚህ ቀጥ ባለው መስመር መጨረሻ ላይ ያለው ትንሹ ቀስት የእግዚአብሔር ልጅ በመጣ ጊዜ በእርሱ በኩል ሰማይና ምድር እርስ በርሳቸው መገናኘታቸውን የሚያሳይ ነው አምላክ በልጁ በኢየሱስ በኩል ሰው መሆኑ በምንም ሊገመት የማይቻል ድንቅ ነው:: የማይሞተው እግዚአብሔር ወልድ ለመሞት ይችል ዘንድ እንደ እኛ ሰው መሆን አስፈለገው:: ጌታ በሞት ላይ ባለድል መሆን የሚችለው በሞቱ በኩል ብቻ ነበር *(ዕብ.2:14-15)*:

## የኢየሱስ ክርስቶስ የመዋጀት ሥራ

የእግዚአብሔር ልጅ ለሰላሳ ዓመታት በዚህች ምድር ላይ ታዋቂ ሳይሆን ኖረ:: ከዚህ ጊዜ በኋላ በሕዝብ ፊት ለመጀመሪያ ጊዜ መሲሂ ሆኖ በመታየት የአባቱን ክብር በእግዚአብሔር ልጅነቱ ገለፀው *(ሉቃ.3:23)*:

*«ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው:: የአንተ ነበሩ ለእኔም ሰጠሃቸው፣ ቃልህንም ጠብቀዋል» (ዮሐ.17:6)::*

*«የእግዚአብሔር በግ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ ሆኖ»:: /ዮሐ.1:29* NIV/

የደህንነትን ሥራ በመስቀል ላይ ፈጸመ ስለ ኃጢአታችን ሞተ:: ስለዚህ ነው ቡናማው መሥመር በማዳን ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ በቀጥታ በመስቀሉ መካከል የሚያልፈው:: በመስቀሉ መካከል «ተፈጸመ» የሚለው አስደናቂ ቃል ተጽፏል:: *(ዮሐ.19:30)*

## የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ

የእግዚአብሔር ልጅ የሞትን ኃይል የወሰደውና ለአንድ ጊዜና ለዘለዓለም በሞት ላይ ድልን የተቀዳጀው በትንሳኤው በኩል ነው:: ጌታ በኋላ በድል ትንሳዔው





በኩል የሚፈፅመውን ይኸንንም ሥራ ቀደም ብሎ በአልአዛር መቃብር በአስደናቂ ቃላት:-

*«ትንሣኤና ሀይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ሕያውም የሆነው የሚያምንብኝ ለዘለዓለም አይሞትም. . .» (ዮሐ. 11:25-26)* በማለት ተናግሮት ነበር::

የክርስቶስ የመዋጀት ሥራ ያለ ትንሣኤው ሙሉ አይሆንም ነበር:: ከዚያም የተነሳ የኃጢአታችንን ሥርየት ልንቀበል አንችልም ነበር:: ነገር ግን ለዘላለም በሞት ተገዢ እንሆን ነበር:: ስለዚህም ነው ትንሣኤው የመዳንን እውነት በአድናቆት የተፈጸመ ሥራ ያደረገው:: ይህንንም:-

*«እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፣ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፣ ይኸውም ዲያብሉስን ነበር:: በህይወታቸው ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነፃ እንዲያወጣ፣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ» (ዕብ.2:14-15)::* በማለት የዕብራውያን መልዕክት ፀሐፊ ያቀርበዋል::

## የኢየሱስ ክርስቶስ እርገት

ከትንሣኤው በኋላ ጌታ ከደብረ ዘይት ተራራ ወደ ሰማይ አረገ:: ደቀ መዛሙርቱ *«እያዩት ከፍ ከፍ አለ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው» (ሐሥ.1:9)::*

የኢየሱስ ክርስቶስ እርገት በሥዕላዊ መግለጫ ላይ ከፍ ብሎ በሚወጣው ቡናማ ቀለም የተገለጠ ነው:: በማቴ. 24:30 እንደተፃፈው ሁሉ «በኃይልና በታላቅ ክብር» ወደ ምድር እስከሚመለስበት ጊዜ ድረስ «በእግዚአብሔር ኃይል ቀኝ ይቀመጣል» *(ሉቃ.22:69)*: የዕብራውያን መልዕክት የክርስቶስን በአብ ቀኝ መቀመጡን ይገልፃል::

*«ኃጢአታችንን በራሱ ካነጸ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ» (ዕብ.1:3)::*
*«እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቁ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን ጸንተን ኃይማኖታችንን እንጠብቅ» (ዕብ.4:14)* በማለት አቅርቦታል::

## የኢየሱስ ክርስቶስ የሊቀ ካህናትነት አገልግሎት

በሰማይ ክርስቶስ ለእርሱ ለተገቡት ሁሉ ሊቀ ካህናት ነው::

*«ከተናገርነውም ዋና ነገሩ ይህ ነው፣ በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን::» (ዕብ.8:1)*

*«ልጆቼ ሆይ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፣ እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» (1ዮሐ.2:1)::*

ዳግም የተወለዱ አማኞች በሙሉ ዘላለማዊው ሊቀ ካህናት ስለ እነርሱ መማለዱን ሊያውቁ ይገባቸዋል:: ምክንያቱም *«ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና»* ተብሎ ተጽፏልና (*ዕብ.7:25*)::

## የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ

የክርስቶስ *የመጀመሪያ መምጣቱ* /በመዋረድ/ ነበር:: *አመጣጡንም* ጳውሎስ «በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፣ ለሞትም ይኸውም ለመስቀል ሞት የታዘዘ ሆነ» (*ፊል.2:8*) በማለት ይገልፀዋል:: በአንፃሩ ደግሞ ዳግም ምጽዓት «በኃይልና በታላቅ ክብር» ይሆናል (*ሉቃ.21:27*):: ነቢዩ ዘካሪያስ ይህን ታላቅ ሁኔታ «በዚያም ቀን እግሮቹ በኢየሩሣሌም ትይዩ በምሥራቅ በኩል ባለው በደብረዘይት ላይ ይቆማሉ» (*ዘካ.14:4*) ብሎታል:: የእግዚአብሔር ልጅ አንድ ጊዜ እንደገና በዚህች ምድር ላይ ይቆማል:: *በራዕ.20:6* መሠረት መሲሃዊ የሰላም መንግስቱን ይመሠርትና በዚህች ምድር ላይ ለሺህ ዓመት ይገዛል:: የክርስቶስ ዳግም መምጣት በካርታው ላይ ወደታች በሚወርደው ቡናማ መስመር የተገለጸ ነው:: መስመሩ በመሲሁ የሠላም መንግሥት ያልፍና በቀጥታ ወደ «አዲስ ሰማይና ምድር» ያመራል (*ራዕ.21:1*)::

## 3. አረንጓዴው መሥመር - እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

በማዳን ሥዕላዊ መግለጫ ላይ መንፈስ ቅዱስ በአረንጓዴ መስመር የተገለጸ ነው:: እርሱም እንደ አብና እንደ ወልድ ዘለዓለማዊ አምላክ ነው::

*«እኔም አብን እለምናለሁ ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፣ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው:: ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር፣ ውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ» (ዮሐ.14:16-17)::*

ጌታ ኢየሱስ ይህን ተስፋ ለደቀ መዛሙርቱ ሲሰጥ መንፈስ ቅዱስ በሙላት ወደ ምድር አልመጣም ወይም አልወረደም ነበር:: ምክንያቱም ኢየሱስ ገና ስላልከበረ ነበር (*ዮሐ.7:39*):: መንፈስ ከአብ ዘንድ ከሰማይ ወደ ምድር አልመጣም ነበር፣ ምክንያቱም ክርስቶስ ወደ አባቱ መመለስ ነበረበትና::*«እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ»* (*ዮሐ.16:7*)





ብሏልና:: ስለዚህ ክርስቶስ በመጀመሪያ ስለ ኃጢዓታችን መሞትና እኛን በደሙ መስዋዕትነት ከአባቱ ጋር ማስታረቅ ነበረበት:: ከዚህ በኋላ ሊቀ ካህናት በመሆን ወደ ሰማይ አረገና በመዋጀት ሥራው በእግዚአብሔር ዘንድ ስለ እኛ ሊታይ ቀረበ (*ዕብ.9:12-26*):: ከዚህ በኋላ ነበር እንደ ተስፋ ቃሉ መንፈስ ቅዱስ መውረድ የነበረበት::

ስለዚህ ነው የሐዋሪያት መልዕክት በተሰቀለውና በተነሳው በክርስቶስ ላይ ያተኮረው:: በሰው ልብ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚያድረው በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ሲታጠብ ብቻ ነው:: የኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት፣ መቀበር፣ መነሳትና ማረግ ለመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ተቀዳሚና አስፈላጊ ነገር ነበር::

## የቤተ ክርስቲያን መመሥረት

ከኢየሱስ ዕርገት ከአሥር ቀን በኋለ መንፈስ ቅዱስ ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ወደ ምድር መጣ:: ይህንንም:-

*«ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምጽ መጣ:: ተቀምጠው በነበሩበትም ቤት ሞላው እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፣ በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው:: በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር:: (ሐሥ.2:2-4)* ከሚለው ህረፍተ ነገር እንረዳለን::

የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ በደህንነት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ወደታች በሚወርድ አረንጓዴ መስመር የተመለከተ ነው:: ይህ «በዓለ ሃምሳ» ተብሎ በሚጠራው ቀን የተከናወነ ነው (*ሐሥ.2:1*):: በዚህ ዕለት ሶስት ሺህ ሰዎች በጌታ ኢየሱስ አመኑና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ (*ሐሥ.2:41*):: ዛሬም ቢሆን ይህን ታሪካዊ የማዳን ታሪክ ቀን «በዓለ ሃምሳ» በማለት እንጠራዋለን:: የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በዚች ምድር የተመሠረተችበት ቀን ነበር::

## የቤተ ክርስቲያን ዘመን

በበጉ /በክርስቶስ/ ደም በታጠቡት ልብ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ያድራል:: ይህ በጎልጎታ መስቀል ላይ በኢየሱስ የተፈጸመውን የማዳን ሥራ በእምነት የሚቀበሉትን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው:: በዚህም በአይሁድና በአህዛብ መካከል ልዩነት የለም:: ምክንያቱም *«በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና»* (*ኤፌ.2:18*):: ተብሎ ስለተፃፈ በተጨማሪም:-

*«ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም:: በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፣ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» (ኤፌ.2:19-20)* የሚል ስለምናነብብ::


የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በምድር ያሉትን አማኞች ያቀፈች ናት:: ጌታ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ከሆነበት ከሁለት ሺህ ዓመታት ጀምሮ በእርሱ የዳኑትን እየተቀበለ በየዕለቱ በቤተ ክርስቲያን ላይ እየጨመረ ነው (*ሐሥ.2:47*)::

በደህንነት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ወደ ጎን የሚሄደው አረንጓዴው መሥመር በዚህ ምድር መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን የኖረበትን ዘመን ያመለክታል:: እኛ የምንኖረው በዚህ የደህንነት ዘመን ውስጥ ነው:: ጌታ የእርሱ የሆኑትን ወደ እርሱ
ለመሰብሰብ በሚመጣበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ወደ ፍጻሜ ይመጣል:: ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ አለች:: ምክንያቱም እንደ ተስፋ ቃሉ መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ ስለ አለ ነው:: (*2ጢ.ሞ.1:14፤ ያዕ.4:5*) የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በሰማይና በምድር ያለች የነበረችና በጣም ድንቅ የሆነች ናት:: ለሰው አእምሮ ቤተ ክርስቲያን የማትጠፋ «መለኮታዊ ሚስጢር» ሆና ትኖራለች (*ኤፌ.3:3*)::

መጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ያላትን መንፈሳዊ ህብረት እንማርና እናውቅ ዘንድ ስለ ቤተ ክርስቲያንና አባላቷ በግምት 700 ያህል መግለጫዎች ይሰጠናል:: የሚቀጥለው ሥዕላዊ መግለጫ ባጭሩ የቤተ ክርስቲያንን ባህርይ የሚገልጹ 24 መግለጫዎችን ይዟል:: ይህ አጭር መግለጫ ሊከፈትና ሊገለጽ የማይቻለውን የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የያዘችውን መንፈሳዊ ህብትና ብልጽግና የሚገልጥ ነው:: በእግዚአብሔር የመዋጀት ዕቅድ ቤተ ክርስቲያን ልዩ ቦታ መያዟ ሊገመት የማይቻል ታላቅ ነገር ነው:: የቤተ ክርስቲያን ዘመን ሁለተኛ ጊዜ የማይመጣ በጣም ምርጥና ልዩ የሆነ የፀጋ ዘመን ነው::








## የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ

ጌታ ቤተ ክርስቲያኑን ወደ ሰማይ እስከሚወስዳት ድረስ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ ይኖራል::

*«ከዚያ በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን እንዲሁም ሁልጊዜ ከእርሱ ጋር እንሆናለን » (1ተሰ.4:17)::*

መንፈስ ቅዱስና ቤተክርስቲያን በዚህ ምድር ላይ አይቀሩም:: በተወሰነው ጊዜ በጌታ ይወሰዳሉ:: ይህ የተወሰነው ጊዜ ሊታወቅና ሊገመት አይቻልም::

*«ወንድሞች ሆይ ስለ ዘመናትና ስለ ወራት ምንም እንዲጻፍላችሁ አያስፈልጋችሁም:: የጌታ ቀን ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ እንዲሁ ይመጣ ዘንድ ራሳችሁ አጥብቃችሁ አውቃችኋልና» (1ተሰ.5:1፤2)::*

በማዳን ሥዕላዊ መግለጫ ቤተ ክርስቲያንን በሚያመለክተው መሥመር መጨረሻ ላይ በትልቅ አረንጓዴ ጥያቄ ምልክት ተመልክቷል:: ይህ የጥያቄው ምልክት እዚያ የተደረገበት ምክንያትም ማንም ሰው የቤተ ክርስቲያንን የመነጠቂያ ሰዓትም ሆነ ጊዜን የማያውቅ መሆኑን ለማሳየት ነው:: ጌታ ቤተ ክርስቲያኑን ሊወስድ በሚመጣበት ጊዜ «በቅጽበት ዓይን» (1ኛ ቆሮ. 15:52) የሚከናወን ጉዳይ ነው:: በመጀመሪያው የግሪክ ትርጉም ይህን ገለጻ በማይታይ /IN AN ATOM/ የአቶም መክፈያ የሚወስድበትን ጊዜ ያህል ማለት ነው :: ይህ ገለጻ የማይከፈል አጭር ጊዜ መሆኑን ያሳያል:: ይህም ማለት መነጠቅ በሰዓት ወይም በደቂቃ ወይም በደቂቃ አንድ አሥረኛ ጊዜ ውስጥ የሚሆን አይደለም፣ ነገር ግን በጊዜ ሊለካ በማይቻል በጣም ፈጣን በሆነ ጊዜ ውስጥ የሚሆን ነው:: ስለሆነም ማንኛውም ዳግም የተወለደ ክርስቲያን ሁልጊዜ የተዘጋጀ መሆን አለበት::

ከጥያቄው ምልክት በላይ ወደ ላይ የሚወጣው አረንጓዴ መሥመር የቤተ ክርስቲያንን መነጠቅ ያመለክታል:: ትንሹ ቀስት በዚህ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ከክርስቶስ ጋር የመገናኛውን ነጥብ ያመለክታል (*1ተሰ.4:17*): የተነጠቀችው ቤተ ክርስቲያን ጌታን በአየር ትቀበለዋለች:: እርሷን ለመቀበልና እጅግ ሰፊ ወደ ሆነው ክብር ሊወስዳት ይመጣል:: ማንኛውም ዳግም የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ ይህን ጊዜ በትልቅ መሻት ሊመለከተውና ሊጠብቀው ይገባል::





## ሦስቱ የሰው ልጅ ታሪክ መሥመሮች
# የዓለም ህዝብ፣ የእሥራኤል ሕዝብና
# የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን

መጽሐፍ ቅዱስ ሁልጊዜ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ስላለው ሕብረት ይናገራል:: ባለፈው ምዕራፍ ስለ መለኮት ሦስትነት /ሥላሴ/ ከተነጋገርን አሁን ደግሞ ትኩረታችን ወደ ሰው ዘር ይሆናል::

### የመዳን ዕቅድ ቁልፍ

በማዳን ታሪክ ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ መካከል ጉልህ በሆኑ በሰማያዊ፣ በቀይና በአረንጓዴ የተሰመሩ ሦስት መስመሮች ይገኛሉ:: እነዚህ ሦስት መስመሮች በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ሦስት የሰው ዘሮችን ያመለክታሉ:: ሐዋሪያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው በመጀመሪያ መልዕክቱ *«ለአይሁድም፣ ለግሪክም ሰዎች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም ማሰናከያ አትሁኑ»* በማለት ጽፏል *(1ቆሮ.10:32)::*

ይህ ጥቅስ በአጠቃላይ የእግዚአብሔርን የመዋጀት ዕቅድ ቁልፍ ነገር ስለያዘ እጅግ አስፈላጊ ጥቅስ ነው:: ሦስቱ ሕዝቦች አንዱ ከሌላው የተለዩ ናቸው ይህንንም ከሚከተለው ማብራሪያ በግልጽ ማየት ይቻላል::

1. አይሁድ ዕብራውያን፣ እሥራኤላውያን (የእሥራኤል ነገድ)
2. ግሪክ /በአይሁድ አባባል ከእሥራኤል ውጭ የሆኑት በሙሉ፣ አህዛብ ተብለው ይጠራሉ::/
3. የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን /አይሁድና አህዛብ በክርስቶስ ያመኑ/ ይህ ማለት ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች ማለት ነው::

| |
|---|
| አሕዛብ |
| እስራኤል 1 ቆሮንጦስ 10,32 |
| አብያተ ክርስቲያን |

ይህ አከፋፈል ለእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ መሠረት ነው:: ሦስቱ የተለያዩት መስመሮች ከላይ የተጠቀሱትን የሦስቱን ህዝቦች ክፍል ያመለክታሉ:: ሰማያዊው መስመር አህዛብን ወይም የዓለምን ህዝቦች ያመለክታል:: ቀዩ መሥመር የእግዚአብሔርን የመዋጀት ታሪክ ከእሥራኤል ህዝብ ጋር ያለውን ይገልጻል:: አረንጓዴው መስመር ደግሞ የክርስቶስ ኢየሱስን ቤተ ክርስቲያን ያመለክታል:: ማንኛውም ሰው ከእነዚህ ከሦስቱ በአንዱ ውስጥ የተካተተ ነው:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ ከእነዚህ ውጭ ሌላ ህዝብ የለም:: እነዚህም :-

## 1. ሰማያዊው መሥመር

# የዓለም ሕዝቦች

### አጭር እይታ

በማዳን ዕቅድ ታሪክ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ የዓለም ሕዝቦች ታሪክ በሰማያዊ ቀለም የተመለከተ ነው:: ይህ መስመር ለብዙ ሺህ ዓመታት በጥፋት ውስጥ ያለውን የሰውን ልጅ ታሪክ ያመለክታል:: ኃጢዓትና ሞትን የሚያመለክተው ጥቁሩ መስመር ነው:: ይህ መስመር የጠፉትን የአዳምን ትውልዶች ያመለክታል:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል *በማቴ.7:13* ወደ ጥፋት በሚወስደው በሰፊው መንገድ ላይ እየተጓዙ ስላሉ ነው:: እዚህ የምንናገረው ስለማያምኑትና አምላክ የለሽ ስለሆኑት እግዚአብሔርን ስለማያውቁ ወይም ለማወቅ ስለማይፈልጉትና እንደዚሁም አስደናቂ የሆነውን የክርስቶስን የማዳን ሥራን ስለማያውቁት (ስለሚቃወሙት) አሕዛብ ነው:: ሐዋሪያው ጳውሎስ *«ከጌታ ፊት ከኃይሉም ክብር ርቀው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ» (በ2ተሰ.1:9)* እንዳለ እድላቸው የዘላለም ጥፋት ይሆናል:: ዛሬ በዓለማችን ከ6 ቢሊዮን በላይ የሆኑ ሕዝቦች ይኖራሉ:: ከእነዚህ አብዛኛዎቹ በሰፊው መንገድ ላይ እየሄዱ ያሉ ናቸው::

ሰማያዊው መስመር በዓለም ታሪክ ውስጥ አሰቃቂ የሆኑትን ጥፋትና፣ ጉስቁልና፣ ጦርነትንና ሞትን ያሳያል:: ባለፉት ብዙ ሺህ ዓመታት ውስጥ አራት ታላላቅ የዓለም ገገርዎች ተነስተው ነበር ነገር ግን ሁሉም ወድቀዋል:: በአሁኑ ጊዜ ዓለም አቀፍ የሆነ መንግስት የለም:: በክርስቶስ ዳግም መምጣት በሚጠፋው በክርስቶስ ተቃዋሚ ዘመን እነዚህ አራቱ ታላላቅ መንግስታት እንደገና ይነሳሉ:: ስለዚህ ነገር ወደ ፊት ሰፋ ባለ ሁኔታ እንመለከታለን::

ሰማያዊው መስመር «በነጩ ዙፋን ፍርድ ያከትማል» ይህ ፍርድ እያንዳንዱ የሚጠፉት (የሚፈረድባቸው) ስለ ስራቸው መልስ የሚሰጡበት ፍርድ ይሆናል:: «ሙታን ሁሉ ተነስተው በእግዚአብሔር ፊት በሚቀርቡበት» በነጩ ዙፋን ፊት የሚከናወን ነው:: *(ራዕ.20:11)* በዚያ «እያንዳንዱ እንደ ሥራው መጠን» የሚፈረድበት ይሆናል:: በተጨማሪም *(ራዕ.20:13)* «በህይወት መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም ወደ እሳት ባህር ተጣለ» *(ራዕ.20:15)* ያልዳኑት የዓለም ህዝቦች አስቃቂ ዕድላቸው የዘለዓለም ጥፋት ነው::





### የጥንቱ ታሪክ

የመጀመሪያዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ አሥራ አንዱ ምዕራፎች የሰውን ዘር ጅማሬን የዓለምን ህዝቦች ታሪክ ይሰጣል:: እነዚህ ምዕራፎች የጥንቱን ታሪክ ይዘዋል:: የሰው ዘርና የዓለም መሠረት እዚህ ተገልጸዋል:: የዚህ ዘመን አራቱ ዋና ዋና ታሪካዊ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው:-

1. የዓለም መፈጠር *(ዘፍ. 1 እና 2)*
2. የሰው ውድቀትና ውጤቶቹ *(ዘፍ.3 እስከ 5)*
3. የጥፋት ውሃ *(ዘፍ.6 እስከ 8)*
4. የባቢሎን ግንብ *(ዘፍ.11)*

እነዚህ ሁኔታዎች ስለምናጠናው ስለ እግዚአብሔር የመዋጀት ምክር በጣም አስፈላጊዎች ናቸው:: ስለሆነም ከዚህ በመቀጠል አጭር ገለጻ እናደርጋለን::

### የዓለም አፈጣጠር

1. *እግዚአብሔር ዓለምን እንዴት ፈጠረ?*

እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው በቃሉ ነው:: «በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ፅኑ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ» *(መዝ.(33):6-9፤ ዕብ.11:3)*::

2. *እግዚአብሔር ዓለምን ከምን ፈጠረ?*

እግዚአብሔር ዓለምን ከምንም /ከማይታዩት/ ፈጠረ *(ዕብ.11:3)*::

3. *እግዚአብሔር ዓለምን መቼ ፈጠረ?*

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ዓለምን ፈጠረ*(ዘፍ.1:1)*::

4. *እግዚአብሔር ዓለምን በማን በኩል ፈጠረ?*

በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ፈጠረ::
*(ዕብ.1:2፤ ቆላ.1:16፤ ዘፍ.1:2፤ (መዝ.(33):6)*

5. *እግዚአብሔር ዓለምን መፍጠሩን በምን እናውቃለን?*

እግዚአብሔር ዓለምን መፍጠሩን የምናውቀው በእምነት ነው *(ዕብ.11:3)*::

6. *በዘፍጥረት 1:1 የዓለም መፈጠር የተገለጸው እንዴት ነው?*

ሀ. እግዚአብሔር ዓለምን በስድስት ቀናት ፈጠረ *(ዘፍ. 1:1-31)*

በ1ኛው ቀን:- እግዚአብሔር ብርሃንን ፈጠረ::
በ2ኛው ቀን:- እግዚአብሔር ከሰማይ በላይና በታች ያሉትን ውሆች ለየና ሰማያትን ፈጠረ::
በ3ኛው ቀን:- እግዚአብሔር ምድርንና ውሀ ለየና ተክሎችን ፈጠረ::

በ4ኛው ቀን፡- እግዚአብሔር በሰማይ ያሉትን ፀሐይን፡ ጨረቃና ክዋክብትን ፈጠረ።
በ5ኛው ቀን፡- እግዚአብሔር ዓሶችንና በሰማይ የሚበሩትን ፈጠረ።
በ6ኛው ቀን፡- እግዚአብሔር እንሰሶችን አራዊትንና ሰውን ፈጠረ።
በ7ኛው ቀን፡- እግዚአብሔር ከሥራው ሁሉ አረፈ (*ዘፍ.2፡1-4*)፡

ለ. እግዚአብሔር ዓለምን በሦስት ዋና ደረጃ በመከፋፈል ፈጠረ።

ሀ. የመጀመሪያው ደረጃ ፍጥረት፣
ዓለምን ወይም ሕይወት የሌላቸውን አካሎች ፈጠረ። (*ዘፍ.1፡1-19*)
1ኛ ቀን ብርሃን
2ኛ ቀን አየር
3ኛ ቀን ምድር ገሰጸ
4ኛ ቀን የሰማይ ህብረ ኮከብ

ለ. የሁለተኛው ደረጃ ፍጥረት
ሕይወት ያላቸው ነገሮችን ፈጠረ። (*ዘፍ.1፡20-25*)
5ኛ ቀን በባህር ያሉትን /ዓሶችን/ በአየር የሚበሩትን /ወፎችን/
6ኛ ቀን በምድር ላይ ያሉትን አራዊት፣እንሰሳት፣ ትላትሎችን

ሐ. የሦስተኛ ደረጃ ፍጥረት
6ኛ ቀን መለኮታዊ ህይወት ሰውን (*ዘፍ 1፡26 እስከ 28*)

*«እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ፣ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድረጎ ፈጠራቸው።»*

እነዚህ ሁሉ በራሳቸው ሙሉ ተደርገው ተፈጠሩ። አስደናቂ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ስለ እነዚህ መፈጠር «እግዚአብሔር ፈጠረ» በሚል ገልጿል።

(*ዘፍ. 1፡1*) «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ»
(*ዘፍ. 1፡21*) «እግዚአብሔር ዓሶችንና ወፎችን ፈጠረ»
(*ዘፍ. 1፡27*) «እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ»

ከዚህ ጋር በመያያዝ በእነዚህ ሦስት የመፍጠር ሂደት የኢቮሊዩሽን ፍልስፍና ሃሰት መሆኑ የተጋለጠ ነው። ምክንያቱም እያንዳንዱ ፍጥረት አስደናቂ በሆነው «እግዚአብሔር ፈጠረ» በሚለው ቃል የተፈጠረ ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር ሕይወት የሌላቸውንና ህይወት ያላቸውን ከብርሃን፣ ከአየር፣ ከምድር ተክሎችና በሰማይ ያሉት (ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ክዋክብት) በመጀመሪያ የፍጥረት ክፍል





በሥልጣናዊ መንገድ ቢፈጥር ኖሮ አሶች፡ ወፎችና ሕይወት ያላቸው እንስሳት በሁለተኛው የመፍጠር ክፍል ሲሆን አይችልም ነበር።

እነዚህ ሕይወት ያላቸው አንሰሳት (ነገሮች) በሁለተኛው የፍጥረት ክፍል የሚገኙ ናቸው። «እግዚአብሔር ፈጠረ» በሚለው አስደናቂ ቃል የተገኙ ናቸው። አሶች ወፎችና እንሰሶች ሕይወት ካላቸው ክፍል ውስጥ ናቸው። እነዚህ የደም ዝውውር፣ የማወቅ፣ ሰቃይን የመረዳት ስሜት አላቸው። አብዛኞቹ በምድር ላይ የሚገኙት እንሰሳት አጥቢዎች ናቸው። እነርሱም መዋለድ፣ ልጆቻቸውን ማሳደግና መጠበቅ ይችላሉ። ከሚሰበር ተክልና ከሚቆረጥ ዛፍ ልዩነት አላቸው። ተክሎችና ዛፎች ሰቃይን የመሰማት ነገር የላቸውም። እንደ ሰው ሲቆስሉ ወይም ሲጎዱ ከሚሰማቸው ከእንሰሳት የተሰዩ ናቸው። እንደ ሰው ሲጎዱ ወይም ሲጨነቁ ይሰማቸዋል። ስለሆነም ከሁለተኛው የፍጥረት ክፍል እንሰሳትን ወደ ሦስተኛ የፍጥረት ክፍል ሰው ወደ መሆን ማደግ የማይቻል ነው። በድጋሚ ደግሞ ይህ ሦስተኛው የፍጥረት ክፍል የተገኘው «እግዚአብሔር ፈጠረ» ከሚለው አስደናቂ ቃል ነው። ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ስለ ተፈጠረ በአፈጣጠሩ ከሌሎች ፍጥረታት ልዩ የሚያደርገው ግልጽ የሆነው ነገር እዚህ ላይ ነው። የእግዚአብሔር ቃል አስር ጊዜ እንዴት እግዚአብሔር ተክሎችንና እንስሳትን «እንደ ወገኑ» እንደፈጠረ ይገልጻል። (*ዘፍ. 1፡11፣12፣21፣24፣25*) የእግዚአብሔር ቃል ሰው በዚህ መንገድ መፈጠሩን አይናገርም። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል (ዘፍ. 1፡27) *«በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው»* ይህ ፍጹም የተሰየና ልዩ የሆነ ነገር ነው።

እዚህ ላይ አንድ ሰው በላቦራቶሪ በሳይንስ ምርምር ጥናት ከሚደረገው የእውነተኛ ሳይንስ የኢቮሉሽን ፍልስፍና የማይስማማ መሆኑን በግልጽ ለማየት ይችላል። የኢቮሉሽን ፍልስፍና /መላምት/ ሁሉን ለሚችለው ሰማይንና ምድርን ለፈጠረው የሚገባውን ክብር ለመስጠት የማይፈልግ ነው። አምላክ የለሽ የሆኑ ሰዎች (እግዚአብሔርን የማያምኑ) በእግዚአብሔር ከመፈጠራቸው ይልቅ ከጦጣ መገኘታቸውን ያምናሉ።

## የሰው የኃጢአት ውድቀትና ውጤቶቹ

የሰው ታሪክ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር በተፈጠረው በአዳም ይጀምራል። ከአዳም በፊት ሌላ ሰው በምድር ላይ አልነበረም። ሰው ሁሉ የመጣው ከአዳም ነው። ከማንኛውም ነገድ ወይም አገር እንምጣ ሁላችንም ከአዳም የመጣን ነን።

*ይህን እንዴት እናውቃለን?*

ሁላችንም ሟች በመሆናችን ከዚሁ እውነቱን ማየት እንችላለን:: የትም ቦታ የማይሞት ሰው ቢኖር ይህ ሰው ከአዳም ያልመጣ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ «ስለዚህ ምክንያት ኃጢዓት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢዓትም ሞት እንደዚሁም ሁሉ ኃጢዓትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ» በማለት ያስተምረናል (*ሮሜ.5:12*):: ከሰው ውድቀት በፊት ሞት በዓለም አልነበረም::

አዳም በተፈጠረበት ጊዜ ያለ ኃጢአት ነበር:: ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም በሆነና ከልካይ በሌለው ህብረት ይኖር ነበር:: በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ኃጢዓት አልነበረም:: አዳም ፍጹም ኃጢዓት በሌለበት ዓለም ውስጥ ይኖር ነበር:: በራሱ ኃጢዓት አልነበረበትም፣ እርሱ በጠቅላላ ኃጢዓት የለሽ ነበር:: ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ ሁለት ምዕራፎች በዘፍጥረት 1 እና 2 የተገለጸ ነው:: በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን ውድቀትና በሰው ላይ የሆኑትን አስፈሪ ውጤቶችን ይገልጻል:: አዳም በኃጢዓት ከወደቀ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት አልነበረውም:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከእርሱ የተገኙ ሁሉ በእርሱ መውደቅ ምክንያት ተበከሉ (ተመረዙ):: መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ከእናቱ ማህፀን ጀምሮ በኃጢዓት እንደተጸነሰና በኃጢዓት እንደተወለደ ይናገራል (*መዝ.(51):5*):: *«ሁሉም በድለዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል»* (*ሮሜ. 3:23*):: *«የኃጢአት ዋጋ ሞት ነው»* (ሮሜ. 6:23):: ሁላችን ከአዳም የተገኘን ስለሆነ ሁላችንም ሟቾች ነን:: ምክንያቱም በአዳም ውስጥ ነበርንና (*1ቆሮ.15:22*):: ይህ በአዳም ውስጥ ላሉት የሰው ዘር አስፈሪ እውነት ነው::

*እግዚአብሔር ሰውን ለምን ለፈተና ፈጠረው?*

1. እግዚአብሔር ሰውን ፈቃድ የሌለው ባሪያ፣ አሻንጉሊት ወይም የቼዝ መጫወቻ እንዲሆን አልፈለገም:: ከዚህ ይልቅ ሰውን በፈቃደኝነቱ የሚታዘዝና ከአምላኩ ጋር ፍጹም የሆነ ሕብረት እንዲኖረው ፈቅዶ ነበር::
2. እግዚአብሔር ህብረት የሚያደርገው ቅዱስ ከሆነው ፈቃዱ ጋር ህብረት ከሚያደርግ ሰው ጋር ብቻ ነው::
3. ሰው በተፈጥሮ ላይ መግዛት ይችል ዘንድ አስቀድሞ ለእግዚአብሔር ህግ መገዛት አስፈልጎት ነበር:: (መታዘዝን ያልተማረ በኋላ ትዕዛዝ መስጠትን አይችልም)
4. ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ስለሆነ በሆነው ፈቃድ፣ ሃሳብና ደስታ ስሜቶች ስላሉት ሊፈተን የሚችል ነው::





*የሰው ውድቀት እንዴት ሊመጣ ቻለ?*

የሰው ውድቀት «አትብላ» ካለው ከእግዚአብሔር ቃል ብቻ ሊመጣ የሚችል ነበር:: ከዚያ ሰይጣን ለሰው የሚከተሉትን ፍላጎቶች ሰጠው::

1. እግዚአብሔር የከለከለው እንዲኖራቸው፣
2. እግዚአብሔር ያልገለጸላቸውን እንዲያውቁ፣
3. እግዚአብሔር ያልፈቀደውን እንዲሆኑ::

*ሰይጣን ሰውን እንዴት ያጠምዳል?*

1. በሥጋው ፈቃድ «ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ አየች» (*ዘፍ.3:6*)
2. በነፍስ ፈቃድ «እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ» (*ዘፍ.3:5*)
3. በመንፈስ ፈቃድ «በውኑ እግዚአብሔር አዟልን ?» (*ዘፍ.3:1*)

*ሰይጣን እንዴት የእግዚአብሔርን እውነት እንዳይታዘዙ አደረገ?*

1. በእግዚአብሔር ቃል እንዲጠራጠሩ «በውኑ እግዚአብሔር አዟልን?»
2. ለእግዚአብሔር ቃል እንዳይታዘዙ «አትሞቱም»
3. ከእግዚአብሔር ቃል የራሱን (የሰይጣንን) ቃል በመተካት «እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ»

*ሰው ለሰይጣን ወጥመድ የሰጠው መልስ ምን ነበር?*

1. ሰው ሊፈተን በሚችልበት አደገኛ ቦታ ራሱን ሰጠ፣
2. ሰው ራሱን ከፈታኙ ጋር ለመወያየት ሰጠ፣
3. ሰው የእግዚአብሔርን የእውነት ቃል ከመጠበቅ ችላ አለ፣
4. ለፈታኙ የማታለል ቃል ሁለት ጆሮውን ከፈተ፣
5. ሰው እምነት ያለው እግዚአብሔር በፈጠራቸው ነገሮች እንጂ በእግዚአብሔር አይደለም፣
6. የእግዚአብሔርን ቃል መመሪያው አድረጎ መውሰዱ

*የሰው ውድቀት ውጤቶች*

1. ሰው በኃጢዓቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለየ፣
   «በዚህ ዓለም ያለ አምላክ ነበራችሁ» *ኤፌ.2:12 ኢሳ.59:2*
2. ሰው በኃጢአቱ ምክንያት የሰይጣን ተገዢ ሆነ፣

«ኃጢዓትን የሚያደርግ የኃጢዓት ባሪያ ነው።» (ዮሐ. 8:34፤ ቆላ.1:13፤ 2ጴጥ.2:19፤ ዮሐ. 8:44፤ የሐዋ.10:38፤ ዮሐ. 26:18)

3. በኃጢዓቱ ምክንያት ሰው ለሞት ተገዢ ሆነ።
«የኃጢዓት ዋጋ ሞት ነው።» (ሮሜ. 6:23፤ ዘፍ. 2:17)
   - *መንፈሳዊ ሞት፡- (ኤፌ.2:1፤ሉቃስ. 9:60፤ ሉቃ.15:23)*
   - *የስጋ ሞት፡- (ዕብ.9:27፤ 1ቆሮ.15:22፤ ሮሜ. 8:10)*
   - *የዘላለም ሞት፡- (ራዕ.20:6 እና ራዕ. 14፤21:8)*

4. ሰዎች ሁሉ ኃጢዓተኞች ስለሆኑ የሞት ተገዢዎች ናቸው። (ሮሜ 3:23 ፤ሮሜ 5:12-19፤ ሮሜ 6:23፤ 1ቆሮ. 15:21፤22 ፤ መዝ.(51):7

5. ኃጢዓት የሰውን ማህበራዊ ሥርዓት በአጠቃላይ አጥፍቶታል። ጥላቻ፣ ውሸት፣ ጦርነት፣ ሞት ጋብቻዎችን፣ ቤተሰቦችን፣ ሕብረተሰቡንና ሕዝቦችን በሙሉ እያሸነፈ ሔደ። ሰዎች በዚህች ምድር ላይ አንዱ ለሌላው መኖር ማለት ምን እንደሆነ ማወቅ አልቻለም። በፈንታው ግን እርስ በእርስ መቃረን ጀመሩ (ሮሜ.1:21-32፤ ገላ.5:19-21፤ 1ጢሞ.1:9-10)። እግዚአብሔር በኖህ ዘመን ማንኛውንም በጥፋት ውሃ የሚፈርድ ሆነ። ከኖህ ስምንቱ ቤተሰብ በስተቀር በሙሉ ኃጢዓት በክሎት ስለነበር እግዚአብሔር የሰውን ዘር በውሀ ለማጥፋት ፈረደ /ወሰነ/።

6. ኃጢዓት ከሰው ውጪ የሆኑትንም ፍጥረታት አጥፍቶአል። በአዳም ኃጢዓት በኩል የኃጢዓት እርግማን በጠቅላላው ተፈጥሮ ላይ በተክሎችና በእንስሳት ላይ መጥቷል (ዘፍ.3:17-19፤ ሮሜ.8:19-23)። እንስሳት እርስ በእርሳቸው የሚበላሉና የሚሞቱ ሆኑ። ተክሎች እንኳን የሚደርቁና የሚሞቱ ሆኑ ሞት ዓለምን ገዛ።

## የባቤል ግንብ

የሰው ዘር ለማይ ጠቀስ ከተሞችንና ግንቦችን ለመስራት በመነሳቱ የጥንቱ ታሪክ መደምደሚያው ላይ መጣ (ዘፍ.11:4)። አምላክ የለሽ የሆነው የሰው ዘር በራሱ ጉልበት ለማይን ለማወክ ያደረገው ሙከራ ነበር። ባቤል ማለት የአምላክ ደጅ /በር/ ማለት ነው /BAB-EL/ እግዚአብሔር ግን በፍርድ ጣልቃ ገባ። ተመልሰው ከተማቸውን እንዳይሰሩ ቋንቋቸውን በመደባለቅ በምድር ላይ






በተናቸው (ዘፍ.11:8)። ከዚያን ጊዜ በኋላ ባቤል የሚለው ትርጓሜ መደባለቅ (መዘበራረቅ) የሚል ሆነ (ዘፍ.11:9)።

*ከዘፍ.12* ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስ አዲስ ምዕራፉን ይጀምራል። በአብርሃም በኩል እግዚአብሔር ራሱን ለእሥራኤል ልጆች ሰጠ። ከዚህ በኋላ የዓለም ህዝቦች ከእሥራኤል ታሪክ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ ብቻ ነው የሚገኙት።

መጽሐፍ ቅዱስ ከዘፍ.*12* ጀምሮ እስከ *ሐሥ. 12* ድረስ 39 የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትና የማቴዎስ፣ የማርቆስ፣ የሉቃስና የዮሐንስ ወንጌሎች ከእሥራኤል ሕዝብ ጋር ያለው ግንኙነት ይናገራል። *ከሐሥ.13* ጀምሮ ወንጌል ወደ መላው የምድር ሕዝቦች መሄዱን ይናገራል። መንፈስ ቅዱስ ከወገን፣ ከቋንቋና ከነገዶች የክርስቶስ ኢየሱስን ቤት ክርስቲያን ይሰበስባል።




## 2. ቀዩ የደህንነት መሥመር
## የእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ከእስራኤል ጋር

### አጭር እይታ

ቀዩ መስመር በእግዚአብሔር የደህንነት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ እግዚአብሔር የእሥራኤልን ነገድ መዋጀቱን የሚያመለክት ነው:: ይህ መስመር ከ 2150 ከ.ክ.ል በፊት ይኖር የነበረውንና ከከለዳውያን ኡር በወጣው በአብርሃም ተአምራዊ ሥራ ይጀምራል:: አብርሃም የ100 ዓመት ሰው በነበረ ጊዜ በእግዚአብሔር ተዓምራዊ አሠራር «ይስሀቅ» ብሎ የጠራውን ልጁን ወለደ ይስሐቅ ደግሞ ያዕቆብን ወለደ:: እነዚህ ሦስቱ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ «የእምነት አባቶች» ተብለው ይጠራሉ:: እነርሱም ለእሥራኤል ነገድና ለደህንነት መገኘት ሥረ መሠረት ናቸው (*ሮሜ.11:16-20*):: እግዚአብሔር ከእነዚህ ሦስቱ የእምነት አባቶች የሚወለዱት ለእግዚአብሔር የተመረጠ ዘር እንደሚሆኑና እነርሱም አንድ ጊዜ እንደገና ለምድር ህዝቦች በረከት እንደሚሆኑ ማለላቸው (*ዘፍ.12:1-3፣ 22:15-18፣ 26:2፣28:12-15*)::

ያዕቆብ በኋላ ደግሞ እሥራኤል የተባለው (ዘፍ. 32:28) በጠቅላላው 12 ልጆች ነበሩት:: ሮቤል፣ ስምኦን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣ ዳን፣ ንፍታሌም፣ ጋድ፣ አሴር፣ ይሳኮር፣ ዛብሉን፣ ዮሴፍና ቢንያም ናቸው:: እነዚህ የ12 የእሥራኤል ነገዶች አባቶች ነበሩ::









በመቶ ሠላሳ ዓመቱ ያዕቆብ ከልጆቹ ጋር ወደ ግብጽ ወረደ:: በግብጻውያን ከመዋለድ እስኪታገዱ ድረስ ጭቆና ቢበዛባቸውም የእሥራኤል ህዝቦች እየበዙ ሄዱ (*ዘፀ.1:8*)::

በአጠቃላይ የእሥራኤል ህዝቦች በግብጽ ምድር ለ 430 ዓመታት ኖረዋል (*ዘፀ.12:40*):: ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ከግብጻውያን ባርነት ነፃ የሚያወጣቸውን ሙሴን ጠራው:: ለአርባ ዓመታት በምድረ በዳ ከተቅበዘበዙ በኋላ በመጨረሻ በኢያሱ መሪነት የተስፋይቱን ምድር መውረስ ችለዋል::

ከዚህ በኋላ በሳዖል በዳዊትና በሰሎሞን በመጀመር እሥራኤላውያን የነገሥታትን ዘመን ጀመሩ:: የእሥራኤል ነገዶች ከግብጽ ከወጡ ከ 480 ዓመታት በኋላ ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሠራና ለእግዚአብሔር ቀደሰው (*1ኛነገ.6:1*) :: ንጉሥ ሰሎሞን እግዚአብሔርን በጥሩ ሁኔታ እያመለከ ሳለ ባረጀ ጊዜ ከአህዛብ ወገን ያገባቸው ሚስቶቹ ልቡን ወደ ጣዖት አምልኮ አዘነበሉበት (*1ነገ.11:4*):: ከንጉሥ ሰሎሞን ሞት በኋላ አሥራ ሁለቱ የእሥራኤል ነገዶች፣ ሰሜኑ የእሥራኤል መንግሥትና የደቡቡ የይሁዳ መንግሥት በመባል በሁለት ተከፈሉ::

በ722 ክ.ል.በፊት ይሁዳና ቢኒያም ሲቀሩ የሰሜኑ አሥሩ የእሥራኤል ነገዶች በአሶራውያን እጅ ወደቁ:: ከ 606-586 እ.ኤ.አ. (ከክርስቶስ ልደት በፊት) ባለው ጊዜ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር የይሁዳንና የቢንያምን ነገዶች ወደ ባቢሎን ማረካቸው:: የሰሎሞን ቤተ መቅደስ በባቢሎናውያን ተደመሰሰ:: ቀጣዩን 600 ዓመታት የእሥራኤል ነገዶች በባቢሎናውያን፣ በሜዶንና በፋርስ፣ በግሪኮችና በመጨረሻም በሮማውያን አገዛዝ ሥር ሆኑ::



የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ መሲሁ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መጣ። እግዚአብሔር ግን በብሉይ ኪዳን በነቢያቱ እንደተናገረው መሲሁ የመዋጀት ሥራውን በኢየሩሣሌም ፈጸመ። እስራኤል ንጉሷንና መሲሁን ባታውቅም ክርስቶስ በኢየሩሳሌም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በመሞት ለደህንነት የሚሆን ሥራ ሰራ። በብሉይ ኪዳን ነቢያት እግዚአብሔር በእነርሱ በኩል እንደተናገረው ተከናወነ እስራኤል ጌታዋንና ንጉሷን ኢየሱስን አላወቀችም ነበር ከዚህም የተነሳ ሰቀሉት። ምክንያቱም «ይሁዳ» የመሰናከል ዓለት ሆነባቸው(*1ቆሮ.1:23)* የመስቀሉን ማዳን ተቃወሙ። በዚህም ምክንያት ለ1900 ዓመታት ያህል በዓለም ሕዝቦች መካከል ተበታተኑ ኢየሩሣሌምም በአሕዛብ ተረገጠች (*ሉቃ.21:24*)።

ይህም ቢሆን እሥራኤል አልጠፋችም። በምንም ነገር እግዚአብሔር ህዝቡን አልጣለም(*ሮሜ.11:1*)። *«እግዚአብሔር በፀጋው ስጦታና በመጥራቱ አይጸጸትምና»* (*ሮሜ.11:29)*። ካለፈው አንድ መቶ ዓመታት ጀምሮ እግዚአብሔር ህዝቡን ከዓለም አገሮች ይሰበስብ ጀመር። ከ118 ሀገሮች ወደ ቅድስት ምድር ተመለሱ። ግንቦት 14 ቀን 1948 ዓ.ም. የዛሬዋ የእሥራኤል መንግስት ተመሠረተች። ያልተሟሉና የተደባለቁም ቢሆኑም እንኳን 12ቱ ነገዶች ወደ ቅድስት ምድር ተመልሰዋል። ከየትኛው ነገድ እንደ ሆኑ ማንም አያውቅም። ከሌዊ ነገድ መምጣታቸውንና የዳዊት ቤተሰብ መሆናቸውን የሚያውቁት ካህናቱና ሌዋውያኑ ብቻ ናቸው። አሁንም ቢሆን የአይሁዳውያን ወደ አባቶቻቸው ምድር መመለስ ያሰማቋረጥ እየቀጠለ ነው።

እሥራኤል ሕያው ተዓምር ናት፡ እሥራኤል ለ 4000 ዓመታት በቀሩት በዓለም ነገዶች የተጠላች በጦርም የተወጋችና በከፊልም የተደመሰሰች ነገድ ብትሆንም በፍጹም አልጠፋችም። በአሁኑ ጊዜ በተቃራኒው እንደ እሥራኤል ነገድ የዓለምን ሕዝብ ትኩረት የሳበ በምድር ላይ ሌላ ህዝብ አይገኝም።

ከእስራኤል ህዝብ ጋር ያሰው የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ያበቃ አይደለም። አንድ ቀን እሥራኤል መሲኋን ወደፊት ታውቀዋለች። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «በኃይልና በብዙ ክብር ሲመጣ የወጉት ያዩታል» (*ማቴ.24:30፤ ዘካ.12:10)* ይላል። የተሰቀለውን በማየት ንስሐ ይገቡና ይድናሉ ፣የኃጢዓታቸውን ሥርየት ያገኙና መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ (*ዘካ.12:10-14*)፡ ቀዩ የመዋጀት መስመር የተዋጀው የእሥራኤል ሕዝብ በሺው ዓመት መንግስት ታሪክ ውስጥ ታላቅ ሕዝብ እንደሚሆኑ ያሳያል። በዚህ መንግስት የእግዚአብሔር ልጅ የነገሥታት ንጉስ በመሆን ዓለምን በሞላው ለሺህ ዓመት ይገዛል። (*ራዕ.20:1-10፤ ኢሣ.11:1-10)* በዚህ በመሲሁ መንግሥት ዘመን መላው እሥራኤል ለሌላው የዓለም ህዝብ ሚሲዮናውያን /የወንጌል መልዕክተኞች/ ይሆናሉ። (ዘካ. 8:13፣23፤ ኢሳ. 9:1-6) በሺሁ ዓመት መጨረሻ የእሥራኤል ቀይ የማዳን መስመር ወደ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ያመራል (ራዕ.21:1)። የአሥራ ሁለቱ የእሥራኤል ነገዶች አባቶች ስሞች በተዋቡት በሰማያዊቱ ኢየሩሣሌም በሮች ላይ የተጻፉ ናቸው (ራዕ.21:12)። የተዋጀው የእሥራኤል ነገድ ለዘላለም በሰማይ ይሆናል።





## የእሥራኤል ነገድ ምንነት

### እሥራኤል – ብቸኛና ታላቅ መለኮታዊ ራዕይ የተሰጣት

*«እንግዲህ የአይሁድ ብልጫ ምንድር ነው? ወይስ የመገረዝ ጥቅሙ ምንድነው? በሁሉ ነገር ብዙ ነው። አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃላት አደራ ተሰጡአቸው» (ሮሜ.3:1-2) ::*

እግዚአብሔር ከእሥራኤል ሕዝብ ጋር ያደረገው የመዳን ታሪክ በ39ኙ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍት የተገለጠ ነው። ጠቅላላውን ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን ከእስራኤል ሕዝብ በሆኑት ዕብራውያን የተጻፉ ናቸው። ለምሳሌ ሉቃስ አንዱ ፀሐፊ ነው። ሉቃስ በደም ዕብራዊ አይደለም ሉቃስ ከአንጾኪያ የሆነ ግሪካዊ ዶክተር የጳውሎስ ተማሪና በእርሱ ሥልጣን ስር የጻፈ ነበር። ሉቃስ ብቻ አንዱን ወንጌልና (የሉቃስ ወንጌል) የሐዋርያት ሥራን መጽሐፍት ጻፈ። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ራሱን ለእሥራኤል ብቻ መግለጹን ይናገራል።

*«ቃሉን ለያዕቆብ፣ ሥርዓቱንና ፍርዱን ለእሥራኤል ይናገራል ለሌሎች አሕዛብ ሁሉ እንዲህ አላደረገም፣ ፍርዱንም አልገለጠላቸውም ሃሌሉያ» (መዝ.(147) ፣19፣20)::*

እግዚአብሔር ራሱን ለአህዛብ አልገለጠም፣ ነገር ግን ለተመረጡት ለእርሱ ለራሱ ሕዝብ ገለጠ። መጽሐፍ ቅዱስ የመጣው ከእሥራኤል ነው። ስለሆነም እሥራኤል ብቻ ናት ታላቅ መለኮታዊ ራዕይ ያላት።


### እሥራኤል፣ ብቸኛዋ የደህንነት ህዝብ በዓለም ውስጥ

ከዓለም ፍጥረት በፊት እግዚአብሔር ልጁን ወደዚህ ዓለም ለመላክ ወሰነ (*1ጴጥ.1:19-20*)፡ ስለዚህም ምክንያት ነበር በብሉይ ኪዳን ዘመን ለራሱ የሆነ ህዝብ የመረጠው። ይህ ሕዝብ ለእግዚአብሔር «የካህናት መንግሥትና ቅዱስ ሕዝብ» እንዲሆን ታቅዶ ነበር (ዘፀ.19:6)። ከሌላው ሕዝብ ጋር ሳይደባለቁ /በጋብቻ/ በደም ሀረጋቸው ንጹህ ሆነው እንዲኖሩ የተፈለጉ ነበሩ። በዚያን ዘመን ሌሎቹ ሕዝቦች ጣዖታትንና ሰይጣንን ያመልኩ ነበር። በምንም ነገር እስራኤል ሰይጣንን ያመልኩ ነበር። (*1ቆሮ.10:20)*። በፍጹም በምንም ምክንያት ከእንደዚህ ካለ ርኩሰት ጋር በጥፋት ርኩሰት እንዲተባበሩ አልተፈቀደም ነበር። ስለዚህም እግዚአብሔር ህግን፣ የአምልኮ ሥርዓትንና ተስፋን ሰጣቸው። የእሥራኤል ህዝብ የእግዚአብሔር ልጅ /ሥጋ ሆኖ/ የሚገለጥበት ነገድ እንዲሆን የተለየ ነበር።

በዓለም ዓይን እሥራኤል ሁልጊዜ ታላቅ ምስጢር ሆና የምትኖር ናት፡፡ ብዙ ሰዎች በእሥራኤል ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ሲኖራቸው ሌሎች ደግሞ በተለየ መንገድ ይወድዷታል፡፡ እኛም ከእነዚህ ከሁለቱ በአንዱ ውስጥ እንገኛለን፡፡ እኛ እሥራኤልን እንወዳለን ምክንያቱም አዳኛችን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ከዚህ ነገድ መሆኑን ስለምናውቅ ነው፡፡ የጎልጎታ መስቀል የተተከለው በእሥራኤል ነው፡፡ አዳኙ የማዳን ሥራውን ከኢየሩሣሌም ከተማ ውጪ ፈጸመ፡፡ ስለዚህም መስቀሉ የሚገኘው በቀዩ የመዋጀት መስመር መካከል ነው፡፡ ቀዩ መስመር የፈሰሰውን የጌታችንን ደም ያሳስበናል፡፡ ኢየሩሣሌም የዓለም መዳን መካከለኛ ሥፍራ ናት፡፡ የዓለም መድሃኒት ክርስቶስ ስለሚመጣበት መንገድ ሲወስን እግዚአብሔር እሥራኤልን ብቻ መረጠ፡፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ «መዳን ከአይሁድ ነውና» ስለሚል ነው (***ዮሐ.4:22***)፡ እሥራኤል ብቻ መዳን የሚገኝባትና የደህንነት ተሸካሚ ናት፡፡ መሲሁ ብቻ የመዳን ዋነኛ ነጥብ ነው፡፡ እሥራኤል የተመረጠችበት ዋነኛ ምክንያት የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ሆኖ ስለሚመጣባት ነበር፡፡ ይህ ህዝብ በዚህ ምድር ላይ ሌላ የተለየ መለያ የለውም (ሮሜ. 9:4-5)፡፡

## የሚመጣው መሲህ በእሥራኤል የማዳን ታሪክ ውስጥ ዓለምን የሚያድን ተስፋ መስጠት

እግዚአብሔር ለእርሱ ከተመረጡት ህዝብ ጋር ለአራት ሺህ ዓመታት ይናገር ነበር፡፡ እሥራኤል የሚለው ቃል የሁለት ቃል ጥምር ነው ትርጓሜው «እግዚአብሔር ይዋጋል» ማለት ነው፡፡ ትርጉሙም «እግዚአብሔር ጦርነትን እንደሚመራ» የሚገልፅ ነው፡፡ እግዚአብሔር የጠፋውን የሰው ዘር ከኃጢአት፣ ከሞትና ከሰይጣን ለማዳን ይዋጋል፡፡ ይህ ጦርነት /ውጊያ/ በኤደን ገነት አስደንጋጭ ከሆነው ከሰው ውድቀት የጀመረ ነው፡፡ እግዚአብሔር «በቀደመው እባብ» በሰይጣን ላይ *«በአንተና በሴቲቱ መካከል፣ በዘረህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፡፡ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ»* በሚል ቃል በማለት ጦርነትን አወጀ *(ዘፍ.3:15)*፡፡








ይህ ኃይለኛ ቃል የጥንቱ ወንጌልና የጥንቱ ተስፋ ነው፡፡ ስለ አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስና በጎልጎታ መስቀል ላይ ስለ ተፈጸመው የመዋጀት ሥራ ይናገራል፡፡*«የእግዚአብሔር ልጅ የሰይጣንን ሥራ ሊያፈርስ»* መጥቷል (*1ዮሐ.3:8*)፡ እግዚአብሔር የጠፋውን ሰው ለማዳን ሰው መሆን አስፈለገው *(ማቴ.18:11)* *በዘፍ.3:15* ስለሚመጣው መሲህ የተሰጠው የጥንቱ ተስፋ «ተቀዳሚ ተስፋ» በመባል ይታወቃል፡፡ በመዋጀት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ገፅ 44 ላይ ተመልከት ይህን የሚመጣው ተስፋ የሚያመለክተው ቀይ መስመር ከአዳም ይጀምርና በሴትና በኖህ በኩል በማለፍ ወደ አብርሃም ያመራል፡፡ ይህን ክፍል ከአዳም እስከ አብርሃም ያለውን ጊዜ «ሰውር የሆነው የእግዚአብሔር የመዋጀት ታሪክ» ልንለው እንችላለን፡፡ ስውር የሆነበት ምክንያት ስለሚመጣው ደህንነት ተስፋ ብቻ ስለሚገልፅ ነው፡፡

## ለአብርሃም የተሰጡት ሦስት ጣምራ ተስፋዎች

### አንድ ምድር፣ አንድ ነገድ፣ አንድ በረከት

በዘፍ.12 ያለው የአብርሃም መጠራት ከእሥራኤል ህዝብ ጋር ያለውን የእግዚአብሔርን የማዳን ታሪክ ይጀምራል፡፡ ታሪኩም የዚህ ነገድ አባት በሆነው በአብርሃም የእግዚአብሔርን የማዳን ታሪክ ይጀምራል፡፡ የዚህ ነገድ አባት ለሆነው፣ ለአብርሃም ሦስት ጣምራ ታላላቅ ተስፋዎችን ሲሰጠው መረጠው፡፡

*«እግዚአብሔር አብርሃምን አለው ከአገርህ ከዘመዶችህም፣ ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ፡፡ ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፣ እባርክሃለሁ፣ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፣ የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ» (ዘፍ.12:1-3)፡፡*

### 1. ምድረ - እሥራኤል

እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ የገባለት ምድር የእሥራኤልን ምድር ነው፡፡ እንደ ሕዝቅኤል ትንቢት *«በምድር መካከል በተቀመጠ ህዝብ ናትና»* ***(ሕዝ38:12)*** ፡፡ ትልቁ ሀገር ሲባኖስ እስራኤልን በሰሜን ያዋስናል ትልቁ ተራራማ የሲና ሰላጤ ደግሞ በደቡብ ያዋስናል የሜዲትራኒያን ባህር በምዕራብ በኩል ሲገኝ የዮርዳኖስ ወንዝ ከእሥራኤል በሰተምሥራቅ በኩል ይፈስሳል፡፡ እሥራኤል 28,186 ስክዌር ኪሎ ሜትር ስፋት ያላት ትንሽ ሀገር ናት፡፡ ቢሆንም ይህች አገር ለእኛ በጣም አስፈላጊ ናት፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ በምድር በነበረበት ጊዜ የኖረው እዚህ ነው፡፡ እዚህ ነው ቃል ሥጋ የሆነው፡፡

በዚህች በተረገመች ምድር የተመላለሰውና የዘለዓለሙን የመዋጀት ሥራ በጎልጎታ መስቀል ላይ የፈጸመው በእሥራኤል ምድር ነው። የእሥራኤል ምድር ለዚህ ዓለም ደህንነትና ለዘለዓለም ደህንነታችን የመከናወን መሠረትና ድልድይ ሆነች። ለዓለም ደህንነት መካከለኛ በመሆን የተፈጸመው የማዳን ሥራ ወደ ዓለም አገሮች የሚሰፉና በነገዶች መካከል የሚታወጅ ሆነ። እዚህ በቤተልሔም የዳዊት ዘር በሆነችው በማሪያም በኩል በኃጢዓተኛ ሥጋ ምሳሌ እንደ እኛ ሰው ሆኖ መጣ (*ሮሜ.8:3-4*)። ዘለዓለማዊው ራሱን ዝቅ በማድረግ የባሪያን መልክ ያዘ (*ፊል.2:5-11*)። ለመጀመሪያዎቹ ሰላሳ ዓመታት ያልታወቀ አናጺ ሆኖ በናዝሬት ኖረ። ከዚህ በኋላ እንደ መሲህና ንጉሥ ሆኖ በመታየት ቅፍርናሆምን የአገልግሎት መሠረት ለማድረግ መረጠ። ይህ ዝነኛ ቦታ የምቾት መንደር ተብሎ ይጠራል (የቃሉ ፍቺ ቅፍር መንደር ሲሆን ናሆም ደግሞ ምቾት ማለት ነው) የበረከት ተራራ ከቅፍርናሆም በላይ የሚገኝ ነው። እዚህ ንጉሡ ስምንቱን በረከቶችና የተራራውን ስብከት የሰማይን መንግስት በምድር ላይ አወጀ። በእሥራኤል ምድር ጌታ ኢየሱስ የተራቡትን በመመገብ፣ ድውያንን በመፈወስ፣ አጋንንትን በማውጣት፣ ሙታንን በማስነሳትና የገሊላን ባህር ማዕበል ፀጥ በማድረግ ታምራቱን ሁሉ አደረገ። እዚህ በእሥራኤል ምድር በመስቀል ላይ ሞተ፣ የከበረ ደሙ ፈሰሰ፣ እዚሁ ሞትን ድል አደረገና ከዚህ ወደ ሰማይ አረገ። በዚሁ በእሥራኤል ምድር ውስጥ ባለችው በኢየሩሣሌም እንደገና ይመጣል። እግሮቹ በደብረዘይት ተራራ ላይ ይቆማሉ። (*ሐሥ.1:9-11፣ ዘካ.14:4*)

## 2. የእግዚአብሔር ህዝብ - እስራኤል

እግዚአብሔር ለአብርሃም ታላቅ ሕዝብ እንደሚሰጠው ተስፋ ሰጠው። እግዚአብሔር ህዝቡን እንደ ባህር አሸዋና እንደ ሰማይ ከዋክብት ማብዛቱ ማለት ሳይሆን የእግዚአብሔር የማዳኑን ሥራ ስፋት የሚያመለክት ነው (ዘፍ. 22:17)። እግዚአብሔር ህዝቡ ጥቂት እንደሆነ ራሱ ያውቃልና (*ዘዳ.7:7-8*)። እግዚአብሔር የጠፋውን የሰው ዘር ከኃጢዓትና ከሞት ለማዳን ሲያደርግ የሚቻለውን አጅግ ታልቅ የሆነውን ነገር አደረገ። የኃጢዓት መሥዋዕት እንዲሆን ልጁን ላከው (*ሮሜ.8:3*)። የዓለሙ መድሃኒት በእስራኤል ህዝብ መካከል ሰው ሆነ። የእግዚአብሔር ልጅ በዕብራዊቷ ድንግል ሴት ሥጋ በኩል ወደዚህ ዓለም ገባ።





ከአይሁድ ነገድ የሆነ እውነተኛ ዕብራዊ ነበር። ሰዓሊዎች እንደሚስሉት (የሐሰት ሥዕል) ረጅም ነጣ ያለ ፀጉር ያለው ጀርመናዊ አይደለም። እርሱ ከእስራኤል ነገድ የመጣ ጥቁር ፀጉርና ጥቁር ዓይን ያለው ነበር። እርሱ በማሪያም በኩል ከዳዊት ቤተሰብና ቤት የመጣ ነው (*ሮሜ.1:3፤ 2ጢሞ.2:8*)። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእሥራኤል ነገድ የሆነ እውነተኛ እሥራኤላዊ ልጅ ነው በመስቀል ላይ ስለ ኃጢዓታችን ያፈሰሰው ደሙ የዕብራዊ ደም ነው። ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ ነገድ ስለመጣ እኛም እንደ እግዚአብሔር ልጆች ይህን የእሥራኤልን ነገድ እንወዳለን። ስለ ኢየሱስ ብቻ እሥራኤልን እንወድዳለን። በሌላ በኩል ደግሞ አምላክ-የለሽ የሆኑት ህዝቦች እግዚአብሔርንና ልጁን እንደሚጠሉ የእሥራኤልንም ህዝብ በጣም ይጠላሉ።.

## 3. በረከቱ – በኢየሱስ ክርስቶስ

በሦስተኛ አብርሃም በምድር ላይ በእርሱ በኩል /ፍጥረት ሁሉ/ የሚባረኩበትን ተስፋ ተቀበለ። ይህ በረከት ፍፁም ሰው የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እግዚአብሔር በእርሱ በኩል በሰማያዊ በረከቶች ሁሉ ባረከን (*ኤፌ.1:3*)። አዳም በኃጢዓት በመውደቁ ምክንያት ሰማያዊ በረከቶችን በከፊል አጣን። እርግማን፣ በረከቶችን ማጣትና ሞት በሰው ዘር ላይ ያደረሰው በኃጢዓት ምክንያት ነው። የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ እርግማናችንና ማንኛውም ብልሽትና መጥፋትን በመስቀል ላይ ተሸከመ። ስለ ኃጢዓታችን ሞተ በከበረ ደሙ አነፃንና ዘለዓለማዊ ፀጋውንና ፍቅሩን ሰጠን። በሰማያዊ በረከቶች ሁሉ ባረከን። የክርስቶስ አማኞች በመሆናችን ከእርግማኖች ነጻ የወጣንና በአምላካዊ በረከቶች ሁሉ የተባረክን ነን። በክርስቶስ ሁሉ ነገር አለን። እርሱ ብቻ በህይወትና በሞት መጽናኛችን ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያስን ብቻኛና ሁሉ በሁሉ የሆነ መመኪያችን ነው። እርሱ ካለን ከሰማይና ከምድር የምንጠይቀው ሌላ ምንም ነገር የለንም ሁሉ አለንና።

### ኢየሩሣሌም:- «የታላቁ ንጉሥ ከተማ»

ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሣሌም በእሥራኤል ምድር እምብርት የምትገኝ ናት። ጎልጎታ የመዳን ታሪካዊ መለያ ስለሆነ ብቻ አይደለም። ኢየሩሣሌም ታላቅ ከተማ የሆነችው ፣ በእግዚአብሔር የማዳን እቅድ የተለየ ቦታ ስላላት ነው።
*«መሠረቶቹ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው፣ ከያዕቆብ ድንኳኖች ይልቅ እግዚአብሔር የጽዮንን ደጆች ይወድዳቸዋል። የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ በአንቺ የተከበረ ነገር ይባላል» (መዝ.(87):1-3)* ።

ኢየሩሣሌም የእሥራኤል ህዝብ ዋና ከተማ ብቻ አይደለችም። ነገር ግን በምድር ላይ የእግዚአብሔር ዋና ከተማ ናት። በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ ኢየሩሣሌምን «የታላቁ ንጉሥ ከተማ» በማለት ገልጿታል (*ማቴ.5:35፤ መዝ. 48:2)* በተቃራኒ ደግሞ ባቤል በዚህ ምድር ላይ የሰይጣን ዋና ከተማ ናት። በግሪክኛው ቋንቋ ይህች ከተማ ባቢሎን ትባላለች። የባቤል ከተማ በዘፍ.11 እና በዳንኤልም ከምዕ.1-12 የተገለጠች ናት። የእግዚአብሔር ጠላቶችና እምላክ የለሽነት የተሞላው የሰው ዘር የተሰበሰበበት ከተማ ናት። በዚህም ምክንያት ባቤል ለብዙ ሺህ ዓመታት ኢየሩሳሌምን ስትወጋ ነበር። ይህም በባቤልና በኢየሩሣሌም መካከል ያለ መንፈሳዊ ተጋድሎ ነው። የዓለም ህዝቦች በእሥራኤል ላይ የፖለቲካ ውጊያ የማድረግንም ውጤት አስከትሏል።

*ኢየሩሳሌም« የታለቁ ንጉሥ ከተማ » የሚለውን ስያሜ እንዴት ልታገኝ ቻለች*

*መ*ልሱን በብሉይ ኪዳን በዘፍጥረት *መ*ጽሐፍ ውስጥ እናገኘዋለን። አብርሃም ካህንና ንጉሥ የሆነውን መልከጼዴቅን በተገናኘው ጊዜ በመጀመሪያ እዚያ ተጠቅሳ ትገኛለች።

*«የሳሌም ንጉሰ መልከ ጼዴቅም እንጀራንና የወይን ጠጅን አወጣ፣ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር። ባረከውም፣ አብርሃም ለማይንና ምድርን ለሚገዛ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው አለውም አብርሃምም ከሁሉ እሥራትን ለጠው» (ዘፍ.14:18-20)።*

ኢየሩሳሌም እዚህ ባጭሩ «ሳሌም» በሚል ትታያለች። ይህ አጭር አጠራር በመዝሙር እንደገናም *በዕብ.7:1-2* ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል።

*«እግዚእብሔር በይሁዳ ታወቀ። ስሙም በእሥራኤል ታላቅ ነው። ሥፍራው በሣሌም ማደሪያውም በጽዮን ነው» (መዝ.(76):1-2)።*

የመጨረሻው ቁጥር ሳሌም ኢየሩሳሌም ማለት እንደሆነ በቀጥታ ያመስከታል። እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም የሚያድር ንጉስ ከሆነ *(መዝ.76:2) እግዚእብሔር ለዘለዓለም ይነግሳል (መዝ. (10):16)።* ኢየሩሳሌም እንደ ብሉይ ኪዳን ምስክርነት «የታላቁ ንጉሥ ከተማ» ናት(*መዝ.(48):2)*።

ከዚህ እልፍ በማለት አንድ ምዕራፍ ልንራመድ ይገባናል። ከኢየሩሳሌም ከወጣው ካህናዊ ንጉሥ ወደ ሆነው ወደ መልከ ጻዴቅ ትኩረታችንን ስለሚስበን (ዘፍ.14:18) ቁልፍ የሆነ አስፈላጊ ጥቅስ ነው። ስለ እርሱ በበለጠ ልንመረምር ይገባናል።





*መልከ ጻዴቅ ማን ነበር?*

መልከ ጻዴቅ የሚለው ስም «መልከ» እና «ፀደቀ» የተባሉት ሁለት የዕብራውያን ቃላት ጥምር ነው። መልከ ማለት ንጉሥ ሲሆን ዘዴቅ (ጻዴቅ) ደግሞ ጽድቅ ማለት ነው። ስለሆነም መልከ ጻዴቅ ማለት የጽድቅ ንጉሥ ማለት ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ይህ የጽድቅ ንጉሥ በተመሳሳይ የሳሌም ንጉሥ ነው «ሳሌም» የሚለው ስም ሲተረጎም ሠላም ከሆነ መልከ ጻዴቅ ደግሞ የሰላም ንጉሥ ነው የሚለውን ያሰገኛል (*ዕብ.7:2)*። እንደ ልዑል እግዚአብሔር ካህን አብርሃም ኮሎዶጎምርንና ነገሥታትን ወግቶ ሲመለስ አብርሃምን ሊገናኘውና ሊባርከው ወጣ። አብርሃምን በተገናኘው ጊዜ እንጀራና የወይን ጠጅ አመጣ (*ዘፍ.14:18)*።

*መልከ ጼዴቅ ለአብርሃም እንጀራውንና የወይን ጠጁን ለምን አመጣ?*

የዚህን ምስጢር ግልጽ ልናደርገው ይገባናል። ያለበለዚያ ከኢየሩሣሌም ጋር ያለውን የእግዚአብሔርን ታሪክ ልንረዳ አንችልም። በዕብራውያን መልዕክት ስለዚህ ሰው ስለ መልከ ጼዴቅ *«አባትና እናት የትውልድ ቁጥር የሉትም፣ ለዘመኑ ጥንት ለሕይወቱ ፍጻሜ የለውም፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል»* በማለት ተገልጿል (*ዕብ.7:3)*። እንደዚህ ያለውን ገለጻ ሊያሟላ የሚችል ሌላ ሰው የለም ሁላችንም አባትና እናት የሕይወት ጅማሬና ፍጻሜ አለን። ነገር ግን መልከ ጼዴቅ:-

*«በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል»* (ዕብ.7:3)።

ይህ አስደናቂ ነገር ነው። መልከ ጼዴቅ በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሏል። በምሳሌነቱ የእግዚአብሔርን ልጅ ከመሰለ ከእርሱ ጋር እኩል ነው የጽድቅ ንጉሥ፣ የሠላም ንጉሥ ፣ ለህይወቱ ጥንትና ፍጻሜ የሌለው ካህን ሆኖ ለዘላለም ይኖራል። ስለዚህም ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው ከመልከ ጼዴቅ በኋላ እርሱን መስሎ የሚገኘው ምክንያቱም እርሱ ብቻ በእውነት

- «የጽድቅ ንጉሥ» *(1ቆሮ. 1:30)*
- «የሠላም ንጉሥ» *(ኤፌ. 2:14)*
- «ዘላለማዊ አምላክ» *(ራዕ. 1:18)*
- «ዘላለማዊ ሊቀ ካህናት» *(መዝ.(110):4)* ሆኗል።

እሁን መልከ ጼዴቅ እንጀራና የወይን ጠጅ ስለምን እንዳመጣ እንረዳለን። ይህ ጌታ ኢየሱስ ከ2000 ዓመታት በፊት በስቅለቱ ዋዜማ የመጨረሻውን ፋሲካ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ባከበረበት ጊዜ:-

*«ሲበሉ ኢየሱስ እንጀራን አንስቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀመዛሙርት ሰጠና እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ:: ጽዋውንም አንስቶ አመስግኖም ሰጣቸው:: እንዲህም አለ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ:: ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው») (ማቴ.26:26-28)::*

ብሎ በመስጠቱ መልከ ጼዴቃዊ ትንቢትን አሟላ:: ልክ እንደ መልከ ጼዴቅ የእግዚአብሔር ልጅ የጎልጎታው የመዋጀት ምሳሌ የሆነውን እንጀራና የወይን ጠጅ ለማምጣት ከኢየሩሳሌም መጣ ስጋዬ ስለእናንተ የተቆረሰው ደሜ ስለእናንተ የፈሰሰው በማለት የሰጠው ማለት ነው::

ዩኔ ሥጋ - ስለናንተ የተቆረሰው

ዩኔ ደም - ስለእናንተ የፈሰሰው

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ከመልበሱ ከ 2000 ዓመታት በፊት በክህነታዊ ንጉሥ ሽፋን ተገልጦ አብርሃምን ባረከው:: አብርሃም የእሥራኤል አባት እንደመሆኑ መጠን ይህን በረከት ለእስራኤል ህዝብ አስተላለፈ:: ስለዚህ ነው አስገራሚ የሆነው የደህንነት ታሪክ ከኢየሩሳሌም የጀመረው:: ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ እውነተኛው የእግዚአብሔር ልጅ «በዘላለማዊ ክህነት እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት» *(ዕብ.7:17)* ኃጢአታችንና ውርደታችንን በመውሰድ የእግዚአብሔር በግ በመሆን በጎልጎታ መስቀል ላይ መከራ ተቀበለ *(ዮሐ.1:29)*:: እንደ ነገሥታት ንጉሥና እንደ የጌቶች ጌታ *(ራዕ.19:16)* ለጠፋው የሰው ዘር ተዋጋና «ተፈጸመ» *(ዮሐ.19:30)* በሚለው ቃል የመዋጀትን ሥራ ፈጸመ::

የሚቀጥለው ንጽጽር የመልከ ጼዴቅን ፍቺ የበለጠ ያጠነክረዋል::

| | | |
|---|---|---|
| መልከ ጼዴቅ | — | ኢየሱስ ክርስቶስ |
| አብርሃም | — | የእሥራኤል ህዝብ |
| ሳሌም | — | ኢየሩሣሌም |
| እንጀራ | — | ሥጋው |
| ወይን | — | ደሙ |
| ዘለዓለማዊ የጽድቅ የሠላም ንጉሥ | — | ዘለዓለማዊ የጽድቅና የሠላም ንጉስ |





## የመሲሁ መምጣት

*«ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከህግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፣ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከህግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ» (ገላ.4:4-5)::*

እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ሰው እንዲሆን በፈቀደ ጊዜ ይህችን ዓለም በከፍተኛ ደረጃ ከፍ ማድረጉና መባረኩ ነበር:: በአዲስ ኪዳን «የሰው ልጅ» የሚለው ቃል ሰማንያ ሰባት ጊዜ ተጠቅሷል:: ጌታ ኢየሱስም ራሱን ለመግለጽ ይህን አነጋገር ተጠቅሞታል:: ስለ ክርስቶስ ማንነት እንዲህ እናነባለን::

*ፍጹም አምላክ ነው::*

*ከአምላክ የተወለደ አምላክ፣ ካልተፈጠረው ብርሃን ብርሃን የሆነ፣ ፍጹም ሰው ሆነ፣ ለሰ ሰው ልጆች በጎነት ሲል አምላክ ሰው ሆነ::*

ከዳዊት ዘር ተወላጅ የሆነችው ድንግል ማሪያም የእግዚአብሔር ልጅ የሚመጣበት መንገድ ሆና ተመረጠች:: በብሉይ ኪዳን እንደነበረችው እንደ ሙሴ እህት ስሟ «ማናያም ነበር» (*ዘኁ.26:59*) በግሪክኛ ቋንቋ ይህ ስም ማሪያም /MARI - YAM/ በመባል ይጠራል በኋላም እኛ ሜሪ እያልን የምንጠራው ስም ሆነ::

ድንግል ማርያም ለእግዚአብሔር የተባረከች ዕቃ ሆና ተመረጠች:: ሉቃስ እንደጻፈው የእግዚአብሔር ባርያ ብላ ራሷን ጠርታለች (*ሉቃ.1:38*):: በብሉይ ኪዳን ትንቢት እንደተነገረው ትንቢት የእግዚአብሔር ልጅ በእርሷም በኩል ወደ ተረገመችው ምድር ሰው ሆኖ በቤተልሔም ተወለደ::

*«አንቺ ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ:- አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ:: ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ በእሥራኤል ላይ ገዢ የሚሆን ይወጣልኛል» (ሚል.5:2)::*

ዘለዓለማዊው የእግዚአብሔር ልጅ ወደዚህ ዓለም የመጣው የአባቱን ፈቃድ ለማድረግ እንጂ ለሌላ አልመጣም::

*«መስዋዕትንና መባን አልወደድህም፣ ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ፣ በሙሉ በሚቃጠል መስዋዕትና ስለ ኃጢዓት በሚሰዋ መሥዋዕት ደስ አላለህም:: በዚያን ጊዜ እነሆ በመጽሐፍ ጥቅልል ስለ እኔ እንደ ተጻፈ አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ አልሁ» (ዕብ.10:5-7)::*

የክርስቶስ ሰው መሆንን ከሌላው ልዩ የሚያደርገው ምድራዊ እናት ስትኖረው ምድራዊ አባት አለመኖሩ ነው:: እግዚአብሔር አብ ራሱ አባቱ ነበር:: በዚህ ምክንያት ነበር «የልዑል ልጅ» የተባለውና ጴጥሮስም «የሕያው እግዚአብሔር ልጅ» መሆኑን የተገነዘበው (*ሉቃ.1:1-32፤ ማቴ.16:16-17*):: ልደቱ ፍጹም የአምላካዊ ባህርይ ነበር:: ነገር ግን ሰው በመሆኑ እውነተኛ ዕብራዊ ነበር እናቱ ከዳዊት ንጉሣዊ ቤተሰብ የሆነች ዕብራዊት ነበረች፣ የዕብራውያን ደም ነበራት፣ በዕብራውያን ህዝብ መካከል መለያ የሆነው ጥቁር ዓይኖችና ጥቁር ፀጉር ነበራት:: አንዳንድ ሰዓሊዎች እንደሚስሉት የእግዚአብሔር ልጅ ሰማያዊ አይኖች ወይም የተደበላለቁ ፀጉርና የሰፋ ትከሻ አልነበረውም:: ይህ የብዙ ሰዓሊዎች ግምት ይሆናል ነገር ግን ትክክል አይደለም:: እንደዚህ ያሉ ሥዕሎች ፍጹም ግምታዊና ሐሰትም ናቸው::

*ይህን እንዴት እናውቃለን?*

በ1ኛ ቆሮንቶስ

*«ወንድ ጠጉሩን ቢያስረዝም ነውር እንዲሆንበት ተፈጥሮ እንኳን እያስተምራችሁምን?» በማለት ጳውሎስ ጽፏል:: (1ቆሮ.11:14)*

ስለዚህም ለወንድ ልጅ አጭር ፀጉር ሲኖረው ለእርሱ ክብር ነው:: ዛሬም ቢሆን በእሥራኤል ሃይማኖተኛ የሆኑ አይሁዶች ይህን ይገነዘባሉ:: ወንዶች ረጅም ጢም ሲኖራቸው አጭር ፀጉር አላቸው:: አዳኛችን በሥጋ ዕብራዊ፣ ከይሁዳ ነገድና የዳዊት ልጅ (ማቴ.1:1) ስለሆነ ጥቁር ዓይኖችና አጭር ጥቁር ፀጉር ነበረው::

## ያመሲሁ ተቀባይነትን ማጣት (መጣል)

ኢየሱስም ሲያስተምር ሲጀምር እድሜው ሰላሳ ዓመት ያህል ነበር:: (ሉቃ 3:23) ጌታ ኢየሱስ በእሥራኤል ምድር መሲህ ሆኖ የተገለጸው በምድራዊ ሕይወቱ መጨረሻ ላይ ነበር:: የመጀመሪያዎቹን ሠላሳ ዓመታት ያሳለፈው የዛብሎን ግዛት ክፍል በነበረችው በናዝሬት ከተማ ነበር:: ከዚህ በኋላ በምድር ላይ ለሶስት ዓመት ተኩል በሕዝብ መካከል ተመላለሰ:: *«ኢየሱስም ሊያስተምር ሲጀምር ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ሆኖት ነበር»* (*ሉቃ.3:23*):: ወደ ጠፉት ወደ እሥራኤል ቤት በጎች በመሔድ ንስሐ ይገቡ ዘንድ (ማቴ. 15:24) *«መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ንስሀ ግቡ»* (ማቴ.4:17) በማለት ወደ ንስሐ ጠራቸው:: በሽተኞችን ፈወሰ *(ማቴ.14:14)* ፣ ሙታንን አስነሳ (*ማቴ.11:5*)፣ አጋንንትን አስወጣ *(ማር.1:34)*፣ የተራቡትንም መገበ (*ማቴ.15:32-37*):: በእነዚህ ሁሉ የሰማይ አባቱን ፈቃድ አደረገ *(ዮሐ.10:37-38)* ነገር ግን እሥራኤላውያን አላወቁትም ነበር::





*እሥራኤል መሲኋን ያላወቀችው ለምን ነበር ?*

ለዚህ መልስ የምናገኘው ከነቢዩ ከኢሳያስ መጽሐፍ ውስጥ ነው:: የህዝቡ ልብ ደንዳና እንደነበር ነቢዩ ጽፏል (*ኢሣ.6:9-10*):: እስራኤል ለብዙ መቶ ዓመታት በጣዖት አምልኮት ተውጣ ነበር:: በሙሴ ዘመን እንኳን በወርቁ ጥጃ ዙሪያ ጨፍረዋል (*ዘፀ.32:4-6*):: በመሳፍንት ዘመን ጣዖታትን ተከትለው አምልከዋል (*መሳ.2:11-12*):: ንጉሥ ሰሎሞን ሚስቶቹን ለማስደሰት የእሥራኤልን ህዝብ ወደ ጣኦት አምልኮ መራቸው (*1ነገ.11:4-10*):: እሥራኤል በባቢሎናውያን ተማርከው እስከተወሰዱ ድረስ በዚሁ ሁኔታ ነበሩ:: በእንደዚህ ባለ ርኩሰት መቆየት የሰውን ልብን ያደነድናል ንስሐ የማይገባ ያደርገዋል ጣዖትን የሚያመልክ ያደርገዋል:: በእርግጥም የሚያመልከው ሰይጣንን ነው (*1ቆሮ.10:20*)::

በመጨረሻም መሲሁ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ የእርሱ የሆኑት ህዝቦቹም አላወቁትም:: ዮሐንስ «ወደ ወገኖቹም መጣ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም» በማለት ጽፏል (*ዮሐ.1:11*):: *ንጉሥ* ለሆነው ለእርሱ በእንግዶች ማደሪያ ስፍራ አልተገኘለትም ነበር (ሉቃ.2:7):: *«የሰው ልጅ ራሱን የሚያስጠጋበት ቦታ የለውም»* በማለት ለደቀ መዛሙርቱ ተናግሮአቸዋል (ማቴ.8:20):: በዚህ ሁሉ ውስጥ *«የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየሰበከ»* (ሉቃ. 8:1):: በየሥፍራው እየሄደ ከእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» «በእግዚአብሔር እመኑ፣ በእኔም ደግሞ እመኑ» እያለ በመደጋገም ለአይሁዶች ያስተምር ነበር (*ዮሐ.14:6-1*):: ቢሆንም በእርሱ ያመኑት «ታናሽ መንጋዎች» ነበሩ(*ሉቃ.12:32*):: የአብዛኛው ህዝብ ልብ እንደደነደነ ቀረ (ማቴ.13:15):: የሚያሳዝነው እስከ አሁን ድረስ ምንም ለውጥ አለመሆኑ ነው:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ እቅዳቸው ሁሉ እርሱን ለማጥፋት ሆነ:: *«ፈሪሳውያንም እንዴት አድርገው እንደሚያጠፉት ሸንጎ አደረጉ»* (*ማቴ.12:14*) የከፍተኛ ሸንጎ አባላትም ህይወቱን ለማጥፋት አደሙ (*ዮሐ.11:53*):: ጌታ ኢየሱስ በመደጋገም ወደ አብ የሚሄድበት መንገድ ይህ እንደነበረ ለደቀ መዛሙርቱ ነግሯቸው ነበር::

*«የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል በሽማግሌዎች፣ በካህናት አለቆችም በጻፎችም ሊጠላ፣ ሊገደልም፣ በሦስተኛውም ቀን ሊነሳ ይገባዋል» በማለት ተናግሯቸዋል (ሉቃ.9:22፤ ሉቃ. 9:44-45፤ ሉቃ. 18:31-34)*:: ነገር ግን አስቀድሞ የተናገራቸው ሁኔታ እስኪፈጸም ድረስ ደቀመዛሙርቱ አላስተዋሉም ነበር::

*«የሚወጣበትም ወራት በቀረበ ጊዜ ወደ ኢየሩሣሌም ለመሔድ ፊቱን አቀና» (ሉቃ.9:51)::*

በህዝብ ፊት ያሰው ምድራዊ ህይወቱ በኢየሩሣሌም የሚያበቃ ነበር። አባቱ የሰጠውንም ሥራ ለመፈጸም /ለመጨረስ/ ፈቃደኛ ነበር። (*ዮሐ.4:34*)

### ጌቴሴማኒ

ጌታ ኢየሱስ የመጨረሻ የምድራዊ ህይወቱን ምሽት በጌቴሴማኒ ከደቀመዛሙርቱ ጋር አሳለፈ። በዚያ ስለ ኃጢአታችን ከውስጥ በሆነ ስቃይ በታማኝነት ተሰቃየ። ላቡ በምድር ላይ እንደ ደም ነጠብጣብ ወረደ (*ሉቃ.22:44*)። ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የሆነው ያስቆሮቱ ይሁዳ ወደ ካህናት አለቆች ሔደና ካደው። ወዲያውኑ የካህንት አለቆች ኢየሱስን ያዙትና አሰሩት። በዚህም ደቀ መዛሙርቱ ብቻውን ትተውት ሸሹ (*ማቴ.26:56*)። የካህናት አለቆችና የሸንጎው አባሎች እርሱን ለመግደል የሐሰት ምስክሮች ለመፈለግ ወደ ተሰበሰቡበት ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ቤተ መንግሥት አመጡት (*ማቴ.26:59*)። በምንም ነገር ጥፋተኛ ሆኖ ስላልተገኘ በመጨረሻ ከእርሱ ምክንያትን ለመፈለግ ሊቀ ካህናቱ ጌታን እንዲናገረው ገፋፋው «አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ የሆንህ እንደሆነ እንድትነግረን በህያው እግዚአብሔር አስምንሃለሁ አለው» ኢየሱስም

*«አንተ አልህ፣ ነገር ግን እላችኋለሁ ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ፣ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ» አለው። «በዚያን ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ልብሱን ቀድዶ ተሳድቦአል። ከእንግዲህ ወዲህ ምስክሮች ስለ ምን ያስፈልጋል? እነሆ ስድቡን አሁን ሰምታችኋል፣ ምን ይመስላችኋል?» አለ (ማቴ.26:63-65) ።*

ሊቀ ካህናቱ ልብሱን እንዲቀድድ አልተፈቀደለትም ነበር። እግዚአብሔር ይህን በግልጽ ከልክሎ ነበር (*ዘሌ.21:10*)፡ ስለሆነም ሊቀ ካህናቱ ያደረገው የተከለከለውን ነበር። ሊቀ ካህናቱ በእግዚአብሔር የተቀባና ቅዱስ የቅባት ዘይት የፈሰሰበት ነበር። (*ዘሌ.21:10*) ሊቀ ካህናቱ ቀያፋ ልብሱን በመቅደዱ በአጠቃላይ በብሉይ ኪዳን ያለው የአሮንን ክህነት ሥርዓት በምሳሌ ማፍረሱን ነበር። ብቸኛ፣ እውነተኛና ዘላለማዊ ሊቀ ካህናት በሆነው በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ አንጻር ቆሞ ነበር ይህን ያደረገው (*መዝ.(110):4፤ ዕብ.5:5-10*)።

### ገ በ ታ

ከሊቀ ካህናት ከቀያፋ ፊት የእግዚአብሔርን ልጅ ወደ ግቢ /ፕራይቶሪዮን/ ወሰዱት (*ዮሐ. 18:28*) ይህን ስፍራ የገዢው ግቢ ይሰዋል። ፕራይቶሪዮን በዚያን ጊዜ የይሁዳ ገዢ እንዲሆን በሮሙ ንጉስ በጢበርዮስ የተሾመው የጲላጦስ መኖሪያ





ነበር። የሮም ንጉሥ የምድር ንጉሥ ነበር። ይህ የሮም ንጉሥ በየቀኑ የጁፒተርን ጣዖት በማምለክ ሰይጣንን ያመልክ ነበር። እንደዚሁም ደግሞ እርሱ በሚገዛው ግዛት ሁሉ የበላይ ገዢ በመደረግ ይመለክ ነበር። በግሪኩ የኢኩሜኒ መልካም አምላክ የዚህ ገዢ የበታች እንደራሴ በመሆን ጴንጤናዊው ጌታ ኢየሱስን በሚከተለው መንገድ መመርመር ጀመረ።

*«የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን?» አለው። ኢየሱብም መልሶ መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም አለው ጲላጦስም እንግዲህ ንጉሥ ነህን? አለው። ኢየሱስም መልሶ እኔ ንጉስ እንደሆንሁ አንተ ትላለህ። እኔ ለእውነት ልመሠክር ተወልጃለሁ። ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምጼን ይሰማል አለው» (ዮሐ.18:33፣ 36፣ 37)።*

ያ የሥልጣን ወቅት ነበር። ምክንያቱም በሮማውያን ገዢ ፊት ከላይ የሆነው ሰማያዊ ንጉሥ በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ ሆኖ ሲታይ በሌላ በኩል ደግሞ ከታች የሆነው የሰይጣንን መንግሥት የሮምን መንግሥት የወከለው ጴንጤናዊው ጲላጦስ ይታያል። በውጪ ደግሞ የእሥራኤል ህዝብ ሊቀ ካህናት ውሳኔ እንዲደረግ እየጠየቁ ይጠባበቁ ነበር። ጌታ ኢየሱስን ባዩት ቁጥር «ስቀለው ስቀለው እያሉ ይጮሁ ነበር» (*ዮሐ. 19:6*)። ጲላጦስ ሦስት ጊዜ «በደል አላገኘሁበትም» ብሎ ስለ እርሱ ቢመሠክርም ሊሰሙት አልፈለጉም ነበር (*ሉቃ.23:4፣14፣22፤ ዮሐ.18:38፣ 19:4-6*)። ከዚህ በኋላ ጲላጦስን እጅግ አጽንተው «ስቀለው፣ ስቀለው፡ ከሚለው ጩኸታቸው ጋር እንዲተባበሩ ህዝቡን አነሳሱና አደፋፈሯቸው። ጌታ ኢየሱስን ወደ ውጪ አውጥቶላቸው «እነሆ ሰውየው» አላቸው (*ዮሐ.19:5*)። ጲላጦስ ግን ከፊቱ የቆመው ማን እንደሆነ ተገንዝቦ ነበር። እርሱ ከብዙ ወንጀለኞችና ነፍሰ ገዳዮች ፊት ሰፊት የቆመ ነበር። ክርስቶስ ግን ያለ ኃጢዓትና የተለየ ፍፁም ሰው ነበር። ይህ ሰው እውነተኛው የእግዚአብሔር ልጅ ነበር። ጲላጦስ በፍርሃት ተሞልቶ ሊፈታው ፈልጎ ሳለ አይሁድ «ይህንንስ ብትፈታው የቄሣር ወዳጅ አይደለህም» ብለው ጮኹ (*ዮሐ.19:12*)። «የሮም ንጉሥ የቄሣር ወዳጅ» /አሚኩስ ሴሳሪስ-AMICUS CAESARIS/ የሚሰውን ማዕረግ ሰጥቂት ከፍተኛ ማዕረግ ላላቸው የሚሰጣቸው ስለነበር በዚህ «ማዕረግ» ጲላጦስን በከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ከተቱት። ጲላጦስም የሮም ንጉሥ የክላውዲያ ፕሮኩላን የመጀመሪያ ልጅ የሆነችውን ቀላውዲያ ፕሮኩላንን አግብቶ ስለነበር ይህ ማዕረግ ተሰጥቶት ነበር። ይህች ሴት በማቴዎስ ወንጌል «ስለ እርሱ ዛሬ በህልም እጅግ መከራ ተቀብያለሁ በዚያ ፃዲቅ ሰው ምንም አታድርግ» ያለችው ሴት እንደሆነች

ይታወቃል (*ማቴ.27:19*)፡፡ እርሱም ለማስጠንቀቂያው ዋጋ ሳይሰጥና ተወዳጅነቱን እንዳያጣ ያለው ሥልጣን ለሚቀጥለውም ርምጃ ተገዢ አደረገው፡፡

*«ኢየሱስን ወደ ውጪ አስወጣው፡፡ በዕብራይስጥም ገበታ በተባለ ለቁስ በሚሉት ሥፍራ በፍርድ ወንበር ተቀመጠ፡፡ ለፋሲካም የማዘጋጀት ቀን ነበር፣ ስድስት ሰዓትም የሚያህል ነበር፡፡ አይሁድንም «እነሆ ንጉሣችሁ አላቸው፡፡ እነርሱ ግን «አስወግደው፣ አስወግደው፣ ስቀለው» እያሉ ጮኹ፡፡ ጲላጦስም «ንጉሣችሁን ልስቀለውን?» ብሎ ሲጠይቃቸው የካህናት አለቆችም «ከቄሳር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም» ብለው መለሱለት (ዮሐ.19:13-15)፡፡*

በሮማውያን መንግሥት ንጉሥን መስቀል የማይታሰብ ሲሆን ወንጀለኞች ግን ይሰቀሉ ነበር፡፡ የተማረኩ ነገሥታት እንኳን በሮማውያን ህግ አንገታቸው ይቆረጥ ነበር እንጂ አይሰቀሉም ነበር፡፡ የሮም ዜግነት ያለው ደግሞ በዚህ መንገድ አይገደልም ነበር፡፡ በተለይም ሴቶች በዚህ መንገድ አይገደሉም ነበር፡፡ ምክንያቱም ሮማውያን ባህል አክባሪ ዜጎች ስለነበሩ ነው፡፡ አይሁድ «ስቀለው» እያሉ በከፍተኛ ጩኸት በመጮሃቸው ምርመራውም ከፍተኛ ደረጃ በመድረሱ ጲላጦበ በሐዘን «ንጉሣችሁን ልስቀለውን ?» ብሎ ጮኸ ሊቀ ካህናትም *«ከቄሳር በቀር ንጉሥ የለምን» ብለው መለሱለት (ዮሐ.19:15)*

ይህ የመደምደሚያ ውሳኔ እሥራኤል ያስቸበትን አደገኛ ሁኔታ ይገልፁ ነበር። ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ልጅ ለራሳቸው ውሳኔ እንዳያደርጉ ይገፋፋሉ፡፡ እርሱን መምረጥ ወይም መቃወም እንጂ ሌላ መካከለኛ አማራጭ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ጌታ *«ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል» በማለቱ ነው (ማቴ.12:30)፡፡*

ይህ አባባል ለእሥራኤል የላይኛውን ንጉሥ መቃወም የታችኛውን ምድራዊ ንጉሥ መምረጥ ማለት ነው፡፡ የታችኛው መንግሥት ራሱ ሰይጣን ነው፡፡

*እሥራኤል ንጉሥ የሌላት ለምንድን ነው?*

መልሱን የምናገኘው አስቸጋሪ ከሆነው ከዚህ ሕዝብ ታሪክ ነው፡፡ እሥራኤል ለእግዚአብሔር የተመረጠ ህዝብ ቢሆኑም ለብዙ መቶ ዓመታት ጣዖታትን ማምለክ የተለማመዱና «መልካም ባልሆነው በራሳቸው መንገድ የሚሄዱ አመጸኛ ህዝቦች ነበሩ» (*ኢሣ.65:2*)፡፡ እነዚህ ህዝቦች ራሳቸውን ለጣዖት አምልኮ በመበጠታቸው እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ያስቆጡት ነበር (*ኢሣ.65:3*)፡፡ ጳውሎስ ስለ እሥራኤል ህዝብ በሮሜ መልዕክት *«ለእግዚአብሔር ቀናተኛ እነደ ሆኑ ስለ እነርሱ · መመስከር እችላለሁና ቅናታቸው ግን ከዕውቀት የተነሳ አይደለም፡፡*





*ከእግዚአብሔር የሚመጣውን ጽድቅ ስላላወቁና የራሳቸውን ጽድቅ ለመመሥረት ስለ ፈለጉ፣ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም» (ሮሜ.10:2-3)* በማለት ጽፏል፡፡ ኃጢዓት አሳውሯቸው ነበር ውጤቱም«ንጉሥ የለንም» የሚል ነበር፡፡ ይህ ከፍተኛ ው አደገኛ ነጥብ ነበር እሥራኤል ንጉሥ ነበራት፣ በእግዚአብሔር ልጅ በጌታ ኢየሱስ ይህ ንጉሥ በአይናቸው ፊት ቆሞ ነበር፡፡ እሥራኤል በጣዖት አምልኮ ስለተጠመደችና በሰይጣን ኃይል የተያዙና ህዝቡም ንስሐ የማይገቡና የታወሩ ስለነበሩ ንጉሣቸውንና መሲሃቸውን ለማወቅ አልቻሉም ነበር፡፡ ስለዚህ የሊቀ ካህናቱ ውሳኔ መሐል ሰፋሪነት የሌለው ነበር፡፡ «ከቄሣር በቀር ንጉሥ የለንም» የሚለው ለእግዚአብሔር «አይደለም» ለሰይጣን «አዎን» ማለት ነበር፡፡ ስለዚህ ምክንያት ነበር አዳኙ «እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁና የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ እርሱ ከመጀመሪያ ነፍስ ገዳይ ነበር» ያላቸው (*ዮሐ.8:44*)፡፡

ምርመራው ወደ ፍጻሜ ደረሰ፡፡ አይሁድም ጲላጦስ ላይ ብዙ ጫና አደረጉ፣ ጩኸታቸውም የሚያውክ ሆነ (*ሉቃ.23:23*)፡፡ በመጨረሻም ጲላጦስ ለህዝቡ ጫና ራሱን አስገዝቶ ኢየሱስን እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው፡፡ (*ዮሐ.19:16*)

## ጎ ል ጎ ታ

*«ኢየሱስንም ይዘው ወሰዱት፣ መስቀሉንም ተሸክሞ በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደ ተባለው የራስ ቅል ሥፍራ ወደሚሉት ወጣ፡፡ በዚያም ሰቀሉት፡፡ ከእርሱም ጋር ሌሎች ሁለት አንዱን በዚህ አንዱን በዚያ አድርገው ኢየሱስንም በመካከላቸው በማድረግ ሰቀሉት» (ዮሐ.19:17-18)፡፡*

እሥራኤል መሲኋን ካደች እንደ ማንኛውም ወንጀለኛ በሁለት ነፍስ ገዳዮች መካከል ተሰቀለ፡፡ ሆኖም የእሥራኤል ንጉሥ መሆኑን የቀየረው ምንም ነገር አልነበረም እርሱ ለዘለዓለም ንጉሥ ሆኖ ይኖራል፡፡ ስለሆነም ጲላጦስ በዕብራይስጥ በሮማይስጥና በግሪክ ማንነቱን የሚያስታውቅ ጽሀፈት በመስቀሉ ላይ ሰቀለ፡፡ ቃሉም

«የአይሁድ ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ» የሚል ሲሆን

*በብሔራዊ ቋንቋቸው በዕብራይስጥ*

«ጄሹዋ ሀ ኖዛሪ ሜልኬ ሀ ጂሁዲም»»

*በሮማውያን ብሔራዊ ቋንቋቸው*

«ጂሱስ ናዝሪኑስ ዴክስ ኢሽዳኢሩም»

*በግሪክ ብሔራዊ ቋንቋ ደግሞ*

«ኢየሱስ ሆ ናዝራዮስ ሆ ባሲሊዮስ ቶን አይሁዳዮን» የሚል ነበር::

የአይሁድ ንጉስ ስለ ኃጢዓታችን ለመሞት ወደ ዓለም የሚመጣው የዓለም መድሃኒትና የእግዚአብሔር ልጅ ነው:: እርሱም *«ለሞት ይኸውም ለመስቀል ሞት እንኳን ለሰማይ አባቱ የሚታዘዝ ሆነ» (ፊል.2:8)*: ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ የእባቡን ራስ ቀጠቀጠ *(ዘፍ.3:15)*: በጎልጎታ በመስቀል ላይ ኃጢዓትንና ሞትን አሸነፈ:: ኃጢዓተኞች የሚድኑበትን ብቸኛ ሁኔታ ፈጠረ::

እግዚአብሔር የደህንነት ታሪክ ሁልጊዜ ዘለዓለማዊነትን የሚናገር ነው *(ዕብ.9:12)*: የእሥራኤል ህዝብ የፈለጉትና በተስፋ የጠበቁት ከሮማውያን ባርነት ነፃ የሚያወጣቸውን ምድራዊ መሲህና ደህንነት ነበር::

ወንድም ሆነ ሴት ከውስጥ የሰይጣን ባሪያ ሆነው ዘለዓለማዊ ሠላም ቢኖራቸው ምን መልካምነት አለው? እሥራኤልም ብትሆን ያለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መዳን አይቻላትም:: እርግጥ ነው እግዚአብሔር የመዋጀት ዕቅዱን በራሱ ህዝብ በኩል ተጠቅሟል:: በእነርሱ በኩል ልጁ ሰው ሆኖ እንዲመጣና የመዋጀት ስራውን በምድር እንዲፈጽም አድርጓል:: ነገር ግን ለእሥራኤል መንግስት ሰማይ ለመግባት የኋላ በር ወይም የተለየ በር የላቸውም «በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» የሚለው ጥቅስ ማንኛውንም ሰውና የተመረጡትን የእሥራኤል ዘር እንኳን ሳይቀር የሚመለከት ነው *(ዮሐ.14:6)*::

መሲኋን በመቃወሟ ከእሥራኤል ጋር ያለው የእግዚአብሔር የመዋጀት ስራ ለጥቂት ጊዜ ተቋረጠ:: «ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ» (ማር.1:15) ብሎ ጥሪ ለሰጠው ለመሲሁ ጥሪ የእግዚአብሔር ህዝብ የሰጡት ምላሽ ንጉሳቸውን መስቀል ነበር:: በመዋጀት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ቀይ መስመር ከክርስቶስ ስቅለት በኋላ ዝቅ እያለ መሄዱ ይታያል:: ነገር ግን ይህ ማለት የእግዚአብሔር የደህንነት ታሪክ በዚህ አበቃ ማለት አይደለም:: እሥራኤል በክርስቶስ የሆነውን ደህንነት ብትቃወምም ደህንነት ከእሥራኤል ውጪ ላሉት ህዝቦች የሚሰበክ ሆነ:: ለ2 ሺህ ዓመታት ይህ በመላው ዓለም እስከ አሁን እየተካሄደ ነው በዚህ ሁኔታ ነው ወንጌል ወደ አውሮፓም የደረሰው:: ስለዚህ ጌታችንን ልናወድሰውና ልናመሰግነው ይገባናል::

ከዘፍ.12 እስከ ሐሥ.12 ድረስ ስለ ልጁ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲል እግዚአብሔር በተለይ ከእሥራኤል ምድርና ህዝብ ጋር በተያያዘ የመዋጀትን ታሪክ እንደሠራ ይታያል:: ከሐሥ.13 ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስ በሐዋርያው ጳውሎስ ጉዞዎች ወንጌል እስከ ምድር ዳር ድረስ ለአህዛብ መሰበኩን ያሳያል (ሐሥ.1:8):: የእሥራኤል ህዝቦች በምድራዊ ገዢ ተወሰዱና ከእግዚአብሔር የመዋጀት ታሪክ ወደ ጎን ተተዉ::





## 3. አረንጓዴው የመዋጀት መሥመር


# የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን

### አጭር እይታ

በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ውስጥ ሦስተኛው ክፍል (ህዝብ) የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ናት:: ይህ ክፍል በደህንነት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ሰፊ በሆነ አረንጓዴ መስመር የተመለከተው ነው::

በሁለተኛውና በሦስተኛው ምዕተ ዓመት ይኖሩ የነበሩት የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ቤተ ክርስቲያንን እንደ ሦስተኛ ትውልድ አድርገው ለይመዋት ነበር:: እነዚህ ሦስቱ ክፍሎች አህዛብ በአብርሃም መመረጥ በኩል የመጡት የእሥራኤል ህዝብ አይሁድና በመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የሆኑት ክርስቲያኖች ናቸው:: እነዚህ ሦስቱ የህዝብ ክፍሎች ዛሬም በዓለም ውስጥ ይገኛሉ::

*«እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ»* የሚለውን አረንጓዴው መሥመር በምንመረምርበት ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከምድር ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ መንፈስ ቅዱስ መምጣቱን ተመልክተናል::



*በግሪክ ብሔራዊ ቋንቋ ደግሞ*
«ኢየሱስ ሆ ናዝራዮስ ሆ ባሲሊዮስ ቶን አይሁዳዮን» የሚል ነበር::

የአይሁድ ንጉስ ስለ ኃጢዓታችን ለመሞት ወደ ዓለም የሚመጣው የዓለም መድሃኒትና የእግዚአብሔር ልጅ ነው:: እርሱም *«ለሞት ይኸውም ለመስቀል ሞት እንኳን ለሰማይ አባቱ የሚታዘዝ ሆነ» (ፊል.2:8)*፡ ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ የእባቡን ራስ ቀጠቀጠ *(ዘፍ.3:15)*፡ በጎልጎታ በመስቀል ላይ ኃጢዓትንና ሞትን አሸነፈ:: ኃጢዓተኞች የሚድኑበትን ብቸኛ ሁኔታ ፈጠረ::

እግዚአብሔር የደህንነት ታሪክ ሁልጊዜ ዘለዓለማዊነትን የሚናገር ነው *(ዕብ.9:12)*፡ የእሥራኤል ህዝብ የፈስጉትና በተስፋ የጠበቁት ክሮማውያን ባርነት ነፃ የሚያወጣቸውን ምድራዊ መሲህና ደህንነት ነበር::

ወንድም ሆነ ሴት ከውስጥ የሰይጣን ባሪያ ሆነው ዘለዓለማዊ ሠላም ቢኖራቸው ምን መልካምነት አለው? እሥራኤልም ብትሆን ያለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መዳን አይቻላትም:: እርግጥ ነው እግዚአብሔር የመዋጀት ዕቅዱን በራሱ ህዝብ በኩል ተጠቅሟል:: በእነርሱ በኩል ልጁ ሰው ሆኖ እንዲመጣና የመዋጀት ስራውን በምድር እንዲፈጽም አድርጓል:: ነገር ግን ለእሥራኤል መንግስት ሰማይ ለመግባት የኋላ በር ወይም የተለየ በር የላቸውም «በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» የሚለው ጥቅስ ማንኛውንም ሰውና የተመረጡትን የእሥራኤል ዘር እንኳን ሳይቀር የሚመለከት ነው *(ዮሐ.14:6)*::

መሲኋን በመቃወሟ ከእሥራኤል ጋር ያለው የእግዚአብሔር የመዋጀት ስራ ለጥቂት ጊዜ ተቋረጠ:: «ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ» (ማር.1:15) ብሎ ጥሪ ለሰጠው ለመሲሁ ጥሪ የእግዚአብሔር ህዝብ የሰጡት ምላሽ ንጉሳቸውን መስቀል ነበር:: በመዋጀት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ቀይ መስመር ከክርስቶስ ስቅለት በኋላ ዝቅ እያለ መሄዱ ይታያል:: ነገር ግን ይህ ማለት የእግዚአብሔር የደህንነት ታሪክ በዚህ አበቃ ማለት አይደለም:: እሥራኤል በክርስቶስ የሆነውን ደህንነት ብትቃወምም ደህንነት ከእሥራኤል ውጪ ላሉት ህዝቦች የሚሰበክ ሆነ:: ለ2 ሺህ ዓመታት ይህ በመላው ዓለም እስከ አሁን እየተካሄደ ነው በዚህ ሁኔታ ነው ወንጌል ወደ አውሮፓም የደረሰው:: ስለዚህ ጌታችንን ልናወድሰውና ልናመስግነው ይገባናል::

ከዘፍ.12 እስከ ሐሥ.12 ድረስ ስለ ልጁ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲል እግዚአብሔር በተለይ ከእሥራኤል ምድርና ህዝብ ጋር በተያያዘ የመዋጀትን ታሪክ እንደሠራ ይታያል:: ከሐሥ.13 ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስ በሐዋርያው ጳውሎስ ጉዞዎች ወንጌል እስከ ምድር ዳር ድረስ ለአህዛብ መስበኩን ያሳያል (ሐሥ.1:8):: የእሥራኤል ህዝቦች በምድራዊ ገዢ ተወሰዱና ከእግዚአብሔር የመዋጀት ታሪክ ወደ ጎን ተተዉ::





## 3. አረንጓዴው የመዋጀት መሥመር

## የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን

### አጭር እይታ

በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ውስጥ ሦስተኛው ክፍል (ህዝብ) የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ናት:: ይህ ክፍል በደህንነት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ሰፊ በሆነ አረንጓዴ መስመር የተመለከተው ነው::

በሁለተኛውና በሦስተኛው ምዕተ ዓመት ይኖሩ የነበሩት የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ቤተ ክርስቲያንን እንደ ሦስተኛ ትውልድ አድርገው ይመዋት ነበር:: እነዚህ ሦስቱ ክፍሎች አህዛብ በአብርሃም መመረጥ በኩል የመጡት የእሥራኤል ህዝብ አይሁድና በመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የሆኑት ክርስቲያኖች ናቸው:: እነዚህ ሦስቱ የህዝብ ክፍሎች ዛሬም በዓለም ውስጥ ይገኛሉ::

«እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ» የሚለውን አረንጓዴው መሥመር በምንመረምርበት ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከምድር ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ መንፈስ ቅዱስ መምጣቱን ተመልክተናል::



ይህ የሆነው በበዓለ ሃምሳ /ጴንጤቆስጤ/ ዕለት በኢየሩሳሌም ነበር:: (*የሐሥ.2:1-3)* ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበት ዕለት ነበር:: ከዚህ እለት ጀምሮ የእግዚአብሔር መልዕክተኞች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በዓለም ዙሪያ በያለበት ወንጌልን ለመስበክ ወጡ:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በእግዚአብሔር ቃል ስብከት በኩል እጅግ ብዙ ለዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ጀመሩ:: ከ2000 ዓመታት ጀምሮ ወንጌል አሸናፊ ሆነ:: ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ እውነተኛ መለወጥ ባገኘ ቁጥር የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን እያደገች ትሄዳለች:: እኛ አሁን ያለነው በአህዛብ ዘመን /በአህዛብ ቤተ ክርስቲያን ዘመን/ ውስጥ ነው::

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ዳግም የተወለዱትን አማኞች ያቀፈች አካል ናት:: ለጠፋው ኃጢዓተኛ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ዳግም ልደት መቅደም አስፈላጊው ነገር ነው:: ለዚህ ነው ዩሐንስ ሐዋርያው

*«ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ አይችልም»* በማለት የፃፈው (*ዮሐ.3:33 ከዮሐ.3:5 )ጋር አስተያይ::*

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ዳግም የተወለዱት አማኞች የመጡት ከአህዛብ ወይም ከአይሁድ ነው:: በጌታ ክርስቶስ ኢየሱስ እምነታቸውን ያደረጉት ሰዎች ከአህዛብ ብቻ ሳይሆን ከእሥራኤልም ህዝብ ጭምር ናቸው:: በሉቃስ የተጻፈው የሐዋሪያት ሥራ ከሌሎች የአዲስ ኪዳን 21 መልእክቶች ጋር ለኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የተለዩ ጽሑፎች ናቸው:: እነዚህ መፃሕፍት ከክርስቶስ ኢየሱስ የመዋጀት ስራ በተጨማሪ አማኙ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስላለው ግብረ ገባዊ ኑሮና አምልኮ ያመለክታሉ:: እነዚህ መፅሐፍት ደግሞ እያንዳንዱ አማኝ ወንድም ሆነ ሴት ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በግል ስላላቸው ጉዞ ያስተምራሉ::

የቤተ ክርስቲያን ዘመን የተወሰነ ነው:: ወደ ፍጻሜው የሚደርሰው ጌታ ዳግም የተወለዱትን አማኞች ከምድር ወደ ሰማያዊ ክብር መጥቶ በሚነጥቅበትና በሚወስዳት ጊዜ ነው በራሱ ደም የገዛት ሃብቱ ናትና:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እውነተኛ አማኞች ከጌታ ጋር ለዘላለም ይኖራሉ (*1ተሰ.4:17*):: በአረንጓዴው የመዋጀት መሥመር መጨረሻ ላይ ያለው የጥያቄ ምልክት የመነጠቅን ጊዜ የሚያመለክት ነው:: መነጠቅ የሚሆንበትን ትክክለኛ ቀን መናገር የማይቻል ነው::





## የቤተክርስቲያን ዘመን

### 1. ዓለም አቀፍ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን

በአዲስ ኪዳን ስለ ቤተ ክርስቲያን 100 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል:: በመጀመሪያው በግሪኩ ትርጉም «ኤክሊሺያ» «*ተጠርተው የወጡ*» የሚለው ቃል ቤተ ክርስቲያንን ለመግለጽ ሐዋርያት /የመፅሐፍ ቅዱስ ደራሲያን/ የተጠቀሙበት ቃል ነበር:: አዲስ ኪዳን ይህን ቃል ከጠፋውና በኃጢዓት ከተሞላው ዓለም ተጠርተው የወጡ በጌታ ኢየሱስ ያመኑትን ለማመልከት ተጠቅሞበታል:: «የእምነታችን ጀማሪና ፈፃሚ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ የመጡ ናቸው» (*ዕብ.12:2*)::

### የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን - ከአይሁድና ከአህዛብ

ቤተ ክርስቲያን ዳግም የተወለዱ አማኞች ስብስብ ናት:: በአይሁድና በአህዛብ መካከል ልዩነት የለም:: እስከ ዛሬ ድረስ ከእነዚህ ከሁለት ክፍሎች የሚድኑትን ህዝቦች ጌታ በየቀኑ በቤተ ክርስቲያን ላይ እየጨመረ ነው:: (ሐሥ. 2:47) በገላትያ መፅሐፍ እንደተፃፈው

*«አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፣ ባርያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፣ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ» ከሚለው እናነባለን (ገላ.3:28)::*

የሰው የትውልድ ማንነት በደህንነቱ ምንም መለያ የማያደርግ ነው:: አይሁድ በአካልና በዝርያ አይሁድ ሆነው ነው የሚኖሩት:: ስለዚህም ነው ጳውሎስ አህዛብን ግሪኮች ያላቸው:: ይህም የተለመደው አሕዛብ የሚጠሩበት የመጽሐፍ ቅዱስ አነጋገር ነው:: የሰው የአንድ አገር ዜጋ /ተወላጅ/ መሆኑና የቆዳው መልክ ለደህንነት አስፈላጊ አይደለም:: በዚህ በምድር ሕይወት ብቻ ወንድና ሴት እንለያለን :: ከሞት በኋላ ጾታችን አይታይም:: በእግዚአሔር ፊት ዋጋ ያለው አዲስ ፍጥረት መሆን እንጂ ሌላው አይጠቅምም:: (*ገላ. 6:15*) በክርስቶስ ኢየሱስ በመሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ ዳግም በመወለድ አዲስ ፍጥረት እንሆናለን:: በዳግም ልደት ብቻ ነው የቤተ ክርስቲያን አባል የምንሆነው::

### የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አምላካዊ ሚስጢር

ቤተ ክርስቲያን ምስጢር የሆነች ናት:: ከብሉይ ኪዳን ስለ ቤተ ክርስቲያን በግልፅ ያየ ነቢይ የለም:: ይህ ምስጢር በተለየ መንገድ የተገለጸው ለሐዋሪያው ጳውሎስ ነበር (*ኤፌ.3:3-6*):: (ቤተ ክርስቲያንን አስደናቂ ምስጢርና ፍጥረት የሚያደርጋት «ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው» (*ቆላ.1:18)::*)

*«እናንተ የክርስቶስ አካል ናችሁ:: እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ» (1ቆሮ.12:27)* የሚለው ቃል መፃፉ ነው ቤተክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ በሰማይም በምድርም አለች::

ስለዚህ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስና ቤተ ክርስቲያን የእርሱ አካል የሆነች ናት:: በ *ኤፌ.5:30* ዳግም የተወለደውን የቤተ ክርስቲያንን አባል «የአካሉ ብልት ነን» በማለት ይገልጸዋል::

ይህ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አማኞች ያላቸው የማይነጠል ሰማያዊ ህብረት እግዚአብሔር ሊሰጥ ካሰው ሁሉ እጅግ ታላቅ የሆነ ስጦታ ነው:: ሰዎች በክርስቶስ ዳግም ሲወለዱ ምን እንደሚሆኑና ምን እንደሚፈጠር አያውቁም:: በሰማይና በምድር ወደ ተከበረው ወደ ክርስቶስ ከመጡ በኋላ እግዚአብሔር አብ ሰማያዊ ዓለም ወደ ሆነው ወደ ልጁ መንግሥት ያስገባቸዋል (ቆላ. 1:13):: በመንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ወደ ሆነችው ቤተ ክርስቲያን አባል ያደርጋቸዋል:: በፍጥረት ላይ ራስ ከሆነው ከክርስቶስ ጋር አንድ ይሆናሉ (ቆላ. 1:18)::

## የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን - ለዘላለም የማትሸነፈው

ቤተ ክርስቲያን ሰማያዊ ህብረት /ሕይወት ያለት ድርጅት/ እንደመሆኗ መጠን ሰማያዊ ተስፋዎችና ጥቂት ምድራዊ ተስፋዎችም አሏት:: የገሃነም ደጆች ቤተ ክርስቲያንን ከቶ ሊቋቋሚት አይችሉም *(ማቴ.16:18)*:: የጥንቱ የሮም መንግሥት ገሃነም በቅርቡ የወደቀው የኮሚኒስት ብሎክ ገሃነም፣ የአዶልፍ ሂትለር ገሃነም፣ የንጉሥ ኔሮ ገሃነም ቤተ ክርስቲያንን ሊያሸንፏት አልቻሉም:: ቤተ ክርስቲያን «በአለቅነትና በሥልጣንም ላይ ራስ ከሆነው» ከክርስቶስ የተጣበቀች ናት (ቆላ.2:10):: ስለዚህ ነው አዳኙ «ሥጋን የሚገድሉት ነገር ግን ነፍስን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ» ያለው *(ማቴ.10:28)*:: ቤተ ክርስቲያን በዚህ ምድር ላይ የማትሸነፍ ናት:: በቀራንዮ የድል እግር ስር በክርስቶስ አሸናፊነት ላይ ለዘላለም የተመሠረተች ነች:: ምክንያቱም « ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሰርት አይችልምና፣መሠረቱም እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» *(1ቆሮ. 3:11)*::

## የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን - ከዚህ ዓለም ያልሆነችው

እስከ አሁን በተደረገው ገለፃ እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ምንም ትስስር እንደሌላት በግልጽ ታይቷል:: በመዋጀት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ቤተ ክርስቲያንን የሚያመለክተው ሰፊው አረንጓዴው መሥመር የሰውን ዘር ከሚያመለክቱት ሁለት መሥመሮች በላይ የተደረገ ነው:: ቤተ ክርስቲያን ከምድር ህዝቦችና ከምድራዊ እሥራኤል በላይ በጣም ከፍ ያለች ናት:: ያልዳኑት ህዝቦች ወደ ሚያስፈራው ጨለማ ዘመን እየደረሱ ሳሉ የተመረጠችው እሥራኤል ደግሞ





እስከ አሁን ድረስ ምድራዊ ተስፋዎችን እንደያዘች ናት:: ቤተ ክርስቲያን ግን በእግዚአብሔር ልጅ «ትልቅና ክቡር የሆኑ ተስፋዎች ተሰጥቷታል» *(2ጴጥ.1:4)*:: ስለዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ከዓለምና ከእሥራኤል ጋር የበዛ ምድራዊ ትስስር የላትም:: በክርስቶስ ፍጹምና ሰማያዊ ናት:: ስለሆነም አማኙ በሥጋ አይሁዳዊ ወይም አህዛብ ቢሆን በእግዚአብሔር ፊት ምንም ልዩነት የለውም:: ዋነኛ ው ነገር አማኙ «አዲስ ፍጥረት» መሆኑ ነው *(2ቆሮ.5:17)*:: አስፈላጊው ቁም ነገር አማኙ በዳግም ልደት በኩል የክርስቶስ አባል መሆኑ ነው:: ስለዚህ አማኞች የብሉይ ኪዳን ወደ ሆነው ወደ ሙሴ ህግ፣ በኃጢአት ወደ ተሞላው ዓለምና ስመ ክርስትና ኖሯቸው እምነታቸው ሙት ወደ ሆኑት መመለስ የለባቸውም:: ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ስትተባበር ውጤቱ «ጋለሞታይቱ ባቢሎን» መሆን ነው:: አንድ ቀን ጋለሞታይቱ ባቢሎን እንደምትገለጥ እናውቃለን (ራዕ. 17 እና 18):: ነገር ግን እኛ እውነተኛ አማኞች በመሆን ለቤተ ክርስቲያን የሆንን ነን:: ስለሆነም በብሉይ ኪዳን ህግ ስር መሆን ከቶ አያስፈልገንም:: ያም ማለት እግዚአብሔር ለእሥራኤል ከሰጠው ሕግ ስር ልንሆንና በኢየሩሳሌም ይሰዋ ከነበረው የእንስሳ ደም መስዋዕት ተካፋዮች መሆን አይገባንም ማለት ነው:: በዚህ አውድ የዕብራውያን መልዕክት የሚከተሉትን ያመለክታል::

| | |
|---|---|
| ክርስቶስ ከመላእክት የበለጠ | ዕብ.1 እና 2 |
| [illegible] | [illegible] |
| [illegible] | [illegible] |
| [illegible] | [illegible] |
| [illegible] | [illegible] |
| [illegible] | [illegible] |
| [illegible] | [illegible] |
| [illegible] | [illegible] |

እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ራዕይ /መገለጥ/ ከራዕዮች ሁሉ የበለጠና እጅግ የከበረ ነው:: እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለእሥራኤል ህዝብ የሰጣቸው የወደፊቱን የመዋጀት ስራ ጥላ ብቻ ነበር:: የዚህ የመዋጀት ጥልቅ ሀቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር *(ቆላ.2:16-17 ፤ ዕብ.10:1)*:: የብሉይ ኪዳን ውጭዓዊ ገጽታ እውነተኛውን አዳኛችንን ክርስቶስን ያሳያል:: ነገር ግን የብሉይ ኪዳን ህግ ማንንም ለማዳን የማይቻለው ነበር:: ሰው በህግ በኢየሩሣሌም ባለው ቤተ መቅደስ፣ በብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች በኩል መዳን ቢችል ኖሮ የክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት ከንቱ ይሆን ነበር:: በደሙ የዳኑና በዳግም ልደት ወደ ቤተ ክርስቲያን የተጨመሩ

*«እናንተ የክርስቶስ አካል ናችሁ። እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ» (1ቆሮ.12፡27)* የሚለው ቃል መፃፉ ነው ቤተክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ በሰማይም በምድርም አለች።

ስለዚህ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስና ቤተ ክርስቲያን የእርሱ አካል የሆነች ናት። በ *ኤፌ.5፡30* ዳግም የተወለደውን የቤተ ክርስቲያንን አባል «የአካሉ ብልት ነን» በማለት ይገልጸዋል።

ይህ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አማኞች ያላቸው የማይነጠል ሰማያዊ ህብረት እግዚአብሔር ሊሰጥ ካለው ሁሉ እጅግ ታላቅ የሆነ ስጦታ ነው። ሰዎች በክርስቶስ ዳግም ሲወለዱ ምን እንደሚሆኑና ምን እንደሚፈጠር አያውቁም። በሰማይና በምድር ወደ ተከበረው ወደ ክርስቶስ ከመጡ በኋላ እግዚአብሔር አብ ሰማያዊ ዓለም ወደ ሆነው ወደ ልጁ መንግሥት ያስገባቸዋል (ቆላ. 1፡13)። በመንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ወደ ሆነችው ቤተ ክርስቲያን አባል ያደርጋቸዋል። በፍጥረት ላይ ራስ ከሆነው ከክርስቶስ ጋር አንድ ይሆናሉ (ቆላ. 1፡18)።

## የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን - ለዘላለም የማትሸነፈው

ቤተ ክርስቲያን ሰማያዊ ህብረት /ሕይወት ያለት ድርጅት/ እንደመሆኗ መጠን ሰማያዊ ተስፋዎችና ጥቂት ምድራዊ ተስፋዎችም አሏት። የገሃነም ደጆች ቤተ ክርስቲያንን ከቶ ሊቋቋሟት አይችሉም (*ማቴ.16፡18*)። የጥንቱ የሮም መንግሥት ገሃነም፣ በቅርቡ የወደቀው የኮሚኒስት ብሎክ ገሃነም፣ የአዶልፍ ሂትለር ገሃነም፣ የንጉሥ ኔሮ ገሃነም ቤተ ክርስቲያንን ሊያሸንፏት አልቻሉም። ቤተ ክርስቲያን «በአለቅነትና በሥልጣንም ላይ ራስ ከሆነው» ከክርስቶስ የተጣበቀች ናት (ቆላ.2፡10)። ስለዚህ ነው አዳኙ «ሥጋን የሚገድሉት ነገር ግን ነፍስን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ» ያለው (*ማቴ.10፡28*)። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ምድር ላይ የማትሸነፍ ናት። በቀራንዮ የድል አግር ስር በክርስቶስ አሸናፊነት ላይ ለዘላለም የተመሠረተች ነች። ምክንያቱም « ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሰርት አይችልምና፣መሠረቱም እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» (*1ቆሮ. 3፡11*)።

## የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን - ከዚህ ዓለም ያልሆነችው

እስከ አሁን በተደረገው ገለፃ እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ምንም ትስስር እንደሌላት በግልጽ ታይቷል። በመዋጀት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ቤተ ክርስቲያንን የሚያመለክተው ስፊው አረንጓዴው መሥመር የሰውን ዘር ከሚያመለክቱት ሁለት መሥመሮች በላይ የተደረገ ነው። ቤተ ክርስቲያን ከምድር ህዝቦችና ከምድራዊ እሥራኤል በላይ በጣም ከፍ ያለች ናት። ያልዳኑት ህዝቦች ወደ ሚያስፈራው ጨለማ ዘመን እየደረሱ ሳሉ የተመረጠችው እሥራኤል ደግሞ





እስከ አሁን ድረስ ምድራዊ ተስፋዎችን እንደያዘች ናት። ቤተ ክርስቲያን ግን በእግዚአብሔር ልጅ «ትልቅና ክቡር የሆኑ ተስፋዎች ተሰጥቷታል» (*2ጴጥ.1፡4*)። ስለዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ከዓለምና ከእሥራኤል ጋር የበዛ ምድራዊ ትስስር የላትም። በክርስቶስ ፍጹምና ሰማያዊ ናት። ስለሆነም አማኙ በሥጋ አይሁዳዊ ወይም አህዛብ ቢሆን በእግዚአብሔር ፊት ምንም ልዩነት የለውም። ዋነኛ ው ነገር አማኙ «አዲስ ፍጥረት» መሆኑ ነው (*2ቆሮ.5፡17*)። አስፈላጊው ቁም ነገር አማኙ በዳግም ልደት በኩል የክርስቶስ አባል መሆኑ ነው። ስለዚህ አማኞች የብሉይ ኪዳን ወደ ሆነው ወደ ሙሴ ህግ፣ በኃጢአት ወደ ተሞላው ዓለምና ስመ ክርስትና ኖሯቸው እምነታቸው ሙት ወደ ሆኑት መመለስ የለባቸውም። ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ስትተባበር ውጤቱ «ጋለሞታይቱ ባቢሎን» መሆን ነው። አንድ ቀን ጋለሞታይቱ ባቢሎን እንደምትገለጥ እናውቃለን (ራዕ. 17 እና 18)። ነገር ግን እኛ እውነተኛ አማኞች በመሆን ለቤተ ክርስቲያን የሆንን ነን። ስለሆነም በብሉይ ኪዳን ህግ ስር መሆን ከቶ አያስፈልገንም። ያም ማለት እግዚአብሔር ለእሥራኤል ከሰጠው ሕግ ስር ልንሆንና በኢየሩሳሌም ይሰዋ ከነበረው የእንስሳ ደም መስዋዕት ተካፋዮች መሆን አይገባንም ማለት ነው። በዚህ አውድ የዕብራውያን መልዕክት የሚከተሉትን ያመለክታል።

| | |
|---|---|
| ክርስቶስ ከመላዕክት የበለጠ | *ዕብ.1 እና 2* |
| ክርስቶስ ከሙሴ የበለጠ | *ዕብ.3* |
| ክርስቶስ ከኢያሱ የበለጠ | *ዕብ.4* |
| ክርስቶስ ከአሮን የበለጠ ነው | *ዕብ.5* |
| ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን የክህነት ሥርዓት የበለጠ ነው | *ዕብ.7* |
| ክርስቶስ ከብሉይ ቃል ኪዳን የበለጠ ነው | *ዕብ.8* |
| ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን መቅደስ የበለጠ ነው | *ዕብ.9* |
| ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች የበለጠ ነው | *ዕብ.10* |

እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ራዕይ /መገለጥ/ ከራዕዮች ሁሉ የበለጠና እጅግ የከበረ ነው። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለእሥራኤል ህዝብ የሰጣቸው የወደፊቱን የመዋጀት ስራ ጥላ ብቻ ነበር። የዚህ የመዋጀት ጥልቅ ሀቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር (*ቆላ.2፡16-17 ፣ ዕብ.10፡1*)። የብሉይ ኪዳን ውጭዓዊ ገጽታ እውነተኛውን አዳኛችንን ክርስቶስን ያሳያል። ነገር ግን የብሉይ ኪዳን ህግ ማንንም ለማዳን የማይቻለው ነበር። ሰው በህግ በኢየሩሳሌም ባለው ቤተ መቅደስ፣ በብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች በኩል መዳን ቢችል ኖሮ የክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት ከንቱ ይሆን ነበር። በደሙ የዳኑና በዳግም ልደት ወደ ቤተ ክርስቲያን የተጨመሩ

የእግዚአብሔር ልጆች ወደ «ኋላ እንመለስም» የሚል አንድ መደምደሚያ መሥመር ሊኖራቸው ይገባል::

ቤተ ክርስቲያን ሰማያዊ መሠረት የሆነችና ዘላለማዊና ሰማያዊ መድረሻ ያላት ናት:: እርሷ «የበጉ ሙሽራ» (ራዕ. 21:9) በሰማይ ስጌታዋ ብቻ የሆነች ናት:: ይህም በምንም መንገድ ከእስምና ከእሥራኤል ጋር ትስስር ማድረግ ከቶ እንደማትችል ግልጽ ያደርገዋል:: ስለዚህም ነው ሰፊው አረንጓዴው መሥመር የሰውን ዘር ከሚያመለክቱት ሁለት መሥመሮች በላይ የሚሄደው::

## የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ከጌታ ጋር ለዘለዓለም

ባለፉት 2000 ዓመታት ውስጥ አብዛኛውን ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች አልፈው አንቀላፍተዋል (ሞተዋል):: ዛሬም በሚሊዮን የሚቆጠሩ በዚህ ዓለም ዙሪያ ይኖራሉ:: ቢሆንም ከጴንጤቆስጤ /በዓለ-ሃምሳ/ ጊዜ ጀምሮ ካሉት ክርስቲያኖች ጋር ሲመዘኑ በጣም ጥቂቶች ናቸው:: እንደተመለከትነው ቤተ ክርስቲያን ምስጢር ናት:: ስንት አባሎች እንዳሏት ማንም አያውቅም:: ጌታ ብቻ ነው ለእርሱ የሆኑትን የሚያውቅ (2ጢሞ.2:19) የእርሱ ናቸው ለዘላለምም የእርሱ ሆነው ይቀራሉ፣ ማንም ከእጁ ሊነጥቃቸው አይችልም (ዮሐ.10:28) ብሎአልና::


ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባልታሰበ ጊዜ በደሙ የተገዛችውን ቤተ ክርስቲያኑን ወደ ሰማይ ይነጥቃታል:: ይህም የሚሆነው በአህዛብ ሙላት /ከዓለም በአንዱ ቦታ የመጨረሻው ሰው እምነቱን በክርስቶስ አድርጎ ራሱን ወደ ቤተ ክርስቲያን በጨመረ ጊዜ/ ነው (ሮሜ.11:25፣26):: ይህንን ጊዜ ማንም መገመት አይችልም የመጨረሻው ኃጢዓተኛ (/በመጨረሻ የሚድነው ማለት ነው) ሕይወቱን ወደ አዳኙ የሚመልስበትን ጊዜ ማንም ሰው አያውቅም:: ሆኖም ጌታ ቤተ ክርስቲያንን ሊነጥቅ ሊመጣ ባለው የመጨረሻ ሰዓት መኖራችንን እናውቃለን:: በሌላ አነጋገር «ስአኩለ ሌሊት ሰዓት» ከአምስት ደቂቃ ይልቅ አምስት ሴኮንድ በቀረበው ላይ ነን ቀኑንም ሆነ ሰዓቲቱን ከቶ አናውቅም (ማቴ. 24:36):: በደህንነት አረንጓዴ መሥመር ላይ ያለው የጥያቄ ምልክት ፍቺው ይህ ነው::

መነጠቅ መረዳት በማይቻል ፈጣን ጊዜ ውስጥ ይከናወናል:: «መወሰድ» ወይም «መነጠቅ» (1ኛ ተሰ. 4:17) የሚለው በአዲስ ኪዳን ወደ አሥራ አምስት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል:: የዚህ ቃል ትርጉም «መነጠቅ» ወይም «በድንገት አንድን ነገር መንጠቅ» ማለት ነው:: ከዚህ ድርጊት በስተኋላ መለኮታዊ ኃይል መኖሩን እንድንገነዘብ ያደርገናል:: ቤተ ክርስቲያን «ጌታን በአየር ለመቀበልና ከእርሱ ጋር





ለመኖር ትነጠቃለች» (1ኛተሰ.4:17):: ጌታ ቤተ ክርስቲያንን ለመንጠቅ ወደ ምድር እየታየ አይመጣም:: ይልቅስ ቤተ ክርስቲያኑን በአየር ይገናኛታል::




ይህ በሚሆንበት ጊዜ በህይወት ያሉት «ያንቀላፉትን አይቀድሙም» (1ተሰ.4:15) «በክርስቶስ የሞቱ አስቀድመው ይነሳሉ፣ (1ተሰ.4:16) ከዚህ በኋላ ያልሞቱት በሀይወት ያሉት አማኞች ይለወጣሉ (1ቆሮ.15:51)» በዚያን ጊዜ ብቻ ነው የዳኑት ጌታን በአየር የሚቀበሉትና ከእርሱ ጋር ለዘላለም አንድነት የሚኖራቸው:: የዳኑት ከጴንጤቆስጤ ቀን ጀምሮ «እስከ አህዛብ ሙላት» ድረስ ያሉትን ያጠቃልላል:: ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ እግዚአብሔር ራሱ በወሰነው ጊዜ የሚሆን ነው::

ቤተ ክርስቲያን ወደ ክብሩ ከተነጠቀች በኋላ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ትቆማለች:: ይህንንም

*«መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ እያንዳንዱ በሥጋው የተሰራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናል(2ቆሮ.5:10)*


ከሚለው ጥቅስ እንረዳለን::

ይህ «ፍርድ» የእግዚአብሔር ልጅ ደህንነት ወይም መፍረድን የሚጠይቅ አይደለም:: በዚህ የፍርድ ወንበር ጌታ ለታማኝ ደቀ መዝሙር ምን ሽልማት እንደሚሰጥ የሚወስንበት ነው:: የማንኛውም ክርስቲያን ሥራ በዚህ ፍርድ የተገለጠ ይሆናል:: ሥራው የሚጸና ወይም የሚቃጠል መሆኑ ይገለጻል (1ቆሮ.3:14-15):: የአማኙ የግል መዋጀት በምድር በህይወት በነበረ ጊዜ በሠራው ሥራ ላይ ያረፈ ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመው የመዋጀት ሥራ ላይ ብቻ ያረፈ ነው:: ምክንያቱም *«ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልም፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» (1ቆሮ.3:11)* በማለት ስለተፃፈ ነው::

ከዚህ በኋላ እንደ ነጎድጓድ ያለ

*«የበጉ ሠርግ ስለደረሰ ሚስቱም ራሷን ስላዘጋጀች ደስ ይበለን፣ ሐሴትም እናድርግ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ» የሚል ድምጽ ይሰማል (ራዕ.19:7)::*

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሙሽራ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሙሽሪት ሆነው ይገለጣሉ:: «የበጉ ሠርግ» በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ዘላለማዊውንና የማይሻረውን አንድነት ይደመድማል::




## 2. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን

አዲስ ኪዳን ማንኛውም ዳግም የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ አባል የሆነበትን ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያንና በስም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተብለው በሚጠሩት መካከል ልዩነት ያደርጋል:: ይህ ልዩነት በአጥቢያ ያሉ አማኞች መሰብሰብን ይናገራል:: አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ መላ ምዕመኑ የሚሰበሰቡበት ሥፍራ ነው:: (*ሐሥ.2:42፤ 1ቆሮ.14:23*)

ሐዋሪያው ጳውሎስ ከመልዕክቶቹ ውስጥ ጥቂቶቹን በቀጥታ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ልኳል ለምሣሌ:- «በቆሮንቶስ ላሰች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን» (*1ቆሮ.1:2*) «እግዚአብሔር አብ፣ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም ወደምትሆን ወደ ተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን» (*1ኛ ተሰ.1:1*) በማለት ጽፏል::

### አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - በዓለም ሁሉ

ከ2000 ዓመታት በፊት መንፈስ ቅዱስ በወረደበት ዕለት 3000 ህዝቦች በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመኑ ቀደም ብለን ተመልክተናል:: በኢየሩሳሌም የመጀመሪያዋ የአጥቢያ ማህበረ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው ያኔ ነበር:: ደግሞም የጥንቷ የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን በመባል ትታወቃለች::

በወንጌል መሠራጨት ምክንያት የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያናት በሌሎች ቦታዎች ተመሠረቱ ፤ በሐዋርያው ጳውሎስ ሚሲዮናዊ አገልግሎት ብዙ ሰዎች በተለይ ከአህዛብ በጌታ ኢየሱስ እንዲያምኑ ሆኑ:: ሰዎች በዳኑበት ሥፍራ ሁሉ አዲስ ቤተ ክርስቲያናት ተመሠረቱ:: ዛሬም ቢሆን ይህ ሥራ እንዳለ ነው:: በዓለም አቀፍ ደረጃ የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያናት አሉ:: አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት





ባልሰለጠኑት አገሮች ትናንሽ መንደሮችም ሆነ በሰለጠኑት አገሮች ትላልቅ ከተሞች ይገኛሉ:: ዳግም የተወለዱ አማኞች በትናንሽና በትላልቅ አጥቢያዎች «በጌታ እግር ሥር» በመሰባሰብ ይገኛሉ (*ሉቃ.10:39*)::

### የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - የውጭ ምስክርነት

*«ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ» (ማቴ.18:20)::*

የአማኞች በአጥቢያ መሰባሰብ ግልጽ የሆነ ምስክርነት ነው:: አማኞች «ራስ ወደሆነው ወደ ክርስቶስ» ለማደግ በአንድነት ይሰበሰባሉ (*ኤፌ.4:15*):: በዚህ መሰባሰብ በሚታየውና በማይታየው ዓለም ፊት ከተነሳው ጌታ ጋር አንድ መሆናቸውን በግልጽ ያሳያሉ:: ማንኛውም ዳግም የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ የክርስቶስ አካል አባል የመሆኑና የክርስቶስም ራስ የመሆኑ እውነት በአጥቢያ መሰባሰብ በኩል ግልጽ ሆኖ ይታያል:: አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት የአማኝን የግል ዓላማ የሚያገለግሉ ሳይሆኑ ስለ ክርስቶስ እውነተኛ ምስክርነት የሚሰጡ ናቸው:: በተጨማሪም በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን ይመሰክራሉ:: ይህ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መለያ ነው:: ዋነኛው ዓላማ «ክርስቶስ» ነው::

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በኢየሩሳሌም በነበረችው የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የነበሩት ዳግም የተወለዱት አማኞች የመሰብሰባቸውን ዓላማ በትክክል የተረዱ መሆናቸውን በግልጽ ያሳያል::

*«በሐዋርያት ትምህርት፣ በህብረት እንጀራውንም በመቁረስና በፀሎት ይተጉ ነበር»* ተብሎ ስለ ተፃፈ *(ሐሥ.2:42)::*

1. በሐዋሪያት ትምህርት፣ 2. በህብረት 3. እንጀራውንም በመቁረስና /የጌታን ራት/ በመካፈል 4. በፀሎት በመትጋት በእነዚህ በአራቱ ሕያው ክርስቲያናዊ የህይወት ልምዶች ከጌታ ኢየሱስ ጋር ቀጥተኛ ሕብረት እንደነበራቸው ይገለጻል:: የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምስክርነትና የእያንዳንዱ አማኝ የግል በረከት በዚህ ህብረት ላይ የተመሠረተ ነው::

### አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ

*«...የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ»(1ቆሮ. 3:17)::*

በዚህ ጥቅስ ሐዋርያው ጳውሎስ ቆሮንጦሳውያንን በቤተ ክርስቲያንነታቸው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ መሆናቸውን አስተምሯቸዋል:: በዚህ ጥቅስ መሠረት

እግዚአብሔር በእያንዳንዱ አማኝ ብቻ ሳይሆን ከዚህ በበለጠ በአጥቢያ የአማኞች ማህበር (ህብረት) መኖሩን ያሳያል።

የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሁልጊዜ ቅዱስ ቦታ ነው። ይህን በጥልቅ ልንገነዘበው ይገባናል። የሚያሳዝነው እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ ሕብረት በሰጠው ስርዓቶች ላይ ጥያቄ ማንሳቱ መጠየቁ ላይ ነው። እነዚህ ልምምዶች በእግዚአብሔር ፊት የሚታዩ አይደሉም። እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለማህበረ ምዕመኖቻቸው የራሳችውን ህግ እንዲያቋቁሙ አልተፈቀደላቸውም። እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዓላማዎቻቸውን በእግዚአብሔር ቃል ላይ መሠረት የሚያደርጉ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ናቸው። *(1ቆሮ.1:2፤ ገላ.1:2፤ ፊል.1:1፤ ቆላ.1:2)*

### 3. እያንዳንዱ አማኝ


*«ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖር የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም »* የሚለው ጥቅስ እንደሚያደርግ ያሳየናል *(1ቆሮ. 6:19)*።

መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ ዳግም በተወለደው አማኝ ውስጥ ያድራል። *«መንፈስ ቅዱስ የሰማይ ርስታችን መያዣ ነው ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ ይህም ለክብሩ ምሥጋና ነው »* (*ኤፌ. 1:14*)። ስለዚህ ያለ መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስ ገንዘብ መሆን አይቻልም። ንስሐ የሚገባው ኃጢዓተኛ በፍጹም ልቡ በኃጢዓት ከተሞላ መንገዱ ሲመለስ፣ ኃጢዓቱን ሲናዘዝ፣ የእግዚአብሔርን ልጅ የግል ጌታውና አዳኙ አድርጎ ሲቀበል ዳግም ይወለዳል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ሂደት *«ዳግም መወለድ» «ዳግም ልደት»* ይለዋል (*ዮሐ.3:3*)። ይህ ዳግም ልደት በመንፈስ ቅዱስ የሚመጣ ነው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በተለወጠው ሰው ሕይወት በማደር ይኖራል (*ዮሐ.1:12*)። በክርስቶስ ሙሉ የሆነ አዲስ ሕይወት ይቀበላል። ምክንያቱም ቃሉ *«ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፣ አሮጌው ነገር አልፎአል፣ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗልና (2ቆሮ.5:17)* ስለሚል። ስለዚህ የሰው መለወጥ የመንፈስ ቅዱስ ስራ ነው።

ቀደም ካሉት ምዕራፎች በአንዱ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ከስላሴ ሦስተኛ ወልድ ሁለተኛውና አብ ደግሞ የመጀመሪያው አካል መሆናቸውን ተመልክተናል። መንፈስ ቅዱስ ወደ ክርስቶስ ይመራናል።









ሁለተኛው አካል ክርስቶስ ደግሞ ወደ አብ ይመራናል። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ የደህንነት ራዕይ /መገለጥ/ ነው። ጌታ ኢየሱስ *«እርሱ ያከብረኛል ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና»* በማለት የመንፈስ ቅዱስን ስራ ለደቀ መዛሙርቱ ገልጦላቸዋል (*ዮሐ.16:14*)። መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ልጅ በክብሩ ለለው ነፍስ ያመስክታል። ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚፈልግ ወደ ወልድ መምጣት አለበት። ምክንያቱም ወልድ ብቻ ነው ሰውን በእውነት ወደ አብ መምራት የሚችለው ፤ስለዚህ ነው *«በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም»* በማለት ጌታ ኢየሱስ ያስተማረው /የሚያስተምረው/ (*ዮሐ.14:6*) ዳግም የተወለደ አማኝ የእግዚአብሔር ነው። ስለሆነም እግዚአብሔርን አባቱ ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታው አድርጎ ይቆጥራል ይህ የሚሆነው በመንፈስ ቅዱስ ነው። ምክንያቱም *«በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር አንድ ስንኳ ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል ስለማይችል» (1ቆሮ.12:3)*።

*መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ጋር በመስቀል አሠራር አንድነትን ያመጣል:: ስለዚህ ምክንያት ነው ሐዋሪያው ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ እኛ አማኞች ከክርስቶስ ጋር በመስቀል ላይ መሰቀላችንን፣ ከክርስቶስ ጋር መሞታችንና ከክርስቶስ ጋር መቀበራችንን የጻፈው:: (ሮሜ.6:1-10) የኤፌሶንም መልዕክት ከክርስቶስ ጋር መነሳታችንንና በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋር መቀመጣችንን ያሳየናል (ኤፌ.2:6):: ምክንያቱ ይህ ከክርስቶስ ጋር ያለው አንድነት በመንፈስ ቅዱስ ሥራ በኩል ብቻ የሚመጣ ነው:: «የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም» (ሮሜ.8:9) የሚለውም ጥቅስ ይህንኑ ያፀናልናል::*









*የሰው ሕይወት መለወጥና ዳግም ልደት ፍጹም ውጤት በሚያመጣው በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ ያረፈ ነው:: ኃጢዓተኛው በመንፈስ ቅዱስ ሲማረክ የኃጢዓአቱን ይቅርታ በንስሐና በኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ ያገኛል:: በዚያኑ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ በኩል ወደ ክርስቶስ አካል ይጠመቃል (1ቆሮ.12:12-13):: መንፈስ ቅዱስ አዲሱን አማኝ ከክርስቶስ ጋር አንድ የሆነበትን የኢየሱስ ክርስቶስን የመዋጀት ሥራ ያረጋግጥለታል:: ኃጢአቱ መወገዱንና በአዳኙ መከራ፣ ሞት ሙሉ ይቅርታ ማግኘቱን ያሳያል:: በዳግም ልደት አማኙ የኢየሱስ ክርስቶስ ገንዘብ ይሆንና ዳግም ከተወለዱት ሌሎች አማኞች ጋር የእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን አባል ይሆናል:: ከአዳኙና ከዋጀው ጌታ በማይለይ ሁኔታ የክርስቶስ አካል አባል ይሆናል (1ቆሮ.12:27):: ስለሆነም ዳግም የተወለደው አማኝ ወደፊት የሚኖረው ራሱ ሳይሆን ለእርሱ ሲል ለሞተውና ለተነሳው ነው (2ቆሮ.5:15):: ምክንያቱም የአማኙ ሰውነት (አካል) የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ስለሆነ ነው:: ከዚህ የተነሳ አማኙ ከእምላኩ ጋር ባለው አካሄድ የተለየ ኃላፊነት ይጠበቅበታል:: አማኙ ሰውነቱን እንዴት መያዝና ከእርሱ ምን እንደሚጠበቅ አዲስ አይሆንበትም:: ሐዋርያው ጳውሎስ ቸልተኞቹን ቆሮንቶሳውያንን በዚህ ጉዳይ «በዋጋ ተገዝታችኋልና፣ ሥለዚህ በሥጋችሁ በመንፈሳችሁ እግዚአብሔርን አክብሩት» በማለት ገስጿቸዋል (1ቆሮ.6:20):: ዳግም የተወለደ አማኝ ያለው ምድራዊ ተስፋ ብቻ ሳይሆን ሰማያዊም ተስፋ ነው (ቆላ.1:27):: አዳኙንና ጌታውን ኢየሱስን የሚጠብቅ ዜግነቱ ሰማያዊ የሆነ ነው (ፊል.3:20):: ይህም በዚህ ምድር እንግዳና መጻተኛ እንደመሆን ያለ ህይወት ነው:: (1ጴጥ.2:11) ዳግም የተወለደው አማኝ ስለ እምላኩ የማያቋርጥ ናፍቆት አለው፤ በጌታ ቶሎ መምጣትና ከዚህ ዓለም ተለይቶ ከክርስቶስ ጋር እንደሚሆን በማሰብ ይደሰታል (ፊልጵ.1:23):: ዳግም የተወለዱት ለጠፉትና ላልዳኑት ሸክም አላቸው:: «ሂዱና አህዛብን ሁሉ ደቀመዛሙርቴ አድርጓቸው» (ማቴ. 28:19) የሚለው የጌታ ታላቁ ተልዕኮ በልቡ ውስጥ የሚነድድ ይሆናል:: ከጳውሎስ ጋር «በወንጌል አላፍርም፣ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ነው» በማለት ይመሰክራል (ሮሜ.1:16):: ስለሆነም አማኙ በተገኘው መንገድ ሁሉ መልካሙን ዜና ለጠፉት ሰዎች ለማካፈል ይጥራል:: ኒኮላውስ ሉድቪግ ቪንፎን ሲንስ ርዶርፍ የተባሉ በጊዜያቸው ብዙ ህዝብ ወደ ጌታ የመሩ ሰው እንዲህ ብለው የነፍሳትን ማዳን ይገልጹታል::*

*«እስከ እለተ ሞቴ ድስ ምኞቴ ነፍሳትን ለበጉ ማትረፍ ነው::»*

በ1ኛ.ቆሮ.10:32-33 ላይ ባደረግነው በሦስት የሰው ዘር ጥናት ላይ ተመስርተን በዚህ ነጥብ የተገኙትን የሚከተሉትን ውጤቶች ተመልሰን እንቃኛለን::

1. **የጥንቱ ታሪክ:-** ከዓለም መፈጠር ጀምሮ እስከ ባቢሎን ግንብ ግንባታ ያለውን ጊዜ ይሸፍናል:: እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ ከነበሩት ህዝቦች ጋር በምድር ሁሉ ላይ እስከሚበትናቸው ጊዜ ድረስ ተናገረ:: *(ከዘፍ. ምዕራፍ 1 እስከ 11)*
2. **የእስራኤል ታሪክ:-** ከአብርሃም መመረጥ ጀመረና መሲሁን በመቃወም አበቃ:: (ከዘፍ.12 - ሐሥ.12) እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር የመዳንን ታሪክ በቀጥታ አደረገ:: ነገር ግን በመቃወማቸው የደህንነትን ነገር ወደ አሕዛብ አሳለፈ::
3. **የቤተክርስቲያን ዘመን:-** በመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ጀመረና (ሐሥ.2) ዳግም በተወለዱት መነጠቅ ያከትማል:: እግዚአብሔር በወንጌል በኩል ራሱን ለሰው ዘር ሁሉ ሰጠ:: ቤተ ክርስቲያንም ታየች:: እርሷም አይሁድንና አህዛብን ያቀፈች ናት:: (ሐሥ.13 እስከ ራዕይ.3)

እንደገና አንድ ጊዜ ጥልቅ የሆነውን የደህንነትን ዘመን ታሪክ ለውጥ የተደረገበትን ምክንያት ማጠናከሩ አስፈላጊ ነው:: እንደ *ማቴ. 16:13-19* አዲሱን የፀጋ ዘመን፣ *መዋጀትን፣* መንፈስ ቅዱስንና ለአይሁድ *(ሐሥ.2)* ለሰማሪያውያንና *(ሐሥ.8)* ለአህዛብ *(ሐሥ.10)* ቤተ ክርስቲያንን እንዲከፍት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያው ጴጥሮስ *«የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ ቁልፍ»* ሰጠው:: የሐዋርያት ሥራ ባጭሩ ከብሉይ ኪዳን ዘመን ወደ አዲሱ ኪዳን የፀጋ ዘመን እንዴት ሽግግር እንደተደረገ ይናገራል::ይህ ሽግግር እስከ አሁን ድረስ የቀጠለ ነው:: የሚቀጥለው









## ሁለቱ ክቦች ፍቺ

## እሥራኤል

## በእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት ላይ

በእግዚአብሔር የደህንነት ካርታ ላይ ግልጽ የሆኑ ሁለት ጥቁር ክቦች ታገኛላችሁ:: አንዱ ከቀራንዮ መስቀል አጠገብ የሆነ ነው:: ሌላው ደግሞ ከፍ እያለ ወደ ላይ የሚመጣው የእሥራኤልን ህዝብ የሚወክለውን ቀዩን መሥመር ወደታች በመውረድ በሚያቋርጠው የዓለም ህዝቦችን ከሚያመለክተው ሰማያዊ መሥመር ወደቀኝ ጥቂት እልፍ ብሎ ነው::

ሁለቱም ክቦች በጣም አስፈላጊዎች ናቸው:: በጣም ልዩ የሆነን ሰዓት (ጊዜን) ያመለክታሉ:: «የእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት» ብለን እንሰይመዋለን:: ይህንንም በመመልከት ራሳችን በየትኛው የእግዚአብሔር የማዳን ዘመን ውስጥ እንዳለን እንመለከታለን:: በሌላ አነጋገር በዓለም የደህንነት ታሪክ እንዴት ወደኋላ (መጨረሻ) ላይ እንዳለ ያሳየናል:: ስለዚህ ይህንን ሰዓት እንዴት በጥንቃቄ ማንበብ እንዳለብን መረዳቱ አስፈላጊ ነገር ነው:: በእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት ፊት በደህንነት ታሪክ ውስጥ እጅግ አስፈላጊ የሆኑትን ቀናት የያዘ ነው:: በዚህ ሰዓት ያለው ቀስት ህዝቦችን (ከብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ህዝብ የሆኑትን እሥራኤልን) የያዘ ነው::




| የእግዚአብሔር የአለም ሰዓት ከ1900 ዓመታት በፊት | የእግዚአብሔር የአለም ሰዓት በዚህ ክፍል ዘመን |
|---|---|

በ1ኛ.ቆሮ.10:32-33 ላይ ባደረግነው በሦስት የሰው ዘር ጥናት ላይ ተመስርተን በዚህ ነጥብ የተገኙትን የሚከተሉትን ውጤቶች ተመልሰን እንቃኛለን።

1. **የጥንቱ ታሪክ፡-** ከዓለም መፈጠር ጀምሮ እስከ ባቢሎን ግንብ ግንባታ ያለውን ጊዜ ይሸፍናል። እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ ከነበሩት ህዝቦች ጋር በምድር ሁሉ ላይ እስከሚበትናቸው ጊዜ ድረስ ተናገረ። *(ከዘፍ. ምዕራፍ 1 እስከ 11)*
2. **የእስራኤል ታሪክ፡-** ከአብርሃም መመረጥ ጀመረና መሲሁን በመቃወም አበቃ። (ከዘፍ.12 - ሐሥ.12) እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር የመዳንን ታሪክ በቀጥታ አደረገ። ነገር ግን በመቃወማቸው የደህንነትን ነገር ወደ አሕዛብ አሳለፈ።
3. **የቤተክርስቲያን ዘመን፡-** በመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ጀመረና (ሐሥ.2) ዳግም በተወለዱት መነጠቅ ያከትማል። እግዚአብሔር በወንጌል በኩል ራሱን ለሰው ዘር ሁሉ ሰጠ። ቤተ ክርስቲያንም ታየች። እርሷም አይሁድንና አህዛብን ያቀፈች ናት። (ሐሥ.13 እስከ ራዕይ.3)

እንደገና አንድ ጊዜ ጥልቅ የሆነውን የደህንነትን ዘመን ታሪክ ለውጥ የተደረገበትን ምክንያት ማጠናከሩ አስፈላጊ ነው። እንደ *ማቴ. 16፡13-19* አዲሱን የፀጋ ዘመን፣ መዋጀትን፣ መንፈስ ቅዱስንና ለአይሁድ *(ሐሥ.2)* ለሰማሪያውያንና *(ሐሥ.8)* ለአህዛብ *(ሐሥ.10)* ቤተ ክርስቲያንን እንዲከፍት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያው ጴጥሮስ *«የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ ቁልፍ»* ሰጠው። የሐዋርያት ሥራ ባጭሩ ከብሉይ ኪዳን ዘመን ወደ አዲሱ ኪዳን የፀጋ ዘመን እንዴት ሽግግር እንደተደረገ ይናገራል።ይህ ሽግግር እስከ አሁን ድረስ የቀጠለ ነው። የሚቀጥለው









## ሁለቱ ክቦች ፍቺ
## እሥራኤል
## በእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት ላይ

በእግዚአብሔር የደህንነት ካርታ ላይ ግልጽ የሆኑ ሁለት ጥቁር ክቦች ታገኛላችሁ። አንዱ ከቀራንዮ መስቀል አጠገብ የሆነ ነው። ሌላው ደግሞ ከፍ እያለ ወደ ላይ የሚመጣው የእሥራኤልን ህዝብ የሚወክለውን ቀዩን መሥመር ወደታች በመውረድ በሚያቋርጠው የዓለም ህዝቦችን ከሚያመለክተው ሰማያዊ መሥመር ወደቀኝ ጥቂት እልፍ ብሎ ነው።

ሁሉቱም ክቦች በጣም አስፈላጊዎች ናቸው። በጣም ልዩ የሆነን ሰዓት (ጊዜን) ያመለክታሉ። «የእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት» ብለን እንሰይመዋለን። ይህንንም በመመልከት ራሳችን በየትኛው የእግዚአብሔር የማዳን ዘመን ውስጥ እንዳለን እንመለከታለን። በሌላ አነጋገር በዓለም የደህንነት ታሪክ እንዴት ወደኋላ (መጨረሻ) ላይ እንዳለ ያሳየናል። ስለዚህ ይህንን ሰዓት እንዴት በጥንቃቄ ማንበብ እንዳለብን መረዳቱ አስፈላጊ ነገር ነው። በእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት ፊት በደህንነት ታሪክ ውስጥ እጅግ አስፈላጊ የሆኑትን ቀናት የያዘ ነው። በዚህ ሰዓት ያለው ቀስት ህዝቦችን (ከብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ህዝብ የሆኑትን እሥራኤልን) የያዘ ነው።




| | |
|---|---|
| የእግዚአብሔር የአለም ሰዓት<br>ከ1900 ዓመታት በፊት | የእግዚአብሔር የአለም ሰዓት<br>በዚህ ክፍለ ዘመን |

በየትኛው የደህንነት ታሪክ ዘመን ውስጥ እንኖራለን ለሚለው ጥያቄ መልሱን ለማግኘት ከፈለግን ሁልጊዜ ዓይናችንን እሥራኤል ላይ መጣል አለብን:: ስለዚህ አሁን ከእሥራኤል ጋር ከተያያዙት ጥቂት ታሪኮች እንመለከታለን:: እነርሱም ለመዳን ታሪክ ቀጥተኛና አስፈላጊ ናቸው:: እንደዚሁም ደግሞ ከብሉይ ኪዳንና ከአዲስ ኪዳን ምን ያህሉ ትንቢቶች እንደተፈጸሙ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ እየተፈጸሙ ያሉትን ያሳዩናል:: ምን ያህል በፀጋ የመጨረሻ ቀናትና የዓለም ፍጻሜ ላይ እንዳለን ለመረዳት አስቸጋሪ አለመሆኑን እንገነዘባለን::

### 1. የእሥራኤል ህዝብ መበተን

**በእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት መቁጠሪያ ላይ ያለችው ቀስት ወደ ታች መውረድ**

**እ.አ.አ በ33 ዓ.ም. ስቅለት**

*«ጲላጦስ ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን እንግዲህ ምን ላድርገው? አላቸው ሁሉም ስቀለው አሉ:: ገዢውም ምን ነው? ያደረገው ክፋት ምንድነው? ሲላቸው:: እነርሱ ግን ይሰቀል እያሉ ጩኸታቸውን አበዙ» (ማቴ.27:22-23)::*

*«እነርሱ ግን አስወግደው! አስወግደው! ስቀለው እያሉ ጮኹ:: ጲላጦስም ንጉሣችሁን ልሰቀለውን? አላቸው:: የካህናት አለቆችም «ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም» ብለው መለሱለት:: (ዮሐ.19:15)*

ከላይ እንደተጠቀሰው ጽሕፍት ፈሪሳውያን (መንፈሳዊ ባለስልጣናትና መሪዎች) በመሲሁ በጌታ ኢየሱስ ላይ የሞት ፍርድ ፈረዱበት:: ቀደም ሲል ጌታ በምሳሌው «ይህ በላያችን ሊነግስ አንወድም» ብሎ የተናገረው አሁን እውነት ሆነ:: (*ሉቃ.19:14*) በእግዚአብሔር ጎን ከመቆም ይልቅ ህዝቡን ወክለው የነበሩት ሊቀ ካህናት ከሮም ንጉሥ ጎን ቆሙ:: በይሁዳ የነበረው የሮም መንግስት ተወካይ ጴንጤናዊው ጲላጦስ ጌታን ለሞት የሚያበቃው በደል እንደሌለበት ደጋግሞ ቢመሰክርም ራሱን ለጌታ ተቃዋሚዎች በማንበርከክ በጌታ ላይ የሞት ፍርድ ፈረደበት (*ሉቃ.23:22*)::

ከጥቂት ሰዓታት በኋላ በጣም አስከፊ የሆነ ሁኔታ ተከናወነ:: እሥራኤል «በአመጸኞች እጅ» ንጉሣቸውን ሰቅለው ገደሉት:: (*ሐሥ.2:23*) ሰማያዊውን ንጉሡን በምድራዊ ገዢ ተኩት::

ካለፉት ምዕራፎች በአንዱ ምዕራፍ የሮም ገዢ ጨካኝ ጣዖት አምላኪ እንደነበር ተመልክተናል:: የሮም ከፍተኛ ጣዖት የነበረው የጁፒተር ልጅ ነው ተብሎ ይገመት ነበር:: ከጁፒተር በስተኋላ ያለው ሰይጣን መሆኑ የማያጠራጥር





ነው:: ስለሆነም እሥራኤል አስከፊ ምርጫ ነበር ያደረገችው:: የክብር ጌታዋን በመቃወም የዚህን ዓለም ገዢ መረጠች (*1ቆሮ.2:8*) ፤ ከመቅፀበት የዚህን ዓለም ገዢ መረጡ (*ዮሐ.12:31*)፡ በዚያን ጊዜያት የዚህ ዓለም ገዢ ዋነኛ አገልጋይና የበላይ መሪ የነበረውን የሮምን ንጉሥ እሥራኤል መረጠችው:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይህ መሪ ምን ያህል አስከፊና አጥፊ መሆኑ የተገለጸ ነበረ:: በኋላም የሮም መንግስት መጥቶ የእሥራኤልን ምድርና ህዝብ አጠፋ::

የጌታ ኢየሱስ የስቅለቱ ዓመት መቼ እንደነበር በግምት የተደረገ ነው (*በሉቃ.3:1*)፡ ዮሐንስ መጥምቁ እሥራኤልን ወደ ንስሐ እየጠራ በዮርዳኖስ ወንዝ የታየው በንጉሥ ጢባርዮስ በአሥራ አምስተኛው ዓመት ነበር:: ክ.ል.በኃላ ንጉሥ ጢባርዮስ የአውግስጦስ ወራሽ የሆነው በ14 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) ሲሆን የገዛው ክ.ል.በኋላ ከ27 እስከ 14 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) ድረስ ነበር:: መጥምቁ ዮሐንስ የታየበት የጢባርዮስ አስራ አምስተኛው ዓመት በግምት ከ 28-29 ዓ.ም. ያለው ጊዜ ሊሆን ይችላል:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጌታ ኢየሱስ መሲህ ሆኖ በመገለጥ በእሥራኤል ህዝብ መካከል ለሦስት ዓመት ተኩል /ለ3½ ዓመታት/ ሠራ:: ዘመኑን ለመገመት የሚቻለው ጌታ ኢየሱስ የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ሦስት ጊዜ ከወጣበት እውነት በመነሳት ነው (*ዮሐ.2:13፤ ዮሐ.6:4፤ ዮሐ.12:1*)፡ ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ የተሰቀለው በ33 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) ገደማ ሊሆን ይችላል:: ከኢየሩሳሌም መፍረስ (መደምሰስ) ከአርባ ዓመት በፊት ሮማውያን ከአይሁድ የሞት ፍርድ የመፍረድን መብት ወስደውባቸው ነበር:: ቤተ መቅደሱ የተደመሰሰው በ 70 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) ነበር:: የሞት ፍርድ መፍረድ ካለመቻላቸው የተነሳ ነበር ሊቀ ካህናቱና የህዝቡ ሽማግሌዎች ጌታ ኢየሱስን ወደ ጲላጦስ ያቀረቡት የሞት ፍርድ መፍረድ የሚችለው የሮማውያን መንግሥት ተወካይ ብቻ ነበር::

የጌታ ኢየሱስን ስቅላት ጊዜ ለመቁጠር ሃሳባችንን የሚስበው ከብዙ ዓመታት በፊት የተካሄደው ነገር ነበር:: በቤተልሔም ህፃናትን ያስገደለው ሄሮድስ በኢያሪኮ የሞተው በመጋቢት (April) 2 እ.ኤ.አ. (ከ.ክ.በኋላ) ነው:: የተቀበረው ከቤተልሔም ደቡባዊ ምሥራቅ አስራ ሦስት ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ ከሚገኘው የሄሮድሳውያን ምሽግ ውስጥ ነበር:: እንደ *ማቴ.2:16* መሠረት በሄሮድስ የተገደሉት ህፃናት ዕድሜአቸው ሁለት ዓመትና ከሁለት ዓመት በታች ነበር:: ይህ ጊዜ የዓለም አዳኝ የሆነው ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን 6 ክ.ል.በኋላ ያመጣናል:: የቤተልሔሙ ኮከብ መታየት ስለ ዘመኑ አቆጣጠር ሌላ የአቆጣጠር ምክንያት ሊሰጠን ይችላል:: የሚቀርቡልን ማስረጃዎች ነገሮች በጣም ግልጽ ላይሆኑ ይችላሉ:: ቢሆንም የጌታ ስቅላት የሆነው በ 33 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) ነበር::

## በእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት መቁጠሪያ ላይ ያለችው ሰዓት መቆጣጠሪያ ቀስት እንደገና ወደ ታች መውረድ 70 ዓ.ም ከ.ክ.ል.በኋላ የቤተ መቅደስ መደምሰስ

«ኢየሱስ ከመቅደስ ወጥቶ ሄደ:: ደቀ መዛሙርቱም የመቅደሱን ግንቦች ሊያሳዩት ቀረቡ:: እርሱ ግን መልሶ ይህን ሁሉ ታያላችሁን? እውነት እላችኋለሁ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም አላቸው» (*ማቴ. 24:1-2*): ጌታ ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን በኢየሩሳሌም ስለ ነበረው ቤተ መቅደስ ተንብዮ ነበር:: የዚህ አስደናቂ ግንብ ድንጋይ በድንጋይ ላይ መፍረስ የማይቀር ነበር:: ይህ ትንቢት በግልጽ የሚፈጸምበት ጊዜ እየቀረበ እየመጣ ነበር::

### የእየሩሣሌም መደምሰስ

በ66 ዓ.ም. በሜዲትራኒያን ባህር አጠገብ ባለችው በቂሳሪያ የአይሁድ አመጽ በሮማውያን ላይ ተጀመረ:: በ73 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) ለሰባት ዓመታት የቀጠለው አመጽ በሙት ባህር አጠገብ ባለው በረሃ በማሰዳ መውደቅ ወደ ፍጻሜ ደረሰ:: በ67 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) ሮማውያን በገሊላ አይሁድን ድል አድርገዋቸው ነበር:: በእነዚህ ጊዜያት አራት ተፎካካሪ ገዢዎች ተነስተው ነበር:: በ68 በንጉሥ ኔሮ መገደል ምክንያት በአይሁድ ላይ የነበረው ጦርነት ጋብ ብሎ ነበር:: እነዚህም ገዢዎች ኦቶ፣ ጋልባ፣ ቪቴሊዮስና ቪስፓስያን ነበሩ:: በ69 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) ቪስፓሲያን ዙፋኑን ያዘና የሮም ንጉሥ ሆነ:: በ70 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) ቪስፓስያን ቲቶስ የተባለውን ልጁን ኢየሩሳሌምን እንዲያሸንፍ የጦር ጀኔራል አድርጎ ላከው:: በኋላም ቲቶስ ራሱ በ79 ዓ.ም. የሮም ገዢ ሆነ:: ቲቶስ ከሠራዊቱ ጋር ኢየሩሳሌምን በከበባት ወቅት በውስጧ ከ600,000 ሰዎች በላይ ነበሩ:: የመጡት በመጋቢትና በሚያዝያ ወራት የፋሲካን በዓል ለማክበር ነበር:: በኢየሩሳሌም ይኖሩ ከነበሩትና ለመጡት እንግዶች በቂ ስፍራ ነበር::

ወደ ከተማው ከሚመጣው ከሮም ሰራዊት ተጽዕኖ የተነሳ የከተማዋ በሮች ተዘግተው ነበር:: ከተማዋ በደንብ ተመሽጋ የተሰራች ስለነበር በውስጧ የነበሩት ህዝቦች በኢየሩሳሌም ውስጥ ደህንነት እንደሚኖራቸው ተሰምቷቸው ነበር:: እግዚአብሔር ቅድስቲቷን ከተማና ቤተ መቅደሱን ለጥፋት የማይሰጥ ነው ብለው አስበው ነበር:: ቢሆንም ያለፈ ነገር ነበር እሥራኤል የጥልቁን መንግስት መርጣ ነበር:: የመረጠችውም እነሆ መጣ::

ኢየሩሳሌም ለአምስት ወራት ያህል በሮማውያን ተከባ ነበር:: አስቃቂ ውጊያዎች ተደረገ፤ እሥራኤል ራሷን መከላከል ነበረባት:: በከተማዋ ውስጥ የነበሩት ህዝቦች ወጥመድ ውስጥ ወድቀው ነበር:: ከሌላው የዓለም ህዝብ ተለይተው መቀመጣቸው ከፋ ሆነባቸው:: ታላቅም ረሃብ ሆነ፣ ህዝቡም በድንገት የሚበላውን አጣ::





በዚህም ላይ አይሁድ እርስ በእርሳቸው ጠላታሞች ሆኑ:: የሌላውን ጎተራ መዝረፍ ስለተጀመረ ረሃቡን አባባሰው:: የከተማዋም ነዋሪዎች በዚህ ሁኔታ በጣም ተሰፋ ቆረጡ:: ከረሃቡ ስቃይ የተነሳ እናቶች አዲስ የተወለዱትን የህፃናቶቻቸውን ሥጋ በሉ (*ዘዳ.28:53*):: ፈላቪዮስ ጆሲፋስ የተባለው የአይሁድ ታሪክ ፀሐፊ «የአይሁድ ጦርነቶች» በተባለው መጽሐፉ ውስጥ አዲስ የተወለደውን ልጇን ስለ ቀቀለችው ሴት ስለ ማሪያ ጽፏል:: ያለ ምህረት ሕዝቡን በሽታ ጨረሰው:: በከተማዋ ዙሪያ ያሉት ሸለቆዎች በረሃብ በሚሰቃዩት ሰዎች ሬሳ የተሞሉ ሆኑ:: ሮማውያኑ ለጦርነቶችና ለመስቀሉች (ለስቅላት) መጠቀሚያ በኢየሩሳሌም ዙሪያ በሃያ ኪሎ ሜትር ሥፋት ላይ ያሉትን ዛፎች በሙሉ ቆረጡ:: በየቀኑ ሮማውያን ከ 500 በላይ አይሁዶችን ይሰቅሉ ነበር:: በከተማዋ ውስጥ ወደር በሌለው ሁኔታ ተስፋ መቁረጥ አደገ::

«ከቄሳር በቀር ንጉሥ የለንም» በማለት የእሥራኤል መሪዎች የመረጡት:: ንጉሥ ከአርባ ዓመት በኋላ በጠላትነት ወደ እነርሱ መጣ:: ወታደሮቹ በኢየሩሳሌም በሮች ፊት ለፊት ቆመ:: ከዚህ ጊዜ በኋላ በከተማይቱ ውስጥ ለነበሩት መዳን የሚቻል አልነበረም:: ኢየሩሣሌም ፈጽማ ተወረረች:: የተረፉት ያለ ርህራሄ ታረዱና ከተማይቱም ተደመሰሰች::

### የቤተ መቅደሱ መደምሰስ /ፍጻሜ/

በቅድስቲቱ ከተማ መደምሰስ ምክንያት የጌታችን ትንቢት ተፈጸመ:: ነሐሴ 10 ቀን 70 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) አንድ የሮማውያን ወታደር የሚነድ ችቦ ወደ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ጣለ:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ መላ ቤተ መቅደሱ በእሳት ተያያዘ:: የእሳቱ ኃይል በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበረውን ወርቅ አቀለጠው:: የቀለጠው ወርቅ ከግድግዳው ወደ ወለሉ ወረደ: ከዚያም ከድንጋዮቹ ስንጣቂዎች ውስጥ እየገባ ረጋ:: ወርቁን ለማግኘት የሮም ወታደሮች የከባድ ነገር መፈንቀያ ብረቶቻቸውን አንስተው ድንጋዮቹን ሰባበሩአቸው:: መላ ከተማዋ ከነህንፃዋ በእሳት ጋየች:: ጦርነቱ እስከ መስከረም ድረስ ቀጠለ:: ዛሬም ቢሆን በአስደናቂዋ ከተማ በኢየሩሣሌም ብዙ ፍርስራሾች ይታያሉ:: አዳዲስ የከርሰ ምድር ቅሪቶች በየጊዜው ይገኛሉ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእሥራኤል ህዝብ ስለ ቤተ መቅደሱ መደምሰስ (በቲሻቤ የሀዘን ቀን) በ9ኛው ወር በየዓመቱ ያለቅሳሉ:: የቤተ መቅደሱን ተራራ ከሚከበው 488 ሜትር ርዝመት ካለው ግንብ በስተምዕራብ በኩል 80 ሜትሩ «የልቅሶ ግንብ» የልቅሶ አደባባይ የተባለው ስለዚህ ነው:: ቤተ መቅደሱ የተደመሰሰው በእንደዚህ ዓይነት ሁኔት ነበር:: ጌታ እንደተነበየው *«ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ የማይቀርበት ዘመን ይመጣል» (ሉቃ.21:5-6):: «የአህዛብም ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ኢየሩሣሌም በአህዛብ የተረገጠች ትሆናለች» (ሉቃ.21:24)::*

በ70 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) የቅድስቲቱ ከተማና የቤተ መቅደሱ መደምሰስ ለእሥራኤል ህዝብ የሚያስቅቅ መናወጥ የሆነበትና እስከ አሁን ድረስ ያልተፈወሱበት ጉዳይ ነው:: ከ1900 ዓመታት በላይ አንድ አይሁዳዊ ለታመመ ቤተሰቡ የሚያስተላልፈው ቃል «እኛ ለጽዮንና ለኢየሩሳሌም እንዳዘንን ሃዘናችሁ ሃዘናችን ነው» የሚል ነው::

ኢየሩሳሌም በተከበበችበት በአምስት ወራት ውስጥ 600,000 አይሁዳውያን ሕይወታቸውን አጥተዋል:: «የአይሁድ ጦርነት» ተብሎ ከሚጠራው ከ66 ዓ.ም. እስከ 73 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) ከሆኑት ይህ አንዱ ነበር:: በእነዚህ ዓመታት ሮማውያን 1.1 ሚሊዮን አይሁዶችን ገድለዋል:: በወቅቱ በነበረው «ምድራዊ ንጉሥ» በአስፈሪ ሥራው የአይሁድን ህዝብ አዋርዶ ጥሎአቸዋል:: እውነተኛውን ንጉስ በመቃወማቸውና ምድራዊ ንጉስ በመምረጣቸው በእሥራኤል ህዝብ ላይ ጥፋትና ሞት ወደቀ::

**በእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት መቁጠሪያ ጠቋሚዋ**
**ቀስት እንደገና ወደ ታች መውረድ**
**135 ዓ.ም. ከ.ክ.ል.በኋላ የባረኮቺባ አመጽ**

*«በሰይፍ ስለትም ይወድቃሉ፣ ወደ አህዛብም ሁሉ ይማረካሉ፣ የአህዛብ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ኢየሩሣሌም በአህዛብ የተረገጠች ትሆናለች» (ሉቃ.21:24)* ተብሎ እንደተፃፈው::

ከ132 እስከ 135 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) ባለው ጊዜ ውስጥ በአይሁድና በሮማውያን መካከል ውጊያዎች ተቀሰቀሱ:: አንድ ሐሰተኛ ነቢይ በእሥራኤል ተነሳ ስሙም ባርኮችባ ይባል ነበር:: የስሙ ትርጓሜ «የከዋክብት ልጅ» ማለት ነው:: ይህም ሰው «ከያዕቆብ የሚወጣው ኮከብ» አድርጎ ራሱን ይቆጥር ነበር (*ዘኁ.24:17*): ከሮማውያን ጋር በሚደረገው ጦርነት አይሁድን በድል የሚመራ «መሲህ» ብሎ ራቢ አኪባ የሰየመው ሰው ነበር:: ለሶስት ዓመታት ያልተቋረጠ አሰቃቂ ጦርነት ሆነ:: የሮማ ንጉሥ ሀድሪያን ከጀግኖቹ የሮም ወታደሮች ጋር አመጸኞቹን ደመሰሱአቸው:: ሮማውያን ቀላል ያልሆነ ክስረት ከሰሩ:: በአይሁዳውያን ላይ በነበራቸው ቁጣ በቀል ተበቀሉ ኢየሩሳሌምንም ደመሰሱ::

የባርኮቺባ አመጽ 500,000 አይሁዳውያን ሕይወታችን እንዲያጡ አደረገ:: ሮማውያን አይሁድን ለመደምሰስና ከምድር ገጽ ለማጥፋት ፈልገው ነበር:: ከቤተ ልሔም ደቡባዊ ምዕራብ በምትገኘው በቤዛር ከተማ 300 የአይሁድ ሕጻናት በድንጋይ ላይ ተፈጥፍጠው ተገደሉ (*መዝ.(137):8-9*): ሮማውያን የፈጸሙት ግፍ ሊገመት የማይቻል ነበር:: «ወዮ ለተሸናፊዎች» የሚለውን የሮማውያንን አባባል እናስባለን::





## የኢየሩሳሌም ፍጻሜ

ልክ እንደ 70ኛው ዓ.ም. ኢየሩሳሌም እንደገና የማታመልጥ ሆነች:: በተቃራኒው ጥፋቷ በበለጠ የሚገለጽ ሆነ:: ኢየሩሳሌም እንደ እርሻ ታረሰች:: ጌታ ስለ እየሩሳሌም መደምሰስ የተናገረው በተደጋጋሚ ተፈጸመ:: ኢየሩሳሌም እንደገና ኢየሩሳሌም ተብላ እስከማትጠራ ድረስ በአህዛብ የተረገጠች ሆነች:: ንጉሥ ሀድሪያን ከተማዋን በአራት ወረዳዎች ከፋፈላት:: ከተማዋን የሮም ወታደራዊ ቦታ አደረጋትና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከተማዋን «ኢሊያ ካፒቶሊና» ብሎ ሰየማት:: ኢየሩሳሌም የሚለው የቅድስቲቱ ከተማ ስም ለጊዜው ተደመሰሰ:: ለአራት መከፈሏ እስከ አሁን ድረስ የሚታይ ነው::

በጥንቷ ኢየሩሳሌም በየስድስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የአይሁድ የክርስቲያን፣ የአርመኒያውያንና፣ የእስላም አካባቢዎች ይገኛሉ:: የመጨረሻው የአይሁድ ህዝብ መበተን የሆነው በ135 ዓ.ም. (ከ.ክ.ል. በኋላ) ኢየሩሳሌም በተደመሰሰች ጊዜ ነው:: የእስራኤል ልጆች «እንደ እስረኛ ወደ ዓለም የተወሰዱት» ጌታ ኢየሱስ አስቀድሞ በተናገረው ትንቢት መሠረት ነው (*ሉቃ. 21:24*): ከዓለም አልተወገዱም፣ ወደ ጎንም አልተጣሉም ነገር ግን መበተናቸው በዓለም ውስጥ ሆነ:: እስራኤል የሚለው ስም በጭራሽ ዳግመኛ የማይታሰብ እንዲሆን ተደረገ (*መዝ. 83:4*): ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሮማውያን የቅድስቲቱን ምድር ፍልስጥያ (ከዚህም ፓለስታይን የሚለው ስም ተገኘ) ብለው ጠሯት::

## እስራኤል ለብዙ ክፍለ ዘመናት በውጪ ነገስታት ሥር

ከብሉይ ኪዳን ዘመን ለአምላካቸውና ለንጉሣቸው ባለመገዛታቸው ለብዙ ምዕተ ዓመታት ለባዕድ ነገስታትና፣ ባለሥልጣናት መገዛታቸውን የሚከተለው መግለጫ ያሳያል ለብዙ አመታት ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ እግዚአብሔርን ንጉሣቸው ባለማድረጋቸው በሌሎች ተገዙ:: ቀጥሎ የተዘረዘሩተ መንግሥታት በተለያዩ ጊዜያት እስራኤልን ገዝተዋል::

### 1. የባቢሎን ነገሥታት

| | | |
|---|---|---|
| 1. ናቡከደነፆር | 606/605- 562 | ከ.ል.በ |
| 2. ዪር ማርዶክ | 561- 560 | » |
| 3. ኒርግሊሶር | 559- 556 | » |
| 4. ላባሲ ማሮዶክ /ለ3 ወራት/ | 556 | » |
| 5. ናቦኒ ደሱ | 555- 538? | » |
| 6. ብልጣሶር | 538- 536? | » |

- ➢ ክ.ል.በ = ከክርስቶስ ልደት በፊት ማለት ነው።
- ➢ ክ.ል.በኋ = ከክርስቶስ ልደት በኋላ ማለት ነው።
- ➢ በጥያቄ ምልክት (?) የጠቀሱት ዘመናት በአንዳንድ የታሪክ መጽሐፍት የተሰያዩ ስለሆኑ ነው።

## 2. የሜዶንና የፋርስ ነገሥታት

| | | |
|---|---|---|
| 1. ኮሬሽ /ቂሮስ/ | 538/36- 530 | ክ.ል.በ |
| 2. ካምቢሰስ | 529- 522 | » |
| 3. ባርዲያ (ለ6ወራት/ናቡከደነፆር3ኛ /ለ3 ወራት/ | 522 | » |
| 4. 4ኛው ናቡከደነፆር /3ወራት/ | 521 | » |
| 5. ቀዳማዊ ዳርዮስ | 521 - 486 | » |
| 6. ቀዳማዊ ዘራክሰስ /አሽዌሮስ/ | 485 - 465 | » |
| 7. ቀዳማዊ አርጤክስስ | 465 - 424 | » |
| 8. ዳግማዊ ዳርዮስ | 423 - 405 | » |
| 9. ዳግማዊ አርጤክስስ | 404 - 359 | » |
| 10. ሳልሳዊ አርጤክስስ | 358 - 338 | » |
| 11. አርሳክስ | 337 - 336 | » |
| 12. ሳልሳዊ ዳርዮስ | 335 - 333 | » |

## 3. የግሪክ መንግስት ነገስታት - የዲዮዲቺ ኢምፓየር

| | | |
|---|---|---|
| 1. ትልቁ እስክንድር | 333-323 ዓ.ዓ. | |
| *ከ323 ዓ.ዓ. በፊት ጀምሮ በግብፃውያን አገዛዝ ሥር የተገዙበት* | | |
| 2. ቀዳማዊ ኘቶሎሚ ሶተር | 323 - 282 | ክ.ል.በ |
| 3. ዳግማዊ ኘቶሎሚ ፊላደልፊስ | 282 - 246 | » |
| 4. ሳልሳዊ ኘቶሎሚ ኢውርጌትስ | 246 - 222 | » |
| 5. አራተኛ ኘቶሎሚ ሎፓተር | 222 - 205 | » |
| 6. አምስተኛው ኘቶሎሚ ኢጲፋነስ | 204 - 180 | » |
| 7. አራተኛ ኘቶሎሚ ፊሎሜቶር | 180 - 145 | » |
| ከ180 - 175 በሦርያ አገዛዝ ሥር የተገዙበት | | |
| 8. አራተኛው ሴሉከስ ፊሎፓተር | 187 - 175 | ክ.ል.በ |
| 9. አራተኛው አንቲዎክስ ኢፒፋነስ | 175 - 163 | » |





መቃባውያን ከሶርያውያን ጋር ከ 175 ክ.ል.ቢ ጀምሮ መዋጋት ጀመሩ። ይህም ካህኑ መቃቢስ /ማታቲስ/ እና አምስት ልጆቹ ነበሩ። እነርሱም በጦርነቱ ሞቱ። ከዳዊት ሐረግ ባይሆኑም እንደ ንጉሥ በመሆን ገዙ።

| | | |
|---|---|---|
| 1. ማታቲያስ /መቃቢስ/ አባት | በ166 ክል.በ ሞተ። | |
| 2. ኤልአዛር /ልጁ/ | 161 ክ.ል.በ በጦርነት ላይ ሞተ። | |
| 3. ይሁዳ መቃቢስ /ልጁ/ | 161 ክ.ል.በ በጦርነት ላይ ተገደለ። | |
| 4. ዮሐንስ /ልጁ/ | በ160 ክ.ል.በ በሰው ተገደለ። | |
| 5. ዮናታን /ልጁ/ | 143 ክ.ል.በ በሰው ተገደለ። | |
| 6. ስምዖን /ልጁ/ | 134 ክ.ል.በ በመርዝ ተገደለ። | |
| 7. ዮሐንስ ሐይርካኑስ | 134- 104 | ክ.ል.በ |
| 8. ቀዳማዊ አርስቶቡሉስ | 104- 103 | » |
| 9. እስክንድር ጃናኡስ | 103- 76 | » |
| 10. ሰሎሜ አሌክሳድራ | 76 - 67 | » |
| 11. ዳግማዊ አርስቶቡለስ | 67 - 63 | » |
| 12. ሳልሳዊ ሀይርካኑስ | 63 - 40 | » |
| 13. አንቲጎኖስ | 40 - 37 | » |

## 4. የሮም ነገሥታትና ገዢዎች

| | | |
|---|---|---|
| 1. ፖምፔ ኢየሩሣሌምን ወግቶ የያዛት 63 | ክ.ል.በ | |
| 2. ንጉስ ሄሮድስ | 40/37-4 | » |
| 3. ንጉስ አርኬላዎስ | 4/-6 | ዓ.ም. ክ.ል.በኋላ |
| የሮም ገዢዎች /መስፍንት/ | | |
| 1. ኮፖኒዩስ | 6- 9 | ዓ.ም (ክ.ል.በኋላ) |
| 2. አምቢዩስ | 9- 12 | » |
| 3. አኒዩስ ሩፉስ | 12- 15 | » |
| 4. ቫሊሪዩስ ግራቱስ | 15- 26 | » |
| 5. ጴንጤናዊው ጲላጦስ *(ማቴ. 27:1-2)* | 26- 36 | » |
| 6. ማርሴሉስ | 36- 37 | » |
| 7. ሂራኒዩስ ካፒቶ | 37- 41 | » |
| /ንጉስ አግሪጳ (ሐሥ.12:1-2) | 41- 44 | » |
| 8. ኩስፒስ ፋዱስ | 44- 46 | » |
| 9. ጢባርዩስ ጁሊየስ | 46- 48 | » |
| 10. ቨንቲዲዩስ ኩማኑስ | 48- 52 | » |
| 11. አንቶኒየስ ፊልክስ *(ሐሥ.23:24)* | 52- 60 | » |

12. ጵርቅዮስ ፊስጦስ (*ሐሥ.24:27*) 60- 62 »
13. ቀላውዲዎስ አልቢኑስ 62- 64 »
14. ጊስዩስ ፍሉሩስ 64- 66 »

በ66 ዓ.ም የአይሁድ ጦርነት ተነሳ በ70 ዓ.ም ኢየሩሳሌም ተደመሰሰች:: የእስራኤል ህዝብ በዓለም ተበተኑ::

*የሮማውያን ነገሥታት*

1. አውግስጦስ (*ሉቃ.2:1*) 27 ዓ.ዓ. - 14 ዓ.ም(ከ.ል.በኋላ)
2. ጢባርዩስ (*ሉቃ.3:1*) 14- 37 »
3. ካሊጉላ 37- 41 »
4. ቀላውዲዎስ (*ሐሥ.18:2*) 41- 54 »
5. ኔሮ 54- 68 »
6. ጋልባ / ኦቶ ቢቴሊስ / 68- 69 »
7. ቬስፓሲያን 69- 79 »
8. ቲቶስ 79- 81 »
9. ዶሚቲያን 81- 96 »
10. ኔርቫ 96- 98 »
11. ትራጃን 98-117 »
12. ሀድሪያን 117-138 »

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው አይሁድ ለመጨረሻ ጊዜ ከ132-135 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) በሮም ላይ አመጹ:: በዚህም አመጽ ግማሽ ሚሊዮን አይሁድ ተገደሉ:: ኢየሩሳሌም በተጨማሪ ለአንድ ጊዜ ተደመሰሰች:: ንጉሱ ሀድሪያን «ኤሊያ ካፒቶሊና» የተባለች የአህዛብ ከተማ ስራ በመጨረሻም ኢየሩሳሌም በአህዛብ ተረገጠች:: እስራኤላውያን ወደ ዓለም ሁሉ በምርኮነት ተበታተኑ (*ሉቃ.21:24*):

30 ዓ.ም ፣ 70 ዓ.ም እና 135 ዓ.ም (ከ.ል.በኋላ) በደህንነት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ያላቸው ዓመታት ናቸው:: በአስተምህሮአችን ለረጅም ምዕተ ዓመታት የአይሁድን ህዝብ መዋረድ ያመለክቱናል:: ለ100 ዓመታት ምድራዊ ነገስታት የእስራኤልን ልጆች አዋርደዋል:: መሲሁን በመቃወምና ለመጨረሻ የአይሁድ ህዝብ በዓለም መበተን መካከል *100* ዓመታት ጠፍተዋል::

*ለ100 ዓመታት* የእሥራኤል *ታሪክ* እየደከመ መሄዱን ቀጠለ:: የአይሁድ ህዝብ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ማጣት ብቻ ሳይሆን ቤተ መቅደሱን ቅድስቲቱ ከተማቸውንና በጠቅላላ ሀገራቸውን አጥተዋል:: (በእግዚአብሔር የዓለም ታሪክ ሰዓት ጠቋሚዋ ዝቅተኛ ነጥብ ላይ ደርሳ ቆመች::)






## 2. እስራኤል ተበትና በነበረችበት ዘመን

*«ምድሪቱንም የተፈታች አደርጋለሁ የሚቀመጡባትም ጠላቶቻችሁም ከእርስዋ የተነሳ ይደነቃሉ:: እናንተም ከአህዛብ መካከል እበትናችኋለሁ፣ ሰይፍንም አስመዝዝባችኋለሁ፣ ምድራችሁም የተፈታች ትሆናለች፣ ከተሞቻችሁም ባድማ ይሆናሉ (ዘሌ.26:32-33)::*

*«በእነዚህ አህዛብ መካከል ዕረፍት አታገኝም፣ ለእግርህም ጫማ ማረፊያ አይሆንም፣ በዚያ እግዚአብሔር ተንቀጥቃጭ ልብ፣ ፈዛዛ ዓይን ደካማም ነፍስ ያመጣብሃል:: ነፍስህም ታመነታለች፣ ሌሊትና ቀንም ትፈራለህ፣ በህይወትህም አትታመንም» (ዘዳ.28:65-66)::*

ለ1800 ዓመታት የእሥራኤል ልጆች በዓለም ህዝብ መካከል ተበታተኑ:: ብዙ ጊዜ በአስፈሪ ሁኔታ ስር መኖሪያ እንደሌላቸው ሆነው እንዲኖሩ ተገደዱ:: ለብዙ ዓመታት ሰላምን አጡ:: በአንፃሩ ግን ሊገመት የማይቻል ስቃይ ደረሰባቸው ተሰደዱ፣ ተጣሉ ፣ተጨነቁ ተንቀውም ተገርፈዋል:: እግዚአብሔር የሰጣቸው ምድር በውጭ ገዢዎች እጅ ተደመሰሰች፣ ጌታ ኢየሱስ በምድር በነበረ ጊዜ እንደተነበየው ምድራቸው የተጣለ ሆነ (*ማቴ.23:38*): ለ1800 ዓመታት በመበታተን ጊዜያቸው እስራኤላውያን በአሕዛብ የተረገጡ ሆኑ:: ከ70 ዓ.ም. በአድናቆት እስከተመለሱበት እስከ 19ኛው ምዕተ ዓመት (*ሉቃ.21:24*) የሚቅጥለው ሥዕላዊ መግለጫ እግዚአብሔር ቅድስቲቱን ምድር እንዲረግጡአት የፈቀደላቸውን ሕዝቦች ዝርዝርና *በሉቃ.21:24* የተተነበየውን አሳዛኝ እውነት አስረግጦ ያሳያል::



## የአህዛብ ኢየሩሳሌምን መርገጥና ለማጥፋት መፈለጋቸው

### 1. ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት

1492 ወይም 1502 -- 1448 የእሥራኤል ህዝብ ከግብፅ ወጡ። ፈርዖንና ሠራዊቱ በቀይ ባህር ውስጥ ሰመጡ፣

1452 ከ1052 በመጀመር በመሳፍንትና በነገሥታት ዘመን ሞአባውያን፣ ምድያማውያንና ፍልስጥኤማውያን እስራኤልን ለማጥፋት ፈለጉ፣

1052 ሳዖል ንጉስ ሆነና እስከ 1012 ለ 40 ዓመታት ገዛ፣

1012 ዳዊት በይሁዳ ላይ ለ 76 ዓመት ተኩል ነገሰ፣

1004 ዳዊት ኢየሩሳሌምን አሸነፈና በመላ እሥራኤል ላይ ለ33 ዓመታት ነገሠ፣

972 ሰሎሞን ለ 40 ዓመታት በእሥራኤል ላይ ነገሰ ቤተ መቅደሱንም ሠራ፣

932 በነገስታት ዘመን ግብጻውያን ፣ ሶርያውያን ፣አሞናውያን፣ ሞአባውያንና አሦራውያን የእሥራኤልን ነገድ ለማጥፋት ሞከሩ፣

722 የሰሜኑ የእሥራኤል መንግስት ተደመሰሰ፣አስሩ የሰሜን ነገዶች በአሶራውያን ምርኮኞች ሆነው ተወሰዱ፣

606 ለመጀመሪያ ጊዜ አይሁድ ወደ ባቢሎን ተማረኩ፣

597 አይሁድ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ባቢሎን ተማረኩ፣

586 ለሦስተኛ ጊዜ አይሁድ ወደ ባቢሎን ተማርከው የይሁዳ መንግስት ተደመሰሰ፣ ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምንና ቤተ መቅደሱን አፈረሱ።

536 የባቢሎን መንግስት ተደመሰሰ ፣ የሜዶንና የፋርስ ነገስታት የዓለም ገዢ ሆኑ፣የአይሁድ ህዝብ እንዲመለሱና ቤተ መቅደሱ እንዲሰራ ፈቀዱ፣

516 ሁለተኛው ቤተ መቅደስ ታድሶ ተመረቀ፣

451 በ445 ነህምያ እንደገና የኢየሩሳሌምን ቅጥር ሠራ፣

333 ግሪክ በትልቁ እስክንድር በመመራት በዓለም ኃያል ሆነች፣ በ332 እሥራኤል በግሪክ አገዛዝ ስር ወደቀች፣

312 እስራኤል በግብጽ ይገዙ በነበሩት በግሪክ (በፓቶሎሚክ) ነገሥታት ሥር ሆነች፣

198 እስራኤል በሦሪያ ሴሉሳውያን ሥር ሆነች፣

167 የሦርያው ንጉስ አንቲዖክስ ኤርፋነስ ኢየሩሣሌምን አሸንፎ የጥፋት ርኩሰትን በቤተ መቅደስ ተከለ፣





164 መመሪቅ ኢየሩሣሌምን አሸነፈና ቤተ መቅደሱ ታደሰ። /የቤተ መቅደሱ (ቻኑካ) በመባል ይታወቃል /(ዮሐ.10:22)።

142 የመቃባውያን ነገሥታት ለ100 ዓመታት ያህል እሥራኤልን መሩ፣

63 የሮሙ ጄኔራል ፓምፔ ኢየሩሣሌምን አሸነፈ፣

40 ኤዶማዊና አረባዊ የሆነው ሄሮድስ በእሥራኤል ላይ ንጉስ ሆነ፣

06 ወይም 07 ጌታ ኢየሱስ በቤተ ልሔም ተወለደ፣

04 ሚያዝያ 2 ቀን ሄሮድስ በኢያሪኮ ሞተ ልጁ አርኬላዎስ በእሥራኤል ላይ ንጉሥ ሆነ (ማቴ. 2:22)።

### 2. ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላ

06 አርኬላዎስ ከመንግስቱ ተሻረ፣ ይሁዳ በሮም ጠቅላይ ግዛቶች ላይ ነገሰ

06-66 የሮም ገዢዎች ምድሩን ገዙ፣

26-36 ጴንጤናዊው ጲላጦስ በይሁዳ ላይ መሪ ሆነ፣

18-37 ዮሴፍ ቀያፋ በኢየሩሳሌም የሊቀ ካህንነቱን ቦታ ያዘ፣

33 የክርስቶስ ኢየሱስ ስቅለትና ትንሣኤ ፣ የመንፈስ ቅዱስ መውረድና የቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ሆነ፣

66-73 አይሁድ በሮማውያን ላይ አመጹ፣ /የአይሁድ ጦርነት/ ሮማውያን 1.1 ሚሊዮን የሚሆኑ አይሁድን ገደሉ ፣

70 በሮሙ ጄኔራል ታይተስ በመመራት ሮማውያን ኢሩሳሌምን አሸነፉ፣ ነሐሴ 10 ቀን ቤተ መቅደሱን ደመሰሱ 600.000 አይሁዶችን ገደሉ፣

73 ከሦስት ዓመት ትግል በኋላ በሙት ባህር አጠገብ ያሰችውን፣ ማሳዳን ሮማውያን አሸነፉ፣ሚያዝያ 15 ቀን 960 አይሁድ ራሳቸውን ገደሉ፣

132 ሦስቱ የባርኮቺባ የዓመጽ ዓመታት ጊዜ ሮማውያን 500.000 አይሁድን ገደሉ፣

135 ንጉሱ ሀድሪያን ኢየሩሳሌምን የአህዛብ ከተማ በማድረግ «አይላ ካፒቶላ» ብሎ ሰየማት፣

135 ሮማውያን ቅድስቲቷን ምድር እስከ 326 ዓ.ም.(ክ.ል.በኋላ)ድረስ ገዟት፣

326 በባዛንቲን አገዛዝ ስር እስከ 632 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም የክርስቲያን ከተማና

638 በካሊፍ ኡመር መሪነት አረቦች ቅድስቲቱን ከተማ አሸነፉ፣

687 የኡመር መስጊድ /ዱም ኦፍ ሮክ/ በአራት አመት ጊዜ ውስጥ በኢየሩሳሌም ከነበረው ቤተ መቅደስ ተራራ ላይ ተሰራ፣

711 የኤል-አስካ መስጊድ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ተራራ ላይ ተሰራ፣

750 ከባግዳድ የተነሳው ሙስሊም አባሲድ ኢየሩሳሌምን አሸነፈና ቅድስቲቱን ምድር አስደተዳደረ።

996 እስከ 1071 ፋቲሚድስ በኢየሩሳሌም ላይ ገዙ፣

1071 እስከ 1099 ሴልጁኮች በቅድስቲቷ ምድር ላይ ገዙ።

### 3. የመስቀል ጦርነት ዘመን

1095 ሊቀ ጳጳስ ዳግማዊ አርባን ህዳር 27 ቀን በፈረንሳይ በስተደቡብ በምትገኘው በክሌርሞንት የመጀመሪያውን የመስቀል ጦርነት ጥሪ አደረጉ። የ 200 ዓመታት የአይሁድ ስደት ጅማሬ መነሻ ሆነ።

1099 ወደ ኢየሩሳሌም በተደረገው ጉዞ የመስቀል ጦርነት ተዋጊዎች ከ100. 000 በላይ አይሁድንና እስላሞችን ገደሉ። በሐምሌ 15 ቀን ኢየሩሳሰምን አሸንፈው በያዙበት ጊዜ 65.000 አይሁድና እስላሞችን ገድለዋል።

1099 ጎድፍሪይ የቦውይኑ የጌታን መቃብር ጠባቂ ሆነ ፣

1100 የመስቀል ጦረኞች በሃይፋ ያሉትን አይሁድ በሙሉ ገደሉአቸው።

1101 የቦስኙ ቀዳማዊ ባልድዊን የኢየሩሳሌም ንጉስ ሆነ ፣

1118 የሊቦርጉ ዳግማዊ ቦልዊድን በኢየሩሳሌም ገዛ ፣

1131 የአንጂ ፉልክ በኢየሩሳሌም ላይ ገዛ ፣

1143 ሳልሳዊ ቦልድዊን በኢየሩሳሌም ላይ ንጉስ ሆነ ፣

1147 ሁለተኛው የመስቀል ጦርነት ጀመረ ፣ ብዙ አይሁድ ተገደሉ።

1162 የሊቦርጉ አማላሪክ የአየሩሳሉም ንጉስ ሆነ ፣

1174 አራተኛው ቦልድዊን በኢየሩሳሌም የበላይ ገዢነቱን ወሰደ ፣

1187 በገሊላ ባሰችው የሃቲን በሆነችው ሆርን በተባለችው ቦታ የኩረዱ ሱልጣን ሳላዲን የመስቀል ጦረኞችን በጅምላ ግድያ ደመሰሳቸው።

1187 ሰላዲን በኦክቶበር 2 ኢየሩሳሌምን በመያዝ የ88 ዓመት የፈረንሳይ መስቀል ጦረኞችን ግዛት አስቆመ።

1189 አውሮፓውያን በንጉስ ባርባሮሳ መሪነት በሦስተኛው የመስቀል ጦርነት መልሰው ኢየሩሳሌምን ድል ለማድረግ መከሩ፣

1202 አራተኛ የመስቀል ጦርነት ልጆችን ያቀፈ ነበር ፣

1228 በዳግማዊ ንጉስ ፍሬድሪክ አምስተኛው የመስቀል ጦርነት ተመራ ፣

1241 እንደ ገና የመስቀል ጦረኞች ኢየሩሳሌምን አሸነፉ ፣





1244 ሙስሊሞች ለዳግመኛ ጊዜ ኢየሩሳሌምን አሸነፉ ፣

1248 ዘጠነኛው የፈረንሳይ ንጉስ ሉዊስ ስድስተኛውን የመስቀል ጦርነት መራ፣

1260 የማምሉክ ሱልጣን ባይባረስ ቅድስቲቷን ምድር አሸነፈ፣

1291 ማምሉኮች የመስቀል ጦረኞችን አስወጡ ፣

1291 እስከ 1517 ድረስ ማምሉኮች ቅድስቲቷን ምድር ገዙ።

### 4. የመካከለኛው ዘመን

1400 ማንጎሳውያን በታማርላን መሪነት ቅድስቲቱን ምድር ደመሰሱ፣

1517 የቱርክ ቀዳማዊ ሱልጣን ሳሌም ኢየሩሳሌምን አሸነፈ፣

1517 እስከ 1417 ቱርኮች ቅድስቲቱን ምድር አስተዳደሩ፣

1537 እስከ 1541 የቱርክ ሱልጣን ትልቁ ሱሌይማን እስከ ዛሬ የሚታየውን የኢየሩሳሌምን ከተማ ቅጥር ሠራ፣

1799 ናፖሊዮን ቅድስቲቱን ከተማ ለማሸነፍ ፈልጎ ሙከራው ውጤት የሌለው ሆነና ቱርኮችን በሚጊዶ አጠገብ ተዋጋቸው፣

1832 የግብጽ ኪዳቭ ፓለስታይንን አሸነፈ፣

1840 ቅድስቲቷን ምድር ካወጡት ከአውሮፓ የበላይ ሃይሉች ቱርኮች እርዳታ ጠየቁ፣

1846 ከ700 አመታት በኋላ ሙስሊሞች የመጀመሪያውን ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም እንዲሰራ ፈቀዱ።

1860 ሰር ሙሴ ሞንቴፎር ከተማይቱን እንዲሰሩ የአይሁድ ሕብረት ፈጠረ፣

1882 በፓለስታይን የመጀመሪያው የአይሁድ መስፈር ሆነ፣

1894 የድሬፉስ ፍርድ በአውሮፓ ያሉትን አይሁድ አናጋ፣

1896 ቴዎድሮ ሀርዝል « ዘ ጁዊስ ስቴት » የተባለውን መጽሐፍ አሳተመ፣

1897 ቴዎድሮ ሀርዝል ከነሐሴ 29 ቀን እስከ ነሐሴ 31 ቀን በባሲል የተደረገውን የጽዮናውያን ኮንግሬስ ጥሪ አደረገ፣ በስብሰባውም 199 አባሉች ተሰበሰቡ፣

1898 ጥቅምት 31 ቀን የሚመረቀው የአዳኙን ቤተ ክርስቲያን ለመመረቅ ግርማዊ ንጉስ ዊልሂለም ኢየሩሳሌምን ጎበኘ፣

1917 ፓለስታይን የአይሁድ ምድር መሆኑን ተስፋ የሰጠውን የባልፎሩን ዲክላሬሽን በህዳር 2 ቀን የእንግሊዙ ፓርላማ አሳተመ፣

1917 ታህሳስ 9 ቀን እንግሊዞች ወደ ኢየሩሳሌም ገቡ፣ይህም ለ 400 ዓመታት የቆየውን የቱርክን አገዛዝ እንዲያከትም አደረገው፣

1918 የእንግሊዝ ወታደሮች ጠቅላላውን የቅድስቲቱን ምድር አሸነፉ፤

1922 ዘ ሊግ ኦፍ ኔሽንስን /ዛሬ የተባበሩት መንግስታት የተባለው/ በፓሊስታይን ላይ ያለውን ሞግዚትነት ለእንግሊዞች በሐላፊነት ሰጡ። በግንቦት 15 ቀን 1984 ተግባራዊ ሆነ፤

1947 ህዳር 29 ቀን የተባበሩት መንግስታት ፓለስታይንን ለመክፈል ወሰኑ፤

1948 ግንቦት 14 ቀን ዳዊት ቤን ጉርዮን በአቪብ ከተማ ባለው ሙዝዬም የእስራኤልን ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ አወጀ፤

1967 በስድስቱ ቀን ጦርነት እስራኤል ጠቅላላ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀለላቸውን ምድር አሸንፈው ያዙ። ኢየሩሳሌም ማንም የማይጋራቸው ዋና ከተማቸው ሆነች።

## 5. የፍርሃትና የጥፋት ሚዛን

1017 ፖኘ ቤንዲክት ስምንተኛው አይሁዶች በሮም ራሳቸው እንዲቆረጥ ፈቀዱ፤

1020 ፓፕ ቤንዲክት ስምንተኛው አይሁዶች በሮም እንዲቃጠሉ ፈቀደ፤

1066 አይሁድ በእስፓኝ በአሰቃቂ ሁኔታ ተገደሉ፤

1095 ፓፕ አርበን ዳግማዊ በፈረንሳይ በስተ ደቡብ በምትገኘው ኬሌርሞንት ህዳር 27 ቀን የመጀመሪያውን የመስቀል ጦርነት ጥሪ አደረገ። ይህም ለ200 ዓመታት የአይሁድ ስደት ጅማሬ መነሻ ሆነ።

1096 በመጀመሪያው የመስቀል ጦርነት በሲኒካን የጦር መሪ በጀርመን ከተሞች ምርም፤ ጊልደን፤ከርጽን፤ዌስል፤ኒዩስ፤ሞርስ፤ ግደርቪንቡሮች፤ዙንታን፤ ቦን፤ ኮሎኝ፤አልቴናር፤ ሜይንዝ፤ ስፔይር፤ ትሪይናርና፤በሌሎቹ ከተሞች ሊሲሲንግ ፤ መኳንንት መሪዎች ከ 12,000 በላይ አይሁዶች ተገደሉ።

1096 የመስቀል ጦረኞች በፕራግ ያሉትን የጅምላ ግድያ ፈጸሙባቸው፤

1171 በፈረንሳይ በብሉይዝ ያሉት አይሁዶች በመቃጠል ተገደሉ፤

1179 ፓፕ ኢኖሰንት ሳልሳዊ በላተራን ጉባኤ አይሁድ በራሳቸው ክልል /ጌቶስ/ እንዲቀመጡ አዘዙ፤

1189 በሦስተኛው የመስቀል ጦርነት ጊዜ በእንግሊዝ ከተማዎች አይሁዳውያን ታርደው ተገደሉ።

1194 በጀርመን ከተማ በኒዮስ የአይሁዳውያን ቤተሰብ የሆኑ እናትየው ከነህይወትዋ ስትቀበር አጎትየው በግርፋት እንዲሰቃይ ተደረገ ፤

1209 በፈረንሳይ በቢዚየር የሚኖሩት አይሁዳውያን በሙሉ ተገደሉ ፤





1215 በአራተኛው የላተርን ጉባኤ ላይ ፖፕ ኢኖሰንት ሳልሳዊ ማንኛውም አይሁዳዊ አንድ ዓይነት ልብስ/የዳዊት ኮከብ ያለበት ባጅ/ /ዩኒፎርም/ እንዲለብሱ አዘዙ

1221 በጀርመን በኢርፉት የአይሁድ መኖሪያ ተደመሰሰ ፤አይሁዳውያን በሙሉ ተገደሉ፤

1241 በጀርመን በፍራንክፈርት የነበረው የአይሁድ ቦታ ተወሰደ ፤ 200 አይሁዳውያን ተገደሉ ፤

1247 በፈረንሳይ በቫለረስ የነበሩት አይሁድ በሙሉ ተገደለ ፤

1265 በጀርመን በራይን ወንዝ አጠገብ ባለችው በሲንዚንግ ከተማ ያሉት አሁዳውያን በሙሉ ድራሻቸው እንዲጠፋ ሆነ ፤

1270 በዊለንበርግ ፤ ያሉት አይሁዳውን በሙሉ ተገደሉ ፤

1278 በኢንግላንድ የነበሩት 300 የአይሁድ መሪዎች ተሰቀሉ፤

1283 በጀርመን ከተሞች በከሩዝናች ፤ በሜይንዝ ሜልሪች ስታድ አይሁዶች በጅምላ ተገደሉ ፤

1285 በሙኒች ምኩራብ የነበሩት አይሁዳውያን ተቃጠሉ ፤

1287 በጀርመን ከተማዎች በዌስል ፤ ቦፓርድ ፤ በኮርበን ፤ በናሂ ባለችው በኪርን ፤ ለሐንስቲን ፤ በራሂን ባለችው በቡራውባችና ሙንስትር ማይፊልድ ያሉት በሙሉ በጅምላ ተገደሉ፤

1288 104 አይሁዳውያን በጀርመን በቦን ከተማ ተገደሉ ፤

1289 በፈረንሳይ በትሮይስ 13 አይሁዳውያን ተቃጥለው ተገደሉ ፤

1290 በቀዳማዊ ንጉስ ኢድዋርድ ትዕዛዝ ከኢንግላንድ አይሁድ እንዲወጡ ተደረጉ

1298 በናይት ሪንደፍሊሶች በተደረገው ስደት በደቡባዊ ጀርመንና በአውስትሪያ 146 ማህበረ አይሁድ ተደመሰሱ። ከ20,000 በላይ አይሁዳውያን ተገደሉ። ግድያ የተፈጸመባቸው ዋናዎቹ የጀርመን ከተማዎች ኑርበርግ፤ባምበርግ፤ ሮቷንጃን፤በርቼንግ፤ከሩዚም፤ሞሰባች፤አቼስንፈርትዎዝንበርግ፤ ዊንድዚም ፤ ዊንድዚም ፤ ሮተንበርግ፤ታውጅንና ሌሎችም ነበሩ።

1306 በዳግማዊ ፊልጶስ ከፈረንሳይ አይሁዶች እንዲወጡ ተደረጉ ፤

1321 5000 አይሁዳውያን በደቡባዊ ፈረንሳይ ተገደሉ ፤ በቺኖን የነበሩት አይሁዳውያን ማህበር ተቃጥለው ተገደሉ ፤

1328 በናቪር በፈረንሳይ 5000 አይሁድ በጅምላ ተገደሉ ፤

1332 በከንስታን ሀይቅ ባለችው አርበርሊንገር 400 አይሁዳውያን ተቃጠሉ ፤

1337 በዲጀንደርፍ (በባሪያ ባለችው) የሚኖሩት አይሁዳውያን በጅምላ ተገደሉ፣

1348 በመላ ኢሮፕ / በስፓኝ ፣ በፈረንሳይ . . . ወዘተ. / የቸነፈሩ ምክንያት በክንስታን ሀይቅ ባለችው በሊንዳ የሚኖሩት ፣ በኒክር ባለችው ሆርብ ፣ ኢስሊንግ ፣ ሩትሊንግ ፣ አውግስበርግ ፣ ኮልማርና ኑርበርግ የነበሩት የጀርመን አይሁዳውያን ማህበር ተደመሰሱ::

1349 በቸነፈሩ ምክንያት የአይሁዳውያን ስደት በጀርመን ከተሞች በብርስለው፣ በዊትዝላር፣ሜይንዝ፣ስኮሎኝ፣በራደልፍሩል፣በውዝበርግ፣በፍርድሪችሻፈር፣ በማይን ፍራንክፈርት፣ በድርስዲን፣ በፍልዳ፣በራቬንስበርግ፣ በክንስታን በስፔየር፣በኢለም፣በፍርበርግ፣በስታራስበርግና ስዊስ ከተሞች በዊንተርሁር፣ በዲሲንሆፈን፣ በቻፍሐውሰን፣ በዙርጋ፣ በዙሪች፣ በባዲን፣በሪሁን ፊደን፣ በቅድስት፣ ጋለን፣ በባሴልና በእሚንታል /በሮን/ ተሰራጩ::

1349 2,000 አይሁዳውያን በስትራስበርግ በአደባባይ በህዝብ ፊት ተቃጠሉ::

1355 ፓፓ ቤንዲክት 12ኛው ፐሯግ ያለው የአይሁድ ምኩራብ እንዲፈርስ ፈቀዱ፣

1391 በስፓኝ ባለችው በሲቬላ 5000 የአይሁዳውያን ቤተሰቦች ተደመሰሱ:: 23 የአይሁድ ምኩራቦች ተደመሰሱ::

1391 በዳንዮብ ወንዝ አጠገብ ባለችው በኢንዝ የጀርመን ከተማ 200 አይሁዳውያን ተቃጠሉ::

1391 በመጀመሪያው ሃይለኛ በሆነው የስፔን አይሁዳውያን ስደት ጊዜ በማቃጠያው ስፍራ 20,000 የሚሆኑ አይሁዳውያን በእሳት ነደዋል::

1404 በአውስትሪያ ባለችው በስልዝበርግ የነበሩት አይሁድ በሙሉ ተቃጠሉ፣

1421 212 አይሁዳውያን /ወንድና ሴት/ በቪና አውስትሪያ ተቃጠሉ፣

1478 ግልጽ የሆነው የእስፓኝ ምርመራ ጅማሬ፣

1483 በብዙ የስፓኝ ከተማዎች በካቶሊኮች በተደረገው ምርመራ 30,000 አይሁዳውያን በግልጽ በአደባባይ ተቃጠሉ::

1492 የአርጉኑ ዳግማዊ ፈርዲናንድና የካስቲሏ ኢሳቤላ አሁዳውያን በሙሉ ከእስፓኝ እንዲወጡ አደረጉ ፣

1494 የጳጳሱን አዋጅ በመከተል በብዙ ሺ የሚቆጠሩ አይሁዳውያን ጠንቋዮች ናቸው ተብለው በመገመታቸው በብዙ የአውሮፓ ከተሞች በጭካኔ ተገደሉ::





1496 በንጉሥ ማግማክስ ሚላን ቀዳማዊ መላ አይሁድከኦስትሪያ እንዲወጡ ተደረጉ::

1497 አይሁዳውያን በሙሉ ከፖርቱጋል እንዲወጡ ተደረጉ፣

1501 በስፓኝ ባለችው ቶሊደ ብዙ አይሁዳውያን ተቃጠሉ፣

1504 በሩሲያ ሞስኮ የታወቁት አይሁዳውያን በሙሉ ተቃጠሉ፣

1506 በፖርቱጋል ሊስበን 2000 አይሁዳውያን ተደብድበው ተገደሉ፣

1510 በጀርመን በርሊን 38 አይሁዳውያን ተገረፉና ተቃጠሉ፣

1574 በሜክሲኮ 897 አይሁዳውያን በአደባባይ ተቀጠሉ፣

1614 በጀርመን በፍራንክፈርት የአይሁዳውያን ቦታ ተደመሰሰ፣

1648 በቦግዳን ቺ ሚሊኒኪ፣ በሩሲያውያን፣ በኮሳኮች በዩክራውያን 12,000 አይሁዶች በጅምላ ተገደሉ፣

1648 በፓላንድ ውስጥ ባሉት ኮሳኮች በአሰቃቂ ሁኔታ ተገደሉና ተወገዱ፣

1650 በሩሲያ ባሉት ኮሳኮች ሌሎች 200,000 አይሁዳውያን ተገደሉና ተደመሰሰ·

1670 በቀዳማዊ ሊዎፓልድ 4.000 አይሁዳውያን በኦስትሪያ ካለችው ቪና እንዲወጡ ተደረጉ ፣

1670 እስራኤላውያን ሁሉ ከሜር(ፈራንሣይ) ተባበሩ

1679 በፈረንሳይ ባለችው ሚትዝ ያሉት አይሁዳውያን እንዲወጡ ተደረጉ፣

1680 በማድሬድ /አውቶዳፍ/ በአደባባይ በእንጨት ላይ ተሰቅለው ተቃጠሉ፣

1704-1769 በሺህ የሚቆጠሩ አይሁዳውያን በፖርቱጋል ተገደሉ ፣

1728 ከሊምበርግ/ ሊቮቭ / ፋሊሺያ እንዲወጡ ሆነ ፣

1734 በፓላንድ ባሉት ጌድማኪያን ኮሳኮች 20,000 አይሁዳውያን ተገደሉ ፣

1818 በጀርመን ዎርዝበርግ ከተማ ብዙ አይሁዶች ተገደሉ፣ የቀሩት 400 እንዲወጡ ተደርጎ ሂፕ ሂፕ የሚለው የጩኸት ግሳት ፈነዳ:: ትርጓሜው ኢየሩሳሌም ታጣች (ኢየሩሳሌም ጠፋች ማለት ነው)::

1821 ወደ ብዙ የሩሲያ ከተሞችና ወደ ዩክሬይን የተዛመተው የተጠናከረው የመጀመሪያው አሰቃቂ ግድያ የተጀመረው በኦዲሳ ነው:: ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት መነሳት በፊት ብዙ አይሁዶች ሞተዋል::

1826 በእስፓኙ ምርመራ የመጨረሻው ግድያ፣

1840 በደማስቆ ያሉት የአይሁድ መሪዎች በሀሰት ተከሰሱና ብዙ ስቃይ እንዲቀበሉ ሆኑ፣ በውጤቱ ጥቂቶች ሞቱ፣

**1858** በተጠናከረው ግድያ ውጤት በሺና በሺህ የሚቆጠሩ አይሁዳውያን በሩሲያ ሞቱ ፤

**1859** የተጠናከረው ግድያ እስከ 1871 ድረስ በኦዲሳ በመደጋገም ቀጠለ፣

**1864** በሞሮኮ ቁጣ የተሞላበት ታላቅ የአይሁዳውያን ግድያ ሆነ ፣

**1867** በሩማኑያ ታላቅ የአይሁድ ስደት፣ ተደረገ።

**1881** 792 አይሁዳውያን በዩክራይን ባለች ኪቮ ለሞት ተደረጉ፣

**1881** አሰቃቂ የሆነ ግድያ በኤሊስቤት ግንድ ኡክራኢነ እና 1882 በባልታ ኡክራኢነ

**1883** ጭካኔ የተሞላበት የተጠናከረ ግድያ በደቡባዊ ሩሲያ (በደቡብ ሮስቶቭ) ተካሄደ፣

**1891** በሩሲያ ሞስኮ ያሉት አይሁዳውያን ከሃገር እንዲወጡ መደረግ ፣

**1892** በፓላንድ ሉድዝ 20 የአይሁድ ሰዎች ተገደሉ፣

**1903** በሞልዳሹያ ባሉት ኪሺኒቭና ጎሜል ጭካኔ የተሞላበት ግድያ ሆነ፣

**1905** በብላክ ሃንድረስ በተፈጠረው ምክንያት በ 700 የሩሲያና የዩክሬንያ ከተሞች የተጠናከረ ግድያ ሆነ፣

**1917** በመደጋገም በሆነው የተጠናከረ ግድያ በሩሲያና በዩክሬይን ከ1200 ከተሞች በላይ 30,000 የአይሁድ ወንዶች ፣ ሴቶችና ህፃናት ተገደሉ። ይህም እስከ 1921ዓ.ም ድረስ ቀጠለ።

**1917** በገላትያ ውስጥ ባለችው ካሉዝ አስከፊ ጭካኔ የተሞላበት ግድያ በአይሁድና በፖላንዳውያን ሴቶች ላይ ተደረገ ልጃገረዶችን በመግረፍ አሰቃዩ።

**1919** በሩሲያ ባለችው ፕሮ ኩሮቫ በተጠናከረው ግድያ 1500 አይሁዶች ለግድያ አልፈው ተሰጡ።

**1919** እስከ 1921 በዩክሬናውያን ብሔራዊ ሠራዊት ከ 100 በላይ የተጠናከረ ግድያ በማካሄዳቸው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አይሁዳውያ ተገደሉ፣

**1922** የጀርመን የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ዋልተር ራዚናው በጀርመን በበርሲን ከተማ አይሁዳዊ ስለነበር በብሔረተኞች ተገደለ፣

**1929** ፓለስታይን ውስጥ ባለችው በኬብሮን የሚኖሩት አይሁዶች በሙሉ በአረቦች ተገደሉ ወይም ሀገር ለቀው እንዲወጡ ተደረጉ፣

**1933** እስከ 1945 በመላ የአውሮፓ ከተሞች 6.5 ሚሊዮን አይሁዶች በናዚ ተገደሉ፣ ከእነዚህም 1.5 ሚሊዮን ከ14 ዓመት በታች የነበሩ ህፃናት ነበሩ።





**1936** እስከ 1939 ወደ 500 የሚሆኑ የአይሁድ ወንዶች ፣ ሴቶች ፣ ህፃናት በአረቦች በተነሳ የኑሮና የሥራ ማጣት ሁከት ምክንያት ሞቱ፣

**1941** በኢየሩሳሌም ያለው የአረቡ ሙፍቲ ሐጂ አሚን አልሁሴኒ በጀርመን የበርሊንን ከተማ ጎበኘና ሂትለርን በፓለስታን ያለውን የአይሁዶችን ሥራ በሙሉ እንዲያፈርስ ጥሪ አደረገለት ፣

**1945** እስከ 1948 በተደረገው በአረብ ጦርነትና የስደተኞች መርከቦች መስመጥ ምክንያት ብዙዎች ሞቱ ፣

**1945** እስከ 1953 በቼኮዝላቪያ የሚኖሩ አይሁዶችና ከካምንፐ የተሸነፉት ጀርመኖች አንድ ላይ እንዲሰቃዩ ተደርገው ለሞት አልፈው ተሰጡ፣ ምክንያቱም ሁሉም የጀርመን ቋንቋ ተናጋሪዎች ነበሩና።

**1948** በአምስት የአረቦች ጦር ግንባር በተደረገው የነፃነት ጦርነት 6,000 ሞቱ 9,000 ቆሰሉ/ የአረብና እስስራኤል ጦርነት / ፣

**1956** በስዊዝ ጦርነት ላይ 170 ሞቱ ፣ 700 ቆሰሉ ፣

**1967** በስድስቱ ቀን ጦርነት / በአረቦችና በእስራኤል / 800 ሞቱ 2,600 ቆሰሉ ፣

**1972** በሙኒክ በተደረገው የኦሎምፒክ ጨዋታ ላይ በአረብ ሽብርተኞች 11 እስፖርተኞች ተገደሉ፣

**1973** በሲባኖስ ከነበሩት ወታደሮች 574 ሞቱ፣ 2,780 ቆሰሉ፣

**1982** 574 የሞቱና 2780 በሌባነን ጦርነት የቆሰሉ

**1986** በኢስታንቡል ምኩራብ አምልኮት ላይ እያሉ በቱርኮች አሸባሪዎች 21 ተገደሉ፣

**1991** 2 በሮኬት ድብደባና 72 ከጎልፍ ጦርነት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሞቱ ፣

**1998** ከ1948 ዓ.ም. ጀምሮ 18,250 ወንዶችና ሴቶች በጦርነቶች ሞቱ እነዚህ ወታደሮች በ25,250 ቤተሰቦቻቸውና 62,120 በተጎዱ ወታደሮች ሀዘን ተደረገላቸው፣

**1998** ከ1948 ጀምሮ ከ 2,250 የእስራኤል ወንዶች ፣ ሴቶችና ህፃናት በአረብ አራፋት ሽብርተኖች ተገደሉ። በዓለም አቀፍ የአረብ አራፋት ሽብርተኞች 75 የእስራኤል ዲፕሎማቶች ተገደሉ።

«ደማቸውን ሳልበቀል አላልፍም» እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።(ኢዩ. 4:21)

የእስራኤል ሕዝብ ስደት እንደ ራሷ እንደ እስራኤል ታሪክ የቆየ ነው:: ለአራት ሺህ ዓመታት ያህል የዓለም ሕዝቦች በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ በእስራኤል ሕዝብ ላይ በታላቅ ቁጣ እየተቃወሙአቸው ነበር:: ከአብርሃም መመረጥ ጀምሮ እስከ አሁንም ድረስ እንደ ቀጠለ ነው:: ምንም እንኳን በ70 ዓ.ም. በሮማውያን በእስራኤል ላይ የተፈጠረው ስደት፣ እስራኤል መሲሁን ኢየሱስ ክርስቶስን ባለመቀበሏ (ማቴ.23.27-39):: ከእግዚአብሔር የሆነ ቅጣት ቢሆንም እግዚአብሔር ልጆቹ የሆኑትን የእስራኤልን ሕዝብ ጥሏቸዋል ማለት አይደለም:: በዘመናት ሁሉ በአይሁድ ሕዝብ ላይ የወረደው ጭካኔ የተሞላበት ስደትና ጥፋት፣ እንደዚሁም በሂትለር የወረደባቸው መከራ ተጨምሮ፣ እግዚአብሔር ከልጆቹ ጋር አዲስ የደህንነት ታሪክን ከማድረግ አላገደውም:: እስራኤል የእግዚአብሔርን ቅጣት ለረጅም አመታት ብትቀበልም (ኤር.46:28፤ ሮሜ.11:28-29)::

*«አንተ ባሪያዬ ያዕቆብ ሆይ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ ይላል እግዚአብሔር አንተንም ያሳደድሁባቸውን አክዛብን ሁሉ ፈፅሜ አጠፋለሁናነ አንተን ግን ፈፅሜ አላጠፋህም በህመም እቀጣሃለሁ ያለ ቅጣትም አልተውህም (ኤር.46:28)::*

ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር ዳግም የእስራኤልን ሕዝብ መቀበሉን ብቻ የሚያሳይ ሳይሆን የእስራኤልን ሕዝብ የተቃወሙትን ሁሉ የሚያጠፋ መሆኑንም ያሳያል:: የእስራኤልን ሕዝብ የሚነካ የዓይኑን ብሌን የሚነካ ነው (ዘካ.2:8፤ ዘዳ.32:10):: ይህ እስራኤልን ለሚነካ ግለሰብም ሆነ ቡድን፣ መላውን የዓለም ሕዝብ የሚያመለክት ነው:: የእግዚአብሔር ፍርድ ተመልሶ እስራኤልን የሚቃወሙትን የሚመታ ነው:: በመጨረሻም የዓለም ሕዝቦች በእስራኤል ላይ የሚያደርጉት ጦርነት በራሱ በእግዚአብሔር ላይ እንደሚደረግ ያህል ነው:: እግዚአብሔር የእነርሱ ነው፣ ኪዳኑም ለተመረጡት ሕዝቦቹ የጸና ነው:: መሲሁን ኢየሱስ ክርስቶስን ባለመቀበሏና ባለመታዘዟ እንኳን ለእነርሱ ያለው ኪዳን የጸና ነው:: እስራኤል ወደ እርሷ የተላከውን መሲሁን ኢየሱስን አውቃ ባትቀበልም እግዚአብሔር ልጆቹን አልጣለም (ሉቃ.13:34፤ሉቃ.19:42):: እስራኤል የተጠላችበትና ጦርነቶች የተካሄደባት እውነተኛው ምክንያት ለእግዚአብሔር የተመረጠች ሕዝብ በመሆኗ ነው:: እስማኤል ይስሐቅን አሳድዶታል፣ ምክንያቱም የተስፋውን ቃል ወራሽ ይስሐቅ ስለነበር ነው:: ኤሳው ያዕቆብን አሳድዶት ነበር:: ምክንያቱም ወደ መሲሁ የሚያመለክተውን ተስፋ የተሸከመው ያዕቆብ ስለ ነበር ነው:: በተመሳሳይ መልኩ ፈርዖን በግብፅ የሚወለዱትን የእስራኤል ወንዶች ልጆች ወደ ወንዝ እንዲጣሉ አደረገ:: ሃማ ደግሞ መላ የአይሁድን ሕዝብ ከሜዶንና ከፋርስ ግዛት ድራሻቸውን ለማጥፋት ፈለገ::





የዓለም ሕዝብ በዚህ በተመረጠው በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ያለው አመለካከት እስከ ዛሬ ድረስ ያልተለወጠ ነው:: ታሪክ እንደሚያሳየን በእስራኤል ላይ በተቃውሞ የተነሱት ጠላቶቿ ሁሉ ጠፍተዋል:: ገናና የነበረው የሮም መንግስት ወድቋል:: በባቢሎናውያን፣ በሮማውያንና በመስቀል ጦረኞች የተካሄዱት አስቃቂ መከራዎች የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆነችውን እስራኤልን ለማጥፋት አልቻለም:: መንግስታቸው አልፏል፣ እስራኤል ግን እስከ አሁን አለች::

## 3. የእስራኤል ሕዝብ መመለስ

19ኛው ምዕተ ዓመት በዓለም ተበታትነው ለነበሩት የአይሁድ ሕዝብ ትልቅና ድንገተኛ የሆነ ለውጥ አሳየ:: የፈረንሳይ ገዢ ናፖሊዮን በፈረንሳይ ለሚኖሩት የአይሁድ ሕዝቦች የዜግነትን መብት ፈቀደላቸው:: አስደናቂው ነገር ደግሞ ሌሎች አገሮችም ይህንኑ ተከተሉ:: በፕሩሲያ፣ በኢንግላንድ፣ በአውስትሪያና በኢጣልያ የሚኖሩት አይሁድ የዜግነት መብት ተፈቀደላቸው:: ከዚህ በፊት ያላወቁት ብዙ እድሎች የሥራ መስክ ተከፈተላቸው:: በጥቂት ጊዜ ውስጥ ብዙ አይሁዶች ነጋዴዎች፣ ዶክተሮች፣ የጦር መኮንኖች፣ የፓርላማ ተመራጮችና የመንግስት ሠራተኞች መሆን ጀመሩ:: በተከታዩ ምዕተ ዓመት በአውሮፓ ይኖሩ የነበሩት አይሁዶች የነጻነትን ኑሮ መኖር ጀመሩ::

ይህ ነጻነት በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በደህንነት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታን እንዲያገኙ አድርጓል:: ምክንያቱም አይሁዶች በመንግስታዊ ስፍራ ብዙ ከፍተኛ (ሥልጣናዊ) ስፍራዎችን ስለያዙ ነው:: ይህም አንድ ታሪካዊ ለውጥን አስከተለ:: ይህም በታሪክ መጽሐፍት «የድሬይፍዩስ ፍርድ» ተብሎ የታወቀውን ታሪካዊ ለውጥ አስገኘ::

### የድሬይፉስ ፍርድ

ይህ ፍርድ በታህሳስ 22 ቀን 1894 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) በፈረንሳይ ጦር ውስጥ በመኮንንነት ይሠራ በነበረው አይሁዳዊ መኮንን ላይ የተካሄደ ነበር:: ይህ ሰው አልፈርድ ድሬይፉዩስ ይባላል በዜግነቱ አይሁዳዊ ነበር:: በፈረንሳይ ሠራዊት ውስጥ በመኮንንነት በኋላም በጀኔራልነት ያገለገለ ነበር:: በአጠቃላይ ክሱ በሙሉ ትክክል አልነበረም:: ፍርዱ በደቡብ አሜሪካ በፈረንሳይ ጉያ ባለችው በካይን ጠረፍ በምትገኘው በዲቪል አይላንድ (ደሴት) በእድሜ ይፍታህ እስራት እንዲያሳልፍ ነበር:: ምክንያቱም ከፍተኛ የክህደት ወንጀል የፈጸመ አድርጎ የተገመተ ስለነበር ነው::የተከሰሰው ለውጭ ኃይል ማለት ለጀርመን ሰልሏል በመባል ነበር::

ይህ ብያኔ በዚያን ጊዜ መላ አውሮፓን አስደንቆ ነበር። ከዚህም ሁኔታ በ1791 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) የወጣው አይሁድን ከሌላው ሕዝብ ጋር እኩል የሚያደርገው ህግ በወረቀት ላይ ብቻ የሠፈረ ሆኖ ቀረ። በድሬይፉዩስ ላይ በተበየነው ብያኔ ምክንያት መላ አውሮፓ እንደገና በአይሁዶች ላይ ከፍተኛ ጥላቻ እንዲኖራቸው አደረገ። ጥር 5 ቀን 1895 በፈረንሳይ ጦር አካዳሚ በተደረገው አሳዛኝ ሥነ ስርዓት ላይ ከድሬይፉዩስ ልብስ ላይ የመቶ አለቅነቱ ማዕረግ ተገፈፈ፣ ሰይፉ ለሁለት ተሰበረ። በዚህም አሳፋሪ ድርጊት ከጦሩ ተወገደ። እርሱ ከጦሩ በተወገደ ዕለት ከፈረንሳይ መኮንኖችና ተመልካቾች *«ሞት ለአይሁድ፣ ሞት ለከዳተኞች»* የሚል ጩኸት አስተጋባ ።

በኦውስትሪያ ይኖር የነበረው ቴዎደር ሄርስል የተባለው አይሁዳዊ ጋዜጠኛ ለስዚህ ጩኸት መስክሯል። በቀንና በሌሊት እንቅልፍ እስከሚያጣ ድረስ በዚህ ነገር በጣም ተጨነቀ። «ሞት ለአይሁድ! ሞት ለከዳተኞች!» የሚለው ጩኸት ሕሊናውን ደግሞ ደጋግሞ የሚያስጨንቀው ሆነ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ነገር ዕረፍት የነሳው ሆነ። ቴዎድር ኸርዝል ግንቦት 2 ቀን 1860 ዓ.ም. በቡዳፔስት የተወለደ አይሁዳዊ ነበር። በ1878 በቪያና የሕግ ትምህርት ማጥናት ጀመረ። በ1884 የዶክትሬቱን ዲግሪ ከተቀበለ በኋላ ደራሲና ጋዜጠኛ ሆነ። ትዳር የመሠረተና የቦስት ልጆች አባት ነበር። ከ1891-1895 በፐርሲ ላለው ለቪያናው ኒው ፍሪ ፕሬስ ተወካይ ሆነ። በድሬይፉስ ላይ በተፈረደው ፍርድ የዓይን ምስክርና ስለ እርሱ መልእክት (ሪፖርት) የሰጠ ነበር። ይህ ፍርድ ሕይወቱን ቀየረው። በኋላ «ይህ በድሬይፉስ ላይ የተፈረደው ፍርድ ወደ ጽዮናዊነት ቀየረኝ» ብሏል። ኸርዝል ምንም እንኳን አይሁዶች የእኩልነት መብት ቢኖራቸውም ባሉበት ቦታ የማይፈለጉና የተጠሉ እንደሆኑ ተገነዘበ። ይህ ሰው አንድ ዓላማ ነበረው ይኸውም ወደ አባቶቻቸው ምድር ወደ እስራኤል መመለስ የሚል ነበር። ወደ ቪያና በተመለሰ ጊዜ በአይሁድ እጅግ ተወዳጅ የሆነውን «የአይሁድ ግዛት» የሚለውን መጽሐፍ በጥር ወር በ1896 አሳተመ። ብዙዎች አስተያየታቸውን መቀየር ጀመሩ። ከኸርዝል ሌላ ሌሎች ግለሰቦች ጸሐፊዎች፣ ዶክተሮች የአይሁድ ሕዝብ ወደ ቅድስት ምድራቸው እንዲመለሱ ጥሪ ማድረግ ጀመሩ።





## በእግዚአብሔር የሰዓት መቁጠሪያ ላይ ያለችው ሰዓት ጠቋሚዋ በድንገት ወደ ፊት ተራመደች

## 1897 የመጀመሪያው የጽዮናውያን ስብሰባ

*«እነሆ የእስራኤልን ልጆች ከሄዱባቸው ከአሕዛብ መካከል አወስዳለሁ፣ ከስፍራም ሁሉ እሰበስባቸዋለሁ ወደ ገዛ ምድራቸውም አመጣቸዋለሁ» (ሕዝ.37:21)።*

ቴዎደር ሄርስል የእርሱን ሀሳብ የሚደግፉ ብዙ ጓደኞችንና ደጋፊዎችን አፈራ። ከነሐሴ 29-31 ቀን በ1897 ለሚደረገው የመጀመሪያው የጽዮናውያን ስብሰባ ጥሪ አደረገ። በዚህ ስብሰባ ላይ 199 የሚሆኑ ተመልከቾችና ሁኔታው ያጓጓቸው ሰዎች ተገኙ። ይህን ስብሰባ በትኩረት የተመለከቱት ብዙዎች ነበሩ። ቴዎደር ሄርስል የተከበረ ዝነኛ ሰው ሆነ። አጣዳፊ መልስ በሚያስፈልግ ሁኔታ በድሬይፉስ ላይ የተወሰደውን ፍርድና ፈረንሳዮች የመላ አይሁዶችን ጥፋት መመኘታቸውን ገለጹ። የአይሁድ ሕዝብ ወደ ሀገራቸው ለመመለስ የተቻላቸውን ነገር የማያደርጉ ከሆነ ይህ የመጨረሻ የዕድላቸው ጊዜ እንደሆነ ተነበየ። ቢሆንም ይህ ነገር ቀላል አልነበረም። የአይሁድ ሕዝብ በቀላሉ ወደ ቅድስት አገራቸው ለመመለስ የሚችሉ አልነበሩም። ምክንያቱም ከ1517 ጀምሮ ምድሪቷን ይገዙዓት የነበሩት ቱርኮች ያኔም እየገዟት ስለነበር ነው። ቱርክ በዓለም ኃያል መንግሥት ነበረች። የግዛቱ ስፋት ከዩጎዝላቪያ፣ በግሪክ በኩል በማለፍ እስከ ፐርሺያን ባሕረ ሰላጤ ድረስ ይደርስ ነበር። ሰሜን አፍሪካ፣ ግብፅና ሌሎች የአረብ አገሮች እንኳን የዚህ ታላቅ ግዛት ተገዢዎች ነበሩ። ቢሆንም አይሁድ በማንኛውም ሁኔታ መጡ። አይሁዶች ጥሪውን በግልፅ ሰሙት። በድብቅ ወደ ፓለስታይን በመግባት ባዶ የሆኑትን መሬቶች ከ500 የአረብ ቤተሰቦች ትንሽ በትንሽ መግዛት ጀመሩ። በዚያን ጊዜ ሀገሪቱ በሕዝብ የተሞላች አልነበረችም። ለመጀመሪያ ጊዜ ከ1000 እስከ 2000 አይሁዶች ነበሩ በየአመቱ ይገቡ የነበሩት። ነገር ግን ወዲያዉኑ በአስደናቂ ሁኔታ ቁጥራቸው እየጨመረ መሔድ ጀመረ።

ቴዎደር ሄርስል ያለ እረፍት አይሁዶች ወደ ጽዮን እንዲመለሱ በመምራት የተቻለውን ጥረት ሁሉ አደረገ። የአይሁድ ወደ ተስፋ ምድራቸው መመለስ «ብትፈልጉ ይህ ተረት አይደለም» በማለት ቴዎደር ሄርስል ጻፈ። በሕይወቱ ሳለው ከፍተኛ ግብ ድጋፍ ለማግኘት በመላው ዓለም ዞረ። ዓላማውም ነፃ የሆነ የአይሁድን መንግሥት ማቋቋም ነበር። ሄርስል በፒትስበርግ ያለውን የሩሲያውን ቴሳር ተወካይ ጎበኝቷል።

ይህ ብያኔ በዚያን ጊዜ መላ አውሮፓን አስደንቆ ነበር:: ከዚህም ሁኔታ በ1791 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) የወጣው አይሁድን ከሌላው ሕዝብ ጋር እኩል የሚያደርገው ህግ በወረቀት ላይ ብቻ የሠፈረ ሆኖ ቀረ:: በድሬይፉዩስ ላይ በተበየነው ብያኔ ምክንያት መላ አውሮፓ እንደገና በአይሁዶች ላይ ከፍተኛ ጥላቻ እንዲኖራቸው አደረገ:: ጥር 5 ቀን 1895 በፈረንሳይ ጦር አካዳሚ በተደረገው አሳዛኝ ሥነ ስርዓት ላይ ከድሬይፉዩስ ልብስ ላይ የመቶ አለቅነቱ ማዕረግ ተገፈፈ፣ ስይፉ ለሁለት ተሰበረ:: በዚህም አሳፋሪ ድርጊት ከጦሩ ተወገደ:: እርሱ ከጦሩ በተወገደ ዕለት ከፈረንሳይ መኮንኖችና ተመልካቾች *«ሞት ለአይሁድ፣ ሞት ለከዳተኞች»* የሚል ጩኸት አስተጋባ ::

በኦውስትሪያ ይኖር የነበረው ቴዎደር ሄርስል የተባለው አይሁዳዊ ጋዜጠኛ ስለዚህ ጩኸት መስክሯል:: በቀንና በሌሊት እንቅልፍ እስከሚያጣ ድረስ በዚህ ነገር በጣም ተጨነቀ:: «ሞት ለአይሁድ! ሞት ለከዳተኞች!» የሚለው ጩኸት ሕሊናውን ደግሞ ደጋግሞ የሚያስጨንቀው ሆነ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ነገር ዕረፍት የነሳው ሆነ:: ቴዎድር ኸርዝል ግንቦት 2 ቀን 1860 ዓ.ም. በቡዳፔስት የተወለደ አይሁዳዊ ነበር:: በ1878 በቪያና የሕግ ትምህርት ማጥናት ጀመረ:: በ1884 የዶክትሬቱን ዲግሪ ከተቀበለ በኋላ ደራሲና ጋዜጠኛ ሆነ:: ትዳር የመሠረተና የሶስት ልጆች አባት ነበር:: ከ1891-1895 በፓርሲ ላለው ለቪያናው ኒው ፍሪ ፕሬስ ተወካይ ሆነ:: በድሬይፉስ ላይ በተፈረደው ፍርድ የዓይን ምስክርና ስለ እርሱ መልእክት (ሪፖርት) የሰጠ ነበር:: ይህ ፍርድ ሕይወቱን ቀየረው:: በኋላ «ይህ በድሬይፉስ ላይ የተፈረደው ፍርድ ወደ ጽዮናዊነት ቀየረኝ» ብሏል:: ኸርዝል ምንም እንኳን አይሁዶች የእኩልነት መብት ቢኖራቸውም ባሉበት ቦታ የማይፈለጉና የተጠሉ እንደሆኑ ተገነዘበ:: ይህ ሰው አንድ ዓላማ ነበረው ይኸውም ወደ አባቶቻቸው ምድር ወደ እስራኤል መመለስ የሚል ነበር:: ወደ ቪያና በተመለሰ ጊዜ በአይሁድ እጅግ ተወዳጅ የሆነውን «የአይሁድ ግዛት» የሚለውን መጽሐፍ በጥር ወር በ1896 አሳተመ:: ብዙዎች አስተያየታቸውን መቀየር ጀመሩ:: ከኸርዝል ሌላ ሌሎች ግለሰቦች ጸሐፊዎች፣ ዶክተሮች የአይሁድ ሕዝብ ወደ ቅድስት ምድራቸው እንዲመለሱ ጥሪ ማድረግ ጀመሩ::





## በእግዚአብሔር የሰዓት መቁጠሪያ ላይ ያለችው ሰዓት ጠቋሚዋ
## በድንገት ወደ ፊት ተራመደች
## 1897 የመጀመሪያው የጽዮናውያን ስብሰባ

*«እነሆ የእስራኤልን ልጆች ከሄዱባቸው ከአሕዛብ መካከል እወስዳለሁ፣ ከስፍራም ሁሉ እሰበስባቸዋለሁ ወደ ገዛ ምድራቸውም አመጣቸዋለሁ» (ሕዝ.37:21)::*

ቴዎደር ሄርስል የእርሱን ሀሳብ የሚደግፉ ብዙ ጓደኞችንና ደጋፊዎችን አፈራ:: ከነሐሴ 29-31 ቀን በ1897 ለሚደረገው የመጀመሪያው የጽዮናውያን ስብሰባ ጥሪ አደረገ:: በዚህ ስብሰባ ላይ 199 የሚሆኑ ተመልከቾችና ሁኔታው ያጓጓቸው ሰዎች ተገኙ:: ይህን ስብሰባ በትኩረት የተመለከቱት ብዙዎች ነበሩ:: ቴዎደር ሄርስል የተከበረ ዝነኛ ሰው ሆነ:: አጣዳፊ መልስ በሚያስፈልግ ሁኔታ በድሬይፉስ ላይ የተወሰደውን ፍርድና ፈረንሳዮች የመላ አይሁዶችን ጥፋት መመኘታቸውን ገለጹ:: የአይሁድ ሕዝብ ወደ ሀገራቸው ለመመለስ የተቻላቸውን ነገር የማያደርጉ ከሆነ ይህ የመጨረሻ የዕድላቸው ጊዜ እንደሆነ ተነበየ:: ቢሆንም ይህ ነገር ቀላል አልነበረም:: የአይሁድ ሕዝብ በቀላሉ ወደ ቅድስት አገራቸው ለመመለስ የሚችሉ አልነበሩም:: ምክንያቱም ከ1517 ጀምሮ ምድሪቷን ይገዙዓት የነበሩት ቱርኮች ያኔም እየገዟት ስለነበር ነው:: ቱርክ በዓለም ኃያል መንግሥት ነበረች:: የግዛቱ ስፋት ከዩጎዝላቪያ፣ በግሪክ በኩል በማለፍ እስከ ፐርሺያን ባሕረ ሰላጤ ድረስ ይደርስ ነበር:: ሰሜን አፍሪካ፣ ግብፅና ሌሎች የአረብ አገሮች እንኳን የዚህ ታላቅ ግዛት ተገዢዎች ነበሩ:: ቢሆንም አይሁድ በማንኛውም ሁኔታ መጡ:: አይሁዶች ጥሪውን በግልፅ ሰሙት:: በድብቅ ወደ ፓለስታይን በመግባት ባዶ የሆኑትን መሬቶች ከ500 የአረብ ቤተሰቦች ትንሽ በትንሽ መግዛት ጀመሩ:: በዚያን ጊዜ ሀገሪቱ በሕዝብ የተሞላች አልነበረችም:: ለመጀመሪያ ጊዜ ከ1000 እስከ 2000 አይሁዶች ነበሩ በየአመቱ ይገቡ የነበሩት:: ነገር ግን ወዲያዉኑ በአስደናቂ ሁኔታ ቁጥራቸው እየጨመረ መሔድ ጀመረ::

ቴዎደር ሄርስል ያለ እረፍት አይሁዶች ወደ ጽዮን እንዲመለሱ በመምራት የተቻለውን ጥረት ሁሉ አደረገ:: የአይሁድ ወደ ተስፋ ምድራቸው መመለስ «ብትፈልጉ ይህ ተረት አይደለም» በማለት ቴዎደር ሄርስል ጻፈ:: በሕይወቱ ላለው ከፍተኛ ግብ ድጋፍ ለማግኘት በመላው ዓለም ዞረ:: ዓላማውም ነፃ የሆነ የአይሁድን መንግሥት ማቋቋም ነበር:: ሄርስል በፒትስበርግ ያለውን የሩሲያውን ቴሳር ተወካይ ጎብኝቷል::

በኢየሩሳሌም በጀርመናውያን በተሰራው የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን የምረቃ ስነ ስርዓት ላይ የመጣውን የጀርመኑን ንጉሥ ዳግማዊ ዊሊሁለም ጎብኝቷል:: የባዴኑን ልዑል፣ የኢጣሊያኑን ንጉሥና በሮም ይኖር የነበረውንም ጳጳስም ጎብኝቷል:: ነገር ግን ሕዝቡን ሊመራ ያለበት የአስር ዓመት ዕድሜ ብቻ ቀርቶት ነበረው:: ዕረፍት ከማጣቱ ከትልቅ ድካም የተነሳ በተወለደ በ44 ዓመቱ በ1904 ዓ.ም. ሞተ:: ይረዳ የነበረው በእናቱ፣ በሚስቱ በጁሊያ፣ በሴት ልጆቹ በጳውሊንና ጌርትሩ እንደዚሁም በተወዳጅ ልጁ በሀንስ ነበር:: እርሱ ቢሞትም ታምራት መካሔድ ጀመረ:: የአይሁድ ሕዝብ ቀስበቀስ ወደ ቅድስት ምድራቸው መመለስ ቀጠሉ:: እግዚአብሔር ሕዝቡን ማሰባሰብ ጀመረ::

**በእግዚአብሔር የሰዓት መቁጠሪያ ላይ ያለችው ሰዓት**
**ጠቋሚዋ እንደ ገና ወደ ላይ መውጣት**
**በ1917 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) የባልፎሩ ውሳኔ**

*«ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:: ስለዚህ ደግሞ አደርግላቸው ዘንድ የእስራኤል ቤት ይሹኛል:: ቀን እንደሚሆኑ እንደ ኢየሩሳሌም በዓች እንዲሁ የፈረሱት ከተሞች በሰዎች መንጋ ይሞላሉ፣ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ» (ሕዝ. 36:37-38)*

ከ1914 - 1918 ዓ.ም. የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ሆነ በአውሮፓ ለብዙ ምዕተ ዓመታት ገንነው የነበሩት መንግሥታትና ግዛቶች ወደቁ:: በድንገት የቄሳሮችና የልዑሉች አገዛዝ አበቃለት:: በዚህ ጦርነት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ (1916/17) የእስራኤልን ሕዝብ የሚመለከት ውሳኔ ተወሰነ:: ቻይም ዊዝማን የሚባል ኬሚስት በኢንግላንድ ይኖር ነበር:: በሩሲያ የተወለደና አስራ አራት ወንድሞችና እህቶች ነበሩት:: በትውልዱ (በደም) አይሁዳዊ ነበር:: የታናሽ ወንድሙ ልጅ ኤዛር ዊዝማን የሚባለው በእስራኤል አየር ኃይል ውስጥ የተወደደ ጀኔራል፣ በኋላም የካቢኔ ሚኒስትርና፣ የእስራኤል መንግሥት ፕሬዝዳንት ነበር:: አይሁዶች በሩሲያ እንዲማሩ ያልተፈቀደ ከመሆኑ የተነሳና እንደዚሁም አይሁዶችን የማጥፋት ዕቅድ ስለነበረ ቻይም ዊዝማን ወደ ምዕራብ አውሮፓ በኦውስትሪያ በኩል በመሰደድ ወደ ኢንግላንድ መጣ:: የእንግሊዝ መንግሥት በአንደኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ በማንቸስተር ላለው የኬሚካል ጦር መሣሪያዎች ለሚሠሩበት ኢንዱስትሪ የበላይ አስተዳዳሪ አድርጎ ሾመው:: የኬሚስትሪ ዶክተር እንደ መሆኑ አዲስና አስደናቂ ግኝት አገኘ::





ለኃይለኛ ፍንዳታ የሚውለውን አሲቶንን ከስንዴ ለመሥራት ቻለ:: ስዚህ በተገኘው አዲስ ግኝት በመጠቀም እንግሊዝ ጀርመንን በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ድል ለማድረግ በቃች:: በ1916 ሁለቱም ክፍሎች ጦርነቱን ሊቀጥሉ አልቻሉም:: ወደ ፊት መግፋቱ ለጥቂት ጊዜ አቆሙ:: በዚህ ጦርነት ድንገተኛ ለውጥ መጣ:: ይኸውም በምዕራቦቹ ሕብረት የጀርመንን ጦር ድል የማድረጉ ነገር ነበር:: ጀርመን መቋቋም በማይችለው ሁኔታ የአሜሪካ መንግሥት ታንኮችን በማሰለፍ መዋጋት ጀመረች:: ቻይም ዊዝማን በማንቸስተር ከሎርድ ባልፎር ጋር እንዲተዋወቅ ተደረገ:: በሁለቱ መካከል የጠበቀ ጓደኝነት ተመሠረተ:: ባገኘውም ግኝት ምክንያት የታወቀ ሆነ:: የእንግሊዝ መንግሥት ባደረገው ታላቅ አገልግሎት ዶክተር ቻይም ዊዝማንን የከበረ ሰው አደረገው:: ከፓርላማ አባሎች ዘንድ በማቅረብ እንዲታወቅ ተደረገ:: በፓርላማውም ምን እንደሚፈልግ ተጠየቀ:: አይሁድ እንደመሆኑ መጠን ቻይም ዊዝማን የነበረው ምርጫና ጥያቄ አንድ ነበር:: የእንግሊዝን መንግሥትም የአይሁድ ሕዝብ ወደ ፓለስታይን ወደ ምድራቸው የሚመለሱበትን መንገድ እንዲያመቻቹለት ነበር የጠየቀው:: የእንግሊዝ መንግሥት በዚህ ተስማማ:: ፓለስታይን በምስራቅ እስያና በሕንድ ላለው ለእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ መሸጋገሪያ ድልድይ እንደምትሆን ታሰበ:: እንግሊዞች ፓለስታይንን በጥንቃቄ የተጠናከረ የአውሮፓ ሠራተኞች ቅኝ ግዛት ለማድረግ አሰቡ:: የእንግሊዙ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሎርድ ጀምስ ኧርዘር ባልፎር የተባለው በታሪክ «የባልፎር መግለጫ» ተብሎ የታቀውን ጥቅምት 2 ቀን 1917 ዓ.ም. ታትሞ እንዲወጣ አደረገ:: ይህ አዋጅ ለእስራኤል ሕዝብ ወደ ገዛ ምድራቸው እንዲመለሱ ተስፋ ሰጠ::

ሕብረ ብሔሩ በጦርነቱ ጥሩ ውጤት ያስገኘ ሆነ:: ጀርመን ከቱርክ ጋር በመስማማት በቱርኩ ኦቶማን ኢምፓየር መንግሥት ምድር ላይ 25,000 የጀርመን ወታደሮች አሰፈረች:: ነገር ግን ቱርኮች በማንኛውም አቅጣጫ ድል ተመቱ፤ እንግሊዝ በዚያን ጊዜ በዓለም ኃያል መንግሥት ነበረች:: በእለንባዩ ጀኔራል ኢድሙንድ መሪነት በ1917/18 እንግሊዝ ቱርክን ድል በማድረግ ፓለስታይንን ያዘች:: በዚህም ለ400 ዓመታት ገንኖ የነበረው የቱርክ መንግሥት ወደቀ:: ቅድስቲቷን ምድር ለመያዝ በተደረገው ጦርነት 40,000 የእንግሊዝ ወታደሮች ሕይወታቸውን አጡ:: ጀኔራል እልንባይ በእግሩ ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ገባ:: ጥቅምት 11 ቀን 1917 ዓ.ም. በዳዊት ምሽግ ደረጃዎች ላይ ሆኖ የቱርክ መንግሥት አገዛዝ ማክተሙን ተናገረ በኋላም በዚሁ ቦታ የባልፎሩ ውሳኔ ተነገረ::


በዚያን ቀን ሊነገር በማይቻል ሁኔት የአይሁድ ሕዝቦች ተደሰቱ ወደ ነጻነት የሚወስደው መንገድ የተቃረበ ሆነ:: የምዕራቡ ዓለም ኃይል ለአይሁድ መንግሥት መቋቋሙን የሚደግፍ ሆነ:: ሊግ ኦፍ ኔሽን የበላይ ሞግዚትነቱን ለእንግሊዝ ሰጠ:: የመጀመሪያው የእንግሊዝ ከፍተኛው ኮሚሽነር በትውልዱ አይሁዳዊ ነበር:: ስሙም ሰር ኸርበርት ሳሙኤል ይባል ነበር:: እርሱ ደግሞ መላ አይሁድ ወደ ፓለስታይን እንዲመለሱ ጥሪ አደረገ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአስር ሺህ የሚቆጠሩ አይሁዶች ወደ ቅድስቲቱ ምድር መመለስ ችለዋል:: የአይሁድ ሰፋሪዎች የተጣለውን ምድር በመሥራታቸው የአረብ ሰደተኞች ከዚህ ከተሠራው ግንባታ ጥቅም ፈላጊዎች ሆኑ:: ይህም ደም ወደ መፋሰስ ጠብ መራ:: እነዚህ ፍልሚያዎች በቀጠሉ መጠን እንግሊዞች ደግሞ አረብ ጎን በመሆን የአይሁድን የመመለስን እንቅስቃሴን የሚያውኩ ሆኑ:: ከምስራቅ በዩርዳኖስ በኩል የሚመጡት አረቦች ወደ ሀገሪቱ እንዲገቡ ተፈቀደላቸው::

**Tha "Balfour Declaration"**

**Foreign office,**
November 2nd,1917

Dear Lord Rothschild,

I have much pleasure in conveying to you, on behalf of his majesty's government, the following declaration of sympathy with jewish Zionist aspirations which has been submitted to, and approved by, the cabinet "His majesty's government view with favout the establishment in Palestine of a national home for the jewish people, and will use their best endeavourer to facilitate the achievement of this object, it being clearly understood that nothinmg shall be done which may prejudice the civil and religious rights of existing non- jewish communities in Palestine , or the rights and political status enjoyed by jews in any other country"
I should be greateful if you would bring this declaration to the knowledge og the Zionist federation.



በአንደኛው የዓለም ጦርነት እንግሊዝ ከቱርክ ጋር ባደረገችው ጦርነት አረብ ስለ ሰጠችው ድጋፍ እንግሊዝ ሰመካው ሸሪፍ ሁሴን የአረብ ግዛት ለመስጠት ተስፋ ሰጥታው ነበር:: በእንግሊዝና በአረብ መካከል የነበረው መካከለኛ ሰው (አገናኙ) በአረቢያ





ታዋቂ የሆነው ሰው ቶማስ ኤድዋርድ ላውሬንስ የተባለው ሳው ነበር:: የአረብ መንግሥታት ነጻ የወጡት ከአንደኛው ዓሰም ጦርነት በኋላ ነበር:: የሸሪፎቹ ወንዶች ልጆች በእነዚህ የአረብ መንግሥታት ላይ የበላይ ገዢነት ተሰጣቸው:: በአይሁዶችና በአረቦች መካከል አንግሊዝ በምታካሄደው ፓለቲካ ምክንያት አይሁዶች በጣም ወደ ኋላ የተተው ሆኑ:: በባልፎሩ ውሳኔ እንግሊዝ ለአይሁዶች ልትሰጣቸው የገባችውን የራሳቸውን ምድር በ1922 ዊንስተር ቸርችል ሰሁለት ከፈሉት:: ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምስራቅ በኩል ካለው ከሃገራቸው 76ኅቱ ሰመካው ሸሪፍ ልጅ ሰአሚር አብዱላሂ እንዲሰጥ ተደረገ:: ይህ ሰው ግንቦት 25,1946 ዓ.ም የዮርዳኖስ ሀሽማይት መንግሥት መቋቋሙን አወጀ:: መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከሆነው ምድራቸው ቀሪው 24ኅ በእንግሊዞች ዌስት ባንክ ተብሎ የተጠራው ከዮርዳናስ ወንዝ በስተ ምዕራብ በኩል ያለው ለጽዮናውያን እንቅስቃሴ መሪዎች ተሰጠ:: ይህ 24ኅ ምድር እንደገና በተባበሩት መንግሥታት በሕዳር 29,1947 ዓ.ም. የተከፈለ ሆነ ይህም የመከፈል እቅድ ተብሎ ተጠራ:: በዚህች ትንሽ በሆነች ምድር ግንቦት 14 ቀን 1948 ዓ.ም. ዳቪድ ቤን ጉርዮን የእስራኤልን መንግሥት አወጀ::

***የባልፎሩ ውሳኔ***

የውጭ ጉዳይ ቢሮ

ሕዳር 2 . 1917 ዓ.ም

የተከበሩ ሮትዝሺልድ!

በተከበረው ልዑል መንግሥት ስም ሆኜ ከአይሁድ ጽዮናውያን ብርቱ መሻት ጋር በመተባበር ለእርስዎ ካቢኔ የተሰጠውንና ተቀባይነት ያገኘውን የርኅራኄ አዋጅ ለእርስዎ በመግለጼ እጅግ በጣም ደስታ ይሰማኛል::

የተከበረ መንግሥቱም በመልካም ጎኑ የሚያየው ነገር ቢኖር

በፓለስታይን (በእስራኤል ምድር) የአይሁድ ብሔራዊ ቤት

መቋቋም ሲሆን የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ በማድረግ በተቀላጠፈ


ሁኔታ ይህ ዓላማ ግብ እንዲመታ ነው:: እዚህ ላይ በግልጽ

ሊታወቅ የሚገባው በፓለስታይን (በእስራኤል) በሚኖሩ

አይሁድ ባልሆኑት ማኅበረ ሰብ በሲቪልና በሃይማኖት መብታቸው

ላይ እንዳችም ነገር የማይፈጸምባቸው መሆኑ ነው::

ይህም በየትኛውም አገር እንዳሉት በመብታቸውና በፖለቲካ ደረጃቸው እንደሚደሰቱት አይሁድ ማለት ነው:: ይህን አዋጅ ጽዮናዊው (የእስራኤል) ፌዴሬሽን እንዲያውቁት ካደረጉልኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው::



## በእግዚአብሔር የሰዓት ቀጠራ ላይ ያለችው ሰዓት ጠቋሚዋ እንደገና ወደ ፊት ተራመደች

## 1948 የእስራኤል መንግሥት ምስረታ

*«ለአባቶቻችሁም በሰጠኋት ምድር ትኖራላችሁ» (ሕዝ.36:28)፡፡*

በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል እንግሊዝ ፖለቲካዎቿን በፈጣን መንገድ ለወጠች፡፡ በአዶልፍ ሂትለር መንግሥት ጊዜ አይሁዶች አስቃቂ ስደት ውስጥ ቢወድቁም፡፡ በፓለስታይን የነበረው የእንግሊዝ አስተዳደር ጥቂት የአይሁድ ስደተኞች ብቻ እንዲገቡ ፈቀደ፡፡ ከ6 ሚሊዮን በላይ የሆኑ አይሁዶች አስቃቂ በሆነ (ጭክና በተሞላ) አገዳደል በአውሮፓ ተገደሉ፡፡ ሂትለር ይህን ሕዝብ ጨርሶ ለመደምሰስ ፈለገ፡፡ የእንግሊዝ ፖለቲከኞች ከጊዜ ወደጊዜ በአይሁድ ሕዝብ ላይ በተቃውሞ የሚነሱ ሆኑ፡፡ ይህም ሆኖ ሳለ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ካበቃ ከሦስት ዓመት በኋላ እጅግ አስደናቂ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ ይኸውም ግንቦት 14 ቀን 1948 ዓ.ም. ከ4:00-4:32 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ከተማ ሙዝየም በተገኙት 200 እድምተኞች ፊት የእስራኤል መንግሥት ታወጀ፡፡ ከሰዓት በኋላ በ4 ሰዓት (በ10 ሰዓት) በ1906 የተወለደውና ከፖላንድ ተሰድዶ የመጣው ዳቪድ ቤን ጉርዮን የነጻነቱን አዋጅ በአይሁድ ቋንቋ «አትማውዝ» የተባለውን አነበበው፡፡ በ4:17 (10:17) 37ቱ የአይሁድ መንግሥት ከፍትኛ ባለ ስልጣኖች ይህን አዋጅ ፈረሙ፡፡ በ4:30 (10:30) የተከበሩት እድምተኞች ተነስተው «ሀቲክቫ» (ተስፋው) የተባለውን ብሔራዊ መዝሙር ዘመሩ፡፡ መዝሙሩም የሚከተለው ነው፡፡

*በአይሁድ ነፍስ ውስጥ ስሜት እስካለ ድረስ*
*ጽዮንን የመመኘት ፍላጎት ይኖራል*
*በምድራችን በጽዮን በኢየሩሳሌም እንደገና በነጻነት*
*ለመኖር የነበረው ለሁለት ሺህ ዓመታት የቆየው*
*ተስፋችን አልጠፋም፡፡*

በዚህ ጊዜ ከ600,000 የሚበልጡ አይሁዶች በቅድስቲቷ ምድር ነበሩ፡፡ ይህ ቁጥር በሙሴ ጊዜ ከግብፅ ምድር የወጡትን የወንዶች ቁጥር የሚያህል ነበር፡፡ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ፣ ሬዲዮ ያዳምጡ የነበሩ ሕዝቦች ይህንን ታሪካዊ ሁኔታ አዳምጠውት ነበር፡፡ እንደገና ከ2,000 ዓመታት በኋላ አይሁዶች የራሳቸው ምድር እንዳላቸው አዲስ ተስፋ ያገኙ ሆኑ፡፡ የአይሁድ ሕዝብ ሊነገር በማይቻል ደስታ





ተሞሉ፡፡ ሰዎች በደስታ ተሞልተው በየመንገዱ መጨፈር ጀመሩ፡፡ ከቴዎድር ኸርዝል ጊዜ ጀምሮ ተረት መስሎ የታየው ነገር እውን ሆኖ ተገለጠ፡፡

ስለ አይሁድ መንግሥት ምስረታ የሚናገረውን ጽሁፍ ለማንበብ የፈጀው ጊዜ 17 ደቂቃ ብቻ ነበር፡፡ መስራች አባሎች ስማቸውን በፊርማ ለማስፈርና ከተከበሩት እድምተኞች ጋር ብሔራዊ መዝሙራቸውን ለመዘመር የፈጀባቸው ጊዜ 15 ደቂቃ ብቻ ነበር፡፡ በ4:32 (10:32) ይህ ትልቁ ስነ-ሥርዓት አበቃ ከውስጥ የጦር ዩኒፎርሙን ለብሶ የነበረው ዳቪድ ቤን ጉርዮን ጥቁር ካፖርቱን በማውለቅ:

«ስነ ሥርዓቱ አበቃ፣ ጦርነቱ ይጀምራል» አለ፡፡

## የነጻነቱ ጦርነት 1948 - 1949

ከጥቂት ሰዓታት በኋላ አዲስ የተቋቋመችው የእስራኤል መንግሥት በአረቦች ተወጋች፡፡ ጨቅላ የሆነችውን የእስራኤልን መንግሥትና ሕዝብ ተባብረው በአንድ ምሽት ለማጥፋት በማሰብ አምስት የአረብ መንግሥታት የነበራቸውን ብርቱ ጦር በማሰለፍ በእኩለ ሌሊት በእስራኤል ላይ ጦርነት ከፈቱ፡፡ ዮርዳኖስ ከደብረ ዘይት ተራራ ተኩስ በመክፈት ለ26 ቀናት ሌሊትና ቀን ያለማቋረጥ ኢየሩሳሌምን ደበደቡ፡፡ ግብፅ ከደቡብ ኢራቅ፣ ከምስራቅ ሶሪያና ሊባኖስ ከሰሜን እስራኤልን በጦር ከበቧት ነገር ግን ይህ ጦርነት ለብዙ ጊዜ አልቀጠለም፡፡ ከአረብ ጋር ሊመጣጠን በማይችል ትንሽ ትጥቅ የታጠቀችው እስራኤል ከአስር ወራት በኋላ ድሉን ተቀዳጀች፡፡ በተባበሩት መንግሥታት ጠያቂነት ጦርነቱ እንዲቆም ተደረገ፡፡ በኋላም በሩዶስ ደሴት ውሉ ተፈረመ፡፡ የዓይን ምስክሮች «እግዚአብሔር ባለፈው ጊዜ እንዳደረገው ለእስራኤል ሕዝብ ተዋጋላቸው» በማለት ተናግረዋል (*ኢያሱ.10:12-14*)፡፡ ቢሆንም እስራኤል ለዚህ ጦርነት ከፍተኛ ዋጋ ከፍላለች ስድስት ሺህ ወታደሮች ሕይወታቸውን አጥተዋል፣ ከ9,000 በላይ ቆስለዋል፡፡

እስራኤል በዚህ የነጻነት ጦርነት ድል በመቀዳጀት ብዙ መሬት ያዘች፡፡ በዚህ የብዙ ሕይወት እልፊት በተደረገው ጦርነት ኢየሩሳሌምን ለመያዝ አልቻለችም፡፡ በዮርዳኖሳውያን እጅ ወደቀች፡፡ ኢየሩሳሌም ለቀጣዩ 19 ዓመታት እንደ ተከፋፈለች ቆየች፡፡ እስራኤላውያን በልቅሶ አደባባይ ለመጸለይ አልቻሉም፡፡

## የ1956ቱ የስዊዝ ቀውስ

እንደ ቀድሞው ሰላም አልነበረም። የተኩስ አቁሙ የቆየው ለሰባት ዓመታት ብቻ ነበር። «የስዊዙ ቀውስ» ተብሎ የተጠራው በጥቅምት ወር 1956 የተጀመረው አንባ ገነኑ የግብፁ መሪ ናስር በ1869 በፈረንሳዮች የተሠራውን የስዊዝ ካናልን በግብፅ እጅ እንዲሆን ባደረጉበት ጊዜ ነበረ። የፈረንሳዩ፣ የእንግሊዙና የእስራዔሉ የታንክ ብርጌድ ግብፅን በመውጋት ጉዞአቸውን ወደ ስዊዝ ካናል አመሩ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ጠቅላላ የሲና ባሕረ ሰላጤ በእስራኤል ተወሰደ። ወዲያውኑ የአረብ መንግሥታት ይህንን የፖለቲካ ጉዳይ በማድረግና የእስራኤልን ድል ማድረግ በመቃወም የተባበሩት መንግሥታት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲያደርግ ጥሪ አደረጉ። የዚህም ውጤት እስራኤል ከሲና ወጥታ እንድትሔድ ሆነ። እስራኤል የ170 ሰዎች ሕይወት አጣች 700 ቆሰሉባት።

በእግዚአብሔር ሰዓት መቁጠሪያ ላይ ያለችው ሰዓት
ጠቋሚ እንደ ገና ወደ ላይ ወጣች
የ1967ቱ የስድስቱ ቀናት ጦርነት
*«እስራኤል በኃይል ያደርጋል» (ዘኁ.24:18)*

አምባ ገነኑ የግብፅ ገዢ ናስር ከስዊዙ ቀውስ ከሰባት ዓመት በኋላ በእስራኤል ላይ ሌላ ጦርነት ከፈቱ። ይህ ጦርነት በታሪክ «የስድስቱ ቀን ጦርነት» ተብሎ የተጠራው ነው። የአረብ መንግሥታት የ1948 ዓ.ም. ድል ሲቋቋሙትና ሊረሱት አልቻሉም ነበር። ስለዚህም በሩሲያ ደጋፊነት የጦር ኃይላቸውን አጠናከሩ። ግብፅ፣ ሶርያ፣ ኢራቅና ዮርዳኖስ እስራኤልን ድል ለማድረግ የሚችሉ አድርገው ራሳቸውን ገመቱ። በግንቦት መጨረሻ በ1967 ዓ.ም. እነዚህ አገሮች ሙሉ የጦር ኃይላቸውን አንቀሳቀሱ። ከእስራኤል ጎን ያለው አውሮፓና የሰሜን አሜሪካ የፖለቲካ ጥረት ውጤተ ቢስ ሆነ። የአሜሪካ፣ የፈረንሳይና የጀርመን ሕዝቦች እስራኤልን በመደገፍ በየመንገዱ ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ። የስድስቱ ቀን ጦርነት ሰኔ 5 ቀን 1967 በ7:55 ሰዓት (1:55 ምሽት ላይ) ተጀምሮ በጎላን ኮረብታ ላይ በኩኒትራ የሚገኘው የሶርያ ክፍለ ጦር በመሸነፍ ሰኔ 10 ቀን 1967 ዓ.ም በ2:30 ሰዓት (8:30) ላይ አበቃ። በዚህ ጦርነት እስራኤል የሲናን ባሕረ ሰላጤ፣ ይሁዳን፣ ሰማርያን ጋዛንና የጎላንን ተራራ እንደገና ለመያዝ ቻለች። ሰኔ 7 ቀን 1967 ዓ.ም. የሚቀጥለው እርምጃ ወደ ኢየሩሳሌም ማምራት ሆነ። በ55 ሰዓት ውስጥ የእስራኤል ፓራትሩፐርና የታንኩ ብርጌድ የጥንቷን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነችውን





ከተማ ኢየሩሳሌምን ያዙ። የአረቦችን መስኪዶችና የክርስቲያኖችን ቤተ ክርስቲያንን ለማዳን ሲሉ እስራኤላውያን ከባድ መሳሪያ አልተጠቀሙም ነበር። በዚህ ጦርነት ጠባብ በሆኑት በኢየሩሳሌም መንገዶች ላይ ምርጥ ከሆኑት ወታደሮቹ 183 ወጣቶቿን አጣች። ቢሆንም እስራኤል ግቧ ላይ ደረሰች። ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ መላ የኢየሩሳሌም ከተማ፣ የቤተ መቅደሱ ተራራና የልቅሶ አደባባይ ጭምር ለእስራኤል መንግሥት ሆነ። በዚህ ታምራዊ በሆነው ሁኔታ ጊዜ ታላቁ ራቢ (መምህር) ሽሎም ጎሬን ቀንደ መለከትን በመንፋት «እኛ ወደ መሲሁ ዘመን ገብተናል» ብለው ትንቢታዊ ቃል ተናገሩ። የዕብራውያን ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር የሆኑት ጀሹዋ (ኢያሱ) ፕራውር በመጨመር «የመሲሁን መምጣት መቅረብ በሰሚ ጆሮዎች ለመስማት ይህ ሕዝብ ለ2000 ዓመታት ያህል ነጻነቱን መጠበቅ ነበረበት» በማለት ተናግረዋል።

እስራኤል 800 ወታደሮች ሞተውና 2600 ሲቆስሉባትም እግዚአብሔር እንደገና ለዚህ ሕዝብ ድልን ሰጠ። እግዚአብሔር ለዚህ ሕዝብ እንደ ኪዳኑ እስከ ቤርሳቤህ፣ ከሜድትራንያን ባሕር እስከ ዮርዳኖስ ድረስ ያለውን መላ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምድራቸውንና ኢየሩሳሌምን ጭምር ሰጣቸው።

## የ1973ቱ ዓ.ም የዮም ኪፑሩ ጦርነት

ጥቅምት 6 ቀን 1973 ዓ.ም ዮም ኪፑር በተባለው የአይሁዶች የስርየት በዓል ዕለት የአረቦች ጦርነት በእስራኤል ላይ እንደገና እንደ አዲስ ተጀመረ። ዮምኪፑር ተብሎ በተጠራው ጦርነት ጊዜ ግብፅ ከደቡብ በሲና ካናል በኩል፣ ሶሪያ በጎላን ኮረብታ በኩል ከሰሜን በእስራኤል ላይ ጦርነት ከፈቱ። ይህም ቢሆን እስራኤል በጥሩ ውጤት ተቋቋመቻቸው። ከሦስት ሳምንታት በኋላ የእስራኤል ወታደሮች ከካይሮ 100 ኪሎ ሜትር ከደማስቆ 60 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነበሩ። እስራኤል 2650 ወታደሮች ሲያልቁባት 7500 ደግሞ ቆሰለውባታል። ነገር ግን እንደገና ለዚህ ድል ፍሬ እንድትቋረጥ ተደረገ። የተባበሩት መንግሥታት ጣልቃ በመግባት ይህን የእስራኤልን የድል ጉዞ እንዲቆም አደረገው። ድንገት ሳይታሰብ ሕዳር 19 ቀን 1977 ዓ.ም የግብፁ ፕሬዝዳንት ሳዳት ሲና ባሕረ ሰላጤ የሚመለስበትን መንገድ ከእስራኤል ጋር ለመስማማት ወደ ኢየሩስሌም መጡ። በተባበሩት መንግሥት ጣልቃ ገብነት ሁለቱ ሀገሮች «ካምፕ ዴቪድ አኮርድ» የተባለውን ውል መጋቢት 26 ቀን 1979ዓ.ም ተፈራረሙ፡ሚያዝያ25ቀን1982 ዓ.ም. እስራኤል ሙሉ በሙሉ ከሲና ወጣች። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በእስራኤልና በግብፅ መካከል ሰላም ሰፈነ።

## የ1982ቱ የሊባኖስ ጦር ዘመቻ

እስራኤል ሰኔ 6 ቀን 1982 ዓ.ም በፒ.ኤል.ኦ (PLO) የያሲር አረፋት ሽብርተኞች ላይ እርምጃ እንድትወስድ ተገደደች፡፡ ምክንያቱም አስደንጋጭ በሆነው ካቲዩሻ ሮኬት በመደገፍ በመደጋገም በገሊላ በስተ ሰሜን በሚገኙት ከተማዎችና መንደሮች ላይ ጥቃት ይፈጽሙ ነበር፡፡ እስራኤል እስከ ቤይሩት ድረስ ዘልቆ በመግባት 36,000 የአረፋት ሽብርተኞች ሊባኖስን ለቅቀው እንዲሸሹ አደረገች፡፡ ይህ ጦርነት አሳዛኝ (ልብ የሚሰብር) የሆነ ጥፋትን በእስራኤል ላይ አስከተለ፡፡ እንደገና እስራኤል በዚህ ጦርነት የ547 አባቶችንና የወንዶች ልጆቿን ሕይወት አጣች፡፡

## እስራኤል ሕያው ተዓምር

እስራኤል *መንግስቷን* ከመሰረተችበት ከ1948 *ዓ.ም* ወዲህ በተደረጉት አምስት ጦርነቶች የእስራኤል አምላክ ለሕዝቡ ድልን አቀዳጅቷል፡፡ በብዛትና በጥንካሬ ይበልጧት የነበሩት ጠላቶቿ የሆኑት አረቦች ይህችን አዲስ የተቋቋመችውን *መንግሥት ሊቋቋሟት* አልቻሉም፡፡ በተቀራኒው ግን እስራኤል ከቶ ባልታየ ሁኔታ ማደግ ጀመረች፡፡ በአስርት ዓመታት ውስጥ ለብዙ ዓመታት በረሀ ሆነው የቆዩት ቦታዎች በልምላሜ የተሞሉ ገነቶች ሆኑ፡፡ እስራኤል በየዓመቱ ብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ምግብ ወደ ውጭ የምትልክ ሀገር ሆነች፡፡ ከመቶ ሰባው እጅ የአልማዝ ማዕድን የሚቀረፀው በእስራኤል ነው፡፡ የሙት ባህር አካባቢ በዓለም ከፍተኛው የብሮማይን፣ የፖታሽ፣ የማግኔዢየምና የሌሎች የኬሚካል ማዕድኖች ክምችት የሚገኝበት ቦታ ነው፡፡ ማንኛውም ነገር በአስገራሚ ሁኔታ ከትልቁ ኤሌክትሮኒክ እስከ አነስተኛው የመኪና ጎማ ድረስ በእስራኤል ምድር ይመረታል፡፡ ሀገሪቱ ለጦር የሚያስፈልጉት ከምችቶችና በሕዋ ውስጥ የራሷ ሳተላይትና አውቶማቲክ ቦምቦች አሏት፡፡ እስራኤል ከሌሎቹ ሀገሮች ጋር ስትወዳደር አነስተኛ ሆና ብትታይም በዓለም በጦር ኃይል አራተኛዋ ጠንካራ *መንግሥት* እንደሆነች ይገመታል፡፡


ከ2000 የስቃይና የስደት ዓመታት በኋላ የእስራኤል ሕዝብ መሰባሰብ በአሁን ጊዜ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ተአምር ነው፡፡

- በቱርኮች ተደምስሳ በነበረችው ምድር የመጀመሪያዎቹ የእስራኤል ሰፋሪዎች በ1870 ዓ.ም ወደ ፓለስታይን ተመልሰው ምድሪቱን መርገጣቸው *ተአምር* ነበር፡፡





- እስከ 1948 ዓ.ም ድረስ በፓለስታይን የነበሩት አይሁዶች 600,000 ነበሩ፡፡ ይህም *ተአምር* ነበር፡፡ በሙሴ ጊዜ ከግብፅ ከወጡት የጦር *መሣሪያ መታጠቅ* ከሚችሉት ጋር በቁጥር ተመጣጣኝ ነበሩ፡፡
- አሰቃቂ የሆነውን የሂትለርን አገዛዝ ተቋቁመው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ከሦስት ዓመት በኋላ ግንቦት 14 ቀን 1948 ዓ.ም የእስራኤል *መንግሥት መመስረቱ ተአምር ነበር፡፡*
- ለእስራኤል *መንግሥት ምስረታ* ሁኔታን በማመቻቸት የተባበሩት *መንግሥታት* በ1947 እስራኤልን ለመከፈል ያደረገው ስምምነት ተአምር ነበር፡፡
- የእስራኤል *መንግሥት* ከተመሠረተ በኋላ ከእርሷ በኃይል በሚበልጡት ጠላቶቿ በአምስቱም ጦርነቶች አለመሸነፏ ተአምር ነበር፡፡
- በ1991 ዓ.ም. በባህረገልፉ ሰላጤው ጦርነት ከእስራኤል 74 ሰዎች መሞታቸው ተአምር ነበር፡፡ ምክንያቱም 39 የኢራቅ ስከድ ሚሳኤሎች ከተማዋን መትተዋል፡፡ ሁለት ሚሳይኤሎች ቴልአቪቭን በመምታት 7000 ቤቶችን፣ አፓርታማዎችን ደምስሰዋል፡፡



በቅድስቲቱ ምድር ተአምር በተአምር ላይ ታይተዋል፡፡ ይህንን ዘገባ እስከቻልንበትና እስከወደድንበት ድረስ ልንመዘግብ እንችላለን፡፡ እግዚአብሔር ከዚህ ሕዝብ ጋር እንደ ገና መሥራቱ አስደናቂ ነገር ነው፡፡ ማንኛውም የዓለም ኃይል እስራኤልን ሊያጠፋ አልቻለም፣ አይችልም፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ግንብና የእሳት ቅጥር ስለሆነ ነው (*ዘካ.2:5*)፣ «እርሱ ራሱ ለቤቱ ይቆማል» (ዘካ. 9:8)፡፡

**1897፣ 1917፣ 1948 እና 1967** ዓ.ም በእስራኤል የደህንነት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ለፍራን የያዙ ዓመታት ናቸው፡፡ እነዚህ ዓመታት ዝግ ያለውንና የማይነቃነቀውን የእስራኤልን *መንግሥት* ትንሳኤን ያሳያሉ፡፡

**የ1982ቱ የሊባኖስ ጦር ዘመቻ**

እስራኤል ሰኔ 6 ቀን 1982 ዓ.ም በፒ.ኤል.ኦ (PLO) የያሲር አረፋት ሽብርተኞች ላይ እርምጃ እንድትወስድ ተገደደች፡፡ ምክንያቱም አስደንጋጭ በሆነው ካቲዩሻ ሮኬት በመደገፍ በመደጋገም በገሊላ በስተ ሰሜን በሚገኙት ከተማዎችና መንደሮች ላይ ጥቃት ይፈጽሙ ነበር፡፡ እስራኤል እስከ ቤይሩት ድረስ ዘልቆ በመግባት 36,000 የአረፋት ሽብርተኞች ሊባኖስን ለቅቀው እንዲሸሹ አደረገች፡፡ ይህ ጦርነት አሳዛኝ (ልብ የሚሰብር) የሆነ ጥፋትን በእስራኤል ላይ አስከተለ፡፡ እንደገና እስራኤል በዚህ ጦርነት የ547 አባቶችንና የወንዶች ልጆቿን ሕይወት አጣች፡፡

**እስራኤል ሕያው ተዓምር**

እስራኤል መንግስቷን ከመሰረተችበት ከ1948 ዓ.ም ወዲህ በተደረጉት አምስት ጦርነቶች የእስራኤል አምላክ ለሕዝቡ ድልን አቀዳጅቷል፡፡ በብዛትና በጥንካሬ ይበልጧት የነበሩት ጠላቶቿ የሆኑት አረቦች ይህችን አዲስ የተቋቋመችውን መንግሥት ሊቋቋሟት አልቻሉም፡፡ በተቃራኒው ግን እስራኤል ከቶ ባልታየ ሁኔታ ማደግ ጀመረች፡፡ በአስርት ዓመታት ውስጥ ለብዙ ዓመታት በረሀ ሆነው የቆዩት ቦታዎች በልምላሜ የተሞሉ ገነቶች ሆኑ፡፡ እስራኤል በየዓመቱ ብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ምግብ ወደ ውጭ የምትልክ ሀገር ሆነች፡፡ ከሙት ሰባው እጅ የአልማዝ ማዕድን የሚቀረፀው በእስራኤል ነው፡፡ የሙት ባህር አካባቢ በዓለም ከፍተኛው የብሮማይን፣ የፖታሽ፣ የማግኔዚየምና የሌሎች የኬሚካል ማዕድኖች ክምችት የሚገኝበት ቦታ ነው፡፡ ማንኛውም ነገር በአስገራሚ ሁኔታ ከትልቁ ኤሌክትሮኒክ እስከ አነስተኛው የመኪና ጎማ ድረስ በእስራኤል ምድር ይመረታል፡፡ ሀገሪቱ ለጦር የሚያስፈልጉት ክምችቶችና በሕዋ ውስጥ የራሷ ሳተላይትና አውቶማቲክ ቦምቦች አሏት፡፡ እስራኤል ከሌሎቹ ሀገሮች ጋር ስትወዳደር አነስተኛ ሆና ብትታይም በዓለም በጦር ኃይል አራተኛዋ ጠንካራ መንግሥት እንደሆነች ይገመታል፡፡

ከ2000 የስቃይና የስደት ዓመታት በኋላ የእስራኤል ሕዝብ መሰባሰብ በአሁን ጊዜ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ተአምር ነው፡፡

- በቱርኮች ተደምስሳ በነበረችው ምድር የመጀመሪያዎቹ የእስራኤል ሰፋሪዎች በ1870 ዓ.ም ወደ ፓለስታይን ተመልሰው ምድሪቱን መርገጣቸው ተአምር ነበር፡፡





- እስከ 1948 ዓ.ም ድረስ በፓለስታይን የነበሩት አይሁዶች 600,000 ነበሩ፡፡ ይህም ተአምር ነበር፡፡ በሙሴ ጊዜ ከግብፅ ከወጡት የጦር መሣሪያ መታጠቅ ከሚችሉት ጋር በቁጥር ተመጣጣኝ ነበሩ፡፡
- አሰቃቂ የሆነውን የሂትለርን አገዛዝ ተቋቁመው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ከሦስት ዓመት በኋላ ግንቦት 14 ቀን 1948 ዓ.ም የእስራኤል መንግሥት መመስረቱ ተአምር ነበር፡፡
- ለእስራኤል መንግሥት ምስረታ ሁኔታን በማመቻቸት የተባበሩት መንግሥታት በ1947 እስራኤልን ለመክፈል ያደረገው ስምምነት ተአምር ነበር፡፡
- የእስራኤል መንግሥት ከተመሠረተ በኋላ ከእርሷ በኃይል በሚበልጡት ጠላቶቿ በአምስቱም ጦርነቶች አለመሸነፏ ተአምር ነበር፡፡
- በ1991 ዓ.ም. በባህረገልፉ ሰላጤው ጦርነት ከእስራኤል 74 ሰዎች መሞታቸው ተአምር ነበር፡፡ ምክንያቱም 39 የኢራቅ ስከድ ሚሳኤሎች ከተማዋን መትተዋል፡፡ ሁለት ሚሳይሌሎች ቴልአቪብን በመምታት 7000 ቤቶችንና አፓርታማዎችን ደምስሰዋል፡፡

| **የ100 ዓመት የእስራኤል ስደት** | |
|---|---|
| **33 ዓ.ም** - | **የኢየሱስ መስቀል** |
| **70 ዓ.ም** - | **የቤተ መቅደሱ መደምሰስ** |
| **135 ዓ.ም** - | **የባር ኮቼባ አመጽ** |

በቅድስቲቱ ምድር ተአምር በተአምር ላይ ታይተዋል፡፡ ይህንን ዘገባ እስከቻልንበትና እስከወደድንበት ድረስ ልንመዘግብ እንችላለን፡፡ እግዚአብሔር ከዚህ ሕዝብ ጋር እንደ ገና መሥራቱ አስደናቂ ነገር ነው፡፡ ማንኛውም የዓለም ኃይል እስራኤልን ሊያጠፋ አልቻለም፣ አይችልም፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ግንብና የእሳት ቅጥር ስለሆነ ነው (*ዘካ.2:5*)፣ «እርሱ ራሱ ስቤቱ ይቆማል» (ዘካ. 9:8)፡፡

**1897**፣ **1917**፣ **1948** እና **1967** ዓ.ም በእስራኤል የደህንነት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራን የያዙ ዓመታት ናቸው፡፡ እነዚህ ዓመታት ገሃ ያለውንና የማይነቃነቀውን የእስራኤልን መንግሥት ትንሳኤን ያሳያሉ፡፡

*የእግዚአብሔር ጥሪ ለመቶ ዓመታት የእስራኤልን ልጆች ወደ ቅድስት ምድር የሚሰባቸው ሆነ።*

- ከ1870 ዓ.ም የመጀመሪያ የእስራኤል ሰፋሪዎች ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1976 ዓ.ም መሳው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ምድራቸው በእስራኤል ግዛት ስር እስከ ሆነበት ጊዜ ድረስ መቶ ዓመታት አልፈዋል።

*እንደገና ለመቶ ዓመታት ያህል የእስራኤል ታሪክ ወደ ፊት የቀጠለ ነበር።*

*በአሁኑ ጊዜ በእስራኤል እንደዚህ ያለውን እድገት የምንገነዘበው ለምንድን ነው?*

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት የእስራኤል ደህንነት ግልጽ ከሆነ ከመሰባሰባቸው «ከመመለሳቸውና እንደ ገና ከመመስረታቸው ሁኔታ» የሚጀምር ነው። ከዚህ በመቀጠል በመንፈስ ቅዱስ በሆነ የውስጥ መታደስ ይቀጥላል። አስቀድሞ እንዳየነው የእስራኤል መሰባሰብ ቀጠለ። ለዚህም አንድ መግለጫ አለ። ይኸውም ጌታ ሕዝቡን ወደ ቅድስት ምድር እየመለሰ ነው። የማዳን ዕቅድ ካርታ ይህን በግልጽ ያመለክታል። ከስደት ዘመናቸው በኋላ ከተበታተኑበት ቦታ ወደ ቅድስት ምድር መመለሳቸውና የእስራኤል ሕዝብ መነሳት እንደገና ወደ መሲሁ (ክርስቶስ) ይመራናል። መሲሁ (ክርስቶስ) በሚመለስበት ጊዜ ሕዝቡ በእስራኤል ምድር ይሰባሰባሉ *(ሕዝ.37:1-14)* ፣*(ሕዝ.39:28)*።

**የ100 ዓመታት የእስራኤል መመለስ**

**1897 ዓ.ም - የመጀመሪያው የጽዮናውያን ስብሰባ**

**1917 ዓ.ም - የባልፎሩ ውሳኔ**

**1948 ዓ.ም - የእስራኤል መንግሥት ምስረታ**

**1967 ዓ.ም - የስድስቱ ቀን ጦርነት**

*ፖርስትሮይካና ግላስኖስት ስለምን ታየ?*

ይህን የምስራቁ ብሎክ (የምስራቁ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕብረት) ተብሎ የሚጠራውን መሠረት በማድረግ ይህን ለመረዳት ቀላል ሊሆን ቻለ። በፖርስትሮይካና ግላስኖስት በተደረገው የተሃድሶ ትግል በ19 ኛው ምዕት ዓመት ጅማሬ ላይ በሶቪየት





መንግስት ላይ ውድቀትን አስከተለ። ይህም ተአምር 850,000 የሩሲያ አይሁዶች ወደ ቅድስት አገር ለመመለስ የሚያስችላቸውን የመጀመሪያውን ሁኔታ አመቻቸ።

ዳግም ልደት ያገኙ (ክርስቲያን) የክርስቶስን መምጣት በየቀኑ የሚጠባበቀውን ያህል ማንኛውም እውነተኛ አይሁድ በእስራኤል የመሲሁን መምጣት በየቀኑ ይጠባበቃል። ባለፉት 40 ዓመታት እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያደረገው ታሪካዊ ማዳን የመጨረሻው ቀናት ምልክትና «ጌታ ፈጥኖ ሊመጣ ነው» የሚለውን የእኩለ ሌሊቱን ጩኸት መቃረቡን ያለ አንዳች ስህተት የሚያመለክት ምልክት ነው *(ማቴ.25:6)* ።

**ጌታ ቶሎ ይመጣል!**

## 4. እስራኤል በመጨረሻዎቹ ቀናት

ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ የአይሁድ ሕዝብ ከአለም ወደ አባቶቻቸው ምድር ቢመለሱም እስራኤል ባለማመኗ ያለችበት እውነት ወደ ጎን የሚባል አይደለም *(ሮሜ.11:20-23።)* ስለመሲሁ መምጣት የማይቋረጥ ጥበቃ ቢኖራቸውም እስከዚህ ቀን ድረስ ምንም ለውጥ አልሆነም። በአሁኑ ጊዜ አይሁዶች እውነተኛው አዳኝ የሆነውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አልተገነዘቡትም። ይህም ቢሆን ነገሮች እንደዚሁ የሚቀሩ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ እስራኤል መሲሁን ባለመቀበሏ ምክንያት መውደቋን ወደ አሕዛብ ሁሉ መበታተኗንና የተቀደሰችው ምድር በአሕዛብ እንደምትደመሰስ ቢናገርም እነዚህ ነገሮች ሁሉ ፍጻሜ እንዳላቸውም ይናገራል። ከታች በማነጻጸር በተጻፈው «እስከ» የሚለው ይህን ያመለክታል። በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ካርታ ላይ «የእስራኤል ሕዝብ መበታተኑን» ከሚያሳየው ቀይ መስመር ስር በመጨረሻው ቀናት በአስደናቂ ሁኔታ የእስራኤልን ሕዝብ መመለስ የሚያመለክቱ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይገኛሉ። በቅርቡ እግዚአብሔር ራሱ ወደ ሕዝቡ ይመጣል፣ ምክንያቱም «መድኃኒት ከጽዮን ይወጣል፣ ከያዕቆብም ኃጢአተኛነትን ያስወግዳል» ተብሎ ተጽፏልና *(ሮሜ.11:26)*። በበለጠ ለመረዳት ከዚህ በመቀጠል ስለዚህ ከሚናገሩት ጥቅሶች ጥቂቶቹን በማነጻጸር እንመለከታለን።


*የእግዚአብሔር ጥሪ ለመቶ ዓመታት የእስራኤልን ልጆች ወደ ቅድስት ምድር የሚሰባቸው ሆነ፡፡*

- ከ1870 ዓ.ም የመጀመሪያ የእስራኤል ሰፋሪዎች ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1976 ዓ.ም መላው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ምድራቸው በእስራኤል ግዛት ስር እስከ ሆነበት ጊዜ ድረስ መቶ ዓመታት አልፈዋል፡፡

*እንደገና ለመቶ ዓመታት ያህል የእስራኤል ታሪክ ወደ ፊት የቀጠለ ነበር፡፡*

*በአሁኑ ጊዜ በእስራኤል እንደዚህ ያለውን እድገት የምንገነዘበው ለምንድን ነው?*

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት የእስራኤል ደህንነት ግልጽ ከሆነ ከመሰባሰባቸው «ከመመለሳቸውና እንደ ገና ከመመስረታቸው ሁኔታ» የሚጀምር ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠል በመንፈስ ቅዱስ በሆነ የውስጥ መታደስ ይቀጥላል፡፡ አስቀድሞ እንዳየነው የእስራኤል መሰባሰብ ቀጠለ፡፡ ለዚህም አንድ መግለጫ አለ፡፡ ይኸውም ጌታ ሕዝቡን ወደ ቅድስት ምድር እየመለሰ ነው፡፡ የማዳን ዕቅድ ካርታ ይህን በግልጽ ያመለክታል፡፡ ከስደት ዘመናቸው በኋላ ከተበታተኑበት ቦታ ወደ ቅድስት ምድር መመለሳቸውና የእስራኤል ሕዝብ መነሳት እንደገና ወደ መሲሁ (ክርስቶስ) ይመራናል፡፡ መሲሁ (ክርስቶስ) በሚመለስበት ጊዜ ሕዝቡ በእስራኤል ምድር ይሰባሰባሉ *(ሕዝ.37:1-14)* ፣ *(ሕዝ.39:28)*፡፡



*ፖርስትሮይካና ግላስኖስት ስለምን ታየ?*

ይህን የምስራቁ ብሎክ (የምስራቁ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕብረት) ተብሎ የሚጠራውን መሠረት በማድረግ ይህን ለመረዳት ቀላል ሊሆን ቻለ፡፡ በፖርስትሮይካና ግላስኖስት በተደረገው የተሃድሶ ትግል በ19 ኛው ምዕት ዓመት ጅማሬ ላይ በሶቪየት





መንግስት ላይ ውድቀትን አስከተለ፡፡ ይህም ተአምር 850,000 የሩሲያ አይሁዶች ወደ ቅድስት አገር ለመመለስ የሚያስችላቸውን የመጀመሪያውን ሁኔታ አመቻቸ፡፡

ዳግም ልደት ያገኘ (ክርስቲያን) የክርስቶስን መምጣት በየቀኑ የሚጠባበቀውን ያህል ማንኛውም እውነተኛ አይሁድ በእስራኤል የመሲሁን መምጣት በየቀኑ ይጠባበቃል፡፡ ባለፉት 40 ዓመታት እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያደረገው ታሪካዊ ማዳን የመጨረሻው ቀናት ምልክትና «ጌታ ፈጥኖ ሊመጣ ነው» የሚለውን የእኩለ ሌሊቱን ጩኸት መቃረቡን ያለ አንዳች ስህተት የሚያመለክት ምልክት ነው *(ማቴ.25:6)* ፡፡

## ጌታ ቶሎ ይመጣል!

## 4. እስራኤል በመጨረሻዎቹ ቀናት

ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ የአይሁድ ሕዝብ ከአለም ወደ አባቶቻቸው ምድር ቢመለሱም እስራኤል ባለማመን ያለችበት እውነት ወደ ጎን የሚባል አይደለም (*ሮሜ.11:20-23*፡) ስለመሲሁ መምጣት የማይቋረጥ ጥበቃ ቢኖራቸውም እስከዚህ ቀን ድረስ ምንም ለውጥ አልሆነም፡፡ በአሁኑ ጊዜ አይሁዶች እውነተኛው አዳኝ የሆነውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አልተገነዘቡትም፡፡ ይህም ቢሆን ነገሮች እንደዚሁ የሚቀሩ አይደለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እስራኤል መሲሁን ባለመቀበሏ ምክንያት መውደቋን ወደ አሕዛብ ሁሉ መበታተኗንና የተቀደሰችው ምድር በአሕዛብ እንደምትደመሰስ ቢናገርም እነዚህ ነገሮች ሁሉ ፍጻሜ እንዳላቸውም ይናገራል፡፡ ከታች በማነጻጸር በተጻፈው «እስከ» የሚለው ይህን ያመለክታል፡፡ በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ካርታ ላይ «የእስራኤል ሕዝብ መበታተንን» ከሚያሳየው ቀይ መስመር ስር በመጨረሻው ቀናት በአስደናቂ ሁኔታ የእስራኤልን ሕዝብ መመለስ የሚያመለክቱ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይገኛሉ፡፡ በቅርቡ እግዚአብሔር ራሱ ወደ ሕዝቡ ይመጣል፣ ምክንያቱም «መድኃኒት ከጽዮን ይወጣል፣ ከያዕቆብም ኃጢአተኛነትን ያስወግዳል» ተብሎ ተጽፏልና *(ሮሜ.11:26)*፡፡ በበለጠ ለመረዳት ከዚህ በመቀጠል ስለዚህ ከሚናገሩት ጥቅሶች ጥቂቶቹን በማነጻጸር እንመለከታለን፡፡

| | |
|---|---|
| **የእስራኤል ውድቀት** | **ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ** |
| **እስከ** | |
| **« ...በእነርሱ በደል መዳን ለአሕዛብ ሆነ (*ሮሜ11:11*)** | **« ... የአሕዛብ ሙላት እስኪ መጣ ድረስ (ሮሜ.11:25)** |

| | |
|---|---|
| **የእስራኤል መረገጥ** | **የዓለም መንግሥታት ፍጻሜ** |
| **እስከ** | |
| **« ... ኢየሩሳሌም በአሕዛብ የተረገጠች ትሆናለች»** | **«የአሕዛብ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ»** |
| ***(ሉቃ.21:24)*** | ***(ሉቃ. 21:24)*** |

| | |
|---|---|
| **የእስራኤል መፈታት** | **መሲሁን መጥራት** |
| **እስከ** | |
| **«...እነሆ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ሆኖ ይቀርላችኋል።»** | **«[illegible] በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው»** |
| ***(ማቴ.23:38)*** | ***(ማቴ.23:39) ([illegible])*** |

| | |
|---|---|
| **የእስራኤል መታወር** | **የእስራኤል መመለስ** |
| **እስከ** | |
| **« ... እግዚአብሔር የእንቅልፍ መንፈስን እስከ ዛሬ ድረስ ሰጣቸው » (*ሮሜ. 11:8*)** | **«ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ መጽሐፍት በተነበቡ ጊዜ ሁሉ ያ መጋረጃ በልባቸው ይኖራል» (*2ቆሮ. 3:15-16*)** |





## ጥቂቱ የመዋጀት ታሪክ መስመር

## የአሕዛብ ዘመን

በዚህ ምዕራፍ የአሁኑን የመጨረሻውን ቀን ሁኔታ ለመገምገም ወደሚያስችለንና እጅግ አስፈላጊ ወደ ሆነው የመዋጀት ታሪክ ትኩረታችንን መለስ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ይህ ጊዜ በግምት ከ2600 ዓመታት ይጀመርና እስከ አሁን ድረስ እንደቀጠለ ያለ ነው፡፡ በመዋጀት ዕቅድ ካርታ ላይ ዝቅ ብሎ ቀጭን በሆነ ሰማያዊ መስመር የተመለከተ (የተሰመረ) ነው፡፡ ይህም «የአሕዛብ ዘመን» በመባል ተሰይሟል፡፡

እንደምናውቀው ሁሉ በንጉሥ ሰሎሞን ዘመን የእስራኤል ሕዝብ በጣዖት አምልኮ ተጠምደው ነበር፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእስራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔር በመራቅ የአሕዛብ ጣዖታትን አምላኪ ሆኑ፡፡ የእስራኤል ህዝብ «እንደ አሕዛብ ያለ ርኩሰት ሁሉ መተላለፍን አበዙ፣ በኢየሩስሌምም የተቀደሰውን የእግዚአብሔርን ቤት» በማርከስ ለብዙ ዓመታት ኃጢዓት በመሥራት ቀጠሉ (*2ዜና.36:14*)፡፡ እግዚአብሔር ነቢያቱን በመላክ ቢያስጠነቅቃቸውም ንስሐ ለመግባት እንቢተኞች ሆኑ፡፡ የእስራኤል ሕዝብ ግን «የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ እስኪወጣ ድረስ» ወደ እነርሱ በተላኩት ነቢያት ላይ የሚያሾፉ፣ የሚያላግጡና የሚንቋቸው ሆኑ፡፡ (*2ዜና.36:16*)፡፡ በ606 ከ.ክ.ል.በፊት የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር ግብጻውያንን በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ ባለው በከርከሚሽ ድል በማድረጉ (ኤር. 46:2) ባቢሎን በዓለም ገናና መንግሥት መሆን ጀመረ፡፡ በዚሁ ጊዜ እስራኤል በባቢሎናውያን በመሸነፍ ምርኮኛ ሆና ወደ ባቢሎን ተወሰደች፡፡ በኢየሩሳሌም የነበረው ካህኑ ሕዝቅኤል የእግዚአብሔር ክብር እንዴት ከቤተ መቅደሱ እንደተለየ መስክሯል (*ሕዝ.11:23*)፡፡ ከዚህ በኋላ ጥቂት ቆይቶ በ586 ክ.ል.በፊት ባቢሎናውያን ቅድስቲቱን ከተማ ድል በማድረግ ቤተ መቅደሱን እንዳለ ደመሰሱት፡፡ በዚያም የእግዚአብሔር አገዛዝ ከእስራኤል እንዳበቃ በግልጽ ለመታየት ቻለ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር እስራኤልንም ሆነ በእስራኤል በኩል ዓለምን አልመራም፡፡ ይልቁንም ለው ለእግዚአብሔር ባለመሆኑና በሰይጣን ቁጥጥር ስር በመሆን ዓለምን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ የሚፈልግ ሆነ፡፡ በ606 ክ.ል.በፊት በዓለምና በመዋጀት ታሪክ አዲስ ምዕራፍ ተጀመረ፡፡

| | |
|---|---|
| የእስራኤል ውድቀት | ቤተ ክርስቲያን መነጠቅ |
| እስከ | |
| « ...በእነርሱ በደል መዳን ለአሕዛብ ሆነ (ሮሜ11:11) | « ... የአሕዛብ ሙላት እስኪ መጣ ድረስ (ሮሜ.11:25) |

| | |
|---|---|
| የእስራኤል መረገጥ | የዓለም መንግሥታት ፍጻሜ |
| እስከ | |
| « ... ኢየሩሳሌም በአሕዛብ የተረገጠች ትሆናለች» (ሉቃ.21:24) | «የአሕዛብ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ» (ሉቃ. 21:24) |

| | |
|---|---|
| የእስራኤል መፈታት | መሲሁን መጥራት |
| እስከ | |
| «...እነሆ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ሆኖ ይቀርላችኋል።» (ማቴ.23:38) | «አላችኋለሁ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው» (ማቴ.23:39) (... ዳን.9:26) |

| | |
|---|---|
| የእስራኤል መታወር | የእስራኤል መመለስ |
| እስከ | |
| « ... እግዚአብሔር የእንቅልፍ መንፈስን እስከ ዛሬ ድረስ ሰጣቸው » (ሮሜ. 11:8) | «ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ መጽሐፍት በተነበቡ ጊዜ ሁሉ ያ መጋረጃ በልባቸው ይኖራል» (2ቆሮ. 3:15-16) |





## ጥቂሩ የመዋጀት ታሪክ መስመር

## የአሕዛብ ዘመን

በዚህ ምዕራፍ የአሁኑን የመጨረሻውን ቀን ሁኔታ ለመገምገም ወደሚያስችለንና እጅግ አስፈላጊ ወደ ሆነው የመዋጀት ታሪክ ትኩረታችንን መለስ ማድረግ ይኖርብናል። ይህ ጊዜ በግምት ከ2600 ዓመታት ይጀመርና እስከ አሁን ድረስ እንደቀጠለ ያለ ነው። በመዋጀት ዕቅድ ካርታ ላይ ዝቅ ብሎ ቀጭን በሆነ ሰማያዊ መስመር የተመለከተ (የተሰመረ) ነው። ይህም «የአሕዛብ ዘመን» በመባል ተሰይሟል።

እንደምናውቀው ሁሉ በንጉሥ ሰሎሞን ዘመን የእስራኤል ሕዝብ በጣዖት አምልኮ ተጠምደው ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእስራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔር በመራቅ የአሕዛብ ጣዖታትን አምላኪ ሆኑ። የእስራኤል ህዝብ «እንደ አሕዛብ ያለ ርኩሰት ሁሉ መተላለፍን አበዙ፣ በኢየሩሰሊምም የተቀደሰውን የእግዚአብሔርን ቤት» በማርከስ ለብዙ ዓመታት ኃጢዓት በመሥራት ቀጠሉ (*2ዜና.36:14*)። እግዚአብሔር ነቢያቱን በመላክ ቢያስጠነቅቃቸውም ንስሐ ለመግባት እንቢተኞች ሆኑ። የእስራኤል ሕዝብ ግን «የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ እስኪወጣ ድረስ» ወደ እነርሱ በተላኩት ነቢያት ላይ የሚያሾፉ፣ የሚያላግጡና የሚንቋቸው ሆኑ። (*2ዜና.36:16*)። በ606 ከ.ክ.ል.በፊት የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር ግብጻውያንን በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ ባለው በከርከሚሽ ድል በማድረጉ (ኤር. 46:2) ባቢሎን በዓለም ገናና መንግሥት መሆን ጀመረ። በዚሁ ጊዜ እስራኤል በባቢሎናውያን በመሸነፍ ምርኮኛ ሆና ወደ ባቢሎን ተወሰደች። በኢየሩሳሌም የነበረው ካህኑ ሕዝቅኤል የእግዚአብሔር ክብር እንዴት ከቤተ መቅደሱ እንደተለየ መስክሯል (*ሕዝ.11:23*)። ከዚህ በኋላ ጥቂት ቆይቶ በ586 ክ.ል.በፊት ባቢሎናውያን ቅድስቲቱን ከተማ ድል በማድረግ ቤተ መቅደሱን እንዳለ ደመሰሱት። በዚያም የእግዚአብሔር አገዛዝ ከእስራኤል እንዳበቃ በግልጽ ለመታየት ቻለ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር እስራኤልንም ሆነ በእስራኤል በኩል ዓለምን አልመራም። ይልቁንም ሰው ለእግዚአብሔር ባለመሆኑና በሰይጣን ቁጥጥር ስር በመሆን ዓለምን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ የሚፈልግ ሆነ። በ606 ክ.ል.በፊት በዓለምና በመዋጀት ታሪክ አዲስ ምዕራፍ ተጀመረ።

## 1. *የአራቱ ዓለም ኃያላን መንግሥታት መነሳት*

ስለ አራቱ ታላላቅ ሰው ገዛሽ *መንግሥታት* መነሳት የሚናገረው የትንቢት ዕንብርት የሚገኘው በትንቢተ ዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ ነው። በአጠቃላይ ይህ መጽሐፍ እነዚህን *መንግሥታት* በሁለት ክፍሎ ያሳያል። በዳንኤል ምዕራፍ 2 ያለው የናቡከደነጸር ሕልም የእነዚህን አራት ውጫዊ ገጽታና በዓለም ከፍ ብለው መግነናቸውን የሚያሳይ ነው። ምዕራፍ ሰባት ደግሞ የእነዚህን አራት ነገሥታት ሰይጣናዊ ሲሆኑ ክፋትን የተሞላ ውስጣዊ ባሕርያቸውን ያሳያል። ስለመንግሥታቱ መነሳት የበለጠ ለመረዳት እንዲያስችለን በመጀመሪያ ዳንኤል ምዕ. 2 እና 7ትን እንመለከታለን።

### የናቡከደነጾር ሕልም

በባቢሎን ምርኮ ዘመን ነቢዩ ዳንኤል በንጉሡ ናቡከደነጾር አደባባይ ያገለግል ነበር። በዚህ አገልግሎቱ ላይ ሳለ ዳንኤል ከእግዚአብሔር የተለየ ስጦታ ሕልምን የመተርጎም ስጦታን አገኘ። ንጉሡ ናቡከደነጾር ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ መንፈሱን ያስጨነቀውን ሕልም ለንጉሡ ለመፍታት የተቻለው ነበር። *(ዳን.2:1)*

ንጉሡ ናቡከደነጾር በሰው አምሳል የሆነውን ግዙፍና የሚያንጸባርቅ ምስል አይቶ ነበር። ይህ ምስል ራሱ ወርቅ፣ ደረትና ክንዱ ብር፣ ሆድና ወገቡ ነሐስ፣ ሁለቱ ጭኖቹ ብረት፣ እግሮቹና ጣቶቹ ብረትና ሸክላ የተደባለቁ ነበር። የሰው እጅ ሳይነካው ድንጋይ ከተራራ ተፈንቅሎ በዚህ ምስል ላይ በመውደቅ ምስሉን ምንም ሳያስቀርለት እንደ አውድማ ዕብቅ ፈጨው። ከተራራ የተፈነቀለው ድንጋይ ምድርን የሚሞላ ታላቅ ተራራ ሆነ *(ዳን.2:31-35)* ።

ይህ ምን ማለት እንደሆነ ለንጉሡ ሊነግረው የቻለ ማንም አልነበረም። «በኋለኛው ዘመን የሚሆነውን ለንጉሡ ያሳየውን የዚህን ሕልም ትርጉም ሊፈታ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነበር» *(ዳን.2:36)*።

የናቡከደነጾር ሕልም በማከታተል በምድር ላይ የሚነሱትንና የሚወድቁትን አራት ታላላቅ *መንግሥታትን* የሚያሳይ ነበር። በዚህ ራዕይ የተመልካቹ ትኩረት በእነዚህ በሚነሱት ነገሥታት ላይ በሚታየው አንጸባራቂ በሆነው ውጫዊ ገጽታ ላይ ነበር። ከወርቁ፣ ከብሩና ወ.ዘ.ተ. ተጨማሪ በሳይ ናቡከደነጾር እጅግ ግዙፍና አንጸባራቂ ምስል ነበር የተመለከተው። (ዳን.2:31)





እነዚህ ባሕርያት የእነዚህ የአራቱን *መንግሥታት* ውጫዊ ገጽታና እንደዚሁም በመንግሥታቸው ከፍታና ገናንነት ፍጻሜ ላይ መውደቃቸውን ያሳያሉ።

### የወርቁ ራስ

*«አንተ ንጉሥ ሆይ ! የሰማይ አምላክ መንግሥትንና ኃይል፣ ብርታትንና ክብርን የሰጠህ የነገሥታት ንጉሥ አንተ ነህ። በሚቀመጡበትም ስፍራ ሁሉ የሰው ልጆችንና የምድር አራዊትን የሰማይ ወፎችንም በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶሃል፣ ለሁሉም ገዥ አድርጎሃል አንተ የወርቁ ራስ ነህ። (ዳን.2:37-38)*

ከአራቱ የዓለም *መንግሥታት* የመጀመሪያው በወርቁ ራስ የተመሰለው ከ606-538 ክ.ል.በፊት ድረስ የነበረው ባቤል ወይም ባቢሎን በመባል የሚጠራው የናቡከደናጾር *መንግሥት* ነበር። የመጀመሪያው ገዢ በመሆን እስከ 562 ክ.ል.በፊት ድረስ ገዛ። ከእርሱ በኋላ እስከ 560 ክ.ል.በፊት ዮርማሮዲክ ነገሠ። ቀጥሎም ኒሪማሊሶር እስከ 556 ክ.ል.በፊት ድረስ ገዛ። ከእርሱ ቀጥሎ ደግሞ እስከ 539 ክ.ል.በፊት ድረስ ናቦኒዱስ ገዛ። የመጨረሻው የባቢሎን *መንግስት ንጉሥ* በአሽናፊዎቹ በፋርስ *መንግሥት* የተገደለው ብልጣሶር ነበር። ሞቱም በዳንኤል ተመስከረ *(ዳን.5:30)*።

### የብሩ ደረት

*«ካንተ በኋላ ካንተ የሚያንስ ሌላ መንግሥት ይነሳል» (ዳን. 2:39)* ።

ሁለተኛው የዓለም *መንግሥት* የሜዶንና የፋርስ *መንግሥት* ሲሆን *(ዳን.6:1)* የተነሳው ከባቢሎን *መንግሥት* መውደቅ በኋላ በ536 ክ.ል.በፊት ነበር። ቢሆንም ይህ *መንግሥት* እንደ ባቢሎን የገነነ አልነበረም። ምክንያቱም በትንቢት በብር የተመሰለ ስለነበር ነው። የሜዶንና የፋርሱ *ንጉሥ* ቂሮስ የዓለም ገዢ ሆነ። በ536 ክ.ል.በፊት አይሁዶች ወደ እስራኤል ምድር እንዲመለሱ ፈቀደ (*መጽሐፈ ዕዝራንና ነህምያን* ይመልከቱ)። ከዚያም የሜዶንና የፋርስ *መንግሥት* ለ200 ዓመታት ያህል ቀጥሎአል።

## ሆድና ወገቡ ነሐስ የሆነው መንግሥት

*«ከዚያም በኋላ በምድር ሁሉ ላይ የሚገዛ ሌላ ሦስተኛ የነሐስ መንግሥት ይነሳል»* (ዳን. 2:39)::

በ333 ክ.ል.በፊት የሜዶንና የፋርስን መንግሥት የተካው ሦስተኛው የዓለም መንግስት የግሪክ መንግስት ነበር:: ይህ መንግስት በሃይል ገንኖ የተነሳው የመቄዶንያው ንጉሥ ትልቁ እስክንድር የሜዶንና የፋርስን ንጉሥ ሳልሳዊ ዳርዮስን

በትንሿ እስያ በምትገኘው በቂሊቂያ በተደረገው በኢሱስ ጦርነት ላይ ድል ባደረገበት ጊዜ ነበር:: በሚቀጥሉት አስርት ዓመታት ውስጥ ትልቁ እስክንድር የግሪክን መንግሥት እስከ ሕንድና አፍጋኒስታን ድረስ አስፋፋ:: በ328 ክ.ል.በፊት ትልቁ እስክንድር የባክትሪያን ንጉስ ሴት ልጅን ሮክሳኒን አገባ:: ሆድና ወገቡ ናስ የሆነው የዚህን ወጣት መሪ ግዛት መስፋፋትን ያሳያል::


ትልቁ እስክንድር ሰኔ. 13 ቀን በ323 ክ.ል.በፊት በወባ በሽታ በባቢሎን ሞተ:: ሲሞት እድሜው ሰላሳ ሦስት አመት ነበር:: በእርሱ ሞት ምክንያት የዲአዶኪ ጦርነቶች ፈነዱ:: አራቱ ቅርብ ጓደኞቹና የጦር መኮንኖቹ የነበሩት ድል በማድረግ ትልቁን የግሪክን መንግሥት በመያዝ ለአራት ተከፋፈሉት:: ዲአዶኪ በመባል የሚታወቁ አራት መንግሥታት ተመሠረቱ:: ካሳንደር ግሪክን፣ ሊስማኩስ ትሬስንና በትንሿ እስያ ያሉትን ሴሉከስ ሶርያንና ባቢሎንን፣ በጥሊሞስ ግብፅን በመያዝ ነገሡ:: እነዚህ አራቱ መንግሥታት ለብዙ ጊዜ አልቀጠሉም:: አንድ በአንድ በሮማውያን ድል ተመቱ::





### ናቡከደነጾር ያየው የአራቱ መንግሥታት ሕልም

ዳን. 2:1-49



**የወርቁ ራስ** — አንደኛው የዓለም መንግሥት የባቢሎን- መንግሥት 606-536 ክ.ክ.ል.በ

**የብር ደረት የሆነው** — ሁለተኛው የዓለም መንግስት የሜዶንና የፋርስ መንግሥት 536-333 ክ.ክ.ል.በ

**የነሐስ ወገብ የሆነው** — ሦስተኛው የዓለም መንግሥት የግሪክ መንግሥት 333-31 ክ.ክ.ል.በ

**ጭኖቹ የብረት የሆነው** — አራተኛው የዓለም መንግሥት የሮም መንግሥት 31 ክ.ክ.ል.በ.

ንጉሡ ናቡከደነጾር ያየው ምስል በሰው ምስል የተመሰለ ነበር:: ይህም የሰው አገዛዝ በምድር ላይ መመስረቱን ያመለክታል:: በባቢሎን መንግሥት መመስረት የሰው አገዛዝ ተመሰረተ::

## ጭኖቹ ብረት የሆነው መንግስት

*«አራተኛውም መንግሥት ሁሉን እንደሚቀጠቅጥና እንደሚያደቅቅ ብረት ይበረታል እነዚህንም ሁሉ እንደሚፈጭ ብረት ይቀጠቅጣል ይፈጭማል» (ዳን.2:40)::*

በዳንኤል ትንቢት አራተኛው የዓለም መንግስት የሮም መንግስት ነበር:: ሮማውያን ዓለምን ለመቆጣጠር እንደ ብረት ባለ ጥንካሬ ተዋግተዋል:: የዓለም ኃይል አገዛዝ መውደቅ የጀመረው የሮሙ ቄሳር ኦታቪያን መስከረም 2 ቀን 31 ኢ.ክ.ል.በ. የመጨረሻው የዲአዶካውያንን መንግሥት ታዋቂ በሆነው በአድቲዩም የባሕር ጦር ድል ባደረገበት ጊዜ ነበር:: ይህ መንግሥት በግብጿ ንግስት በክሌኦፓትራ ቁጥጥር ስር ነበር:: ክሌኦፓትራ የእስክንድር ጀኔራል የነበረው የጰጥሌምስ ተወላጅ ነበረች:: ቀሪው የግሪክ መንግሥት ከእርሷ መውደቅ ጋር ጠፋ:: ሮም በዚያን ጊዜ ለነበረው የዓለም መንግስት የበላይ ገዢ ሆነች:: አውግስጦስ ተብሎ የተጠራው ጁሊየስ ኦክታቪያን ከ27 ክ.ል.በ. ጀምሮ የሮም ገዢ ሆነ:: በእርሱ ዘመን የእግዚአብሔር ልጅ ጌታ ኢየሱስ ተወለደ (*ሉቃ.2:1-7*):: ጌታ ኢየሱስ በተሰቀለ ጊዜ ጢባርዮስ ቄሳር የሮም ገዢ ነበር (*ዮሐ.19:13-19*):: ለብዙ ምዕተ ዓመታት የሮም መንግሥት የዓለምን መንግስት ታሪክ ተቆጣጠረች:: በ395 ዓ.ም የሮም መንግስት የዓለምን መንግሥት የምስራቁ የሮም መንግሥትና የምዕራቡ የሮም መንግስት በመባል ተከፋፈለ:: በዳንኤል ትንቢት በብረት የተመሰሉት ሁለቱ ጭኖች እነዚህን መንግስታት የሚያመለክቱ ነበሩ:: (*ዳን.2:33፣40-43*)

ከዚህ በታች ያለው ማፕ የሚያሳየው በ395 ዓመት የሮም ግዛት መከፋፈል
1. የምዕራቡ የሮም መንግስት
2. የምስራቁ የሮም መንግስት







- ይህ ስዕል የሚያሳየው የሰውን ግማሽ የታችኛውን የአካል ክፍል ነው:: እግሮቹ የሚያሳዩት የሮምን በሁለት ክፍሎች መከፈልን ነው::
- እነኚህ በሁለቱ መንግስታት ስር የነበሩ አገሮች በሙሉ አንድነት ሆነው በአሁኑ ዘመን የዓለም አቀፍ የሆነውን ፀረ ክርስቶስ መንግስት በመገንባት ላይ ናቸው::





ይህ የብረቱ መንግሥት ወደ ፍጻሜ መጥቷል:: የምዕራቡ የሮም መንግሥት በ476 ዓ.ም. ወደቀ:: የምስራቁ የሮም መንግሥት ከ1000 ዓመታት በኋላ በ1453 ዓ.ም. ወደቀ::

አራቱ የዓለም ኃያላን መንግስት ዛሬ ታሪክ ሆነው ቀርተዋል:: በትንቢት እንደተነገረው ተነስተው ወድቀዋል:: እጅ ሳይነካው ተፈንቅሎ ስለ ወረደው ድንጋይ ወደ ፊት በስፋት እንመለከታለን:: (ዳን.2:34)

## የአራቱ አራዊት ገጽታ

ብልጣሶር የባቢሎን ንጉሥ ሆኖ በሚገዛበት ዘመን ነቢዩ ዳንኤል ሌላ ራዕይ ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ነበር:: ዳንኤልም ተናገረ እንዲህም አለ:-

*«በሌሊት በራዕይ አየሁ እነሆም አራቱ የሰማይ ነፋሳት በታላቁ ባሕር ላይ ይጋጩ ነበር:: አራትም ታላላቅ አራዊት ከባሕር ወጡ:: እያንዳንዲቷም ልዩ ልዩ ነበረች» (ዳን.7:2-3)::*

ጥቂት ጥቅሶች አለፍ ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ አራቱ አራዊት ምን እንደሆኑ እንዲህ በማለት ይገልጻል::

*«እነዚህ አራቱ ታላላቅ አራዊት ከምድር የሚነሱ አራት ነገሥታት ናቸው» (ዳን.7:17)::*

እነዚህ መንግስታት ማን እንደሆኑ ቀደም ብለን አውቀናቸዋል:: ቀደም ብሎ ናቡከደነጾር በሕልም ያያቸው አራቱ የዓለም መንግሥታት ባቢሎን፣ ሜዶንና ፋርስ፣ ግሪክና ሮም ናቸው:: በመጀመሪያ ግዙፍ በሆነው በሰው ምስል የታዩ ነበር (ዳን.2:31-45):: አሁን ደግሞ በአራት ታላላቅ አራዊት አምሳያ ተገልጸዋል:: እኛ የምንነጋገረው ስለእነዚሁ የዓለም መንግስታት ነው:: ምክንያቱም የመዋጀት ታሪክ ከእነዚህ አራቱ መንግስታት ውጪ የሚሰራ አይደለም:: ጠለቅ ብለን የዳንኤልን ምዕራፍ ሰባት ስንመለከት እነዚህ አራዊት በተፈጥሮ ከሚታዩት አራዊት የተለዩ አስፈሪ ግዙፍ የሆኑ አራዊት ናቸው:: ምክንያቱም የመጀመሪያው አውሬ እንደ ንስር ክንፍ ባለው አንበሳ (ዳን.7:4)፣ ሁለተኛው አውሬ በድብ የተመሰለው «ተነስተህ እጅግ ሥጋ ብላ» የሚል ትዕዛዝ ተቀባይ በሆኑ (ዳን.7:5)፣ ሦስተኛው አራት ክንፎች ባሉት ነብር የተመሰለው (ዳን. 7:6)፣ አራተኛው አውሬ ደግሞ አስር ቀንዶች ባለው አስፈሪ ሁሉን በሚያደቅ፣ ተመስለው የተገለጹ ናቸው (ዳን.7:7):: በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ እንደነዚህ ያሉ አስፈሪና ታላቅ አራዊት የትም

አይገኙም:: ዳንኤል «ሕልሙን ጻፈ ዋነኛውንም ነገር ተናገረ» በማለት ጌታ የገለጠለትን በትክክል መመስከሩ ተጽፎ ይገኛል (ዳን.7:1):: ስለዚህም የእነዚህ ራዕይ ፍቺ ምን እንደሆነ መጠየቅ ይኖርብናል:: በመጀመሪያ እንደዚህ አይነቱን ገለጻ ለመጽሐፍ ቅዱስ እንግዳ ነገር እንዳይደለ ልንገነዘብ ያስፈልገናል:: ብዙ ጊዜ በአይን የማይታዩትን መንፈሳዊ እውነቶችን ለመግለጽ ይጠቅማል:: ለምሳሌ ጌታ ኢየሱስ የማይታየውን የሰይጣንን ኃይላት «በእባብና በጊንጥ» በመምሰል ገልጾታል (ሉቃ.10:19):: እነዚህን ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ከእግራቸው በታች እንዲረግጧቸው ስልጣን ሰጥቷቸዋል:: በተመሳሳይ መልኩ በብሉይ ኪዳን «በአንበሳና ዘንዶ» በራዕይ ዮሐንስ ደግሞ ሰይጣን በ «ታላቅ ቀይ ዘንዶ» ተመስሎ ተገልጿል (መዝ.(91):13፤ ራዕ.12:3፤9):: የዳንኤል አዲሱ ራዕይ ከዚህ በላይ ከተገለጹት ምሳሌዎች ጋር ተመሳሳይ ነው:: በዳንኤል ምዕራፍ ሁለት ላይ ከታዩት አራቱ የዓለም ኃያላን መንግስታት ጋር እነዚህ ታላላቅ አራዊት የተመሳሰሉ መንግስታት ናቸው በአራት ንጽጽር ተመድበዋል:: ባቢሎን በአንበሳ፣ ሜዶንና ፋርስ በድብ፣ ግሪክ አራት ራሶች ባለው ነብርና ሮም አስር ቀንዶች ባለው አስፈሪ አውሬ ተመስለዋል:: በዳንኤል ምዕራፍ ሰባት የሚነሱት መንግስታት አራዊት ናቸው ማለቱ ሳይሆን ውስጣዊ የሆነ የአውሬ ባሕርይ እንዳላቸው ሲያሳይ በዳንኤል ምዕራፍ ሁለት ያለው ደግሞ ውጫዊ አስደናቂ ሁኔታቸውን ያሳያል:: የዳንኤል ምዕራፍ ሰባት የአራቱ አራዊት ራዕይ ድብቅ ሰይጣናዊና አጥፊ የሆነውን የአውሬነት ባሕርያቸውን ያሳያል::

### «ሰው ያለ እግዚአብሔር አውሬ መሆኑ»

ባቢሎን፣ ሜዶንና-ፋርስ፣ ግሪክና ሮም እግዚአብሔር የለሽ መንግስት ነበሩ:: ያለ እግዚአብሔር መግዛታቸው ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን በመቃረን (በእግዚአብሔር ምትክ) ይገዙ ነበር::

እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረበት ጊዜ በዚህች ምድር ላይ የመግዛትን ስልጣን ሰጠው (ዘፍ.1:28):: እግዚአብሔር ከአዳም ጋር ቃል ኪዳን አደረገ (ሆሴ. 6:7):: ሰውም ይህችን ውብ ዓለም በእግዚአብሔር ስልጣን ስጪነት እንዲገዛ አድርጎ ሾመው:: ሰው በመውደቁ የሰይጣንና የሞት ተገዢ ሆነ::





«እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ» (ዘፍ.3:5) ለሚለው የሰይጣን ሹክሹክታ የሚታዘዝ ሆነ:: ሰው ራሱን የራሱ አምላክ በማድረግ በእግዚአብሔር ላይ መመካቱን ትቶ ዓለምን ለመግዛት ፈለገ:: እግዚአብሔር ከኖህ ጥፋት በኋላ ሰዎችን በምድር ላይ ለመበተን ተገድዶ ነበር፣ ምክንያቱም እግዚአብሔርን የሚቃረን መንግስት ለመመስረት አስበው ስለነበር ነው (ዘፍ.11:1-9)::

ይህች መንግስት በዓለም ከፍተኛ የሆነችው ባቢሎን ነበረች:: ሆኖም እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ለመመስረት አብርሃምንና የእስራኤልን ነገድ መረጠ:: ኢየሩሳሌምን የእርሱ ማደሪያ ቦታ፣ መካከለኛና፣ የዓለም ዋና ከተማ እንድትሆን አደረጋት:: እስራኤል ከዓላማዋ በመውደቋና ጣዖት አምላኪ በመሆኗ ለአራቱ ታላላቅ የዓለም መንግስታት መነሳት በር ተከፈተ:: በ606 ከ.ል.በፊት ከአራቱ ኃያላን መንግስታት ባቢሎን የመጀመሪያዋ በመሆን ተነሳች::

ዳንኤል ምዕራፍ አራት ከእነዚህ አራቱ የዓለም መንግስታት ውስጥ የመጀመሪያውን መንግስትና ገዢ የባቢሎንን ንጉስ የናቡከደነጾርን ትዕቢትና ውድቀት ይገልጻል::

*«ይህች እኔ በጉልበቴ ብርታት፣ ለግርማዬ ክብር፣ የመንግሥቴ መኖሪያ እንድትሆን ያሠራኋት ታላቂቱ ባቢሎን አይደለችምን?»* በማለት በትዕቢት ቃል ራሱን ሲያከብር ይታያል (ዳን. 4:30)::

ይህ ባሕርይ በኃጢዓት የተሞላውንና አመጸኛ የሆነውን የሰውን ባሕርይ ይገልጻል:: ናቡከደናጾር ራሱን አምላክ አደረገና ራሱን አምላኪ ሆነ:: ወደፊት እንደምናየው የክርስቶስ ተቃዋሚም ባሕርይ በተመሳሳይ ሁኔታ የተመሰለ ነው:: እርሱም አንድ ቀን ራሱን አምላክ በማድረግ ያውጃል:: (2ተሰ.2:4)

## ዳንኤል ያየው የአራቱ አራዊት ምስል

ዳን. 7:1-28

| | | |
|---|---|---|
|  | የአንበሳ ምስል | አንደኛው የዓለም መንግሥት<br>**የባቢሎን መንግሥት**<br>606-536 ኪ.ክ.ል.በ |
|  | የድብ ምስል | ሁለተኛው የዓለም መንግስት<br>**የሜዶንና የፋርስ መንግሥት**<br>536-333 ኪ.ክ.ል.በ |
|  | ባለ አራቱ ራስ ነብር | ሦስተኛው የዓለም መንግሥት<br>**የግሪክ መንግሥት**<br>333-31 ኪ.ክ.ል.በ |
|  | አስር ቀንድ ያለው አውሬ | አራተኛው የዓለም መንግሥት<br>**የሮም መንግሥት**<br>31 ኪ.ክ.ል.በ. |

እነዚህ አስፈሪ እንስሶች ለዳንኤል የታዩት ከውጭ ያማረና ያሸበረቀው የአራቱ መንግስታት መልክ ሳይሆን በውስጣቸው ያለው አስቀያሚው የአጋንንታዊውን እውነተኛ ጠባይ ነው።





የባቢሎናውያን ንጉስ ትዕቢት አስደንጋጭ ወደ ሆነው ውድቀት መራው:: ለሰባት ዓመታት እግዚአብሔር መንግስቱን ወሰደበት:: «በዚያም ሰዓት ነገሩ በናቡከደነጾር ላይ ደረሰ፣ ጠጉሩም እንደ ንስር፣ ጥፍሩም እንደ ወፎች፣ እስኪረዝም ድረስ ከሰዎች ተሰይቶ ተሰደደ፣ እንደ በሬም ሣር በላ፣ አካሉም በሰማይ ጠል ረሰረሰ» (*ዳን.4:33*):: የወርቁ ራስ የሆነ ናቡከደነጾር ንስሃ እስኪገባ ድረስ እንደ እንስሳ ሆነ:: መጽሐፍ ቅዱስ አስደናቂ የሆነው የሰው ውጫዊ ባሕርይ የውስጡ የአውሬነቱ ባሕርይ መሆኑን በግልጽ ያስረዳል:: አመጸኛ የሆነው ንጉስ እንደ እንስሳ በምድረ በዳ የሚኖር ሆነ (ዳን. 2:38):: በዚህም እንደ አራዊት በሆነ ባሕርዩ ለዓለም ተገለጸ::

*«ሰብዕና ያለ እግዚአብሔር እንደ እንስሳ ይሆናል»* ወይም በቀላሉ *«ሰው ያለ እግዚአብሔር ሲሆን እንስሳ ይሆናል ማለት ነው።»*

ብዙ ጊዜ የዓለም መሪዎች ፣ ኃያላንና ነገስታት በሚያጠፋ እንስሳ ይመሰላሉ:: የዓለምን ሰዎች ይጨቁናሉ፣ ለራሳቸው መጠቀሚያ ያደርጋሉ፣ ጦርነቶችን ያስነሱና ደም ያፋስሳሉ:: እግዚአብሔርን በመቃረን ራሳቸውን በእግዚአብሔር ምትክ በማድረግ የሚገዙ አመጸኛ መሪዎች ራሳቸው አውሬ ከመሆናቸው ሌላ በእነርሱ የሚገዙትም ሰዎች ደግሞ እንደ አውሬዎች ይሆናሉ:: አመጸኛውና ሰይጣናዊው ዓለምን የሚያስጨንቀው የመጨረሻው አውሬ ፀረ ክርስቶስ ይሆናል::

## 2. ፀረ ክርስቶስና መንግሥቱ

ወደ ፍጻሜው ዘመን እየተጠጋን በሄድን ቁጥር ግልጽ ሆኖ የሚታየው ነገር ፀረ ክርስቶስ መንግስት እንዴት እንደሚመሠረትና ፀረ ክርስቶስ እንዴት ፈጥኖ እንደሚገለጽ ነው:: የአዲስ ኪዳን አማኞች እንደመሆናችን መጠን በመጨረሻዎቹ ቀናት ስለ ፀረ ክርስቶስ የመንግስቱ መገለጥ እንዴት እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛውን ገለጻ ልናውቅ ይገባናል::

ፀረ ክርስቶስ መንግስት በድንገት ከሰማያት የሚወርድ አይደለም:: ነገር ግን ደህንነትን ባላገኙ በብዙ ቢሊዮን በሚቆጠሩ በዚህች ምድር ላይ በሚኖሩ ሰዎች ሕብረት የሚመሰረት ነው:: እነሳሉ ከማንኛውም ነገድ፣ ባሕል፣ የፓለቲካ፣ ኢኮኖሚና የሃይማኖት ክፍል ቢሆን ልዩነት የሚያመጣ አይደለም:: የክርስቶስ ተቃዋሚ መንግስት የሰዎች (ኃጢዓተኝነት) እየጨመረ የመሔዱ ውጤት ነው::

ፀረ ክርስቶስ በዓለም የሚገለጠው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኃይልና በክብር ከመመለሱ በፊት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል (2ተሰ.2:1-12) ። በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ የሚኖሩት ሕዝቦች «ይድኑ ዘንድ የእውነትን ቃል ስላልተቀበሉ» በእርሱ እጅ ይወድቃሉ። (2ተሰ.2:10)

የእውነተኛው ንጉስ እውነተኛው ወንጌል ለሁለት ሺህ ዓመታት ገደማ በመላው ዓለም ተሰብኳል (ዮሐ.14:6፣18:37)። አውሮፓ የክርስቲያን አምብርት በመባል ተገልጻ ነበር። ምክንያቱም ወንጌል በስፋት በዚያ ተሰብኮ ስለነበር ነው። ከጊዜ በኋላ ሁኔታዎች ሁሉ ተለዋወጡ። ከሁለት ሺህ የጸጋና የደህንነት ዓመታት የመጨረሻ ፀረ ክርስቶስ ሲነሳ ወንጌልን በተቃወሙትና በናቁት እምነታቸውንም በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባላደረጉት ላይ ፍርድ ይሆናል። ስለሆነም ፀረ ክርስቶስ መነሳት የሚሆነው ወንጌልን ሰምተው ለመቀበል ባልፈለጉት ሕዝብ መካከል ነው። ፀረ ክርስቶስ መነሳት በምድር ላይ ከሰዎች አመጸኝነትና ክርስቶስን ከመቃወም ጽዋ መሙላት የተነሳ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ፀረ ክርስቶስና መንግሥቱ የሚናገሩ ስምንት ምዕራፎች አሉ። እነርሱም:-

| | |
|---|---|
| 1. ዳንኤል 2:1-49 | 5. ማቴዎስ 24:1-31 |
| 2. ዳንኤል 4:1-34 | 6. 2ተሰሎንቄ 2:1-12 |
| 3. ዳንኤል 7:1-28 | 7. 1ዮሐንስ 2:18-22 ፣4:3 |
| 4. ዳንኤል 9:1-27 | 8. ራዕይ 11:1-19፣21 |

ስለዚህ ትምህርት ጥናት ስናደርግ የሚከተሉትን ሁለት ነገሮች መዘንጋት የለብንም።

## 1. ፀረ ክርስቶስ ሰው ነው

ሰዎች የሚያከብሩት፣ የመጨረሻው አስተዳዳሪና መሪ በኃጢዓት የተሞላው የመጨረሻው ሰው ነው። በሰዎች ላይ ከፍተኛውን ክፋት የሚያሰራጭ ነው። ፀረ ክርስቶስ ሰዎች የሚጠብቁት ከፍተኛና የተአምራት ሰው ነው። በሰዎች መካከል ሰላምን የሚመሰርት መስሎ የሚታይ ብቻ ሳይሆን የዓለምን የኢኮኖሚ ችግርና ዓመጽ እንደሚያስወግድም ተስፋ የሚሰጥ ነው።





## 2. ፀረ ክረስቶስ መንግስት አለው

ዛሬ ይህ ጨለማ መንግስት ጥላውን በዓለም ላይ እያጠላ ነው። ጠቅላላ ዓለምም ወደዚሁ እየደረሰ ነው። በሚቀጥለው ጥናታችን የፀረ ክርስቶስ መንግስት መሠረቱ የት እንደሆነ እንመለከታለን።

## የፀረ ክርስቶስ መንግስት እና አራቱ- የጥንቱ ዓለም መንግስታት መታደስ

የፀረ ክርስቶስ መንግስት ከጥንቱ ከአራቱ የዓለም ኃያላን መንግስታት ከነበሩት ከባቢሎን፣ ከሜደንና ፋርስ፣ ከግሪክና ከሮም አዋላኝ አገሮች፣ ባሕሎችና መንፈሳዊ ኃይላት የሚመሠረት ነው። አዲስ ኪዳን ይህን ግልጽ በሆነ መንገድ እንደሚከተለው ያሳያል።

*«አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፣ አስር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፤ በቀንዶቹም ላይ አስር ዘውዶች፣ በራሶቹም ላይ የስድብ ስም ነበር። ያየሁትም አውሬ ነብር ይመስል ነበር፣ እግሮቹም እንደ ድብ እግሮች፣ አፉም እንደ አንበሳ አፍ ነበር። ዘንዶውም ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን ሰጠው»* (ራዕ.13:1-2)።

በዚህ በራዕይ የታየውና የሚነሳው አውሬ ፀረ ክርስቶስ ነው። ባሕሩ እንደ (መዝ.(65):7፤ ኢሳ.17:12-13) የውሃ ባሕር ሳይሆን ሰዎችና አሕዛብ ናቸው።


ይህንን ትንቢት ለመረዳት መለስ ብለን በብሉይ ኪዳን የተጠቀሰውን አንድ ጊዜ መቃኘት ይኖርብናል። ነቢዩ ዳንኤል በራዕዩ በአራት አራዊት የተመሰሉትን አራቱን የዓለም መንግሥታት (ባቢሎንን፣ ፋርስን፣ ግሪክንና ሮምን) አይቷል (ዳን.1:18)። እነዚህ አራዊት የወጡት ከባሕር ውስጥ ነበር። ባሕሩም ሕዝብን የሚያመለክት ነበር። ዳን.7:1-28 ከራዕ.13:1-2 ጋር ስናወዳድር ብሉይና አዲስ ኪዳን ትንቢታዊ ግንኙነት እንዳላቸው በግልጽ እንረዳለን። ዳንኤል አራቱ የዓለም መንግስታት ከሕዝብ እንደሚወጡ እንዳየው ሁሉ ዮሐንስ ደግሞ ፀረ ክርስቶስ ከሕዝብ መካከል እንደሚነሳ ገልጿል። ስለዚህ አውሬ ጠለቅ ብለን ስንመለከት የአራቱ አራዊት ጥምር ሆኖ እናገኘዋለን ምክንያቱም:-

1. አፉ አንበሳ
2. እግሮቹ የድብ
3. መልኩ የነብርና
4. አስር የብረት ቀንዶች ነበሩት

በዚህ ገለጻ የጥንቶቹን የዓለም መንግስታት ለመረዳት የሚያስቸግር አይደለም። ወደ ፊት እነዚህ ነገስታት የሚነሱት ተራ በተራ ሳይሆን በአንድ ላይና በአንድ ጊዜ ነው። በመጨረሻዎቹ ቀናት የሚነሳው ፀረ ክርስቶስ የእነዚህ የአራቱ መንግስት መታደስ ነው እንጂ ሌላ አለመሆኑ ግልጽ ሊሆን ያሻል። በደህንነት ዕቅድ ካርታ ላይ ያለው ጥቁሩ ቀስት ወደዚህ ህብረት የሚያመለክት ነው።

አራቱ የጥንቱ መንግስታት ባቢሎን፣ ሜዶንና ፋርስ ግሪክና ሮም ተራ በተራ እየከሰሙ የሔዱ ቢሆንም በፍጻሜ ዘመን እንደገና ተመልሰው ይታያሉ። የሚከተለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስዕላዊ መግለጫ መመልከት ይቻላል።

1. «አፉ የአንበሳ» የሆነው በዳን.7:4 በአንበሳ ከተመሰለው ከባቢሎን የሚመጣ ነው።
2. «እግሮቹ በድብ» የተመሰለው በዳን.7:5 በድብ ከተመሰለው ከሜዶንና ፋርስ የሚመጣ ነው።
3. «በነብር መልክ» የተመሰለው በዳን7:6 አራት ራሶችና አራት ክንፎች ባለው በግሪክ መንግሥት የተመሰለውን ያመለክተናል።
4. በ «አስር የብረት ቀንዶች» የተመሰለው በዳን.7:7-8 አስር ቀንዶችና ብረት ጥርሶች ባሉት የተመሰለውን የሮምን መንግሥት ያስታውሰናል።








በአራቱ በወደቁት መንግሥታት የነበሩት ባሕርያት በመጨረሻው ቀናት በሚነሳው ፀረ ክርስቶስ በአንድነት ተጣምረው የሚታዩ ይሆናሉ። የዚህ አስፈሪ የሆነው መንግስት የግዛቱ እምብርት በባቢሎን፣ በሜዶንና ፋርስ፣ በግሪክና በሮም ድንበሮች ላይ ይሆናል። ስለሆነም የዚህ ፀረ ክርስቶስ መነሳት ከእነዚህ መንግስታት ከአንዱ ነው ብሎ መጠበቁ የማያስኬድ ነው። ለምሳሌ ከሮም መንግስት ብቻ ይነሳል ስለዚህ በተሰጠው ትንቢታዊ ቃል ግልጽ የሆነ ነገር ነው። ልክ አስፈሪ የሆነው «አውሬ ከባሕር እንደ ወጣ» (ራዕ. 13:1) አራቱ ታላላቅ አውሬዎች (ዳን. 7: 3-17) አራቱ የጥንቱ መንግስታት አንድ ሆነው በመታደስ ፀረ ክርስቶስ መንግስት ይገለጻሉ።

| የፀረ ክርስቶስ መንግስት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዳን.2:1-49 | | ዳን.7:1-28 | የዓለም መንግሥታት | ፀረ ክርስቶስና መንግሥቱ |
| ራሱ የወርቅ |  | አንበሳ | ባቢሎን | የአንበሳ አፍ |
| ደረቱ የብር | | ድብ | ሜዶንና ፋርስ | እግሮቹ የድብ |
| ወገቡ የነሐስ | | ባለ አራቱ ራስ ነብር | ግሪክ | አካሉ የነብር |
| ጭኖቹ የብረት | | ባለ አራቱ ቀንድ አስፈሪው አውሬ | ሮም | የአስፈሪው አውሬ አስሩ ቀንዶች |

## *የፀረ ክርስቶስ መንግስት - የሰይጣን አምሳያ*

እንደተለመከትነው የሚመጣው ፀረ ክርስቶስ መንግስት በአዲስ ኪዳን ውስጥ በአስፈሪ አውሬ ተመስሏል:: ከተጠቀሱት አስር ቀንዶች ሌላ ይህ አውሬ ሰባት ራሶች አሉት (ራዕ.13:1):: ቀጥሎ በምናደርገው ጥናት የዚህን አውሬ የኋላ ታሪኩንና ፍቺውን ስንመረምር ይህን ትንቢት በትክክል ልንረዳ እንችላለን::

ይህ አውሬ ሰምን ሰባት ራሶች ኖሩት ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንደገና ስለ አራቱ መንግስታት (ስለ ባቢሎን፣ ሜዶንና ፋርስ፣ ግሪክና ሮም) በዳንኤል መጽሐፍ በአራት ታላላቅ አራዊት የተመሰሉትን መመልከት ይኖርብናል (ዳን.7:1-28):: በአውሬው ላይ ስላሉት ራሶች ጠለቅ ብለን ገለጻውን ስንመረምር የሚከተለውን እንረዳለን::

| | | |
|---|---|---|
| ባቢሎን | በአንበሳ የተመሰለው | አንድ ራስ |
| ሜዶንና ፋርስ | በድብ የተመሰለው | አንድ ራስ |
| ግሪክ | በነብር የተመሰለው | አራት ራስ |
| ሮም | በአስፈሪው አውሬ የተመሰለው | አንድ ራስ |
| | *በጠቅላላ ድምር* | ሰባት ራስ |

## ተምሳሌተ ሰይጣን

ከላይ በተመለከትነው ንጽጽር *በራዕ.13:1* ባለው ፀረ ክርስቶስ መንግስት ላይ ያሉት ሰባቱ ራሶች *በዳንኤል 7* የተጠቀሱት የአራቱ የዓለም መንግስት ራሶች ጠቅላላ ድምር ነው:: ይህ እንደገና የሚያረጋግጥልን ነገር በመጨረሻዎቹ ቀናት ባቢሎን ሜዶንና ፋርስ፣ በግሪክና ሮም ከፀረ ክርስቶስ መንግስት ጋር በማበር ተሐድሶ እንደሚያደርጉ ነው:: ሆኖም በዚህ ነጥብ ላይ አንድ እርምጃ ወደፊት መሔድ ይኖርብናል:: እየተነጋገርን ያለው የሰባቱ ራሶች ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ በመጨረሻው መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሰው ይገኛሉ::

*«ሌላ ምልክት በሰማይ ታየ፣ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶችም ነበሩት፣ በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩ» (ራዕ.12:3)*

ይህ ትልቁ ዘንዶ ማን ነው? ዘንዶው «የቀደመው እባብ ዲያብሎስና ሰይጣን» እንደሆነ ተገልጾአል (*ራዕ.12:9*):: ፀረ ክርስቶስ መንግስት ሰባት ራሶች የተመሰለው የሰይጣን ተምሳሌት ናቸው:: ሰይጣን ራሱ ደግሞ በሰባት ራሶች ባሉት ዘንዶ ተመስሏል:: ስለሆነም ሰይጣን ዋናው ተምሳሌት ነው::





*ምሳሌ:- አራቱ የዓለም መንግስታት*

ሰይጣን በዓለም ላይ ስልጣን የተሰጠው ስለሆነና *(ሉቃ.4:6)* እስራኤልም የእግዚአብሔር ሕዝብ ከመሆን በመውደቁ (እግዚአብሔር በሕዝቡ በኩል መለኮታዊ አገዛዙን ያላደረገበት ምክንያት) በ606 ክ.ል.በፊት የዓለም ስልጣን ላልዳኑት ሕዝብ የተሰጠ ሆነ:: ይህን የአሕዛብ ዘመን ጅማሬ ብለን እንጠራዋለን:: *(ሉቃ.21:24)* ሰይጣን ሳይከለከል በእነዚህ አሕዛብ ስልጣኑን ሊለማመድ ቻለ:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ከዚህ ቀጥሎ እንደምንመለከተው በጠቅላላው በራሱ የተመሰሉትን ሰባት ታላላቅ ራሶች ከእነዚህ የዓለም አሕዛብ እንዲወጡ አድርጓል::

| | |
|---|---|
| **1ኛው ራስ: የባቢሎን አገዛዝ** | **ናቡከደነፆርና ተከታዮቹ(ወራሾች)** |
| **2ኛው ራስ: የሜዶንና ፋርስ አገዛዝ** | **ቂሮስና ተከታዮች (ወራሾቹ)** |
| **የግሪክ አገዛዝ** | **ትልቁ እስክንድርና አራቱ ተከታዮች** |
| **3ኛው ራስ: ግሪክ፣ሶርያ ፣ባቢሎን** | **ሴሉከስና ወራሾቹ** |
| **4ኛው ራስ: ግሪክ፣ግብፅ** | **በጥሊሞስና ወራሾቹ** |
| **5ኛው ራስ: ግሪክ፣ትሬስና ትንሹ እስያ** | **ሊስማኩስና ወራሾቹ** |
| **6ኛው ራስ: ግርክ፣ሜቄዶን** | **ካሳንደርና ወራሾቹ** |
| **7ኛው ራስ: የሮም አገዛዝ** | **አውግስጦስና ወራሾቹ** |

በገሃዱ ዓለም እነዚህ ሰባቱ ራሶች የአራቱ የጥንቱ መንግስታት አመጸኛ በሆኑት ሰባት መንግስታት ተመስለዋል:: ገሃድ ባልሆነው ዓለም ግን ከእነዚህ መንግስታት በስተኋላ ሆኖ የሚገዛውን ሰይጣንን ይወክላሉ:: ሆኖም አራቱ የዓለም መንግስታት ከመንግስቶቻቸው (ሰባት ራሶች) ጋር ጠፍተዋል:: ስለዚህ ሊመጣ ላለው ለክርስቶስ ተቃዋሚ መንግስት ሰይጣናዊ ምሳሌ ሆነዋል::

## ምስሉ: ፀረ ክርስቶስና መንግሥቱ

በሚቀጥለው ገጽ ላይ ያለውን መግለጫ እንመልከት:: ሰባቱም ራሶች በመልክዓ ምድር አቀማመጥ የሚያገኙት በዓለም የእግዚአብሔር ዋና ከተማ በሆነችው በኢየሩሳሌም አጠገብ (አካባቢ) ነው:: በመግለጫው ላይ ያሉት ሰባቱ ጥቋቁር ነጠብጣብ የሰባቱ ሰይጣናዊ ራሶች የኃይላቸው እምብርት ናቸው:: ሰባቱ ዋና ከተማዎች በአራቱ የዓለም መንግሥታት ውስጥ የተመለከቱት ናቸው:: ሦስቱ በእስያ፣ ሦስቱ በአውሮፓና አንዷ በአፍሪካ ነው የሚገኙት::

## የፀረ ክርስቶስ መንግስት - የሰይጣን አምሳያ

እንደተለመከትነው የሚመጣው ፀረ ክርስቶስ መንግስት በአዲስ ኪዳን ውስጥ በአስፈሪ አውሬ ተመስሏል:: ከተጠቀሱት አስር ቀንዶች ሌላ ይህ አውሬ ሰባት ራሶች አሉት (ራዕ.13:1):: ቀጥሎ በምናደርገው ጥናት የዚህን አውሬ የኋላ ታሪኩንና ፍቺውን ስንመረምር ይህን ትንቢት በትክክል ልንረዳ እንችላለን::

ይህ አውሬ ለምን ሰባት ራሶች ኖሩት ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንደገና ስለ አራቱ መንግስታት (ስለ ባቢሎን፣ ሜዶንና ፋርስ፣ ግሪክና ሮም) በዳንኤል መጽሐፍ በአራት ታላላቅ አራዊት የተመሰሉትን መመልከት ይኖርብናል (ዳን.7:1-28):: በአውሬው ላይ ስላሉት ራሶች ጠለቅ ብለን ገለጻውን ስንመረምር የሚከተለውን እንረዳለን::

| | | |
|---|---|---|
| ባቢሎን | በአንበሳ የተመሰለው | አንድ ራስ |
| ሜዶንና ፋርስ | በድብ የተመሰለው | አንድ ራስ |
| ግሪክ | በነብር የተመሰለው | አራት ራስ |
| ሮም | በአስፈሪው አውሬ የተመሰለው | አንድ ራስ |
| | *በጠቅላላ ድምር* | ሰባት ራስ |

### ተምሳሌተ ሰይጣን

ከላይ በተመለከትነው ንጽጽር *በራዕ.13:1* ባለው ፀረ ክርስቶስ መንግስት ላይ ያሉት ሰባቱ ራሶች *በዳንኤል 7* የተጠቀሱት የአራቱ የዓለም መንግስት ራሶች ጠቅላላ ድምር ነው:: ይህ እንደገና የሚያረጋግጥልን ነገር በመጨረሻዎቹ ቀናት ባቢሎን ሜዶንና ፋርስ፣ በግሪክና ሮም ከፀረ ክርስቶስ መንግስት ጋር በማበር ተሐድሶ እንደሚያደርጉ ነው:: ሆኖም በዚህ ነጥብ ላይ አንድ እርምጃ ወደፊት መሔድ ይኖርብናል:: እየተነጋገርን ያለው የሰባቱ ራሶች ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ በመጨረሻው መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሰው ይገኛሉ::

*«ሌላ ምልክት በሰማይ ታየ፣ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶችም ነበሩት፣ በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩ» (ራዕ.12:3)*

ይህ ትልቁ ዘንዶ ማን ነው? ዘንዶው «የቀደመው እባብ ዲያብሎስና ሰይጣን» እንደሆነ ተገልጾአል *(ራዕ.12:9)*:: ፀረ ክርስቶስ መንግስት ሰባት ራሶች የተመሰለው የሰይጣን ተምሳሌት ናቸው:: ሰይጣን ራሱ ደግሞ በሰባት ራሶች ባሉት ዘንዶ ተመስሏል:: ስለሆነም ሰይጣን ዋናው ተምሳሌት ነው::





*ምሳሌ:- አራቱ የዓለም መንግስታት*

ሰይጣን በዓለም ላይ ስልጣን የተሰጠው ስለሆነና *(ሉቃ.4:6)* እስራኤልም የእግዚአብሔር ሕዝብ ከመሆን በመውደቋ (እግዚአብሔር በሕዝቡ በኩል መለኮታዊ አገዛዙን ያላደረገበት ምክንያት) በ606 ክ.ል.በፊት የዓለም ስልጣን ላልዳኑት ሕዝብ የተሰጠ ሆነ:: ይህን የአሕዛብ ዘመን ጅማሬ ብለን እንጠራዋለን:: *(ሉቃ.21:24)* ሰይጣን ሳይከለክል በእነዚህ አሕዛብ ስልጣኑን ሊለማመድ ቻለ:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ከዚህ ቀጥሎ እንደምንመለከተው በጠቅላላው በራሱ የተመሰሉትን ሰባት ታላላቅ ራሶች ከእነዚህ የዓለም አሕዛብ እንዲወጡ አድርጓል::

| | |
|---|---|
| 1ኛው ራስ: የባቢሎን አገዛዝ | ናቡከደነፆርና ተከታዮቹ(ወራሾች) |
| 2ኛው ራስ: የሜዶንና ፋርስ አገዛዝ | ቂሮስና ተከታዮቹ (ወራሾቹ) |
| የግሪክ አገዛዝ | ትልቁ እስክንድርና አራቱ ተከታዮቹ |
| 3ኛው ራስ: ግሪክ፣ ሶርያ ፣ባቢሎን | ሴሉከስና ወራሾቹ |
| 4ኛው ራስ: ግሪክ፣ ግብፅ | በጥሊሞስና ወራሾቹ |
| 5ኛው ራስ: ግሪክ፣ ትሬስና ትንሹ እስያ | ሊስማኩስና ወራሾቹ |
| 6ኛው ራስ: ግርክ፣ ሜቄዶን | ካሳንደርና ወራሾቹ |
| 7ኛው ራስ: የሮም አገዛዝ | አውግስጦስና ወራሾቹ |


በገሃዱ ዓለም እነዚህ ሰባቱ ራሶች የአራቱ የጥንቱ መንግስታት አመጸኛ በሆኑት ሰባት መንግስታት ተመስለዋል:: ገሃድ ባልሆነው ዓለም ግን ከእነዚህ መንግስታት በስተኋላ ሆኖ የሚገዛውን ሰይጣንን ይወክላሉ:: ሆኖም አራቱ የዓለም መንግስታት ከመንግስቶቻቸው (ሰባት ራሶች) ጋር ጠፍተዋል:: ስለዚህ ሊመጣ ላለው ለክርስቶስ ተቃዋሚ መንግስት ሰይጣናዊ ምሳሌ ሆነዋል::

### ምስሉ: ፀረ ክርስቶስና መንግሥቱ

በሚቀጥለው ገጽ ላይ ያለውን መግለጫ እንመልከት:: ሰባቱም ራሶች በመልክዓ ምድር አቀማመጥ የሚያገኙት በዓለም የእግዚአብሔር ዋና ከተማ በሆነችው በኢየሩሳሌም አጠገብ (አካባቢ) ነው:: በመግለጫው ላይ ያሉት ሰባቱ ጥቋቁር ነጠብጣብ የሰባቱ ሰይጣናዊ ራሶች የኃይላቸው እምብርት ናቸው:: ሰባቱ ዋና ከተማዎች በአራቱ የዓለም መንግሥታት ውስጥ የተመለከቱት ናቸው:: ሦስቱ በእስያ፣ ሦስቱ በአውሮፓና አንዷ በአፍሪካ ነው የሚገኙት::

በመጨረሻው ቀናት ይህ በትክክል በድጋሚ ይከናወናል:: የጥንቱ አራቱ መንግስታት በፀረ ክርስቶስ መንግስት በአጠቃላይ ተሣድሶ በማድረግ እንደሚገለጹ ሁሉ ሰባቱም ራሶች በ(ራዕ.13:1-2) እንደተገለጸው በድጋሚ ይታያሉ:: እነዚህ ሰባት ራሶች በኢየሩሳሌም ዙሪያ ተቀምጠው የሚገኙት ስውር የሆነው የሰይጣናዊ ኃይላት ናቸው (ዳን.10:13፣20):: እነዚህ አጭር የሆኑት አስተያየቶች ሰይጣን ከራሱ ሌላ ምስል እንደማያመጣ ይገልጻሉ:: እንዳለፈው የጥንቱ ዘመን ምስያ በመጨረሻው ቀናት በፀረ ክርስቶስ መንግስት በተመሳሳይ ታይቶ በማይታጠቅ ሁኔታ ግልጽ ሆኖ ይታያል::

የአራቱ የዓለም መንግስታት በአንድ ጊዜ በድጋሚ የመታየቱ እውነት ዓለም ከዚህ በፊት ያላየችው የተጠናከረ ኃይል መታየቱን ያመለክታል:: የሰው ዘር ከዚህ ከተጠናከረው ኃይል ውጤት ማንኛውም አስቸጋሪ የሆነውን ነገር የሚጋፈጥ ይሆናል:: ያለፉት የአራቱ መንግስታት መሪዎች ድል ባደረጓቸው በአዋሳኝ ሀገሮች ላይ ስልጣናቸውን ተለማምደው ነበር:: ሆኖም በቅርቡ አስፈሪ የሆነው መንግስት መካከለኛ (እምብርት) በታውን በጥንቱ መንግስታት ድንበሮች ላይ ይመሠርታል:: ከዚህ ጠንካራ የሆነው ኃይላቸው በዓለም ሁሉ የሚሠራጭ ይሆናል:: አንድ ሰው በማይገመት ሁኔታ በአመጸኝነቱ ሁሉን ከስሩ በማድረግ ይህን መንግስት ይመራል:: ስለ መሪነቱ በሰይጣን ቁጥጥር ስር ካሉት ሰዎች የአምላክነት ክብርና ሙገሳ ይስበዋል:: ይህ ሰው ተራ ሰው ሳሆን አውሬ የሆነ፣ ጨካኝ ሰው ነው:: አዲስ ኪዳን ይህን መሪ በሚገባቸው በአውሬ በመምሰል ይገልጸዋል:: *(ራዕ.11:7፣13:1፣2፣12፣ 14፣15፣17፣18፣ 14:9፣11፣ 15:2፣ 16:13 17:3፣7፣8፣11፣13፣16፣17፣ 19:19-20፣ 20:10)*:: ስለዚህ ያለው ገለጻ «የክርስቶስ ተቃዋሚ» የሚለው ለእኛ የተለመደ ገለጻ ነው:: *(1ዮሐ.2:18፣ 22፣ 4:3፣ 2ዮሐ.7)*









**እነዚህ በእንግሊዘኛው 121 ላይ ያለው ካርታ ማንም ሳይሆን ሰይጣን ራሱ ነው ይህን መንግስትና የክርስቶስ ተቃዋሚውን ሰው የሚቆጣጠረው:: ከሁሉቱም ሰይጣናዊ ምሳሌውን እናገኛለን::**

| ተምሳሌት | እምሳያና | ተመሳሳይነት |
|---|---|---|
| ሰይጣን | አራቱ የዓለም መንግሥታት | የፀረ ክርስቶስ መንግሥት |
| ራዕ.12:3-9 | ዳን.7:1-28 | ራዕ.13-19 |
| ሰይጣን በማይታየው ዓለም ውስጥ ሰባት ራሶችና አስር ቀንድ ባለው ዘንዶ በመመሰል ይታያል:: እርሱ የኃጢአትና የክፋት ምንጭና መነሻ፣ ለዚህ ለወደቀ ዓለም በሚታየውና በማይታየው ላይ ገዢ ነው:: | በብሉይ ኪዳን አራቱ የዓለም መንግስታት በሚስፈሩ አራዊት ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች ባላቸው ተመስለዋል:: የማይታየውን የሰይጣንን ተምሳሌት በሚታየው ዓለም ይፈጥራሉ::<br>• ባቢሎን<br>• ሜዶንና፣ፋርስ<br>• ግሪክ<br>• ሮም | በአዲስ ኪዳን የፀረ ክርስቶስና መንግስቱ ከጥልቁ በሚወጣ አስፈሪ አውሬ በመመስል ይታያል:: ይህ አውሬ በሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች ተመስሏል:: የሰይጣን ተምሳሌነትና የዳን.7 መንግስታት በመምሰል ይታያል:: |

በመጨረሻው ቀናት ይህ በትክክል በድጋሚ ይከናወናል:: የጥንቱ አራቱ መንግስታት በፀረ ክርስቶስ መንግስት በአጠቃላይ ተሃድሶ በማድረግ እንደሚገለጹ ሁሉ ሰባቱም ራሶች *በ(ራዕ.13:1-2)* እንደተገለጸው በድጋሚ ይታያሉ:: እነዚህ ሰባት ራሶች በኢየሩሳሌም ዙሪያ ተቀምጠው የሚገዙት ስውር የሆነው የሰይጣናዊ ኃይላት ናቸው *(ዳን.10:13፤20)*:: እነዚህ አጭር የሆኑት አስተያየቶች ሰይጣን ከራሱ ሌላ ምስል እንደማያመጣ ይገልጻሉ:: እንዳለፈው የጥንቱ ዘመን ምስያ በመጨረሻው ቀናት በፀረ ክርስቶስ መንግስት በተመሳሳይ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ግልጽ ሆኖ ይታያል::

የአራቱ የዓለም መንግስታት በአንድ ጊዜ በድጋሚ የመታየቱ እውነት ዓለም ከዚህ በፊት ያላየችው የተጠናከረ ኃይል መታየቱን ያመለክታል:: የሰው ዘር ከዚህ ከተጠናከረው ኃይል ውጤት ማንኛውም አስቸጋሪ የሆነውን ነገር የሚጋፈጥ ይሆናል:: ያለፉት የአራቱ መንግስታት መሪዎች ድል ባደረጓቸው በአዋሳኝ ሀገሮች ላይ ስልጣናቸውን ተለማምደው ነበር:: ሆኖም በቅርቡ አስፈሪ የሆነው መንግስት መካከለኛ (ኢምብርት) ቦታውን በጥንቱ መንግስታት ድንበሮች ላይ ይመሠርታል:: ከዚህ ጠንካራ የሆነው ኃይላቸው በዓለም ሁሉ የሚሠራጭ ይሆናል:: አንድ ሰው በማይገመት ሁኔታ በአመጸኝነቱ ሁሉን ከስሩ በማድረግ ይህን መንግስት ይመራል:: ስለ መሪነቱ በሰይጣን ቁጥጥር ስር ካሉት ሰዎች የአምላክነት ክብርና ሙገሳ ይሰጠዋል:: ይህ ሰው ተራ ሰው ሳሆን አውሬ የሆነ፣ ጨካኝ ሰው ነው:: አዲስ ኪዳን ይህን መሪ በሚገዛቸው በአውሬ በመምሰል ይገልጸዋል:: *(ራዕ.11:7፣13:1፣2፣12፣ 14፣15፣17፣18፤ 14:9፣11፤ 15:2፣ 16:13 17:3፣7፣8፣11፣13፣16፣17፣ 19:19-20፣ 20:10)*:: ስለዚህ ያለው ገለጻ «የክርስቶስ ተቃዋሚ» የሚለው ለእኛ የተለመደ ገለጻ ነው:: *(1ዮሐ.2:18፤ 22፣ 4:3፣ 2ዮሐ.7)*








**እነዚህ በእንግሊዘኛው 121 ላይ ያለው ካርታ ማንም ሳይሆን ሰይጣን ራሱ ነው ይህን መንግስትና የክርስቶስ ተቃዋሚውን ሰው የሚቆጣጠረው:: ከሁሉቱም ሰይጣናዊ ምሳሌውን እናገኛለን::**

| ተምሳሌት | አምሳያና | ተመሳሳይነት |
|---|---|---|
| ሰይጣን | አራቱ የዓለም መንግሥታት | የፀረ ክርስቶስ መንግሥት |
| ራዕ.12:3-9 | ዳን.7:1-28 | ራዕ.13-19 |
| ሰይጣን በማይታየው ዓለም ውስጥ ሰባት ራሶችና አስር ቀንድ ባለው ዘንዶ በመመሰል ይታያል:: እርሱ የኃጢአትና የክፋት ምንጭና መነሻ፣ ለዚህ ለወደቀ ዓለም በሚታየውና በማይታየው ላይ ገዢ ነው:: | በብሉይ ኪዳን አራቱ የዓለም መንግስታት በሚስፈሩ አራዊት ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች ባላቸው ተመስለዋል:: የማይታየውን የሰይጣንን ተምሳሌት በሚታየው ዓለም ይፈጥራሉ::<br>• ባቢሉን<br>• ሜዶንና፣ፋርስ<br>• ግሪክ<br>• ሮም | በአዲስ ኪዳን የፀረ ክርስቶስና መንግስቱ ከጥልቁ በሚወጣ አስፈሪ አውሬ በመመሰል ይታያል:: ይህ አውሬ በሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች ተመስሏል:: የሰይጣን ተምሳሌነትና የዳን.7 መንግስታት በመምሰል ይታያል:: |

## ፀረ ክርስቶስ – የመጨረሻው የዓለም ገገር

የሚለው በግሪኩ ቋንቋ «አንቲ-ክሪስቱስ» ማለት ሲሆን «የክርስቶስ ምትክ (ተቃዋሚ) ማለት ነው:: አንቲ ማለት ምትክ /ተቃራኒ/ «ክርስቶስ» ማለት ደግሞ «የተቀባ» ማለት ነው:: በዕብራይስጡ ደግሞ «መሲህ» የሚለው ቃል የተቀባ ማለት ነው:: መሲሁ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በእግዚአብሔርና በመንፈስ ቅዱስ የተቀባውና የእስራኤል ሕዝብ ንጉስ ነው(*ማቴ.3:16-17፤ ሉቃ.1:31-35*) በሰይጣን የተቀባው ፀረ ክርስቶስ የሚያታልል በአመጽ የተሞላና ተቃዋሚው የእስራኤል ንጉሥ ይሆናል::

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት የሰው ዘር እንደ ፀረ ክርስቶስ ዓለም ከአሁን በፊት ከቶ አይታው የማታውቀው መንግስት ይሆናል:: አንድ ቀን መላው ዓለም ከቁጥጥሩ ስር ይሆናል::

*«ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው:: በነገድና በወገን፣ በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው» (ራዕ.13:7)::*

በተመሳሳይ ሁኔታ ይህችን ዓለም ለመግዛት የመጨረሻው መሪ ይሆናል፤ ክርስቶስ በክብር በሚገለጥበት ጊዜ በእርሱ ላይ በመፍረድ ያጠፋዋል::

*«በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመፀኛ ይገለጣል» (2ተሰ.2:8)::*

### የፀረ ክርስቶስ ስሞች

ፀረ ክርስቶስ የሆነውን የአመፅ ሰው መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ የተለያዩ ስሞችን በመስጠት ይገልጸዋል:: በዮሐንስ መፅሐፍ አራት ጊዜ ብቻ « ፀረ ክርስቶስ» በመባል ተገልጿል (*1ዮሐ.2:18-22፤4:3፤2ዮሐ.7*):: በሌሎች ቦታዎች ደግሞ በሚከተሉት ሁኔታ ተገልጿል::

| | |
|---|---|
| «ኃጢያተኛ ሰው» | (2ተሰ.2:3) |
| የእግዚአብሔር «ተቃዋሚ» | (2ተሰ.2:4) |
| «አመጸኛ» | (2ተሰ.2:3-4) |
| «በስሙ የሚመጣ» | (ዮሐ.5:43) |
| «አውሬው» | (ራዕ.11:7፤13:1፤14:11፤17:8) |

እነዚህ መግለጫዎች መጽሐፍ ቅዱስ ፀረ ክርስቶስን ብቻ ለመግለጽ የተጠቀመባቸውና በተጨማሪም በመጨረሻው የዓለም መሪ ውስጥ ያለውን ሰይጣናዊ ባሕርይ የሚገልጹ ናቸው:: በዓለም ግን የታወቀ ስብእዊ መጠሪያ ስም ይኖረዋል::





### የፀረ ክርስቶስ ተፈጥሮ

እንደ ዓለም ገገር ፀረ ክርስቶስ ሰይጣናዊ የሆነ ሥጋ የለበሰ ሰው ነው:: ይህም ማለት ከዚህ በፊት በዓለም ላይ ከቶ ታይቶ የማይታወቅ ሥጋ ለበስ ሰይጣን ነው:: ካለፉት ነገስታት ወይም መሪዎች መካከል በኃይል በመግዛት ይህን መሪ የሚስተካከል አይኖርም:: ፀረ ክርስቶስ የሚነሳው ከሕዝብ መካከል ነው፣ የሚወለደውም ከሴት ነው:: እዚህ ሊገለጽ የሚያስፈልገው ነጥብ ቢኖር አባት ያለውና ከሰው ከፍ ባለ ሁኔታ የሚወለድ መሆኑ ነው:: ምክንያቱም ሰይጣን የእግዚአብሔርን ነገር ቅጅ የሚያደርግ ስለሆነ የክርስቶስን ከድንግል መወለድ ቅጅ ያደርጋል:: ማርቲን ሉተር «ሰይጣን እንደ ጦጣ የእግዚአብሔር ነገር ቅጂ የሚያደርግ ነው»: ብሉታል:: ጌታ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ አሠራር አባቱ እግዚአብሔር የሆነና ምድራዊ አባት የሌለው፣ ከሰው በተለየ መንገድ የተወለደ ነው (*ማቴ.1:18-23፤ ሉቃ.1:31-35*) ዮሴፍ አሳዳጊው ሞግዚት አባቱ ነበር:: ሰይጣንም ፀረ ክርስቶስ ምድራዊ አባት የሌለው በማስመሰል ከተፈጥሮ በተለየ ሁኔታ በሰይጣናዊ መንገድ ከስጋ እንዲወለድ ያደርገዋል::

<table>
<tr><th colspan="7">መለኮታዊና ስላሴና ሰይጣናዊ ሦስትዮሽ</th></tr>
<tr><td>አቃጅ<br>እግዚአብሔር ሰላ ደህንነት አቀደ</td><td>እግዚ<br>አብሔር<br>አብ</td><td></td><td>ሰይጣን<br>አቃጅ</td><td>ፀረ<br>እግዚአብሔር</td><td>ሰይጣን<br>በሰው<br>ውስጥ</td><td>የሰው ዘር<br>በፖለቲካ<br>ሕብረት<br>ማድረግ</td></tr>
<tr><td>አስፈጻሚ<br>ጌታ ኢየሱስ<br>መዋጀት ፈጸመ</td><td>እግዚ<br>አብሔር<br>ወልድ</td><td></td><td>ፀረ ክርስቶስ<br>አስፈጻሚ ነው</td><td>ፀረ<br>ወልድ</td><td>ሰይጣን<br>በሥጋ</td><td>የሰው ዘር<br>በኢኮኖሚ<br>ሕብረት<br>ማድረግ</td></tr>
<tr><td>ፈጻሚ<br>መንፈስ ቅዱስ<br>በእኛ ውስጥ<br>ደህንነትን<br>ይፈጽማል::</td><td>እግዚ<br>አብሔር<br>መንፈስ<br>ቅዱስ</td><td></td><td>ሀሰተኛው<br>ነቢይ<br>ፈጻሚው<br>ይሆናል</td><td>የመንፈስ ቅዱስ<br>ተቃራኒ</td><td>ሰይጣን<br>በመንፈስ</td><td>የሰው ዘር<br>በሃይማኖት<br>ሕብረት<br>ማድረግ</td></tr>
</table>

መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን እንደዚህ አይነት ነገር ሲደረግ እንደሚቻል አመልክቷል:: *በዘፍ.6:4* ከጥፋት ውሀ በፊት ቁመታቸው ረጃጅም የሆኑ (በእብራይስጡ ኔፍሊም) ተብለው የሚጠሩ እንደነበሩ እናነባለን:: እነዚህ ረጃጅም ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆችና የሰው ልጆች ግንኙነት ውጤት ነበሩ:: በሌላ አነጋገር ሰዎች በአጋንንት የተያዙበትና መናፍስት ስጋ በመልበስ ከሴቶች ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ማድረግ የቻሉበት ጊዜ ነበረ ማለት ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ተፈጥሮአዊ ባልሆነ መንገድ ውጤት የተገኙትን «ኔፍሊም» ብሎ

ይጠራቸዋል:: ይህም ማለት በህገወጥ የተረገዙ፣ በመጥፎ መንገድና ተፈጥሮአዊ ባልሆነ መንገድ የተወለዱ ማለት ነው:: እነዚህ ሰይጣናዊ ዝርያዎች በጥፋት ውሀ ጊዜ ጠፍተዋል:: በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ሞገስ ያገኙት የኖህ ቤተሰብ የሆኑት ስምንት ሰዎች ብቻ በመርከብ ተጠብቀው ዳኑ (*ዘፍ.6:8*)::

በሚሊዮን መስከ በአረማውያን ከተማዎች እንደዚህ ዓይነት ነገሮች እንደተከሰቱ ያስተምሩናል:: ወደ ቻይና ሔዶ የነበረው ትልቁ ሚስዮናዊ ህድሰን ቴይሰር ሰሰ ቀበሮ ምስል አማልክቶችና በእነዚህ ቀበሮ መሰል አጋንንታዊ መያዝ በቻይና ብዙ አስከፊ ስራ እንደሚሰራ ሪፖርት አድርጓል:: የቻይና ሴቶች የቀበሮ ራስ ባላቸው ፍጥረታት በመያዝ ሌሊት በሥጋቸው መከራ እንደሚቀበሉ ተናግሯል:: እነዚህ ሴቶች ግልጽ የሆነ ውሳኔ ወስነው ጌታ ኢየሱስን የግል አዳኛ ቸው አድርገው ሲቀበሉ በራዕይ ይታዩ የነበሩት ይጠፉና ሴቶቹም ነጻ ይወጡ ነበር:: ለምሳሌ:- የግሪክ ጥንታዊ ታሪክ አማልክት ከሴቶች ጋር ወሲባዊ ግንኙነት በማድረግ ግማሽ አማልክት የሆኑ ወንዶች ልጆችን እንደወለዱ ይናገራል::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ከመምጣቱ በፊት እንደ ኖህ ዘመን እንደሚሆን ሲናገር ይህን ነገር በድጋሚ እንደሚሆን ማመልከቱም ጭምር ነበር (*ማቴ.24:37-39*):: ዛሬም እንኳን ሴቶች እንዴት ከሰይጣንና ከመንፈሳዊ ሠራዊቱ ጋር እንደሚደንሱ የሚገልጹ አስፈሪ ፊልሞች እየተሠሩ ናቸው:: እነዚህ ፊልሞች ወንዶች ልጆች እንዴት ሰይጣናዊ ኃይል እንደሚኖራቸው ይገልጻሉ:: ፀረ-ክርስቶስ በሰይጣን አባትነት በሰይጣናዊ አሠራር ከተፈጥሮ አሰራር ውጪ በሆነ ርኩሰት ድርጊት የሚወሰድ ፍጡር ነው:: ግልጽ በሆነ ቃል «የሰይጣን ልጅ» ነው ማለት ነው:: ፀረ ክርስቶስ የሚገሰጥና በተቃራኒው የጌታ ኢየሱስን ቦታ በዓለም የሚይዝ ከሆነ ሰይጣናዊ ባህሪ ይኖረዋል ማለት ነው:: ምክንያቱም ቀደም ብለን እንደጠቀስነው በሥጋ የተገለጠ ሰይጣን ነውና:: በዚህም የሰው ዘር የሚታለል ይሆናል:: ጌታ ኢየሱስ ከሰማያዊ አባቱ ጋር ፍጹም የሆነ ሕብረት ያለውና ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሆነ ነው (*ዮሐ.10:30*):: በተቃራኒው ደግሞ ፀረ ክርስቶስ ከሰይጣን ጋር ፍጹም የሆነ ሕብረት ያለውና ከእርሱም ጋር አንድ የሆነ ነው:: ቀጥሎ ያለው አጭር አስተዋፅዖ መለኮታዊ ስላሴን የሚቃረን ሰይጣናዊ ሶስትዮሽ መኖሩን የሚያሳይ ነው::





## የፀረ ክርስቶስ መነሻ

የክርስቲያኖች ተቃዋሚ መንግስት መሪ የሆነው ፀረ ክርስቶስ አንድ ቀን በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ «ራሱን አምላክ» በማድረግ እንደሚቀመጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ቀደም ብሎ ጽፎላቸዋል (2ተሰ.2:4):: ይህ ዐረፍተ ነገር ፀረ ክርስቶስ መሠረቱ የት እንደሆነ ለማወቅ የሚጠየቀውን ጥያቄ ለማገናዘብ እጅግ አስፈላጊ ነው:: የጥንቱ የአራቱ የዓለም መንግስታት የባቢሎን፣ የሜዶንና ፋርስ፣ የግሪክና የሮም መንግስታት በመታደስ የሚነሳ መሆኑን ተመልክተናል:: በመታደሱ ቀድሞ የነበረው ብቻ ነው ተመልሶ የሚታደሰው:: ስለዚህ መጪው ፀረ ክርስቶስ መንግስት በኢየሩሳሌም ባለው ቤተ መቅደስ ራሱን አምላክ አድርጎ በማስቀመጥ አምልኮን የሚጠይቅ ከሆነ ከቀደሙት (ከጥንት) አራት የዓለም መንግስታት መካከል አንድ መሪ በተመሳሳይ ይህን ያደረገ መኖር አለበት::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል አስፈላጊ የሆነ ጥቆማ ይሰጠናል:: እርሱም ከብዙ ምዕተ ዓመታት በፊት በነቢዩ ዳንኤል «የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ስፍራ...» የተባለውን ትንቢት በመጥቀስ ተናግሯል (*ማቴ.24:15*):: በተመሳሳይም ንባብ በብሉይ ኪዳን ትንቢት ውስጥ ፍርሃተ እግዚአብሔር ፀባይ በሌለው ሰው መምጣት በጣም ከፍ ያለ ውድመት በተቀደሰው ስፍራ ላይ እንደሚያስከትል ይናገራል (*ዳን.9:27፤ 11:31*):: «የተቀደሰችው ስፍራና» «መቅደስ» በኢየሩሳሌም ያለውን ቤተ መቅደስ መሆኑን በግልጽ ያመለክታል:: ይህም በብሉይ ኪዳን ዘመን በኢየሩሳሌም ያለውን ቤተ መቅደስ ያፈረሰ መሪ ነበር ወይ? ወደሚለው ጥያቄ ያመጣናል ይህ ከሆነ ትንሽ ግልጽ የሆነ መረጃ አግኝተናል ማለት ነው:: ምክንያቱም ፀረ ክርስቶስ በተመሳሳይ መንገድ ይህን ያከናውናል:: በርግጥ የጥንቱ የዓለም መንግስታት አልፈዋል:: ሆኖም ለሰባቱ ራሶች ስውር የሆነውን ሰይጣናዊ አመራር የሰጣቸው ዛሬም ከበስተኋላ (ከበስተጀርባ) አለ ማለት ነው:: ይህ ሰይጣናዊ አገዛዝ (መንግስት) በክርስቶስ ተቃዋሚ መንግሥት እንደገና በዓለም መድረክ ላይ አንድ ጊዜ ይታያል:: በአራቱ የጥንቱ የዓለም መንግሥታት ዘመን ወደገዙት ነገሥታትና ወራሾቻቸው ትኩረት ሰጥተን ስንመለከት የሚከተሉትን ግንዛቤዎች እናገኛለን:: የመጀመሪያው ራስ ባቢሎን ይህን አይወክልም ምክንያቱም ባቢሎናውያን በ586 ክ.ክ.ል.በ. ቤተ መቅደሱን አፈረሱት እንጂ አንድም የባቢሎን ንጉሥ በቤተ መቅደሱ ውስጥ አልተቀመጡም፣ ሁለተኛው ራስ ደግሞ ሜዶንና ፋርስ ይህን አይወክልም

ምክንያቱም ሜዶንና ፋርስ ቤተ መቅደሱ ተመልሶ እንዲሠራ ፈቀዱ እንጂ አንድም ንጉሥ ከእነርሱ በቤተ መቅደሱ ውስጥ አልተቀመጠምና አራተኛ ራስ በጳጥሊሞሳውያን የተመራው ግብጽና አምስተኛ በትሬስና በትንሹ እስያ የገዛው ሊስማክስ ቤተ መቅደሱን ከቶ አልነኩም። በካሳንደርና በወራሾቹ የተመራው ስድስተኛ ራስ ሜቄዶንያ ከቤተ መቅደሱ ጋር ምንም ግንኙነት አልነበረውም። ሰባተኛው ራስ የዓለም መንግሥት የሆነው ሮም ማንም ማርሻል ወይም ንጉሥ ወደ ቤተ መቅደሱ ሳይገባ ነሐሴ 10 ቀን 70 ዓ.ም. ከክ.ል.በኋላ ቤተ መቅደሱን በጠቅላላው እጠፋው። በ63 ክ.ል.በፊት ኢየሩሳሌምን ድል ያደረገው የሮሙ ንጉሥ ፓምፔ ብቻ ነበር ወደ ቤተ መቅደሱ የገባው። ሆኖም በቤተ መቅደሱ ውስጥ ያሉትን ነገሮች አልነካም ነበር ይህ ቤተ መቅደስ ሁለተኛው ቤተ መቅደስ ነበር። በ70 ዓ.ም. ሮማያውያን የደመሰሱት ቤተ መቅደስ ሄሮድስ መንግሥቱን በገነባበት ዘመን (40-4 ከክ.ል.በፊት) የተሠራው ሦስተኛው ቤተ መቅደስ ነበር። ስለዚህም ነው (በዮሐ.2:20) ላይ ያለው ቤተ መቅደሱ በአርባ ስድስት አመት መሠራቱን የሚናገረው። የሮም መንግሥት መሪ ከሆኑት በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ ራሱን ያስቀመጠ እልነበረም።

*ታዲያ የሚቀረው የትኛው ራስ ነው ?*

ሦስተኛው ራስ አስፈሪ በሆነው በአራተኛው ንጉስ በአንቲዮኩስ ኤፒፋነስ የሚመራው ሶርያ ብቻ ይቀራል። በ168-165 ከክ.ል.በፊት በኢየሩሳሌም ባለው ቤተ መቅደስ እንደ ዚውስ ልጅ (የግሪክ ጣዖት) አምላክ በመባል ተመልኳል። በእግዚአብሔር ቤት መሰዊያ ላይ አሳማ ሰውቷል። የእስራኤልንም ሕዝብ ለማጥፋት ሞክሯል። ፀረ ክርስቶስም የሚሠራው እንደዚሁ ነው። እንደ ሶሪያዊው የሚታይ ሰይጣናዊ ራስ ይነሳል። በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ራሱን ያስቀምጥና የጥፋት ርኩሰቱን ይመሠርታል።

*ፀረ ክርስቶስ የሚነሳው ከእስራኤል ሕዝብ ወይስ ከዓለም ሕዝብ ነው ?*

ፀረ ክርስቶስ ከየት ይመጣል ለሚለው ጥያቄ ራሱ ሌላ ሁለተኛ ጥያቄ ይወልዳል። ይህንንም እኛ ማጣራት አለብን። ጌታ ኢየሱስ በዘመኑ ለነበሩት አይሁዶች እንዲህ ብሎ ነበር።

*«እኔ በአባቴ ስም መጥቻለሁ፣ አልተቀበላችሁኝም፣ ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ እርሱን ትቀበሉታላችሁ» በማለት ተናግሯቸዋል (ዮሐ.5:43)።*





እነዚህ ቃሎች አይሁዶች ከእውነተኛው መሲህ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይልቅ ፀረ ክርስቶስ የሆነውን ሀሰተኛውን ክርስቶስ መሲህ አድርገው እንደሚቀበሉት ግልጽ ያደረጉታል። በአራተኛው ምዕተ ዓመት ላይ ይኖሩ የነበሩት የቤተ ክርስቲያን አባቶች እነ ኢራኑስ፣ ሂፓላይት፣ አምብሩስ ፀረ ክርስቶስ ከእስራኤል ሕዝብ መካከል የሚነሳ ሰው እንደሆነ የሚጠቁመውን ሀሳብ ይደግፉ ነበር። አይሁዶች ከእነርሱ ሕዝብ ውጭ የሚመጣውን መሲህ አድርገው እንደማይቀበሉት ግልጽ የሆነ ጉዳይ ነው። ለእነርሱ ብሉይ ኪዳን ከፍተኛ ስልጣን ያለው ነውና። ተስፋ የተገባው መሲህ:-

1. *የንግሥና ነገድ ካለው ከይሁዳ ነገድ እንደሚመጣ (ዘፍ.49:8-12)።*
2. *መንግሥቱ ትልቅ እንደሚሆንና በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጥና ለሰላሙና ለመንግሥቱ ፍጻሜ እደሌለው ይናገራል (ኢሳ.9:7)።*

በመጽሐፍት ትርጉም የአይሁድ ሕዝብ እንደ ንጉሳቸው አድርገው የሚቀበሉት አንድን መሲህ ብቻ ነው። ይህ መሲህ ከእስራኤል ከይሁዳ ነገድ የሚመጣው «የዳዊት ልጅ ነው» ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መሲሁና ንጉሳቸው አድርገው ስላልተገነዘቡና ስላልተቀበሉት በፀረ ክርስቶስ እጅ ይወድቃሉ። ምክንያቱም መሲሁ በሥጋ ይገለጣል ብለው እስከ አሁን ድረስ እየጠበቁ ስላሉ ነው። የአዲስ ኪዳን አማኞች እንደ መሆናችን መጠን የንጉስ ልጅ የሆነችው ማርያም የእግዚአብሔርን ልጅ እንደወለደችና እርሱም እንደገና በሥጋ እንደማይመጣ እናውቃለን። ስለዚህ ምክንያት ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ አማኞች ከእንግዲህ ወዲህ ክርስቶስን በሥጋ የምናውቀው አይደለንም ብሎ የጻፈላቸው። (*2ቆሮ.5:16*)። መሲሁ በሥጋ ይገለጣል ብለው ስለሚጠብቁት በዚህ ምክንያት የአይሁድ ሕዝቦች በክርስቶስ ተቃዋሚ ይታለላሉ።

ፀረ ክርስቶስ የዚህ ዓለም ሕዝቦች ታላቅ መሪ ይሆናል። በሌላው ጎን ደግሞ በአይሁዶች ለመከበር በደም ሀረግ አይሁዳዊ መሆን አለበት። ከዓለም ታሪክ ልምምድ እንደታየው ይህ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ አልበርት አንስታይን፣ ካርል ማርክስ፣ ዋልተር ራዜናው ወይም ሄነሪ ኪሲንጀር (የዓለም መሪዎች የነበሩት) በደም አይሁዳዊ ነበሩ። ታሪኩ አሳዛኝ የሆነው የእስራኤል ትልቁ ሰላይ ኤሊ ኮሄን ጥሩ ምሳሌ ነው። ኮሄን ሳይታወቅ በሶርያ እያለ ለብዙ ዓመታት የእስራኤል ስውር አገልጋይ ነበር። ይህ ሰው ለሶርያ ፕሬዚደንት ቢሮ የቀረበና ከፍተኛ ስፍራ የተሰጠው ግለሰብ ነበር። እንድ ቀን በስለላ ላይ እንዳለ እጅ ከፍንጅ ተይዞ ያለ ምህረት በደማስቆ ከተማ በግንቦት ወር 1965 ዓ.ም. ተሰቀለ። በደም አይሁዳዊ ሆኖ ሳለ በመንግስት ሥራ

ከፍተኛ ስፍራ የመያዙ ነገር ችግር አይፈጥርም:: ተራ ለሆኑ ሰዎች ይህ የተቻለ ከሆነ ለፀረ ክርስቶስማ እንዴት አይቻልም?

## የፀረ ክርስቶስ አገዛዝ ጊዜ

ፀረ ክርስቶስ ሲነሳ «... ከዓለም መጀመሪያ አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ያልሆነ ከእንግዲህም ከቶ የማይሆን» ጊዜ ይሆናል:: (*ማቴ.24.21*) አዳኛችን «እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር» ብሏል:: (*ማቴ.24:22*) ይህ ጊዜ ዓለም በዘመናት ሁሉ አይታ የማታውቀው አስጨናቂ ጊዜ ይሆናል:: ይህ ጊዜ ፍትህ የሚጠፋበትና አመጽ (ክፋት) እየበዛ የሚታይበት ጊዜ ነው(*ማቴ.24:12*): በማይገመት ሁኔታ አመጽ እየበዛ ይሔዳል:: ወደ ፊት እንደምንመለከተው እግዚአብሔር የማይታሰፍ ውስን ጊዜ እንዳደረገ እንመለከታለን:: ያለ መከልከል «ለሁሉም ዘመን አለው» (መክ. 3:1) ለማለት ይቻላል:: እግዚአብሔር በዘመናት ሁሉ አስቸጋሪ ጊዜያትን በእጁ ውስጥ በማድረግ ለመቆጣጠር የሚችል መሆኑ ግልጽ ነው:: እግዚአብሔር በዓለም ሁኔታዎች ጣልቃ በመግባትና በመምራት የመዋጀትን እቅድና ታሪክ እንዲቀጥል ያደርጋል:: የፀረ ክርስቶስ አገዛዝ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተጠቀሰ ለሚከተለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንችላለን::

*ፀረ ክርስቶስ በምድር ላይ የሚገዛው ለምን ያህል ጊዜ ነው?*

ቀደም ብሎ ብዙ ጊዜ እንደተጠቀሰው ፀረ ክርስቶስ በጌታ በክርስቶስ ኢየሱስ የተመሰለ ሰይጣናዊ ቅጅ ነው:: ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት መሲሁ አዳኛችን የመዋጀትን ሥራ ለመፈጸም የፈጀበትን ጊዜያት ያህል የፀረ ክርስቶስም አጥፊ የሆነውን ሥራውን በምድር ላይ ለመሥራት ተመሳሳይ ጊዜ ይወስድበታል::

ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል እንደገለጸው በግምት ከ3 እስከ 3 ተኩል ዓመታት አገልግሎቱን በአደባባይ እንደሰጠ ለማየት ይቻላል:: ሥራውን በግልጽ ከጀመረበት እስከ መስቀል ሞቱ ድረስ ሶስት የፋሲካ በዓላትን (ሦስት ዓመታት) በኢየሩሳሌም አከበሯል (*ዮሐ.2:13፤ 6:4፤ 12:1*): ፋሲካ በዓመት አንድ ጊዜ የሚመጣና ጌታ በመጀመሪያው ፋሲካ ከመታየቱ በፊት ጥቂት ጊዜያት ቀደም ያለ ሲሆን፣ ከዚህ በመነሳት በህዝቡ መካከል ከሦስት ዓመታት በላይ እንዳገለገለ ግልጽ ይሆናል:: እንዲሁም ፀረ ክርስቶስ የክርስቶስ ኢየሱስን ቅጂ በማድረግ ለሦስት ዓመታት ተኩል የማታለል ሥራውን ያከናውናል::

እግዚአብሔር ሁልጊዜ የእስራኤልን ሕዝብ እንደሚዋጅ አድርጎ የሚናገር ከሆነ፣ እስራኤል በመጽሐፍ ቅዱስ በትንቢተ ዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ ዓይን





የሚጣልባት ከተማ ናት ማለት ነው:: እግዚአብሔር ታማኝ ስሆነው አገልጋዩ በእስራኤል ላይ የተወሰነውን የፍርድና የጸጋን ጊዜ በግልጽ በማሳየት:-

«አመፃን ለማስቆም ኃጢአትን ለማስወገድ በደልን ለማስተሰረይ ዘላለማዊ ጽድቅን ለማምጣት ራዕይና ትንቢትን ለማተምና እጅግ ቅዱስ የሆነውን ለመቀባት ስለ ህዝብህና ስለተቀደሰችው ከተማህ ሰባ ሱባዔ ታውጆአል:: *(ዳን. 9:24)*:

እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ የሰባው የባቢሎን ምርኮ ዘመን ፍርድን ብቻ የወሰነ ሳይሆን ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ:: (ዳንኤል ይህን ራዕይ በተቀበለበት ጊዜ ይኖር የነበረው በዚህ ጊዜ ውስጥ ነበር) ይህ ማለት ምን ማለት ነው? አንድ ሳምንት ሰባት ቀናት እንዳሉት ሁሉ ሰባት የሚለው ሰባት ዓመታትን የያዘ ነው:: የእስራኤል ሕዝብ ምድሪቱን እንዲሰልሉ ሰላዮችን ለአርባ ቀናት ልከው ነበር:: በዚህም ለአርባ ዓመታት ወደ ተስፋይቱ ምድር ሳይገቡ በምድረ በዳ ቆይተዋል:: በዚህም በእስራኤል ላይ የሰባ ዓመት ፍርድ ብቻ የተወሰደ ሳይሆን ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ፣ ይህም ማለት እነዚህ ሰባቱ ሳምንታት በጠቅላላው የሰባት ዓመታት ጊዜያት ይሆናሉ ማለት ነው::

በማዳን ዕቅድ ካርታ ላይ ሰባ ጊዜ ሰባትን የሚያመለክተው መስመር ከአራቱ የዓለም መንግስታት ስር ይታያል:: በመዋጀት ታሪክ ሂደት ውስጥ እነዚህን «ሰባቶች» የሚገልጸው (በዳንኤል ምዕ. 9: 25-26)

*«ይህን ልብ ብለህ አስተውል፣ ኢየሩሳሌም እንድትታደስ ትዕዛዝ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ መሲሁ እስከሚመጣበት ድረስ ሰባት ሳምንትና ስልሳ ሁለት ሳምንት ናቸው» በሚል ተገልጿል::*

የኢየሩሳሌም ቅጥር ተመልሶ መሠራት የጀመረው በፋርሱ ንጉሥ በአርጤክስስ ከ20ኛው ዓመት ላይ ነበር (*ነህ.1:1፤2:1*): የጥንቱ ታሪክ ግኝት እንደሚነግረን ይህ ጊዜ ከ445 ወይም ከ451 ከክ.ል.በፊት እንደሆነ ነው ትንቢቱ ቆጠራውን የሚያደርገው:: በእነዚህ ታሪካዊ ቀናት ላይ ተመስርቶ ነው (ዳን. 9:24-27)::

**7 ሰባቶች ( ሳምንቶች ) :- 7 × 7 = 49 ዓመታት**

**<u>62 ሰባቶች ( ሳምንቶች ) :- 62 × 7 = 434 ዓመታት</u>**


**ጠቅላላ ድምር = 483 ዓመታት**

ኢየሩሳሌም ተመልሶ መሠራት ትዕዛዙ የተሰጠበት 451 ከክ.ል.በፊት ነው ብለን ከተቀበልንና በዚህ ላይ 483 ዓመታትን ብንደምር ይህ ቆጠራ በቀጥታ ወደ 32 ከክ.ል.በኋላ ዓመት ያመጣናል:: በ 0 ላይ አንድ ዓመት መጨመር አለብን:: ይህም ወደ 33 ከክ.ል.በኋላ ዓመት ይወስደናል:: ዳንኤል ስለዚህ:-

*«ከስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባትም በኋላ መሲሕ ይገደላል፣ በእርሱም ዘንድ ምንም የለም»* በማለት ተናግሯል (*ዳን.9:26*)::

ይህ መሲህ ወይም «የተቀባው» ሰብዙ ጊዜ ይጠበቅ የነበረው ከእስራኤሉ መሲህ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ አልነበረም:: እርሱ በመጣ ጊዜ ግን የራሱ ሕዝቦች አልተቀበሉትም ነበር (*ዮሐ.1:10-11*) በተቃራኒው ግን ሰቀሉት (*ዳን.9:26*)::

የመጀመሪያዎቹ ስድሳ ዘጠኙ ሳምንታት (ሰባቶች) በመሲሁ መምጣት ጊዜ ተፈጽመዋል:: ሰባኛው ሱባኤ (ሳምንት) ግን ሳይፈፀም ቀርቷል:: ይህ ሰባኛው ሰባት ገና አልተጀመረም:: ምክንያቱም እስራኤል መሲኋን ስላልተቀበለች እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የነበረውን የማዳን ሥራ ጣልቃ በመግባት ለጊዜው ስላቆመ ነው:: ባለፈው ምዕራፍ እንዳየነው እግዚአብሔር በወንጌል ሥራው ትኩረቱን ወደ አሕዛብ አደረገ:: አይሁዶች በጌታ እስከ ተወሰነላቸው ጊዜና ተመልሰው የእስራኤል ሕዝብ ሆነው እስከሚሰበሰቡበት ጊዜ ድረስ ከአባቶቻቸው ምድር ወጥተው በአሕዛብ መካከል እንዲበታተኑ ተደርጓል (*ሉቃ.21:24*):: እስከዚያ ድረስ ቅድስቲቷ ምድር የተፈታች ሆና ትቆያለች:: (ዳን. 9:26፣ ማቴ. 23:38) ለብዙ ምዕተ ዓመታት በእስራኤል ምድር ላይ የውጭ ሕዝቦች ገዙ፣ አሰቃቂም ውጊያዎችን ተዋጉባት ምድሪቱንም አጠፏት:: በእነዚህ ጊዜያት በዓለም ዙሪያ ብዙ አይሁዶች አሰቃቂ ስደቶችን ተቀበሉ:: በመጨረሻዎቹ ቀናት እግዚአብሔር ትኩረቱን እንደ ገና ወደ ራሱ ሕዝብ ይመልሳል:: ለብዙ አሰርት ዓመታት አይሁዶች ወደ አባቶቻቸው ምድር እየተመለሱ ናቸው:: ይህ ተአምራት በመላው ዓለም ዓይን ፊት እየተከናወነ ነው:: ዋናው ነገር፣ የእስራኤል ከፉ ጠላቶች እንኳን ቢሆኑ ይህን መሰባሰባቸውን ሊያቆሙ አለመቻላቸው ነው:: ከዚህ በስተጀርባ ያለውን የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው:: እስራኤል እንደገና ወደ ፊት ወደ ትንቢቱ ፍፃሜ እየተጠጋች ነው:: ምክንያቱም መሲሁ ሊመጣ ስለሆነ ነው::









ወንጌል ለሁለት ሺህ ዓመታት በመላ አለም ተሰብኳል:: በቁጥር ያልተወሰኑ ሰዎችም በጌታ ኢየሱስ ላይ ወዳለው እውነተኛና ሕያው እምነት መጥተዋል:: ዛሬም ጌታ የዳኑትን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እየሰበሰበና በየቀኑም በእነርሱ ላይ እየጨመረ ነው:: (*ሐሥ.2:47*) «የአሕዛብ ሙላት» (*ሮሜ.11:25*) ሲሞላና ቤተ ክርስቲያን በክብር በተነጠቀች ጊዜ በቀጥታ ጌታ ከእስራኤል ጋር ያለውን የመዋጀት ታሪክ ይቀጥላል:: በዚያን ጊዜ *የ(ዳን.9:24)* ትንቢት ይፈጸምና የመጨረሻው «ሱባኤ» ይቀጥላል::

በእስራኤል ላይ ሰባ ጊዜ ሰባት ወይም 490 ዓመታት እንደተቀጠረ እናስታውስ:: ስድሳ ዘጠኙ ሰባቶች (ሳምንታት) ወይም 483 ዓመታት ተፈጽመዋል:: ሰባቱ ዓመታት ወይም አንዱ ሳምንት ብቻ ቀርቷል:: ይህ የዳንኤል ሰባኛውና የመጨረሻው ሰባት የሆነው ሱባዔ ጌታ «በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና» ሆኖ ከመምጣቱ በፊት ይፈጸማል (ማቴ.24:30):: አምላክ የለሹም (አመጸኛው) የእስራኤል ሕዝብ ወደዚህ የፍርድ ጊዜ እየደረሰ ነው:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለ ልጁ የሰጠውን ምስክርነት አልተቀበሉትም (ተቃውመውታል) (1ኛዮሐ. 5:10) ስለዚህም የሰይጣን ልጅ በሆነው በክርስቶስ ተቃዋሚ እጅ ይወድቃሉ::

ይህ የአመጽ ሰው *(2ተሰ.2:3)* ከእስራኤል ጋር የተለየ ሕብረት ይመሠርታል:: ከዚህ ሕዝብ ጋር ቃል ኪዳን ለመመስረት ይታገላል፣ እስራኤልም በቃል ኪዳኑ ትያዛለች:: ምክንያቱም በመሳሳት ንጉሳቸውና መሲሁ አድርገው ስለሚቀበሉት ነው::

በብሉይ ኪዳን ዘመናት እስራኤል ከእዳዲስ ከሚነግሱት ነገሥታት ጋር ቃል ኪዳን ታደርግ ነበር:: ከዳዊት ጋር *(2ሳሙ.2:4፣5:3)*፣ ከሰሎሞን ጋር *(1ነገ.1:32-40)*፣ ከሮብአም ጋር *(1ነገ.12:1)*፣ ከኢዩ ጋር *(2ነገ.9:1-13)*፣ ከኢዩኤል



*ጋር(2ነገ.11:4፣ 12፣17)* ቃል ኪዳን እንዳደረጉ ተጽፏል:: አንድ ጊዜ እስራኤል «በራሱ ስም የሚመጣውን» (ዮሐ. 5:43) ስትቀበል ይህ ድርጊት እንደገና በድጋሚ ይከናወናል:: የዳንኤል የመጨረሻው ሰባት ዓመት በዚህ እጥፋ የሆነው ቃልኪዳን በእስራኤልና በሐሰተኛው ንጉስ መካከል ይጀምራል:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ቃል ኪዳን ከሀሰተኛው ንጉስ ከፀረ ክርስቶስ ጋር በማያያዝ:-

*«እርሱም ከብዙ ሰዎች ጋር ጽኑ ቃልኪዳን ለአንድ ሱባኤ (ሰባት አመታት) ያደርጋል» (ዳን.9:27)* ይላል::

በዳንኤል 9:24-27 ያለው ጠቅላላ ትንቢት እንደሚያሳየው ይህ አንዱ ሳምንት ያለ ጥርጥር ያልተፈጸመው ሳምንት ነው:: በሰባትና በስድሳ ሁለት ላይ ሰባት ሲደመርበት ሰባው ሳምንት (ሰባው ሱባኤ) ይሆናል:: በኋላ እንደምናየው ፀረ ክርስቶስ በዚህ በሰባኛው ሳምንት መጨረሻ ላይ ፍርድ ይከናወንበታል::

ፀረ ክርስቶስ ምን ያህል ጊዜ እንደሚገዛ ይህ ግልጽ ያደርገዋል:: በጠቅላላው ለሰባት ዓመት ይገዛል:: ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያለው የሰባት ዓመት የቃል ኪዳን ቆይታ ጊዜ ጋር እኩል ይሆናል:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት የሚገዛበት ጊዜ በሁለት የ3 ዓመት ተኩል ዓመታት ይከፈላል::

### የመጀመሪያዎቹ የ3½ ዓመታት «ሰላም ሰላም ሰላም»

በእነዚህ በመጀመሪዎቹ ሶስት ተኩል ዓመታት አገዛዙ ጊዜ ፀረ ክርስቶስ የሰውን ዘር በሰላምና በብልጽግና ይባርካል:: በአስቸጋሪው ጊዜ እንደ ተጠበቀው መሲህ፣ ከሰው አዕምሮ አስቸጋሪ የሆኑትን ነገሮችን ሊፈታ የሚችል መስሎ ይገለጣል:: በተሰያዩ መስኮች በማህበራዊና በኢኮኖሚ መስክ ሊታመን በማይቻል መልኩ በሚያደርገው እድገት የተነሳ መላ አለም በእርሱ ይደነቅና ያከብረዋል::

አይሁዶች ፀረ ክርስቶስ ከእነርሱ ጋር በሚያደርገው ቃል ኪዳን በኢየሩሳሌም አዲስ በተሠራው ቤተ መቅደሱ የብሉይ ኪዳን መስዋዕት እንደሚሰዋ ያረጋግጥላቸዋል:: ያለ ጥርጥር በዚህ ጊዜ ከሚታዩት ምክንያቶች አንዱ ሕዝቦች «ሰላምና ደህንነት» ነው ማለታቸው ነው (*1ተሰ.5:3*)::

ዛሬም እንኳን «ሰላምና ደህንነት» ነው የሚለው በዓለም ፖለቲካ ዋናው የመወያያ ጉዳይ ነው:: የታወቀው መግለጫ «ሰላም እናድርግ» የሚለው ነው:: ከዚህ ጋር ጎን ለጎን የሚመሳሰለው የአይሁዶች ትምህርት መሲሁ ከመምጣቱና ይህን ሰላም ከመመስረቱ በፊት የሰው ዘር በመጀመሪያ ወደ ሰላም መድረስ አለበት የሚል ነው:: እዚህ ላይ የሚመጣው ፀረ ክርስቶስ ስለ ሰላም ያለውን መፈክር ልንገነዘብ እንችላለን::





ፀረ ክርስቶስ በዚህ ብሩህ በሆነ የሰላም መልእክት ዓለምን ያስደንቃል:: በዚህም የዚህ ችግር መፍትሔ እንደተገኘለት መስሎ ይታያል:: ሆኖም አጭሩ «የሰላም» ጊዜና ውጫዊ የሆነው ብልጽግናና ጠቅላላው ደህንነት አደገኛ ሕልሞች ብቻ ናቸው::ሰዎችን እስራኤልንና መላ አለምን የሚያታልል (የሚያስት) ሆኖ ይቀራል:: ፍጹም የሆነውን ሰላም ያለ እግዚአብሔር ለማግኘት መጣሩ ፍጹም የማይቻልና ሕልም ብቻ ነው:: በተለይም በአመጸኛውና (*2ተሰ.2:8*) እግዚአብሔርን በሚቃወመው ግዛት (*2ተሰ.2:4*) እኛ ወደዚህ የመታለል ዘመን እየተጠጋን ያለን ሐዋርያው ጳውሎስ ለሰጠው ማስጠንቀቂያ ከፍተኛ ትኩረት ልንሰጠው ይገባናል:: ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች በጻፈው በመጀመሪያ መልእክቱ ሐዋርያው ጳውሎስ በሚመጣው በፀረ ክርስቶስ መንግስት ስላለው ሀሰተኛ ስለሆነው አጭር ሰላም በትንቢት እይታው:-

*«ሰላምና ደህንነት ነው ሲሉ ያን ጊዜ ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል»* በማለት ጽፎላቸዋል (1ተሰ.5:3)::

በብሉይ ኪዳን ዘመን እንኳን ነብዩ ኤርምያስ የእስራኤል ልጆች *«ሰላም ሳይሆን:- ሰላም ሰላም ይላሉ»* ስለሚለው ስለ ሀሰት አላማቸውና አካሄዳቸው ጩኸት ዘልፏቸዋል (ኤር.6:14) ::

### የመጨረሻዎቹ የ3½ ዓመታት፣ ታላቁ መከራ


የሰባተኛው ሳምንት አጋማሽ ከተፈጸመ በኋላ በፀረ ክርስቶስ መንግስት በአይሁድ ላይ አሉታዊ ለውጥ ያሳያል:: በነቢዩ ዳንኤል:-

*«በሱባኤውም እኩሌታ መስዋዕትንና ቁርባንን ያስቀራል» (ዳን.9:27)* ተብሏልና::

ይህም ማለት ከ3-1/2 ዓመታት በኋላ ፀረ ክርስቶስ ከእስራኤል ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን በድንገት ያፈርስና ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የብሉይ ኪዳን መስዋዕትንና ቁርባንን ያስቀራል:: በዚህ ምትክ ራሱን አምላክ አድርጎ በማወጅ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ራሱን ያስቀምጣል (*2ተሰ.2:4*): በመጀመሪያ ራሳቸውን በአማልክት ደረጃ ያስቀመጡት የሮማውያን ነገሥታት ነበሩ:: የፀረ ክርስቶስ ከዚህ በበለጠ ራሱን አምላክ በማድረግ ይሠራል:: ከዚህም ትዕቢቱ የተነሳ አምላካዊ አክብሮትን ከሕዝብ ይጠይቃል:: ይህን ጥያቄውን በሰዎች ላይ እንዴት በኃይል እንደሚያከናውን ያውቃል (*ራዕ.* 13:15):: ሆኖም አይሁዶች ለጥያቄው ድጋፍ ባለመስጠት ሀሳቡን ይቃወሙታል:: ይህም የሚሆነው በአንድ አምላክ ላይ ካላቸው እምነት የተነሳ ለሰው መስገድ የማይቻላቸው ስለሆነ ነው:: በዚህም ምክንያት ማንንም ሰው፣ ፀረ ክርስቶስን እንኳን ቢሆን አያመልኩም:: በዚህ ምትክ እግዚአብሔርን ብቻ ያመልኩታል::

እይሁዶች ጥያቄውን በመቃወምና ባለመታዘዛቸው ምክንያት ፀረ ክርስቶስ በመጨረሻ ትክክለኛ ባሕርዩን ይገልጣል:: በዓለም ታሪክ ታይቶ የማይታወቀውን ስደት በእይሁዶች ላይ ያካሄዳል:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ስለዚህ ጊዜ «ታላቁ መከራ» እንደ ሆነና ከዚያ በፊት በዓለም ያልታየና ወደፊትም ደግሞ የማይታይ እንደሆነ ተናግሯል (ማቴ. 24:21):: በተመሳሳይ ሁኔታ በብሉይና በአዲስ ኪዳን «የያዕቆብ የመከራ ዘመን» (*ኤር.30:7*) ወይም ደግሞ «ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ:- እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደ እርሱ ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል::» *(ዳን.12:1)* በማለት ተተንብዮአል::

በአሁኑ ዘመን ባለው ስነ መለኮታዊ መግለጫ «ታላቁ መከራ» በማለት ይጠቀማል:: ሆኖም በከፍተኛ ደረጃ ልንገነዘበው የሚያስፈልገው እውነት «ታላቁ መከራ» የሚመለከተው የእስራኤልን ምድርና ሕዝብ ነው:: ይህ ግልጽ ሊሆን የሚችለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ላይ የተናገረውን በጥንቃቄ ስናጠና ነው:: እርሱም ያለው :-








1. «በተቀደሰችው ስፍር» (ማለትም በኢየሩሳሌም ያለው ቤተ መቅደስ) ቁ.15
2. «ከይሁዳ መሬት» ቁ.16
3. «በስገነት ላይ» ስላሉ ሰዎች (በአብዛኛው የእስራኤላውያን ቤቶች ዝርግ የሆነ ጣራ አላቸው) ቁ.17
4. «ሽሽታችሁ በሰንበት እንዳይሆን» ቁ.20 (እስራኤላውያን ብቻ ናችው ሰንበት የሚጠብቁት)
5. «ሽሽታችሁ በክረምት እንዳይሆን» ቁ.20 (እስራኤላውያን 300 ያህል ፀሐያማና ሞቃት ቀናት አሏቸው::)

ኢየሱስ በግልጽ ስለ እስራኤል ወይም በይሁዳ ስለሚኖሩት አይሁዳውያን ነበር የተናገረው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ስለተጠቀሰውና አስቃቂ ስለሆነው መከራ ስናስብ «የያዕቆብ የመከራ ዘመን» የሚለው በእስራኤል ላይ የሚደርስ ፍርድ እንደሆነ እንገነዘባለን:: በሚከተሉት የንባብ ክፍሎች *(ዳን. 7:25፤12:7፤ራዕ.11:2-3፤ 12.6-14፤ 13:5)* ውስጥ «1260 ቀናት»፣ «42 ወራት»፣ «ዘመን ዘመናትና የዘመን እኩሌታ» በማለት ይናገራሉ:: እያንዳንዱ ጊዜያት 3-1/2 ዓመታት ወይም የሶስት ሳምንትና ተኩል ናቸው:: ከላይ የተጠቀሱት ጊዜያት *በ ዳን.9:27* የተጠቀሰውን የሰባኛውን ሳምንት እኩሌታ እንደሆነ ያመለክታሉ:: ምክንያቱም ታላቁ መከራ የሚሆነው በእነዚህ 3-1/2 ዓመታት ጊዜ ነው:: ይህም እስራኤል በእግዚአብሔር ፍርድ ስር የምትቆይበት ጊዜ ነው:: ሰባው ሱባኤ የዳንኤልን ሕዝብ የሚመለከት ከሆነና (*ዳን.9:24*) በሕዝብህ ላይ ስለሚል የዳንኤል ሕዝብ የእስራኤል ሕዝብ ከሆነ አስቃቂ የሆነው ታላቁ መከራ እስራኤልን የሚመለከት እንደሆነ ልንገነዘብ እንችላለን::

*ታላቁ መከራ ለእስራኤል ምን ማለት እንደሆነ?*

ቀደም ብለን እንደተናገርነው የፀረ ክርስቶስ እስራኤል በዘመናት ሁሉ ካየችው የበለጠ ታላቅ የእይሁድ የመከራ ስደት እንድትቀበል ያደርጋታል:: ነብዩ ዘካርያስ ስለዚህ:-

*«በምድር ሁሉ ላይ ሁለት ክፍል ተቆርጠው ይሞታሉ ይላል እግዚአብሔር፣ ሦስተኛውም ክፍል በእርስዋ ውስጥ ይቀራል:: ሦስተኛውንም ክፍል ወደ እሳት አገባለሁ፣ ብርም እንደሚነጥር አነጥራቸዋለሁ:: ወርቅም እንደሚፈተን እፈትናቸዋለሁ፣ እነርሱም ስሜን ይጠራሉ፣ እኔም እሰማቸዋለሁ፣ እኔም ይህ ሕዝቤ ነው እላለሁ:: እርሱም እግዚአብሔር አምላኬ ነው ይላል» በማለት ተናግሯል (ዘካ. 13:8-9)::*

እንደዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ቃል አነጋገር ከእስራኤል የሚቀረው ሲሶው ሕዝብ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ስለ ቅሬታው ሕዝብ ብዙ ጊዜ ይናገራል፡፡ አዲስ ኪዳን እነዚህን ሕዝቦች *በ ማቴ.24:22፤24፤31፤* ሮሜ.11:7 እና በሌሎችም ቦታዎች «የተመረጡ ሕዝብ» በማለት ይጠቅሳቸዋል፡፡ ከአይሁድ ሕዝብ በዚህ በታላቁ መከራ ሁለት ሦስተኛው የሚጠፉ ከሆነ፣ ይህ ጊዜ ለእስራኤል የተሀድሶና በፍርድ (በቅጣት) የማለፍ ጊዜ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡

ይህ የእሳትና የመከራ ፍርድ (ቅጣት) እውነተኛውን መሲህ ኢየሱስ ክርስቶስን ለሚፈልጉ አይሁዶች ከታላቁ መከራ ፍጻሜ ላይ እንዲገሰጡ (እንዲታዩ) የሚያደርጋቸው ዕቅድ ነው፡፡ እነዚህ ቅሬታዎች መላ እስራኤል የተባሉት ይሆናሉ (*ሮሜ.11:26*)፡፡ እነዚህን በሙሉ ልብ በመጠበቅ፣ በመቀበልና በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው በማለት ወደ እርሱ ይጮሃሉ (ባሩክ ሀባ ዊ በኪም አዶናይ) (*ማቴ.23:39*)፡፡

ዛሬ ጥቂት የአይሁድ የሃይማኖት ክፍሎች መሲሁ የሚመጣው ሁለት ጊዜ ነው የሚለውን አስተያየት ይደግፋሉ፡፡ ይህም እንደ ቤን ጆሴፍ (የዮሴፍ ልጅ) ከዚያ በኋላ እንደ ቤን ዳቪድ (የዳዊት ልጅ) ሆኖ ይመጣል የሚሉት ናቸው፡፡ ቤን ጆሴፍ (የዮሴፍ ልጅ) ሀሰተኛው ነው ቤን ዳቪድ (የዳዊት ልጅ) እውነተኛው ነው፡፡ ወደዚህ መደምደሚያ እንዴት መጣችሁ? ለሚለው ጥያቄ ብዙ የአይሁድ መምህራን የሚሉት እውነተኛውን መሲህ ማወቅ የሚቻለው ከሀሰተኛው መሲህ ስህተቶችና ማታለል የተነሳ ነው ይላሉ፡፡

በመከራው ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ የዮሴፍ አስር ወንድሞች ወደ ግብፅ በመጡ ጊዜ የሆኑትን ይሆናሉ፡፡ ዮሴፍን አላወቁትም ነበር፡፡ በዚህ በእርሱ ተፈተኑና ተጣሩ በመጨረሻ ከራሳቸው የሕሊና ወቀሳ ግፊት የተነሳ «በእውነት ወንድማችንን በድለናል፣ እኛን በመማጠን ነፍሱ ስትጨነቅ አይተን አልሰማነውምና ስለዚህ ይህ መከራ መጣብን» በማለት እርስ በእርሳቸው ተነጋገሩ (*ዘፍ.42:21*)፡፡ በመከራቸው ዘመን እስሩ ወንድማማች ስለ ሰሩት ኃጢአት ሕሊናቸው ወቀሳቸው፡፡ በዮሴፍ ፊት በደለኞች መሆናቸውን ተገነዘቡ፡፡ ከውስጥ ከልባቸው መራራ የሆነ ሐዘን በማዘን ስለ ክፉ ስራቸው ተጸጸቱ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ታላቁ መከራ የአይሁድ ሕዝብ በደላቸውን እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል፡፡ በሐሰተኛው መሲህ እጅ በመውደቃቸውና ቀደም ብለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እውነተኛው መሲህ አድርገው ባለመቀበላቸው ከውስጥ የሆነ እውነተኛ ጸጸት ይጸጸታሉ፡፡





ስለዚህም ታላቁ መከራ ለእስራኤል ሕዝብ የተሀድሶ ፍርድ ነው፡፡ የእስራኤልን ህዝብ ጥልቅ ወደ ሆነ ንስሀና የልብ ለውጥ ለማምራት የታቀደ አሠራር ነው፡፡ በመጨረሻም የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅ በአክብሮት ይቀበሉታል (*ኤር.46:28፤ ሉቃ.21:24*)፡፡

## የታላቁ መከራ ምንነት ሳልዳኑት የዓለም ሕዝቦች

ታላቁ መከራ በመጀመሪያ ችግር የሚፈጥረው በእስራኤል ምድርና ሕዝብ ላይ ቢሆንም እንኳ ከዚያም አልፎ በመላው ዓለም ላይ የሚያመጣው ችግር አለው፡፡ ልንረሳው የማንችለው ነገር ቢኖር በተለይም በዚህ በመከራው ዘመን በመላው ዓለም አመጸኝነትና ክርስቶስን የመቃወም (የመጥላት) ነገር በፍጥነት እየጨመረ የመሄዱን ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም መላው የሰው ዘር በሙሉ፡-

1. *ከሐደማኖት የተለዩ* ይሆናሉ ይህም ማለት የዓለም ይሆናሉ ማለት ነው፡፡
2. *በርኩሰት የሚቀጥሉ ገድ የለሽ* ይሆናሉ ይህም ማለት ራሳቸውን ለሥጋ ምኞት በማስገዛት በሁሉም አጸያፊ፣ ከእውነትና ከቅድስና የተለዩ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡
3. *በሰይጣን ቁጥጥር ስር* መሆን ይህም ልበ ደንዳኖች በእግዚአብሔር ቃል የማይደሰቱና በሰይጣን ክፉ ኃይላት እንደሚያዙ ያመለክታል፡፡

ስለዚህም የመጨረሻዎቹ ቀናት በሰይጣናዊ የአሠራር ባሕርይ የተያዙ ናቸው፡፡ አንዳንዶች በዓለም ተሀድሶ ይሆናል ብለው እንደሚጠብቁት አይደለም፡፡ ሰዎች ከእግዚአብሔር ከመለየታቸው የተነሳ፣ በተለይም በፀረ ክርስቶስ መንግስት አንድ ቀን መላው ዓለም ለሰይጣን የሚሰግዱ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል፡-

*«ለዘንዶውም ሰገዱለት፣ ዘንዶው ለአውሬው ሥልጣንን ሰጥቶታልና፣ ለአውሬውም አውሬውን ማን ይመስለዋል፣ እርሱንስ ሊዋጋ ማን ይችላል እያሉ ሰገዱለት» በማለት ይናገራል (ራዕ.13:4)*፡፡

ይህ አስደንጋጭ ሁኔታ አመጸኛ የሆነውን የሰው ዘር ውስጣዊ ሁኔታ ፈጽሞ የተበላሸ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ አውሬውን ማለትም የፀረ ክርስቶስና ዘንዶውን፣ ራሱን ሰይጣንን ያከብራሉ ይህ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚጠራ ይሆናል፡፡ የሰው ዘር ወደ ሰማይ መሄድ የማይፈልግ ከሆነ ወደ ሲኦል የሚሄድ ይሆናል፡፡ የፀረ ክርስቶስ ዘመን የዘላለሙ ቅጣት እስኪጀምር በምድር ላይ ተወዳዳሪ የሌለው ሲኦል ይሆናል ማለት ነው፡፡

## የመጨረሻው ቀናት የምጥ ጣር ጅማሬዎች

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ስለ መጨረሻዎቹ ቀናት በተናገረበት ጊዜ «ስለ ምጥ ጣር ጅማሬዎች» ተናግሯል (*ማቴ.24:8*)፡ እንደምናውቀው ሁሉ የምጥ ጣር የሚሆነው ልጅ ከመወለዱ በፊት ነው:: እነዚህ ምጦች በድንገት የሚሆኑና በመጀመሪያም በተለያዩ ጊዜያት የሚመጡት ናቸው::

| የምጥ ጣር ጅማሬዎች በመጨረሻዎቹ ቀናት እንደ ማቴ.24:1-36 | የምጥ ጣር ጅማሬዎች ሙሉ ይዞታ በመጨረሻዎቹ ቀናት እንደ ራዕ.6:1-7፤17 |
|---|---|
| የማቴ 24 እና ራዕ 6 ንጽጽር | |
| **1. ሀስተኛ ነቢያት**<br>ማታለል፣ ሀሰተኛ መሲሀ፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ (ማቴ. 24:4፣5፣11፣23-26) | **1ኛው ማህተም በነጭ ፈረስ**<br>የተቀመጠው ማታለል፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ፣ ሀሰተኛ ነቢያቶች (ራዕ.6:1-2) |
| **2.ጦርነቶች**<br>የጦርነት ወሬዎች፣ ሕዝብ በሕዝብ ላይ (ማቴ. 24:6-7) | **2ኛው ማህተም በቀይ ፈረስ**<br>የተቀመጠው ሰላም እጦት፣መገዳደል፣ ታላቁ ጦርነት (ራዕ.6:3፣4) |
| **3.ችግር ጊዜ**<br>ረሀብ (ማቴ. 24:7) | **3ኛው ማህተም በጥቁር ፈረስ**<br>የተቀመጠው የችግር ጊዜ፣ረሀብ (ራዕ.6:5፣6) |
| **4.ቸነፈር**<br>ተላላፊ በሽታ፣ የሕዝብ ማለቅ (ማቴ. 24:7) | **4ኛው ማህተም በሐመር ፈረስ**<br>የሕዝብ ማለቅ፣ ሞት፣ ተላላፊ በሽታ (ራዕ..6:7፣8) |
| **5. ስደት**<br>መከራ፣ ሰሞት አልፎ መሰጠት (ማቴ. 24:9) | **5ኛው ማህተም የሰማዕታት**<br>ከመሰውያው ስር ስደ፣ መከራ፣ ስቃይ፣ ለሞት አልፎ መሰጠት (ራዕ.6:9-11) |
| **6. የምድር መናወጦች**<br>የተፈጥሮ ጥፋት (ማቴ. 24:7) | **6ኛው ማህተም የምድር መናወጦች:-**<br>መናወጥ የፀሐይ መጨለም፣ የጨረቃ እንደ ደም መሆን (ራዕ.6 12-17) |
| **7. እስራኤል**<br>ከታላቁ መከራ መጠበቅ፣ መታደስና መዋጀት (ማቴ. 24:14-36) | **7ኛው ማህተም ከእስራኤል የታተሙ**<br>144.000 በታላቁ መከራ ጊዜ ለመጠበቅ የታተሙ (ራዕ.7:1-17) |
| **ጌታ ኢየሱስ ይመጣል**<br>**ማቴ.24:30** | |





ልጁ እስከሚወለድበት ድረስ ተደጋግመው የሚቀጥሉና በመደጋገም እየባሱ የሚሔዱ ይሆናሉ:: ጌታ የደህንነትን ታሪክ ለመግለጽ በየዕለቱ የሚታዩትን ሁኔታዎች በመጠቀም ተናግሯል:: በዚህ ምድር ላይ ከቀራንዮና ከበዓለ ሀምሳ ጀምሮ በጸጋ ዘመን ውስጥ ኖረናል:: ይህ የጸጋ ዘመን በጌታ መምጣትና በቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ያበቃል:: ጌታ ከጸጋው ዘመን ጀምሮ፣የመከራውን ጊዜና እስከ እርሱ መምጣት ያለውን የምጥ ጣር ጊዜ በማለት ጠርቶታል:: ጌታ ይህን የሽግግር ዘመን «የሺው ዘመን መንግሥት» በማለት ገልጾታል::

| የምጥ ጣር ጅማሬዎች መጨመር በመጨረሻዎቹ ቀናት እንደ ራዕ. 8:1-12 ፤ 17 | የምጥ ጣር ፍጻሜያቸው በመጨረሻቹ ቀናት እንደ ራዕይ.13:1-19 ፤ 21 |
|---|---|
| በምድር ሲሶ ላይ የሚሆን ፍርድ | የሰው ዘር ፍርድ ፍጻሜ |
| **1ኛው መለከት**<br>የተፈጥሮ ሲሶ መቀጠል(ራዕ.8:6፣7) | **1ኛው ጽዋ**<br>የሰው ዘር ሁሉ በተለያዩ በሽታዎች መያዝ (ራዕ.16:1-2) |
| **2ኛው መለከት**<br>የባሕር ሲሶው መበላሸት (ራዕ.8:8፣9) | **2ኛው ጽዋ**<br>የውሀ ወደ ደም መለወጥ፣ በውስጣቸው ያሉት በሙሉ መሞት (ራዕ.16:3) |
| **3ኛው መለከት**<br>የወንዞችና የምንጮች መበከል (ራዕ.8:10፣11) | **3ኛው ጽዋ**<br>የወንዞችና የምንጮች መበከል (ራዕ.16:4-7) |
| **4ኛው መለከት**<br>የፀሐይ፣ የጨረቃና የከዋክብት ሲሶ መመታት (ራዕ.8:12፣13) | **4ኛው ጽዋ**<br>የፀሐይ በሙሉ መመታት፣ የሕዝብ በጸሐይ ኃይል መቃጠል (ራዕ.16:8፣9) |
| **5ኛው መለከት**<br>የጥልቁ መከፈት፣ በሰይጣን ኃይል ብዙ<br>ስቃዮች መሆን (ራዕ.9:1-12) | **5ኛው ጽዋ**<br>በክርስቶስ ተቃዋሚ ምክንያት በመንግስቱ ላይ ጨለማና ሥቃይ (ራዕ.16:10፣11) |
| **6ኛው መለከት**<br>ከሰዎች ሲሶ በጦርነት መገደል (ራዕ.9:13-21) | **6ኛው ጽዋ**<br>በአርማጌዶን የክርስቶስ ተቃዋሚወታደሮች በጠቅላላ መገደል (ራዕ.16:12-16) |
| **7ኛው መለከት**<br>በታላቁ መከራ ጊዜ የእስራኤል መጠበቅና መዳን (ራዕይ 11:1-12፤17) | **7ኛው ጽዋ**<br>አስቃቂ የምድር መናወጦች (ራዕ.16:17-21)<br>አጠቃላይ ፍርድ በባቢሎን ላይ (ራዕ.17:1-18 እና ምዕ. 24) |
| **ጌታ ተመልሶ ይመጣል!**<br>***ራዕይ.19:11-21*** | |

ባጭሩ እንደምናያቸው እነዚህ የምጥ ጣሮች ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት የሚከናወኑ ናቸው:: የፀረ ክርስቶስ በሚመጣው በታላቁ መከራ ጊዜ ወደ ሙላት ይደርሱና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽ ሲመጣ ያበቃሉ:: ጌታ በ*(ማቴ.24:8)* ስለተናገረው «ስለ ምጥ ጅማሬ» በበለጠ ለመረዳት ወደ አስራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ፍጻሜ ቀስ ብለን መሔድ አለብን:: ይህ ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ በቅድስት ምድር የመሰባሰብ ጅማሬ ነው:: ራሳቸውን ከዓለምና ከደህንነት ታሪክ ጋር ያያያዙ ሰዎች እንደሚሉት እነዚህ «የምጥ ጣሮች» የጀመሩት በ1897 አስቀድሞም ነበር በተደረገው የመጀመሪያው የጽዮናውያን እንቅስቃሴ ጊዜ ነበር::

በዚያን ጊዜ በዓለም ያለ ማንኛውም ሰው ስለዚህ ጉዳይ ትኩረት አልሰጠውም ይመለከተዋል:: ከአስራ ሰባት ዓመታት በኋላ በአንደኛው ዓለም ጦርነት ፍንዳታ በዓለም የሚኖሩ ሰዎች «የምጥ ጣር» ስለሆኑት ጊዜያት በግልጽ ማስታወስ (መገንዘብ) ጀመሩ:: በአራቱ በጥንቱ መንግስታት ድንበሮች ላይ በተለይም በአውሮፓና በእስያ ያሉት መንግስታትና ግዛቶች ወደቁ አዲስ አገሮች መንግስታት፣ ግዛቶችና ዲሞክራሲዎች ተመሠረቱ:: በዚህ ትርምስ ውስጥ ሕዳር 2 ቀን 1917 ዓ.ም. በባልፎሩ ውሳኔ አይሁዳውያን ብሔራዊ ምድር (የእስራኤል ምድር) እንደሚኖራቸው የተስፋ ጭላንጭል ታየ::

ቀጣዩ የምጥ ጣር ማለትም 2ኛው የዓለም ጦርነት ዳግም ከ20 ዓመት በኋላ ተከሰቶ:: ከ1939-1945 ዓ.ም. ዓለምን አናወጣት የፖለቲካዋንም ይዞታ ቀየረው:: የምስራቁ ብሎክ (ሕብረት)፣ የምዕራብ ኢንዱስትሪ የበለጸጉት ሕዝቦችና የሦስተኛው ዓለም ሀገሮች ምስረታ የዚህ ጦርነት ውጤት ናቸው:: ያለ ጥርጥር የእነዚህ የምጥ ጣር ዋና ምክንያት በግንቦት 1 ቀን 1948 ዓ.ም. የሆነው የእስራኤል መንግስት መመስረት በእነዚህ ጥቂት መረጃዎች መሰረት በዓለም ሕዝቦች ውስጥ የሚሆኑ የምጥ ጣሮች ከእስራኤል ጋር የተያያዙ መሆናቸውን እንገነዘባለን:: በመቀጠል የአሁኗ የእስራኤል መንግስት እንደ ተዓምር ብቅ ብላ ታየች::

ይህ ሁኔታ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የዓለም ሕዝብ ሰላም አላገኘም:: በየክልሉ የምጥ ጣሮች እየፈነዱ ናቸው:: ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ 140 የሚያህሉ ጦርነቶችና ውዝግቦች ተከስተው ከ30 ሚሊዮን የሚበልጡ ሰዎች ሞተዋል:: የእግዚአብሔር ዋና ከተማ የሆነችው ኢየሩሳሌም በ1967 ዓ.ም. የእስራኤል ምድር ሆነች ከስድስቱ ቀን ጦርነት በኋላ የምጥ ጣሮች በአስደናቂ ሁኔታ እየጨመሩ መጡ:: በዮርዳኖስና በቀይ ባሕር መካከል ያለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው የተስፋ ምድር በእስራኤል እጅ ገባ:: ከዚህን ጊዜ ጀምሮ የምጥ ጣሮች አላቆሙም:: ከዚህ





በፊት ያልሆኑ ድንገተኛ ለውጦች ታይተዋል:: ክስተቶቹ ባፋጣኝ አንዱ በአንዱ ላይ እየተነባበሩ በግልጽ እየታዩ ናቸው:: በጊዜው የሚታዩትን ሂደቶች ስንመለከት ይህን በግልጽ ያመለክቱናል:: ለምሳሌ ያህል:- አለም አቀፍ ሽብርተኝነት በ1967 ዓ.ም. ተጀመረ፣ ዓለም አቀፍ የሰይጣን ቤተ ጸሎት መመስረት፣ የወሲባዊ ትምህርት በትምህርት ቤት መሰጠት፣ ሰዶማዊ ድርጊቶች በግልጽ መሆን፣ ነፃ የሆነ የሞራል ሕግ መመስረት፣ በወጣቶች መካከል እፅ የመጠቀሙ ነገር መጨመሩ፣ የሩቅ ምስራቁ ሃይማኖት ወደ ምዕራቡ ዓለም መግባት፣ በክርስትና ሀገሮች አክራሪ የሆነ የእስልምና ሃይማኖት መግባት፣ በአጠቃላይ የሩቅ ምስራቁ ቴራፒ (ዮጋ፣ አውቶጀኒክ ስልጠና መካሔድ፣ የደረቅ መርፌ ሕክምና ወ.ዘ.ተ)፣ የድሎት ምግቦች፣ የሲጋራና የመጠጥ ፍጆታና የምድራዊ ደስታ ፍላጎት መጨመር በዓለም እየተስፋፋ ያለው ሰይጣናዊ የሆኑት የሮክና የፖፕ ሙዚቃዎች፣ ምስጢራዊ ሰይጣናዊ አሰራሮች፣ አመጽ፣ ግብረ ገደቢስነትና ከፋት የተሞሉባቸው ጽሑፎች ፊልሞችና ቪድዮዎች በየስቶሩ መብዛትና መገኘት ናቸው:: በአሁኑ ጊዜ አሕዛብ የሰይጣናዊ ሃይማኖቶችን (አምልኮዎችን) አዲስ ተሐድሶን እየተለማመዱ ናቸው:: ሰዎች ፀሐይን ያመልካሉ፣ የተለያዩ የጥንቆላ በዓላትን ያከብራሉ፣ ማንኛቸውንም ዓይነት አስማቶችን ይለማመዳሉ:: በአሁኑ ጊዜ ያለው ሕብረተ-ሰብ ሃይማኖታዊ ልምምዶችን፣ ማሰላሰልንና መመራመርን ስለመናፍስት ማውራትን፣ አስማትንና ድግምትን በመጠቀም ላይ ይገኛል:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ ሲል «እንደ ኖህ» ዘመን እንደሚሆን አመልክቷል *(ማቴ.24:37-39)*::

እነዚያ የኖህ ዘመን ክፉ ልምምዶች ዛሬም ከእኛ ጋር እንዳሉ የማይካድ ሀቅ ነው:: የውጭውን ዓለም ሁኔታ ትኩረት ሰጥተን ብንመለከት የመጨረሻው ዘመናት ምጥ ጣሮች እየተፋጠኑ በመሔድ ላይ እንዳሉ ያረጋግጡልናል:: እየጨመረ ያለው ጥፋትና የአከባቢ (የመጠጥ ውሃ የመሬትና የአየር) ብክለት ዓለም አቀፍ የሙቀት መጠን መጨመር (የኦዞን መቀደድ) የውቅያኖሶች መበከል (የነዳጅ ዘይት ዝቃጭ) እየጨመረ ያለው በሽታ (የመበረዝ፣ የላንባ ነቀርሳ፣ የኤድስ ወ.ዘ.ተ) የምጥ ጣሮች ናቸው ብዙ መመዝገብ ይቻላል:: በየቀኑ የሚታተሙትን ጋዜጦቻችንን ስናይ በእነዚህ ልምምዶች የተሞሉ ናቸው::


ሆኖም ይህ ሁሉ «የምጥ ጣር መጀመሪያ» ነው፣ ምክንያቱም ፀረ ክርስቶስ ከመገለጡ በፊት እየጨመሩ የሚታዩ ናቸው:: ቀጥሎ ጨመቅ ተደርገው የተገለጡት ቻርቶች በ ማቴዎስ 24 የተጠቀሱትን የምጥ ጣር ዓይነቶች እንዴት እንደሚጀምሩና ከዚያም በመቀጠል እስከ መጨረሻው የአስፈሪው ፍርድ ቀናት ድረስ መቀጠላቸውን

የሚያሳዩ ናቸው:: ከ ራዕ.6-19 ያሉት ፍርዶች መስኮታዊ ፍርዶች ናቸው:: ማለትም በቀጥታ ከእግዚአብሔር የሚመጡ ፍርዶች ናቸው ማለት ነው:: በመጨረሻው ቀናት በአጋጣሚ የሚከሰቱ ማንኛውም ዓይነት የተፈጥሮ ጥፋቶች አይደሉም:: እነዚህ ፍርዶች ለብዙ ሺህ ዓመታት ወንጌልን ላለመቀበል በመረጡትና ወንጌልን በተቃወሙት ላይ የሚወርዱ መሆናቸውን ልንገነዘብ ያስፈልገናል:: እግዚአብሔርንና ጌታ ኢየሱስን እንዲቃወሙት ያደረጋቸውን ፀረ ክርስቶስን የሚቀበለው ይህ ሕዝብ ነው:

*መጽሐፍ ቅዱስ* በራዕይ መጽሐፍ የተጻፉትን ሶስቱን ዓይነት ፍርዶች በመለየት አስቀምጧቸዋል::

1. የማህተም ፍርዶች (*ራዕይ.6:1-17፣ 8:1)*
2. የመለከት ፍርዶች (*ራዕይ.8:2-9:21፣ 11:15)*
3. የጽዋው ፍርዶች (*ራዕይ.16:1-2)*

እነዚህ ፍርዶች ሁሉ በፀረ ክርስቶስ የመከራ ዘመን በሰው ዘር ላይ የሚወርዱ ናቸው:: ስለዚህም በማዳን ዕቅድ ካርታ ላይ በቤተ ክርስቲያንና በክርስቶስ ዳግም መምጣት ባለው ጥያቄ ምልክት መካከል የተደረገ ነው:: የዚህ




ፍርድ ጊዜ ሊገመት የማይቻል አስፈሪ የሆነ ነው:: ከላይ የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በምናነብበት ጊዜ «እነዚህ ቀኖች ባያጥሩ» *ሥጋ* የለበሰ ሁሉ ባልዳነ ነበር የሚለውን ልንገነዘብ እንችላለን (*ማቴ.24:22)*::

ስለዚህ ፀረ ክርስቶስ የሚያመጣው መከራ ለእስራኤል ተሐድሶ ፈተናና ፍርድ መሆኑን ያመለክታል:: በሌላ አነጋገር እስራኤልን ለሚመጣው እውነተኛ መሲህ የሚያዘጋጃት ነው ማለት ነው:: በመጀመሪያ እስራኤል ፀረ ክርስቶስን ይቀበሉትና በኋላ ግን የሚጠይቀውን አምላካዊ አክብሮት ባለመስጠት ይቃወሙታል:: ሆኖም ትልቁ መከራ ለሚጠፉት (ጌታን ሳልተቀበሉት)





የጥፋት ፍርድ ይሆንባቸዋል:: ምክንያቱም ዘንዶውንና አውሬውን በግል ስለሚያመልኩት (*ራዕ.13:4)* በዚህም ሰይጣን የሚጠይቀውን አምልኮት በቀጥታ ስለሚሰጡት ነው::

## ፀረ ክርስቶስና ሐሰተኛው ነቢይ

የፀረ ክርስቶስ ማንነትና መንግስቱን በተመለከተ ቀደም ያሉት መግለጫዎች ግልጽ አድርገውታል:: ታላላቅና እታላይ የሆኑት ኃይላት በዓለም ማንኛውንም ሰው ለፀረ ክርስቶስ እንዲሰግድ ያደርጉታል (*ራዕ.13:4)*:: መጽሐፍ ቅዱስ ክፉና የሰይጣን መናፍስት የዓለም ነገሥታትን ለማታለል እንደሚዞሩ ይናገራል (*ራዕ.16:13-14)*:: ከእነዚህ የጨለማ ኃይላት እርዳታ ውጪ መላው ዓለም በሌላ ኃይል ለፀረ ክርስቶስ ሊሰግድለት አይችልም::

የራዕይ መጽሐፍ የፀረ ክርስቶስ በፀረ-ክርስቲያናዊ የዓለም መንግስታት ላይ የመጨረሻው መሪ በመሆን አስፈሪ ስልጣኑን ለብቻው እንደማያሳይ ይነግረናል:: ተከታዩ የሆነው ረዳቱ በጎኑ ይቆማል:: ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ

*«ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፣ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር» በማለት ይናገራል (ራዕ.13:11)::*

እዚህ ሁለተኛውን አውሬ እንመለከታለን:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አውሬ «ሀሰተኛው ነቢይ» በማለት ይገልጸዋል:: (*ራዕ.19:20)* ይህ አውሬ የመለኮት ተቃዋሚ የሆነው የሰይጣናዊ ሦስትዮሽ ሦስተኛው ሰው ነው:: ራሱንም እንደሚከተለው ይገልጻል:: የሠይጣን ሦስትነትም እንደሚከተለው ይገለፃል::

1. ዘንዶው:- ራሱ ሰይጣን (*ራዕ.12)*
2. ከባሕር የሚወጣው አውሬ-የፀረ ክርስቶስ (*ራዕ.13:1-8)*
3. ከምድር የሚወጣው አውሬ - ሀሰተኛው ነቢይ (*ራዕ.13:11)* ናቸው::

ከመለኮት ሁለተኛውና ሦስተኛው ማንነት (ኢየሱስ ክርስቶስና መንፈስ ቅዱስ) ከላይ ከሰማይ ወደ ምድር ወርደዋል:: በተቃራኒው ደግሞ የሰይጣን ሦስትዮሽ ሁለተኛውና ሦስተኛው አካል (ፀረ ክርስቶስና ሀሰተኛው ነቢይ) ከታች ከጥልቅ ይመጣል:: (ራዕ 11:7፣ 17:8) ፀረ ክርስቶስ ከባሕር ሲወጣ (ከአሕዛብ መካከል) (*ራዕ.13:1)* በተቃራኒው ደግሞ ሐሰተኛው ነቢይ ከምድር (ከእስራኤል) ይወጣል:: በእስራኤል ከሚኖሩት ሰዎች አንዱ ሊሆን ይችላል::

የሚቀጥለው ንጽጽር ሀሰተኛው ነብይ የመንፈስ ቅዱስ ተቃራኒ እንደሆነ ያሳየናል:: በቅጂ (የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በማስመሰል) ሰዎችን ለክርስቶስ ተቃዋሚ እንዲሰግዱ ያደርጋል::

| መንፈስ ቅዱስ ዮሐ. 16:13-15 | ሀሰተ[illegible] |
| --- | --- |
| 1. መንፈስ ቅዱስ እንደሚነድ እሳት ከሰማይ መጣ (ሐሥ.2:1-4):: | 1. ሀሰተኛው ነቢይ ከሰማይ እሳት እንዲወርድ ያደርጋል (ራዕ 13:13):: |
| 2. መንፈስ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስን ያከብራል (ዮሐ.16:14-15):: | 2. ሀሰተኛው ነቢይ ፀረ ክርስቶስን ያከብራል (ራዕ. 13:15):: |
| 3. መንፈስ ቅዱስ ዳግም የተወለዱትን አብንና ወልድን እንዲያመልኩ ይመራል (ዮሐ. 4:23-24):: | 3. ሀሰተኛው ነቢይ ሰዎች ፀረ ክርስቶስንና ሰይጣንን እንዲያመልሉ ያበረታታል (ራዕ. 13:13-17):: |
| 4. መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያቱ በኩል ድንቅና ተዐምራትን ያደርጋል (ዕብ.2:4):: | 4. ሀሰተኛው ነቢይ ምልክቶችንና ታምራቶችን ያደርጋል፡ (ራዕ.13:13):: |
| 5. መንፈስ ቅዱስ አማኞችን ያትማል (2ቆሮ. 1:22፤ ኤፌ.1:13፤ 4:30) | 5. ሀሰተኛው ነቢይ የማያምኑትን የራሱን ምልክት ያትምባቸዋል (ራዕ. 13:16) |
| 6. መንፈስ ቅዱስ በመስቀል ላይ የተፈጸመውን የደህንነትን ሥራና የክርስቶስ ትንሣኤ ከፍ ከፍ ያደርጋል(1ቆሮ.1:23፤2:2፤ዮሐ.14:6፤ ሐሥ.1:8፣ 1ጴጥ.1:11፤ 1ተሰ.1:4-6):: | 6. ሀሰተኛው ነቢይ የፀረ ክርስትስን መቁሰልና መነሳት /መፈወስ / ከፍ ከፍ ያደርጋል /የክርስቶስ ትንሣኤ ቅጅ በማድረግ ሰይጣናዊ ትንሣኤ/ (ራዕ.13:12):: |
| 7. መንፈስ ቅዱስ አማኞች ክርስቶስን እንዲመስሉ ይለውጣል:: (2ቆሮ.3:17፣18 ሮሜ.8:26-30) | 7. ሀሰተኛው ነቢይ የፀረ ክርስቶስን ምስል እንዲያመልኩ ይጋብዛል:: (*ራዕ.13:14-15*):: |

*ሁለቱም ፀረ ክርስቶስና ሀሰተኛው ነቢይ በመዋጀት ካርታ ላይ በስም ተጠቅሰዋል:: እነዚህ ሰይጣናዊ ሰዎች ሰዎችን ወደ ጥልቁ ለመሳብ አንድ ላይ ይገሰጣሉ::*

*የሐሰተኛው ነቢይ ሚና በፀረ ክርስቶስ መንግስት ምንድን ነው?*

እንደ (*ራዕ.13:11-18*) መሠረት ሀሰተኛው ነቢይ የፀረ ክርስቶስ አስተዋዋቂ ነው:: ፀረ ክርስቶስ ስልጣን በፊቱ በማድረግና ስለ እርሱ በመቆም ሰዎች ይህን





የመጨረሻውን የዓለም መሪ እንዲያከብሩትና መለኮታዊ አክብሮት እንዲሰጡት ያደርጋል (*ራዕ.13:14*)፡ ማንኛውም ሰው ሀሰተኛውን ነቢይ ለመቃወም ምርጫ አለው:: አስፈሪና አስገዳጅ ኃይል ከእርሱ ጀኔራል ጋር ይሆናል:: እሳች ኃይሎች ማለት ነው:: ፀረ ክርስቶስ ወይም ምስሉን (የአውሬውን ምስል) ላለማምለክ አሻፈረኝ የሚሉት ይሰደዳሉ፣ ይገደላሉ:: (*ራዕ.13:15*)

### ሐሰተኛው ነቢይ

- *እንደ ዘንዶው ይናገራል (ራዕ.13:11)*
- *ፀረ ክርስቶስ ስልጣን ይጠቀማል (ራዕ.13:12)*
- *ታላላቅ ምልክቶችን ያደርጋል (ራዕ.13:13)*
- *ከሰማይ እሳት እንዲወርድ ያደርጋል (ራዕ.13:13)*
- *ሰዎች ፀረ ክርስቶስን ለማክበር «ምስል» እንዲያበጁ ያስገድዳል (ራዕ.13:14)*::
- *ለአውሬው ምስል እስትንፋስ ይሰጠዋል (ራዕ.13:14፣15)*
- *ማንኛውም ሰው «ምልክትን» እንዲቀበል ያስገድዳል (ራዕ.13:16፣17)*

ከእነዚህ ጥቂት ነጥቦችን እንመልከት::

### «እንደ ዘንዶው ይናገራል»

*ሀሰተኛው ነቢይ ከፀረ ክርስቶስ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ባሕርይ አለው:: ከፍተኛ የመናገር ችሎታ አለው:: በተለይም ፀረ ክርስቶስን ከፍ ከፍ በሚያደርግበት ጊዜ የንግግር ችሎታው የተገለጠ ይሆናል:: በተጨማሪ እንደ ፀረ ክርስቶስ «በአማልክት አምላክ ላይ በትዕቢት» ይናገራል (ዳን.11:36)፡ «እግዚአብሔርንም ለመሳደብ ስሙንም፣ ማደሪያውንም፣ በሰማይም የሚያድሩትን ሊሳደብ» አፉን ይከፍታል:: (ራዕ.16:6) መለኮታዊ፣ ሰማያዊ፣ የከበሩና ዘላለማዊ የሆኑትን ማንነቶችና ነገሮች እንደ እድፍ አድርጎ በማሰብ ፍጹም ዋጋ የሌላቸው ከንቱዎች አድርጐ ይቆጥራል (ሮሜ.1:28)፡ የሰይጣን ዜና አሰራሮች የዚህችን ዓለም ውበት ለዓለም ሕዝቦች ብሩህ አድርገው በመሳል እንዴት እደሚያታልሉ ያውቃሉ (ማቴ.4:8)፡ መላው የሰው ዘር ከእውነት በመለየት፣ ከተስፋዎች ሁሉ ርቀው በመወሰድ (በአጠቃላይ በምድራዊ ቁሳቁሶችና በሚያልፉት ነገሮች በመወሰድ) መላ ሕይወታቸውን ከታላቁ መሪ ፀረ ክርስቶስ ጋር የተጣበቀ ያደርጉታል:: ከእግዚአብሔር በመራቅ ወደ ከፋው ክህደት ይገባሉ:: የዚህ ሰይጣናዊ ነቢይ ንግግር ቁጥር የሌላቸውንና በአጠቃላይ በሰይጣን የተያዙትን ሕዝቦች ለሰይጣን እንዲሰግዱ ያደርጋቸዋል (ራዕ.13:4)::*

## «ታላላቅ ምልክቶችን ያደርጋል»

ዛሬ እየጨመሩ ስላሉት «ምልክቶችና ተዓምራቶች» ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ እውነት ነው:: በየአቅጣጫው በዜና ማሰራጫዎች ይታያሉ:: ጋዜጦችና ቴሌቪዥኖች አስደናቂ የሆኑ ሁኔታዎችን፣ ስሜታዊና ተዓምራዊ የሆኑ ነገሮችን ያቀርባሉ:: እነዚህ ነገሮች በሕዝብ መካከል የተገለጡ ሆነዋል ምክንያቱም የሚስቡ ስለሆኑ ምልክቶችና ታምራቶች በፀረ ክርስቶስ መንግስት ከፍተኛ ስፍራ አላቸው:: ሰይጣን ጉጉት ያላቸውን ሰዎች እንዴት እንደሚስብ ያውቃል:: ስለዚህም ሀሰተኛው ነቢይ ብዙ ታላላቅ ሥራዎችን ይሠራል:: «እሳትንም እንኳን ከሰማይ ወደ ምድር በሰው ፊት እስኪወርድ ድረስ» ያደርጋል (*ራዕ.13:13*):: በታምራቱ የተደነቁት የሰው ዘሮች ከመሳሳታቸው የተነሳ በእነዚህ ታምራት አድራጊዎች የተገለጠው ኃይል ከእግዚአብሔር የመጣ ነው በማለት ያምናሉ::

የፀረ ክርስቶስ ተዓምራታዊ መዳን (በድጋሚ መነሳት) በብዙ ሰዎች ላይ ከፍተኛ ውጤት ያስከትላል ያመጣል:: ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ

*«ከራሶቹም ለሞት እንደታረደ ሆኖ አንዱን አየሁ፣ ለሞቱ የሆነውም ቁስል ተፈወሰ:: ምድርም ሁሉ አውሬውን እየተከተለ ተደነቀ» በማለት ይናገራል (ራዕ.13:3::)*

ከፀረ ክርስቶስ መገለጥ ጋር የተያያዘው የመጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ነው:: ለሞት የሚሆን ወደሞት የሚያደርስ መቁሰል በእርሱ ላይ ከደረሰ፣ በእርግጥ ይገደላል ማለት ነው:: ለሞት የሆነ አደጋ የሚደርስበት ሰው ይሞታል:: ስለሆነም ፀረ ክርስቶስ ወደፊት ይሞታል ማለት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ለሞቱ የሆነው ቁስሉ በድንገት እንደሚፈወስ ይነግረናል:: ይህም ማለት ፀረ ክርስቶስ ተሐድሶ ደርጋል ወይም በተለየ ሁኔታ ይገለጻል ማለት ነው:: ፀረ ክርስቶስ ለመላው ዓለም እርሱ እውነተኛው መሲህና መሪ መሆኑን ለመግለጽ በሰይጣናዊ መንገድ የክርስቶስ ኢየሱስን ትንሳኤ በማስመሰል ይጠቀማል:: ለጊዜው ይህ «ምልክት» አይሁድን እንኳን የሚስባቸው ይሆናል:: ስረጅም ዘመናት የተጠበቀው መሲህ እርሱ ነው በማለት ፀረ ክርስቶስን ይቀበሉታል:: በኢየሩሳሌም በነበርንበት ጊዜ ጥቂት አይሁዶች «ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት አልዓዛር በቢታንያ ከሞት እንደተነሣ (ዮሐ. 11:1-45) ኢየሱስ ክርስቶስም ከሙት የተነሳና በኢየሩሳሌም ጎዳናዎች የተዘዋወረ ቢሆን ኖሮ መላ እስራኤል በእርሱ ያምኑ ነበር» ብለውናል:: ፀረ ክርስቶስ የሚያደርገው ልክ እንደዚህ ነው::





ፀረ ክርስቶስ ሙት ከቀረበ ህልውና ይነሳል፤ ራሱንም እውነተኛ መሲህ በማድረግ ይገልፃል:: ኢየሱስ ክርስቶስን ግን ይቃወማል (ይኮንናል):: በዚህ ድርጊቱ እስራኤላውያን ብቻ ሳይሆኑ መላው ዓለምም ጭምር ይወሰዳል:: በክርስቶስ ኢየሱስ ተቃዋሚ መንግሥት ምልክቶችና ታምራቶች ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ይሆናሉ:: በሀሰተኛው ነቢይ እጅ አደገኛ የማታለያ መሣሪያዎች ይሆናሉ::

## ፀረ ክርስቶስ ለክብሩ «ሰዎች ምልክትን እንዲቀበሉ ያስገድዳል»

በኃጢአት የወደቀው ሰው ሁልጊዜ የሚያመልከውን ምስል ይፈጥራል (ይሠራል):: ብሉይ ኪዳን ብዙ ሰዎች እራሳቸው ለሰሯቸው ምስሎች እንደ ሰገዱ ይናገራል:: በፀረ ክርስቶስ መንግሥትም በከፍተኛ ደረጃ የዚህ ዓይነቱን የጣዖት አምልኮት የሚለማመዱ ይሆናሉ:: ከምልክቶቹና ከታምራቶቹ ጎን ሌላ ሰይጣናዊ የሆነ ሁለተኛ ኃይል የሚሔድ ይሆናል:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህን «የአውሬው ምስል» በማለት ይገልጸዋል::

## የአውሬው ምስል

*«በአውሬውም ፊት ያደርግ ዘንድ ከተሰጡት ምልክቶች የተነሳ በምድር የሚኖሩትን ያስታል፣ የሰይፍም ቁስል ለነበረውና በሕይወት ለኖረው ለአውሬው ምስልን እንዲያደረጉ በምድር የኖሩትን ይናገራል» (ራዕ.13:14)::*

ቀደም ብለን እንዳየነው ሐሰተኛው ነቢይ ከሚያደርጋቸው ምልክቶችና ታምራቶች የተነሳ በተሰጠውና በሕዝብ ዘንድ በተመሰከረለት ሥልጣኑ ለፀረ ክርሰቶስ ዓለም አቀፍ ስግደት (አምልኮ እንዲደረግ) ይጠይቃል:: ይህን እያደረጉ ሰዎች ሁሉ ለፀረ ክርሰቶስ ምስልን እንዲያደርጉ ጥሪ ያደርጋል:: ሰዎች ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በተለያዩ መንገዶች ሲተረጉሙ ይችላሉ:: ስለምስሉቹ ቀጥሎ ያሉትን ሁለት ታሪካዊ ገፅታዎች እንመስከታለን:: አንደኛ፡ በንጉሡ ናቡከደነጾር ሕልም የባቢሎን የመጀመሪያው የዓለም መንግስት በትልቅ ምስል መጀመሩ አስደናቂ የሆነ ነገር ነው:: ይህን ቀደም ባለው ምዕራፍ ተመልክተናል:: *«አንተ ንጉሥ ሆይ! ታላቅ ምስል አየሀ፣ ይህም ምስል ታላቅና ብልጭልጭታው የበዛ ነበር በፊትህም ቆሞ ነበረ:: መልኩም ግሩም ነበር» (ዳን.2:31)::*

አሁን በመጨረሻዎቹ ቀናት በፀረ ክርስቶስ መንግስት ሰዎች ቁስሉ ስተፈወሰው ለአውሬው ክብር ምስልን እንደሚሠሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (*ራዕ.13:14*)፡ እንደምናውቀው ሁሉ ሀሰተኛው ነቢይ ሰዎች ለፀረ ክርስቶስ ምስል እንዲያደርጉ ያስገድዳል፡፡ ለዚህ ጣዖት ለሆነ ምስል የማይሰግዱት ደግሞ ይገደላሉ፡፡ ይህ ልክ ከ2600 ዓመታት በፊት ናቡከደነጾር ያደረገውን ይመስላል፡፡ እርሱ የፀረ ክርስቶስ አመልካች እንደ መሆኑ መጠን ከሥሩ የሚገዙትን «እርሱ (ናቡከደነጾር) ላቆመው ምስል» እንዲሰግዱ ጠይቋል (*ዳን.3:5*)፡

በማቴዎስ ወንጌል ጌታ ኢየሱስ ከታላቁ መከራ ጋር በተያያዘ «የጥፋት ርኩሰት» በተቀደሰው ስፍራ ስለመቆሙ ተናግሯል (*ማቴ.24:15*)፡ ቀደም ብሎ በብሉይ ኪዳን ነቢዩ ዳንኤል በቤተ መቅደስ ስለሚቆመው «የጥፋት ርኩሰት» ተናግሯል (*ዳን.9:27*)፡ ይህም ማለት «በተቀደሰው ስፍራ (በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ) የፀረ ክርስቶስን ምስል እንደሚከተል ያሳያል፡፡ አስደንጋጭ የሆነም ጣዖታዊ ሥነ ሥርዓት ይካሄዳል፡፡ ከዚህ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ጋር በተያያዘ አስከፊ የሆነ ክፉ ነገር ይደረጋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ፡-

*«የአውሬው ምስል ሊናገር እንኳን ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሁሉ ሊያስገድላቸው ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው»ይላል ራዕይ.13:15፡፡*

ታላላቅ ሰይጣናዊ ኃይላት ይህን በድን የሆነውን ምስል *ሕይወት* እንዲኖረው ያደርጉታል፡፡ ምስሉ መናገር ይጀምርና ሰምስሉ ላሰመስገድ አሻፈረኝ የሚሉትን ሰዎች እንዲገደሉ ያደርጋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ሰይጣን አጥፊ የሆነውን ሥራውን ወደ ፍፃሜ ያደርሳል (ያመጣል)» ሰዎችን ወደ አጠቃላይ ጥፋቱ እንዲገቡ ያስገድዳል፡፡ የዚህ «የአውሬው ምስል» ፍቺ በትክክለኛ ቃል «የጥፋቱ ርኩሰት» ይባላል፡፡

ሁለተኛ፡ በዚህ ክፍል ሌላ ሊታይ የሚገባውን ትልቅ ነገር እናገኛለን፡፡ በምንኖርባቸው በመጨረሻዎቹ ቀናት ብዙ ምስሎች ከቀን ወደ ቀን እያጥለቀለቁን ናቸው፡፡ እነዚህ ምስሎች ወደ ፊት በተራመደው ቴክኖሎጂ እትመት፣ ፊልሞች፣ ቴሌቪዥንና ቪድዮ ኢንዱስትሪዎች የሚፈጠሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ምስሎች በአሁኑ ጊዜ በኃጢአት የተሞሉትን የሰዎችን ፍላጎቶች የሚያረኩ ናቸው፡፡ በእነዚህ መጠን ብዙ ምስሎች በመረዳት (በመደገፍ) የሰው ዘር በዚህ ምድርና በማይታየው ዓለም





ባለው ሕይወት ላይ ትኩረት ማድረግ ይችላል፡፡ ውጤቱም የሰው ዘር በልቡ ለተከላቸው ምስሎች የሚገዛና በቁጥጥራቸው ሥር የሚሆኑ ነው፡፡ በበለጠ የሰው ዘር በማየት ስለሚመራ የማመኑ ነገር ያነሰ ይሆንበታል፡፡ ማየት ሰውን በሚታየው፣ በአመጸና በሚያልፍ ነገር ላይ እንዲቆራኝ ያደርገዋል፡፡ እምነት (ማየት ሳይሆን) ሰውን ወደ ዘላለሙና ወደማይጠፋው ህይወት ይመራዋል (*2ቆሮ.5:7፤ ዮሐ.20:29)*፡፡ ፀረ ክርስቶስ መላውን የሰው ዘርን ለማሳት እንዲቻለው የዜና ማሰራጫዎችን ዘመናዊ ምስሎችን መጠቀሚያ ለማድረግ የመያዝ ችሎታ አለው፡፡ በተለይም ቴሌቪዥን በዘመናዊ ሳተላይት ቴክኖሎጂ በመደገፍ የክርስቶስን ተቃዋሚ በመላ ዓለም በማንኛውም ቤትና መኖሪያ ሥፍራ በአንድ ጊዜ እንዲገኝ ያደርገዋል፡፡ በዚህ ገለጻ ቴሌቪዥን ሰዎች ሁሉ በቁጥጥሩ ስር የሚገቡለት «የሚናገር ምስል» ይሆናል ማለት ነው፡፡ በቀላል መንገድ ፀረ ክርስቶስ «መንፈሱን» በሰዎች ልብና ቤት ለማስገባት ያስችለዋል ማለት ነው፡፡ ለይጣናዊ በሆነ ኃይል ፀረ ክርስቶስ የሰውን ዘር ከእርሱ ሊርቁ ወይም ሊቃወሙት በማይችሉበት ሁኔታ በታላቅና በአስደናቂ ኃይል ይይዛቸዋል፡፡ እነርሱም እርሱ የጠየቀውን አምልኮና ስግደት ይሰጡታል፡፡

## «ሰዎች ሁሉ ምልክት እንዲቀበሉ ያስገድዳል»

ባለንበት ዘመን አማኞችም ሆኑ ከሃዲያን (የማያምኑ) በይበልጥ እየተደነቁ ናቸው፡፡ በፍጥነት እያደገ ባለው ቴክኖሎጂ በተለይም በኮምፒዩተርና በኤሌክትሮኒክ በሚሰሩት ኢንድስትሪዎች፣ የሰው ልጅ በመጽሐፍ ቅዱስ ፀረ ክርስቶስ ብሎ ወደሚጠራው እየተፋጠኑ በመድረስ ላይ ነው፡፡ (*ራዕ.*11-19) የሰው ዘር በሙሉ በዚህ ተቃዋሚ በቁጥጥር ስር እንደሚሆን ይገልጻል፡፡ በምድር ላይ የሚኖሩት ሰዎች በሀሰተኛው ነቢይ (ሀሰተኛው የሰይጣን ስብዕና) አማካኝነት ፀረ ክርስቶስን ያከብሩታል፣ ሰይጣንን ያመልካሉ፣ ለአውሬው ምስል እዲሰግዱ ይገደዳሉ (*ራዕ.13:1-18*)፡

የፀረ ክርስቶስ መንግስት (በአንድ መሪ ስር የሆነ አገዛዝ)፣ ሰዎች በቁጥጥሩ ስር የሚውሉበት አገዛዝ ብቻ ሳይሆን ባሪያም የሚደረጉበት ነው፡፡ ሀሰተኛው ነቢይ ሰዎችን ለፀረ ክርስቶስ ተገዢዎች ለማድረግ ለማታለል የሚያስችለውን የመጨረሻውን ስልት በመጠቀም ለማንኛውም ሕዝብ ግልጽ የሆነውን መሣሪያ ይጠቀማል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ሰይጣናዊ መሣሪያ «የአውሬው ምልክት» በማለት ይገልጸዋል፡፡

## የአውሬው ምልክት

*«ታናናሾችና ታላላቆችም ባለ ጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎችም ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም በግንባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ፣ የአውሬው ስም ወይም የስሙ ቁጥር ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል ያደርጋል። ጥበብ በዚህ አለ። አእምሮ ያለው የአውሬውን ቁጥር ይቁጠረው፣ ቁጥሩ የሰው ቁጥር ነውና፣ ቁጥሩም በድበት መቶ በድሳ ስድስት ነው» (ራዕ.13:16-18)።*

በአሁኑ ቀናት ያለ ቁጥር የሚሰራ ነገር እንደሌለ ግልጽ ነው። ሰዎች በማንኛውም ቦታ በባንክ ቢሆን፣ በኢንሹራንስ ኩባንያ፣ በመንግስታዊ ቢሮዎች በመጋዚኖች፣ በሱቆች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በዩኒቨርስቲዎች ወይም በማንኛውም ሕዝባዊ ድርጅቶች ቁጥር ተሰጥቷቸው ወይም የኮምፒዩተር ኮድ የተሰጣቸው (የተመዘገቡ) ናቸው። የዚህ ምዝገባ አሰራር ለብዙዎች ሊገለጽ የማይቻል ምስጢራዊ ስሜትን ያሳድርባቸዋል። በአሁኑ ጊዜ የዚህ ምዝገባ ስፋት ከግለሰብ ቁጥጥር ባሻገር አልፎ ሄዷል። በአሁኑ ቀናት ስለ እርሱ ማንነትና ሁኔታ በኮምፒዩተር ተመዝግቦ የት እንደሚገኝ እውነተኛ ሊሆን የሚችል የለም። ሰዎችን በታላላቅ መንግስትና ኩባንያ መመዝገብ (በተጨማሪ ሁኔታን በሚመዘግቡ የዕርዳታ ማዕከላት) በዓለም አቀፍ አንዱን ከሌላው ጋር ለማያያዝ የሚቻልበት ዘዴ አሁን ግልጥ እየሆነ ነው። በክልላዊ ድንበሮች ሳይወሰኑ በማንኛውም ሁኔታ ስር ኢንፎርሜሽንን (ሀሳብን) ለመለዋወጥ የሚቻል ሆኗል። ያልተገለጡ (በሀሳብ ያሉ) ፖለቲካዊና ሕዝባዊ ሥርዓቶች ተሰውረው አይቀሩም። በዚህ ምትክ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የተገለጡ (እውን የሆኑ) ይሆናሉ። በአጭሩ እንደምንመለከተው የቴክኖሎጂ እድገት ለፀረ ክርስቶስ ዓለምን በሙሉ ባርያና በቁጥጥሩ ስር ሊያደርግ የሚችልበትን መሣርያ እየሰጠው ነው። እንደ (*ራዕ.13:16*) በፀረ ክርስቶስ አገዛዝ ዘመን ሀሰተኛው ነቢይ ማንኛውንም ሰው በእጁ ወይም በግንባሩ ምልክት እንዲቀበል ያስገድዳል። ያለዚህ ምልክት ማንኛውም ግለሰብ ሊገዛም ሆነ ሊሸጥ አይችልም (*ራዕ.13:17*)። ይህም ማለት ከማንኛውም ለሕይወት ከሚያስፈልገው ነገር የተወገደ ይሆናል ማለት ነው። የገንዘብ፣ የምግብ፣ የልብስ፣ የህክምናና ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑትን መብቶች ከማጣት የተነሳ ለመቃወምም ሆነ ጭቆናዊ ከሆነው አገዛዙ ማምለጥ አይቻልም። ስለሆነም በመጨረሻ አብዛኛውን ሕዝብ በመስማማትና በመከተል ሕዝቡ የአውሬውን ምልክት ይቀበላል። በቴክኒካዊ





አሰራር የማይታይ ኮምፒውተራዊ «ምልክት» መቀበል በሰው ቆዳ ላይ ቴክኒካዊና ልምምዳዊ ጉዳይ ያለው ብቻ ሳይሆን ከዚህ በበለጠ ሁኔታ

*የአውሬው ምልክት ፍቺ ምንድን ነው?*

ብለን እንድንጠይቅ ያስገድደናል «የአውሬው ምልክት» የፀረ ክርስቶስ ምልክት ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ «ምልክቱ» «የአውሬውን ስም ወይም የስሙን ቁጥር» የያዘ ነው(*ራዕ.13:17*)።ለዚህ መሪ ራሳቸውን በሰጡ ሰዎች የሚደረግ ነው።

የዚህ ምልክት ፍቺ በእጅና በግንባር ላይ ከሚታየው ምልክት ባሻገር የላቀ ነገር አለው። ከዚህ ከሚታየው ሥራ በስተኋላ አስፈሪና የማይታይ እውነታ ይከናወንበታል። ይህንን ምልክት መቀበል ማለት ራስን ለዲያብሎስ በመስጠት በሰይጣናዊ ማህተም መታተም ማለት ነው። ይህ አሠራር ዳግም ለተወለዱ የእግዚአብሔር ልጆች በመንፈስ ቅዱስ የመታተሙ ተቃራኒ የሆነ አሠራር ነው (*ኤፌ.1:13፣ 2ቆሮ.1:22*)። ሰው ይህን ምልክት በመቀበል ዘላለማዊ የሆነ ጥፋቱን ያትማል።

*«ሦስተኛም መልአክ ተከተላቸው፣ በታላቅ ድምፅ እንዲህ እያለ ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግድ በግንባሩም ወይም በእጁ ምልክቱን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ደግሞ በቁጣው ጽዋ ሳይቀላቀል ካዘጋጀው ከእግዚአብሔር ቁጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል። በቅዱሳንም መላእክትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሠቃያል። የሥቃያቸውም ጢስ ለዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ይወጣል። ለአውሬውና ለምስሉም የሚሰግዱ፣ የስሙንም ምልክት የሚቀበሉ ሁሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም» ተብሎ ተጽፏል። (በራዕይ.14:9-11)*

የአውሬውን ምልክት የሚቀበሉ ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች ለፀረ ክርስቶስና ለሰይጣን ግልጽ የሆነ የመጨረሻ ውሳኔያቸውን መስጠታቸውንና በግልጽ እርሱን በማምለክ ማክበራቸውን ያሳያሉ። ለዘላለምም ከእውነተኛው አምላክና አዳኝ የተለዩና የጠፉ ይሆናሉ።

*የ666 ፍቺ ምንድን ነው?*

666ትን በተመለከተ ብዙ ዓይነት አመለካከቶችና ግምቶች አሉ። ሆኖም ግን ስለ 666 የተሰጡትን ግምታዊ ሀሳቦች ወደ ጐን በመተው በግልፅ በተጻፈው ላይ እናተኩራለን። (ራዕ. 13:17) ይህ ቁጥር ስለ ስሙ ቁጥር የሚናገር መሆኑን እርግጠኛ ነን። የፀረ ክርስቶስ ስም በዚህ ቁጥር ውስጥ የተሰወረና (ምስጢር) የሆነ

ነው ማለት ይቻላል:: በዕብራውያን፣ በግሪክና በላቲን ስሞች በቁጥር የሚገለጡ ናቸው፣ ምክንያቱም የእነዚህ ቋንቋዎች ፊደላት ቁጥር አላቸው:: ለምሳሌ በግሪክና በዕብራውያን ቋንቋ አልፋ /አሌፍ=1፣ ቤታ/ ቤት=2፣ ጋማ /ጋሜል=3፣ ኤዴልታ/ ዳሌጥ=4 ወ.ዘ.ተ. በማለት ፊደላት በቁጥር ይለየማሉ:: ስለዚህም የግሪክና የዕብራውያን ፊደላት በሙሉ የቁጥር ስያሜ አላቸው በላቲን ጥቂት ፊደላት ብቻ ናቸው የቁጥር ስያሜ ያላቸው:: I=አንድ II=ሁለት፣ III=ሦስት፣ IV=አራት፣ V=አምስት፣ X=አስር፣ XX=ሀያ፣ L=ሀምሳ፣ C=መቶ፣ D=አምስት መቶ፣ M=አንድ ሺህ :: ሌሎቹ ቁጥሮች ከእነዚህ ቁጥሮች የሚወሰዱ ናቸው:: የሚቀጥለው ምሳሌ ይህን ያሳየናል:: ከተሐድሶ በፊት እንደ ነበሩት እንደ ፒተር ዋልዱስ፣ ጆን ዊክሊፍ፣ ጃን ሁስ፣ ተሐድሶ ካደረጉ ከማርቲን ሉተር፣ ከሁልድርቼ ዝዊንግሊ፣ ከጆን ካሊቪን ጋር የሮሙ ጳጳስ ፀረ ክርስቶስ ነው በማለት ገምተው ነበር:: እነዚህ ሰዎች በሶስት ደረጃ ከተሠራው ከጳጳሱ ዘውድ (ቲአራ) ላይ የተጻፈውን VICARIUS FILII DEI (የእግዚአብሔር ልጅ ምትክ) የሚለውን ማዕረግ በመውሰድ 666 ቁጥርን ይተረጉሙታል:: VICARIUS FILII DEI (ቪካሪዩስ ፊሊ ዴያ) ማለት የእግዚአብሔር ልጅ ተወካይ ማለት ነው:: የላቲኑን ፊደል በመውሰድና ለፊደላቱ የተሰጡትን ቁጥሮች በአንድ ላይ ሲደመሩ ውጤቱ 666 ይሆናል::

| V | I | C | AR | I V S | F I | L | I | I D | E I |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ↓ | ↓ | ↓ | | ↓ ↓ | ↓ | ↓ | ↓ | ↓ ↓ | ↓ |

**5 + 1 +100 + 1+5 + 1 +50+ 1+ 1 + 500+ 1=666**

ይህን ምሳሌ ቁጥሩ እንዴት ከፊደላት ቁጥር ድማሬ እንደሚመጣ ያሳያል:: በተጨማሪም አንድን ቁጥር ወደ ስም ለመተርጎም የሚቻለው በመጀመሪያ ስሙ የሚታወቅ ሲሆን ነው:: በፀረ ክርስቶስ ነገር ላይ ግን ስሙን በቅድሚያ ያወቀ ስለሌለ 666 የሚለውን ቁጥር በስሙ ትርጉም ለመፍታት አይቻልም:: ፀረ ክርስቶስ አንድ ቀን በሚገለጥበት ጊዜ ግን አንጎል ያላቸው (አእምሮ ያላቸው) ይህን ቁጥር ለመተርጎም ይተጋሉ(*ራዕ.13:18*)::

በዚያን ቀን በፀረ ክርስቶስ መንግስት ቁጥሩ ታላቅ ሰይጣናዊ መግለጫ (መለያ) የሆነ ታላቅ ፍቺ እንዳለው ይታወቃል:: ሰይጣን ዓለምንና፣ ሰዎችን በሙሉ ለመቆጣጠር የእያንዳንዱን ሰው ልብ ለመያዝ ይፈልጋል:: ይህም ግልጽ የሆነና





የታወቀ ነገር ነው:: በሙሉ መገዛት ባለበት ቦታ «ሰዎች በሰይጣን ተይዘዋል» ለማለት እንችላለን:: ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ መንግስት የሆነ አስደንጋጭ (አስፈሪ) እውነታ ነው:: ሰይጣን በሂደት የሰዎችን ስብዕና በማጥፋት የሰውን ዘር በእርሱ ቁጥጥር ስር እንዲሆኑ ያስገድዳል:: በዚህ ምክንያት እያንዳንዱ ግለሰብ ወደ ምንምነት ይዘቅጣል:: በመጨረሻም ግለሰብነት የሌለው በህዝብ መንከል እንደ ቁጥር ሆኖ ይገኛል:: ግለሰቡ እንደ ተሳቢ ፍጥረት (እንስሳ) ለፀረ ክርስቶስ ባርያና ተገዢ ይሆናል:: በዚያም ሰይጣን የመጨረሻ ግቡን ያከናውናል::ማንኛውም የዚህ አባል የሆነ ያለ ጥርጥር ሰይጣንን ያመልካል::ጥልቅ የሆነው የ666 ቁጥር ፍቺ ይህ ነው::

## ፀረ ክርስቶስ ላይ የሚካሔደው ፍርድ

ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን በፀረ ክርስቶስና በመንግስቱ ላይ ስለሚወሰደው ፍርድ ቀደም ብለው ተናግረዋል:: በትንቢተ ዳንኤል በተወሰነው ጊዜ ፍጻሜ እንደሚሆን ይናገራል (*ዳን.9:24*):: ስለዚህ ትኩረት ሰጥተን ስንመረምር ይህ ፍርድ በሁለት ክፍል የተከፈለ ይሆናል::

1. የፀረ ክርስቶስ መንግስት ፍርድና
2. የፀረ ክርስቶስ የሃሰተኛው ነቢይ ፍርድ

## 1. የፀረ ክርስቶስ መንግስት ፍርድ

ለማስታወስ ያህል የባቢሎኑ ንጉሥ ናቡከደነጾር የለው ገጽታ ያለውና ለማየት አስፈሪ የሆነ ምስል ማየቱን ቀደም ብለን ተመልክተናል:: የዚህ ምስል ራስ ወርቅ፣ ደረትና ክንዶቹ ብር፣ ወገቡና ጭኖቹ ነሐስ፣ እግሮቹ ብረትና የእግሮቹም ጣቶች ብረትና ሸክላ ነበሩ (*ዳን.2:31-33*):: መጽሐፍ ቅዱስ

*«እጅም ሳይነካው ድንጋይ ከተራራው ተፈንቅሉ ከብረትና ከሸክላ የሆነውን የምስሉን እግሮች ሲመታና ሲፈጭ አየህ:: የዚያን ጊዜም ብረቱና ሸክላው፣ ናሱና ብሩ ወርቁም በአንድነት ተፈጨ :: በመከርም ጊዜ በአውድማ ላይ እንዳለ እብቅ ሆነ፣ ነፋስም ወሰደው፣ በታውም አልታወቀም፣ ምስሉንም የመታ ድንጋይ ታላቅ ተራራ ሆነ፣ምድርንም ፈጽሞ ሞላ»ይላል (ዳን.2:34-35)::*

ቀደም ባለው ምዕራፍ የናቡከደነጾር ሕልም ምስል በዚህ ምድር ላይ አምላክ የለሽ (አመጸኛ) የሆነውን የሰውን አገዛዝ እንደሚያመለክት ግልጽ

ተደርጓል። በእነዚህ ቀናት አራት በወርቅ፣ በብር፣ በነሐስና በብረት የተመሰሉ ታላላቅ የዓለም መንግስታት እንደሚነሱ ተነግሯል። በእነዚህ መንግስታት እግዚአብሔር ሳይሆን ማዕከሉን የያዘ ሰው ነበር። እነዚህ አራቱ መንግስታት በጊዜያቸው መጥተው ሄደዋል (አልፈዋል)። በመጨረሻዎቹ ቀናት እንደገና በፀረ ክርስቶስ መንግስት ይገሰጣሉ (*2ተሰ.2:3*)። በምድር ላይ የሰው የአመጸኝነት ጽዋ የተሞላ ይሆናል። ይህ መንግስትና ከእርሱ በፊት የነበሩት መንግስታት ጭምር በጌታ እየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት የሚፈረድባቸውና የሚጠፉ ይሆናሉ (ዳን. 2:24 ፣35)።



**የፀረ ክርስቶስ ፍርድ በዳንኤል አገላለፅ**

«ከዚህም በኋላ ዳንኤል ንጉሡ የባቢሎንን ጠቢባን ያጠፋ ዘንድ ወዳዘዘው ወደ አርዮክ ገባ በገባም ጊዜ፦ የባቢሎንን ጠቢባን አታጥፋ፤ ወደ ንጉሡ አስገባኝ እኔም ፍቺውን አሳያለሁ አለው (ዳን 2:24)»።

«ድንጋዩም እጅ ሳይነካው ከተራራ ተፈንቅሉ ብረቱንና ናሱን ሸክላውንና ብሩን ወርቁንም ሲፈጨው እንደየህ እንዲሁ ከዚህ በኋላ የሚሆነውን ታላቁ አምላክ ለንጉሡ አስታውቆታል፤ ሕልሙም እውነተኛ ፈቺውም የታመነ ነው» (ዳን.2:35)

ትንቢት የተነገረለት «ድንጋይ» በሰው የተመሰለውን ምስል እግሮች መታና ምስሉን ያጠፋዋል (ይደመስሰዋል)። ይህም ማለት በምድር ላይ የመጨረሻው መንግስት በሆነው በፀረ ክርስቶስ መንግስት በመጀመር አስቀድመው የነበሩትን ሌሎችን መንግስታት ጭምር መታሰቢያ እስከማይገኝላቸው ድረስ ክርስቶስ ፈጽሞ ይደመስሳቸዋል ማለት ነው። (ዳን. 2:35) በእነርሱ ቦታ «የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስና ለዘላለም ጸንቶ የሚኖር መንግስት ይመሠርታል» (*ዳን.2:44*)። ይህ የሚሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግስቱንና ግዛቱን ለመመስረት «በኃይልና በክብር» ሆኖ ሲመጣ ነው (*ማቴ.24:30*)። «የማንም እጅ» ሳይነካው (የሰው እጅ





ሳይረዳው የሚመጣው ድንጋይ) (ዳን2:39) ከእግዚአብሔር ልጅ ከኢየሱስ በስተቀር ሌላ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚመሰክረው ሁሉን ቻይ አምላክ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የሆነችውን አዲሷን ፍጥረት የመሠረተበት የማዕዘን ድንጋይ ነው። (*መዝ.(118):22፤ ኢሳ.28:16፤ ማቴ.21:42-44፤ ኤፌ.2:20፤ ሮሜ.9:33፣ 1ጴጥ.2:6*)።

በዚህ ዓለት (ድንጋይ) በክርስቶስ ኢየሱስ የማያምን ሁሉ በማዕዘኑ ድንጋይ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጨ ይሆናል። ያለ እግዚአብሔርና ያለ ክርስቶስ ኢየሱስ ይገዙ የነበሩት መንግስታት በሙሉ በተመሳሳይ ሁኔታ ይጠፋሉ። አራቱ የዓለም መንግስታት ባቢሎን፣ ሜዶንና ፋርስ፣ ግሪክና ሮም ከብዙ ጊዜ በፊት ወድቀዋል (ጠፍተዋል)። ነገር ግን የእነዚህ መንግስታት መንፈስና ሰይጣናዊ ኃይል በዓመጸኛው ሕዝብ ውስጥ ገብተው በመስራት የቀጠሉ ናቸው። በአሁኑ ቀናት የግሪክና የሮማውያን ባሕሎችና ቋንቋዎች ዘመናዊውን የአውሮፓን አህጉር ምን ያህል እንደሳቡት መገመት ይቻላል። በአንጻሩ የዘመኑ የአውሮፓ ሕዝብ ወንጌልንና የክርስቶስን ማዳን እንደሚቃወሙ ገምቱ። ይህም የሆነበት ምክንያት በአስመሳዩና በፀረ ክርስቶስ መንፈስ ተማርከው በመወሰዳቸው ነው። ይኸውም መንፈስ የአሁኗን የእስራኤልን መንግስት ከሚቃወሙት በስተ ጀርባ ሆኖ የሚያስተላልፈው ዜና መሠረት የሌለውና ሀሰት ነው። ወቅታዊው የሕብረተሰብ ሁኔታና ሀሳቦች እስራኤልን በመቃወም እየጨመሩ ናቸው። በመጨረሻዎቹ ቀናት የእግዚአብሔር የፍርድ ድንጋይ አመጸኛ የሆኑትን የሰው ዘር መንግስታት በሙሉ ይደመስሳቸውል። በፍጻሜም ዘላለማዊ መዋጀትን በቀራንዮ መስቀል ላይ የፈጸመው አዳኙ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ደህንነት በተቃወሙትና በምትኩ ፀረ ክርስቶስና መንግስቱን በመረጡት ሁሉ ላይ ፈራጅ ሆኖ ይገለጣል።

## 2. የፀረ ክርስቶስና የሀሰተኛው ነቢይ ፍርድ

በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጊዜ ፀረ ክርስቶስና ሀሰተኛውም ነቢይ የሚፈረድባቸው ይሆናል። ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ *«አውሬውም ተያዘ በእርሱም ፊት ተአምራትን እያደረገ የአውሬውን ምልክት የተቀበሉትን ለምስሉም የሰገዱትንም ያሳተ ሐሰተኛው ነቢይ ከእርሱ ጋር ተያዘ ሁለቱም በሕይወት ሳሉ በዲን ወደሚቃጠል ወደ እሳት ባሕር ተጣሉ» ይላል (ራዕ.19:20)።*

ከእግዚአብሔር ልጅ ከጌታ ኢየሱስ በቀር «ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔርን የብርቱ ቁጣውን ወይን መጥመቂያ» የሚረግጥ የለም (*ራዕ.19:15*)፡ አመጸኝነት በፀረ

ክርስቶስ ጽዋውን ከሞላ በኋላ ቅዱስና ትክክለኛ የሆነውን ፍርድ ይቀበላል:: ፀረ ክርስቶስ በሥጋ የተገለጠ ኃጢአት ነው:: ይህም ማለት በእርሱ የኃጢአትና የአመጸኛነት ጽዋ የሞላበት ነው ማለት ነው:: ስለዚህ ነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ያለውን የሰይጣንን አገዛዝ «በአፉ መንፈስ» በማጥፋት ወደ ፍፃሜ የሚያመጣው (2ተሰ.2:8)::

ሀሰተኛው ነቢይ ፀረ ክርስቶስ የተቀበለውን ስቃይ በተመሳሳይ ሁኔታ ይቀበላል:: እንደ ሃይማኖት መሪ የዓለም መሪ የሆነውን ፀረ ክርስቶስን በዓለም ሰዎች ፊት ክፍ በማድረግ አክብሮታል:: የዓለምን ሰዎች ለዚህ ዓለማዊ መሪና ለስዕሉ እንዲሰግዱ ከማሳቱም በላይ የሰይጣን ማህተም የሆነውን ምልክቱን በእጃቸውና በግንባራቸው እንዲቀበሉ ያስገድዳቸዋል:: ስለሆነም በፍጻሜው ፀረ ክርስቶስ የሚቀበለውን ፍርድ ይቀበላል:: «ሁለቱም በሕይወት ሳሉ በዲን ወደሚቃጠል የእሳት ባሕር» ይጣላሉ:: (ራዕ.19:20) ሁለቱም በሰይጣን ሥልጣን ስርተዋል:: (ራዕ.13:2-4) ሁለቱም አንድ ላይ ይፈረድባቸዋል:: ከሺህ ዓመት በኋላ ሰይጣን ወደዚያ ወደ እሳቱ ባሕር ይከተላቸዋል:: ሰይጣን የተፈረደበት ስለሆነ ፀረ ክርስቶስና ሀሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ይጣላል:: (ራዕ.20:10)

ፀረ ክርስቶስና መንግስቱን በተመለከተ በእነዚህ አስተያየቶች ማጠቃለያ ላይ የሚከተለው ቻርት በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና በፀረ ክርስቶስ መካከል ያለው ንጽጽር የሚያሳይ ይሆናል:: ይህ ንጽጽር በእርግጥ የሚመጣው ፀረ ክርስቶስ ፣ የክርስቶስን ቦታ ለመያዝና ለመወከል የሚጥር አስመሳይ ክርስቶስ እንደሆነ ያሳያል::

| [illegible] | ፀረ ክርስቶስ |
|---|---|
| (ማር.1:1) | (1ዮሐ.2:22) |
| 1. ኢየሱስ ክርስቶስ ስልጣን ሁሉ ከሰማይ አባቱ ተሰጥቶታል:: (ዮሐ.3:35) | 1 ሥልጣንና ኃይል ሁሉ ከሰይጣን አለው:: (ራዕ.13:2) |
| 2. ኢየሱስ ክርስቶስ ከአባቱ፣ከክብር፣ ከላይ መጥቷል:: (ዮሐ.3:31) | 2. ፀረ ክርስቶስ ከታች ከጥልቁ ከሰይጣን ይመጣል:: (ራዕ.17:8) |
| 3. ኢየሱስ ክርስቶስ ከአባቱ በመንፈስ ቅዱስ ተወልዷል:: (ሉቃ.1:35) | 3. ፀረ ክርስቶስ በሰይጣናዊ ኃይል ይመጣል:: |
| 4. ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተገለጠ እምላክና ነው:: (1ጢሞ.3:16) | 4. ለሥጋ የተገለጠ ሰይጣናዊ ነው:: |
| 5. ኢየሱስ ክርስቶስ አባቱን ብቻ ያከብራል:: (ዮሐ.17:4) | 5. ፀረ ክርስቶስ ሰይጣንን ያከብራል ለሰይጣንም ይኖራል:: (ራዕ.13:1-10) |
| 6. ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ የአባቱን ፈቃድ ይፈጽማል:: (ዮሐ.17:4) | 6. ፀረ ክርስቶስ አጥፊ የሆነውን የሰይጣንን ሥራ ይፈጽማል:: (ራዕ.13:1-10) |
| 7. ኢየሱስ ክርስቶስ ለአባቱ ክብር መስጠት ብዙ | 7. ፀረ ክርስቶስ ለሰይጣን ክብርን |






| | |
|---|---|
| ተዓምራትን በምድር ላይ ለደርጓል:: (ዮሐ.9:4) | በመስጠት ብዙ ሐሰተኛ ምልክቶችን ያደርጋል (2ተሰ.2:10):: |
| 8. ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ወደ ሰማያዊ አባቱ ዕውነት ይመራል (ዮሐ.14:6):: | 8. ፀረ ክርስቶስ ሰዎችን ወደ አመጽ ይመራል:: (2ተሰ.2:10) |
| 9. ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሰዎችን ይዋጃል ያድናል (ማር.10:45) | 9. ፀረ ክርስቶስ ሰዎችን ወደ ጥፋት ይለባል:: (2ተሰ.2:10) |
| 10. ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን አዋረደ፣ የባርያን መልክ ያዘ:: (ፊል.2:5-8) | 10. ፀረ ክርስቶስ ራሱን እግዚአብሔርን ከሚያመልኩት በላይ ከፍ ከፍ ያደርጋል (2ተሰ.2:4) |
| 11. ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ ሊባርክ ይመጣል (ሉቃ.19:10):: | 11. ፀረ ክርስቶስ መነሳት የሚያምኑትንም ለማያምኑትም ፍርድ ነው:: (2ተሰ.2:4) |
| 12. ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች ሰማያዊ አባቱን እንዲያመልኩ ያስተምራል:: (ዮሐ.4:24) | 12. ፀረ ክርስቶስ ሰዎችን ለሰይጣን እንዲሰግዱ ያስገድዳል:: (ራዕ.13:4) |
| 13.ኢየሱስ ክርስቶስ ትሁት የሆነና አባቱን የሚያከብር ነው::(ኢሳ.42:2፣ ዮሐ.8:49) | 13 ፀረ ክርስቶስ ታላቅ ነገር የሚናገርና ትዕቢተኛ እግዚአብሔርን የሚሳደብ ነው::(ራዕይ.13:5-6) |
| 14. ኢየሱስ ክርስቶስ የአባቱ ምሳሌ ነው:: (ዕብ.1:3፣ ቆላ.1:15፣ ዮሐ.14:9) | 14. ፀረ ክርስቶስ የሰይጣን ምሳሌ ነው:: (ራዕ.12:3፤ 13:1-2) |
| 15. ኢየሱስ ፍጹም አምላክና ኃጢአት የሌለበት ፍጹም ሰው ነው:: (ሮሜ.9:5፣ 2ቆሮ.5:21) | 15. ፀረ ክርስቶስ ፍጹም ሰይጣንና የአመጽ ሰው ነው:: (2ተሰ.2:3) |
| 16. ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማያዊ አባቱ ስም መጣ:: (ዮሐ. 5:43) | 16. ፀረ ክርስቶስ በራሱ ስም ይመጣል:: (ዮሐ.5:43) |
| 17. ኢየሱስ ክርስቶስ የሰማያዊ አባቱ ባሕርይ አለው:: ዕብ.1:3 | 17. ፀረ ክርስቶስ ሰይጣናዊ ባሕርይ አለው:: 2ተሰ.2:3 |
| 18. ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠ እግዚአብሔር ፍቅር ነው:: (1ዮሐ.4:9) | 18. ፀረ ክርስቶስ እግዚአብሔርን የሚቃወም፣ የአመፅ ልጅ የእግዚአብሔር ጠላትና የአመፅ ሰው ነው(2ተሰ.2:3-8):: |
| 19. ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ህግ ፈጻሚል::(ማቴ.5:17፣ሮሜ.10:4) | 19. ፀረ ክርስቶስ በባሕርዩ አመጸኛ ነው (2ተሰ.2:3-9፤ዳን.7:25) |
| 20.ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን የመምሰል ሚስጥር ነው:: (1ጢሞ.3:16፤ ማቴ.11:27) | 20. ፀረ ክርስቶስ የዓመፅ ሚስጢር ነው:: (2ተሰ. 2:7) |
| 21. ኢየሱስ ክርስቶስ ራስን ዝቅ የማድረግን መንገድ ተከትሏል (ፊል.2:5-8) | 21. ፀረ ክርስቶስ ራስን ከፍ የማድረግ መንገድ ይከተላል:: (ራዕ.17:8) |
| 22. ኢየሱስ ክርስቶስ በትህትናው በአባቱ ከፍ ከፍ ተደርጓል:: (ፊል.2:9-11) | 22. ፀረ ክርስቶስ ጥልቅ ወደ ሆነው ጥፋት ይጣላል::(ራዕ.17:8፣19:20-21) |
| 23. ኢየሱስ በክብር የተነሳና ለአንዴና ለመጨረሻ ሞትን ድል ይደረገ ነው (1ቆሮ.15:20፤ ዕብ.2.14):: | 23. ፀረ ክርስቶስ ትንሳኤን ቅጂ ያደርጋል (የሞቱ ቁስል መፈወስ) (ራዕ. 13:3-14):: |
| 24. ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከብሯል (ይከብራል) (ዮሐ.16:14) | 24. ፀረ ክርስቶስ በሀሰተኛው ነቢይ ይከብራል:: (ራዕ.13.11-18) |
| 25. ኢየሱስ ክርስቶስ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ በሰማይና በምድ ይገዛል፣ ያስተዳድራል:: (ራዕ.11:15፣22:1-5) | 25.ፀረክርስቶስ የሚፈረድበት፣የሚጠፋና ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ የሚኮነን ነው::(ራዕ.19:20፣20:10) |

# የጎግና ማጎግ

ወደ ጌታ ኢየሱስ ምጽአት እየቀረብን ስንሄድ በመጨረሻዎቹ ቀናት ስለሚሆነው ነገር፣ በብሉይ ኪዳን የተነገረ፣ ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ ከቶ ያልተፈጸመ ሌላ ታሪካዊ ሁኔታ እንመለከታለን:: የነቢዩ *ሕዝ. 38 እና 39* በመጨረሻዎቹ ቀናት ስለሚካሄድ ታላቅ ውጊያ ይናገራሉ *(ሕዝ.38:1-16)*:: እጅግ ታላቅ የሆነ ሠራዊት ከእስራኤል በስተ ሰሜን ያሉት በመሰባሰብ የእስራኤልን ሕዝብ ይከብባሉ *(ሕዝ.38:15-16)*:: ይህ ቅድስቲቱን ምድር የሚከብበውን ሠራዊት የሚመራው ኃይል «በማጎግ ምድር የሚኖር ጎግ» በመባል ተገልጿል:: *(ሕዝ.38:2)*

ይህን ለመጀመር «በማጎግ ምድር የሚኖር ጎግና የፀረ ክርስቶስ መንግስት» ሁለቱ የተለያዩ በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገሩ ትንቢቶች መሆናቸውንና አንዱ ከሌላው የተለዩ መሆኑን ግልጽ ልናደርግ ይገባናል:: በመጨረሻዎቹ ቀናት የሚነሱ ሁለት የተለያዩ ኃይላት ናቸው:: በማዳን ታሪክ ቻርት ላይ የማጎግ ጎግ ፀረ ክርስቶስ ከመነሳቱ በፊት የሚነሳና አሰቃቂ አገዛዙን የሚጀምር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል::

1. ነቢዩ ሕዝቅኤል የማጎግን ጎግ በአምስት የተለያዩ ስሞች ይጠራቸዋል:: ነርሱም ሮሽ፣ ሞሳህ፣ ቶቤል፣ ጎግና ማጎግ ናቸው:: *(ሕዝ.38:1-3)* እነዚህ ስሞች ከእስራኤል በስተሰሜን በኩል ያሉትን የአሕዛብን ግዛቶች ያመለክታሉ:: *(ሕዝ.38:15)*






የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ማብራሪያ

እንደ ፍላቪዩስ ጆሰፉስ የአይሁድ የታሪክ ሰው ገለጻ የማጎግ ትውልዶች ከእስራኤል በስተሰሜን በጥቁር ባሕር አካባቢ የሚኖሩት ናቸው:: (በዘፍ.10:2) የኖህ ልጅ የያፌት ልጆች ማጎግ፣ ቶቤል፣ ሞሳህን ጎሜር ተብለው እንደተጠሩ ተጽፎ ይገኛል:: የስላቪክ ሕዝቦች የማጎግ ቶቤልና የምሳህ ትውልዶች ናቸው:: የጀርመን ሕዝብ ግን የጎሜር ትውልድ ናቸው:: ዛሬ እነዚህ ሕዝቦች ሁሉ ከኤሌብና ከዳንዮብ ወንዞች በስተሰሜንና ምስራቅ ባሉት ሀገሮች ውስጥ ይኖራሉ:: ያም ማለት በአውሮፓ በስተ ምስራቅና ከፀረ ክርስቶስ መንግስት ድንበር ውጪ ናቸው:: ነገር ግን በመጨረሻው ጊዜ የሚነሱትን ሁለት የተለያዩ ታላላቅ ኃይላትን የሚመሠርቱ ናቸው::

2. የሮሽ፣ የምሳህ፣ የቶቤል፣ የጎግና የማጎግ ስሞች ፍቺ ፀረ ክርስቶስ ከመነሳቱ በፊት የሚነሳ ሌላ ኃይል እንደሚነሳ የሚገልጹ እውነታ ናቸው:: እንደ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 38 እና 39 መሠረት ይህ ኃይል በእስራኤል ምድር ውስጥ የሚደመሰስ ነው::

በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የሩሲያ ደቡባዊ መንግሥት ከዋናው ከተማ ከኪቭ ጋር ሮሽ ተብሎ ይጠራ ነበር:: ትርጉሙም «ዋና አለቃ፣ መጀመሪያ፣ አንደኛ ማለት ነው» (በአዲሱ ዓለም አቀፍ ትርጉም ሐህሞ ግርጌ ሮሽ ዋና አለቃ በመባል ተተርጉሞ ይገኛል:: (ሕዝ. 38:2-3) ሮሽ የሚለው ስም በኋላ ሩሲን እንደተባለና




# የጎግና ማጎግ

ወደ ጌታ ኢየሱስ ምጽአት እየቀረብን ስንሄድ በመጨረሻዎቹ ቀናት ስለሚሆነው ነገር፣ በብሉይ ኪዳን የተነገረ፣ ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ ከቶ ያልተፈጸመ ሌላ ታሪካዊ ሁኔታ እንመለከታለን:: የነቢዩ ሕዝ. 38 እና 39 በመጨረሻዎቹ ቀናት ስለሚከሄድ ታላቅ ውጊያ ይናገራሉ (ሕዝ.38:1-16):: እጅግ ታላቅ የሆነ ሠራዊት ከእስራኤል በስተ ሰሜን ያሉት በመሰባሰብ የእስራኤልን ሕዝብ ይከብባሉ (ሕዝ.38:15፥16):: ይህ ቅድስቲቱን ምድር የሚከብበውን ሠራዊት የሚመራው ኃይል «በማጎግ ምድር የሚኖር ጎግ» በመባል ተገልጿል:: (ሕዝ.38:2)

ይህን ለመጀመር «በማጎግ ምድር የሚኖር ጎግና የፀረ ክርስቶስ መንግስት» ሁለቱ የተለያዩ በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገሩ ትንቢቶች መሆናቸውንና አንዱ ከሌላው የተለዩ መሆኑን ግልጽ ልናደርግ ይገባናል:: በመጨረሻዎቹ ቀናት የሚነሱ ሁለት የተለያዩ ኃይላት ናቸው:: በማዳን ታሪክ ቻርት ላይ የማጎግ ጎግ ዐረ ክርስቶስ ከመነሳቱ በፊት የሚነሳና አስቃቂ አገዛዙን የሚጀምር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል::

1. ነቢዩ ሕዝቅኤል የማጎግን ጎግ በአምስት የተለያዩ ስሞች ይጠራቸዋል:: እነርሱም ሮሽ፣ ሞሳህ፣ ቶቤል፣ ጎግና ማጎግ ናቸው:: (ሕዝ.38:1-3) እነዚህ ስሞች ከእስራኤል በስተሰሜን በኩል ያሉትን የአሕዛብን ግዛቶች ያመለክታሉ:: (ሕዝ.38:15)








እንደ ፍላቪዮስ ጆሴፉስ የአይሁድ የታሪክ ሰው ገለጻ የማጎግ ትውልዶች ከእስራኤል በስተሰሜን በጥቁር ባሕር አካባቢ የሚኖሩት ናቸው:: (በዘፍ.10:2) የኖህ ልጅ የያፌት ልጆች ማጎግ፣ ቶቤል፣ ሞሳህን ጎሜር ተብለው እንደተጠሩ ተጽፎ ይገኛል:: የስላቪክ ሕዝቦች የማጎግ ቶቤልና የምሳህ ትውልዶች ናቸው:: የጀርመን ሕዝብ ግን የጎሜር ትውልድ ናቸው:: ዛሬ እነዚህ ሕዝቦች ሁሉ ከኤሲብና ከዳንዩብ ወንዞች በስተሰሜንና ምስራቅ ባሉት ሀገሮች ውስጥ ይኖራሉ:: ያም ማለት በአውሮፓ በስተ ምስራቅና ከፀረ ክርስቶስ መንግስት ድንበር ውጪ ናቸው:: ነገር ግን በመጨረሻው ጊዜ የሚነሱትን ሁለት የተለያዩ ታላላቅ ኃይላትን የሚመሠርቱ ናቸው::

2. የሮሽ፣ የምሳህ፣ የቶቤል፣ የጎግና የማጎግ ስሞች ፍቺ ፀረ ክርስቶስ ከመነሳቱ በፊት የሚነሳ ሌላ ኃይል እንደሚነሳ የሚገልጹ እውነታ ናቸው:: እንደ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 38 እና 39 መሠረት ይህ ኃይል በእስራኤል ምድር ውስጥ የሚደመሰስ ነው::

በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የሩሲያ ደቡባዊ መንግሥት ከዋናው ከተማ ከኪቭ ጋር ሮሽ ተብሎ ይጠራ ነበር:: ትርጉሙም «ዋና አለቃ፣ መጀመሪያ፣ አንደኛ ማለት ነው» (በአዲሱ ዓለም አቀፍ ትርጉም ሐህሞ ግርጌ ሮሽ ዋና አለቃ በመባል ተተርጉሞ ይገኛል:: (ሕዝ. 38:2-3) ሮሽ የሚለው ስም በኋላ ሩሲን እንደተባለና



ከዚያም ሩሲያ ተብሎ እንደተሰወጠ ይገመታል:: የምሳህ ትርጓሜ ደግሞ ሀብት መውረስ (መበዝበዝ፣ መሻት) ማለት ሲሆን መስኮብ የሚለው ስም ከዚህ የተወረሰ እንደሆነ ይታመናል:: ቶቤል ማለት «የጦር መሳሪያ ሠሪ» ማለት ነው:: ከእርሱ ቶብልሲክ እንደ ወጣ ይገመታል:: በአሁኑ ጊዜ በዓለም ከፍተኛ የጦር ከምችት ያለው በምስራቅ እውሮፓ ነው:: ከጎግ (ከፍተኛ፣ ዋና) ካህን፣ ካውክና ካውካሱስ የሚሉት ስሞች ወጥቷል:: እንደ አይሁዳዊው የታሪክ ሰው ፍላቪዩስ ጆሴፉስ አባባል የያፌት ዝርያዎች ከካውካሱስ በስተደቡብ እንደ ሰፈሩ ይታወቃል:: ማጎግ የሚለው ስም ትርጉም «መስፋት» ወይም «የቤተ ሰብ ፈጥኖ መብዛት» ማለት ነው:: ከዚህም የተነሳ የምስራቅ አውሮፓ ሕዝቦች መብዛትን ልናይ እንችላለን:: እምስቱ ሮሽ፣ ሞሳህ፣ ቶቤል፣ ጎግና ማጎግ የተባበረውን ሩሲያን እንደሚመሰርቱ እንናገራለን:: በዚህም ጎግ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወት ይሆናል:: ሩሲያ ከእስራኤል በስተሰሜን ትገኛለች:: ኢየሩሳሌምና ሞስኮ በአንድ ሎንግትዩድ (የምድር የሀሳብ መስመር) ላይ ይገኛሉ::

3. የማጎግ ጎግ ከፍተኛ የእስራኤል ጠላቶች ከሆኑት ከአረቦች መንግስታት ጋር ሕብረት ይመሠርታል:: እንደ (*ሕዝ.38:5-6*) ወደፊት በቅድስቲቱ ምድር ላይ በሚደረገው ወረራ ብዙ የአረብ መንግስታት እንደሚተባበሩ ለማየት ይቻላል:: ፋርሶች ሙሮች፣ ሊቢያውያን፣ ጎሜርና ቶጋርማ ይሰለፋሉ:: ሙሮች ኢትዮጵያን ጎሜር ጀርመንና ቶጋርማ ቱርክን ይወክላሉ:: ሳባ (አረቢያ) ዲዳንና ተርሴስ ተካፋይ እንደሚሆኑ (በሕዝ.38:13) ተጠቅሰዋል:: ወደ እነዚህ ነገሥታት ስንመለከት በሕዝ.38 መሠረት በሰሜንና በደቡብ ማጎግ ጎግና የአረቦች መንግስታት ቅንጅትን ልንመለከት እንችላለን:: በየዕለቱ የሚወጡት ጋዜጦች ለዓመታት የሆነው የዚህን ዕድገት ሪፖርት ያስተጋባሉ::

4. የማጎግ ጎግና የክርስቶስ ተቃዋሚ መንግሥት የተለያዩ ኃይላት መሆናቸውን ለማወቅ የሚያስችለው እውነት በሁለቱም ላይ የሚካሔደው የእግዚአብሔር ፍርዶች የተለያዩ መሆናቸው ነው::

*(በሕዝ.38:18-23)* እንደተጻፈው የማጎግ ጎግ ወዲያውኑ በእስራኤል ላይ ወረራ እንዳካሄደ በእግዚአብሔር ተፈርዶበት በእስራኤል ምድር ውስጥ ይደመሰሳል:: በእስራኤል ጠላት በሆነው ሠራዊት ላይ ተፈጥሮአዊ የሆኑ መቅሰፍቶች ማለት የምድር፣ የባሕር፣ የአየር መናወጥ፣ የበረዶ፣ ዝናም፣ እሳትና እጥፊ የሆነ ዝናብ ይወርድበታል::





እነዚህ አስቃቂ መቅሰፍቶች በራሱ በሠራዊቱ መካከል ችግር ይፈጥራል:: በድንገት በሠራዊቱ መካከል ተወዳዳሪ የሌለው መበጣበጥን ይፈጥራል:: ይህም እርስ በእርሳቸው ይገዳደላሉ (*ሕዝ.38:21*):: ሠራዊቱ ከፍተኛ የደም መፋሰስን በመካከላቸው ያደርጋሉ (*ሕዝ.38:22*): ሠራዊቶችን የሚገድልና የእጅግ ከፍተኛ ወታደሮችን ጥፋት የሚያመጣ ታለቅ መቅሰፍት በድንገት ይገስጣል:: በማጎግ ጎግ ላይ የሚወርደው ፍርድ ተፈጥሮአዊ መቅሰፍቶች ብቻ እንደሆኑ ግልጽ ነው:: ነገር ግን በክርስቶስ ተቃዋሚ ላይ የሚወርደው ፍርድ «... ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው» በሚል ቃል ተገልጿል (*2ተሰ.2:8*):: ይህ ጌታ «በኃይልና በታላቅ ክብር» ሲገለጥ የሚሆን የተለየ ፍርድ ነው (*ማቴ.24:30*):: ይህ የክርስቶስ ኢየሱስ ተቃዋሚ ከመገለጡ በፊት የማጎግ ጎግን ከሚያጠፋው የተለየ ነው::

5. ፍርድ የሚካሔድባቸው ስፍራዎች እንኳን አንዱ ከሌላው የተለየ ነው:: የማጎግ ጎግ መቃብር ሐሞንጎግ ተብሎ ይጠራል (የሐሞንጎግ ሸለቆ ማለት ነው):: ይህም የሚገኘው ከሙት ባሕር በስተምስራቅ በኩል ነው (ሕዝ.39:11-16):: በሌላ በኩል ፀረ ክርስቶስ የሚደመሰሰው ከእስራኤል በስተሰሜን በኩል ከ250 ኪሎ ሜትር ርቀት በላይ በሚገኘው በአርማጌዶን ላይ ነው (*ራዕ.16:12-16፣ 19:11-21*)::

6. ከዚህ በላይ ደግሞ የማጎግ ጎግ ወደ እስራኤል የሚዘምተው ለመማረክና ለመበዝበዝ *(ሕዝ.38:12)* ሲሆን ፀረ ክርስቶስ ግን ዓለምን በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግና የሰው ዘር ሁሉ እንዲሰግዱለት በመመኘት ነው:: *(ራዕ.13:3-8)*

7. በመጨረሻም የሚመጣው ወረራና በእርሱ ላይ የሚወርደው ፍርድ እኛ ባለንበት ጊዜ ሲሆን ይችላል:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል እስራኤል «ያለ ቅጥርና ያለ መወርወሪያ ያለ መዝጊያ» የሆነች ሀገር ትሆናለች (ሕዝ.38:11)፣ (*ዘካ.2:8*):: ዛሬ እስራኤል በእንደዚህ ባለ ሁኔታ እንዳለች እናገኛለን:: ከ1918 ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ አንድም የእስራኤል ከተሞች ቅጥር የላቸውም:: ሕዝቡም የሚኖረው ባልተመሸጉ ከተማዎችና ሸለቆዎች ነው (ኪቡቲዝምና ምሻቪም) ::

ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው በመጨረሻዎቹ ቀናት የክርስቶስ ተቃዋሚ ከመምጣቱ በፊት የማጎግ ጎግ ባጠቃላይ አመጸኛ፣ ኃይለኛና በፖለቲካም ነፃ የሆነ ኃይል ይሆናል:: በእስራኤል ተራሮች ላይ በእግዚአብሔር ይፈረድበታል (*ሕዝ.39:4*:) ከዚያ በኋላ ፀረ ክርስቶስ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት እስኪፈረድበት ድረስ ከፍ ወዳለው ሕብረቱ ይደርሳል::

የሥነ መለኮት ሰው ኮንራድ ቡስሚር (1874-1944) በ1931 ዓ.ም የትንቢት ቃል ስለ ሩሲያ ምን ይላል? (what does The Prophetic word say about Russia?) የሚል መጽሐፍ ጻፈ:: በመጽሐፉ ውስጥ ሰሮሽ፣ ለምሳህና ለቶቤል ዋነኛ አለቃ የሚሆናቸው ጎግ ሌላ ሳይሆን ሩሲያ እንደሆነ ተጠቅሷል:: የሰጠውን ግምት ተቀባይነት ባላቸው ሀሳቦች በመደገፍ ጽፏል:: እነርሱንም በዚህ ፍሬ ነገር ላይ ሰማከል እንፈልጋለን:: እመጸኝነት ወደ ፍርድ ይመራል በሚለው ርዕስ ስር የሚከተለውን ጽፏል::

በሕዝቅኤል ራዕይ ውስጥ ሰሮሽ፣ ለሞሳህና ለቶቤል ዋና አለቃ ስለሚሆናቸው ጎግ ምን መደምደሚያን እናገኛለን? ወደሚለው ጥያቄ እንመለስ:: ይህን ጥያቄ በአእምሮአችን ይዘን የሕዝቅኤልን ትንቢት ባጠቃላይ ብንመለከት፣ ትንቢቱ በመጨረሻዎቹ ቀናት ስላለው ስለ ጎግ ታሪክ ሆኖ እናገኘዋለን:: በመጨረሻዎቹ ቀናት የእግዚአብሔር ተቃራኒ የሆነ ኃይለኛ መሪ ይገለጣል:: ጎግ ለእግዚአብሔር ፍርድ የተዘጋጀ (የበሰለ) ኃይል እንደሆነ የታወቀ ነው:: በሬ በእራዱ ወደ ሚታረድበት እንደሚነዳ ሁሉ እግዚአብሔርም (ይሆዋ) በጎግ አፍንጫ ውስጥ ስናግ በማስገባት(*ሕዝ.38:4*) ወደ ፍርድ ይስበዋል:: (*ሕዝ.39:2*) ነገር ግን ስለ ጎግ ቀደም ያለ ታሪክ ባናገኝም ጎግ ሰምንና ስለ ምን ወደ እግዚአብሔር ፍርድ ስር እንደሚመጣ ለማወቅ እንፈልጋለን ነቢዩ አልጠቀሰውም:: ሕዝብን ስድ የለቀቀ ሰው ያለ ምክንያት በአንድ ምሽት በፍርድ ስር አይሆንም:: ቀደም ሲል በአመጸኝነት የኖሩበት ረጅም ታሪካዊ ሂደት ሊኖር ይችላል:: እንደዚህ ያለ ዕድገት በሩሲያ ታሪክ ውስጥ እናገኛለን:: ስለዚህ ውጤቱ ሩሲያ የዚህን ዓይነት ታሪክ ልታሳይ ይሆን? ብለን ራሣችንንም ብንጠይቅ የኛ ሃሳብ (መልስ) አዎን ይሆናል::

ቀደም ብለን ከማንኛዎቹም ከአውሮፓ ሕዝቦች የሩሲያ ታሪክ በጥላቻና በፍርሀት የተሞላ እንደሆነ ጠቅሰናል:: ይህ ባይሆን እንኳን ሩሲያ ሁልጊዜ ክርስቲያኖችን የምታሳድድ የእግዚአብሔር ጠላት ነበረች:: ቦልሺቪኮች የአሁኑን የሩሲያን ባሕርይ ሰመመስረት መጀመሪያዎቹ አይደሉም:: በቄሳሮች ዘመን የግሪክ ኦርቶዶክሶች ነበሩ:: በብሔራዊ መዝሙር ቄሳር «የኦርቶዶክስ ቄሳር» እንደሆነ ተደርጎ ተከብሯል:: ስለሆነም ክርስትና በሩሲያ በግልጽ የታወቀ ነበር:: በመላ ሩሲያ ታላላቅ ገዳማት፣ ግዙፍ የሆኑ ካቴድራሎች ከፍተኛ የአምልኮት ስርአቶችና የክርስትና በዓላት፣ ልምዶች ወጎችና የቅዱሳን ምስሎች ይገኛሉ:: ከ40 ዓመታት በፊት በቅዱስ ሲኖዶስ ላይ የበላይ ጠባቂ የሆነው ፓቢዶኖሲው ስለ ምዕራብ ሀገሮች





እመጸኝነት ተናግሯል:: ነገር ግን ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች እምነታቸውን በነፃነት ይለማመዱ ነበርን? የባብቲስት እድላቸው እንዴት ነበር? የፒተርስበርግ ከፍተኛ ባለ ሥልጣናት ወደ ጌታ ኢየሱስ ሲመለሱ እድላቸው እንዴት ነበር? የኮሉኔልን ፓስቻኮውና የተከበረውን ኮርፍና የሌሎቹን ታሪክ እንረሳው ይሆን? ዳግማዊት ካቴሪን ሜኖናይቶችን ወደ ሩሲያ ተቀብላ ማስገባቷ እውነት ነው:: ነገር ግን ይህን ያደረገችው ስለ እምነት ነው ወይስ ጠንካራ ገበሬዎችን ስለ ፈለገች ነው? በዓለም ጦርነት ጊዜ የተገባላቸው ነጻነት ሜኖናይቶች ተፈቅዶላቸዋልን? ቀዳማዊ እስክንድር መጽሐፍ ቅዱስ በሩሲያ እንዲሰራጭ ፈቅዷል:: ቢሆንም በመጀመሪያ የሩሲያ ኦርቶዶክስ መፍቀድ ነበረባት:: ይህ የሚያስገርም ነገር አይደለምን? ስለ ሚስጢራዊው ቄሳር እስክንድር በመንፈሱ ባይታደስ በማዳም ዲ ክሩድንር የተሳበው የሕይወቱና የሞቱ ሚስጢር እስከ አሁን ድረስ ያልታወቀ ነው:: ለቅዱስ አልያንስ መሠረት ከሌለው ሀሳባቸውና ሕልማቸው የተሳበ ነበር:: በሩሲያ እውነተኛ ክርስትና ተቀባይነት እንዳልነበረው ሁሉ ተቀባይነት አልነበረውም:: ከእርሱ ቀጥሎ የነበሩት ወራሾቹ በመንግስቶቻቸው ዘመን ክርስቲያኖችን አሳድደዋል፣ አስረዋል ወደ ሳይቤርያም ወስደዋል:: ምንም እንኳን ዛሬ በቦልሺቪያውያን በእግዚአብሔር ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ቢፈጠርም አዲስ ነገር አይደለም:: አንዳንድ ሰዎች አሁን በሩሲያ ያለው እግዚአብሔርን የመጥላት ምክንያት በጀርመን የነበረው የሊበራሊዝም ውጤት ነው ብለው ጀርመንን ምክንያት ቢያደርጉም ታላቅ የድፍረት ሀሳብ ነው:: በእርግጥ ጀርመንም የክርስትና ተቃዋሚ ለመሆኗ ድርሻ ነበራት ዛሬም አለ:: ይህ በሊበራሊዝምና በሶሺያሊዝም ብቻ ሳይሆን በኦርቶዶክስና በመንግስቱም አብያተ ክርስቲያናት ያለ ነው:: በሩሲያ በክርስቲያኖች ላይ ያለው ጥላቻ በጀርመን የመነጨ አይደለም :: መሠረቱ በራሷ በሩሲያ የሆነና የተወለደ ነው:: የቄሳር ወታደሮችንና ፖሊሶችን በሚደግፉ የሩሲያ ቤተ ክርስቲያናት ኃይላቸውን ይጠቀሙ (ይለማመዱ) ነበር:: ዘሬ ኃይሏ በሶቪየቶች ላይ ነው:: ከመጀመሪያው ጋር ሲመዛዘን ዛሬ የበለጠ ሰይጣናዊ ሆናለች:: የኦርቶዶክስ ካባዋን ጥላለች:: ነገር ግን የጎግ መንፈስና ባሕርይ ከጥንት ጀምሮ በሩሲያ እንደነበር ዛሬም አለ:: ዛሬ ያለ ክርስትና ማስክ ትታያለች:: *በሕዝ.38* እና *39* እንደተጻፈው ወደ መጨረሻ ጥፋቷ እየቀረበች ነው:: ይህን ብንልም እውነተኛ አምልኮና መልካም ሥራ ከሩሲያና ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በጭራሽ የጠፉ ነበር ብለን እንክድም:: ከሰዎቻቸው መካከል ጥቂቶቹ መልካም አምላካዊ ባሕርይ ያላቸው አሉ:: በዚህም አንድ ቀን በታላቁ በእግዚአብሔር መንጋ

ውስጥ ብዙ ሩሲያኖች ይገኛሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ነገር ግን ይህ የሩሲያን መንግስት፣ ቤተ ክርስቲያንና የማጎግን ምድር ጎግን አመጸኛ ባሕርይ አይለውጠውም፡፡ አስቀድሞ በሃይማኖት ሽፋን ስር የነበረው ባሕርዩ ዛሬ የበለጠ ግልጽ የሆነና የሚታይ ሆኗል፡፡ የማጎግ ጎግ ለምን ወደ እስራኤል ምድር ለምርኮና ለብዝበዛ እንደሚመጣ ባለው ዋና ምኞት ላይ በተመለከተ *(ሕዝ.38:12)* ቡሶሚር የሚያስደንቅ አመለካከት ስለ ሩሲያ አድርጓል፡፡ «የጎግ ዓላማዎች፣ ብዝበዛና ምርኮ» በሚለው ርዕስ ስር የሚከተለውን ጽፏል፡፡ ነቢዩ ሀሳባችንን የሚስቡ ብዙ የጎግን ባህርያት ይገልጻል፡፡ ከአላማዎቹ አንዱ ለራዊቱን ለመቆጣጠር ያለው ግፊት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ስለ ብዝበዛ ያለው ምኞትና ስግብግብነት ነው፡፡ ጎግ ሚለው ስም ትርጓሜው «ከፍ የተደረገው፣ መሪ፣ ገገርና ኃይል የተሞላ» ማለት ነው፡፡ እንዲህ ያለውን በትዕቢት የተሞላ የምናለብኝ ድንፋታን እንደ ሩሲያ ያስተጋባ በዓለም ላይ ሌላ መንግሥት አለን? ምንም እንኳን ዳንኤል ሌሎቹን መንግስታት ለአደን እንደተጠሙ አራዊቶች ቢመስላቸውም፣ ከሩሲያ በስተቀር የሕዝብን ብዛት እንደ ዳምጠ (መንገድ የሚደለድል መኪና) መጠቀሚያ ያደረገ መንግስት የለም፡፡ ሩሲያ ብዙ ሚሊዮን ሕዝቦች ያላት ምድር ናት፡፡ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ብዙ ሠራዊት ያስለፈች እርሷ ነበረች፡፡ በ1914 ዓ.ም የጀርመን ጠላቶች የዚህ ሠራዊት ብዛት መላ ጀርመንን ይደመስሳል በሚል ሀሳብ ተወስደው ነበር፡፡ ዛሬም ቢሆን ሶቪየቶች በህዝብ ብዛትና በዓለም አመጽ ዓለምን ለመቆጣጠር ይመኛሉ፡፡ *በሕዝ.38* በሌላ መልኩ ይገለጽ እንጂ የጎግም መንፈስ ተመሳሳይ ነው፡፡ *(በሕዝ.38:4-6)* ያለው ክፍል በ1914 ብዛት ያለው ከፍተኛ ሠራዊት የፕሩሲያን ምስራቃዊ ድንበርን መውረሩን (መደምሰሱን) ያስታውሰናል? በማሱረን የሩሲያ ሠራዊቶች የተቀበሩባቸው መቃብሮች በሙት ባሕር በስተ ምስራቅ ያለው «የሐምንጎግን» ሸለቆ እያስታውሱንምን? *(ሕዝ.39:16)*

ሌሎች የስግብግብነትና የስስት ባሕርያት በሩሲያ የሚታዩ ናቸው፡፡ *(በሕዝ.38:12-14)* ይህ ለሀብት ያለው መሻት ጎግን የሚገፋፋው ግፊት እንደሆነ እናነባለን፡፡ ይህ የሩሲያ ደካማ ጎን መሆኑን ሁልጊዜ መጥቀስ የሚያስፈልገን አይደለም፡፡ ጎለኝነት፣ በወንጀል አታልሎ ገንዘብ መውሰድ፣ ሌብነት ለሶቪያል ክፍሎች የየለቱ ትዕዛዝ ነበር፡፡ በከፍተኛ ደረጃ የነበሩት ከድሀው ወይም ከመንግስቱ በበዘበዙት ይደሰቱ ነበር፡፡ ፈረንሳይ የሶቪየትን ወዳጅነት ለማግኘት በ1893 ዓ.ም. የላከችው በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ወደ መላፍንቱ ኪስ የገባ ነበር፡፡ በሩሲያ ጃፓን





ጦርነት ጊዜ የሩሲያ የጦር መኮንኖች ለራሳቸው ሠራዊት የተገባውን ብዙ ገንዘብ ለራሳቸው ዘርፈው ወስደዋል፡፡ የሩሲያ ሕዝብ በዓለም ጦርነት የተሰለፉበት ዋናው ምክንያት ሀብት ለማትረፍና ምድር ለመያዝ ካላቸው ፍላጎት የተነሳ ነበር፡፡ ዛሬስ በሩሲያ ከዚህ የተለየ የሚታይ ነገር አለን? እንደምንመለከተው ተቀባይነትን ለማግኘት በጣም እየጣሩ ናቸው፡፡ በነገስታት ዘመን እንደነበሩት ጨካኞችና ሌቦች ሆነው መታየትን አይፈልጉም፡፡ ነገር ግን እሁንም ቢሆን የሚያምናቸው የለም፡፡ የሩሲያ ሕዝቦች ሁሉም ነገር የተወሰደባቸውና ለራሳቸው ምንም ነገር እንዲያኖሩ ያልተፈቀደላቸው ናቸው፡፡ የሩሲያ መሪዎች የራሳቸውን ኪሶች ለመሙላት ወደ ኋላ ብለዋል ብሎ የሚያስብ ያለ ይመስላልን? እኛም አናስብም፣ ትኩረታችንም (ጥናታችን) ይህን ያረጋግጥልናል፡፡

ተራው ሕዝብ በስልፍ ሲቆም (ሕቃ ለመግዛት) የእነርሱ ፓርቲ አባል ያልሆነ ለውድቀትና ለሞት ሲዳረግ እነርሱ ግን በምቾትና በድሎት ይኖራሉ፡፡ ኮሚዩኒዝም ሩሲያን ባለጠጋ እያደርጋትም የኮሚዩኒዝም ልምምዶቹ (የሥራ ልምምዶች) ምንም ውጤት አምጥተው አያውቁም፡፡ ጎግ ሀብትን ለመሰብሰብ ካለው ስግብግብነት የተነሳ አንድ ቀን የከንዓንን ሀብት ለመበዝበዝና ለመዝረፍ ያስብና ያለውን የጦር ኃይል ሁሉ ለጦርነት ያዝዛል፡፡ ነገር ግን ጎግ አይሳካለትም፡፡

ለሮሽ፣ ለምሳህና ለቶቤል አለቃ ስለሚሆናቸው የማጎግ ምድር ጎግ ሩሲያ ስለ መሆኑ ግምታችን ትክክል ከሆነ «ስለ ሩሲያ የትንቢት ቃል ምን ይላል?» ለሚለው ጥያቄ እንደሚከተለው መልስ መስጠት እንችላለን፡፡

ሩሲያ የዓመጸኛ ኃይል መቀመጫ ከፍተኛ የጥፋት ታሪክ ያላት ናት፡፡ ይህ ኃይል በመጨረሻዎቹ ቀናት የእግዚአብሔር ጠላት ይሆናል፡፡ የተመረጠውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከመንፈሳዊ ነገሯ ይልቅ ስለ ምድራዊ ሀብቷ ይወራራታል፡፡ ነገር ግን ከፍተኛ ዘመቻው ተወዳዳሪ በሌለው በእግዚአብሔር ፍርድ ወደ ፍጻሜው ይደርሳል፡፡ ጎግ (ሩሲያ) በዓለም ሕዝብ መካከል ላለው የክርስትና ተቃውሞ ሕብረትና ለአስቃቂ ጥፋታቸው ምሳሌ ነው፡፡ የዚህ ሕብረት ኃይልና ዕድገት የክርስቶስ ተቃዋሚ ከመነሳቱ በፊት ያደገ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ከክርስቶስ ተቃዋሚ በፊት በእግዚአብሔር የፍርድ እሳት የተደመሰሰ ይሆናል፡፡ ሆኖም በኋላ የሚነሳው የክርስቶስ ተቃዋሚ በጎግ ላይ የወረደውን ማስጠንቀቂያ ምሳሌ ለሆነው ለእግዚአብሔር ፍርድ ቦታ የማይሰጥ ወይም ወደ ኋላ የማይመለስ ይሆናል ፡፡ ስለሆነም በተመሳሳይ የጥፋት መንገድ በመሄድ የባስ እድል ያገኘዋል፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያ ወደ እሳት ባሕር የሚጣለው እርሱ ስለሚሆን ነው፡፡ *(ራዕ. 19:20)*

በዚህ ትንቢት ብርሃን በሩሲያ ያለውን የአሁኑን እድገት ልንገመግም እንችላለን:: በታላቁ የመከራ ዘመን በምንም ነገር ይህች ሀገር የመሸሸጊያ ሀገር አትሆንም ነገር ግን ከሌሎች መንግስታት በፊት ወደ ጥፋት የምትሄድ ትሆናለች:: የጉበኛው ቃል «ወደዚያ እንሒድ» የሚል ሳይሆን «ከዚያ እንውጣ» የሚል ነው::

በመጨረሻም ቡስሚር በራዕ. 20 የተጠቀሰው «ጎግ» *በሕዝ.38 እና 39* ከተጠቀሰው «የማጎግ ምድር ጎግ» ጋር ስላለው ግንኙነት አስተያየት ሰጥቷል:: *በሕዝ.38-39* እና *በራዕይ 20* መካከል ያለው ግንኙነት በሚለው ርዕስ ስር የሚከተለውን ገለጻ ይሰጣል::

*በሕዝ. 38 እና 39* የተጠቀሱት ስሞች በራዕይ ላይ ተጠቅሰው ይገኛሉ:: ከክርስቶስ 1000 ዓመታት አገዛዝ በኋላ የማጎግ ጎግ በሰይጣን መሪነት የሰውን ዘር በሙሉ በእግዚአብሔርና በቅዱሳኑ ላይ ወዳለው የመጨረሻ ከፍተኛ ተቃውሞ ያመራል:: *በሕዝ. 38 እና 39* የተጠቀሰው ሁኔታ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነውን? ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ሁለቱን ክፍሎች ቢያያይዟቸውም እኛ ግን በነገሩ አንስማማም:: *የራዕዩ 20* የማጎግ ጎግ፣ ለሮሽ፣ ለምሳህና ለቶቤል ዋና አለቃ ከሚሆናቸው የማጎግ ምድር ጎግ ጋር አንድ አይደለም:: የስማቸው ልዩነት አንዱን ከሌላው ጋር እንዳናዛምዳቸው ማስጠንቀቂያ ነው:: ከሺው አመት የክርስቶስ አገዛዝ በኋላ የመጨረሻው ፍርድና የመጨረሻው ቀን እንደሚመጣ (*በራዕይ 20*) እናነባለን:: ሰይጣን አውሬውና ሀሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት የእሳት ባሕር ይጣላል:: ዓለምም ይፈረድበታል፣ ለሰማይና ለምድርም ቦታ አይገኝላቸውም (ይጠፋሉ) :: ሙታን በሙሉ በታላቁ የነጩ ዙፋን ፊት ይቀርባሉ:: *በሕዝ.38 እና 39* የጎግ ጥፋት እንደሚከተልና *በኢዩ.2 እና 3* የሰሜን ምድር ጥፋት እንደሚከተል በተጠቀሰው መሠረት ለእስራኤል የመዳን ጊዜ ስለ መኖሩ ለመገመት አያዳግትም:: የጎግ ሙታን (ሬሳ) ለመቅበር የሰባቱ ወራት ጊዜ አይበቃም:: (መዝ. 39:12) ወይም ከሠራዊቱ በግፍ ተወስዶ የነበረውን ንብረት ለማጥፋት ያለው ሰባት ዓመት የለም:: ይህን ችግር እንዴት እንፈታዋለን? ነቢዩ ዮሐንስ ሕዝቅኤልንና ትንቢቱን የተረዳ አልነበረም በማለት አንዘጋም:: የትንቢትን ቃል በጣም ያጠናውን የምሁሩን አውበርሊንን ሀሳብ በቀላሉ እንከተላለን ጎግና ማጎግ የተባሉት ስሞች ቋሚ ስሞች መሆናቸውን ይደግፋል:: የተለየ ሕዝብን የሚገልጹ ሳይሆን ሁኔታን (ታሪክን) የሚገልጹ ናቸው (*በራዕ. 20:8*): የተገለጹት በዚህ ሁኔታ ነው ነገር ግን ይህን ሁኔታ በሌላ አቅጣጫ እንመለከተዋለን:: የጎግ ሠራዊት በእስራኤል ላይ





በሚያደርገው ዘመቻ መላ ሠራዊቱ በሙሉ ያልቃሉ:: ነገር ግን ሴቶችና ሕፃናት በጎግ ሠራዊት ውስጥ አይሠለፉም ብለን ከገመትን ሰራዊቱ ወንዶች ብቻ ናቸው ማለት ነው:: (ዛሬ የሩሱያ ሴቶች በሩሲያ ሠራዊት ውስጥ ያገለግላሉ) ስለሆነም የጎግ፣ የሮሽ፣ የሞሳህ፣ የቶቤል፣ የጎሜርና የቶጋርማ ሕዝቦች (ነገዶች) ይኖራሉ ብለን እንገምታለን:: እነዚህ ሕዝቦች በብሉይ ኪዳን ከተጠቀሱት ከከንዓን ሕዝቦች ጋር አወዳድሩት:: የሚጠፉ የሚደመሰሱም ነበሩ:: ነገር ግን ቢመቱም እስከ አሁን ድረስ አሉ:: በመጽሐፈ አስቴር የተጠቀሰው የእስራኤል ጠላት የሆነው ሐማ አማሌቃዊ የሆነው የአጋግ ትውልድ ዝርያ አጋጋዊ ነበር:: ይህ የአጋግ ንጉሥ ሳኦል ሕይወቱን ያተረፈው፣ ነገር ግን በሳሙኤል የተገደለው ነበር::

በቤተ ልሔም ሕፃናትን የገደለው ሄሮድስ የኤሳው ትውልድ የሆነ ኤዶማዊ ነበር:: ከዚህ በመነሳት የጎግ ሕዝቦች ወደ ፊት የሚኖሩና እንደገና ተጠናክረው የሚያድጉ እንደሆነ ለመገመት እንችላለን:: የ1000 ዓመት መንግስት ይመጣል:: የሰው ልጆች የሚበዙበትና ከዚህ በፊት ከቶ ባልሆነ ሁኔታ ምድርን የሚሞሉበትና ሊገመት የማይቻል የበረከት ጊዜ ይሆናል:: ይህ ጊዜ ከጎግ ጋር ሕብረት ላደረጉት መንግስታት ጥሩ ጊዜ ይሆንላቸዋል:: የጎግ ቤት እንኳን በራሱ ምድር ታላቅ ሕዝብ ይሆናል (*በራዕ.20:8*): «ጎግና ማጎግን እንዲያሳስታቸው ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል» የሚለው ስለዚህ ነው:: ይህም ማለት ከሰሜን እስከ ደቡብ ያሉትን ሕዝቦች የሚያመለክት ነው ማለት ነው:: ይህ የምድሩን አቀማመጥ የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን የውስጣቸውንም ባሕርይ የሚያሳይ ነው:: ከጽዮን መንፈሳዊ ነገርና ከደህንነትዋ ከመለየታቸው ምክንያቱም ጽዮን *በሕዝ.38:12* እንደምናነበው የዓለም ደህንነትና ታሪክ ማዕከል ስለሆነች ነው:: የበረከት ዘመን በሆነው በክርስቶስ መንግስት ጊዜ እንኳን ጎግና ማጎግ በሞኝነት ራሱን የለየ ይሆናል:: በሐሞን ጎግ ሸለቆ ያለውን መቃብር ብዛት በሙሉ ንቃት ያስታውሱት ይሆንን? በቀል ለመውሰድ ይፈልጋሉን?

ምንም እንኳን አመጸኛው ሰይጣን በሺሁ ዓመት ጊዜ ስለታሰረ ባይኖርም በ1000 ዓመታት በፊት የጎግና የማጎግ ወላጆች በእግዚአብሔር ላይ ከፍተኛ ጥላቻ እንዳደረጉት ሁሉ የመጨረሻም ጊዜው በእግዚአብሔር ላይ በጥላቻ የሚነሱት መጨረሻዎቹ የሚሆኑት ከዚህ የተነሳ ነው:: ለሰይጣን አመቺ በመሆን እርዳታ የሚሰጡት ቀዳሚዎቹ እነርሱ ይሆናሉ:: ከሰይጣን ጋር በመሆን የመጨረሻውን ጦርነት ለማድረግ ይደፍራሉ:: አለቃቸው በአባቶቻቸው ዘመን ከነበረው መሪ የባሰ

ክፉ ይሆናል። ሰይጣን ራሱ መንገዱን ይመራል። ነገር ግን በእርሱና በእነርሱ ላይየሚወርደው ፍርድ በሌሎቹ ላይ ከወረደው የከፋ ይሆናል። በዚህ የዓለም ታሪክ ወደ ፍጻሜው ይመጣል፣ ምክንያቱም የጎግና የማጎግ ጦርነት የሰው ዘር ድጋፍ ሲገኝ እንደማይችል ያረጋግጣል። በ1000 የበረከት ዓመታት ጊዜ የሰው ዘር ኃጢአተኛ በመሆን ይቀጥላል (ይቆያል)። እግዚአብሔር ዓለምን በእሳት በማጥፋት አዲስ የከበረ ዓለም በመፍጠር ከሰው ጋር ያለውን የመጨረሻውን ግቦች የሚፈጽመው በዚህ መንገድ ብቻ ነው። ይህን አዲሱን ዓለም የሚፈጥረው

«እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ» ባለው መሰረት ነው።





*የሦስቱ የዋናዎቹ መዋጀት መያያዝ የጋራ ግብ*

# የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት

በመጀመሪያው ጥናታችን መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን ሶስት ሕዝቦችን ለይቶ ማሳየቱን አግኝተናል። (*1ቆሮ.10:31-32*) እነርሱም፦

**1. የዓለም ሕዝቦች (አሕዛብ)**

**2. የእስራኤል ሕዝብ**

**3. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ናቸው።**

በማዳን ታሪክ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ እነዚህ ሦስት ሕዝቦች በሦስት ወፋፍራም መስመሮች፣ እያንዳንዱ የራሱን ዓላማ በመያዝ እንደሚሄድ ተመልክተዋል። ነገር ግን በመጨረሻ ሁሉም በዓለም ወደማይናወጠው ሁኔታና የደህንነት ታሪክ ያመራሉ። እርሱም የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ነው። ይህም ሰው ቢገነዘበውም ባይገነዘበውም ይሆናል።

የሦስቱን የዋናዎቹን የመዋጀት ታሪክ መያያዝ ስናጠና ሦስት አመለካከቶች እንዳሉ ልንረዳ ያሻል። ይኸውም፦

**1. አህዛብ እንደሚዋረዱ (ዝቅ እንደሚሉ)**

**2. የእስራኤል ሕዝብ ከፍ እንደሚሉ**

**3. የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ወደ ቤቷ (መንግሥተ ሰማይ) እንደምትሔድ።**

እነዚህ ሦስቱ ሕዝቦች ከሚመጣው ንጉስ (ከጌታ ኢየሱስ) ታሪክ ጋር የሚያያዙት እንዴት ነው? በዚህ ጥያቄ ላይ እንወያያለን። ቅርብ በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም ምጽአት ላይ ስላለው ስለ ራሳችን አቋም እንደገና ለመመርመር እድል ይኖረናል።

ክፉ ይሆናል:: ሰይጣን ራሱ መንገዱን ይመራል:: ነገር ግን በእርሱና በእነርሱ ላይየሚወርደው ፍርድ በሌሎቹ ላይ ከወረደው የከፋ ይሆናል:: በዚህ የዓለም ታሪክ ወደ ፍጻሜው ይመጣል፣ ምክንያቱም የጎግና የማጎግ ጦርነት የሰው ዘር ድጋፍ ሲገኝ እንደማይችል ያረጋግጣል:: በ1000 የበረከት ዓመታት ጊዜ የሰው ዘር ኃጢአተኛ በመሆን ይቀጥላል (ይቆያል):: እግዚአብሔር ዓለምን በእሳት በማጥፋት አዲስ የከበረ ዓለም በመፍጠር ከሰው ጋር ያሰውን የመጨረሻውን ግቦች የሚፈጽመው በዚህ መንገድ ብቻ ነው:: ይህን አዲሱን ዓለም የሚፈጥረው

«እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ!» ባለው መሰረት ነው::





*የሦስቱ የዋናዎቹ መዋጀት መያያዝ የጋራ ግብ*

# የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት

በመጀመሪያው ጥናታችን መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን ሶስት ሕዝቦችን ለይቶ ማሳየቱን አግኝተናል:: (*1ቆሮ.10:31-32*) እነርሱም:-


1. የዓለም ሕዝቦች (አሕዛብ)
2. የእስራኤል ሕዝብ
3. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ናቸው::

በማዳን ታሪክ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ እነዚህ ሦስት ሕዝቦች በሦስት ወፋፍራም መስመሮች፣ እያንዳንዱ የራሱን ዓላማ በመያዝ እንደሚሄድ ተመልክተዋል:: ነገር ግን በመጨረሻ ሁሉም በዓለም ወደማይናወጠው ሁኔታና የደህንነት ታሪክ ያመራሉ:: እርሱም የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ነው:: ይህም ሰው ቢገነዘበውም ባይገነዘበውም ይሆናል::

የሦስቱን የዋናዎቹን የመዋጀት ታሪክ መያያዝ ስናጠና ሦስት አመለካከቶች እንዳሉ ልንረዳ ያሻል:: ይኸውም:-

1. አህዛብ እንደሚዋረዱ (ዝቅ እንደሚሉ)
2. የእስራኤል ሕዝብ ከፍ እንደሚሉ
3. የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ወደ ቤቷ (መንግሥተ ሰማይ) እንደምትሔድ::

እነዚህ ሦስቱ ሕዝቦች ከሚመጣው ንጉስ (ከጌታ ኢየሱስ) ታሪክ ጋር የሚያያዙት እንዴት ነው? በዚህ ጥያቄ ላይ እንወያያለን:: ቅርብ በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም ምጽአት ላይ ስላለው ስለ ራሳችን አቋም እንደገና ለመመርመር እድል ይኖረናል::




በመጀመሪያ የክርስቶስ ዳግም መምጣት የአንድ ጊዜ ሁኔታ መሆኑን ግልጽ ልናደርግ ይገባናል። ጌታ የሚመለሰው በመደጋገም ብዙ ጊዜ ሳይሆን አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ስለዚህ እውነት ያለው አንድ ነገር ቢኖር የክርስቶስ ዳግም መምጣት በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ የተለየ ውጤት ስላለው ነው በጊዜው እያንዳንዱ ግለሰብ ከእነዚህ ከሦስቱ ሕዝቦች በየትኛው ውስጥ መገኘ ቱን እናያለን። ይህ ጥያቄ እያንዳንዱ ግለሰብ የራሱን ሁኔታና የዘላለም ደህንነቱን እንዲወስን ያደርገዋል። ያ! ሕዝብ የክርስቶስን ዳግም መምጣት በተለያዩ መንገድ መገናኘቱን በቀላሱ ለመግለጽ የሚቻለው ከራሱ ሕይወት ጋር በማነጻጸር ነው። እያንዳንዳችን ከሌላው ሕዝብ ጋር በተለያየ መንገድ ግንኙነት ያለን ግለሰቦች ነን። ለምሳሌ ያገባ ሰው ለሚስቱ ባል ብቻ ሳይሆን ለልጆች አባት፣ ለወላጆቹ ልጅ፣በአጠገቡ ለሚኖሩት ጎረቤት አብረውት ከሚሠሩት ጋር የሥራ ባልደረባ ነው። የክርስቶስ ኢየሱስ መምጣት አንድ ጊዜ የሚሆን ሁኔታ ነው። ነገር ግን በተለያዩ የሕዝብ ክፍሎች ላይ የተለያዩ ውጤቶች ይኖረዋል። ለአሕዛብ፣ ለእስራኤል ሕዝብ፣ ለቤተክርስቲያኑ ይመጣል። ነገር ግን ሁሉም በተለየ መንገድ ይያዛሉ።





በእርግጥ የክርስቶስ መምጣት ዋናው ትዕይንት ነው። የዓለም ታሪክ በሙሉና የደህንነት ታሪክ ወደ አንድ ሁኔታ ብቻ እያመራ ነው፡እርሱም ይህን ዓለም ወደሚፈጽመው ወደ ክርስቶስ ነው። አሳዛኙ ነገር አብዛኛውን የዚህ ዓለም ሕዝብ ይህን እየተጠባበቁት አይደለም። ይህን ታላቅ ሁኔታ ምን ማለት እንደሆነ በበለጠ በግልጽ መረዳትየሚያስፈልገን ስለዚህ ነው። በደህንነት "ታሪክ" ቻርት ላይ የጌታ መመለስ በቅደም ተከተል የተመለከተ ነው። የክርስቶስ ዳግም መምጣት የሚጀምረው ለራሱ ስለሆነው ሕዝብ ነው። በደሙ የተገዙ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና ወደ ሰማያዊ ክብር ይወሰዳሉ።ከዚህ በኋላ ጌታ ከሕዝቡ ጋር በዓመጸኛው ሕዝብ ላይ ሊፈርድ፣የእስራኤልን ሕዝብ ለማዳንና የመሲሁንየሰላም መንግስት ለማንገስ (ለመመስረት) ይመጣል። አሁን ከላይ እንደተጠቀሰው የክርስቶስን ዳግም መምጣት በቅደም ተከተል እንመለከታለን።

## 1. ጌታ ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያኑ መመለሱ

ዳግም ለተወለዱት አማኞቹ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሙሽራቸው በመሆን ይገለጣል። «በመጨረሻው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንበመንግስተ ሰማይ እንደ በጉ ሚስት ሆና ትታያለች»። ራስዋን ስላዘጋጀች «ያጌጠና የተጣራ ቀጭን የተልባ ዕግር ልብስ» እንድትጎናጸፍ ተሰጣት። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ ይህ የተጣራው ልብስ የቅዱሳን የጽድቅ ሥራ እንደሆነ ተገልጿል። *(ራዕ.19:7-8፣ 1ቆሮ.1:31)*። ይህ ዳግም የተወለዱ አማኞች ምልክት ነው። በመቀጠል መጽሐፍ በሰማይ ስለሚከናወነው «የበጉ ሰርግ» ይናገራል።የበጉ ሰርግ በቃላት ሊነገር የማይቻል የደስታ ጊዜ ይሆናል።*(ራዕ.19:7-9)*

ይህ ታሪክ ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በጻፈው መልእክቱ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያኑ ያለውን የማይደመሰሰውን ሕይወት የሚገልጽ ነው። በሌሎቹ ነገሮች መካከል በወንድና በሴት መካከል ያለው ጋብቻ ታላቅ ሚስጥር እንዳለው ጽፏል። ከዚህ ሚስጢር በስተጀርባ ጋብቻ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያኑ ስላለው ከፍተኛ ሚስጢር ይናገራል *(ኤፌ.5:31-32)*። ስለሆነም መጽሐፍ ቅዱስ ዳግም የተወለዱት አማኞች ከጌታ ኢየሱስ ሙሽራ ጋር ለዘላለም አንድነት እንዳላቸው ይገልጽልናል።

መጽሐፍ ቅዱስ ጌታ ሙሽራውን (ቤተ ክርስቲያኑን) ወደ ሰማያዊ ቤቷ ሊወስድ የሚመጣበትን ሁኔታ «መነጠቅ» በሚል ሀሳብ ይገልጻዋል።

*«ጌታ ራሱ በትዕዛዝ፣ በመላእክት አለቃ ድምጽ፣ በእግዚአብሔር መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፣ በክርስቶስ የሞቱ አስቀድመው ይነሳሉ:: ከዚያን በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን» (1ተሰ.4:16-17)*

ጌታ ኢየሱስ ወደ አባቱ ከመሄዱ በፊት አንድ ቀን እንደገና ተመልሶ እንደሚመጣ ለደቀ መዛሙርቱ ነገሯቸዋል:: የሚከተለውን አስደናቂ ተስፋ ሰጥቷቸዋል::

*«በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፣ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፣ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሔዳለሁ፣ ሄጄም ስፍራ ባዘጋጀሁላችሁ፣ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ» (ዮሐ.14:2-3)::*

ጌታ ተመልሶ የሚመጣበትን ጊዜ ማንኛውም አማኝ አያውቀውም:: ምክንቱም አብ በስልጣኑ ለራሱ ብቻ ስለያዘው (ስለጠበቀው) ነው (ማቴ.24:36::) ነገር ግን ማንኛውም ዳግም የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ «የተባረከውን ተስፋ» (ቆላ.1:27):: በልቡ የጠበቀ አንድ ምኞት ብቻ ይኖረዋል፣ ይኸውም ከጌታ ጋር ለመኖርና ወደ ቤቱ የመሄድ ምኞት ነው::


ለ2000 ዓመታት የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ለዚህ ለተባረከው ጊዜ ራሳቸውን ሲያዘጋጁ ቆይተዋል:: ከጌታቸው መመለስ በስተቀር ሌላ በናፍቆት (በጉጉት) የሚጠብቁት የላቸውም:: መቅረዛቸውን በዘይት ሞልተው ሙሽራውን ለመቀበል ይወጣሉ (ማቴ.25:1-13):: ልባቸው «ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን» የሚሻ ነው:: ምክንያቱም «ሕይወታቸው በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና» (ቆላ.3:1-3):: ዓለምን የካዱና ምንም ነገር ከቶ ከክርስቶስ እንደማይለያቸው ሆነው በክርስቶስ ላይ የተጠማጠሙ ስለሆኑ ይህ ነገር ብቻ ወደ ግባቸው ይመራቸዋል (ያደርሳቸዋል) (ፊል.3:14):: ጌታ ይህን ተስፋ ከቶ አያስቀረውም::

በጥንቱ የግሪክ ትርጉም (1ቆሮ.15:52) ኢን አቶሞ (ስቃ ሮቋቂቂቂ) «በአንድ አቶም» ነው በሚል የተጻፈ ነው:: ጌታ ሲመጣ በቅጽበት ዓይን ከእርሱ ጋር ይሆናሉ:: የግሪኩ ቃል አቶሞስ (ሮቋቂቂቂቋ) የሚለው ቃል ፍቺው ሊከፋፈል የማይቻል አጭር ጊዜ ማለት ነው:: መነጠቅ በጊዜ ሲመጠን በማይቻል ቅጽበታዊ ጊዜ የሚሆን ነው:: በዚህ ጊዜ በምድር ላይ ያሉት ያልሞቱት አማኞች «አንቀላፍተው ያሉትን» አይቀድሟቸውም:: (1ተሰ.4:15) ይህ ጥቅስ ጌታ ኢየሱስ





ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን በምድር ሳይሆን በአየር ላይ እንደሚገናኛት ያስተምረናል:: በደህንነት ታሪክ ላይ ያለው ሥዕላዊ ቻርት «በአየር ላይ የመገናኛ ቦታ» በማለት ያመለክተዋል:: (1ተሰ.4:17) በዚህ ነጥብ ላይ ከፍ እያለ ወደ ላይ የሚወጣው አረንጓዴ መስመር (የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን) ወደ ታች ዝቅ እያለ ከሚወርደው ቡናማ መስመር (የእግዚአብሔር ልጅ) ጋር ይገናኛል:: ከዚያ ቦታ ለዘላለም የተገናኙ ይሆናሉ:: ይሄ ነገር ሲከናወን በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ያሉት አማኞች ከግባቸው የደረሱ ይሆናሉ:: በሰማያዊው አባታቸው ቤት ይገባሉ፣ በዚያም «ለዘላለም ከጌታ ጋር» ይሆናሉ (1ተሰ.4:17):: ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ላይ የኃጢአት ዋጋ የሆነውን የሞት ዕዳ ስለ ከፈለላቸው እንዳቸውም አይፈረድባቸውም:: (ዮሐ.5:24) በታላቁ አስቃቂ በሆነው የመከራ ዘመን ውስጥ አያልፉም:: ባለፈው ምዕራፍ እንዳየነው ያ ጊዜ በዓመጸኛው ሕዝብ ላይ የሚወርደው ፍርድ ስለሆነ ነው:: ሊመጣ ካለው መከራ ያመለጡ ይሆናሉ:: (1ተሰ.1:10) ስለሆነም የክርስቶስ ኢየሱስ ሙሽራ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ወደ ቤቷ ትሔዳለች:: በምድር ላይ ያለው አስቃቂ ፍርድ ሳይሆን የሚጠብቃት ሰማያዊ ክብር ነው::



## 2. የኢየሱስ ክርስቶስ ለአህዛብ መመለስ፡-

ጌታ ኢየሱስ በዳግም ምጽአቱ ጊዜ የእግዚአብሔርን ልጅ (እርሱን) እውነተኛውን መሲህ በተቃወሙትና በእርሱ ምትክ የክርስቶስን ተቃዋሚ በተቀበሉና ባልዳኑት ሕዝቦች ላይ ፈራጅ በመሆን ይገለጣል:: የራዕይ መጽሐፍ የሚመጣውን ጌታ *«የእግዚአብሔርን የብርቱ ቁጣውን»* ፍርድ የሚፈጽም አድርጎ ይገልጸዋል (*ራዕ. 19:15)::* በራዕ.16:14 ላይ ዮሐንስ ይህን ቀን *«ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን»* በማለት ገልጸዋል:: የብሉይ ኪዳን ነቢያት *«የጌታ ቀን»* ብለው ጠርተውታል:: ይህ ቀን በእግዚአብሔር ቁጣ የተሞላ አስፈሪ ቀን ነው:: ቀጥሎ የተጠቀሱት ይህንን ቀን ያመለክታሉ::

*«የእግዚአብሔር ቀን ቀርቦአልና፣ አልቅሱ፣ ሁሉን ከሚችል አምላክ ዘንድ እንደሚመጣ ጥፋት ይመጣል» (ኢሳ.13:6)::*

*«እነሆ ምድሪቱን ባድማ ሊያደርግ፣ ኃጢአተኞችዋንም ከእርስዋ ዘንድ ሊያጠፋ ጨካኝ ሆኖ በመዓትና በጽኑ ቁጣ ተሞልቶ የእግዚአብሔር ቀን ይመጣል» (ኢሳ.13:9)::*

*«የእግዚአብሔር ቀን ቀርቦአልና ለቀኑ ወዮ! እርሱ ሁሉን ከሚችል ከአምላክ ዘንድ እንደ ጥፋት ይመጣል» (ኢዩ.1:15)*፡፡

*«የእግዚአብሔር ቀን ቀርቦአልና፣ እግዚአብሔር መስዋእትን ዘጋጅቶአልና፣ የጠራቸውንም ቀድሶአል፣ በጌታ በእግዚአብሔር ፊት ዝም በሉ» (ሶፎ.1:7)*፡፡

*«የእግዚአብሔርን ቀን ለምትፈልጉ ወዮላችሁ! ጨለማ ነው እንጂ ብርሃን አይደለም» (አሞ.5:18)*፡፡

ፍርድ በእርግጥ ይመጣል:: (በ*ሐሥ.17:31) መሠረት* እግዚአብሔር «ቀን ቀጥሮአል በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለው» በዓለም ላይ ሊፈርድ የሚመጣው ይህ «ሰው» ማን ነው? መልሱ በዮሐንስ ወንጌል ይህ ሰው ከራሱ ከእግዚአብሔር ልጅ በስተቀር ሌላ እንዳልሆነ «ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም» በማለት በግልፅ ተጽፏል (*ዮሐ.5:22)*፡፡





ጌታ ኢየሱስ በጠፋት በዓለም ሕዝቦች ላይ ሲፈርድ ተመልሶ ሲመጣ «በታላቁ ንጉሥ ከተማ» (ማቴ. 5:35) በኢየሩሳሌም የሚከናወን ይሆናል:: ነቢዩ ዘካርያስ በመጽሐፉ «እግሮቹ በኢየሩሳሌም ትይዩ በምሥራቅ በኩል ባለው በደብረዘይት ላይ ይቆማሉ» ብሏል:: *(ዘካ.14:4) ደቀ* መዛሙርቱ ዓይን ፊት ወደ ሰማይ አርጎበት ወደ ነበረው ሥፍራ ይመለሳል (*የሐሥ.1:9-11)* ነገር ግን ከእርገቱ አንድ የተለየ ነገር አለ:: «በኃይልና በታላቅ ክብር» ሆኖ ሲመጣ የአለሙ ፈራጅ ብቻውን አይደለም:: ነገር ግን «በሰማይ ያሉት ጭፍራዎች ነጭና ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ለብሰው በአምባላዮች ፈረሶች ተቀምጠው ይከተሉታል» ተብሎለታል:: *(ማቴ.24:30፣ ራዕ.19:14)* ስለሆነም ጌታ ከቅዱሳኑ ጋር በዓለም ሊፈርድ ይመጣል:: የእግዚአብሔር ልጆች በክርስቶስ ደም የተዋጁ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ናቸው::*(1ተሰ.3:13፣ ይሁዳ 14)* መጽሐፍ ቅዱስ በሌላ ቦታ «ቅዱሳን በዓለም እንደሚፈርዱ» (ከክርስቶስ ጋር) ይናገራል *(1ቆሮ.6:2)*፡፡

በማዳን ታሪክ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ የክርስቶስ ዳግም መመለስ ወደታች በሚወርዱ መስመሮች በአረንጓዴና በቡናማ ቀለም የተመለከቱ ናቸው:: ሁለቱ ቀለሞች የእግዚአብሔር ልጅ ከቅዱሳኑ ጋር በዓለም ሕዝቦች ሊፈርድ እንደሚመጣ ያመለክታሉ::

በዚህ የፍርድ ጊዜ ልንመረምራቸው የሚያስፈልጉ ሁለት ሁኔታዎች አሉ:: እነርሱም :-

1. የአርማጌዶን ጦርነት
2. የሕዝብ መፈረድ ናቸው

## የአርማጌዶን ጦርነት

መጽሐፍ ቅዱስ *በራዕይ ምዕራፍ 16* ውስጥ አርማጌዶን ስለተባለው ቦታ ይናገራል *(ራዕ16:16)*፡ አርማጌዶን ማለት የሚጊዶን ተራራ ማለት ነው:: ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ሚጊዶን ወደ ተባለው ስፍራ ትኩረት እንድናደርግ ያደርገናል:: ይህ ቦታ ከእስራኤል በስተ ሰሜናዊ ምስራቅ ባለው በኢዝርኤል ሸለቆ ውስጥ የሚገኝ ነው *(1ኛነገ.9:15)* በዚህ ቦታ ከማንኛውም ጊዜ የበለጠ በእግዚአብሔርና በሚመጣው ንጉስ በጌታ ኢየሱስ ላይ ያለው ጥላቻ ይካሄዳል:: በቅርቡ በአርማጌዶን ላይ ከፍተኛ ፍርድ ይካሄዳል:: መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስ ተቃዋሚ ከሚያመጣው የመከራ ዘመን ፍጻሜ ላይ ክፉ መናፍስት ከሰይጣን፣ ከክርስቶስ ተቃዋሚና ከሀሰተኛው ነቢይ ጋር በሥራ ላይ ይውላሉ::

«ከዘንዶውም አፍ፣ ከአውሬውም አፍ፣ ከሀሰተኛውም ነቢይ አፍ፣ ጓጉንቸር የሚመስሉ ሦስት ርኩሳን መናፍስት ሲወጡ አየሁ» (ራዕ.16:13)::

እነዚህ መናፍስቶች በሰይጣን አታላይነት የክርስቲያን ተቃዋሚዎች ከሆኑት ብዙ ሠራዊትን ከዓለም ይሰበስባሉ::


«ምልክት እያደረጉ የአጋንንት መናፍስት ናቸውና፣ በታላቁም ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን ወደሚሆነው ጦር እንዲያሰከትቷቸው ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይወጣሉ» (ራዕ.16:14)::

ታላቅ ሠራዊት ከዓለም በዚህ «ሁሉን በሚገዛው በታላቁ በእግዚአብሔር ቀን» ሕብረት አድርገው የመሰባሰባቸው እውነታ እግዚአብሔር ለርኩሳን መናፍስት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ የሚፈቅድላቸው መሆኑን ያሳያል:: እግዚአብሔር ይህን መንገድ የመረጠበት ምክንያት የክርስቲያን ተቃዋሚ የሆኑትን የሕዝብ ብዛት በአንድነት ለመሰብሰብ (ለማከማቸት) ነው::

«በዕብራይስጥም አርማጌዶን ወደሚባል ስፍራ አሰከተቱአቸው» (ራዕ.16:16)::

ከዚህ ውጪት የተነሳ በቅድስቲቱ ምድር፣ በኢዝርኤል ውስጥ ባለው ሸለቆ እስራኤልን የሚወርር ታላቅ ሠራዊት ይከማቻል:: የሚከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስለ ፍርድ በግልጽ ይናገራል::

«አንድም መልአክ በፀሐይ ውስጥ ቆሞ አየሁ:: በሰማይም መካከል ለሚበሩ ወፎች ሁሉ መጥታችሁ የነገሥታትን ሥጋና የሻለቆችን ሥጋ የብርቱዎችንም ሥጋ የፈረሶችንም በእነርሱም የተቀመጡትን ሥጋ የጌታዎችንና የባርያዎችንም፣ የታናናሾችንና የታላላቆችንም ሁሉ ሥጋ እንድትበሉ ወደ ታላቁ ወደ እግዚአብሔር እራት ተከማቹ ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ» (ራዕ 19:17-18)::








ይህ ሠራዊት «በአምባላይ ፈረስ ላይ» ከሚቀመጠውና ከሠራዊቱ ጋር ጦርነት ለማድርግ ራሱን በሚያዘጋጀው በክርስቶስ ተቃዋሚ የሚመራ ይሆናል::

«በፈረሱም የተቀመጠውን ጭፍራዎቹንም ይወጉ ዘንድ አውሬውና የምድር ነገሥታት ጭፍራዎቻቸውም ተከማችተው አየሁ» (ራዕ.19:19)::

በራዕይ 19:11 «በፈረስ ላይ» ተቀማጩ ማን እንደሆነ እናገኘዋለን::

«ሰማይ ተከፍቶ አየሁ:: እነሆም አምባላይ ፈረስ የተቀመጠበትም የታመነና እውነተኛ ይባላል በጽድቅም ይፈርዳል፣ ይዋጋልም:: ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ናቸው፣ በራሱ ላይም ብዙ ዘውዶች አሉ:: ከእርሱም በቀር አንድ እንኳ የማያውቀው የተጻፈ ስም አለው:: በደምም የተረጨ ልብስ ተጎናጽፎአል፣ ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል» (ራዕ.19:11-13፤ ዮሐ. 1:1)::

ይህ ጥቅስ «በፈረስ ላይ የሚቀመጠው» መጪው ንጉስ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ያሳያል:: የሚከተሉት ሠራዊት «በሰማይም ያሉት ጭፍሮች» በመባል የተጠሩ ሲሆን «ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ የለበሱ» ናቸው በመባል ተገልጸዋል (ራዕ.19:14):: ቀደም ብለን እነዚህ ባሕርያት የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ባሕርያት እንደሆኑ ተመልክተናል:: ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር ለመፍረድ ይመጣል:: በአርማጌዶን የሰው ልጆች አመጸኝነትና በክርስቶስ ላይ ያለው ጥላቻው ጣሪያውን የመታ (የደረሰ) ይሆናል:: በክርስቶስ ተቃዋሚ መሪነት ብዙ ሠራዊት ከመላ ዓለም ከመጪው ጌታ ጋር ለመዋጋት ወደ ጦርነት ለመሔድ ይዘጋጃሉ:: ይህ ዕብደት ነው ብለን ልንገልጸው እንችላለን:: ሕዝቦች ለፍርድ መዘጋጀታቸው ግልጽ ነው:: የነገሥታት ንጉሥ፣ የጌቶች ጌታ» (ራዕ. 19:16) ወደ አርማጌዶን ሜዳ ለፍርድ የሚመጣው ስለዚህ ነው::

«አሕዛብንም ይመታበት ዘንድ ስለታም ሰይፍ ከአፉ ይወጣል:: እርሱም በብረት በትር ይገዛቸዋል:: እርሱም ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔርን የብርቱ ቁጣውን ወይን መጥመቂያ ይረግጣል» (ራዕ. 19:15)::

ከዚህ በኋላ ነቢያት በብሉይ ኪዳን አስቀድመው የተነበዩለት «የጌታ ቀን» ይመጣል:: በዚህ ጊዜ «አመፃን ይጨርሳል» (ዳን.9:24):: አመጸኝነት ከመላ ዓለም ይደመሰሳል (ወደ ፍጻሜው ያመጣዋል):: አዳኙ ከእግዚአብሔር ተልኮ ከኢየሩሳሌም ከተማ ቅጥር ውጭ በቀራንዮ መስቀል ላይ ዓለምን የማዳን ሥራውን ፈጽሟል (ዕብ13:12):: በዚያን ቀን «ከኢየሩሳሌም ከተማ ውጭ» የዓለም ፈራጅ በመሆን «የእግዚአብሔርን የቁጣውን መጥመቂያ» ለመርገጥ ይገለጣል (ራዕ.14:19-20) ::

በመጀመሪያ የሚፈረድበት «ተቃዋሚውና ራሱን ከፍ የሚያደርግ» ነው:: *(2ተሰ.2:4)* እርሱም በአርማጌዶን ከሠራዊቱ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ለመጓዝ የሚዘጋጀው «የክርስቶስ ተቃዋሚ» ነው:: ቀደም ባለው ምዕራፍ እንደተገለጸው በጠቅላላ የተደመሰሰ ይሆናል:: «የምድር ነገስታትና ጭፍሮቻቸው» «የዓመጽን ሰው» ያመለኩና መጪውን ጌታ ለመዋጋት የተከተሉት ሁሉ በአርማጌዶን የጦርነት ሜዳዎች ላይ ይገደላሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ *«በፈረስ ላይ ከተቀመጠው ከአፉ በሚወጣው ሰይፍ ተገደሉ»* ይላል *(ራዕ.19:19-21)*: ይህ ፍርድ አስፈሪ ፍርድ ነው:: ምክንያቱም የተገደሉት ደም እስከ ፈረሶች ልጓም የሚደርስ ርቀቱ ሺህ ስድስት መቶ ምዕራፍ ሆኖ የሚደርስ ነው *(ራዕ.14:20)*: የግሪኩ ቃል ስታድያ (Stadia) በእስፖርት ሁኔታዎች ጊዜ ለመለኪያ የሚጠቀሙበት ነበር:: በ(King James Translation) ትርጉም ምዕራፍ በመባል ተተርጉሟል:: እርሱም 185 ሜትር ርዝማኔ ያለው ነው:: በሮማውያን መለኪያ ደግሞ 192 ሜትር ርዝመት ያለው ነው:: ከዚህ በመነሳት 1600 × 185 ወይም 1600 × 192 ስፋት ያለው የምድር ርዝመት ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህም ወደ 300 ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው፣ የተገደሉት ሰዎች ሬሳ ከፍታው ግማሽ ሜትር የሆነ ክምር የሚገኝበት ነው:: እንዴት ያለ ተወዳዳሪ የሌለው ጥፋት ነው! ኢየሱስ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ ከኢየሩሳሌም 300 ኪሎ ሜትር ዲያሜትር ያለው ክብ ስዕል ብንስል በኢዝራኤል ሸለቆ ውስጥ የሚገኘው የሚጊዶን (የአርማጌዶን) የጦር ሜዳ ከኢየሩሳሌም 150 ኪሎ ሜትር ያህል የራቀ ሆኖ ነው የምናገኘው:: ስለሆነም ይህ ቦታ የሚገደሉት ከሚወድቁበት እጅግ ሰፊ ከሆነው የመሬት ስፋት ጥቂቱ ነው:: ይህም በክርስቶስ ተቃዋሚ ተታልለው የሚመጣውን ንጉስ ለመውጋት ከመላ ዓለም የሚመጡት ሕዝቦች ብዛት ምን ያህል ብዙ እንደሆኑ ለመገመት ያስችለናል:: ያለ ጥርጥር ከዚህ በፊት በአርማጌዶን እንደሚሆነው ጦርነት ሞትና ደም ያለ የሚመስል ዓለም የስጠችው ምስክርነት አይኖራትም (የላትም):: «በህያው እግዚአብሔር እጅ በፍርድ መውደቅ የሚያስፈራ ነው»:: *(ዕብ.10:31)*

## ፍርድ በአሕዛብ

በነቢዩ ኢዩኤልና በማቴዎስ የተገለጸው የአሕዘብ መፈረድ ከአርማጌዶን ጦርነት በኋላ የሚከናወን ነው::

*«የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱ ጋር ቅዱሳን መላእክት ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል:: አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፣ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል» (ማቴ.25:31-32)::*





*(ማቴዎስ 25:31-46)* የሚናገረው እንዳንዶች እንደሚያምኑት ስለ መጨረሻው ፍርድ ሳይሆን ስለ አሕዛብ መፈረድ ነው:: ይህም ከሚከተሉት ሀሳቦች የተነሳ ነው::


1. ጌታ ኢየሱስ ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር ይመለስና (ቁ.31) በኢየሩሳሌም በክብር ዙፋን ላይ ይቀመጣል *(ዘካ.14:9፤ ኤር.3:17)*:
2. እንደ *(ማቴ.25:31-32)* አባባል እሱ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ይገዛል፣ በዓለምም ሕዝብ ላይ ይፈርዳል *(ኢዩ.3:2-12፣ መዝ.93:1-2፤ 94:1-7፤ 97:1-7)*:
3. በመጨረሻ ጊዜ በሙታን ላይ እንደሚፈርደው ራዕይ 20:11-15 ሳይሆን በሕይወት ባሉት ብቻ ነው የሚፈርደው::
4. በአሕዛብ ላይ የሚፈርደው «ከእነዚህ ወንድሞች» ለተባሉት ባሳዩት ምህረትና ርኅራኄ ላይ በተመረኮዘ ነው:: «እነዚህ ወንድሞች» የተባሉት «የንጉሡ ወንድሞች» የእስራኤል ልጆች (ህዝቦች) መሆናቸው ግልጽ ነው:: *(ማቴ.25:34-40)* ለእስራኤል ያደረጉት ምህረት የፍርዱ መለኪያ ነው::
5. «ብሩካን» የተባሉት ሕዝቦች ምህረትን ያደረጉት «ወንድሞች» ለተባሉት ብቻ ሳይሆን ለሰማያዊው ንጉስም ነው:(ማቴ 25:40)
6. በቁጥር 40 ስለዚህም በእነዚህ ወንድሞች ላይ ባሳዩት ምህረት ምህረቱን በእነርሱ ላይ በመዘርጋት ወደ እንድ ሺህ ዓመት ምድራዊ መንግስቱ እንዲገቡ ይፈቅድላቸዋል:: *(ማቴ.25:34-46)*
7. «የተባረኩት» ሕዝቦች ምህረትን ስላደረጉ ወዲያውኑ የሚድኑ አይደሉም:: ይህ ከሆነ ንጉሡ በቀራንዮ መስቀል ላይ ስለ ዓለም ኃጢአት መሞቱ በከንቱ ነው ማለት ነው:: የተባረኩት በሰማያዊው መንግስት በምድር ላይ ሲኖሩ በእውነትና በትህትና ንስሐ በመግባት በተፈጸመው በንጉሡ የማዳን ሥራ ማመን ይኖርባቸዋል:: የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አባልነት የተገባቸው አይደሉም:: በመሲሁ መንግስት ፍጻሜ ገደማ ብዙዎች እንደሚያደርጉት ንጉሡን ይክዱታል:: *(ራዕ.20:7-10)*
8. እነዚህ ወንድሞች በእርግጥ የእስራኤል ልጆች ናቸው:: እህዛብም የእስራኤል ህዝብ ባሳዩት ርህራሄ መሠረት እንደዚሁ ንጉሱም ለእነርሱ ይራራላቸዋል:: ኢዩ 4:1-21

9. የንጉሡ «ወንድሞች» ንጉሡ ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ የተወለደባቸው ሕዝቦች ተወላጆች ናቸው:: እንደ *(ሮሜ9:1-5)* ባለው መሠረት የንጉሡ ሥጋዊ ወንድሞች ናቸው፣ ምክንያቱም ንጉሡ የተወለደው ከይሁዳ ነገድ ነውና:: ከአይሁድ ነገሥታት ትውልድ ሀረግ ካሉት ከድንግል ማርያም ከመወለዱ በሥጋና በደም ዕብራዊ ነው *(ዕብ.2:14-16)* ::

10. በኃጢአታቸው ምክንያት በዓለም ሙሉ የተበታተኑ ቢሆኑም «ወንድሞች» ናቸው:: ነገሥታት፣ መሳፍንት፣ መስዋዕት፣ መስዊያ፣ መቅደስ፣ ደህንነት፣ በውስጣቸው ያደረ መንፈስ ቅዱስ ስላልነበሯቸው የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት አልነበራቸውም *(ሆሴ.3:4-5፤ ማቴ.23:37-39)* ::

11. የዚህ ፍርድ መመዘኛው (ማቴ 25:31-45) በእርግጥ ርህራሄ ነው:: አህዛብ ለእስራኤል ህዝብ ርህራሄን በማሳየታቸው በዚሁ መጠን የሰማዩ መንግሥት ንጉሥ ለእነዚህ አህዛብና ለእያንዳንዱ ዘመዶቻቸውም ጭምር ርህራሄን ያሳያል ርህራሄ (ቁጥር 33-40)

12. በኢዩ.3:1-17 እግዚአብሔር በእስራኣል ላይ በፈጸሙት በደል እደሚፈርድባቸው የሚናገር ክፍል እናገኛለን:: *(ማቴ.25:31-46)* የሚፈረድባቸው ለእስራኤል ባሳዩትና ባላሳዩት ምህረታቸው የተነሳ ነው *(ማቴ.25:41-46)*::




በአሕዛብ ፍርድ የሚሆነው በኢየሩሳሌም ነው::እዚያ በዓለሙ ሁሉ ላይ በሚፈርደው ፊት አሕዘብ ሁሉ ይቀርባሉ::መጽሐፍ ቅዱስ «በፍርድ ሸለቆ» የብዙ ብዙ አሕዛብ ክምችት እንደሚሆን ይናገራል *(ኢዩ.4:14)*:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «የፍርድ ሸለቆ» የተባው «የኢዮሳፌጥ ሸለቆ» ተብሎ ተጠርቷል *(ኢዩ.3:2)* ይህ ስፍራ በሞርያ ተራራና በኢየሩሳሌም ባለው በደብረ ዘይት ተራራ መካከል ያለው የቄድሮን ሸለቆ ነው:: በዚህ ቦታ መጪው ንጉስ ሊፈርድባቸው አሕዛብን ሁሉ ይሰበስባል::





*«እግዚአብሔርም በጽዮን ሆኖ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይጮሀል፣ በኢየሩሳሌምም ሆኖ ቃሉን ይሰጣል:: ሰማይና ምድርም ይናወጣሉ፣ እግዚአብሔር ግን ለሕዝቡ መሸሸጊያ፣ ለእስራኤልም ልጆች መጠጊያ ይሆናል » (ኢዩ.4:16)::*

*«ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፣ ፀሐይም እንደ ማቅ ጠጉር ጥቁር ሆነ፣ ጨረቃም በሞላው እንደ ደም ሆነ፣ በለስም በብርቱ ንፋስ ተናውጣ ቃሪያዋን ፍሬ እንደምትጥል የሰማይ ከዋክብት ወደ ምድር ወደቁ፣ ሰማይም እንደ መፅሐፍ ተጠቅልሎ አለፈ:: ተራራዎችና ደሴቶችም ሁሉ ከስፍራቸው ተወሰዱ:: የምድር ነገስታትና መኳንንት ሻለቃዎችም ባለፀጋዎችም ሐይለኛዎችም ባሪያዎችም ጌቶችም ሁሉ በዋሾችና በተራራዎች አለቶች ተሰወሩ:: ተራራዎችና አለቶችንም በላያችን ውደቁ፣ በዙፋኑም ከተቀመጠው ፊት ከበጉም ቁጣ ሰውሩን፣ ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቷልና፣ ማንስ ሊቆም ይችላል አሏቸው» (ራዕ.6:12-17 )::*

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ግልጽና ለመረዳት የሚቻሉ ቀላል ስለሆኑ ሌላ መጨመር አስፈላጊ አይደለም::

በአሕዘብ ፍርድ ጊዜ ጌታ ልዩነት ማድረጉ ግልጽ ነው:: እርሱ «እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል» *(ማቴ.25:32)*:: ሰዎች ከየትኛው ክፍል እንደሚሆኑ የሚወስናቸው በእግዚአብሔር ምርጦች ሕዝብ ላይ ባላቸው አቋም ነው:: ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ምህረት የፍርዱ መለኪያ ነው:: ለእስራኤል ምህረትን ያደረጉና አይሁድን በስደታቸው ጊዜ የረዷቸው ሕዝቦች ስለ «ታናናሾቹ ወንድሞቹ» ከጻድቁ ፈራጅ ምህረትን ይቀበላሉ:: በእግዚአብሔር አብ የተባረኩ ይሆናሉ፣ ወደ መሲሁ የሰላም መንግስት እንዲገቡ ይፈቅድላቸዋል *(ማቴ.25:34)*:: ይህም የሚሆንበት ምክንያት «የሚምሩ ብፁአን ናቸውና ይማራሉ» ተብሎ ስለ ተጻፈ ነው *(ማቴ.5:7)*:: «ምህረትም በፍርድ ላይ ይመካልና» *(ያዕ.2:13)* ነገር ግን ይህ ወዲያውኑ ይድናሉ ማለት አይደለም:: ይህ ከሆነ በመልካም ሥራ ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት ይቻላል ማለት ነው:: ይህ ከጥያቄ ውጪ የሆነና ደህንነት በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የሆነውን የአዲስ ኪዳን መልእክትንና እርሱ በግልጽና በማያሻማ መንገድ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፣ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ብሎ ያተመውን ቃል የሚቃረን ነው *(ዮሐ.14:6፤ ሮሜ.3:21-28)*:: ሆኖም ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት የተፈቀደላቸው በሺው የሰላም ዓመታት ጊዜ ውስጥ ንስሐ የመግባትና ወደ መሲሁ የመመለስ ዕድል አላቸው:: ማንኛውም ሰው ምህረት በማድረጋቸው ንጉሡ ከባረካቸው ጭምር ንስሐ መግባት አለበት::

እስራኤልን የጠሉትና ንጉሡንም መጥላታቸውን የገለጹት ሕዝቦች ሁሉ ወዲያውኑ «ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው ወደ ዘላለም እሳት» ይጣላሉ *(ማቴ.25:41)*:: በማዳን ታሪክ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ከክርስቶስ ዳግም መምጣት ቀጥሎ ዝቅ ብሎ ወደ ታች ወደ ዘላለም ፍርድ የሚወርደው የቀጭኑ ሰማያዊ መስመር ፍቺ ይህ ነው::

«ከበጎቹ» ከሆኑትና፣ ወደ መሲሁ መንግስት እንዲገቡ ከተፈቀደላቸው በስተቀር ያልዳኑት የዓለም ሕዝቦች በእግዚአብሔር የመዋጀት ዕቅድ ወደ ፊት ቦታ የላቸውም:: ምክንያቱም የክርስቶስን ተቃዋሚ የተከተሉና ያመለኩ፣ እግዚአብሔርን የካዱና ጠላቱ የሆኑ ስለሆኑ የሚጠብቃቸው አስፈሪው ፍርድ ብቻ ነው *(ራዕ.13:8፤ ሮሜ.1:28-32)*:: ማንኛውም ሰው ያለፈውንና የአሁኑን የዓለምን ሁኔታ በትኩረት የሚመለከት ከሆነ የዓለም ሕዝቦች ወደዚህ እያመሩ እንዳሉ ለመረዳት አያደግተውም:: በግልጽና ያለ ጥርጥር ወደታች ማለትም ወደ መቅሰፍት፣ መደምሰስ፣ ፍርድና ወደ ዘላለም ጥፋት እያሽቆለቆሉ ናቸው::

## 3. የኢየሱስ ክርስቶስ ለእስራኤል ሕዝብ መመለስ

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመለስ ለእግዚአብሔር ምርጦች ሕዝብ ንጉሳቸውና መሲህ በመሆን ይመጣል:: እስራኤል እስከዚህ ቀን ድረስ ንጉሷን ያልተቀበለች ብትሆንም ይህ ሁኔታ እስከ መጨረሻው ድረስ የሚቀጥል ሆኖ እንደማይቀር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: አዳኙ (ጌታ ኢየሱስ) በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ የሕዝብ መሪዎች ለነበሩት ለጸሐፍትና ለፈሪሳውያን እንዲህ በማለት ነግሮአቸው ነበር:: *«እላችኋለሁና በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም» (ማቴ.23:39)::*

በዚያን ጊዜ የሕዝቡ መሪዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መሲህ አድርገው አልተቀበሉትም ነበር:: *በነቢዩ (ኢሳያስ 9:16)* «ይህን ሕዝብ የሚመሩ ያስቷቸዋል፣ ተመሪዎችም ይጠፋሉ::» ተብሎ ተነግሯልና:: ስለሆነም መላ ሕዝቡን ለሁለት ሺህ ዓመታት ደምና ለቅሶ ለተሞላበት መከራ ዳረጉት:: የክርስቶስ ተቃዋሚ በመጨረሻዎቹ ቀናት የሚያመጣው ታላቁ መከራ ለእስራኤል ሕዝብ አሰቃቂ የሆነ የሀዘንና የስደት ጊዜ ይሆንባቸዋል:: ከእያንዳንዱ ነገድ 12,000 ከአስራ ሁለቱ ነገድ የሆኑት 144.000 ብቻ ታላቁን መከራና ስቃይ ይቋቋሙታል:: *(ራዕ.7:4-8)* ሊቋቋሙት የሚችሉት በአንድ ምክንያት ብቻ ነው::ምክንያቱም እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ*(ራዕ.7:2-4)* ከጠላቶቻቸው





የተጠበቁ እንዲሆኑ በግንባራቸው ላይ ስላተመባቸው ነው *(ራዕ.7:3 ፤ሕዝ.9:4-6)*:: እንደ *ዘካ.13:8* መሠረት በመጨረሻዎቹ ቀናት ከእስራኤል ሕዝብ አንድ ሦስተኛው ብቻ የሚቀሩና የጌታችንን ስም የሚጠሩ ይሆናሉ:: እነርሱም ወደ እርሱ ይጮኻሉ፣ ጌታም ይመልስላቸውና

*«እኔም ይህ ሕዝቤ ነው እላለሁ፣ እርሱም እግዚአብሔር አምላኬ ነው (ዘካ.13:9)»* ይላል:: እስራኤል ወደ ፊት ካለባት ከፍተኛ ችግር ባሻገር መጪውን መሲህ ለመገናኘት ክፍ እያለች ነው::

በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽዓት በተለያዩ ሕዝቦች ላይ (በቤተ ክርስቲያን፣ በእስራኤልና በዓለም ሕዝቦች) የተለያዩ ሁኔታዎች እንደሚፈጥር ጠቅሰናል:: የእርሱ መመለስ ለዓለም ሕዝቦች ለፍርድ ሲሆን ለእስራኤል ሕዝብ ግን ለመጨረሻና ለዘላለም ሊያድናቸው መሲህ ሆኖ ይመጣላቸዋል::

ጌታ ሲመለስ «በኢየሩሳሌም ላይ የሚመጡትን አሕዛብ ሁሉ ለማጥፋት» ይመጣል (*ዘካ.12:9*):: በዚያኑ ጊዜ «በዳዊት ቤት ላይ፣ በኢየሩሳሌምም በሚኖሩት ላይ የሞገስንና የልመናን መንፈስ» ያፈስስላቸውል *(ዘካ.12:10)*:: ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመለሰው አንድ ጊዜ ብቻ ስለሆነ በማዳን ታሪክ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ይህን የሚያመለክተው አረንጓዴና ቡናማ መስመር አንድ ቀጥ ያለ መስመር ብቻ ነው::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ በሚመለስበት ጊዜ የሚገለጸው በታላቅ ክብር ነው:: ይህ ሁኔታ ለእስራኤል ለብዙ ሺህ ዓመታት ቃል ኪዳን ስለተገባለቸው መሲህ ተስፋ መፈጸም የሚሆን ብቻ አይደለም:: የመንቀጥቀጥና የድንጋጤም ጊዜ ነው የሚሆንባቸው:: ምክንያቱም «የወጉትንና» በመስቀል ላይ «የቸነከሩትን» ስለሚለያዩት ነው:: «የምድር ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ» *(ራዕ.1:7)*:: በዚህ ጥቅስና *(በማቴ.24:29-31)* ላይ «ፍዩል» (Phule) የሚለውን የግሪክ ቃል እናገኛለን ትርጉሙም የምድር ነገዶች፣ ወይም ወገኖች ማለት ነው::

በእስራኤል ምድርና በመላ የዓለም ሀገሮች ተበታትነው ያሉትን የእስራኤልን ትውልዶችን የሚያመለክት ነው:: በዕብራይስጥ ቋንቋ መሬትን ኧርዝ (Eretz) ይሏታል ትርጉሙም:- ምድር ማለት ነው:: ኤሬትስ እስራኤል ማለት እስራኤል ምድር ማለት ነው:: ስለዚህም *(ራዕ.1:7)* የሚያመለክተው በመላ ዓለም ተበታትነው ያሉትን አስራ ሁለቱን ነገዶችና በእስራኤል ምድር ያሉትን አስራ ሁለቱን ነገዶች ነው:: የሚመጣው መሲህ በመስቀል ላይ የተሰቀለው የዓለም አዳኝ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ማንም ከእነርሱ የገመተ አልኖረም:: ሕዝቦች ሁሉ እርሱን በጲላጦስ ፊት ካዱት፣ *(ሐሥ.3:14-15)* «ከቄሳር በስተቀር ንጉስ የለንም» (*ዮሐ.19:15*):: ብለው መሪዎቻቸው

በጮኹ ጊዜ እርሱ ገዢያቸው እንዳልሆነ በመቁጠር መካዳቸው ነበር *(ሉቃ.19:14)* ለብዙ ጊዜ በግልጽ የካዱትን ያከብሩታል፣ ይገዙላታል:: ይህ ግንዛቤ መላ እስራኤልን ከመሪዎቻቸው ጀምሮ እስከ ተራው ሕዝብ ድረስ ወደ እውነተኛ ንስሐ ያመጣቸዋል::

*«ሰውም ለአንድያ ልጁ እንደሚያለቅስ፣ ያለቅሱለታል፣ ለውም ለበኩር ልጁ እንደሚያዝን በመራራ ኃዘን ያዝኑለታል» (ዘካ.12:10)::*

ልጅ የሞተበት በተለይም የበኩር ልጅ የሞተበት ማንኛውም ሰው ቤተሰብ ስለ ልጁ በብርቱ እንደሚያለቅሱና እንደሚያዝኑ ይታወቃል:: የእስራኤል ሕዝብ በመጨረሻው ጌታ ኢየሱስ መሲአቸው መሆኑን ሲገነዘቡ የሚያለቅሱትና የሚያዝኑት ልክ እንደዚሁ ነው:: መስስ ብለው ወደ ኋላ ሲመለከቱ ከእርሱ ርቀው ከመንገድ ወጥተው በራሳቸው መንገድ መሔዳቸው ተረድተው ሲያዝኑ መከራ ተቀባዩ ስለ ሆነው አገልጋይ የሚናገረው ታላቁ *የኢሳ.53:1-12* የንስሃ ዝማሬያቸው ይሆናል:: ነቢዩ ዘካርያስ እስራኤል መሲሁን በሚቀበሉበት ጊዜ የሚገቡትን ንስሐና ሐዘን በሚከተሉት ቃላት ገልጸዋል:: (ኢሳ. 53:6) በቃል ኪዳን የመጀመሪያ ነበሩ:: እሁን ግን የመጨረሻዎቹ ሆነዋል:: *(ማቴ.19:30፣ 20:16)*:: ነቢዩ ዘካርያስ እስራኤልን መሲሁን በምትቀበልበት ጊዜ የሚገቡትን ንስሃና ሐዘንን በሚከተሉት ቃላት ገልጾታል::

*«ምድሪቱም ታለቅሳለች፣ እያንዳንዱ ወገን ለብቻው፣ የዳዊት ቤት ወገን ለብቻቸው፣ሴቶቻቸውም ለብቻቸው፣ የናታን ቤት ወገን ለብቻቸው፣ ሴቶቻቸውም ለብቻቸው፣የሌዊ ቤት ለብቻቸው፣ ሴቶቻቸውም ለብቻቸው፣ የሰሜኢ ወገን ለብቻቸው፣ ሴቶቻቸውም ለብቻቸው፣ የቀሩት ወገኖች ሁሉ እያንዳንዱ ወገን ለብቻቸው ያለቅሳሉ» (ዘካ.12:12-14)::*

*ማቴ.24:30* በእስራኤል ምድር የሚኖሩት ነገዶች ሁሉ እንደሚያለቅሱና እንደሚያዝኑ ይናገራል:: መጽሐፍ ቅዱስ *በዘካ.12:12-14* ባለው ክፍል ስለ አንድ ምክንያት በተለይ ሴቶች እንደሚያለቅሱና እንደሚያዝኑ በማጠንከር ይናገራል:: ፈርሃ እግዚአብሔር ያላቸው ሴቶች በተለይም ከይሁዳ ነገድ የሆኑት በሚያረግዙበት ጊዜ የመሲሁ እናት የመሆን ዕድል እንዳላቸው ማሰት መሲሁ ከእነርሱ እንደሚወለድ ይገምቱ ነበር የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን ልጅ መሲህ መሆኑን ባለመገንዘባቸውና ባለመቀበላቸው ምክንያት ወደ ፊት ገና ይወለዳል ብለው ይጠብቃሉ:: ዛሬም ቢሆን መሲሁ በሥጋ እንደሚመጣ ሃይማኖታውያን በሆኑት በአይሁዶች ዘንድ የታወቀ ነገር ነው:: አንድ ጊዜ አንድ አይሁዳዊ እንድ እርጉዝ ሴት ብዙ ሰዎች በተሳፈሩበት እውቶቡስ ውስጥ ስትገባ የሚያደርጉትን ነገረኝ ሃይማኖቱኛ





አይሁድ በዕድሜ የገፉ ቢሆን እንኳን ተነስቶ መቀመጫ ይሰጧታል:: በዕድሜ ወጣት በመሆኗና መቆም እንደምትችል ራሷን አድርጋ በመገመት ለሰውየው አክብሮት በመስጠት እንቢ ብትል እንኳን በዕድሜ የገፋው ሰው በመነሳት «እባክሽን ተቀመጭ በማህጸንሽ የተሸከምሽው መሲሁ ሲሆን ይችላል:: በፊቱ ልነሳና ልቁም» ይላታል:: በዚህ ስለ መሲሁ ስላላቸው ጥበቃ ልንስቅ እንችል ይሆናል:: እኛ ግን ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ከንጉስ ዳዊት ዘር የሆነችው ማርያም መሲሁን መውለድዋን እናውቃለን *(ሉቃ.2:1-14፤ ገላ.4:4፤ ሮሜ.1:3፤ 2ጢሞ.2:8)*:: የእስራኤል ሕዝብ መሲሁን እንዴት በትኩረት እንደሚጠብቁ ይህ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመለስ ለመላው እስራኤል ከፍተኛ ሀዘን እንደሚሆንባቸው ግልጽ ነው:: ምክንያቱም የሚጠብቁት መሲህ ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት መጥቷልና:: የእስራኤል ሕዝብ እሁን ግን ያንን የመሲሁን የመወለድ ታምር ባለመቀበላቸው፣ እርሱ ሲመጣ እርሱ መሆኑን ሲያዩና ሲገነዘቡ፣ ያዝናሉ መራራ ለቅሶም ያለቅሳሉ::

ሕዝቡ ንጉሡንና መሲሁን መራራ በሆነ ሀዘንና በእውነተኛ ንስሐ ወደ እርሱ በመመለስ ሲቀበሉት የፀጋ ሰዓት ይመጣላቸዋል:: ከዚህ በኋላ ታማኙ ጌታ ኃጢአታቸውን ይደመስስላቸውና *(ሮሜ.11:27)* በመላ የእስራኤል ቤት ላይ ምህረትን ሲያፈስላቸው (ሕዝ. 39:25) መላ እስራኤል ይድናሉ (ሕዝ. 39:29) የዳኑት *(ሮሜ.11:26)* የእግዚአብሔር ሕዝቦች በንጉሳቸው መሪነት ወደ መሲሁ የሰላም መንግስት ይገቡና ለሺህ ዓመት የእግዚአብሔር የወንጌል መልእክተኞች ይሆናሉ::
ስለዚህ ወደፊት እስራኤላውያን በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ የተከበረ ጊዜ አላቸው:: አንዳንዶች እንደሚያምኑት ጌታ ሕዝቡን የጣላቸው አይደለም:: ለጥቂት ጊዜ ሕዝቡን ትቷቸው ነበር:: ምክንያቱም በእግዚአብሔር ልጅ አላመኑም ነበርና:: በአጭር ቀናት ውስጥ ስለ መጨረሻዎቹ ቀናት የተነገሩት ትንቢቶች በዓይናችን የሚፈጸሙ ይሆናሉ:: የእስራኤል ሕዝብ እንደገና ወደ ቅድስት ምድራቸው እየተሰበሰቡ ናቸው:: እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የሚዋጅበትና የሚቀበልበት ጊዜ እየቀረበ ነው:: እስራኤል ወደ መዳኗ በከፍተኛ ደረጃ እየቀረበች ነው::

**የወደፊቱ ሶስቱ የሰው ዘር ክፍሎች:-**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **ቤተ ክርስቲያን** | - | **ወደ ቤቷ መሔድ** | - | **ክብሯ** | ***(1ኛ ተሰ.4:17 ዮሐ.14:3)*** |
| **እስራኤል** | - | **ወደ ከፍታዋ መሔድ** | - | **መሲሁን ለመገናኘት** | **(ሮሜ 11:26 ኢሳ.59:20)** |
| **አህዛብ** | - | **ውርደት** | - | **ለፍርድ** | **(25:41)** |


## *የሦስቱ የዋናዎቹ የማዳን መስመሮች ትይይዝ በመዋጀት ታሪክ ፍጻሜ ላይ*

# የመሲሁ የሰላም መንግስት

የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር ከእግዚአብሔር የተቀበለው ታላቅ ራዕይ ዳን. 2:1-45 ስለ አራቱ መንግስታት፣ ስለ ባቢሎን፣ ስለሜዶንና ፋርስ፣ ስለግሪክና ስለሮም የሚናገረው በተሰጠው በዘላለማዊና በማይደመሰሰው መንግስት ተስፋ የሚደመደም ነው::

*«በእነዚያም ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሳል፣ ለሌላ ሕዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል፣ እነዚያንም መንግሥታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች፣ ታጠፋቸውማለች፣ ለዘላለምም ትቆማለች» (ዳን.2:44)::*

በዚህ ቦታ መጽሐፍ ቅዱስ የሚነገርለት መንግስት ገና ወደ ፊት የሚመጣ ነው:: እንዳለፉት እንደዚህ ምድር ነገሥታት በሰው ሳይሆን ጊዜው ሲደርስ በራሱ «በሰማይ አምላክ» የሚመሠረት ይሆናል:: ይህ ጊዜ የሚሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «በኃይልና በታላቅ ክብር» ሲመጣ መሆኑን በማዳን ታሪክ ተምረናል:: ጌታ ለፍርድ በሚገለጥበት ጊዜ የምድር መንግስታት ሁሉ፣ አመጽና ኃጢአት ለዘላለም ከምድረ ገጽ ላይ ይጠፋሉ::








በክርስቶስ ተቃዋሚና በአሰቃቂ አስተዳደሩ መደምሰስ ለብዙ ሺህ ዓመታት የቆየው የአሕዛብ ዘመን ያበቃል ያከትማል *(ሉቃ.21:24)*: የአመጽ ጀማሪና የመጀመሪያ አመጸኛ የሆነው «ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ» (ራዕ. 12:9) የተባለው በዓለም የማሳትና የማጥፋት ሥራውን ለአንድ ሺህ ዓመታት አይሠራም:: አሕዛብን እንዳያስት ለይጣን ለሺህ ዓመት ታስሮ ወደ ጥልቁ ይጣላል *(ራዕ.20:1-3)*:

ስለሆነም ዓለም ሊመጣ ላለው ለመጨረሻው መንግስትና ለማዳን ታሪክ የተዘጋጀች ትሆናለች *(ራዕ.19:19-21)*: ይህ መንግስት የመሲሁ «የሰላም መንግስት» ወይም «የሺህ ዓመት መንግስት» በመባል ይታወቃል:: በስሙ እንደተጠቀሰው ይህን መንግስት የሚመሠርተው የእስራኤል ሕዝብ መሲህ በሆነው በእውነተኛው የሰላም አለቃ በሆነው እንጂ በሌላ ሲሆን አይችልም:: *(2ሳሙ.7:1-29፤ ሉቃ.1:31-35)* ይህ መንግስት በምድር ላይ የሚቆየው ለሺህ ዓመታት ነው *(ራዕ.20:1-10)*: ነገር ግን የእግዚአብሔር መንግስት (የሰማይ መንግስት) ለዘላለም የጸና ሆኖ ይመሠረታል *(ራዕ.11:15፤ 22:5)*:

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ተስፋ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ ግልጽ የሆነውን የእግዚአብሔር መንግስት በዚህ ምድር ላይ ይመሠርታል በሚል ላይ ያረፈ ነበር:: አስቀድሞ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተነገረውና በማዳን ታሪክ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ እንደሚታየው የሺህን ዓመት መንግስት ወደ ዓለም ፍጻሜ የሚመራው የማዳን ታሪክ የተያያዘ ነው:: ሆኖም ይህ የሺው ዓመት መንግስት ከሰማይ መንግስት ጋር አንድ አድርጎ ማየት አያስፈልግም:: ነገር ግን ይህ መንግስት በምድር ላይ የእግዚአብሔር አገዛዝ የሆነ ነው:: በዚህ መንግስት የእስራኤል ህዝብ፣ አሕዘብና ቤተ ክርስቲያን የራሳቸው የሆነ ሥራ አላቸው::

በዚህ ላይ ተመሥርተን እንደ እኛ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓገም እስከ ሺሁ ዓመት መንግስት ዓመት የማይፈጸሙትን ብዙ ትንቢቶች እንመርምር::

## 1. እስራኤል - የመላ ዓለም በረከት

ክብዙ ሺህ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለፈርዖን «እስራኤል የበኩር ልጄ ነው፣ ይገዛልኝ ዘንድ ልጄን ልቀቅ አልሁህ» በማለት ተናግሮት ነበር *(ዘፀ.4:22-23)*: የበኩር ልጅ የሆነው እስራኤል ክብዙ ዓመታት በፊት ከግብፃውያን የባርነት ቀንበር የዳኑ ብቻ አይደለም:: ነገር ግን በዓለም ሕዝብ መካከል ከመበታተንና ከስደትም ነፃ የወጡ ይሆናሉ *(ዘፀ.14:30)*: ጌታ ሲመለስ

የእስራኤል ሕዝብ ሲድኑና ጌታን ሲቀበል እስራኤል የአሕዛብ ራስ ትሆናለች *(ዘዳ.28:13)*፡፡ በመሲሁ የሰላም መንግስት ጊዜ እስራኤል ለዓለም በረከት ትሆናለች፡፡ በንጉሡ አገልግሎት ዓለምን ወደ ሰላም የምትመራ ትሆናለች፡፡ (ኢሳ.19:24) ጌታ በመንግስቱ ያላቸውን መብትና ሥራ እንዲህ በማለት አውጆላቸዋል፡፡

*«እስራኤል ሆይ፣ አንተ ባርያዬ ነህ በአንተ እከብራለሁ» (ኢሳ.49:3)*

*«በምድር አሕዘብ ሁሉ መካከል ለክበረ ለምና ለምስጋና አደርጋችኋለሁ» (ሶፎ.3:20)፡፡*

*«ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ፣ እናንተም የካህናት መንግስት የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ» (ዘፀ.19:5-6)፡፡*

ስለዚህ በሺሁ ዓመት መንግስት ጊዜ በአሕዛብ መካከል መሪ ትሆናለች፡፡ በቅድስናና በመንፈሳዊ መንገድ አገልጋይ በመሆን ለመላ ዓለም ታላቅ በረከት ትሆናለች፡፡ *(ዘፍ.12:3፤ 26:4፤ 28:14)*

## እስራኤል - ለጌታ የመልእክተኛ ህዝብ

እስራኤል ወደ ምድሯ ስትመለስ፣ በመሲሁ ዘመን እውነተኛ ተልዕኮዋንና ወንጌል በመላ ዓለም ማሰራጨቷን ትፈጽማለች፡፡

*«ከጽዮን ሕግ፣ ከኢየሩሳሌምም የእግዚአብሔር ቃል ይወጣልና» (ሚክ.4:2)፡፡*

*«ምስጋናዬን እንዲናገሩ ለእኔ የፈጠርሁት ሕዝብ» (ኢሳ.43:21)፡፡*

ጌታ ሕዝቡን ቃሉን እንዲያውጁና ወንጌል በዓለም ሁሉ እንዲሰብኩ ይጠቀምባቸዋል፡፡ ያም ታላቅ ውጤት ያለው ይሆናል፡፡ ምክንያቱም *«በዚያ ዘመን ከአሕዛብ ቋንቋ ሁሉ አሥር ሰዎች የአንዱን የአይሁዳዊ ሰው ልብሰ ዘርፍ ይዘው፣ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር እንዳለ ሰምተናልና ከእናንተ ጋር እንሂድ ይሉታልና»* (ዘካ. 8:23)፡፡

እንደ ተርሴሱ ተወላጅ እንደ ሳዖል ይሆናል፡፡ ከተለወጠ በኋላ ጳውሎስ የአሕዛብ ሐዋርያ ሆነ፡፡ ወንጌልን በመስበክ፣ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ወደ ጌታ ኢየሱስ በመመለስና አብያተ ክርስቲያናትን በያለበት በማቋቋም የሮምን መንግስት የገለባበጠ ሆነ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በሺሁ ዓመት መንግስት ጊዜ የተለወጠውና የዳነው እስራኤል ወንጌል የሚሰብክና ብዙ አሕዛብን ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመልስ ይሆናል፡፡ በዚህ አኳኋን እስራኤል «ከእግዚአብሔር እንደሚወርድ





ጠል፣ በሣር ላይ እንደሚወርድ ካፊያ» በምድር ላይ በረከት ትሆናለች *(ሚክ.5:7፤ ኢሳ.19:24፤ዘካ.8:13)*፡፡ ከዚህ በኋላ ማንኛውም ሰው *በዮሐ.4:22 «መዳን ከአይሁድ ነው»* የሚለውን በእውነት ግልፅና ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 2. አሕዛብ – አብረው የመንግሥቱ ወራሾች መሆናቸው

«የክርስቶስ ዳግም መምጣት» በሚለው ምዕራፍ ውስጥ በሺው ዘመን መንግስት ጥቂት አሕዛብ ብቻ ወደ መንግስቱ መግባታቸውን ተመልክተናል *(ማቴ.25:31-40)*፡፡ ለማስታወስ ያህል የእግዚአብሔር ሕዝብ ለሆኑት ለእስራኤል ምህረት ያደረጉት በአሕዛብ ፍርድ ጊዜ ምህረትን አግኝቶ እንደ ንጉሡ ቃል «የተባረኩ» ሆነው ወደ ሺሁ ዓመት መንግስት እንዲገቡ የተፈቀደላቸው መሆናቸውን ተመልክተናል፡፡ እንደ ገና ጠንከር አድርገን መናገር የሚያስፈልገን ነገር ቢኖር «የተባረኩት» ምህረትን ስላደረጉ ብቻ የማይድኑ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህ ከሆነ የአዳኙ ለዓለም ኃጢአት በመስቀል ላይ መሞቱ ከንቱ ነው ማለት ይሆናል፡፡ በእውነትና በትክክል ንስሐ በመግባት በተፈጸመው በንጉሡ የማዳን ሥራ ማመን አለባቸው፡፡ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ ይህ በትክክል እንደሚከናወን ይመሰክራሉ፡፡ በሺሁ ዓመት መንግስት ኃይለኛ በሆነው የወንጌል መልእክት ብዙ አሕዛብ ወደ ኢየሩሳሌም «የሠራዊትን ጌታ እግዚአብሔርን» ለመፈለግ ተሰብስበው ይመጣሉ *(ዘካ.8:22)*፡፡ በሙሉ ልባቸው ወደ ጌታ ይመለሳሉ፡፡ *(ዘካ.2:11)* ክርስቶስንም ጌታቸውና ንጉሣቸው አድርገው በመቀበል (ኢሳ. 19:19-20) ራሳቸውን ለእርሱ ብቻ ያስገዛሉ፡፡ መላ አሶር፣ መላ ግብፅና መላ እስራኤል ይመጣሉ (ኢሳ.19: 21-25)፡፡ ጌታም እነርሱን በመቀበልና በመባረክ የሚከተለውን ይላቸዋል፡፡

*«ሕዝቤ ግብፅ የእጁም ሥራ አሦር ርስቴም እስራኤል የተባረከ ይሁን» (ኢሳ.19:25)፡፡*

እነዚህና ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሺሁ ዓመት መንግስት ጊዜ ከልባቸው ንስሃ የሚገቡትንና ጌታን የሚፈልጉትን ጌታ የሚቀበላቸው መሆኑን ግልጽ ያደርጉታል፡፡ እውነተኛ ወራሽ ከሆኑት ከእስራኤል ጋር የመሲሁን መንግስት አብረው የሚወርሉ ይሆናሉ *(ኢሳ.19:25)*፡፡ ጌታ ኢየሱስ በአሕዛብ ፍርድ ጊዜ ለመንግስቱ ለተወሰኑት የሚያውጀውን ቃል

*«እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግስት ውረሱ » (ማቴ.25:34)፡፡*

## 3. ኢየሱስ ክርስቶስ - የመላው ዓለም ንጉስ

በዚህ ምድር ላይ የሺው ዓመት መንግስት በእግዚአብሔር ልጅ ሲመሠረት፣ በእርሱ ብዙ የመጽሐፍ ክፍሎች የተፈጸሙ ይሆናሉ::

*«እኔ ግን ንጉሤን ሾምሁ፣ በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ» (መዝ.2:6)::*

*«እግዚአብሔር ነገሠ፣ ምድር ሐሴትን ታድርግ፣ ብዙ ደሴቶችም ደስ ይበላቸው» (መዝ.97:1)::*

*«አቤቱ፣ ሥራህ ሁሉ ያመሰግኑሀል፣ ቅዱሳንህም ይባርኩሀል፣ የመንግሰትህን ክብር ይናገራሉ፣ ኃይልህንም ይነጋገራሉ፣ ለሰው ልጆች ኃይልህን የመንግሰትህን ግርማ ክብር ያስታውቁ ዘንድ:: መንግስትህ የዘላለም መንግስት ናት፣ ግዛትህም ለልጅ ልጅ ነው» (መዝ.145:10-13)::*

እነዚህና ሌሎች የብሉይና የአዲስ ኪዳን ክፍሎች በሺሁ ዓመት መንግስት ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉስ ሆኖ እንደሚገዛ ስላለው እውነት ይመስክራሉ:: ከብዙ ጊዜ በፊት ነቢዩ ዳንኤል የእግዚአብሔር ልጅ ከአባቱ መንግስትን መቀበሉን የሚያሳየውን ታላቅ ራዕይ ተመልክቷል:: ራዕዩም

*«በሌሊት ራዕይ አየሁ፣ እነሆም፣ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ፣ ወደ ፊቱም አቀረቡት:: ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩም ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግስትም ተሰጠው፣ ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፣ መንግሰቱም የማይጠፋ ነው» የሚል ነው (ዳን.7:13-14)::*

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በታወጀበት ጊዜ እንኳን ተስፋ የተሰጠው የእግዚአብሔር ልጅ የሚመጣው ንጉስ እንደሚሆን ነበር:: *«ታላቅ ይሆናል፣ የልዑል ልጅም ይባላል፣ ጌታ አምላክም የአባቱን ዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፣ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሳል፣ ለመንግስቱም መጨረሻ የለውም»* (ሉቃ.1:32-33)::

ነቢዩ ኢሳይያስ፣ የሚመጣውን ገዢ፣ የተገነዘበው አንድ ቀን ይህን ዓለም በመለኮታዊ ኃይልና ስልጣን የሚገዛ አድርጎ ነበር::

*«ሕፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፣አለቅነትም ጫንቃው ላይ ይሆናል፣ ስሙም ድንቅ መካር፣ኃያል አምላክ፣የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል:: ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው*





*ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሰቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፣ ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም:: የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል» (ኢሳ.9:6-7)*

ስለሆነም የኢየሱስ ክርስቶስ መንግስት ሁሉን ያቀፈና ያጠቃለለ ይሆናል:: «እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል «ከባሕር እስከ ባሕር፣ ከወንዝ (ኤፍራጥስ ማለት ነው) እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ይገዛል» *(መዝ.72:8)* ጌታ በኢየሩሳለም ብቻ ሳይሆን *(ኢሳ.24:23)* «በምድር ሁሉ ላይም» ንጉስ ይሆናል *(ዘካ.14:9)*:: መንግስቱ በምድር ላይ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በመላ ዓለም እንዴት እንደሚሰፋና እንደሚሞላ የሚገልጽ ይሆናል::

እነዚህን ጥቂት ጥቅሶች ስንመረምር፣ ወዲያውኑ የምንገነዘበው ነገር ቢኖር የሚመጣው መሲህ፣ በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጠውና በታላቁ የስላም አገዛዝ የሚገዛው ገና እንደሆነና እንዳልተፈጸመ ነው:: የተስፋው ንጉስ እስከ አሁን የተጠላ ንጉስ ነው:: ካለፈው ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የሕዝብ ጩኸት «ይህ በላያችን ሊነግስ እንወድድም» «ከቄሳር በስተቀር ንጉስ የለንም» የሚል ነው:: *(ሉቃ.19:14፤ ዮሐ.19:15)*

በአሁኑ ጊዜ ዓለም በሩህሩሁና በጻድቁ «የነገሥታት ንጉስና የጌቶች ጌታ» በሆነው አገዛዝ ስር አይደለችም (*ራዕ.19:16:*) ነገር ግን ሊመጣ ባለው በፀረ ክርስቶስና በገዢዎቹ እጥፊ በሆኑት የዓለማት ኃይላት ሥር ናት::. ሆኖም በሺሁ ዓመታት መንግስት በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረው አስደናቂና ክብር የተሞላበት የክርስቶስ ኢየሱስ አገዛዙም በምድር ላይ የተፈጸመ ይሆናል:: «በትረ መንግስት ከይሁዳ አይጠፋም፣ የገዢም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል» የሚለውና (*ዘፍ.49:10)* «በስማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ» የሚለው በእውነት የተፈጸመ ይሆናል:: *(ፊል.2:10-11)* የሰማይ ኃይላትም በደስታ በመሞላት «ሃሌ ሉያ ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላካችን ነግሶዓልና» ይላል (*ራዕ.19:6)*::

## 4. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን – ከንጉሡ ጋር የምትገዛ

በሺው ዘመን መንግስት ቤተ ክርስቲያን የት ናት? ብለን እንጠይቅ:: ከእስራኤልና ከአሕዛብ ጎን በመጪው ሺህ ዓመት ቤተ ክርስቲያን የተለየ ሥራ አላት:: መለስ ብለን እንደገና በትኩረት እንመልከት:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን «የክርስቶስ አካል» ናት:: ማንኛውም ዳግም የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ የቤተ ክርስቲያን አባል ነው (*1ቆሮ.12:27*): ቤተ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን ራስ ከሆነው ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የማትለይ ከእርሱ ጋር የተያያዘች መንፈሳዊ አካል ናት (*ቆላ.1:18*): የመነጠቅ ጊዜ ሲመጣ፣ የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ጉዞዋን የፈጸመች በመሆን «ከጌታ ጋር ሁልጊዜ» ትሆናለች (*1ተሰ.4:17*): ራሱን ጌታን በመምሰል አስደናቂ ወደ ሆነው ሰማያዊ ክብር የተለወጠች ትሆናለች::የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ከአባሉቹ (ዳግም ከተወለዱት አማኞቹ ጋር ለዘላለም የተባበረ ይሆናል::አባሎቹም ራስ ከሆነው ከክርስቶስ ክብር ለዘላለም ተካፋዮች ይሆናሉ::(*2ተሰ.2:14፤ቆላ.3:4፤ 1ቆሮ.1:9)*

ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ስትሆን፣ ከእርሱ ጋር ለዘላለም የምትኖር ብቻ ሳይሆን እብራ የምትገዛ ትሆናለች (*2ጢሞ.2:11-12*:) ጌታ በግልጽ «እኔ ደግሞ ድል እንደነሳሁ፣ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደ ተቀመጥሁ፣ ድል ለነሳው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጠጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ» ይላል (*ራዕ.3:21*::) ጌታ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር (ሲመለስና በደሙ ከተገዛችው ቤተ ክርስቲያን) (1ኛተስ. 3:13) በምድር ላይ መንግስቱን ሲያቋቁም አብረው ተካፋይ ይሆናሉ:: አክሊል የተሰጣቸውና የተመረጡ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው:: እነርሱም ከንጉሳቸው ጋር አብረው ይገዛሉ:: ዓለምን ሲፈርድ አብረው የሚፈርዱ ይሆናሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ በአዲስ ኪዳን ስለዚህ ነገር እንዲህ ይላል::

*«ዙፋኖችንም አየሁ፣በእነርሱም ላይ ለተቀመጡት ዳኝነት ተሰጣቸው ስለ ኢየሱስም ምስክርና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቆረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት፣ ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን ምልክቱንም በግንባራቸውና በእጆቻቸውም ላይ ያልተቀበሉትን አየሁ፣ ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ» (ራዕ.20:4::)*

ሐዋርያው ጳውሎስ «ቅዱሳን በዓለም እንደሚፈርዱ «እስረግጦ ተናግሯል (*1ቆሮ.6:2*):: ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን እባሎች ከንጉሳቸው ጋር ሆነው በሚፈርዱበት ጊዜ በመላእክት ላይም እንደሚፈርዱ ተናግሯል:: ቃሉም *«በመላእክት እንኳ እንድንፈርድ እታውቁምን» የሚል ነው (1ቆሮ.6:3::)*





እነዚህ እረፍተ ነገሮች እጅግ አስደናቂ ናቸው:: የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በእግዚእብሔር ጸጋ ከፍ መደረጓንና ያላትን ከፍተኛ ስፍራን ያመለክታሉ:: ባላት ባሕርይ በማያጠራጥር ሁኔታ የእግዚአብሔር ሕዝብ «በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ» የተባረከች ናት (*ኤፌ.1:3*):: በሌላ በኩል ደግሞ እስራኤል በምድር ያለች የእግዚአብሔር ሕዝብ ናት የምታገኘውም ምድራዊ በረከትን ነው:: (*ኢሳ.60:21*) የማንዘነጋው ነገር ቢኖር የከበሩት የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አማኞች የተለወጡና ወደ ፊትም ምድራዊ አካል ሳይሆን መንፈሳዊ፣ የከበረ ሰማያዊ እካል ያላቸው ይሆናሉ (*ፊል.3:21፤ 1ቆሮ.15:40-49*):: ስለሆነም በምድር ላይ የገጽታቸው ሁኔታ ጌታ ከትንሣኤ በኋላ ያለው ገጽታ ይሆናል:: ወደ ክብር ስለተለወጡ፣ ለሰማያዊ ዓለም የተገቡ በመሆናቸው የማይታዩ (መንፈሳዊ አካል ያላቸው) ይሆናሉ:: ጌታ ከትንሣኤው በኋላ እንዳደረገው (በመብላትና በመጠጣት ማለት ነው) በምድር ሕይወት ተካፋይ ይሆናሉ:: (ማቴ.26:29፤ ሉቃ.24:39-43፤ ዮሐ.20:27) በሌላ በኩል ደግሞ እስራኤል በሺሁ መንግስት ዘመን ለዚህ ዓለም ኑሮ የተገባች ትሆናለች:: ጌታዋንም በሥጋዋ የምታገለግል ትሆናለች:: ይህም ማለት በተፈጥሮ በሥጋና በደም ማለት ነው (ዕብ.2:14):: በሺው መንግስት ዘመን አይሁድ የከበረው ጌታ ተገዢዎች ሲሆኑ የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን እባሎች ግን ከከበረውና በዙፋን ላይ ከተቀመጠው ጌታ ጋር እብረው የሚገዙ ይሆናሉ:: (2ጢሞ.2:12፣ ማቴ.19:18)

## 5. ኢየሩሳሌም - ለዓለም የደህንነት ማዕከል

ሁልጊዜ ኢየሩሳሌም በምድር ላይ የእግዚእብሔር ዋና የዓለም ከተማ በመሆን ቆይታለች:: እግዚእብሔር ክብሩ በኢየሩሳሌም እንጂ በሌላ ከተማ እንዲቀመጥ ፈቅዶ አያውቅም:: በብሉይና በአዲስ ኪዳን «የታላቁ ንጉስ ከተማ» በተባለችው እንጂ (መዝ.(48):2፤ ማቴ.5:35)::

በነቢዩ ሕዝቅኤል ዘመን የእግዚአብሔር ክብር ከኢየሩሳሌም ተለየ:: ምክንያቱም እስራኤል ሕዝብ ንስሃ ያልገቡ በመሆናቸውና ወደ እግዚአብሔር ባለመመለሳቸው ነበር (ሕዝ.11:22-24):: ይህም ቢሆን ጌታ ከተማዋን አይጣላትም ነበር ነቢያቱ እነጋገር «ኢየሩሳሌምን ዳግመኛ ይመርጣል» (ዘካ.2:12) በኢየሩሳሌም መካከል እኖራለሁ» (ዘካ. 8:3) «እንደገና ወደ መቅደሱ» ይመጣል (ሚል.3:1፣ ሕዝ.43:1-5)::

እነዚህ ትንቢቶች በከፊል የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ኢየሩሳሌም በገባና «ቅደሱን ባነፃ» ጊዜ ተፈጽመዋል:: (ሉቃ.19:46-47) ሆኖም ገና በሙላት

አልተፈጸሙም:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኃይልና በክብር ሆኖ የሺሁ ዓመት መንግስት ለመትከል ሲመለስ፣ በዚያን ጊዜ የጌታ ክብር በኢየሩሳሌም ወደ ተሠራው አዲሱ ቤተ መቅደስ ይመለሳል:: (ሕዝ.43:1-5) የኢየሩሳሌም ጎዳናዎች በአጠቃላይ በደስታ ይሞላሉ:: ምክንያቱም ጌታ ለከተማዋ ከሰጣት በረከተቶችና ሰላም የተነሳ ይህ ይሆናል (ኤር.33:9-11):: ሕዝቡ ከትልቅ ደስታ ጋር ሐዋርያት በታላቅ ምስጋና

**«ክብሩን አይተናል»** ይላሉ:: (*ዮሐ.1:14*)

ኢየሩሳሌም በዓለም ላይ የእግዚአብሔር ዋና ከተማ ትሆናለች (መዝ.(87):3):: ምክንያቱም ጌታ በአካል በእርሷ ውስጥ ስለሚገኝ:: ከተማዋ «የቅድስና»፣ «የጽድቅና»፣ «የእምነት» ከተማ ብቻ አትሆንም (ኢሳ.1:26-27፣ 4:3-6):: ነገር ግን በሚያንጸባርቅና አስደናቂ በሆነው በእግዚአብሔር ውበት የምታንጸባርቅ ትሆናለች (ኢሳ.62:1-3):: ወደ ከተማዋ ርኩስ የሆነ ሁሉ አይገባባትም (ኢሳ.52:1፤ ዘካ.2:11):: በፈረሶች ላይ ያለው ሻኩራ ላይ እንኳን «ለእግዚአብሔር የተቀደሰ» የሚል ጽሑፍን የያዘ ይሆናል:: (ዘካ.14:20)

*«በዚያም ዘመን ኢሩሳሌምን የእግዚአብሔር ዙፋን ብለው ይጠሯታል፣ አሕዛብም ሁሉ ወደ እርስዋ ይሰበሰባሉ፣ ከእንግዲህም ወዲህ ክፉውን እልከኛ ልባቸውን ተከትለው አይሔዱም» (ኤር.3:17)::*

በሺሁ ዓመት የጌታ በምድር ላይ ተገልጾ መገኘት በአሕዛብ ላይ ትልቅ ሚና ይኖረዋል:: ምክንያቱም :-

*«ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ታላቅ ይሆናልና፣ በየስፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ፣ ንጹሕም ቁርባን ያቀርባሉ፣ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ሆኗልና፣ ይላል የሠራዊት ጌታ» ስለሚል ነው:: (ሚል.1:11)*

አህዛብ «ለእግዚአብሔር ይሰግዱ ዘንድ... በየዓመቱ» ወደ ኢየሩሳሌም ይወጣሉ:: *(ዘካ.14:16)* እርስ በእርሳቸው :-

*«ከጽዮን ሕግ፣ ከኢየሩሳሌምም የእግዚአብሔር ቃል ይወጣልና፣ ብዙዎች አሕዛብ ሔደው ኑ ወደ እግዚአብሔር ተራራ፣ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ፣ እርሱም መንገዱን ያስተምረናል፣ በፍለጋው እንሔዳለን» ይባባላሉ:: (ሚል.4:2)*

የእስራኤል ልጆችም ይህችን ከተማ ይናፍቋታል:

*«በኤፍሬም ተራሮች ላይ ያሉ ጠባቆች ተነሱ ወደ ጽዮን ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔር እንውጣ ብለው የሚጮኹበት ቀን ይመጣል» (ኤር.31:6)::*





ንጉስና መሲህ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ መገኘት የተነሳ በሺው ዘመን መንግስት ጊዜ በዚህ ምድር የእግዚአብሔር ዋና ከተማ የሆነችው ኢየሩሳሌም ለመላው ዓለም የደህንነት ማዕከል ትሆናለች:: ሰዎች ወደዚህች ከተማ በመምጣት ደህንነትን ይፈልጋሉ፣ ደህንነትንም በዚህች ከተማ ያገኛሉ:: ምክንያቱም «ሕግ ከጽዮን፣ ከኢየሩሳሌምም የእግዚአብሔር ቃል ይወጣልና»(ሚክ.4:2)

*«ስለ ጽዮን ዝም አልልም፣ ስለ እየሩሳሌምም ጸጥ አልልም ፣ጽድቅዋ እንደ ጸዳል፣ ማዳንዋም እንደሚበራ ፋና እስኪ ወጣ ድረስ» (ኢሳ.62:1)*

## 6. ጽድቅና ሰላም - የመንግሥቱ ባሕርያት

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሺሁ ዓመት መንግስት አገዛዙን ሲመሠርት ረጅምና አሰቃቂ በሆነው በሰው ዘር ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰላምና ፍትህ ያለው አገዛዝ በምድር ላይ ይሆናል:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል የእግዚአብሔር ልጅ «የጽድቅ ንጉስ» ብቻ ሳይሆን «የሰላምም ንጉስ» ነው (ዕብ.7:2):: ፍትህ የሌላቸው አገዛዝ ያከትማሉ:: ጦርነቶችና አመጸኝነት ተወግደው በመንግስቱ ታሪክ ብቻ ሆነው ይቀራሉ::

*«በዘመኑ ጽድቅ ያብባል፣ ጨረቃም እስኪያልፍ ድረስ ሰላም ብዙ ነው» (መዝ.(72):7)::*

*«ዓይኑም እንደምታይ አይፈርድም፣ ጆሮውም እንደምደትሰማ አይበይንም:: ነገር ግን ለድሆች በጽድቅ ይፈርዳል፣ ለምድርም ድሆች በቅንነት ይበይናል፣ በአፉም በትር ምድርን ይመታል፣ በከንፈሩም እስትንፋስ ክፉዎችን ይገድላል» (ኢሳ.11:3-4)::*
*«የወገቡ መታጠቂያ ጽድቅ፣ የጎኑም መቀነት ታማኝነት ይሆናል» (ኢሳ.11:5)*

### የሺሁ ዓመት ጽድቅ

ክድካማቸው የተነሳ ግብረ ገባዊነት ያላቸው ክግብ ሲያደርሱ ያልቻሉትን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች በኃይላቸው ሊመሠርቱ ያልቻሉትን ገና ቤተ ክርስቲያናትም ለመፈጸም የሞከሩትንና የደከሙበትን፣ በመሲሁና የእግዚአብሔር ሰው በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ርህራኄና ትክክለኛ አገዛዝ ስር እውን ይሆናሉ:: ለሕዝብ ሁሉ ትክክልና ፍጹም የሆነ አስተዳደር ይሆናል:: የብሉይ ኪዳን ነቢያት የእግዚአብሔር ልጅ ሲመለስ ምን እንደሚሆን አውጀዋል:: አዋጁም:-

*«እነሆ! ለዳዊት ጻድቅ ቁጥቋጥ የሚነሳበት ዘመን ይመጣል ይላል እግዚአብሔር፣እርሱም እንደ ንጉስ ይነግሳል፣ይከናወንለታልም፣በምድርም ፍርድንና*

*ጽድቅን ያደርጋል። በዘመኑም ይሁዳ ይድናል እስራኤልም ተዘልሎ ይቀመጣል፣ የሚጠራበትም ስም፦ እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ ነው (ኤር.23፡5-6)።*

ጻድቁ ንጉስ «ለችግረኞች ሕዝብ በጽድቅ ይፈርዳል፣ የድሆችንም ልጆች ያድናል፣ ክፉውንም ያዋርዳል» (መዝ.(72)፡4)። የደካሞችን ጩኸት ይሰማል፣ «ከግፍና ከጭንቀት ነፍሳቸውን ያድናል» (መዝ.72፡14)። ክፉውን ይመታል፣ «በአፉም በትር ምድርን ይመታል፣ በከንፈሩም እስትንፋስ ክፉዎችን ይገድላል» (ኢሳ.11፡4)።

*«የዋሃን ደስታቸው በእግዚአብሔር ይበዛል። በሰዎች መካከል ያሉ ችግረኞችም ሐሤትን በእስራኤል ቅዱስ ያደርጋሉ። ጨካኝ ሰው አልቆአልና፣ ፌዘኛውም ጠፍቶአልና ለኃጢአትም ያደፈጡ ሁሉ ይቆረጣሉና»* (ኢሳ.29፡19-20)።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች በሺሁ ዓመት መንግስት ኃጢአተኞች መኖራቸውንና ኃጢአተኞችም እንደሚፈረድባቸው ጭምር ያመለክታሉ (ኢሳ.65፡20) ሁልጊዜ እውነተኛ ጽድቅ በኃጢአት ላይ የመፍረድንም ነገር አጣምሮ የያዘ ነው። ሰይጣን የታሰረና ሰዎችን የማያታልል ስለሆነ በሽው ዘመን መንግስት ያለው ፍርድ ከምንጊዜም ይልቅ የጠነከረ ይሆናል (ራዕ.20፡13)። ይህ በማንኛውም መንገድ ለመበደል በሚያስብ ግለሰብ ላይ የበለጠ ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን የሚያበዛ ነው። የእውነተኛው ፍትህ ንጉስ ፍጹም የሆነ ጻድቅ ፈራጅ ይሆናል። በዚህ ዘመን በሰውና በእግዚአብሔር ላይ የሚደረገው ኃጢአት እንደ በፊቱ ሳይሆን የቀነሰ ይሆናል።

የሰማያዊ ንጉስ የአገዛዙ ሥርዓት ብለን የምንጠራው የተራራው ስብከት በዚህ ቦታ የሚነበብ ብቻ አይሆንም። (ማቴ. 5፡7-29) የፍጹም ጽድቅ የሞራል መለኪያ ይሆናል። በመሲሁ ዘመን፣ እምነት፣ ተስፋ ፍቅርና መልካምነት ከሕዝብ ሁሉ የሚፈለጉ ይሆናሉ። ይህን እውነተኛ ጽድቅ መፈጸምና ማድረግ የሚችለው አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ «የጽድቅ ንጉስ» የሆነው ብቻ ነው።

## የሺሁ ዓመት ሰላም

ቃየል አቤልን ከገደለበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ዓለም የማያቋርጥ የጦር ሜዳ ሆናለች (ዘፍ.4፡8)። ይህ በሺዎች ዓመታት የሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ያልተለወጠና አሁንም ያለ ነገር ነው። ዘለቄታ ያለው ሰላም በሕዝቦች መካከል እንዲኖር (ትጥቅን ለማስፈታት) የተደረጉ ስምምነቶች፣ የሰላም ስምምነቶችና ሌሎችም ጥረቶች ሁሉ ውጤት አልባ ሆነዋል። ክፋት የተሞላባቸው ጦርነቶችና ጥፋት አልጠፉም። በተቃራኒው ግድያ እየበዛ ሄዷል። ዛሬ የዘመኑ ቴክኖሎጂ





ባፈራቸው የጦር መሣሪያዎች በመጠቀም የሚደረጉት ጦርነቶች ከምንጊዜውም ይልቅ የሚያስከፉና አስፈሪዎች ሆነዋል።

ዓለም (በዳን.7፡1-28) በተጠቀሱት አስፈሪ አራዊት አገዛዝ ኃይል እስካለች ድረስ እነዚህ የጥፋት ሁኔታዎች የማያቆሙ ናቸው። ሰይጣን «ከመጀመሪያ ነፍስ ገዳይ» የሆነና በዚያው የሚቀጥልም ስለሆነ። (ዮሐ.8፡44) በእርሱ ቁጥጥር ስርም ያሉት ሁሉ ከእርሱ የሚወርሱት ሌላ ሳይሆን ግድያን፣ ጦርነትን፣ ሞትንና ጥፋትን ብቻ ነው። በመሲሁ ዘመን እነዚህ አስከፊ ሁኔታዎች ያበቁ ይሆናሉ። የነገሥታት ንጉስ (ራዕ.19፡16) የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛው «የሰላም አለቃ» (ኢሳ.9፡6) ሆኖ ዓለምን «በብረት በትር» (መዝ.2፡9) እየገዛ (ኤር.23፡5) «ፍርድንና ጽድቅ» ሲያደርግ ሲገመቱ የማይችሉ ነገሮች ይከናወናሉ።

*«በአሕዛብም መካከል ይፈርዳል፣ በብዙ አሕዛብም ላይ ይበይናል፣ ሰይፋቸውን ማረሻ ጦራቸውንም ማጭድ ለማድረግ ይቀጠቅጣሉ፣ ሕዝብ በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሣም፣ ሰልፍም ከእንግዲህ ወዲህ አይማሩም» (ኢሳ.2፡4።)*

ይህ ለረጅም ጊዜ ይጠበቅ የነበረው የመንግስታት ትጥቅ የመፍታት ጅማሬ ይሆናል። የጦር መሣሪያዎች ይደመሰሳሉ፣ ለጦርነት የሚደረገው ጥሪ ያበቃል። ታንኮች ቀልጠው ማቀዝቀዣ መሥሪያ ይሆናሉ። ለወታደሮች የሆነው ባጀት ለበጎ ሥራ የሚውል ይሆናል። ወታደሮች ከሥራቸው የተሰናበተ ይሆናሉ። የመከላከያ ሥርዓት የተሻረ ይሆናል። ለመጀመሪያ ጊዜ የአውቶሚክ ኃይል ለሰላም ሥራ ጥቅም ላይ ይውላል። ዛሬ ተረት መስሎ የሚታየው የሚነገረው ነገር በሺው ዘመነ መንግስት እውን ሆኖ ይታያል። ይህም እውነተኛና ፍጹም የሆነው ሰላም በምድር ላይ (ሉቃ. 2፡14) እውን ሆኖ ይታያል። ኢየሱስ ክርስቶስ «የሰላም ንጉሥ» ከሆነው በቀር ይህን፣ ማንኛውም ሰው፣ መንግስት፣ ድርጅት፣ የሰው ሀሳብና ማንኛውም ዓይነት ትምህርት ሲመሠረት አይችልም።

## 7. የፍጥረት መዋጀት - የሁሉም ነገር መታደስ

የሺውን ዓመት መንግስት በረከቶች ካለፈው የዓለም ጊዜና ከደህንነት ታሪክ ጋር ልናወዳድረው አንችልም። ይህ ጊዜ በጣም የተለየ ጊዜ ይሆናል። ይህ የሚሆንበት ምክንያት የከበረው ጌታ በኢየሩሳሌም መሪ ስለሚሆንና ሰላምና ፍጹም የሆነ የጽድቅ አገዛዝ በምድር ላይ በእርሱ በኩል ስለሆነ ብቻ አይደለም። የመሲሁ የሰላም መንግስት ውጫዊ ገጽታዎች አስቀድመው በዓለም ላይ ከነበሩት መንግስታት የተለዩ ይሆናሉ። ከዚህ ቀጥሎ ጥቂቶቹን በምሳሌነት እንመልከታቸው።

*ኢየሩሳሌም «የትልቁ የንጉሡ ከተማ» የሆነችው በምድር ላይ ካሉት ይልቅ ከፍ ባለው ተራራ ላይ ትሠራለች» (ኢሳ.2:2)::*

*ፀሐይ «አሁን ከምታበራው ይልቅ ሰባት እጥፍ የደመቀች ትሆናለች ጨረቃም «አሁን ፀሐይ ያላትን ድምቀት ያህል ትደምቃለች» (ኢሳ.30:26)::*

የመቶ ዓመት ዕድሜ ያለው ሰው እንኳን ጎልማሳ ሆኖ ይቆጠራል:: የዕድሜ እርዝማኔ አዳምና ማቱሳሉ እንደኖሩበት ለብዙ መቶ እመታት የረዘመ ይሆናል (ኢሳ.65:20፣ ዘካ.8:4፣ ዘፍ.5:1-32):: የመቶ ዓመት ዕድሜ ያለው ጎልማሳ በሚሞትበት ጊዜ የተረገመ ኃጢአተኛ እንደሆነ ተደርጎ ይገመታል (ኢሳ.65:20::)

እንሰሳትና እራዊት ለማዳዎች ይሆናሉ፤ እርስ በእርሳቸውም አይበላሉም:: ተኩላዎች ከበጎች ጋር፣ ነብሮች ከፍየሎች ጋር አብረው ይተኛሉ:: ታናሽ ብላቴና ጥጆችን፣ የአንበሳ ደቦሎችንና ከብቶችን በአንድነት አብሮ ይመራቸዋል:: ከብቶችና ድቦች በአንድ መስክ ላይ ለግጦሽ አብረው ይሰማራሉ:: አንበሳ ገለባ ይበላል፣ ሕፃን ልጅ ከዚህ በፊት መርዘኛ ከነበሩት ከኮብራና ከእፉኝት ጋር ይጫወታል:: በምድር ላይ በእንስሶችና በእራዊት ላይ ሰላም ይሆናል (ኢሳ.11:6-8፣ 65:25፣ ሮሜ.8:19-25)::

በአዳም ኃጢአት ምክንያት የተረገመችው ምድር ከእርግማን ትፈታና እስራኤል እንደ ገና እንደ ኤደን ገነት ታብባለች:: (ዘፍ.3:17-19፤ ኢሳ.27:6፣ 51:3 ፤ሕዝ.36:35) በረሃዎች ለም ምድር፣ ምድረ በዳዎች ፍሬ የሚያፈሩ ይሆናሉ:: (ኢሳ.41:18-19) ተራሮች በእህል በወይን ጠጅና ዘይት የተሞሉ ይሆናሉ:: ሰዎች በወቅቱ ያርሳሉ ያመርታሉ፣ ይተክላሉ:: የወይን ፍሬያቸውንም ይሰበስባሉ (አሞ.9:13-14):: ምርቱ የተትረፈረፈ ከመሆኑ የተነሳ ረሃብ ያለፈ ሙት ነገር ይሆናል:: (ኢሳ. 49:10፤ ኢዩ.2:19-24)

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች በቂ ናቸው:: እነዚህ ትንቢቶች በመላ የዓለም ታሪክ ውስጥ ያልተፈጸሙ እንደሆኑ እንገነዘባለን:: ነገር ግን ወደ ፊት እንደሚሆኑ እንጠባበቃለን:: እነዚህ እውነተኛ የምድር ዳግም ልደት ስለሆነው ስለ መላ ዓለም መታደስ ይናገራሉ (ማቴ.19:28):: እግዚአብሔር ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ የተናገረው «የመታደስ ዘመን» ይሆናል:: (ሐሥ.3:21) የክርስቶስ የመዋጀት ሥራ ተፈጥሮን በሙሉ ያካተተ ነው:: በሰማያዊው ንጉስ አገዛዝ ሥር ፍጥረት ሁሉ ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊት ወደነበረበት ሁኔታ ይመለሳል:: ዛሬ ፍጥረት ሁሉ «የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃል» (ሮሜ.8:19):: ጌታ ኢየሱስ የመሲሁን ሰላማዊ መንግስት ሊመሠርት እስከ





ሚመጣበት ጊዜ ድረስ ፍጥረታት «ከጥፋት ባርነት ነፃ ወጥተው፣ ወደ እግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነጻነት» ከቶ እይደርሱም (ሮሜ.8:21)::

## 8. የሺሁ ዓመት መንግስት ፍጻሜ የዓለም ዘመን ፍጻሜ

በሺሁ ዓመት መጨረሻ ላይ ሰይጣን እንደገና ከእስራቱ ይፈታና ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የማሳት ኃይሉን ይገልጻል::

«ሺሁም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል፣ በአራቱም በምድር ማዕዘን ያሉትን አህዛብ ጎግንና ማጎግን እዲያስታቸው ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል፣ ቁጥራቸውም እንደ ባሕር አሸዋ የሚያህል ነው» (ራዕ.20:7-8)::

ሰይጣን ከእስራቱ የሚፈታበት ምክንያት በሺው ዓመት መንግስት የሚኖሩት ሕዝቦች የራሳቸው ምርጫ እንዲኖራቸው ነው:: (ጌታን ኃይሉንና ክብሩን ለሺህ ዓመታት የተለማመዱትን ወይም ለሺህ ዓመታት በጥልቁ ታስሮ የነበረውን የተሸነፈውን ጠላት ሰይጣንን) :: እያንዳንዱ ሰው የራሱን ምርጫ ይወስናል:: ሆኖም ውጤቱ ለማመን በጣም የከበደ ይሆናል:: በጌታ ላይ ዓለም አቀፍ የሆነ የሕዝብ አመጽ ይሆናል:: ከአራቱ የምድር ማዕዘናት ጎግና ማጎግ በመነሳት ወደ ኢየሩሳሌም ዘመቻ ያደርጋሉ:: (ጎግና ማጎግ ዓመጸኛ ሕዝቦች መግለጫ ሲሆን በመሳሳት በሕዝ.38 እና 39 ላይ ካለው ማጎግ ጎግ ጋር እንዳናገናኘው ልንጠነቀቅ ይገባናል)::

*«ወደ ምድር ስፋት ወጡ፣የቅዱሳንንም ሰፈርና የተወደደችውን ከተማ ከበቡ»(ራዕ 20:9)*

አንድ ጊዜ የክርስቶስ ኢየሱስ ተቃዋሚ በዓለም ከተታለሉት ሕዝቦች ጌታንና ሰማያዊ ቅዱሳንን በአርማጌዶን ጦርነት ላይ ለመዋጋት ብዙ ሠራዊት ሰብስቦ ነበር:: አሁን ደግሞ ሰይጣን ራሱ በመሲሁ የሰላም መንግስት ዘመን የነበሩትን ሕዝቦች በንጉሳቸውና በቅዱሳን ላይ ጦርነት እንዲያደርጉ ያስታቸዋል:: በዚህ ቦታ ጦርነት አይካሄድም:: ለዚህ ለመጨረሻውና ከፍተኛው ለሆነው በእግዚአብሔርና በከበረው ጌታ ላይ ለተደረገው አመጽ ከእግዚአብሔር የሚሰጠውን መልስ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ተጽፎ ይገኛል::

*«እሳትም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ በላቻቸው»* (ራዕ.20:9)::


ከዚህ በኋላ ወዲያውኑ «የነጩ ዙፋን ፍርድ» ተብሎ በሚጠራው ፍርድ ሰይጣን ይፈረድበታል (ራዕ.20:10-15)::

## *ሦስቱ የድነት ዋና መስመሮች በጊዜና በዘላለማዊነት ማቋረጫ መንገድ ላይ መገናኘት*

# የመጨረሻው ፍርድ

ይህ ፍርድ የዚህ ዓለም የመጨረሻው ፍርድ ይሆናል:: ከዚህ በኋላ የሚሆን ሌላ ፍርድ የለም:: የሚከናወነውም በመጨረሻው ቀን በዓለም ፍጻሜና በዘላለማዊነት ማቋረጫ መንገድ መካከል ነው:: ከዚህ እግዚአብሔር ለብዙ ሺህ ዓመታት ከሶስቱ የሰው ዘሮች ጋር ያደረገውን የደህንነት ታሪክ የሚያመለክቱት ሦስቱ ዋናዎቹ የደህንነት መስመሮች ወደ ፍጻሜ ይመጣሉ:: ከእስራኤልና ከአሕዛብ የዳኑት ሕዝቦች ሁሉ (በአጠቃላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን) ወዲያውኑ ወደ አዲሱ ሰማይና ወደ አዲሱ ምድር ይገባሉ (ኢሳ 65:17፤ 2ጴጥ 3:13፤ ራዕ. 21፡ 1-2):: ነገር ግን በዘመናት ሁሉ አመፀኞች የሆኑትና ያልዳኑት ሕዝቦች በእግዚአብሔር ፊት በመጨረሻ የነጩ ዙፋን ፊት በፍርድ የሚቀርቡ ይሆናሉ:: ፍርዱም:-

1. በሰይጣን ላይ ራዕ 20:10
2. አሁን ባሉት ሰማይና ምድር ላይና ራዕ 20:1፣
3. ባልዳኑት ሕዝቦች ላይ የሚሆን የእሳት ፍርድ ነው:: (ራዕ 20:15)




## የሰይጣን መፈረድ

ሰይጣን የሚፈረድበት የዓለምን ሕዝቦች በእግዚአብሔርና በመሲሁ ላይ እንዲያምፁ ካደረገ በኋላ በሺው ዓመት መጨረሻ ላይ ነው:: (ራዕ 20:98)

«ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳትና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣሉ፣ ለዘለዓለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሰቃያሉ::» ራዕ 20:10

ይህ የትልቁ አሳች ፍፃሜ





ይሆናል በመጨረሻ የሚፈረድበት የሰይጣን ሶስትዮሽ ከሆኑት የመጨረሻው ዲያብሎስ ነው:: እርሱ አንድ ጊዜ ሰውን በመፈተን ለውድቀት በመዳረግ ያደረሰና ለብዙ ሺ ዓመታት ሰውን በኃጢአት ሕይወት፣ በአመጽና በሞት የገዛ ነው:: የእግዚአብሔ:ር ልጅ በጎልጎታ መስቀል ላይ እስካሸነፈው ድረስ ሁልጊዜ በእግዚአብሔር እቅድ ላይ ያሴርም ነበር:: ይህ የእግዚአብሔርና የሰው ልጆች ጠላት የሆነው ክፉ በቅርብ ጊዜ የመጨረሻ ፍርዱን ያገኛል:: ይህም የሚሆነው የክርስቶስ ተቃዋሚና ሀሰተኛውን ነቢይ ወደ ተጣሉበት የዘላለም ጥፋት በመጣል ይሆናል (ራዕ. 19:20):: ከዚህ ፍርድም በኋላ « የዚህ ዓለም አምላክ » አይሆንም ኃይሉ ለአንድ ጊዜና ለዘለአለም የተሰበረ ይሆናል (ዮሐ 12:31):: በዚያ ቀን ኢየሱስ ክርስቶሰ በጎልጎታ መስቀል ላይ የጀመረው ድንቅ የሆነው ድል ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚነትን ያገኛል:: ከዚህ በኋላ « ዘንዶው፣ የቀደመው እባብ፣ ዲያብሎስ፣ ሰይጣን » (ራዕ 12:9) የተባለው አያስትም፣ አያጠፋም፤ ኃጢአትና ሞት ከዚህ በኋላ ከቶ አይኖሩም::

## የሰማይና የምድር መፈረድ

በሰይጣን ላይ ፍርድ ከተካሄደ በኋላ፣ የመጨረሻው ፍርድ በዚህ ዓለም ላይ ይሆናል::

*« ታላቅና ነጭ ዙፋንን በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፣ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ፣ ስፍራም አልተገኘላቸውም» (ራዕ 20:11) «ምድር ከሰው ውድቀት ጀምሮ በሰው ኃጢአት ምክንያት በሞትና በአመፅ ስለተበከለች ከእግዚአብሔር ፊት ልትሸሽ ይገባታል (ኢሳ 24: 1-3)::*

ሰማይም ከእግዚአብሔር ፊት ሊሸሽ ይገባዋል:: ምክንያቱም የብርሃን መልአክ የነበረው ሉሲፈር (የንጋት ኮከብ) በኃጢአት ስለ ወደቀ፣ ሰይጣን (ጠላትም) ስለ ሆነና ክፉ መናፍስት በሰማይ ስፍራ ይገዙ ስለነበር ነው (ኤፌ 2:2፣ 6:12፤ ኢዮ 15:15)::

ይህ ፍርድ ሲከናወን የዓለም ፍፃሜ ይሆናል:: « ሰማያትና ምድር፣ ባሕርና የብስ » ከመሰረታቸው ይናወጣሉ (ሐጌ 2:6) :: ምድርም እንደ ሰከረ ሰው ትንገዳገዳለች፣ እንደ ዳስ ትወዛወዛለች» (ኢሳ 24:20) :: ምድርም « እንደ ልብስ ታረጃለች» «እንደ ጢስም በንና» ትጠፋለች (ኢሳ 51:6):: ሰማያትም « እንደ

መፅሐፍ ጥቅልል ይጠቀለላሉ» (ኢሳ 34:4፤ ራዕ 6:14) ፡፡ የሰማይም ፍጥረታት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣሉ፣ ሰማይ በሙሉ ከግምት በላይ በሆነ ሁኔታ በታላቅ ድምፅ ይጠፋሉ (2ኛ ጴጥ. 3:10፣12 ኢሳ. 24:19፣20)፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሰማይና ምድር ያልፋሉ ብሏል (ማቴ. 24:35)፡፡ በዚያን ቀን ይህ ቃል ይፈፀማል፡፡ ሰማይ በጠቅላላ በምድጃ ውስጥ እንዳለ እሳት ይነድዳል፡፡ የሚታዩት ነገሮች ሁሉ እንዳሉ ይጠፋሉ፡፡ በራዕይ 20:11 «ስፍራ አልተገኘላቸውም» ተብሎ እንደተፃፈው ከዚህ ፍርድ በኋላ ከትላልቆቹ ከዋክብት ጀምሮ እስከ ትንሿ አተም ድረስ ምንም አይቀሩም፡፡ ስለሆነም የሚታየውና የማይታየው አሮጌው ፍጥረት ወደ ፍፃሜው ይመጣል፡፡ ይህም የእሳት ፍርድ ፍጥረት ላደረገው አመፅ የኃያሉ እግዚአብሔር ምላሽ ነው (ራዕ. 20:8-9)፡፡ በተጨማሪም በሰማይና በምድር ላይ ባለው ኃጢአት ላይ የሚሆነው የእግዚአብሔር የፅድቅ ፍርድ ይሆናል፡፡ በታላቁ ነጩ ዙፋን ላይ ያለው ትክክለኛው ፈራጅ ጌታ ኢየሱስ ነው፡፡ ምክንያቱም አባቱ ፍርድን ሁሉ ለእርሱ ሰጥቶታልና፡፡

*« ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም! የሰው ልጅም ስለ ሆነ የፍርድ ስልጣን ሰጠው » ዮሐ 22:27*

ፃድቅ የሆነውና ኃጢአት የሌለበት የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ ስለ ኃጢአተኞች ሁሉ ኃጢአት ስለተፈረደበት በዚህ ምክንያት አባቱ እርሱ ብቻ ዓለምን በፅድቅ እንዲፈርድ ሥልጣንን ይሰጠዋል (ሐሥ. 17: 31)፡፡ በመጨረሻው ፍርድ ሰማይና ምድር ከእርሱ ፊት የሚሸሹት ስለዚህ ነው፡፡

## ያልዳኑት ኃጢአተኞች ፍርድ

በራዕይ 20: 11-15 ያለው የታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ ባልዳኑት ኃጢአተኞች ላይ የሚሆነው የመጨረሻው ፍርድ ነው፡፡ ያለ እግዚአብሔርና ያለ ክርስቶስ የሞቱት የማያምኑት ሰዎች እግዚአብሔር በሕያዋንና በሙታን ላይ እንዲፈርድ በወሰነው ፊት ለፍርድ ይቆማሉ (ሐሥ. 10:42፤ 1ጴጥ 4:5)፡፡

*« ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፣ መፃሕፍትም ተከፈቱ! ሌላ መፅሐፍም ተከፈተ! እርሱም የሕይወት መፅሐፍ ነው፣ ሙታንም በመፃህፍት ተፅፎ እንደ ነበር እንደ ስራቸው መጠን ተከፈሉ » ራዕ 20: 12፡፡*





አማኞች በነጩ ዙፋን ፍርድ አይቀርቡም፡፡ ጌታ ኢይሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የኃጢአታቸውን ፍርድ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ምትክ ሆኖ ስለ ተሸከመላቸው አይፈረድባቸውም፡፡ እንዲሁም በእርሱ ላይ ባላቸው እምነት ከሞት ወደ ሕይወት ስለተሻገሩ ኃጢአታቸው ዳግም አይታሰብም (ሕዝ. 33:16፣ ሚክ 7:19)፡፡ በታላቁ የነጩ ዙፋን ፊት የሚቀርቡት ያላመኑ፣ ኃጢአተኞች፣ አመፀኞችና የጠፉት ብቻ ናቸው፡፡

*« ባሕርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ፣ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፣ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈሉ» (ራዕ 20: 13)፡፡*

የዚህ ፍርድ መስኪያ ከሺው ዓመት በፊት ጌታ በሚመሰስበት ጊዜ አሕዛብ ለእስራኤል ካሳዩት ምህረት ከሚደረገው ፍርድ የተለየ ነው፡፡ ነገር ግን በነጩ ዙፋን ፍርድ ሰዎች በፍርድ ፊት በመቅረብ እግዚአብሔር እንደ ሥራቸው መጠን ይፈርድባቸዋል፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ ሰው በስራው ስራ እንደሚፈርድበት ይነግረናል፡፡ ምክንያቱም ኃጢአተኛው በእግዚአብሔር ፊት የማፀድቀው በሥራው ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ባለው እምነት ነው፡፡ (ገላ 2:16፤ ሮሜ 3:20፣28፤ ኤፌ 2:8-9)፡፡

የነጩ ዙፋን ፍርድ አንድ ሰው የዳነ ነው ወይስ የጠፋ ነው በሚል ጥያቄ ላይ የሚያነጋግር ሀሳብ አይደለም፤ የፍርዱ ጥያቄ ያለቀው ሰውዬው ምድራዊ ሕይወቱ ባበቃ ጊዜ ነው፡፡ የነጩ ዙፋን ፍርድ ግን ንስሐ ያልገባው ኃጢአተኛ ሊቀበል ያለውን ቅጣትና የፍርድ መጠን የሚወስን ነው፡፡ አዳኝ ጌታ ስለ ገሊላውያን ከተማዎች ስለ ኮራዚ፣ ስለ ቤተ ሳይዳና ስለ ቅፍርናሆም ባለቀስ ጊዜ የተናገረው ከእነዚህ ከገሊላውያን ከተማዎች ይልቅ በፍርድ ቀን ለሰዶም እንደሚቀልላት ነው፡፡ ምንም እንኳን ጌታ ኢየሱስ በእነዚህ ከተማዎች ታላላቅ ታምራቶችን ቢያደርግም ሕዝቡ ንስሐ አልገባም ነበር (ማቴ. 11:20-24)፡፡ ስለሆነም ሰዎች በሚፈረድባቸው ጊዜ የፍርዱ መጠን የተለያየ ይሆናል፡፡ የጠፉት በሙሉ እኩል የሆነ ፍርድ አይቀበሉም፡፡ የሚፈረድባቸውም እግዚአብሔርን ባወቁት መጠን፣ ስለ ድነት በተረዱት መጠንና ለሕሊናቸው በመታዘዛቸው መጠን ነው፡፡ « ያወቀ ግን መገረፍ የሚገባውንም ያደረገ ጥቂት ይገረፋል»፡- « ብዙም ከተሰጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል፣ ብዙ አደራም ከተሰጠው ከእርሱ አብዝተው ይሹበታል » (በሉቃስ 12:48ሎ ተብሎ ስለተፃፈ ነው፡፡

ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው፣ ማንኛውም ሰው በታላቁ በነጩ ዙፋን ፊት የሚቀርብበት ምክንያት ክርስቶስን የግል አዳኙ አድርጎ ባለመቀበሉ ነው:: ነገር ግን የቅጣቱና የፍርዱ መጠን እንደ ሥራው መጠን ይሆናል:: በፍርዱ ጊዜ ማንኛውም ሰው በሕይወት ዘመኑ የሰራው ስራ የተመዘገበበት መጽሐፍ ይከፈታል:: ልክ እንደ ግል ማህደር በማይጠፋ አመዘጋገብ የማንኛውም ሰው ኃጢአት የተመዘገበ ነው:: ማንኛውም በንግግርና በሥራ፣ በሀሳብና በተቃውሞ የተደረገ ኃጢአት የተገለጠ ይሆናል:: በዚያም ቀን « ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ » በሮሜ 3:10 ተብሎ እንደተጻፈው ቃል ጋር ማንኛውም ሰው የሚስማማ ይሆናል::

የሰማያዊ መዝገብ መጽሐፍ በሚከፈትበት ጊዜ በቀኝና በግራ ያሉት ይለያሉ:: ለዚህ ማስረጃ የሮሜ መልዕክት «ቸርነት የሚያደርግ የለም፣ አንድስንኳ የለም » ይለናል (ሮሜ. 3:12) :: ያልዳነው ኃጢአተኛ በታላቁ በነጩ ዙፋን ፊት ለራሱ የሚያሳየውና ለራሱ የሚከላከልበት ምንም ነገር አይኖረውም:: ምክንያቱም ስራዎቹ በሙሉ በእግዚአብሔር በኩል የተደረጉ አይደሉምና (ዮሐ 3:21) :: ለእግዚአብሔርና ለሰው ጥቅም የተደረጉ መልካም ራስን የመስዋት ስራዎች በክርስቶስ ፍቅርና ለእግዚአብሔር ክብር በመሆን ካልተደረጉ ዋጋ ቢስ መሆናቸውን ስናይ ይህ የሚያስጨንቀን እውነታ ይሆናል:: ሁላችንም እግዚአብሔርን ስናገለግል የምናደርግባቸውን ምክንያቶችና ዓላማዎቻችንን አጥብቀን መመርመር ይገባናል::

የሰዎች መልካም ሥራና ምግባር በምድር ያደረጉት የተፃፉበት መፃሕፍት ብቻ የሚከፈቱ አይደሉም:: እግዚአብሔር በሰባቱ የመገለጥ መፃሕፍት እንደገለፀው በሰዎች ላይ ይፈርዳል:: ሰባቱም እንደሚቀጥለው ተዘርዝረዋል:: እግዚአብሔር ሰዎችን በመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የመገለጥ መፃሕፍት ያለ መለየት በተጠያቂነት ስለሚሰጡት መልስ ይይዛቸዋል:: የመገለጡ መፅሐፍት የሚከተሉት ናቸው:-

1. ፍጥረት፣ ተፈጥሮና ሰማይ (መዝ. 19:1-7፤ ሐሥ. 14:17፤ ሮሜ 1:19-20)
2. ሕሊና (ሮሜ 2:12-16)

እግዚአብሔር አይሁድንና ክርስቲያኖችን፣ ቀጥሎ ባሉት 5 መፃሕፍት ተጠያቂ ያደርጋቸዋል::

3. የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መፅሐፍ ቅዱስ (መዝ (138):2 ፤ ዮሐ 17:17)



*የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ማብራሪያ*

4. ኢየሱስ ክርስቶስና የማዳን ሥራው (ዮሐ 14:6፣9 ፤ 2ቆሮ 5:19-20)
5. መንፈስ ቅዱስ (ዮሐ 16:7-11)
6. በእስራኤል የደህንነት ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት (ዮሐ. 4: 22 ፤ ሮሜ 9:4-5)
7. በአሕዛብ ታሪክ የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት (ዘዳ.32:8፤ኤር18:1-10)::

እግዚአብሔር በጠፉት ኃጢአተኞች ላይ ፍርዱ ፍፁም ትክክል ሆኖ እናገኘዋለን፣ ምክንያቱም ከእነዚህ መፃሕፍት ቀጥሎ « የሕይወት መፅሐፍ » ይከፈታል በእርሱ ውስጥ ማንኛውም ዳግም የተወለደ ሰው ስም ተመዝግቦአል:: በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ሁሉ ስማቸው በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ይገኛል (ራዕ 3:5፤ ሉቃ. 10:20፤ ፊል 4:3):: ነገር ግን ያልዳኑት ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ ባለማመናቸው ምክንያት ስማቸው ከዚህ ከሕይወት መፅሐፍ ውስጥ ይደመሰስና የሚጠፉ ይሆናል (መዝ. (69): 28፤ ዘፀ 32:32::

*« በሕይወት መፅሐፍ ስሙ ተፅፎ ያልተገኘ ማንኛውም ሰው በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ» (ራዕ 20:15) ::*

የጠፉት ሰዎች ዕድል ፈንታ እጅግ አስደንጋጭ ይሆናል:: መፅሐፍ ቅዱስ ስለ «መከራና ጭንቀት» (ሮሜ 2:9) «ስለ ለቅሶና ጥርስ ስለማፋጨት» (ማቴ. 22:13) ፤ «በውጭ ስላለው ጨለማ» (ማቴ. 8:12)፤ ስለ «ቁጣና ጥፋት» (ዘዳ. 5:9) ፤ «ስለ እቶኑ እሳት» (ማቴ. 13: 42)፤ «ስለ ወሕኒ» (ማቴ. 5:25) «ስለ ገሀነም» ፤(ማር. 9:45) «ስለ ዘላለም ቅጣት» (ማቴ. 25:46)፤ ይናገራል:: ደግሞም «ስለማይሞተው ትል» ይናገራል (ማር. 9: 48)፤ «ስለማይጠፋውም እሳት» (ማር. 9: 48)፤ «በዲን ስለሚቃጠል ባህር» (ራዕ. 19: 20) ይናገራል:: መፅሐፍ ቅዱስ ለፍርድ « በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ እንደሆነ» ይናገረናል (ዕብ. 10:31) ፤ ለሚጠፉት ሰዎች « አስመወለዳቸውም የሚሻል እንደሆነም» ይናገራል (ማቴ. 26: 24)፤ «የስቃያቸውም ጢስ ከዘለዓለም እስከ ዘላለም» ይወጣል (ራዕ. 14:11):: መፅሐፍ ቅዱሳችን ከዘላለም እስከ ዘላለም ብሎ የተረጎመው ዋናው የግሪኩ ትርጉም መጨረሻ የለሽ እንደሆነ ያመለክታል::

ስለሆነም የመጨረሻው የሆነው አሮጌው ዓለም፣ የሺህ ዓመት መንግስት ባልዳኑት ሕዝብ ላይ በሚካሄደው በእግዚአብሔር ፍርድ ያከትማል:: ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ፍርዱ የእሳት ፍርድ ይሆናል:: በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ የተካሄዱትን ሦስት ፍርዶች በአጭሩ እንመልከታቸው::

**በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ ሦስቱ የፍርድ ዓይነቶች**

1. የውኃ ፍርድ - የጥፋት ውኃ (ዘፍ. 6 እስከ 8)
2. የደም ፍርድ - የጎልጎታ መስቀል (ዮሐ. 19:30)
3. የእሳት ፍርድ - የትልቁ የነጭ ዙፋን (ራዕ. 20: 10-15)





## የእግዚአብሔር የማዳን ሀሳብ መፈፀም


## አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር

በታላቁ ነጩ ዙፋን የሚደረገው ፍርድ የአሮጌው ዓለም ፍፃሜ ይሆናል:: አሁን ፍፁም ወደ ተሰየው ዓለም «አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር» ወደ ሆነው እንገባለን:: ይህን ፍፃሜ የሌለውንና ለዘላለም በበረከት የተሞላውን አዲሱን ዓለም እንመልከት::

### 1. ዘለዓለማዊነት

በራዕ 21 እና 2 ለዳኑት ለእግዚአብሔር ዝቦች የዘላለማዊነት ጅመሬ ምን እንደሚመስል ይገልፃል:: ዳግም የተወለዱት አማኞች ሁሉ የተባረኩ ይሆናሉ::

የእግዚአብሔር ልጅ «ለዘላለም እንደማይጠፋ» ተናግሯል:: ዮሐ 3:16 የዘላለም ይህወት መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው የእግዚአብሔር ህይወት ነው:: የዘላለም ሕይወት ለዘላለም መኖር ያለበት ሕይወት ነው:: ማንም ሰው ይህን ሕይወት ከራሱ ሊያገኘው አይችልም፣ ምክንያቱም «ሁሉ ኃጢዓትን ሰርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል» (ሮሜ.3:23):: «ልጁ የሚያምኑት የዘላለም ሕይወት አለው» (ዮሐ. 3:36):: ይህ የዘላለም ሕይወት የሚጀምረው አንድ ሰው በክርስቶስ እምኖ ዳግም ሲወለድ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስንና የማዳን ሥራውን በሙሉ ልቡና ሕይወቱ ያልተቀበለ ሰው ዳግም ልደትን አያገኝም::



ስለሆነም የመጨረሻው የሆነው አሮጌው ዓለም፣ የሺህ ዓመት መንግስት ባልዳኑት ሕዝብ ላይ በሚካሄደው በእግዚአብሔር ፍርድ ያከትማል። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ፍርዱ የእሳት ፍርድ ይሆናል። በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ የተካሄዱትን ሦስት ፍርዶች በአጭሩ እንመልከታቸው።

## በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ ሦስቱ የፍርድ አይነቶች

1. **የውሃ ፍርድ - የጥፋት ውኃ** (ዘፍ. 6 እስከ 8)
2. **የደም ፍርድ - የጎልጎታ መስቀል** (ዮሐ. 19:30)
3. **የእሳት ፍርድ - የትልቁ የነጭ ዙፋን** (ራዕ. 20: 10-15)






### የእግዚአብሔር የማዳን ሀሳብ መፈፀም

## አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር

በታላቁ ነጩ ዙፋን የሚደረገው ፍርድ የአሮጌው ዓለም ፍፃሜ ይሆናል። አሁን ፍፁም ወደ ተለየው ዓለም «አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር» ወደ ሆነው እንገባለን። ይህን ፍፃሜ የሌለውንና ለዘላለም በበረከት የተሞላውን አዲሱን ዓለም እንመልከት።

### 1. ዘለዓለማዊነት

በራዕ 21 እና 2 ለዳኑት ለእግዚአብሔር ዝቦች የዘላለማዊነት ጅመሬ ምን እንደሚመስል ይገልፃል። ዳግም የተወለዱት አማኞች ሁሉ የተባረኩ ይሆናሉ።




የእግዚአብሔር ልጅ «ለዘላለም እንደማይጠፋ» ተናግሯል። ዮሐ 3:16 የዘላለም ይህወት መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው የእግዚአብሔር ህይወት ነው። የዘላለም ሕይወት ለዘላለም መኖር ያለበት ሕይወት ነው። ማንም ሰው ይህን ሕይወት ከራሱ ሊያገኘው አይችልም፣ ምክንያቱም «ሁሉ ኃጢዓትን ሰርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል» (ሮሜ.3:23)። «ልጁ የሚያምኑት የዘላለም ሕይወት አለው» (ዮሐ. 3:36)። ይህ የዘላለም ሕይወት የሚጀምረው አንድ ሰው በክርስቶስ አምኖ ዳግም ሲወለድ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስንና የማዳን ሥራውን በሙሉ ልቡና ሕይወቱ ያልተቀበለ ሰው ዳግም ልደትን አያገኝም።

ይህም ሰው ለዘላለም ከሚኖረው አዲስ ሰማይና ምድር ለዘላለም ዕድል ፈንታ አይኖረውም። ወደዚህ ዓለም ለመግባትየሚያስችሉትን ነገሮች የሉትምና፣ ምክንያቱም:-

1. በክርስቶስ ደም ስላልተዋጀና (ኤፌ. 1:7)
2. በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ስላልተወለደ (ቲቶ. 3:5)

ጌታ ኢየሱስ ከብዙ ጊዜ በፊት ታዋቂ ለሆነው ለእስራኤል መምህር ለኒቆዲሞስ « እውነት እውነት እልሃለሁ፣ ሰው ከውሀና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት አይችልም» ብሎ ነግሮታል (ዮሐ. 3:5)።

በንስሐና በዳግም ልደት አዲስ ፍጥረት የሆኑት ብቻ ወደ አዲሱ ሰማይና ወደ አዲሱ ምድር ይገባሉ (2ኛ ቆሮ. 5:17) ። ከእግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት የተቀበሉ ስለሆኑ ከእርሱ ጋር ለዘላለም ይኖራሉ።

## 2. ፍፃሜው (መጨረሻው)

እግዚአብሔር ማንኛውንም የማዳን እቅዱን በአዲሱ ሰማይና ምድር ይፈፅማል። እግዚአብሔር በሁሉን ቻይነቱ ዓለምን የፈጠረና የተበላሸውንም ያዳነ ብቻ አይደለም። እርሱ የጎደለውን ሁሉ ያደርጋል። እንደ መፅሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ በሦስቱ ሁኔታዎች ውስጥ ይጓዛል።

1. የዓለም መፈጠር
2. የዓለም ማዳን
3. የዓለም ፍፃሜ

እንደ ዕብ 12:2 የእግዚአብሔር ልጅ «የእምነታችን ራስና ፈፃሚ» ነው። ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ውስጥ ጣልቃ በመግባት ለፍፃሜው ዓለም ሰውን እንደሚያድን አጠንክሮ ይናገራል። መሠረቱና ለዚህ አስፈላጊ የሆነው ነገር በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ላይ የተከናወነው የማዳን ሥራ ነው። ነገር ግን ዳግም የተወለዱት የእግዚአብሔር ልጆች ከግባቸው እስኪደርሱና በሰማያዊ ክብር ዘላለማዊ የሆነውን ሙላት እስኪያገኙ ድረስ በእምነት እንጂ በማየት መራመድ የለባቸውም (2ኛ ቆሮ. 5:7) ።





## 3. የማይናወጠው መንግስት

አማኞች በሙሉ «የማይናወጠውን መንግስት» «የማይጠፋውንና እድፈት የሌለበትን የማያልፈውን መንግስት» ተስፋ ያደርጋሉ። (ዕብ. 12:28፤ 1ጴጥ 1:4 ) እግዚአብሔር አዲስ ሰማይንና ምድርን ሲፈጥር መንግስቱ ፍፁም ይሆንና በማዳን ታሪክ አዲስ ዘመን ይጀምራል። ከጴንጤቆስጤ ቀን ጀምሮ እስከ መነጠቅ ቀን ድረስ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ወደ ሆነው መንፈሳዊ መንግሥት የክርስቶስን አካል ይሰበስባል። ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር ልጅ በምድር ላይ በመሲህነቱ መንግስት ለሺህ ዓመት ይገዛል። ይህ መንግስት የልጁ (የኢየሱስ) መንግስት ይሆናል። ሆኖም የመንፈስ ቅዱስና የልጁ መንግስት ወደማይናወጠው ዘላለማዊው አዲስ ሰማይና ምድር ወደሆነው ወደ እግዚአብሔር አብ መንግስት ይጠቃለላል። ከዚህ በኋላ ልጁ የተዋጀውን ፍጥረት በሙሉ በአባቱ እግር ስር ካስገዛ በኋላ «እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል» (1ቆሮ. 15:28) ።

## 4. የመጨረሻው ግብ

ወደ አዲሱ ሰማይና ምድር የሚገቡት የዳኑት ሕዝቦች ብቻ ናቸው። ራዕይ 21 እና 22 በጥንቃቄ ብናነብ ሦስቱም የሰው ዘሮች ክፍሎች እንደገና በዘላለማዊው ዓለም ውስጥ መገኘታቸውን እናረጋግጣለን። እነርሱም

1. የዳኑት አሕዛብ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ብርሃን ውስጥ ይመላለሳሉ (ራዕ. 21: 24-26)
2. ከአስራ ሁለቱ የእስራኤላውያን ነገዶች የዳኑት ይገኛሉ። የአስራ ሁለቱ ነገዶች ስሞች በሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም በእንቁ ባጌጡት አስራ ሁለት በሮችዋ ላይ ተፅፈው ይገኛሉ (ራዕ. 21:12-13) ።
3. ቤተክርስቲያን በበጉ ሚስትና ሙሽራ በመመስል በሰማይ ትገኛለች (ራዕ. 21:9)።

ይህ ጌታ የጀመረውን ማንኛውንም ነገር በመጨረሻ ማከናወኑን ወደ ፍፃሜ ማምጣቱን ያረጋግጥልናል። ማንኛውም ሰው ትክክለኛውን የአዳኙን የክርስቶስ ኢየሱስን መንገድ ቢመርጥ ወደዚህ ግብ ይደርሳል።

**ኢየሱስ ክርስቶስ!!**

*« እኔ መንገድና እውነት፣ ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» በማለት ስላረጋገጠ ነው (ዮሐ 14:6) ።*

## መግለጫ ክፍል 1፡

# ሁለቱ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረጎች

የኢየሱስ ክርስቶስ ትስግውትነት (Incurnation) ሰው የመሆን ነገር (የቃለ ሥጋ መሆን) የዘላለማዊው እግዚአብሔር ታላቅ ሚስጢር ነው። የዚህን ተወዳዳሪ የሌለውን ተዓምራዊ እይታ መረጃ የሚሰጠን መፅሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። ይህ ቀላል የሆነ ጥናት አይደለም። ስለሆነም የመፅሐፍ ቅዱስን ቅዱሳት መፃሕፍት እርስ በርስ በማስተያየት (በማገናዘብ) ልንተረጉም ይገባናል። ሁልጊዜ ስለ ክርስቶስ ስብዕና በአዲስ ኪዳን የተዘገበውን ከብሉይ ኪዳን ትንቢት ጋር በማስተያየት መመልከት አለብን። ብሉይ ኪዳን መሠረት ያላደረገና በአዲስ ኪዳን ላይ ብቻ ያረፈ የክረስቶ ትስግውትነት ጥናት ግልፅ ስለማይሆን ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ ልንራመድ እንችላለን። ስለሆነው ለሚቀጥለው ጥናታችን ሁልጊዜ ወደ ብሉይ ኪዳን በማጣቀስ እንመለከታለን።

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጌታ የአዳኙ የኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት የተለያዩ የትውልድ ሐረጎች አሉ። እነርሱም በ(ሉቃስ 3:23-38) ሌላው ደግሞ (በማቴ. 1:1-17) ውስጥ ይገኛል። ቀለል ባለ እይታ እነዚህ ሁለት የትውልድ ሐረጎች የተለያዩ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል። ለምሳሌ ሉቃስ ወንጌል 76 የሆኑ የአባቶች ስም ሲኖሩት የማቴዎስ ወንጌል ደግሞ 42 የአባቶች ስሞችን ይዟል። ሉቃስ የትውልድ ሐረጉን በዮሴፍ ሲጀምር ማቴዎስ ደግሞ በአብርሃም ይጀምራል። የሁለቱ የትውልድ ሐረጎች በጥንቃቄ ሲነጻጸሩ ከአብርሃም እስከ ዳዊት ያሉት ስሞች ተመሳሳዮች ናቸው። ከዚያ በኋላ የትውልድ ሐረጉ በሁለት የተለያዩ ሐረጎች ይከፈላል። የመጀመሪያው ከዳዊት እስከ ናታን ሲሆን፣ (ሉቃ. 3: 31) ሁለተኛው ከዳዊት ወደ ሰሎሞን የትውልድ ሐረግ ያመራል (ማቴ. 1:6) ። በመጨረሻም ሁለቱን የትውልድ ሀረጎች የማርያም እጮኛ የሆነውን ዩሴፍን ይዘግባሉ። ነገር ግን አንዱ ዮሴፍን የያዕቆብ ልጅ (ያዕቆብ ዮሴፍን ወለደ (ማቴ. 1:16) ብሎ ሲዘግብ ሌላው ደግሞ ዮሴፍን የኤሊ ልጅ አድርጎ ዘግቧል (ሉቃ 2:23)። ዮሴፍ ከናታን ወደ ዳዊትና ከሰሎሞን የሆኑ ሁለት የትውልድ ሐረጎች ሊኖሩት አይችሉም።



የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ማብራሪያ

### የኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ዘርነቱ የትውልድ ሐረግ
ሉቃስ እንደዘገበው ሉቃ.3:23-38

| | |
|---|---|
| ኢየሱስ ክርስቶስ | ሜልያ |
| ማርያም/ ዮሴፍ | ማይናን |
| ኤሊ | ማጣት |
| ማቲ | ናታን |
| ሌዊ | ዳዊት |
| ሚልኪ | እሴይ |
| ዮና | ኢዮቤድ |
| ዮሴፍ | ቦዔዝ |
| ማታቲዩ | ሰልሞን |
| አሞጽ | ነዓሶን |
| ናሆም | አሚናዳብ |
| ኤሲሊም | አራም |
| ናጌ | አርኒ |
| ማአት | ኤስሮም |
| ማታትዩ | ፋሬስ |
| ሴሜይ | ይሁዳ |
| ዮሴፍ | ያዕቆብ |
| ዮዳ | ይስሐቅ |
| ዮናን | አብርሃም |
| ሬስ | ታራ |
| ዘሩባቤል | ናኮር |
| ሰላቲያል | ሴሮህ |
| ኔር | ራጋው |
| ሚልኪ | ፋሌቅ |
| ሐዲ | አቤር |
| ዮሳስ | ሳላ |
| ቆሳም | ቃይንም |
| ኤልሞዳም | አርፋክስድ |
| ኤር | ሴም |
| ዮሴዕ | ኖኅ |
| ኤልኣዛር | ላሜህ |
| ዮራም | ማቱሳላ |
| ማጣት | ሄኖክ |
| ሌዊ | ያሬድ |
| ስምዖን | መላልኤል |
| ይሁዳ | ቃይናን |
| ዮሴፍ | ሄኖስ |
| ዮናን | ሴት |
| ኤልአቄም | አዳም |

### የኢየሱስ ክርስቶስ የነገሥታት ዘርነቱ የትውልድ ሐረግ
ማቴዎስ እንደዘገበው ማቴ.1:1-17

አብርሃም
ይስሐቅ
ያዕቆብ
ይሁዳ
ፋሬስ
ኤስሮምን
አራም
አሚናዳብ
ነአሶን
ሰልሞን
ቦዔዝ
ኢዮቤድ
እሰይ
•ዳዊት
ሰሰሞን
ሮብአም
አቢያ
አሳፍ
ኢዮሳፍጥ
ኢዮራም
ዖዚያን
ኢዮታም
አንካዝ
ሕዝቂያስ
ምናሴ
አሞጽ
ኢዮሲያስ
ኢኮንያን
ሰላቲያል
ዘሩባቤል
አብዩድ
ኤልያቄም
አዛር
ሳዶቅ
አኪም
ኤልዮድ
አልዓዛር
ማታን
ያዕቆብ
ዮሴፍ/ ማርያም
ኢየሱስ ክርስቶሰ

ታዲያ እነዚህ የተሰያዩትን የትውልድ ሐረጎች እንዴት እንገልፃቸዋለን? በማዳን ታሪክ (Salivation History) ውስጥ ምንን ያመሳክታሉ? በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ሁለቱ የጌታችን የትውልድ ሐረጎች እርስ በእርሳቸው አይጋጩም:: ነገር ግን እርስ በእርሳቸው እየተደጋገፉ የእግዚአብሔርን ልጅ ስብዕና ሚስጢር ይገልፃሉ:: በተጨማሪም የአዳኙን፣ የንጉሡንና የመሲሁን የኢየሱስ ክርስቶስን ሰው ሆኖ መወለድ የሚገልጡ መሰከታዊ ራዕዮች (መገለጥ) ናቸው::

የደህንነት ታሪክ ቻርት የሁለቱንም የትውልድ ሐረጎች ስሞች ይዟል:: በቻርቱ ዙሪያ በሁለት ትይዩ ቀስቶች ተፅፈዋል:: በስተ ግራ ያለው በርከት ያሉ የኢየሱስ ክርስቶስን የቀድሞ አባቶችን የትውልድ ሐረግ የያዘው በሉቃስ ወንጌል የተመዘገቡት ናቸው:: በስተ ቀኝ ያሉት ደግሞ የአዳኙ የቀድሞ አባታችን የትውልድ ሐረግ የያዘው በማቴዎስ ወንጌል የተመዘገቡት ናቸው:: አብዛኞቹ የመፅሐፍ ቅዱስ ምሁራን በማቴዎስ የተመዘገበው የትውልድ ሐረግ የዩሴፍ፣ በሉቃስ የተመዘገበው የትውልድ ሐረግ ደግሞ የማርያም እንደሆነ ይስማማሉ:: ስለሆነም ሁለት አይነት አቀራረቦች (አቋሞች) ይኖሩናል ማለት ነው:: እነርሱም:-

1. በሉቃስ የተመዘገበው የትውልድ ሐረግ ከማርያም በሥጋ የተወለደው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የዳዊት ልጅ መሆኑን ይገልፅልናል (ሉቃስ 3: 23-38) ::
2. በማቴዎስ የተመዘገበው የትውልድ ሐረግ እንደ ተስፋ ቃሉ በዮሴፍ በኩል የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥና መሲሁ መሆኑን ያመለክተናል (ማቴ. 1: 1-17) ማለት ነው::

በእግዚአብሔር ልጅ ትስግውትነት (ሰው መሆን) ውስጥ ሁለቱም ማርያምና ዮሴፍ በጣም አስፈላጊ ናቸው:: በመቀጠል ይህንን በበለጠ እንገልፀዋለን::

## 1. የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ እንደ ሉቃስ ወንጌል

አራቱ ወንጌላት ከእግዚአብሔር ቃል ክፍል የሆኑ ድንቅና የተለዩ ናቸው:: እያንዳንዱ በተለያየ ገፅታ የኢየሱስ ክርስቶስን ስብዕናና ሥራ ይገልፃሉ:: ማቴዎስ ንጉስነቱንና ሥራውን ይገልፃል፣ ማርቆስ አገልጋይነቱን ይገልፃል፣ ዮሐንስ ደግሞ በእግዚአብሔር ልጅነቱና ክብሩ ላይ ያተኩራል:፤ ነገር ግን ሉቃስ ከሌሎቹ በበለጠ የጌታ የኢየሱስን ስብዕና ይገልፃል:: የሰው ልጅ የሚለው መጠሪያ ገለፃ ለማንያ ሰባት ጊዜ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል:: በብሉይ ኪዳንም (በዳን. 7:13-14፣ በመዝ. (80):17) ውስጥ ጌታ «የሰው ልጅ» ተብሎ ተጠቅሷል::





በእያንዳንዱ ወንጌላት መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ልጅ በተለያየ መንገድ ይገልፀዋል:: አራቱ ወንጌላት እርስ በእርሳቸው የሚደጋገፉ (የሚገላለፁ) ከሆነ የአዳኙን ሙሉ ሰብዕና (ታሪክ) ለማግኘት ሁሉንም ወንጌላቱን መመልከት አለብን:: መፅሐፍ ቅዱስን ስንተረጉም በመንፈስ የተነዱትን ፀሐፊዎች ልዩ የሆነ እይታ በአእምሮ መያዙ በጣም አስፈላጊ ነው:: ይህ ሁለቱን የትውልድ ሐረጎች በተሻለ መንገድ ለመርዳት ይረዳናል:: ስለሆነም በማሳጠር እንመልከታቸው::

- የማቴዎስ ወንጌል የሚያተኩረው «በጌታ ኢየሱስ ንጉስነቱ» ላይ ነው::
- የማርቆስ ወንጌል የሚያተኩረው «በጌታ ኢየሱስ አገልጋይነት» ላይ ነው::
- የሉቃስ ወንጌል የሚተኩረው «በጌታ ኢየሱስ የሰው ልጅነት» ላይ ነው::
- የዮሐንስ ወንጌል የሚያተኩረው «በጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅነት» ላይ ነው::

### የማርያም የትውልድ ሐረግ ሉቃስ 3:23-38

በመጀመሪያ ሰላምን አብዛኞቹን የመፅሐፍ ቅዱስ ምሁራን የሉቃስ ወንጌል በማርያም የትውልድ ሐረግ ላይ ስለ ማተኮሩ እውነታ ስለ መሳባቸው እንመረምራለን::

ቀደም ብለን እንደ ገለፅነው የሉቃስ ወንጌል በጌታ ኢየሱስ ስብዕና ላይ የሚያተኩር ነው:: እንደ ሉቃስ ወንጌል የጌታ ኢየሱስን ስብዕና (ሰው መሆን) በእያንዳንዱ ሁኔታ ላይ የሚገልፅ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሌላ መፅሐፍ የለም:: በሁለተኛ ሳሙኤል መፅሐፍ ውስጥ ንጉስ ዳዊት መሲሁና የእስራኤል ንጉስ የሆነው ከእርሱ ዘር እንደሚወለድ ተስፋ እንደተቀበለ ተፅፏል (2ሳሙ. 7:1-29):: ከአንድ ሺ ዓመት በኋላ የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ሆኖ በተወለደ ጊዜ ትንቢቱ ተፈፃሚ ሆኗል:: እርሱ የተስፋው የዳዊት ልጅ፣ የዳዊት የትውልድ ሐረግ ቅርንጫፍ፣ ኃያሉ የይሁዳ ንጉስና የእስራኤል ሕዝብ መሲህ ነው:: ሉቃስ በጌታ ስብዕና ላይ የሚያተኩር ከሆነ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የትውልድ ሐረግ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ጎላ ብሎ የምናየው በሥጋ (ሰው ሆኖ ስለ መምጣቱ) ስለመምጣቱ ነው (ሉቃ. 3:23-28)::

የኢየሱስ ትውልድ ሐረግ የተያያዙ 76 የትውልድ አባቶችን የያዘ ነው:: ይህም ጌታ በናታንና በዳዊት በኩል እስከ መጀመሪው ሰው እስከ አዳም ድረስ ያለውን የተፈጥሮ ውርስን የሚከተል መሆኑን ያሳያል:: ይህ መፅሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ፍፁም ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም መምጣቱን ይመሰክራል::

(ሕንግዲህ «ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለች» ዕብ 2:14 ተብሎ ተፅፏልና) ምክንያቱም ማንኛውም ሰው ከተወለደ ጀምሮ በኃጢአት የጠፋ ስለሆነ ክርስቶስ የደህንነት ሥራ ለማከናወን «በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ» ሰው ሆኖ መጣ:: በዚህ ምክንያት መፅሐፍ ቅዱስ በአንድ በኩል ዌየሰው ልጅዥ ብሎ ሲጠራው (ሉቃ. 19:10)፤ በሌላ በኩል ደግሞ «የኋለኛው አዳም» ወይም «ሁለተኛው ሰው» ብሎ ይጠራዋል (1ቆሮ. 15:45፣ 47)::

መፅሐፍ ቅዱስ ድንግል የእግዚአብሔርን ልጅ እንደወለደች ያስተምራል (ሉቃ. 1:31-35፣ ኢሳ. 7:14) በሌላ በኩል ደግሞ በመሲሁ እንደ ማንኛውም ሰው የሥጋ አባት የለውም:: ስለሆነም በማርያም በኩል በሥጋ እውነተኛው «የዳዊት ልጅ» ነው:: ከዮሴፍ ሰብአዊ የሆነ ውርስ የለውም፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ብቻ አባቱ ነውና:: የሰው አባት የለውም፣ ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስ እንጂ (ሉቃ. 1:35፤ ማቴ. 1:18-21) የሉቃስ ወንጌል የትውልድ ሐረግ የሚያጠናክረው ይህንኑ ነው:: ዮሴፍ የኢየሱስ አባት አይደለም:: ነገር ግን የእርሱ አባት መስሏቸው ነበር (ሉቃ. 3:23) ዮሴፍ ለእግዚአብሔር ልጅ ሞግዚት ብቻ ነበር:: ስለሆነም መፅሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዮሴፍ የወረሰው ስብዕና እንዳለው የሚናገረው የለውም::

ነገር ግን ከማርያም ጋር ያለው የተለየ ነው:: መፅሐፍ ቅዱስ ማርያም ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን የወለደች ሴት እንደሆነች ይናገራል (ማቴ. 1:16):: በማርያም በኩል ብቻ ነው የእግዚአብሔር ልጅ ፍፁም ሰው የሆነው «በእርሷ ሰውነት በኩል ነው ጌታችን በሥጋችንና በደማችን የተካፈለው» (ዕብ. 2:14) በእርሷ በኩል ነው የተስፋው «የዳዊት ልጅ» ሆኖ ወደ አዳም ዘሮች የመጣው የእግዚአብሔር ልጅ በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ተወለደ ማርያም እውነተኛ የዳዊት ቤት ሴት ልጅ ናት ማለት ነው:: (ሮሜ 1:3፣ 2ጢሞ. 2:8) የእግዚአብሔር ልጅ በሥጋ ከዳዊት ዘር ከሆነ፣ ምድራዊ እናቱ ማርያም ከዳዊት ቤተሰብና የትውልድ ሐረግ የመጣች መሆን አለባት ማለት ነው:: በማሳጠር የሚከተለውን ማጠቃለያ እናድርግ (በሉቃ. 3:23-38) ያለው የትውልድ ሐረግ በሥጋ የዳዊት ልጅ ሆኖ የተወለደውን የኢየሱስ ክርስቶስን ከሰው የሆኑትን አባቶችን ሐረግ የዘገበ ነው:: ከአዳም ጀምሮ በዳዊትና በናታን በኩል እስከ ክርስቶስ ያለውን የትውልድ ሐረግ የያዘ ነው:: ይህም የዓለሙ አዳኝ ከሰው ዘር የመጣ መሆኑን ያረጋግጥልናል:: ክርስቶስ ስብዕናውን በማርያም በኩል ካገኘና (በሉቃ. 3:23-38) ያለው ከአዳም ጀምሮ ያሉትን ቅድመ አያቶችን የዘገበ ከሆነ ይህ የትውልድ ሐረግ የማርያም የትውልድ ሐረግ ማለት ይሆናል::





በዚህ ትርጉም (አተረጓጎም) ላይ አንድ አስቸጋሪ ነገር አለ ይኸውም የማርያም ስም በዚህ የትውልድ ሀረግ አንዴም አለመጠቀሱና የዮሴፍ ስም በሁለቱም የትውልድ ሐረጎች መጠቀሱ ነው:: (ሉቃ. 3:23፤ ማቴ. 1:16) ይህ እንዴት ሊብራራ ይችላል?

## ማርያም የይሁዳ ሕጋዊ ልጅ መሆንዋ

ማርያም የዳዊት ቤት ሴት ልጅ እንደሆነች ቀደም ብለን አረጋግጠናል:: ስለሆነም እንደ ንጉስ ዳዊት እርስዋም ከይሁዳ ነገድ ናት እንደ ሉቃስ 3:23-38 ዮሴፍ የኢየሱስ አባት እንዳልሆነ ሆኖም ግን በአባት መመስሉን ጠቅሰናል:: ዮሴፍ አንዱ ከናታን ሌላው ደግሞ ከሰሎሞንና ከዳዊት የሆኑ ሁለት የትውልድ ሐረጎች ሊኖሩት እንደማይችል ግልፅ ነው:: በሉቃስ የትውልድ ሐረግ ማርያም ያልተጠቀሰችበት ምክንያት አንድ ገለፃ ብቻ አለ:: ምንም እንኳን መፅሐፍ ቅዱስ ይህንን በዝርዝርና በግልፅ ባያብራራውም ማርያም ከዳዊት ቤተ ሐረግ ውስጥ መሆንዋ የማይቀር ነው:: ይህን እንዴት እናረጋግጠዋለን?

ማንኛውም መፅሐፍ ቅዱስን የሚያውቅ ሰው መፅሐፍ ቅዱስ ስለ ሰዎች ሲናገር በአመዛኙ ወንዶቹን ብቻ የሚዘግብ እንደሆነ ያውቃል:: በጥንት ጊዜ በምስራቁ ዓለም ሕዝባዊ ጉዳዮችን የሚያከናውኑት ቤተሰቦቻቸውን የሚደግፉና ሕዝባዊ ሥራዎችን የሚሠሩት ወንዶች ብቻ ነበሩ፣ ሴቶች ግን በቤት ላለው ሥራ እንደ ልብና ነፍስ ሆነው በቤት ለሚሠራው ሥራ ኃላፊዎች ነበሩ (ምሳ. 31:1-31) ::

አውግስጦስ ቄሳር ግብር ለማስገበር በፈለገ ጊዜ በሮም ግዛት ሁሉና እስራኤልን ጨምሮ የሕዝብ ቆጠራ እንዲደረግ ትዕዛዝ አወጣ:: ይህ ሴቶችን የማይመለከት ስለነበር ቆጠራው ቅድሚያ የተሰጠው ለወንዶች ነበር:: ነገር ግን መፅሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ ስንመለከት ይህ ከማርያም ጋር የሆነ እንዳልሆነ እንመለከታለን:: በዚያን ጊዜ ለነበረው ልማድና ጠባይ ተቃራኒ በሆነ መንገድ ማርያም ከእጮኛዋ ጋር ሆና ወደ ቤተ ልሔም ለመመዝገብ ተጓዘች::

«ዮሴፍም ደግሞ ከዳዊት ወገን ስለ ነበር በገሊላ ካለችው ከናዝሬት ከተማ ተነስቶ በይሁዳ ወደሆነችው ቤተ ልሔም ወደምትባል ወደ ዳዊት ከተማ ፀንሳ ከነበረች ከእጮኛው ከማርያም ጋር ይፃፍ ዘንድ ወጣ» (ሉቃ. 2:4-5)::

በእውነት ከሆነ እንደዚህ ያለው ጉዞ ማርያምን የሚጠይቅ አልነበረም:: በናዝሬትና በቤተልሔም መካከል ያለው የ170 ኪሎ ሜትር ርቀት በእግር መጓዝን

የሚጠይቅ ነበርና። ማርያም የመውለጃዋ ጊዜ ቀርቦ ሳለ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለች ይህን ጉዞ መጓዝ ለእርስዋ አድካሚና የማይቻል ነበር። አደገኛ ጉዞ ስለነበር በእርሷና በሕፃኑ ላይ ችግር ሊፈጠር ይችል ነበር። እድል ቢሰጣት ኖሮ በማንኛው ሁኔታ ይህን ጉዞ አትጓዘውም ነበር። ታዲያ ማርያም ወደ ቤተልሔም ሔዳ በዚህ የሕዝብ ቆጠራ መመዝገብ ለምን አስፈለጋት?

ለዚህ አንድ መልስ ብቻ አለ። ማርያም ግብር ለመክፈል የሚያስችል የሚመዘገብ ውርስ በቤተ ልሔም ይኖራት ይሆናል ስለሆነም ይህን ጉዞ መጓዝ ነበረባት፣ ምክንያቱም ወራሽ ስለነበረች ለርስቷ ግብር ለመክፈል በርስቷ መመዝገብ ነበረበትና።

በዘኍልቁ መፅሐፍ ውስጥ ሴቶች ልጆች ውርስ መውረስ ስለሚገባቸው የተሰጠ የእግዚአብሔር ሕግ ይገኛል። የሰለጰዓድ ሴቶች ልጆች አባታቸው በምድረበዳ ውስጥ ስለሞተና የሚወርሱ ወንዶች ልጆች ስላልነበሩት በእስራኤል መካከል መውረስ እንዲችሉ ጥያቄ ይዘው ከሙሴ ፊት ቀርበው ነበር። ሙሴም ይህን ጉዳይ በእግዚአብሔር ፊት አቀረበና እግዚአብሔርም ሴቶች ልጆች መውርስ እንደሚገባቸው ያለውን ሕግ ሰጠው።

*«የሰለጰዓድ ልጆች እውነት ተናግረዋል፣ በአባታቸው ወንድሞች መካከል የርስት ድርሻ ስጣቸው፣ የአባታቸውን ርስት ለእነርሱ አሳልፈህ ስጣቸው። ለእስራኤልም ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው «ሰው ቢሞት ወንድ ልጅም ባይኖረው ርስቱ ለሴት ልጁ ይለፍ (ዘኍ. 27:7-8) ።»*

በዚህ ሕግ መሠረት ሴቶች ልጆቹ የአባታቸውን ርስት ሁሉ እንዲወርሱ ተፈቀደላቸው። ነገር ግን አንድ የተለየ ሁኔታም ነበር ውርስን የምትወርስ ሴት ልጅ ማግባት ያለባት ከራሷ ነገድ ብቻ ነበር።

*«እግዚአብሔር ስለ ስለጰአድ ሴቶች ልጆች ያዘዘው ነገር ይህ ነው፦ የወደዱትን ያግቡ፣ ነገር ግን ከአባታቸው ነገድ ብቻ ያግቡ። እንደዚሁም የእስራኤል ልጆች ርስት ከነገድ ወደ ነገድ ምንም አይተላለፍ፣ ከእስራኤልም ልጆች እያንዳንዱ ወደ አባቶቻቸው ነገድ ርስት ይጠጉ። ከእስራኤልም ልጆች እያንዳንዱ ሰው የአባቶቹን ርስት ይወርስ ዘንድ ከእስራኤል ልጆች ነገድ ሁሉ ርስት ያላት ሴት ልጅ ሁሉ ከአባቷ ነገድ ባል ታግባ። እንደዚህም ከአንድ ነገድ ወደ ሌላ ነገድ ምንም ርስት አይተላለፍ፣ከእስራኤልም ልጆች ነገድ እያንዳንዱ ወደ ርስቱ ይጠጋ» (ዘኍ.36:6-9)።*





ስለሆነም ከይሁዳ ነገድ የሆነች ሴት ልጅ ከአሴር ነገድ የሆነውን እንድታገባ አይፈቀድም ነበር። ከተጋባች ወደ አሴር ይዘው ያመጣችው የወረሰችው ውርስ ወዲያውኑ ለአሴር ነገድ ይሆን ነበር። ይህም አልተፈቀደም ነበር። ሴቶች ሊወርሱ የሚችሉት ደግሞ በቤተሰብ መካከል ወንድ ልጅ ከሌለ ብቻ ነበር።

ይህ ሁኔታ በትክክል ማርያምን የሚመለከት ነበር። እርሷ ከዳዊት ቤተሰብ ስለነበረች ከይሁዳ ነገድ ነበረች። ወራሽ ወንድ ልጅ ስላልነበረ ከአባቷ ወርሳ ነበር። ወራሽ ሴት ልጅ በመሆኗ ልታገባ የሚፈቀድላት ከይሁዳ ነገድ ብቻ ነበር። ሕጉ በእርሷ ላይም የሚሠራ ነበርና። ልክ እንደ ማርያም ዮሴፍም «ከዳዊት ቤት ወገን» ስለነበር ከይሁዳ ነገድ የመጣ ነበር። (ሉቃ. 2:4) ይህ ጉዳይ በቤተልሔም በሃይማኖት ሥርዓትና በመንግስታዊ ጉዳይ በሕግ የታወቀ ነበር። ዮሴፍ ማርያምን ሊያጭና እርሷን በማግባት ውርሷን እንዲወርስ ተፈቅዶለት ነበር።

መፅሐፍ ቅዱስ ዮሴፍና ማርያም የመጋባታቸውን እውነታ ያረጋግጥልናል። የሉቃስ ወንጌል ማርያም እጮኛው እንደነበረች በግልፅ ያሳያል (ሉቃ. 2:5)። በዚህ ጉዳይ ላይ ዮሴፍን የሚመለከት ነገር መሆኑ የተረጋገጠ ምክንያት አለ። በእስራኤል የሆነችን ሴት ያገባ ሁለት አባቶች አሉት። ይኸውም ወላጅ አባትና ሕጋዊ የሆነ የሚስቱ አባት ናቸው። በአሮጌው ባሕል መሠረት በሚስቱ የትውልድ ሐረግ ውስጥ የእሱ ስም በግልፅ ይመዘገባል። ስለሆነም ዮሴፍ በሁለቱ የትውልድ ሐረጎ ውስጥ ይታያል። በመጀመሪያ በማቴዎስ ወንጌል የትውልድ ሐረግ ውስጥ ወላጅ አባቱ በሆነው «የያዕቆብ ልጅ» በሚል ተፅፏል (ማቴ. 1:16)። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በሉቃስ 3:23 በወላጅ አባቱ ላይሆን ሕጋዊ አባት (የማርያም አባት) በሆነው የኤሊ ልጅ በሚልተመዝግቧል። አንድ ሰው በሁለት የትውልድ ሐረግ ውስጥ ስሙ ተጠቅሶ ሲገኝ (በእስራኤል የተለመደ ባህል ስለነበር) ምንም ገለፃ የሚያስፈልገው አልነበረም። ምክንያቱም ወራሹ ሴትን አግብቷልና።

በብሉይ ኪዳን ጊዜያት በእስራኤል ሕዝብ መካከል ባለው ባሕል ባል በወራሽ ሚስቱ የትውልድ ሐረግ ውስጥ ስሙ ይመዘገብ እንደነበር የነህምያ መፅሐፍ ያረጋግጥልናል።

«ከካህናቱም የኤልያስብ ልጆች፣ የአቆስ ልጆች ከገለዓዳዊው ከቤርዜሊ ልጆች ሚስት ያገባ ባለሙያ የተጠራ የቤርዜሊ ልጆች» (ነህ. 7:63) «በስሙም የተጠራ» የሚለው ገለፃ ውርስ የወረሰችውን ሴት ባል በሚስቱ የትውልድ ሐረግ መግባቱን ያረጋግጥልናል። (በአማቹ) በዘኍ 27:1-11 እና 36:1-13 ያለው የሴቶች

የመውረስ ሕግ በዚያን ጊዜ በጥብቅ በሥራ ላይ የዋለ ነበር። በዚህም ምክንያት በቤተ ልሔም ያለው የማርያምና የዮሴፍ ውርስ በይሁዳ ነገድ ውስጥ መቅረት ነበረበት (ከዳዊት ቤተሰብና ከይሁዳ ነገድ ስለሆኑ) ምንም እንኳን ከቤተልሔም 170 ኪሎ ሜትር በስተሰሜን በዛብሎን ምድር ባለችው በናዝሬት ቢኖሩም ርስታቸው ወደ ሌላ ነገድ መተላለፍ የለበትም ስለሆነም አውግስጦስ ቄሳር ዓለሙ ሁሉ እንዲፃፍ ትዕዛዝ ባወጣበት ጊዜ ረጅምና አድካሚ የሆነውን ጉዞ ወደ ቤተልሔም ለመጓዝ ሁለቱም ተገደዋል። ምክንያቱም ርስታቸው ስለነበር ነው። ማርያም በቤተ ልሔም ውርስ ስለነበራት ከባልዋ ጋር ወደ ቤተልሔም ለቆጠራ ለመመዝገብ ሔደች።

ይህ ማርያም ውርስ እንዳላትና ከይሁዳ ነገድ የሆነች ሴት ልጅ ስለመሆንዋ በቂ ማስረጃ ነው። እስከ አሁን የተነጋገርንበትን ብናጠቃልለው በሉቃስ 3:23-38 የተጠቀሰው ያለው የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ የማርያም የትውልድ ሐረግ ነው ወደሚለው መደምደሚያ ያደርሰናል።

## 2. የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ እንደ ማቴዎስ ወንጌል

በሚቀጥለው ጥናታችን ሁለት ቀዳሚ ጥያቄዎችን መመለስ ያስፈልገናል።

1. በማቴዎስ 1:1-17 እና በሉቃስ 3:23-38 መካከል ያለው የቤተሰብ ሐረግ ዋነኛ ልዩነት ምንድን ነው?
2. በማቴ 1:1-17 ያለው የትውልድ ሐረግ የዮሴፍ መሆኑን እንዴት እናረጋግጣለን?

በመጀመሪያ ልዩነታቸውን እንመርምር፤ ቀደም ብለን እንደጠቀስነው የማቴዎስ ወንጌል የሚያተኩረው የእግዚአብሔር ልጅ ተስፋ የተደረገው መሲህና የእስራኤል ንጉስ እንደሆነ ነው። እንደ ማቴዎስ እይታ በፃፈው የትውልድ ሐረግ ላይ ልዩነት አለ፤ በሉቃስ ያለው የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተሰብ በማርያምና በዮሴፍ በመጀመር በናታንና በዳዊት በኩል አልፎ እስከ አዳም ሲሔድ፣ በማቴዎስ የተዘገበው ያለው የትውልድ ሐረግ ዳግም ከአብርሃም ይጀምርና በዳዊትና በሰሎሞን በኩል አልፎ የማርያም ባል ወደ ሆነው ወደ ዮሴፍ ይደርሳል። ለእነዚህ ልዩነቶት ምክንያት አሉ። ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ሉቃስ የኢየሱስ ክርስቶስን የትውልድ ሐረግ የሚገልፀውና የሚያተኩረው በሥጋ ስለመወለዱ ወይም በእግዚአብሔር ልጅ ሰብዕና ላይ (ሰብዕናውን) ነው። ስለዚህ ነው የትውልድ ሐረጉ ወደ መጀመሪያው ሰው ወደ አዳም ያመራው፤ ማቴዎስ የተለየ አቀራረብ አለው። ምክንያቱም





በእግዚአብሔር ልጅ ላይ የሚያተኩረው የእስራኤል ንጉስ በመሆኑ ላይ ነው። ስለዚህ ነው እንደ ሉቃስ አቀራረብ የትውልድ ሐረጉ እንደ ሉቃስ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰብዕና ላይ ያልተመሰረተውና ያላተኮረው። በሌላ መልኩ የመሲሁን ንጉሳዊ የደም ሀረግ ነው የጠቀሰው በጥልቀት ሲታይ ይህ ምን ማለት ነው?

ማቴዎስ የትውልድ ሐረጉን «የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መፅሐፍ» በማለት ይጀምራል ማቴ 1:1።

ይህ ጥቅስ የኢየሱስ ክርስቶስን የደም ሐረግ የእስራኤል ሕዝቦች አባቶች ከንጉሳዊ ቤተሰብ ከሆኑትና ዳዊትን በመጥቀስ እስከ አብርሃም ያለውን ያጠናክራል። ይህን በማድረግ

1. የንጉስ ዳዊት ቤት «ልጅ» ስለሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉስ ነው።
2. «የአብርሃም ልጅ» «ዘር»፣ «ዝርያ» የምድ (አህዛብ ሁሉ የሚባረኩበት ነው። እንደዚሁም እርሱ እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል ኪዳን የገባለት የኪዳኑ ፍፃሜ ነው። (ዘፍ 12: 3፣ 18:18፣ ገላ 3:16) የሚለውን እውነት ላይ እንድናተኩር ያደርገናል።

ይህን አስፈላጊ የሆነውን ግንኙነት በተሻለ መልኩ ለመረዳት በብሉይ ኪዳን ያለውን የደህንነትን ታሪክ መለስ ብለን እንደገና መመርመር ይኖርብናል።

እግዚአብሔር አብርሃምን በመረጠበት ጊዜ ከሕዝበ እስራኤል ጋር የደህንነትን ታሪክ የማቀድ ብቻ ሳይሆን የመጪው ንጉስ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ ከእርሱ እንደሚሆን መለኮታዊ ተስፋንም ሰጠ። እግዚአብሔር ለአብርሃም ምድር፣ ሕዝብና በረከት እንደሚሰጠው ተስፋ ገባለት። (ዘፍ. 12: 1-39፣ 22:18 ከገላ. 3:16 እስከ ኤፌ. 1:3 ጋር አገናዝቡት)። ከብዙ ዓመታት በኋላ ያዕቆብ የሞቱ ጊዜ በቀረበ ጊዜ አስራ ሁለቱን ልጆቹን ወደተኛበት አልጋ ሊባርካቸው በጠራቸው ጊዜ አራተኛው ልጁ ይሁዳ የተለየ ተስፋ ተቀብሎ ነበር፤ ተስፋውም

የበትረ መንግስት ከይሁዳ አይጠፋም፣
የገዢም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል፣
ገዢ የሆነው እስኪመጣ ድረስ፣
የአህዛብ መታዘዝ ለእርሱ ይሆናል የሚል ነበር (ዘፍ 49: 10)።

ከአስራ ሁለቱ ከእስራኤል ነገዶች ይሁዳ የንጉስ ነገድ፣ አንድ ቀን የእስራኤል ንጉስ የሚመጣበት ነገድ ሆነ ይህ ተስፋ ከያዕቆብ በመጀመር በይሁዳ ነገድ ትውልድ በማለፍ አንድ ቀን ነቢዩ ሳሙኤል የበግ እረኛውን ዳዊትን በእስራኤል ላይ ንጉሥ

አድርጎ እስከ ቀባው ጊዜ ድረስ ቀጠለ 1ሳሙ 16: 1-13 በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ይሁዳ የእስራኤል ነገስታት የሚመጡበት ነገድ እንደሆነ ተስፋውን አረጋገጠ:: ዳዊት በኢየሩሳሌም በመላ እስራኤል ሲያስተዳድር እግዚአብሔር ንጉሱና መሲሁ ከእርሱ ዘር እንደሚነሳ ተስፋ ሰጥቶታል:: (2.ሳሙ 7:1-29)

*«ዕድሜህም በተፈፀመና ከአባቶችህም ጋር ባንቀላፋህ ጊዜ ከወገብህ የሚወጣውን ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሳለሁ፣መንግስቱንም አፀናለሁ» (2.ሳሙ 7: 12-13):*

*«ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ፣ ለባርያዬ ለዳዊት ማልሁ፣ ዘርህን ለዘላለም አዘጋጃለሁ፣ ዙፋንኑም ለልጅ ልጅ እመሰርታለሁ» (መዝ (89): 3-4) ::*
*«እኔም ደግሞ በኩሬ አደርገዋለሁ፣ ከምድር ነገሥታትም ከፍ ይላል:: (መዝ. (89) :27)*

ለሺህ ዓመታት ይህ የታደሰው ተስፋ በዳዊት ንጉሳዊ ሐረግ በኩል አልፎ በመጨረሻ «የዘመኑ ፍፃሜ እስኪደርስና» ለማያዊው ንጉሥ ከድንግል ማርያም በሥጋ ሰው ሆኖ እስከመጣ ጊዜ ድረስ ቀጠለ (ገላ. 4:4):: መልአኩ በናዝሬት የመሲሁን መወለድ ባወጀበት ጊዜ ለዳዊት የተሰጠውን ተስፋ በጥብቅ አረጋገጠ::

*«እነሆም ትፀንሻለሽ፣ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፣ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ እርሱም ታላቅ ይሆናል፤ የልዑል ልጅም ይባላል፣ ጌታ አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል. በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሳል፣ ለመንግስቱም መጨረሻ የለውም» (ሉቃስ 1:31-33)::*

ስለሆነም ስለሚመጣው የእስራኤል ንጉስ መሰኮታዊ ተስፋ በአብርሃም ጀመረና፣ በዳዊት መቀባት የእስራኤል መንግስት እስከተመሰረተበት ጊዜ ድረስ ንጉሳዊ በሆነው በይሁዳ ነገድ ትውልድ በኩል ቀጠለ:: ከዚያም በሰሎሞን ቤትና በሌሎቹም ነገስታት በኩል በመሰኮት የተመሰረተው የእስራኤል መንግስት በባቢሎናውያን እስከተደመሰሰ ጊዜ ድረስ ቀጠለ:: ነገር ግን ተስፋው ሳይነካ በባቢሎናውያንም ማራኪነት ሳይደመሰስ፣ በዳዊት የዘር ሐረግ በኩል የዘላለሙ ንጉስና መሲሁ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ መጣበትና ተስፋው በክብር እስከተፈፀመበት ጊዜ ድረስ ቀጠለ::





በዳዊት የተጀመረውን ንግስና ጨምሮ መላው የእስራኤል ነገስታት በእግዚአብሔር የተቀቡ ነበሩ:: በዕብራይስጡ «የተቀባው» ለሚለው ቃል «መሲህ» የሚለው ነው:: የተቀባው (መሲሁ) ክርስቶስ የመጣው ለዳዊት ተስፋ ከተሰጠው ሐረግ ነው:: ከዳዊት ቤተሰብ የሆነ በእስራኤል የነገሰ ማንኛውም ንጉስ ለሚመጣው ንጉስ መንገድ የሚያዘጋጀና ለኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ ጠራጊ ነበር::

ይህን የደህንነት ታሪካዊ መግለጫ በአእምሮአችን ብንይዝ በማቴዎስ ስለተመዘገበው የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ ለመረዳት ችግር አይገጥመንም:: ከአብርሃም እስከ ዳዊት፣ ከዳዊት እስከ ባቢሎን ምርኮ፣ ከባቢሎን ምርኮ እስከ ክርስቶስ ያለው ጊዜ ሦስት ዋና ዋና ጊዜያት ሲኖሩት እያንዳንዱም ጊዜ 14 ትውልዶችን የያዘ ነው (ማቴ 1:17):: እነዚህ ሁሉ ትውልዶች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከእስራኤል መንግስት ጋር ግንኙነት አላቸው:: ሆኖም ይህ መስመር ከአብርሃም ከዳዊትና ከዮሴፍ እስከ ክርስቶስ ድረስ ሁለት ሺ ዓመታት ጊዜን ወስዶአል:: የእግዚአብሔር ልጅ ስም በዚህ የነገስታትና የተስፋዎች የትውልድ መስመር የመጨረሻው ሆኖ መመዝገቡ መሲህ መሆኑን አስረግጦ ለማስረዳት የታቀደ ዕቅድ ነው:: ይህም የእግዚአብሐር ልጅ የእስራኤል ንጉስ እንደሆነ ካተኮረው ከእርሱ መሰረታዊ እይታ ጋር ይስማማል::

በማቴዎስ ያለውን የትውልድ ሐረግ ከተረዳን የሚነሳውን ሌላውን ጥያቄ ለመፍታት ይረዳናል:: ሁለቱን የትውልድ ሐረጎች ስንመረምር ማቴዎስ ከሉቃስ ይልቅ የዘገበው ጥቂት የአባቶችን የትውልድ ሐረግን ነው:: ማቴዎስ ከጥቂቶች ታዋቂዎች በስተቀር ሁሉንም የትውልድ ሐረግ አላካተተም:: ለምሳሌ ሠቃት የሌላቸውንና ኃጢአተኞችን ባዕድ አምላኪ የሆኑ ነገስታትን ትቷል:: ምክንያቱም በማዳን ታሪክ ውስጥ አላስፈላጊ ናቸውና:: ይሄ ችግር የሚያመጣ አይደለም፤ ምክንያቱም ማቴዎስ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠውን ተስፋ የመፈፀሙን ነገር ሊናገር ስለፈለገ እንደሉቃስ ሁሉንም የትውልድ ሐረግ መዘርዘር አላስፈለገውም:: ስለዚህ ነው የማቴዎስ ወንጌል በበለጠ ስለ እግዚአብሔር ልጅ መንፈሳዊና ምሳሌያዊ ፍች የያዘው:: የሉቃስን የትውልድ ሐረግ ግን የምንረዳው የክርስቶስን የደም ሐረግ እስከ አዳም በመሄድ ለማረጋገጥ እንደሆነ ነው::

ስናጠቃልለው በማቴዎስ ያለው የትውልድ ሐረግ ለለምን የዩሴፍን ቤት እዳመሰከተ የሚያሳየውን ጥያቄ ለመግለፅ እንገደዳለን::

## የዮሴፍ የትውልድ ሐረግ ማቴ 1:1-17

በሉቃስ 3:23-38 ያለውን የቤተሰብ መስመር የማርያምን የትውልድ ሐረግ በመጀመሪያ እይታ ለመገንዘብ ችግር ቢኖርም በተቃራኒው በማቴ 1:1-17 ባለው ስለ ዮሴፍ ይህ ችግር አይኖረንም:: ምክንያቱም የእርሱ ንጉሳዊ በሆነ የደም ሐረግ ሕብረት ስለመኖሩ በግልፅ የታተተ ነው::

«ያዕቆብ ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን የወለደችውን የማርያምን እጮኛ ዮሴፍን ወለደ» (ማቴ. 1:16) ስለሆነም ዮሴፍ የያዕቆብ የሥጋ ልጁ ነበር እንጂ የኤሊ ልጅ አልነበረም (ሉቃስ 3:23):: ያለ ምንም ጥያቄ ዮሴፍ ከዳዊትና ከሰለሞን የትውልድ ሐረግ የሆነ ነው:: ስለሆነም በማንኛውም ጊዜ ወደ አያቶች መለስ በማለት እነዚህን ንጉሳዊ ቤተ ሰቦች መጥቀስ ይችላል:: በማቴዎስ ባለው ንጉሳዊ የትውልድ መስመር መሰረት ማንኛውም ሰው የዳዊትን የሰለሞንና የዮሴፍን የቤተሰብ መስመር በመጥቀስ ጌታ ኢየሱስ በዳዊት ዙፋን ላይ የንጉስነት መብት እንዳለው ማረጋገጥ ይችላል:: ይህ መብት ተቀባይነት ያገኘ ነበር:: ምክንያቱም ዮሴፍ ማርያምን ስላገባና የኢየሱስ አሳዳጊ አባት ስለሆነ ነው (ሉቃ 3:23፣ 4:22):: የማርያም የትውልድ ሐረግ በዳዊት በኩል ወደ ናታን ቤት ስለሚሄድ ይህ ማረጋገጫ በእርሷ በኩል የሚጎድለው ነገር አለው (ሉቃ. 3:31):: ምንም እንኳን እነዚህ ከዳዊት የመጡ ዝርያዎች ቢሆኑም በእስራኤል ላይ በንግስና አልገዙም ነበር:: ስለሆነም ከዳዊት ከሰሎሞንና ከዮሴፍ ንጉሳዊ መስመር ውስጥ የሆኑ አይደሉም::

ነገር ግን ይህን ሃሳብ እንደገና ማጠናከር ይኖርብናል:: ምንም እንኳን ኢየሱስ ክርስቶስ የዮሴፍን ልጅ ቢባልም እንኳን ከዮሴፍ ጋር ምንም ዓይነት ተፈጥሮአዊ ግንኙነት አልነበረውም:: ክርስቶስ ከንፅህት ድንግል የተወለደና እግዚአብሔር ብቻ አባቱ የሆነ ማንነት ነው (ሉቃስ 31:35፤ ኢሳ 7:14):: ስለሆነም ከዮሴፍ ጋር በስጋ ዝርያ የሚገናኙበት ምንም ነገር የለም:: ዮሴፍ አሳዳጊው (ሞግዚቱ) ብቻ ነበር:: ይህ በማቴዎስ ያለው የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ በበለጠ መንፈሳዊና ምሳሌያዊ ጠባይ እንዳለው ይበልጥ ያጠናክረዋል:: ምክንያቱም ኢየሱስ ከዮሴፍ በሥጋ የተወለደ አይደለምና:: በሥጋ የንጉሳዊ ቤተሰብ ስለመሆኑ ስህተት ከሌለው መሰረታዊ ከሆነው ከመፅሐፍ ቅዱስ ምስክርነት ጋር የሚጋጭ መሆን የለበትም (ማቴ 1:16)::





መግለጫ ክፍል 2:

# ከመፅሐፍ ቅዱስ የጊዜ ቆጠራ ጋር ያለው ችግር

የእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ በዓለም ታሪክ ውስጥ የሚከናወን ከሆነ የዓለም ታሪክ ቀናትን እንድንጠቀም እንገደዳለን:: ከክርስቶስ ልደት በፊትና ከክርስቶስ ልደት በኋላ በሚለው በእኛ የጊዜ ቆጠራ ላይ እናርፋለን:: ነገር ግን ይህ ካሌንደር (የጊዜ አቆጣጠር) ትክክል ስላልሆነ ችግር ይኖረናል::

## የእግዚአብሔር ልጅ ሰው የሆነው መቼ ነው?

በንጉሱ በአውግስጦስ ዘመነ መንግስት የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ሆኖ ወደዚህ ወደ ተረገመው ዓለም በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ይህን ልዩ የሆነውን ታሪካዊ ቀን ለመመዝገብ ካሌንደር (የቀን መቁጠሪያ) በእጁ የያዘ ታሪክ ፀሐፊ አልነበረም:: ከዓለሙ አዳኝ ልደት ከአምስት መቶ ዓመት በኋላ ነው አንድ ሰው ኢየሱስ ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም የመጣትን ዘመን ፍለጋ የጀመረው:: ይህም ተደርጎ የነበረው ሮም በነበረው ጳጳስ በዳግማዊ ዮሐንስ ከ533-535 እ.አ.አ. ነበር:: እጅግ የከበረው የአዳኙ ኢየሱስ ክርስቶስ መቼ እንደተወለደ መርምሮና ጥናት እንዲያደርግ ዳዮኒስስ ኤክሲገስ ለተባለው ምሁር መነኩሴ ሥራውን ሰጠው:: ዲዮኒሰስ ኤክሲገስ ዝርያው ከስኬዝ የሆነና በሮም ከ500-550 ዓ.ም. ድረስ የኖረ ነበር:: በሮማውያን ነገስታት ጊዜ ላይ በማረፉ ምክንያት በምርምሩ ጥቂት ስህተት ገባበት:: ብዙ ነገስታት ለዓመታት በአንድነት ገዝተው ስለነበር በዚህ ምክንያት የምርምሩ ውጤት ትክክል አልነበረም:: ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው በዜሮ ዓመት ላይ ሳይሆን ስድስት ወይ ሰባት ዓመት ቀደም ብሎ ነበር ::

ይህም ቢሆን ሁል ጊዜ በጥናታችን የምንጠቀመው ሲወርድ ሲዋረድ በደረሰን (Traditional) አሁን በእጃችን ባለው ካሌንደር ነው:: ፍላቪየስ ጆሴፉስ የተባለው አይሁዳዊ የሆነው ታሪክ ፀሐፊ «ጥንታዊ» የአይሁዶች ታሪክ «የአይሁድ ጦርነቶች» በተባሉት መፅሐፍቱ ሕፃናትን በቤተ ልሔም ያስገደለው ታላቁ ሄሮድስ የሞተው ሚያዝያ 2 ቀን የሮም ከተማ ከተመሰረተች ከ750 ዓመታት በኋላ ነው በማለት ፅፏል:: የሮም ከተማ የተመሰረተችው ከጌታ ኢየሱስ ልደት ከ753 - 754 ኢ.ክ.ል.በ ከሆነ ሄሮድስ የሞተው ከጌታ ልደት አራት ዓመት ቀደም ብሎ ነው ማለት ነው:: ስለሆነም የእግዚአብሔር ልጅ የተወለደው በ6 ከ.ክ.ል.በ ነው ማለት ነው:: ምክንያቱም በማቴ 1:16 ላይ የተገደሉት ሕፃናት ሁለት ዓመትና ከሁለት ዓመት በታች እንደነበሩ ተፅፏል:: ጥቂቶች ደግሞ በከዋክብት በሚደረገው ቆጠራ በመጠቀም የጌታ ልደት የሆነው በ7 አ.ክ.ል.በ (ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት) ነው

ብሰዋል:: እነዚህ ዘገባዎች እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ ከሆነ ራሳችንን ከእነርሱ እናርቅና ስፍራ ሳንሰጣቸው እዚሁ እንተዋቸውና እንለፍ::

## የእግዚአብሔር ልጅ የተሰቀለው መቼ ነው?

ይህን ጊዜ ስመቁጠር በጣም አስቸጋሪ ነው:: ከዚህ በፊት በገጽ 141 ላይ (ዐነህ. 1፣2 እና 2:1) በመመስረት ስለ ሰባው ሱባኤ (ሳምንታት) ስመግለፅ ሞክረናል:: በእነዚህ ክፍሎች የፋርስ ንጉስ ቀዳማዊ አርጤክስስ በነገሰ በ20ኛው ዓመት ሰጠጅ አሳላፊው ሰነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች እንዲሰራ እንደፈቀደለት ተፅፎአል:: በጥሩ ሁኔታ በተመዘገበ ታሪክ ይህ ንጉስ የፋርስ ንጉስ ሆኖ የነገሰው ከ465-464 ከ.ክ.ል.በ እ.እ.አ. ባለው ጊዜ ነበር:: ስለሆነም 445 ከ.ክ.ል.በ የንግስናው ሃያኛው ዓመቱ ነበር ማለት ነው:: ከ483 ላይ 445 ከ.ክ.ል.በ ብንቀንስ ጌታ የተሰቀለው በ38 ዓ.ም ማለት ነው:: (ዳን. 9:24-27) ውስጥ 62ኛውንና እና 7ኛውን ስለሚለው ሱባኤ (ሳምንታት) በገፅ 127 ይመልከቱ):: ነገር ግን ይህ የማይሆን ነገር ነው፣ ምክንያቱም ጴንጤናዊው ጲላጦስ በይሁዳ ላይ ገዢ የነበረው ከ26-36 ዓ.ም ስለነበርና ቀያፋም ሊቀ ካህናት የነበረው ከ18-37 ዓ.ም ስለነበር ነው:: እነዚህን ቀናት ሁሉ ስንቆጥር ከ533 ዓ.ም ጀምሮ በክርስትናው ዓለም የምጠቀምበትን ትክክል ባልሆነው የዳዮነሲስ ኤክሲገስ ካሌንደርን ነው:: ሌላ የፋርስን ታሪክ በተመለከተ የጊዜ ቆጠራ የፋርስ ንጉስ የቀዳማዊ አርጤክስስን 20ኛውን ዓመት በ458 እና በ445 መካከል በ13 ዓመታት ልዩነት ያደርገዋል:: ስለሆነም አንድ ሰው በዚህ በሜዶናውያን ዓመት ቢቆጥር የፋርስን ንጉስ 20ኛውን ዓመት 451 እ.ክ.ል.በ ላይ ያደርገዋል:: ከ483 ላይ 451 ሲቀነስ ውጤቱ ጌታ የተሰቀለው 32 ዓ.ም ላይ ነው ወደሚለው ያደርሰናል:: አንድ ፕሮፌሰር ይህን በማፅደቅ በፋርሳውያን መነሻዎችና በግሪኩ ታሪክ ፀሐፊ በሆነው በሄሮዲት (ከ490-424 እ.ክ.ል.በ በነበረው) ላይ በመመስረት የፋርስን ታሪክ ፅፏል::

የአይሁድ ቀን አቆጣጠር በጨረቃ ልደት ላይ የተመሰረተና የዓመት ቀናቸው 360 ቀናት መሆኑን በአእምሮአችን መያዙ ለመረዳታችን የሚረዳን ይሆናል:: ስለዚህ ነው በራዕይ 11:2-3፤ 12:6፤ 14፣ 13:5 የተጠቀሱት $3^{1/2}$ ዓመታት በ42 ወርና በ1260 ቀናት የተገለፁት:: መፅሐፍ ቅዱስ የዓመቱ ቀናትን 360 ቀናት አድርጎ ስለሚቆጥር የአይሁድ ካሌንደር ከእኛ ካሌንደር የአምስት ቀናት ልዩነት አለው:: አይሁዶች ካሌንደራቸውን ከእኛ ካሌንደር ጋር ለማስተካከል አዳር ከተባለ አስራ ሶስተኛ ወር በአዳርና በኒባን ወራት (በጥርና በየካቲት መሃል ማለት ነው) መካከል መጨመር አስፈለጋቸው:: 483 ዓመታትን 360 ቀናት ባለው





የአይሁድ ቀን አቆጣጠር ብንቆጥር 2415 ቀናት ይኖሩናል (ይህም 7 ዓመት ማለት ነው):: በዚህ መንገድ የስድስቱን ወይም የሰባቱን ዓመት ጥያቄ ስንፈታ የኢየሱስ ክርስቶስን ስቅለት በ32 ወይም 33 ዓ.ም ገደማ እናደርገዋለን::

## እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡት መቼ ነው?

ይህ ሁኔታ በደህንነት ታሪክ ውስጥ ከእግዚአብሔር በሲና ተራራ መገለጥ፣ ክአስርቱ ትዕዛዛትና ከመገናኛ ድንኳኗ መሰራት ጋር የተያያዘ (የተዛመደ) ነው:: በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ በእምነት በማረፍ በአስራ ሁለተኛው ወይም በአስራ ሦስተኛው ምዕተ ዓመት ክክርስቶስ ልደት በፊት የእስራኤል ልጆች ወደ ከንዓን ገብተዋል ተብሎ በዘመኑ የሃይማኖት ሰዎች የተሰጠውን የተሳሳተ አቆጣጠር እንቃወማለን:: መፅሐፍ ቅዱስ ለራሱ እንዲናገር እንፍቀድና ትኩረታችንን ወደ ሚከተሉት ቀናት እናድርግ::

1. እንደ መሳፍንት 11:26 የእስራኤል ልጆች በእስራኤል ምድር በምስራቅ ዮርዳኖስ በምናሴና በገለአድ ለ300 ዓመታት መኖራቸውን እናያለን::
2. እንደ ሐዋርያት ሥራ 13:20 እስከ ነቢዩ ሳሙኤል ድረስ ለ450 ዓመታት እግዚአብሔር መሳፍንት እንደ ሰጣቸው እንመለከታለን:: የእስራኤል ልጆች እስከ 12ኛውና 13ኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ከግብፅ ሳይወጡና ወደ ከነዓን ካልገቡ እዚህን 450 ዓመታት እንዴት እናስታርቃቸዋለን?
3. በ1ነገ. 6:1 መሠረት ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን መስራት የጀመረው የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ከወጡ ከ480 ዓመታት በኋላ ነው:: የእስራኤል ልጆች እስከ 12ኛውና እስከ 13ኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ከግብፅ ሳይወጡና ወደ ከነዓን ሳይገቡ ክቆዩ እነዚህን 480 ዓመታት እንዴት እናስተናግዳቸዋለን::

### ምን የታመኑ የዓመታት ቁጥሮች ይኖሩናል?

በምንጥላቸው ቀናት ምትክ የታመኑትን ቀናት እንጠቀማለን:: እስራኤል በ1996 እ.ኢ.አ የኢየሩሳሌምን 3000ኛው የልደት ቀን አከበረች:: ከ3000 ላይ 1996 ብንቀንስ ወደ 1004 ከ.ኢ.ል.በ ያመጣናል:: ይህም ጊዜ ንጉስ ዳዊት የኢያቡሳውያንን ከተማ ድል ያደረገበትና ኢየሩሳሌምን የ12ቱ ነገዶች ዋና ከተማ ያደረገበት ጊዜ ነበር (2ሳሙ. 5:1-10፤ 1ዜና 11:1-8):: እንደ አይሁድ ቀን አቆጣጠር እነዚህ ቀናት በትክክል የታመኑ ናቸው:: ንጉስ ዳዊት በ1012 ከ.ክ.ል.በ ንጉስ ከመሆኑ አስቀድሞ ለ$7^{1/2}$ ዓመት በአይሁድ ነገድ ላይ በኬብሮን ነግሷል:: በዚያው ዓመት ንጉስ ሳኦል

ሞተ። በ ሐሥ. 13:21 መሰረት ሳኦል በእስራኤል ላይ ለ40 ዓመት ነግሷል። ስለሆነም በእስራኤል ላይ የነገሰው በ1052 ከ.ክ.ል.በ ነው ማለት ነው። ከእርሱ በፊት የመጨረሻው መስፍን የሆነው ሳሙኤል ነቢይ ሆኖ አገልግሏል። ሳኦል በነገሰበት 450 የዘመነ መሳፍንትን ጊዜ ላይ ብንደምርበት ወደ 1502 ከ.ክ.ል.በ ያደርሰናል። ከመሳፍንት በፊት እስራኤላውያን በኢያሱ መሪነት የተስፋይቱም ምድር ድል በማድረግ ያሂት። ይህን ለመፈፀም ብዙ አስቸጋሪ ዓመታት ፈጅቶባቸዋል። እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ከመግባታቸው በፊት በምድረ በዳ ለ40 ዓመታት ቆይተዋል። እስራኤላውያን ከግብፅ ከመውጣታቸውና በምድረ በዳ ለ40 ዓመታት ከመንከራተታቸው በፊት በግብፅ ለ430 ዓመታት ኖረዋል (ዘፀ. 12:40)። እነዚህ ቁጥሮች ልክ ናቸው፣ አቆጣጠሩም ትክክል ነው።

## ከቤተ መቅደሱ መሰራት ከ480 ዓመት በፊት ከግብፅ መውጣት ሆነ

እስከ አሁን በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባሉት አስተማማኝ (ትክክል) በሆኑት ቁጥሮች እየሰራን ነበር። ጥናታችን ስንቀል ግን የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ስለ ወጡበት ጊዜ ሌላ ችግር ይገጥመናል። ንጉስ ዳዊት በ1012 አ.ክ.ል.ብ ከነገሰና ለ40 ዓመታት ከገዛ፣(2ሳሙ 5:4-5) ንጉስ ሰሎሞንም የነገሰው በ972 አ.ክ.ል.በ ነው ማለት ነው። እርሱ ደግሞ በእስራኤል ላይ ለ40 ዓመታ ገዝቷል። (1ነገ 11:42) ሰሎሞን በነገሰ በአራተኛው ዓመት ቤተ መቅደሱን መስራት ጀመረ (1ነገ. 6:1፣ 37) ይህም ዘመን 968 አ.ክ.ል.በ ነበር።

እንደ 1ነገ. 6:1 የቤተ መቅደሱ ግንባታ የተጀመረው ከግብፅ ከወጡ ከ480 ዓመታት በኋላ ነበር። ከሰሎሞን ንግስና ከአራት ዓመት በኋላ ይህን 480 ዓመት ብንቀንስ (ከ972-4 = 986) የእስራኤል ልጆች ከግብፅ የወጡት በ1448 አ.ክ.ል.በ ነበር ወደሚለው ድምዳሜ ላይ ያደርሰናል። ይህን ቀጠራ ብንከተል እስራኤላውያ ከግብፅ የወጡበትን ጊዜ ወደ 50 ዓመት ልዩነት ያመጣዋል። የተባረከው የስነ መለኮት በጀርመን ካለችው ከውፐርታ ፕሮፌሰር የሆነው ዶክተር አብርሃም ሚይስተር (1901-1990) አዳም የተፈጠረው በ4160 አ.ክ.ል.በ ነው በማለት ቀጠራውን ጀመረና አብርሃም የተወለደው በ2212 አ.ክ.ል.በ እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡት በ1492 አ.ክ.ል.በ ነው ብሉአል። ስለሆነም እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡት በ1500 አ.ክ.ል.በ አካባቢ ነው ወደሚለው ማጠቃለያ ልንደርስ እንችላለን። ሌሎቹን በመፅሐፍ ቅዱስ ሊረጋገጡ የማይችሉትን በኢንሳይክሎፒድያ ውስጥ ያሉትን አስተያየቶች ልናስወግዳቸው ይገባናል።





ለምሳሌ ከ1492 አ.ክ.ል.በ ወደ ኋላ ብንሔድ እስራኤላውያን በግብፅ ለ430 ዓመታት መቆየታቸውን እናውቃለን (ዘፀ. 12:40) ይህ ከገላትያ 3:16-17 ካለው ጋር ይስማማል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ሕግ የሰጠው ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ቃል ኪዳን ከገባላቸው ከ430 ዓመታት በኋላ ነበር። እነዚህ በግብር የቆይታ 430 ዓመታት ወደ ኋላ ወደ 1992 አ.ክ.ል.በ ይወስዱናል። ይህ ጊዜ የእምነት አባት የሆነው ያዕቆብ በ130 ዓመቱ ከመላ ቤተሰቡ ጋር ወደ ግብፅ የወረደበት ጊዜ ነበር። ከእነዚህ 130 ዓመታት ብንነሳ የያዕቆብና የኤሳው ልደት በ2052 አ.ክ.ል.በ እንደነበር እንችላለን። እነርሱ ሲወለዱ አባታቸው ይስሐቅ 60 ዓመቱ ነበር። ይህ ማለት ይስሐቅ የተወለደው በ2112 አ.ክ.ል.በ ነበር ማለት ነው። ይስሐቅ ሲወለድ አብርሃም 100 ዓመቱ ነበር። ስለሆነም አብርሃም የተወለደው በ2212 አ.ክ.ል.በ ነበር ማለት ነው። በቻርቱ ላይ የአብርሃምን የልደት ጊዜ ወደ 2150 አ.ክ.ል.በ በማድረግ አክብበነዋል።

እነዚህ ገለፃዎች ሁል ጊዜ ትክክለኛውን ጊዜ መስጠት አዳጋች እንደሆነ ግልፅ ያደርጉልናል። ነገር ግን ከተጋነኑ ወዲያና ወዲህ ከሚያወዛውዙን ቁጥሮች ጋር መሆን አንፈልግም፣ ሆኖም በመፅሐፍ ቅዱስ በተሰጡት በጣም ልንረካ ያስፈልገናል። በመፅሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱት ሁኔታዎች በአመዛኙ ትክክለኛውን የተቃረበ ጊዜን ለመስጠት ያስችሉናል። መፅሐፍ ቅዱስ የደህንነት ታሪክ የእግዚአብሔርን የደህነትን እቅድ በመግለፅ የሚያሳስበን ነው። መፅሐፍ ቅዱስ በተቀዳሚ የሚገልፅልን የኢየሱስ ክርስቶስን የማዳን ሥራውን እንጂ ቁጥርን አይደለም።

መግለጫ ክፍል 3:

# በእግዚአብሔር የማዳን እቅድ ውስጥ የቤተ መቅደሶች መስፋፋት


በዚህ ክፍል በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ የቤተ መቅደሱን የተሰያዩ ንድፎችና እነርሰም እንዴት እንደተቀያየሩ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተፃፈውን እናጠናለን::

የቤተ መቅደሱ መኖር ዋና ዓላማ የቅዱስ እግዚአብሔርና የኃጢአተኛው ሰው መገናኛ ቦታ ነው::በዚህ ቦታ ካህናት መስዋዕት ያቀርባሉ፣ ሊቀ ካህናቱ ደግሞ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቃሉ:: ከሰው ውድቀት በፊት ቤተ መቅደስ አልነበረም፣ ምክንያቱም ሰው ያለ ኃጢአት ስለነበር መስዋዕት የሚያስፈልገው አልነበረምና:: እንደዚሁም በአዲሱ ሰማይና በአዲሱ ምድር ቤተ መቅደስ አይኖርም፣ምክንያቱም ኃጢአት ለአንዴና ለዘላለም የተደመሰሰ ስለሚሆን ነው::

በቻርቱ ላይ የተሰያዩት ቤተ መቅደሶች በማዳን ታሪክ ውስጥ ጠቅላላውን ስፋት የያዙበትን የራሳቸውን መስመር መስርተዋል:: በአስር ሰዎችም ተከፋፍለዋል እሁን የእያንዳንዱን ይዘትና ፍቺ በግልፅ እንመረምራለን::

## 1. ቤተ መቅደስ ያልነበረበት ጊዜ

### ዘፍ 1 እና 2



ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊት በሚያስደንቅ ደስታ የሚደሰትና ከእግዚአብሔር ጋር ፍፁም የሆነ ህብረት ነበረው:: ሰው ያለ ኃጢአት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ይኖር የነበረውም ያለ ኃጢአት በሆነ ዓለም ውስጥ ነበር:: ከእግዚአብሔር ጋር እና ከተፈጥሮ ጋር በነበረው ሕብረት ምንም የኃጢአት ዱካ (ምልክት) አልነበረም ምክንያቱም ኃጢአት አልነበረምና:: በኤደን ገነት የእግዚአብሔር መገኘት ከሰው ጋር ነበር (ዘፍ. 3:8):: ሰው በማንኛውም ጊዜ ከአምላክ ጋር የሚገናኝበት መንገድ ነበረው:: ይህ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው የቅርብ ግንኙነትና ደስታ በሰው ቃላት ሊገለፅ የማይቻል የሚቀጥልና ክብር የተሞላበት እውነታ ነበር ነገር ግን ሰሁለቱ ሰዎች ለአዳምና ሔዋን ብቻ የተወሰነ ነበር:: ሁለቱም ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው






ሕብረት ያልታወከና ያልተቋረጠ ስለነበር ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት ቤተ መቅደስ ወይም መስዋዕት አያስፈልጋቸውም ነበር::

## 2. መስዋዕት


### ዘፍ 4:4፣ 8:20



ከሰው ውድቀት በኋላ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ሕብረት በማጣቱ ምክንያት መስዋዕትና መቅደስ አስፈለገው:: በቀደመው ታሪክ ማንኛውም ሰው ያለ ሁሉ ያለ ልዩነት መስዋዕት ሲያቀርብ ተስተውሰዋል:: ለምሳሌ ስለ ሰዎች ሲታሰብ ቃየንና አቤል፣ ኖህ፣ አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብና ኢዮብን እንጠቅሳለን:: (ዘፍ.4:3-4፤ 8:20፤ 15:6፤ 26:25፤ 31:54፤ ኢዮብ 1:5):: ከቃየን በስተቀር ሁልጊዜ ሰዎች የእንስሳ ደም ይሰዉ ነበር:: ምክንያቱም ስለ ኃጢአተኛው በምትክነት በሚሞተው በደል በሴለበት እንስሳ ያምኑ ስለነበር ነው:: እግዚአብሔር የመስዋዕት ሥርዓት ሰጠ፣ ምክንያቱም ኃጢአተኛው ሰው እንደገና ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብ እንዲችል፣ ይቅርታንና ስርየትን እንዲያገኝ ስላስፈለገ ነው:: እስከ ሙሴ እንኳን እያንዳንዱ የቤተሰብ ኃላፊ (አባት)፣ እያንዳንዱ የነገድ መሪ ስለ ራሱና ስለ ቤተሰቡ መስዋዕት ይሰዋ ነበር::

## 3. ተየአምልኮ ድንኳን

### ከ.ክ.ል.በ 1492 /1448 እስከ 968/961



እግዚአብሔር እስራኤላውያን ከግብፅ ካወጣቸው በኋላ በሲና ተራራ ላይ አዲስ የመስዋዕትና የቤተመቅደስ አምልኮ ስርዓትን ሰጣቸው:: በዚህ ጊዜ ማንኛውም ሰው በያሰበት ያቀርብ የነበረው ግላዊ የመስዋዕት ጊዜ አከተመ::


በዚህ ምትክ ሙሴ የቤተ መቅደሱን፣ ከመስዋዕቶቹ፣ ከካህናትና ከአምልኮ ጋር ያለውን የተከበረውን ራዕይ (መገለጥ) ተቀበለ:: ቤተመቅደሷ የመገናኛ ድንኳን የእግዚአብሔር ማደሪያ በሚል ይታወቅ ነበር:: ግልጽ የሆነው የእግዚአብሔር ክብር (ሽኪና) በዚህች ድንቅ ድንኳን ውስጥ ባለው በቅድስተ ቅዱሳን ያድር ነበር:: በየቀኑ ካህናት ተፈላጊውን መስዋዕት ያቀርባሉ:: ሊቀ ካህናቱበታላቁ የስርየት ቀን (ዮም ኩፑር) መላ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር ያስተራርቅ ነበር:: በዚህች ምድር ላይ በድንኳኗ በሚደረገው

መስዋዕቶችና በካህናቱ አገልግሎት ወደ እግዚአብሔር ፊት የመቅረቢያ መንገድ የነበራቸው እስራኤላውያን ብቻ ነበሩ:: ሌሎቹ አሕዛብም በጣዖት ቤታቸው ጣዖትን ያመልኩ ስለ ነበር በሰይጣንና በሰራዊቱ ፊት የሚቀርቡበት መንገድ ነበራቸው (1ቆሮ. 10:20) :: ነገር ግን የድንኳኗ እውነተኛ አመልካችነት በጣም ጥልቅ የሆነ አመልካችነት ነበረው:: የድንኳኗ፣ የክህነቱና የካህናቱ አገልግሎት፣ የመስዋዕቶቹና የቤተ መቅደሱ ንዋየ ቅድሳቱ በሙሉ የጌታ የአዳኙ የኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ ተምሳሌት ነበሩ:: በዕብራውያን መልዕክት «ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና» ተብሎ ተገልጧል (ዕብ. 10:1)::

እንዲሁም *«እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና አካሉ ግን የክርስቶስ ነው»* ተብሎ ተፅፏል (ቆላ. 2:16-18)::

## 4. የሰሎሞን ቤተመቅደስ

### ከ.ክ.ል.በ 968/961 - 586




ለ480 ዓመታት ገደማ ድንኳኒቱ የእግዚአብሔርና የሕዝቡ መገናኛ ሆና አገልግላለች:: ንጉስ ሰሎሞን በነገሰ በአራተኛው ዓመት ትክሉን ቤተመቅደስ መስራት ጀመረ:: የቤተ መቅደሱም ክብር በኢየሩሳሌም ከተሰሩት ሁሉ በጣም የላቀ ነበር:: (1 ነገ 6:1) ይህን ታላቅ ሕንፃ ለመስራት መጠኑ ብዙ የሆነ ወርቅና ብር ተጠቅመው ነበር:: የቤተ መቅደሱ ሥራ በሰባተኛው ዓመት እንዳበቃ በተመረቀበት ቀን ግልፅ የሆነው የእግዚአብሔር ክብር (ሸኪና) ካህናቱ ገብተው ማገልገል እስከማይችሉበት ድረስ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ገብቶ ነበር:: (1ነገ 8:10-11፤ 2ዜና 5:14):: በዚሁ ጊዜ ተንቀሳቃሽ የነበረችው የድንኳን መቅደስ የአገልግሎቷን ዘመን ፈፀመች::

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ማንኛውም መስዋዕት ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ባሰራው ቤተመቅደስ የሚደረግ ሆነ:: ከዓመታት በፊት እግዚአብሔር ቤተመቅደሱ በሞርያ ተራራ ላይ የሚሰራበትን ትክክለኛውን ቦታ ለሙሴ ገልጾለት ነበር:: ነገር ግን እግዚአብሔር ሕዝቡ ከአምላካቸው ጋር የሚገናኙበት በእስራ ሁለቱ ነገዶች መካከል ሊሰራ ስላለው መቅደስ ቀደም ብሎ እቅዱን በዘፀ. 20:24 እና በዘዳ. 12:4-6 ላይ ሰጥቶ ነበር:: እርሱ ኢየሩሳሌምን መረጠ፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ልጅ ከሺ ዓመት በኋላ ከሞርያ ተራራ በስተ ሰሜን ባለው በቀራንዮ ኮረብታ ላይ ዘላለማዊ ደህንነትንና ከእግዚአብሔር ጋር የማስታረቅን ሥራ የሚፈጽም ነበርና:: (2ዜና.






5:19-21) ኢየሱስ ክርስቶስ በራሱና በፈፀመው የማዳን ሥራ (ክርስቶስ) እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠውን የመቅደሱን፣ የመስዋዕቶቹንና የክህነትን ጥላና ተምሳሌት ለአንዴና ለዘላለም ፈፀመው::

## 5. የዘሩባቤል ቤተ መቅደስ

### ከ.ክ.ል.በ 516 እስከ 70




ባቢሎናውያን በ586 ከ.ክ.ል.በ የሰሎሞንን ቤተ መቅደስ ደመሰሱት (አፈራረሱት) ከ70 ዓመት በኋላ በ516 ከ.ክ.ል.በ ሁለተኛው ቤተ መቅደስ በእስራኤል ተሰራ:: ይህ የቤተመቅደሱም የተሰየመው በአይሁዱ መስፍን በዘሩባቤል ስም ነበር::

ከጥቂት ምዕተ ዓመታት በኋላ ታላቁ ሄሮድስ የዘሩባቤልን ቤተ መቅደስ አስፋው ለአርባ ስድስት ዓመት አርባ ሜትር ከፍታ ያለውን የመቅደሱን አጥርና ትልቅ የሆነውን የቤተ መቅደሱን ቅርፅ ሰሩ (ዮሐ. 2:20):: በስተ ደቡባዊ ምስራቅ ዳርቻ በኩል የሚከበበው «የቤተ መቅደሱ ጫፍ» ተብሎ የሚጠራው ግንብ ሰባ አምስት ሜትር ከፍታ ያለውና ወደ ቄድሮን ሸለቆ የሚዘልቅ ነበር:: ጠቅላላ አቋሙ ሐውልት ይቋስል ነበር:: በደቡባዊ ዳርቻ በኩል ርዝመቱ 488 ሜትር እና 283 ሜትር ስፋት ያለው ሲሆን በስተ ሰሜን በኩል ደግሞ 321 ሜትር ስፋት ነበረው:: አሁንም እንኳን ቢሆን በምዕራብ በኩል ባለው ቅጥር በቁፋሮ ቅርሶች የተገኙት ስለዚህ ታላቅ ግንብ ምስክርነታቸው ይሰጣሉ (ማቴ. 24:1-2) :: ዛሬ በምዕራብ በኩል ያለው ቅጥር «የልቅሶ አደባባይ» በመባል ይታወቃል:: ነገር ግን ሰሎሞን ሰርቶት እንደነበረው ዓይነት ቤተ መቅደስ የእግዚአብሔር ክብር በዚህ ቤተ መቅደስ አልተገኘም:: ነገር ግን (በዮሐ. 1:14) ያለው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት እስከሚፈፀም ድረስ ጌታ እግዚአብሔር በክብሩ ወደዚህ መቅደስ አልገባም:: ዮሐ. 1:40 የሚለው ቃልም ሥጋ ሆነ፣ ፀጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ፣ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን::» ነው:: ወደ ቤተመቅደሱ በገባ ጊዜ ገንዘብ ለዋጮችን አስወጣ፣ ቤተ መቅደሱንም ከእርግብ ሻጮች አፀዳ:: (ዮሐ. 2:14-16) እዚያ ብዙ ታምራቶችን አደረገ፣ ሕዝቡንም አስተማረ (ማቴ. 21:14፤ ሉቃ 19:47) :: ቀራንዮ መስቀል ላይ በመስዋዕትነቱ የብሉይ ኪዳንን መስዋዕቶችን ፈፀማቸውና፣ በአጠቃላይ የሃይማኖት ሥርዓቶችን ከቤተ መቅደስ አስቀራቸው:: ስተወሰነ ጊዜ የተሰጠው የብሉይ ኪዳን

የክህነት አገልግሎት በእርሱ ወደ ፍፃሜ መጣ፣ ምክንያቱም ክርስቶስ እውነተኛው ሊቀ ካህናትና ዘላለማዊ ክህነት በሰማይ ስላለው ነው:: «እነርሱም ያ መሐላ ካህናት ሆነዋልና፣ እርሱ ግን ጌታ አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘለዓለም ካህን ነህ ብሎ ማለ አይፀፀትም ብሎ በተናገረለት ከመሐላ ጋር ካህን ሆኖአልና፣ ያለ መሐላ ካህን እንዳልሆነ መጠን እንዲሁ ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኖአል:: እነርሱም እንዳይኖሩ ሞት ስለ ከለከላቸው ካህናት የሆኑት ብቻ ናቸው፣ እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለ ሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው» (ዕብ. 7:20-24)::

## 6. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ መቅደስ

### ዮሐ 2:21





በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ትክክለኛውና እውነተኛው መቅደስ ተብሎ ተጠርቷል:: አዳኙ «ስለ ሥጋው መቅደስ» (ዮሐ 2:21) በተናገረ ጊዜ ስለ ብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች ሀሳብ መስጠቱ ብቻ ሳይሆን የተናገረው ስለ ድንኳኒቱ፣ ስለ ሰሎሞንና ስለ ዘሩባቤልም ቤተ መቅደስ ነበር :: ምክንያም እነርሱ የሥጋው ቤተ መቅደስ ጥላ ነበሩና:: ከዓለም ፍጥረት በፊት እንኳን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ራሱን መስዋዕት አድርጎ ስለ ኃጢአታችን ራሱን በመስቀል ላይ ለመስጠት ፈቃደኛ ነበር:: ስለዚህ መስቀል ከኃጢአት ያድነናል:: ስለሆነም የቀራንዮ መስቀል አዳኙ ወደዚህ ዓለም ከመምጣቱ ከሺ ዓመታት በፊት ጥላውን በድንኳኒቱና በብሉይ ኪዳን ቤተ መቅደሶች ላይ ጥሎ ነበር:: ሙሴ ድንኳኒቱን በሰራ ጊዜ ጌታ በሲና ተራራ ላይ በገለፀለት ዓይነትና ምሳሌ መሰረት መቅደሱን ሰርቷል (ዘፀ. 25:9፣ 40፤ 26:30፣ 27፣ 8፣ 39:43):: ይህ ምሳሌ የመለኮታዊው የኢየሱስ ክርስቶስ ጥላ ነበር:: በውጭ በሚታዩት በድኳኒቱ፣ በብሉይ ኪዳን ቤተ መቅደሶችና ንዋየ ቅዱሳቱ የመስቀል እውነትነት በምሳሌነት ተገልጾ ነበር:: ኃጢአት የሌለበትና የእግዚአብሔር በግ ሆኖ እንከን የሌለበት መስዋዕት የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ጥላ ነበሩ::

የብሉይ ኪዳን ስርዓት ጥላነት በአዲስ ኪዳን ተፈፃሚነትን ሲያገኝ በቤተ መቅደሱ በሚቃጠለው መስዋዕት መሰዊያ ቦታ ምትክ የኢየሱስ ክርስቶስ እግሮች በመስቀል ላይ በሚስማር ተቸነከሩ:: በውጭው አደባባይ ባለው የመታጠቢያ ሳህን









ምትክ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጎን ደምና ውሀ ፈሰሰ:: (ዮሐ. 19:34) ወርቅማው መቅረዝ በቆመበት ቦታ የክርስቶስ ቀኝ እጁ በምስማር ተቸነከረ:: በቤተ መቅደሱ አስራ ሁለት ሕብስቶች ለመታሰቢያ በሚቀመጡበት ጠረጴዛ ቦታ የኢየሱስ ግራ እጅ በመስቀል ላይ በምስማር ተቸነከረ:: በቤተ መቅደሱ በቅድስተ ውስጥ ለፀሎት እጣን በሚጨስበት መሰዊያ ቦታ የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ «አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና» ብሎ ፀለየ (ሉቃ. 23:34) በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ የኪዳኑ ታቦት ከስርየት መክደኛና የሕጎቹ ፅላት በቆሙበት ቦታ የእግዚአብሔር ልጅ ራሱን አዘንብሎ «ተፈፀመ» ብሎ ጮኸ:: የኢየሱስ ክርስቶስ የሥጋው መቅደስ ፍቺ ይህ ነው:: በዚህ መቅደስ ማለትም በሥጋው መስዋዕትነት ብቻ ነው ከቅዱስ እግዚአብሔር ጋር መገናኘት የምንችለው (ዕብ. 10:4-10)::

## 7. የቤተ ክርስቲያን መቅደስ

### ኤፌ. 2:20፤ 2ቆሮ 6:16




ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ላይ በሰራው ፍፁም በሆነ የማዳን ሥራ መሰረትነት በበዓለ ሃምሳ የመጀመሪያዋ ቀን ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ተመሰረተች (ዮሐ. 7:39) እንደ መፅሐፍ ቅዱስ ዘገባ ከዚያ ቀን ጀምሮ ብዙ የዳኑና ዳግም የተወለዱ አማኞች የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ «አባል ሆኑ» (2.ቆሮ 6:16)::


የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ቤተ መቅደስ የመሆን ጉዳይ ታላቅ ሚስጢር ነው (ኤፌ. 5:32):: እነዚያ «ሕያዋን ድንጋዮችና» «የመንፈሳዊ ቤት» የሆኑት ብቻ ናቸው ፍቺውን መጨበጥ (ማወቅ) የሚችሉት (1ጴጥ. 2:5):: በኤፌሶን መልዕክት ውስጥ እስከ አሁን ድረስ በመስራት ላይ ስላለው ሕንፃ እናነባለን (ኤፌ. 2:21):: ኢየሱስ

ክርስቶስ ግንበኛው ነው:: ደሙ ደግሞ የዚህ ህንፃ ዋናው መገንቢያው መሳሪያ ነው:: እያንዳንዱ ዳግሞ የተወለደ አማኝ የዚህች የማትደመሰሰውን ሰማያዊ ሕንፃ ከጌታ ጋር አብሮ የሚሰራ ነው:: የማትደመሰሰበትም ምክንያት የመሰኮታዊነት ባሕርይ ስላትና ሰዘላለም ፀንታ ሰሰምትኖር ነው::

ይህ እውነት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መቅደስ፣ ሕንፃ፣ (ቤተ ክርስቲን) ወይም ትልቅ ካቴድራል እንዳይደለች ያመለክተናል:: እንደዚሁም ይህች ሰማያዊ ሕንፃ ቤተክርስቲያን በአሁኑ ዘመን በዚህ ምድር ላይ ሚኖሩ በስም ክርስቲያኖች ነን ባዮች የሆኑትና ስለ እግዚአብሔርና በኢየሱስ ክርስቶስ ስላለው ደህንነት ለማወቅ የማይፈልጉትን የያዘች አይደለችም:: የዚህች ሕንፃ አባል የሚሆኑት የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን (መቅደስ) «ለእግዚአብሔር መኖሪያነት በመንፈስ» የሚሰሩና በንስሐና በዳግም ልደት የኢየሱስ ክርስቶስ የሆኑት ብቻ ናቸው::

## 8. ሦስተኛው ቤተ መቅደስ

**2ተሰ 2:4**



እስከ አሁን ድረስ አብዛኞቹ የእስራኤል ሕዝቦች መሲሀቸውን አላወቁትም በዚህ ምክንያት ነው በቀራንዮ መስቀል ላይ የተፈፀመውን የማዳን ሥራ የማይቀበሉት :: በተጨማሪም በዕብ 7:1-10፣ 18 የእስራኤል ሕዝብ ላይ እንደ ተፃፈው የመስዋዕቶች፣ የክህነት ሥራና የቤተ መቅደስ አምልኮ ከብዙ ዓመታት በፊት በክርስቶስ የተፈፀመ መሆኑን ሊያውቁ አልቻሉም:: ሃይማኖታውያን አይሁዶች ቤተ መቅደሱ ተመልሶ እስካልተሰራ ድረስ የእስራኤል መንግስት ያልተሟላ ሆኖ ይቆያል ብለው ያምናሉ:: ትክክሉ ቤተ መቅደስ ሲሰራ በማዳን ታሪክ ውስጥ በኢየሩሳሌም ከተሰሩት መቅደሶች ሦስተኛው ቤተ መቅደስ ይሆናል::


እንደ መፅሐፍ ቅዱስ ቃል አንድ ቀን የክርስቶስ ተቃዋሚ ዙፋኑን ሲተክል፣ ራሱን እንደ አምላክ እንዲመለክ የሚያደርግበትና የጥፋትንም ርኩሰት የሚያቆምበት ቦታ ይህ ቤተ መቅደስ ነው (ዳን. 9:24-27፤ ማቴ. 24:15፤ 2ተሰ. 2:4፤ራዕ. 11:1-2):: ይህ ሕንፃ, ከክርስቶስ ተቃዋሚ ጋር አብሮ ይደመሰሳል፣ ምክንያቱም ላልዳኑት የእስራኤል ሕዝብ እፍራሽ ዓላማ (ወደ ደህንነት እንዳይመጡ ማለት ነው) ስላለው ነው:: ቢሆንም የሃይማኖት ሰዎች ይህን ሦስተኛውን ቤተ





መቅደስ በእስራኤል በሞርያ ተራራ ላይ ለመስራት በየጊዜያቱ ብዙ ዝግጅቶች እያደረጉ ናቸው:: የቤተ መቅደሱን የመገልገያ እቃዎችና የክህነትን ልብሶች እየሰሩ ነበር:: ነገር ግን ለእኛ የሦስተኛው ቤተ መቅደስ መሰራት የመጨረሻው ዘመን መሆኑን ከሚያሳዩን ምልክቶች ዋነኛው የቤተመቅደሱ መሰራት ነው:: ጌታ ኢየሱስ በቅርብ እንደሚመጣ በግልፅ ይነግረናል::

## 9. በሕዝቅኤል ከምዕ. 40-48 ያለው ቤተ መቅደስ





በሕዝቅኤል 40 እና 48 መስዋዕቶችና ክህናት ስላሉት በዚህ ምድር ከአሁን በፊት ከቶ ስላልታየው ቤተ መቅደስ ነቢዩ ይገልፅልናል:: ይህ ቤተ መቅደስ እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ የሺ ዓመት መንግስት ድረስ አይሰራም:: ቅርጹ (መልኩ) ልዩ የሆነ፣ በዓይነትና በመጠን በአጠቃላይ ከድንኳኗ፣ ከሰሎሞንና ከዘሩባቤል ቤተ መቅደስ የተለየ ይሆናል:: ክህነታዊ አገልግሎትና መስዋዕቶቹ ከብሉይ ኪዳኖቹ ጋር የማይወዳደር ነው:: እንደ መፅሐፍ ቅዱስ ገለፃ የእግዚአብሔር ክብር ዳግም ይገባበታል (ይታይበታል) (ሕዝ. 43-1-5)::

በምዕ. 8:4፤ 9:3፤ 10:3-4፤ 18-19፤ እና 11:23 ነቢዩ እንዴት የእግዚአብሔር ክብር በእስራኤል የርኩሰት ኃጢአት ምክንያት (ሸክና ግልፅ የሆነው የእግዚአብሔር ክብር ማለት ነው) ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ለቅቆ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ወደ ምስራቅ እንደሚሄደ ይገልፅልናል:: ነገር ግን በሕዝ 43:4-5 ግልፅ የሆነው የእግዚአብሔር ክብር ከምስራቅ የደብረ ዘይትን ተራራ በማለፍ በኢየሩሳሌም ያለውን ቤተ መቅደስ እንደገና ስመሙላት ስለ መመለሱ ይነግረናል:: እንደገና ሁሉን ቻይ አምላክ ከሕዝቡ ጋር ይሆናል:: ከሕዝ 40 እስከ 48 በተጠቀሰው ቤተ መቅደስ እግዚአብሔር ስለሚገለፅ «እግዚአብሔር ከዚያ ነው» ተብሎ የተፃፈለት ቦታ ይህ ቦታ ነው ሕዝ 48:35::

በዚህ ቤተመቅደስ የሚሰውት ጥቂት መስዋዕቶች ምሳሌያዊ ፍቺ ይኖራቸዋል:: እንደ ጌታ እራት በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈፀመውን መስዋዕት እንደ መታሰቢያ ሆነው ያመለክታሉ::

## 10. ቤተመቅደስ የሌለበት ራዕይ 21 እና 22




ሰው በኤደን ገነት በኃጢአት ከመውደቁ በፊት ቤተ መቅደስና መስዋዕት አልነበረም:: ይህም የሆነበት ምክንያት የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ያለ ኃጢአት ስለነበሩ መሆኑን ቀደም ብለን ጠቅሰናል:: የመፅሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች ንጹህ፣ ስለሆነውና ስላልተበከለው እንዲሁም፣ ኃጢአትና ሞትን ስለማያውቀው ዓለም ይገልፃሉ:: ስለዚህ ነው በመጀመሪያ እግዚአብሔር ፈጥሮ በጨረሰ ጊዜ «እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፣ እነሆም እጅግ መልካም ነበር» ተብሎ የተፃፈው (ዘፍ. 1:29-31)::

የመፅሐፍ ቅዱስ የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች ዳግም ሰዎች ኃጢአት በሌለባቸው አዲስ ሰማይና ምድር እንደሚኖሩ እንደገና እናነባለን:: ራዕይ 21 እና 22 በዚህ በአዲሱ ዓለም ኃጢአት ስለማይኖር ቤተ መቅደስ ካህናትና መስዋዕት አያስፈልጉም (ራዕ. 22:3)::

ስለሆነም የሰው ልጅ ታሪክ ኃጢአት በሌለበት ዓለም ጀምሮ ኃጢአት በሌለበት ዓለም ይጨርሳል:: እግዚአብሔር በእነዚህ ሁለት ጊዜያት መካከል የማዳን ዕቅዱን በመስቀል ላይ በተከናወነው የማዳን ሥራ ይሠራል:: በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ በሙሉ የእግዚአብሔር ልጅ ለአንዴና ለዘላለም በኃጢአት፣ በሞትና በሰይጣን ወደሚከናወነው ዘላላማዊ ድል ያመለክታሉ:: አዲሱ ሰማይና ምድር በዚህ ላይ ብቻ ስለተመሰረቱ በአጠቃላይ ኃጢአት በዚህ ዓለም አይገኝም:: በዚህ ምክንያት መስዋዕት፣ የክህነት አገልግሎትና ቤተ መቅደስ አያስፈልጉም:: በሌላ አባባል በአዲሱ ዓለም መስዋዕትና የቤተመቅደስ አምልኮ አያስፈልጉም ምክንያቱም በእግዚአብሔር ልጅ የተፈፀመው ደህንነት ፍፁምና ዘላለማዊ ስለሆነ ነው:: ኃጢአተኛው ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ለማድረግ ንስሐ ከመግባትና ድንቁ አዳኝ በእርሱ የተፈፀመውን የደህንነት ሥራ በእምነት ከመቀበል በስተቀር የሚያደርገው ሌላ አይኖረውም:: ማንኛውም ዳግም የተወለደና የዳነ አማኝ ወደ አዲሱ ሰማይና ወደ አዲሱ ምድር የሚገባው ለዘላለም በክርስቶስ ደም ፍፁም ንፁህ ከተደረገ ነው:: (ቆላ 2:10፤ ዕብ 10:14፤ 11:40):: ይህ ሰው ከክርስቶስ ሰማያዊ የሆነውን ክቡር ሥጋ በመስወጥ የተቀበሰና እንደ እግዚአብሔር ያለ ኃጢአት የሆነ ነው (ፊል.





3:20-21):: ኃጢአት የሌለበትና ከቅዱሱ እግዚአብሔር ጋር ፍፁም የሆነ ሕብረት ስላለው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ሲፈልግ መስዋዕቶችና ቤተ መቅደስ አያስፈልጉትም:: ደህንነት በክርስቶስ ደም አማካኝነት ወደ ፍፁምነትና ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ዘላለም ሕብረት ከመራ ዘላለማዊና ክብር የሞላበት ደስታ ይኖራል ማለት ነው:: ስለዚህም ዮሐንስ በራዕይ ወደ ፊት ስላለው ዓለም (አዲስ ሰማይና ምድር) መቅደስ አልተመለከተም:: በሰማይ ስላሉት ስለዳኑት ሲናገር ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክና በጉ መቅደስዋ ናቸውና መቅደስ በእርሷ ዘንድ አላየሁም በማለት ድፏል (ራዕ. 21:22):: የዳኑትና የተነጠቁት አማኞች ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ናቸው፣ እግዚአብሔርም በእነርሱ ውስጥ ነው (ዮሐ. 14:20፤ 17:21-24):: እንደዚህ ያለው ሕብረት ወደ ፍፅምና ሲደርስ የመገናኛ ቦታ፣ በቤተ መቅደስ ያለው አምልኮ ወይም መስዋዕቶች መታሰቢያቸው ሁሉ ይጠፋል::

## መግለጫ ክፍል 4:

# በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ውስጥ ሰባቱ ዘመናት

የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ ታሪክ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጹትን የተለያዩትን ዘመናት መለየት ካልቻልን ልንረዳው አንችልም። በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የእውነትን ቃል በቅንነት መናገር ብሎ የጻፈለት ቃል አስፈላጊ ነገር ነው (2. ጢሞ 2:15)። መፅሐፍ ቅዱስ ትጉህ ለሆነ የመፅሐፍ ቅዱስ ተማሪ ለመረዳት አስቸጋሪ የሆነ መፅሐፍ አይደለም። ምክንያቱም ግልፅነት ባለው መንገድና ሥርዓት ባለው መገለፅ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስለሆነ ነው።

በዚህ ዓለም በእግዚአብሔር የማዳን ሒደት ውስጥ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ዘመናት» ብለን የምንጠራቸውን ጊዜያት እናገኛለን። (Dispensation) ዘመናት የተባለው ቃል ከግሪክና ከላቲን የተወሰደ ነው። የግሪኩ ኦኮኖሚያ (Oikomia) የተባለው ቃል ዘጠኝ ጊዜ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሷል። በላቲኑ ቮልጌት ዲስፐንሳቲዮ (Dispensation) ተብሎ ተተርጉሟል። መጋቢ ወይም ቤተ ሰብ ማለት ነው። ከበስተኋላ ያለው ሀሳብ እግዚአብሔር የደህንነትን ታሪክ እንደ ቤት ሐላፊ ወይም መጋቢ ሆኖ የሚያካሂድ ነው ማለት ነው። ይህ ኦኮኖምያ ወይም የደህንነት መጋቢነት በኤፌሶን 1:10፤ 3:2-9 ፤በቆላ 1:26 እና 1ጢሞ 1:4 ላይ ተጠቅሶ ይገኛል። ሐዋርያው ጳውሎስ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ምስጢር መጋቢ ነበር። በጠቅላላው የማዳንን ታሪክ ሂደት ስንመለከት የተለያዩ ሰባት ዘመናትን መለየት እችላለን። እነርሱም፦

1ኛ. በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ የመጀመርያው ዘመን «የፍጽምና ዘመን»

2ኛ. በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ ሁለተኛው ዘመን «የሕሊና ዘመን»

3ኛ. በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ ሦስተኛው ዘመን «የመግዛት ዘመን»

4ኛ. በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ አራተኛው ዘመን «የተስፋ ዘመን»

5ኛ. በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ አምስተኛው ዘመን «የሕግ ዘመን»

6ኛ. በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ ስድስተኛው ዘመን «የጸጋ ዘመን»


7ኛ. በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ ሰባተኛው ዘመን «የሰላም ዘመን»ናቸው።





## 1. ድንግልና


### ዘፍ 1 እስከ 2




ከውድቀት በፊት ሰው ኃጢአት በሌለበት በፍጽምና ዘመን ኖረ በአዳምና በሔዋን እንደዚሁም በአካባቢያቸው ባለው ተፈጥሮ በፍጹም ኃጢአት አልነበረባቸውም። በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው ሕብረት ፍጹም ያልታወከና ከጥፋትም ነጻ የሆነ ነበር። ይህ ዘመን ሰምን ያህል ጊዜ እንደቆየ ማንም አያውቅም። ነገር ግን የሰው በደል በእርሱና በእግዚአብሔር መካከል በጣም ሰፊ የሆነ መለያየትን አመጣ። የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ሕብረት ያጡ ብቻ አልነበረም። ነገር ግን የእግዚአብሔር ክብርም የጎደላቸው ሆኑ (ሮሜ 3:23) ኃጢአት ወደ ዓለም በመግባቱ የፍጽምና ዘመን አከተመ።

## 2. የሕሊና ዘመን

### ዘፍ.4:7 ሮሜ 2:12-16




ከፍፅምና ዘመን ቀጥሎ የሕሊና ዘመን ቀጠለ። ከሰው ውድቀት በኃላ ማንኛውም ሰው ደህና አድሪጎ በመልካምና በክፉ መካከል ያለውን ልዩነት አወቀ ዘፍ 3:22 ይህ ውስጣዊ የሆነ እውቀት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ነው። ኃጢአተኛው ከበደል ነፃ አይደለሁም ማለትም አይችልም። መፅሐፍ ቅዱስ ማንኛውም ሰው ሕሊና እንዳለው ይናገራል (ሮሜ 2:12-16)። በመጨረሻው የፍርድ ጊዜ ማንኛውም ሰው ስለ ሥራው መልስ ይሰጥ ዘንድ በእግዚአብሔር ይጠራል።


ሰው መልካሙንና ክፋውን የማወቅ ነገሩ እስከ አሁን ያልተሰወጠ ስለሆነ ሰብዙ ሺህ አመታትም በሕሊና ዘመን ውስጥ ኖረዋል። በደህንነት ታሪክ ውስጥ ይህ ዘመን ያበቃው በጥፋት ውሀ ፍርድ ጊዜ ነው። በዚያን ጊዜ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ እዲገስፀው ወደማይፈቀድስት ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። በክፋት የተሞላ ሆኖ ነበር (ዘፍ. 6:5)። የአመፅ ከፍታው በጣም ያየለበት ጊዜ ስለነበር እግዚአብሔር

ሰውን በመፍጠሩ እስከ መፀፀት ድረስ አድርሶት ነበር:: (ዘፍ. 6:6):: ስለዚህም ከስምንቱ ከኖህ ቤተሰቦች በስተቀር መላው ዓለም በጥፋት ውሀ ጠፋ:: ኖህ በእግዚአብሔር ስላመነና በአስቸጋሪው ጊዜ እንኳን ታማኝ ሆኖ ስለቆመ እነዚህ ቤተሰቦች ሰመዳን በቁ::

ከኖህ ሶስቱ ልጆቹ ከሴም፣ ከካምና ከያፌት ሦስቱ የሰው ዘሮች ተወለዱ እነርሱም ሴማውያን (ሴሚቲክ)፣ ከነዓናውያንና (ሐማይት) ያፌታውያን ናቸው::

## 3. የመግዛት ዘመን

### ዘፍ 9:6




ከጥፋት ውሀ በኋላ ጌታ ከኖህ ጋር አዲስ ዘመን ጀመረ:: ይህም የመግዛት ዘመን የሰው ባለ ሥልጣንነት ዘመን ነበር:: የዚህ ዘመን ዋናው መሠረት ሕጉ ነበር:: *ዋየሰውን ደም የሚያፈስስ ሁሉ ደሙ ይፈሰሳል፣ ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጥሮታልና (ዘፍ. 9:6)::*

ይህም ማለት ማንኛውም ሰው ይህን ሕግ የሚጥስና ሰውን የሚገድል በእግዚአብሔር ላይ አደጋ እንደጣለ ይቆጠራል፣ ምክንያቱም ሰው በእግዚአብሔር መልክ ስለተፈጠረ ነው (ዘፍ. 1:27):: ይህን ሕግ ተግባራዊ ለማድረግ ሰውን ባለ ሥልጣን አድርጎ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነገር ሆነ:: ሰዎች በአንድነት መኖር እንዲችሉ በሥልጣን ተዋረድ የመግዛት አከሄድ ተፈጠረ መንግስት ተቋቋመ:: በገገርና ተገገር ሂደትሌሎች ሃይሎች የሚገዙለት ሥልጣን ተመሰረተ:: ለምሳሌ መንግስት አመፀኞችን የመቅጣት ሥልጣን አለው:: ምክንያቱም በመንግስት ላይ ማመፅ (ለመንግስት ስልጣን አለመገዛት ማለት ነው) በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ነው:: ምክንያቱም ባለ ሥልጣናት በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸውና::

ይህ መለከታዊ ትዕዛዝ በሮሜ መልዕክት እንደምንማረው በአዲስ ኪዳንም የፀና ነው (ሮሜ 13:1-7):: ጌታ ኢየሱስ በመላው ዓለም ላይ የነገስታት ንጉስ ሆኖ በሺሁ ዓመት እስከሚገዛበት ጊዜ ድረስ ለስልጣን የመገዛት ነገር የማይለወጥ ነገር ነው::

ከዚህ በኋላ እውነተኛው አገዛዝ (የእግዚአብሔር መንግስት) በምድር ላይ በክርስቶስ ኢየሱስ አማካኝነት ይገዛል:: ይህም ማለት ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ፍፁማዊ አገዛዝ ሥር ይሆናል ማለት ነው::






ነገር ግን ይህ የመግዛት ዘመን በደሀንነት ታሪክ ውስጥ ያበቃው በባቢሎን ግንብ ግንባታ ጊዜ ነው:: የሰው ዘር እንደገና አመፀኛ ሆነ:: የራሱንም ስም ለማስጠራት ጥረት አደረገ (ዘፍ. 11:1-9):: ሰዎች በራሳቸው ኃይል የሱማያውያን አገዛዝ ሂደት ለማወክ እድማ መቱ:: በእግዚአብሔር የተመሰረተውም የሕግ አገዛዝ የማይሰራ ሆነ፣ ምክንያቱም ይህ አመፀኝነት በሥራ ላይ እንዳይውል የሚገታው ኃይል በሰው ዘንድ አልነበረም::

ነገር ግን ይህን ዕድቅ ያልሆነውን ዕቅዳቸውን ጌታ ወደ ፍፃሜ አመጣው:: እግዚአብሔር ቋንቋቸውን በመደበላለቅ በምድር ላይ ተበታትነው በራሳቸው መንገድ እንዲሔዱ አደረጋቸው (ሐሥ. 14:16):: ስለሆነም በማዳን ታሪክ ውስጥ የመግዛት ዘመን ወደ ፍፃሜው መጣ::

## 4. የተስፋ ዘመን

### ዘፍ.12:1-3 ገላ 3:16





አራተኛው ዘመን የጀመረው በአብርሃም መመረጥ ነው:: አብርሃም በዘመኑ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ በአንድ ነገር የተለየ ነበር:: በእግዚአብሔር ያመነ ሰውና እምነቱ ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረለት ሰው ነበር (ዘፍ. 15:6፤ ሮሜ 4:3)::

አብርሃም የእስራኤል ሕዝብ አባት ሆነ:: በዚህ ምክንያት ከእግዚአብሔር ሦስት ተስፋዎችን ተቀበለ (ዘፍ. 12:1-3):: በመጀመሪያ ምድርን (የእስራኤል ምድር የሆነችውን) በሁለተኛ ዘሩ ትልቅ ሕዝብ እንደሚሆንና (የእስራኤልን ሕዝብ) በስደተኛ ከዚህ ምድርና ሕዝብ ተስፋ የተገባለት መሲሁ የእግዚአብሔር ልጅ አንድ ቀን እንደሚነሳ ነው:: እነዚህ ሦስቱ ተስፋዎች ቀጣዩና አዲሱ ዘመን ምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ይገልፃሉ:: ሦስቱም በክርስቶስ ላይ የሚያተኩሩ ስለሆኑ እንደ ገላ 3:14-18 በክርስቶ የመጀመሪ መምጣት የተፈፀሙ ሆኑ::

የተስፋው ዘመን በሌላ ውድቀት ተፈፀመ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከቄሳር በስተቀር ሌላ ንጉስ የለንም ብለው እንዲሰቀል ለሮማውያን አሳልፈው በሰጡት ጊዜ መሲሁን መቃወማቸው ነበር::(ዮሐ. 1:11፣ 19:13-15፤ሐሥ.3:14-15፤ሉቃስ 19:14)

## 5. የሕግ ዘመን

### ሮሜ 10:4፤ ገላ. 3:19-26





የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ባርነት ነፃ ከወጡ በኋላ እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ሕግን ሰጣቸው:: አስርቱ ሕግጋት በሲና ተራራ ላይ በታወጁ ጊዜ በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ የሕግ ዘመን የተባለው አዲስ ዘመን ጀመረ:: ይህ ዘመን ከሌሎቹ ዘመናት ጋር ሲነፃፀር የጸጋ ዘመን ከተባለው ዘመን ጋር ለብዙ መቶ አመታት ጎን ለጎን ሄዷል:: መፅሐፍ ቅዱስ በማዳን ታሪክ (Salivation History) ውስጥ ስለ ኃጢአት ሕግ ገባ ወይም ተጨመረ የሚለው ስለዚህ ነው (ሮሜ 5:20፤ ገላ. 3:19):: ኃጢአትን በሕሊናችን ማወቅ የምንችለው በሕግ በኩል ብቻ ነው (ሮሜ 3:20):: የዚህ የ5ኛው ዘመን ትልቁ ዓላማ ሰው ተስፋ ቢስ የሆነ፣ ደህንነት የሚያስፈልገው መሆኑን የሚያሳይ ነው:: አንድ ሰው ከሕግ አንዱን ቢተላለፍ በሁሉም በደለኛ ይሆናል (ያዕ. 2:10):: ስለሆነም የእግዚአብሔርን ፅድቅ መድረስ አይችልም:: ስለዚህ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያደርስ ሞግዚት ሆነ (ገላ. 3:24):: የእግዚአብሔር ጽድቅ ሕግ በሚጠይቀው በሕግ ሥራ ሳይሆን የእግዚአብሔር ጽድቅ በሆነው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የሚገኝ መሆኑን ያስተምረናል (1ቆሮ.1:30) መፅሐፍ ቅዱስ እርሱ የሕግ ፍፃሜ መሆኑን ያረጋግጥልናል::በእርሱ የሚያምን ሁሉ ፃድቅ ነው (ሮሜ 10:4)::

ምንም እንኳን ሕግ «ተፈፀመ» በሚል አነጋገር በመስቀል ላይ በጮኸው በእግዚአብሔር ልጅ የተፈፀመ ቢሆንም እስራኤል መሲሁን አላወቀችውም (ዮሐ. 19:30):: ቢያውቁት ኖሮ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር (2ቆሮ. 2:8) ይህ የሕግ ዘመን መሲሁን በመቃወም ተፈፀመ (ማቴ. 23:37-39)::

## 6. የምህረት ዘመን

### 2ቆሮ 6:1-2፤ ሐሥ. 4:12




ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ከመጣ፣ ከተሰቀለ፣ ከሙት ከተነሳና ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ እግዚአብሔር በጣም የተለየ የመንፈስ ቅዱስ ዘመን የሆነውን የጸጋ ዘመን አስገባ (ኤፌ. 1:1-10፤ 3:2-9) ይህ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ዘመን እንደሆነም ቀደም ብለን አውቀናል:: እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ ወሰን የሌለውን የጸጋ ጊዜ





በወንጌል መስበክ በኩል ለዓለም ሰጥቷል:: በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ማንኛውም ሰው በበጉ (በኢየሱስ) ደም በኩል ለዘላለም የሚድን ይሆናል::

ይህ የጸጋ ዘመን በበዓለ ሃምሳ በኢየሩሳሌም በመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ተጀመረ (ሐሥ. 2:1-41):: በቤተ ክርስቲያንም መነጠቅ ጊዜ ያከትማል (1ተሰ. 4:13-18) ሐዋርያው ጳውሎስ በሁለተኛው የቆሮንቶስ መልዕክት ስለ ደህንነት ቀን ሲፃፍ ስለዚህ ለሁሉም ስለተሰጠው የፀጋ ጊዜ መናገሩ ነበር (2ቆሮ 6:1-2) ለሁለት ሺ ዓመታት ያህል በጸጋ ዘመን ውስጥ እየኖርን ነው ያለነው፣ ዛሬም ቢሆን ጌታ የሚድኑትን ወደ ቤተ ክርስቲያን እየጨመረ ነው ያለው (ሐሥ. 2:47):: ነገር ግን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንም ዘመን እንዳለፉት ዘመን በጥፋት ይፈፀማል:: የክርስቶስ ኢየሱስ ተቃዋሚ መነሳት ለሺዎች ዓመታት ወንጌልን ሰምተው ነገር ግን በክርስቶስ የተሰጠውን ደህንነት በተቃወሙት ላይ ለፍርድ ነው:: በዚህ ምትክ ሰዎች ሰይጣንን እውሬውን ያመልካሉ:: በራዕይ 13:16 666 የተነገረለትን ቁጥር ያለውን የአውሬው ምልክት በቀኝ እጃቸውና በግንባራቸው ሲቀበሉ የሰይጣንን ማህተም መቀበላቸው ነው:: ይህ ሲከናወን ሊያመልጡበት የማይችሉትን የእግዚአብሔርን ፍርድ በራሳቸው ላይ መጥራታቸው ነው:: ይህ የጸጋ ዘመን ከየትኛውም በምድር ላይ ከነበሩት ዘመናት የበለጠ በአስፈሪ ፍፃሜ ያበቃል::

## በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ አንቀጽ መካከል ያለ አጭር ጊዜ

### «አስፈሪው የታላቁ መከራ ዘመን»


የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ምድር የምትነጠቅበትን ጊዜ ሰዎችም ሆኑ የሰማይ መላዕክት አያውቁትም (ማቴ. 24:23):: ነገር ግን አንድ የተረጋገጠ ነገር አለ:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ በንጥቀት ጊዜ ከአማኞች ጋር ይህችን ምድር ይተውና ወደ ሰማይ ይመለሳል:: በዚያ ጊዜ ሰዎች በንስሐ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮችና የሰማያዊ አባት ልጆች የሚሆኑበት የፀጋ ዘመን ያበቃል::

ቀደም ባለው ምዕራፍ ከቤተ ክርስቲያን ዘመን በኋላ (በጸጋ ዘመን) በእስራኤልና በመላው ዓለም ላይ አጭር የሆነ የፍርድ ጊዜ ይሆናል:: በዚህ ጊዜ የክርስቶስ ተቃዋሚ ገደብ የለሽ የሆነ ታላቅ ብጥብጥ በምድር ላይ እንዲያደርግ ይፈቀድለታል:: ይህ ጊዜ ባያጥር ኖሮ ማንም የማይድንበት አስቸጋሪ ይሆን ነበር (ማቴ 24:22)::

ይህ አስፈሪው የክርስቶስ ተቃዋሚ ዘመን እያንዳንዳቸው ሦስት ዓመት ተኩል ለሆኑ ሁለት ጊዜያት የተከፈለ ነው። ይህም የምህረት እባት ምን ያህል አፍቃሪ እንደሆነ ያረጋግጥልናል። ለሰዎች ዓመታት ከቆየው የፀጋ ዘመን በኋላ ለሰባት ዓመት የሚቆይ የፍርድ ዘመን ይከተላል። በዘመናት ሁሉ ከነበሩት ይህ አስቸጋሪ ጊዜ በክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም መምጣት ያከትማል። ጌታ በኃይልና በታላቅ ክብር ሲገለጥ የክርስቶስ ተቋዋሚ፣ ሀሰተኛው ነቢይና ሰዎች ሁሉ ይፈረድባቸዋል። ነገር ግን እስራኤል ትድናለች፣ ምክንያቱም በመጨረሻ መሲኋን ትቀበላለችና።

## 7. የሰላም ዘመን

### ኢሳ 11:1-9፣ መዝ(72)1-17




ለእስራኤልና ለዓለም በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣት ጊዜ በእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ ውስጥ ሰባተኛው ዘመን «የሺህ ዓመት ዘመን» የመሲሁ የሰላም ዘመን ተብሎ የሚጠራው ይጀምራል።

በዚህ ዘመን በክርስቶስ በመስቀል ላይ የተፈፀመው የማዳን ሥራ በፍጥረት ሁሉ ላይ የሚሠራ ይሆናል። እርግማን በሰው ላይ ብቻ ሳይሆን በተፈጥሮም ላይ ወድቋል/ደርሷል/። ምድር ሾህና እሜክላ ታበቅላለች ሰውም በድካምና በጥረት ይሰራል (ዘፍ. 3:17-19)። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን እርግማን ከፍጥረት ሁሉ ላይ ለማንሳት የሾህ አክሊልን ደፋ። በሺሁ ዓመት ወንጌል የሚሰማ ብቻ ሳይሆን በኃይልና በሥልጣን ሲሰራ የሚታይም ይሆናል። በአብዛኛው ከኃጢአት እርግማን ነጻ ሲወጣ በመላ ዓለም የተገለፀ ይሆናል (ሮሜ 8:19-25) የሰላም ንጉስ በምድር ላይ ሲገዛ እውነተኛው ሰላም መላ ዓለምን ይገዛል። (በፖለቲካዎች ሁሉ ላይ እንኳን)። ይህ በምድር ላይ እጅግ አስደናቂ ዘመን ይሆናል። የሰው ዘርም አስቀድሞ በገነት ይኖር እንደነበር ይኖራል። ሆኖም ይህ ዘመን በሰው ኃጢአት ምክንያት ያከትማል ሰይጣን ለአንድ ሺህ ዓመት ከታሰረ በኋላ ከስራቱ ይፈታል። እንደገና አብዛኛውን የሰውን ዘር እግዚአብሔርንና ክርስቶስን እንዲክዱት በማድረግ ይመራቸዋል። ምንም እንኳን ሰው በሺው ዓመት በመለኮታዊ በረከቶች በደስታ እየኖረ መሲሁን ቢያየውም፣ ሁሉን በሚችለው ላይ ወደሚደረገው ግልፅ አመፅ





ራሱን አሳልፎ በመስጠት ራሱን ወደ ስህተት ይመራል። ለጥፋትና ለኩነኔ ዲያብሎስን ይከተላል (ራዕ. 20:7-10)

እግዚአብሔር በተለያዩት ዘመናት ውስጥ ተራ በተራ ፍፁምና ዘላለማዊ የሆነውን ደህንነት ገልጿል። ይህም ወደ ልጁ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያመለክቱ በተለያዩ ተከታታይ መገለጦች የተከናወነ ነው። የኃጢአት ጨለማ በሰው ላይ ከወደቀ በኋላ የፀጋ ፀሐይ ቀስ በቀስ መውጣት ጀመረ። የዓለም ደህንነት የንጋት ብርሃን ሙሉ ወደ ሆነው የመዳን ቀን እስከሚደርስበት ጊዜ ድረስ ከቀራንዮ መስቀል ብርሃኑ እየጨመረና እየጎላ የሚንፀባርቅ ሆነ (ምሳ. 4:18፤ 2ቆሮ 6:2)። ከራዕይ 21 ጀምሮ ወደ ፊት ባለው ክፍል ኃጢአት፣ ሞትና የክፋት ምንጭ የሆነው ዲያብሎስ ለዘላለም የተሸነፉ ይሆናሉ። ከዚህ በኋላ የጊዜ ቆጠራ ስለማይኖር ዘመን ወይም ዓመታት አይኖሩም። ደስታና ክብር የተሞላበት ዘላለምነት ብቻ ይኖራል። የዳኑት በሙሉ ከእግዚአብሔር ልጅ ከተወደደው አዳኝና ከሙሽራው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ከዘላለም እስከ ዘላለም ይኖራሉ (ራዕ. 22:1-5)። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች በዘመናት ሁሉ ያመኑበትን፣ በብዙ መዝሙሮች የዘመሩለትንና ያመሰገኑትን በዘለዓለሙ አምልኮ ይፈፅሙታል።

ድካሞቼና ፈተናዎቼ ሲያበቁ
በዚያች ውብ ጠረፍ በደህና ስደርስ
ከማመልከው ጌታ አጠገብ ስገኝ
በዘመናት ሁሉ ደስታ ለእኔ ይሆናል።

*ያ ነው ክብሬ የሚሆን ቻርለስ ዘ ገብርኤል 1956-1952 አዝማች ኢየሱስ ክርስቶስ «በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፣ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፣ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሔዳለሁ።» (ዮሐ. 14:2)*

*«አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር ስለወደድኸኝ ክብሬን እንዲያዩ እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ።» (ዮሐ. 17:24)*

*«ዓይኖቼ ንጉሱን በውበቱ ያዩታል።» (ኢሳ. 33:17) ይላል።*

**«ከኢየሱስ ብቻ በቀር ማንንም አላዩም።»**
**(ማቴ 17:8)**

# ምሥጋና

ከሁሉ አስቀድመን በዚህ በዘመነ ፍጻሜ በመንፈሱ በመካከላችን ተገኝቶ ይህንን እውነት ለእኛ ያካፈለንን እግዚአብሔርን ከልብ እናመሰግናለን:: እንዲሁም ደግሞ የእግዚአብሔር መጠቀሚያው ሆና ይህንን መጽሐፍ በጀርመንኛ ቋንቋ ያዘጋጀልንን አባታችንንና ወንድማችንን ፓስተር ዮአኪም ላንገሐመርን ጌታ ይባርከው እንላለን:: ይህ « ይህች ዓለም ምን ትሆናለች» በሚል ርዕስ ብዙ ቁም ነገርችን· ይዞ ተዘጋጅቶ ከብዙ ድካም በኋላ በእግዚአብሔር እርዳታ ለአንባቢያን እንዲበቃ የብዙ ወንድሞችና እህቶችን ተሳትፎ ጠይቋል:: አንድ ሰው ዩትኛውንም ዓይነት መጽሐፍ ቢጽፍ የእኛ እንጂ የእኔ ብቻ ለማለት አይደፍርም:: ምክንያቱም በውስጡ የሰዎችን ጠቃሚ ሃሳቦች፣ አስተያየት፣ ምክርና እርማት ማግኘቱ የማይቀር ነውና:: አሁንም ይህንን መጽሐፍ ለናዘጋጅ ከጀርመንኛ ወደ እንግሊዘኛ ትርጉም ወ/ም ማቲው ወከር፣ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ወ/ም ሽመልስ ረጋ፣ጽሑፉን በማረም መጋቢ ተኩ ከበደ፣ ወ/ም በድሩ ሁሴን፣ ወ/ም የራስሚ ጋሳቲስና ወ/ም ሽመልስ ረታ በኮምፒዩተር የጽፈት ሥራ የተባተፉትን እህት አባይነሽ አርጋንጉንና እህት ዲና በላይነህን ጌታ ይባርካችሁ እያልን ለበርካታ ዓመታት ከጀርመን ወደ ኢትዮጵያ እየተመላለሰን ይህን መጽሐፍ በከፍተኛ ድካም በዚህ መልኩ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ለማድረግ ያገዘንን እግዚአብሔርን በድጋሚ ከልብ እናመሰግናለን:: ክብር ለእግዚአብሔር እስከዘላለም ዓለም ይሁን!!

<u>አዘጋጆች፡-</u>
ሚሽነሪ ሽመልስ ረታ እና ዮታ ረታ